# የኢትዮጵያ ፡ እምነት ፡ በሦስቱ ፡ ሕግጋት ፡፡

ከሊቀ ፡ ጠበብት ፡ አያሌው ፡ ታምሩ ፡

ተዘጋጀ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

www.ethiopianorthodox.org

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡
በሠላሳ ፡ አናደኛው ፡ ዓመተ ፡ መንግሥት ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡
ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ታተመ ።



ብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወፓትርያርክ ፡ ዘኢትዮጵያ ፤ ሐዋርያ ፡ ዘኢኮነ ፡ በእንተ ፡ ሰብእ ፡ ወኢኮነ ፡ እምኀበ ፡ ሰብእ ፡ ዘእንበለ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ገላ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

www.ethiopianorthodox.org

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ። አሜን ። አብን፡ወላዳ
ወልድን ፡ ተወላዲ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሠራጺ ፡ ብዬ ፡ ልዩ ፡ ሦስት ፡ አንድ ፡ አምላክ
በሚኾን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አምኜ ፤ ረድኤቱን ፡ አጋዥ፡አ
ርጌ ፤ በሕገ ፡ ልቡና ፡ በሕገ ፡ ኦሪትና ፡ በሕገ ፡ ወንጌል ፡ እየተሻሻለና ፡ እያደገ ፡ የሄ
ውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ መሠረታዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ ታሪክ ፡ ለመጻፍ ፡ ይህን ፡ መቅድም
አዘጋጀሁ ።

መቅድም ፡ ማለት ፡ ተቀዳሚ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ከዕውር ፡ ፊት ፡ መሪው ፡ ከአ
ማች ፡ ፊት ፡ ፊታውራሪው ፡ እንደሚገኝ ፤ ከዋናው ፡ መጽሐፍ ፡ በፊት ፡ የሚገኘውና
የመጽሐፉን ፡ ዝርዝር ፡ ዓላማ ፡ በጠቅላላ ፡ የሚያሳየው ፡ መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ መ
ድም ፡ (ተቀዳሚ) ፡ ይባላል ።

እኔ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ትምህርት ፡ የለኝም ፤ ዕድሜዬም ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። የኢ
ዮጵያንም ፡ ትምህርት ፡ የጀመርኩበት ፡ ጊዜ ፡ ፲፱፻፳፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ መሪጌታ ፡ ከበበው ፡ መሪጌታ ፡ እውነቴ ፡ መሪጌታ፡ክንፉ
መሪጌታ ፡ ዓልማው ፡ ከተባሉት ፡ መምህራን ፡ ጸዋትወ ፡ ዜማን ፡ ከጣዕመ ፡ ዝማሬው
ጋራ ፤ አለቃ ፡ ማርቆስ ፡ መሪጌታ ፡ ወልደ ፡ ኪዳን ፡ መሪጌታ ፡ ያሬድ ፡ ከተባሉት ፡ መ
ህራን ፡ የግእዝን ፡ ቋንቋ ፡ ከጠቅላላ ፡ ሙያው ፡ ጋራ ፤ እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የሐ
ሳትን ፡ ጣዕመ ፡ ትርጓሜ ፡ በጥቂቱ ፤ ከብሉያት ፡ አራቱን ፡ ብሔረ ፡ ነገሥት ፤ ከአባ
አካሉ ፤ ትርጓሜ ፡ ዳዊት ፡ ከነቢያትና ፡ ከሰሎሞን ፡ ጋራ ፤ ከመምህር ፡ እጅጉ ፡ ( ዘ
ልደ ፡ ማርያም ) ፡ የውዳሴ ፡ ማርያምና ፡ የቅዳሴ ፡ ማርያም ፡ ትርጓሜ ።

በብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወፓትርያርክ
መልካም ፡ ፈቃድና ፡ ትእዛዝ ፡ ከመምህር ፡ ፊላታዎስ ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ መንፈሳዊ
ትምህርት ፡ ቤት ፤ መጽሐፈ ፡ ኢሳይያስ ፡ መጽሐፈ ፡ ፲ቱ ፡ ወ፪ቱ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያት ፡ መ
ሐፈ ፡ አስቴር ፡ መጽሐፈ ፡ ዮዲት ፡ መጽሐፈ ፡ ጦቢት ፡ ከነትርጓሜያቸው ፤ ከመጋቤ
ምስጢር ፡ ጌራ ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታሰቢያ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፤ ስምንቱን፡ብሔ
ኦሪትና ፡ መጽሐፈ ፡ ዳንኤልን ፡ ከነትርጓሜያቸው ። እንዲሁም ፡ ከመምህር ፡ ጽጌ
( አቡነ ፡ ማርቆስ ፡ ዘጐጃም ) ፡ ወንጌል ፡ እያነበብሁ ፡ ከመምህር ፡ ገብረ ፡ ማርያም
መጽሐፈ ፡ ኪዳንና ፡ ትምህርተ ፡ ኅቡአት ፤ በኋላም ፡ ዛሬ ፡ የመርሐ ፡ ዕውራን ፡ ትም
ርት ፡ ቤት ፡ አስተማሪ ፡ ከኾኑት ፡ ከአቶ ፡ ሥዩም ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ በስዊድን ፡ ወን
ላዊት ፡ ሚሲዮን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አዲሱን ፡ የዐይነ ፡ ስውሮችን ፡ ትምህርት ፡ በ
ጠን ፡ ተምሬያለሁ ።

ይኹን ፡ እንጂ ፤ ትምህርቴ ፡ እንደ ፡ መምህሮቼና ፡ እንደ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶቹ
ብዛት ፡ ሙሉ ፡ አይደለም ። ዕውቀቴም ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። ይህንኑ ፡ ከየመምህራኑ
ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ያሰማኹትን ፡ የትምህርት ፡ ጣዕም ፡ በጥቂቱ ፡ እንዳውቀውና ፡ እንዳስ

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ውለው ፡ ያደረገኝ ፤ ምሬቱንም ፡ ያጠነከረብኝ ፡ አዲሱ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ የትምህርት ፡ ዐይ
ነቶችን፡ስለ፡አስገኘና ፡ በወንጌላዊት ፡ ሚሲዮን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በነበርኩበት ፡ ጊዜ ፡
በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በሌሎቹ ፡ አብያተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ መካከል ፡
ያለውን ፡ ልዩነት ፡ በደንብ ፡ ለማጥናት ፡ ስለ ፡ አገዘኝ ፤ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ራሴን ፡ መቈጣ
ጠር፡ስጀምር ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በሎንዶን ፡ ያሳተሙትን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ፡
በቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ወመዘክር ፡ አዘውትሬ ፡ መመልከቴ ፤ ከመልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድ
ማሱ ፡ ጀምበሬና ፡ ከመምህር ፡ ይኄይስ ፡ ወርቄ ፡ በጥብቅ ፡ መነጋገሬ ፡ ነው ።

ኾኖም ፡ ዕውቀቴ ፡ በዚህ ፡ ኹሉ ፡ ፍጹም ፡ ሊኾን ፡ አልቻለም ። ግን ፡ ስለ፡ ኢት
ዮጵያ ፡ ታሪክ ፤ ስለ ፡ ቀናችው ፡ ሃይማኖቷና ፡ ስለ ፡ ተቀደሰው ፡ ምግባሯ ፤ በእግዚአብ
ሔርና ፡ በእሱዋ ፡ መካከል ፡ ስላለውም ፡ ጥኑ ፡ ፍቅር ፡ በሕሊናዬ ፡ የሚወጣው ፡ የሚወ
ርደው ፡ ሐሳብ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ያቃጥለኛል ። ቆሜ ፡ ተቀምጬ ፡ ተኝቼ ፡ ተነሥቼ ፡ በም
ሄድበትና ፡ በማርፍበት ፤ በምበላበትና ፡ በምጠጣበት ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ ትኩር ፡ አድርጌ ፡
የምመለከተው ፡ እሱኑ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

በዚህም ፡ ምክንያት ፡ በመኝታዬ ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ የጤና ፡ እንቅልፍ ፡ አጥቼ ፡
ሕልም ፡ ይኾንብኝና ፤ ኢትዮጵያ ፡ ታበጽሕ ፡ እደዊሃ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ። ፩ዱ፡ነገሩ፡
ለኵሉ ፡ ዓለም ። ወያመጽኡ ፡ እምሳባ ፡ ወርቀ ፡ ወስሂነ ። ቃል ፡ ወልድ ፡ እኁየ ፡ ናሁ ፡
ውእቱ ፡ መጽአ ። ንግሥተ ፡ ዐዜብ ፡ ትትነሣእ ፡ አመ ፡ ዕለተ ፡ ደይን ። ናሁ ፡ መስግላን ፡
መጽኡ ፡ እምብሔረ ፡ ጽባሕ ። ሑር ፡ ትልዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ሰረገላ ። ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ።
ተሣሀለነ ፡ በሞተ ፡ ወልዱ ። ስለሚሉትና ፡ እነሱንም ፡ ስለ ፡ መሳሰሉት ፡ ቃላት ፤
ሙሴን ፡ ዳዊትን ፡ ኢሳይያስን ፡ ንግሥተ ፡ ሳባን ፡ ማቴዎስን ፡ ዮሐንስን ፡ ሉቃስን ፡
ፊልጶስን ፡ ጳውሎስን ፡ ስጠይቅ ፡ አድራለሁ ።

ይኹን ፡ እንጂ ፤ ጥበብን ፡ የሚሻ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ሳያወላውል ፡ ሳያጠራጥር፡ ከእ
ግዚአብሔር ፡ ይለምን ፤ እግዚአብሔርም ፡ ንፍገት ፡ የሌለው ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡ ይሰጠ
ዋል ፡ ያዕ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፭ ፡ ብሎ ፡ ሐዋርያው ፡ ያዕቆብ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፤ እግዚ
አብሔር ፡ አምላኬ ፡ የለመንኩትን ፡ ስላልነሣኝ ፤ በዕውቀቴ ፡ ሳይኾን ፡ በቸርነቱ ፡ እየተ
ረዳሁ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ሳዘጋጅ ፡ ምስጋናዬን ፡ ለእሱ ፡ አስቀድማለኹ ።

ቀጥሎም ፡ ያነሣሣኝን ፡ ምክንያት ፡ ለአንባቢዎች ፡ እገልጣለሁ ፤ እኔ ፡ የውጪ ፡
አገር ፡ ትምህርት ፡ የሌለኝ ፡ መኾኔንና ፡ በውጪ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፉ ፡ መጻሕፍትን ፡
አለማንበቤን ፡ እላይ ፡ እንደ ፡ ገለጥኹት ፡ አሁንም ፡ ደግሜ ፡ እገልጥላችኋለሁ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ትውልዳቸው ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ ኾኖ ፡ በዕለት ፡ ጕብኝት ፡ የመጠ
ኑን ፡ ያኽል ፡ ያውም ፡ ባለመተባበር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ የጻፉ ፡
የውጪ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። አብዛኞቹም ፡ ከ፲፰ኛው ፡ ፻ ፡ ዓመት ፡
ወዲህ ፡ በተለይም ፡ ከዐድዋ ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ የተነሡ ፡ ናቸው ።



እነዚህ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ካዘጋጁዋቸው ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ውስጥ ፡ ኢትዮጵያ
ውያን ፡ ጸሐፊዎች ፡ እየተረጐሙ ፡ በአማርኛ ፡ ገልጠዋል ። ከግልባጮቹም ፡ አብዛኞቹ፡
ከፈረንሳይኛና ፡ ከጣልያንኛ ፡ የተመለሱ ፡ መኾናቸው ፡ ነው ።

ሀ) እነዚህ ፡ መጻሕፍቶች ፡ የኢትዮጵያ ፡ እምነት ፡ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ ወደ ፡ ሰሎ
ሞን ፡ ከመሄዷ ፡ በፊት ፡ መኖሩን ፡ ክደው ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ፡
ይላሉ ።

ለ) ስለ ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ሲናገሩ ፤ የቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ መሠረት ፡ መኾኑን ፡ ክደው ፡
የዕብራይስጥ ፡ የጽርዕ ፡ የዐረብና ፡ የላቲን ፡ ዲቃላ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ይናገራሉ ።

ሐ) በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተጻፉትን ፡ ቃላት ፡ ለቃዴስ ፡ በርኔ ፡ እያደረጉ ፡ ይተ
ረጕማሉ ።

መ) ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ከሰሎሞን ፡ መወለዱ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ለዳዊት ፡ ተስፋ ፡
ወራሽ ፡ መኾኑንና ፡ ታቦተ ፡ ጽዮን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መምጣቷንም ፡ ሳይቀር ፡ ያዋ
ጁን ፡ በጀሮ ፡ ይክዳሉ ።

ሠ) ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ከመቀበሏ ፡ በፊት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ከተቀበ
ለችም ፡ በኋላ ፡ በዘመነ ፡ ክርስትና ፡ ሳይቀር ፡ ኢትዮጵያ ፡ በወፍ ፡ በዛፍ ፡ በዘንዶና ፡
በልዩ ፡ ልዩ ፡ አራዊት ፤ በሰማይ ፡ ሰራዊትና ፡ በክፉዎች ፡ መናፍስት ፡ ታመልክ ፡ እንደ ፡
ነበረ ፡ ያወራሉ ። መቅደሶቻቸውና ፡ መሠዊያዎቻቸው ፡ የት ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ግን ፡ አይና
ገሩም ።

ረ) ሰብአ ፡ ሰገል ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መኾናቸውንና ፡ የትንቢቱ ፡ ባለቤቶች ፡
መኾናቸውን ፡ ክደው ፡ የሌላ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በድንገት ፡ የተጠሩ ፡ አረመኔዎች ፡ እንደ ፡
ነበሩ ፡ ይናገራሉ ።

ሰ) ኢትዮጵያ ፤ ክርስቲያን ፡ መባል ፡ በአንጾኪያ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ክርስ
ትናን ፡ የተቀበለች ፡ አገር ፡ መኾኗን ፡ ክደው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክርስትና ፡ ባ፬ኛው ፡ መቶ ፡
ዓ ፡ ም ፡ በቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ስብከት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይናገራሉ ። እንዲሁም ፡ ብዙ፡
ሌላ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ክብር ፡ እየሰረዘ ፡ የወገኑን ፡ ታሪክ ፡ እያጕለመሰ ፡ የሚሄድ ፡ ወሬ፡
ይገኝባቸዋል ። ኾኖም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እነዚህን ፡ መጻሕፍቶች ፡ አንብበው ፡ የጸፏቸ
ውንና ፡ የተጻፉበትን ፡ ዘመን ፡ ካጠኑ ፤ ኀይለ ፡ ቃላቸውንም ፡ ከተረዱ ፡ በኋላ ፤ እውነት፡
ነው ፡ ብለው ፡ አምነው ፡ ተርጕመው ፡ ለሕዝብ ፡ ከማቅረባቸው ፡ ይልቅ ፡ ተቃዋሚዎ
ቻቸውን ፡ ይከራከራሉ ። እንደ ፡ እውነቱ ፡ ቢኾን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በኢትዮጵያ፡አልፎ ፡
አልፎ ፡ አደጋዎች ፡ ባይጠፉ ፤ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ቢቃጠሉና ፡ መጻሕፍትም ፡
ቢቈነጠሉ ፡ ጥቂቶች ፡ በግእዝ ፡ የተጻፉ ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍት፡እስከ ፡ ዛሬ ፡ አልታጡም ።
አልደረስኩባቸውም ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ እንኳ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በቅርብ ፡ ይገ
ኛልና ፡ ከእሱ ፡ እያስማሙ ፡ ሊጽፉ ፡ የሚገባ ፡ ሲኾን ፡ የኢትዮጵያን ፡ መጻሕፍት ፡ ከግ
እዝ ፡ ቋንቋ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ጥሎ ፤ የባዕድን ፡ ወሬ ፡ ተከትሎ ፡ የሀገርን ፡ ታሪክ ፡ በዚ

www.ethiopianorthodox.org

ያው ፡ መወሰንና ፡ መሠረታዊውን ፡ ትቶ ፡ ጫፉን ፡ ዋናውን ፡ ትቶ ፡ ጥገኛውን፡ማጽደቅ ፡
ተገቢ ፡ ባልኾነም ፡ ነበር ።

እንዲያውም ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልባቸው ፡ አንዳንድ ፡ ታላላቅ ፡ ሊቃውንት ፡ እንኳ ፡
በመኃልየ ፡ ሰሎሞን ፡ የተገለጠውን ፡ የንግሥተ ፡ ሳባን ፡ ታሪክና ፡ ትንቢት፡ለውጠው ፡
ለግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ . . . ሰጥተው ፡ እንዲሁም ፡ ብሉያት ፡ ከዕብራይስጥ ፤ ሐዲሳት፡
ከጽርዕና ፡ ከዕብራይስጥ ፡ መምጣታቸው ፡ ሲታመን ፤ በሐዲሱ ፡ አስጠግተው፡የብሉይ፡
ኪዳን ፡ መጻሕፍት ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ መገልበጣቸውን ፡ ጨምረው፡ክደው ፡
ብሉያትና ፡ ሐዲሳት ፡ ከጽርዕ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ባ፬ኛው ፡ ፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሰላማ ፡ ዘመን ፡
ተተርጕመዋል ፡ ብለው ፡ ከመጻፋቸው ፡ ይልቅ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚባለው ፡ ስምም ፡ ያን ፡
ጊዜ ፡ ከጽርዕ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በመናገራቸውና ፡ በጽሑፍ ፡ በማስፈራቸው ፡
ኀዘኔ ፡ እየጠነከረ ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ እየጨመረ ፡ ስለ፡ሄደ ፤ እኔ ፡ ልጀምረውና ፡ ሌላ፡
ዐይናማ ፡ ሊቅ ፡ አበጥሮ ፡ አጣርቶ ፡ ይጽፈዋል ፡ በማለት ፡ ለጊዜው ፡ እንደ ፡ ረኃብተኛ፡
ሰው ፤ ሰው ፡ ያየኛል ፡ ሰው ፡ ይታዘበኛል ፡ ሳልል ፡ በጥቂቱ ፡ የዋዜማ ፡ ያኽል ፡ ይህን ፡
መጽሐፍ ፡ አዘጋጅቻለሁ ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎም ፡ ከላይ ፡ ስለ ፡ ዘረዘርኳቸው ፡ ነገሮች ፡ አጭር ፡ አጭር ፡ መግ
ለጫ ፡ እሰጣለሁ ።

ሀ) ኢትዮጵያ ፡ ከእስራኤል ፡ ያገኘችው ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ጽላትን ፡ ሌዋውያን ፡
ካህናትን ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሃይማኖትን ፡ አይደለም ። ሃይማኖቷ ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ አባ
ቶቿ ፡ የወረሰችው ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖት ፡ ከአበው ፡ ተመሥርቶ ፡ ንግሥተ ፡
ሳባ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ከመሄዷዋ ፡ በፊት ፡ ለመኖሩ ፡ ምስክሮቹ ፡ ኑኅ ፡ ዘመን ፡ ብቻ ፡
ሳይኾን ፡ የመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ታሪክና ፡ የንግሥተ ፡ ሳባ ፡ መንገድ ፡ ቃላተ ፡ ትንቢቷም ፡
ናቸው ። የመልከ ፡ ጼዴቅን ፡ ታሪክ ፡ ወደፊት ፡ እናገኘዋለን ።

ግን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መነኰሳት ፤ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ለመቀበል ፡ ጊዜ ፡ ካል
ኾነ ፡ በቀር ፡ ጥፍር ፡ አለመቍረጥን ፡ ጠጕር ፡ አለመላጨትን ፡ የላመ ፡ የጣመ ፡ አለመ
ቅመስን ፡ ዳባ ፡ መልበስን ፡ ጸሎት ፡ ማዘውተርን ፤ ባንድ ፡ በኣት ፡ ተወስኖ ፡ መኖርን ፡
ከመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ እንደ ፡ ወረሱት ፡ ስናስታውስ ፡ ይህ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ መቼ ፡ እንደ ፡
ነበረ ፡ ብንጠይቅ ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ ከመሠራቱ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡
ያስረዳናል ።

ይህ ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፤ አብርሃም ፡ ዐሥራት ፡ (ካሥር ፡ አንድ ፡) የሰጠው ፡ እሱ ፡
መኾኑንና ፡ ክህነቱም ፡ የወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ ኾኖ፡መኖሩን ፤ አብርሃምንም ፡
መባረኩን ፡ መጻሕፍት ፡ ሲነግሩን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዕድል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
ምን ፡ ያኽል ፡ እንደ ፡ ኾነና ፡ በስሙም ፡ ማመኗ ፡ ከመቼ ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ልንረ
ዳው ፡ እንችላለን ።



እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ታሪክና ፡ ትንቢት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ የታወቀውን፡ክብረ ፡ ነገሥት ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ብንታመነውም ፡ እንኳ፡
ዓለም ፡ ተስማምቶ ፡ የተቀበለው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ የወጣለቱን ፡ የሰሎሞንን ፡ ስም ፡ ሰምታ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሄደች፡በማለቱ ፡
ታላቋ ፡ ንግሥት ፡ በሌላ ፡ ( ጣዖት ) ፡ አምልኮት ፡ ያልረከሰች ፤ በአምልኮተ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ የጸናች ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ ይገልጥልናል ።

ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ እስኪ ፡ እናስታውስ ።

የጣዖት ፡ ዜጎች ፡ ሲኾኑ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሲፈልጉ ፡ የተገኙ ፡ እነማን፡ናቸው ?
በጣዖታውያን ፡ ዘንድስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ሲል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም፡ሲጠራ ፡
ተገኝቶ ፡ በእሳት ፡ በስለት ፡ ያልተሠቃየ ፡ ማነው ? እንግዲህ ፡ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ ሌላ ፡
የምታመልክ ፡ ከኾነ ፡ ታምሪን ፡ የተባለው ፡ ነጋዴ ፡ የሸቀጥ ፡ ዕቃ ፡ መለቃቀሙን ፡
ትቶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ሲጠራ ፤ የሌላ ፡ ንጉሥ ፡ ታሪክ፡ሲያወራ ፤ የኢትዮጵያን፡
ሃይማኖት ፡ ሲያኰስስ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ሃይማኖት ፡ ሲያነጋግሥ ፡ ቢገኝ ፤ ከእሳት ፡ ከስ
ለት ፡ በአንደኛው ፡ ባልተቀጣም ፡ ነበረን ? ምናልባትም ፡ ሴት ፡ ብትኾን ፡ በአእምሮዋ፡
ደካማነት ፡ ነው ፡ ትሉኝ ፡ ይኾናል ። እኔም ፡ ሴት ፡ ብትኾን ፤ የአእምሮ ፡ ድካም፡ ቢያገ
ኛትም ፡ ኖሮስ ፤ መንግሥቴ ፡ ከመንግሥቱ ፤ ሀብቴ ፡ ከሀብቱ ፤ ሃይማኖቴ ፡ ከሃይማኖቱ ፡
ይበልጣልን ፤ ሰሎሞን ፡ ማነው ? እግዚአብሔርስ ፡ ማነው ? አንተስ ፡ ምን ፡ ብትደፍረኝ፡
በፊቴ ፡ ይህን ፡ ታወራለህ ፡ ብላ ፡ በቀጣችው ፡ ነበር ፡ ብዬ ፡ እመልስላችኋለሁ ።

ይልቅስ ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ሌላውን ፡ እንመልከት ፤ ታላቂቱ ፡ ሃይማኖተኛዪቱ ፡
ኢትዮጵያዊት ፡ ንግሥት ፡ ባካባቢዎቿና ፡ በድንበሮቿ ፡ የሚገኙት ፡ ነገሥታትና ፡
ዜጎቻቸው ፤ ዕንጨት ፡ እየጠረቡ ፡ ደንጊያ ፡ እያለዘቡ ፡ ሲያመልኩ ፤ እሷ ፡ ሰማ
ያዊውን ፡ አምላክ ፡ በማምለኳ ፡ ይህን ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ስትመለከተው ፡ ልዩ ፡
ልዩ ፡ ጣዖታት ፡ በነበሩዋቸው ፡ በከነዓናውያን ፡ አገሮች ፡ የሃይማኖት ፡ ወገን ፡ ሰሎሞ
ንንና ፡ ዜጎቹን ፡ በማግኘቷ ፡ በደስታ ፡ ልትፈልጋቸው ፡ ሄደች ። ከዚያም ፡ ደርሳ፡ የሃይ
ማኖታቸውን ፡ ጥልቅነት ፡ የሃይማኖቷንና ፡ የሃይማኖታቸውን ፡ ኅብረት ፤ የምግባሯንና፡
የምግባራቸውን ፡ ስምምነት ፡ ከተረዳች ፡ በኋላ ፤ ደስ ፡ ብሏት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመ
ሰገነች ። እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ ሃይማኖቷን ፡ በሥራ ፡
ስለ ፡ ገለጠችው ፡ በጊዜው ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ትነሣለች ፤ ይህችንም ፡
ትውልድ ፡ ትፋረዳታለች ፡ ብሎ ፡ ከመመስከሩ ፡ በፊት ፤ የነቢያት ፡ ጌታ ፡ ስም፡ወደ፡ ተጠ
ራበት ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ ነቢያት ፡ ያልደረሱበትን ፤ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡
በወንጌሉ ፡ የገለጠውን ፡ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፡ እንድትናገር ፡ መንፈስ ፡ ትንቢትን ፡ ስለ ፡
አደላት ፤ የዳዊትን ፡ ትንቢት ፡ ከዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ስብከት ፡ ማለት ፡ ከአብራክኺ ፡
የተገኘውን ፡ በዙፋንኺ ፡ አነግሥልሀለኹ ፡ ያለውን ፡ በአባቱ ፡ እሪና ፡ ያለ ፡ አንዱ፡ልጁ፡
ነገረን ፡ ከማለት ፡ አስማምታ ፡ አጣምራ ፡ አስተባብራ ፤ ቃል ፡ ወልድ ፡ እጉየ ፡ ናሁ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ውእቱ ፡ መጽአ ። ( ቃል ፡ ወልድ ፡ በሥጋ ፡ ወንድሜን ፡ (ሰሎሞን) ፡ ኾኖ ፡ እነሆ ፡ እሱ፡ ራሱ ፡ መጣ ) ፡ ብላ ፡ ተናገረች ። መኃ ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፳ ።

እንዲሁም ፡ በመስቀሉ ፡ ቀን ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ልጃገረዶች ፡ እየተከተሉ ፡ ሊያለቅሱለት ፡ ፃእ ፡ ትርአያ ፡ አዋልደ ፡ ጽዮን ፡ ለንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ በአክሊል ፡ ዘአስተቀጸለቶ ፡ እሙ ፡ አመ ፡ ዕለተ ፡ ሕማሙ ፤ አመ ፡ ዕለተ ፡ መርዓሁ ፤ ወአመ ፡ ዕለተ ፡ ፍሥሓ ፡ ልቡ ። (ያሰበው ፡ ድኅነተ ፡ ምእመናን ፡ በእሱ ፡ መከራ ፡ ተፈጽሞለት ፡ ደስ ፡ ያለው ፤ ንጉሡ ፡ ክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ለተዋሕዶ ፡ በመረጠበት ፡ ቀን ፡ እናቱ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ያቀዳጀችውን ፡ የእሾኽ ፡ አክሊል ፡ ደፍቶ ፡ ታዩት ፡ ዘንድ ፡ የጽዮን ፡ ልጃገረዶች ፡ ኑ ፡ ውጡ ፡ ) እያለች ፡ የቀሰቀሰቻቸው ፡ ይህች ፡ ነቢይት ፡ ናት ።

መኃ ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፲፩ ። አስደናቂውም ፡ ወልድ ፡ እኁየ ፡ ሊተ፡አወነ ፡ ሎቱ ፡ ( ወንድሜን ፡ ሰሎሞንን ፡ ኾኖ ፡ ያየኹት ፡ ወልድ ፡ ለኔ ፡ ነው ፡ እኔም ፡ ለሱ ፡ ነኝ ፡ ) መኃ ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ። ስትል ፡ በራሷና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የገባችው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ነው ።

ሊቃውንቱ ፡ ግን ፡ መኃልይን ፡ የተናገረችው ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ናት ፡ ሲሉ ፡ በጣም ፡ ያሳዝኑኛል ። የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ልጅማ ፡ ሰሎሞንን ፡ ያኽል ፡ ሰው ፡ ስባ፡ ጐትታ ፡ ጣዖት ፡ ወደማመልክ ፤ አንበጣ ፡ ወደ ፡ መሠዋት ፡ ያደረሰችው ፡ አይደለችምን ።

« ኢትዮጵያውያን ፡ ሆይ » ።

እውነተኛውን ፡ ታሪክ ፡ ወደ ፡ መከተል ፡እግራችሁንም ፡ ዐይናችሁንም ፡ አንሡ፡ ይህች ፡ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ አናጢዎች ፡ የናቋት ፡ ደንጊያ ፡ ናት ፤ እኛ ፡ የልቡናችን ፡ መዓዝን ፡ ማቅኛ ፡ መሰብሰቢያ ፡ እናድርጋት ።

ስለ ፡ ንግሥተ ፡ ሰባ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢፈቅድልኝ ፡ በሚቀጥለው ፡ መጽሐፍ ፡ እገልጥላችኋለሁ ።

ለ) ስለ ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ገለጥኩላችኹ ፡ ኹሉ ፡ የግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ዲቃልነቱ ፡ እንጂ ፤ አባትነቱ ፡ አይወራም ። መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ግን ፡ ፩ዱ ፡ ነገሩ ፡ ለኵሉ ፡ ዓለም ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ በሰናዖር ፡ ሜዳ ፡ ግንብ ፡ መሥራት ፡ እስከ ፡ ጀመሩበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የዓለሙ ፡ ቋንቋ ፡ አንድ ፡ (አ) ፡ (ሀ) ፡ (ግእዝ) ፡ ነበረ ፡ ሲል ፡ እየተናገረ ፡ እየመሰከረ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የዕብራይስጥ ፡ የጽርዕ ፡ ያረብና ፡ የላቲን ፡ ዲቃላ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ባጭሩ ፡ ስለ ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ጥንታዊነት ፡ ዐርብ ፡ ቀዳሚት ፡ የተባሉት ፡ ቃላት ፡ የሚሰጡት ፡ ምስክርነት ፡ ብቻ ፡ እንኳን ፡ ሊያስረዳን ፡ ይችላል ። እንዴት ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ እነዚህ ፡ ቃላት ፡ የመጀመሪያውን ፡ ስሜት ፡ ያለቀቁ ፡ በመኾናቸው ፡ ነው ። በሌሎቹ ፡ ቋንቋዎች ፡ ዕለታት ፡ አንድ ፡ ኹለት ፡ የሚለውን ፡ መሥመር ፡ ሳይለቁ ፤ ተመሳሳይ ፡ ድምጣቸውንም ፡ ሳይለውጡ ፡ ካንድ ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ይዘልቃሉ ። በግእዝ ፡ ግን፡ ከሰባቱ ፡ ዕለታት ፡ ዐምስቱ ፡ ተራቸውንና ፡ ተመሳሳይነታቸውን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ኹኖ ፡ ኹለቱ ፡ ( ዐርብና ፡ ቀዳሚት ) ፡ የስም ፡ ተራቸውንና ፡ ተመሳሳይነታቸውን ፡ ለቀው ፡



ዐርብ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሔዋንን ፡ ከአዳም ፡ ጐን ፡ ሲፈጥር ፡ የመኝታ ፡ እንቅልፍ ፡ እንደ፡ ጣለበት ፡ ሠርክ ፡ ማለትን ፡ መስሎ ፡ ተከትሎ ፡ ስለሚሄድና ፡ ቀዳሚት ፡ ማለት ፤ እግዚአብሔር ፡ ሥራውን ፡ ፈጽሞ ፡ ያረፈባት ፡ መኾኑን ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በእሱዋ ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ሰንበት ፡ እንደምትሠራባት ፡ ማመልከትንም ፡ ጨምሮ ፡ ስለሚገልጥ ፡ እነዚህ ፡ ኹለት ፡ ቃላት ፡ ( ዐርብና ፡ ቀዳሚት ) ፡ ምስጢርን ፡ ብቻ ፡ ይከተላሉ ።

እንግዲህ ፡ እነዚህ ፡ ቃላት ፡ መዋዕለ ፡ ፍጥረትን ፤ ዜና ፡ ፍጥረትን ፡ በመጥቀስ ፡ ከስሙ ፡ ጋራ ፡ ሲመሰክሩለትና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንደምናገኘው ፡ አባትነቱን ፡ ሽሮ ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ መስጠት ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ።

ስለዚህ ፡ እኛ ፡ አግዓዝያን ፡ (የነጻነት ፡ ባለቤቶች) ፡ መኾናችንን ፡ የምናምን ፡ ከኾነ ፡ የቋንቋችንንም ፡ አንደኛነትና ፡ አባትነት ፡ ልናውቅለት ፡ ይገባናል ። ወንድምቼ፡ ለነጻነታችሁ ፡ ምክንያት ፡ አትስጡት ። ገላ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ላሳስባችሁ ፡ የሚገባኝ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ ስለ ፡ ቀዳሚት ፡ ሰንበት ፡ ከተቃዋሚዎች ፡ የሚቀርበው ፡ ሐተታ ፡ ነው ። ይኸማ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ የተቀበለችው፡አይደለምን፡ የሚል ፡ ጠያቂ ፡ ቢኖር ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ ለቀዳሚት ፡ ሰንበት ፡ ፍጻሜዋ ፡ እንጂ ፤ መጀመሪያዋ ፡ አለመኾኗን ፡ ለማወቅ ፡ መጽሐፈ ፡ ኩፋሌን ፡ እንዲመለከት ፡ እያሳሰብሁት ፡ ይህ ፡ ባይመስለው ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ማን ፡ ትባል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ባስረዳኝ ፡ ጊዜ ፡ መልሱን ፡ እሰጠዋለሁ ። ለዐርብ ፡ ግን ፡ ሰበብ ፡ አትስጡት ።

ሐ) መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲገባ ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ተተርጕሞ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ከዕብራይስጥ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ተተርጕሞ ፡ አይደለም ።

ስለዚህም ፡ በአንዳንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ጽርዑና ፡ ግእዙ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚሉትን ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፤ እንዲሁም ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ የተተረጐመው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በረሃ ፡ ይላል ። ምክንያቱም ፡ ጽርዑና ፡ ግእዙ፡ ከመጀመሪያው ፡ ዕብራይስጥ ፡ በመስማማት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ማለታቸው ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ቅንአት ፡ ምቀኝነት ፡ ሳይቀላቀሉበት ፡ የተገኙ ፡ በመኾናቸው ፡ ነው ። ምስክርነታቸውም ፡ የታመነ ፡ ነው ። ከአዲሱ ፡ ዕብራይስጥ ፡ የተተረጐሙት ፡ መጻሕፍት ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚለውን ፡ በረሃ ፡ ማለታቸው ፤ አይሁድ ፡ መጻሕፍትን ፡ ከለወጧቸው ፡ ወዲህ ፡ የተገኙ ፡ በመኾናቸው ፡ ነው ።

ልዩ ፡ አስተያየት ፡ አላቸው ፡ ተብለው ፡ የሚታመኑት ፡ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ እንኳን ፡ በመዝሙር ፡ ፸፩ ፡ ቍጥር ፡ ፱ ፡ ይገንዩ ፡ ቅድሜሁ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በመዝሙር ፡ ፷፫ ፡ ቍጥር ፡ ፲፬ ፡ ወሀብኮሙ ፡ ሲሳዮሙ ፡ ለሕዝበ፡ኢትዮጵያ ፡ የሚለውን ፡ ሲያስረዱ ፡ አዲሱን ፡ ግልባጭ ፡ በመከተል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ማለትን ፡ በረሃ፡ ወደ፡ማለት፡ ከመለወጣቸውና፡ የኢትዮጵያን ፡ ታላቅ ፡ ተስፋ ፡ ለቃዴስ ፡ በርኔ ፡ ከመስጠታቸው ፡ ይልቅ ፡ ዕብራይስጢው ፡ በረሃ ፡ የሚለውን ፡ ጽርዑ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይላል ፡ ስለዚህም ፡ ኢትዮጵያ ፡ መባል ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የተሰጣት ፡ በአቡነ ፡ ሰላማ ፡ ዘመን ፡ ነው ፤ ብሉይ ፡ ኪዳንም ፡ ከሐዲስ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኪዳን ፡ ጋራ ፡ ከጽርዕ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ የተመለሰው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ኢትዮጵያ፡ ፫ ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ የተጠራችበትን ፡ ስም ፤ ብሉይ ፡ ኪዳንም ፡ ከዕብራይስጢ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ መተርጐሙን ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ በተባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ አስተባብለዋል። ነገር ፡ ግን ፡ የተናገሩትን ፡ ረስተው ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አመካኝቶባቸው ፡ እንደ ፡ ኾነ፡ እንጃ ፡ እንጂ ፤ የሀገራችን ፡ ሰዎች ፡ ዕብራይስጥ ፡ ጠፍቷል ፡ ይላሉ ፡ በማለት ፡ ተነሥተው ፡ ዐሳባቸውን ፡ ሲሰጡ ፡ ወርቁ ፡ ደረቁ ፡ ትንቢት ፡ ጠፋ ፡ እንጂ ፤ ቋንቋቸውስ ፡ አልጠፋም ፡ ብለዋል ። ደረቁ ፡ ትንቢት ፡ ለመጥፋቱ ፡ ሲያስረዱም ፡ ከዕብራይስጢ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ የተተረጐመው ፡ አሪት ፡ እንደ ፡ ጽርዑ ፡ ቀጥተኛ ፡ መኾኑን ፡ ከገለጡ ፡ በኋላ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ የተጻፈው ፡ አሪት ፡ ዛሬም ፡ ዓለም ፡ የተስማማበትና፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ መጽሐፍ ፡ ጐደሎ ፡ መኾኑን ፡ ገልጠዋል ። ከሞታቸው ፡ በፊት ፡ ያሳተሙትን ፡ መዝገበ ፡ ፊደል ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፋቸውን ፡ መመልከት ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ላይ ፡ መጻሕፍት ፡ ከዕብራይስጢ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ተተርጕመዋል ፡ ካልክ፡ ዕብራይስጢ ፡ ለግእዝ ፡ አባቱ ፡ መኾኑ ፡ አይደለምን ፡ የሚል ፡ ጠያቂ ፡ ቢኖር ፡ ከዕብራይስጢ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ተተረጐሙ ፡ የምል ፡ በዕብራውያን ፡ አፍ ፡ የተነገሩትን ፡ አሪት ፡ ነቢያትን ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ መጽሐፈ ፡ ሄኖክን ፡ አይደለም ፡ ብዬ ፡ እመልስለታለሁ ።

እንግዲህ ፡ ጽርዑ ፡ ከአባቱ ፡ ጥንታዊ ፡ ዕብራይስጥና ፡ ከወንድሙ ፡ ከግእዝ ፡ በመስማማት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያለውን ፤ ለቃዴስ ፡ በርኔ ፡ መስጠት ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ። አሪት ፡ ግዕዝስ ፡ ሐሜት ፡ ከሌለው ፡ ከጥንታዊው ፡ ዕብራይስጥ ፡ የተቀዳ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ቃዴስ ፡ በርኔን ፡ በየመልካቸው ፡ ስለሚያውቃቸው ፤ በየስማቸው ፡ ለይቶ ፡ ያስታውሳቸዋል ። ስለዚህም ፡ መሪነቱን ፡ ዐውቀን ፡ መንገዱን ፡ ጠብቀን ፡ ብንከተለው ፡ ከመልካም ፡ ፍጻሜ ፡ እንደሚያደርሰን ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ።

## « ኢትዮጵያ ፡ ሆይ ፡ » እኔ ፡ ክብርሽን ፡ ለሌላ ፡ አልሰጥም ።

መ) ስለ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ንጉሠ ፡ ሰሎሞን ፡ የአባቱን ፡ ዙፋን ፡ በወረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ዙፋንኽ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ሞቆ ፡ እንደ ፡ ጨረቃ ፡ ደምቆ ፡ አባትነትህም ፡ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ። ከልጅ ፡ ልጅኽም ፡ በዙፋንኽ ፡ የሚተካ ፡ አላጠፋም ፡ ብሎ ፡ በራሱ ፡ ምሎ ፡ የሰጠው ፡ ቃል ፡ ኪዳን፡ ከሰሎሞን ፡ በሚወለደው ፡ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ እንደሚፈጸምለት ፡ በመንፈስ ፡ ትንቢት ፡ ተገልጦለት ፡ ሲናገር ፡ አቤቱ ፡ ፍርድኽን ፡ ለንጉሡ ፡ ስጠው ፡ ብሎ ፡ ለጊዜው ፡ ለሰሎሞን ፡ ከጸለየለት ፡ በኋላ ፡ እውነተኛ ፡ ቃልኽንም ፡ ለንጉሡ ፡ ልጅ ፡ አድርግለት ፡ የሚል ፡ ጸሎተ ፡ ትንቢቱን ፡ ጀምሮ ፡ ወአኀስሮ ፡ ለዕቡይ ፡ ብሎ ፡ ድል ፡ አድራጊነትን ፡ ወይጸናዕ ፡ ምስለ ፡ ፀሐይ ፡ ብሎ ፡ ኑኀ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥትን ፤ ይገንዩ ፡ ቅድሜሁ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብሎ ፡ ተስፋው ፡ ለእስራኤል ፡ ሳይኾን ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ መኾኑን ፤ እምርዶ ፡ ወእምትዕግልት ፡ ያድኅና ፡ ለነፍሶሙ ፡ ብሎ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለሕ



ዝቡ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ አባትም ፡ ጭምር ፡ መኾኑን ፤ ወዘልፈ ፡ ይጼልዩ፡ በእንቲአሁ ፡ ብሎ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የዳዊትን ፡ መሪነት ፡ ተከትለው ፡ እግዚኦ ፡ አድኅኖ፡ ሀቦ ፡ ለንጉሥ ። ጽድቀከኒ ፡ ለወልደ ፡ ንጉሥ ። አግርር ፡ ፀሮ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ። ዕቀብ ፡ ንግሦ ፡ ወሰራዊቶ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ (አቤቱ ፡ ፍርድኽን ፡ ለንጉሡ ፡ ስጠው ፡ (ግለጥለት) ፡ እውነተኛ ፡ ቃልኽንም ፡ ለዐልጋ ፡ ወራሹ ፡ አድርግለት ፡ (በዙፋኑ፡ ተካለት) ፤ በሩቅ ፡ በቅርብ ፡ ያሉ ፡ ጠላቶቹን ፡ በእጁ ፡ ጨብጦ ፡ በእግሩ ፡ ረግጦ ፡ እንዲገዛ ፡ አድርገው ፤ የንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ የእገሌን ፡ መንግሥቱን ፡ ሰራዊቱን ፡ ጠብቅ ፡ እያሉ ፡ ዘወትር ፡ እንደሚጸልዩለት ፤ ወኵሎ ፡ አሚረ ፡ ይድኅርዎ ፡ ብሎ ፡ ዘወትር ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሕየው ፡ አበ ፡ ነጋሢ ፡ የንጉሥ ፡ የንግሥት ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ያንግሥኽ ፡ እያሉ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸውን ፡ እንደሚመርቁ ፡ የተናገረው ፡ ትንቢት ፡ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ስለ ፡ ተፈጸመ ፤ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክና ፡ ልጆቹ ፡ ለንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ የተስፋውና ፡ የዙፋኑ ፡ ወራሾች ፡ ኾነው ፡ በመገኘታቸው ፡ የመንግሥተ ፡ ዳዊት ፡ ክብር ፡ መንግሥተ ፡ አኵስምንና ፡ መንግሥተ ፡ ሳባን ፡ ተዋሕዶ ፡ ሲገሠግሥ ፡ የ፫ ፡ ሺሕ ፡ ዘመናት ፡ ጕዞ ፡ አሳልፎ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ዐርፎ ፡ እናየዋለን ።

እንግዲህ ፡ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ አብአኒ ፡ ንጉሥ ፡ ውስተ ፡ ጽርሑ ፡ ብላ ፡ በንጉሥ፡ ሰሎሞንና ፡ በእሱዋ ፡ መካከል ፡ የተፈጸመውን ፡ ምስጢር ፡ ስትገልጥ ፤ ንጉሥ ፡ ሰሎሞንም ፡ ከርሥኪ ፡ ስውጠ ፡ ሥርናይ ፡ ወሕጹር ፡ በጽጌ ፤ (ማሕፀንሽ ፡ የስንዴን ፡ ቅንጣት ፡ የያዘ ፡ ነው ፤ ስንዴውም ፡ በአበባ ፡ የተከበበ ፡ ነው ፡ ብሎ) ፡ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክን ፡ ከእሱ ፡ መፅነሷንና ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ አያቱ ፡ ዳዊት ፡ እምቅድመ ፡ ፀሐይ፡ ሀሎ ፡ ስሙ ፡ ( ስሙ ፡ ከፀሐይ ፡ በፊት ፡ ነው ) ፤ ማለት ፡ ፀሐየ ፡ ጽድቅ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመወለዱ ፡ በፊት ፡ የዳዊት ፡ ሥጋዊ ፡ ተስፋና ፡ ዐልጋ ፡ ወራሽ ፡ መኾኑን ፡ በተናገረለት ፡ መሠረት ፡ በክርስቶስ ፡ ምሳሌነት ፡ ያጌጠ ፡ ያሸበረቀ ፡ መኾኑን ፡ ሲያረጋግጥ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ታሪክ ፡ የሚያጠራጥሩበት ፡ ምን ፡ ይኾን ?

ስለ ፡ ታቦተ ፡ ጽዮንም ፤ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ውስተ ፡ ዕረፍትከ ፡ አንተ ፡ ወታቦተ ፡ መቅደስከ ። (በመመስገኛህ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ካለችው ፡ ከታቦተ ፡ ጽዮን ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ማረፊያኽ ፡ ለመሄድ ፡ ተነሥ ) ፡ ብሎ ፡ በተናገረበት ፡ አርእስት ፡ መሠረትነት ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በዳዊት ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ የቆመውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በመጥቀስ ። እግዚአብሔር ፡ ጽዮንን ፡ ለዘላለም ፡ ማደሪያ ፡ አድርጎ ፡ መምረጡንና ፡ በዚሁም ፡ ወበህየ ፡ አበቍል ፡ ቀርነ ፡ ለዳዊት ፡ (በዚያ ፡ ቦታ ፡ ለዳዊት ፡ የሚተካ ፡ ልጅ፡ እሰጠዋለሁ ፤ ሥልጣኑንም ፡ አጸናለታለሁ ፤ ለልጁም ፡ ማኅቶተ ፡ መንግሥትን ፡ አዘጋጅለታለሁ ፤ ጠላቶቹን ፡ አዋርዳቸዋለሁ ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ቅዱስነቴ ፡ በፍሬ ፡ ላይ ፡ ፍሬ፡ እየጨመረ ፡ ይኖራል) ፡ ማለት ፡ ዘወትር ፡ እመሰገንበታለሁ ፡ ማለቱን ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ኹሉ ፡ ታቦተ ፡ ጽዮን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በአኵስም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ መኖሯንና ፡ የኢትዮጵያ፡ ነገሥታት ፡ በአኵስም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ለዳዊት ፡ ተስፋ ፡ ተቀባዮች ፤ ለእግዚአብ

www.ethiopianorthodox.org

ሔር ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ አገልጋዮች ፡ በመኾን ፡ መሢሐዊን ፡ ሥርዐተ ፡ መንግሥት ፡ ሲፈጽሙ ፡ እናያቸዋለን ።

ይህን ፡ የሚያስተባብል ፡ ቢኖር ፡ መንግሥተ ፡ አኵስምን ፤ መንግሥተ ፡ ሳባን ፤ መንግሥተ ፡ ዳዊትን ፡ ወርሶ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኀይል ፡ ነግሦ ፡ ከዓለም ፡ ነገሥታት ፡ መካከል ፡ አርዕድ ፡ አንቀጥቅጥ ፡ በሚባል ፡ ልብሰ ፡ መንግሥቱ፡የሚታወቀውን ፡ ተፈሪውን ፡ የይሁዳ ፡ አንበሳ ፡ ይመልከት ።

ሰ) ኢትዮጵያ ፤ መንፈሳዊ ፡ ዕውቀቷን ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ በሕገ ፡ ወንጌል ፤ ሥጋዊ ፡ እድገቷን ፡ በመንግሥተ ፡ አኵስም ፡ በመንግሥተ ፡ ሳባ ፡ በመንግሥተ ፡ ዳዊት ፡ እያስፋፋች ፤ እያገለመሰች ፤ እያጠነከረች ፡ የኖረችና ፡ ዛሬም ፡ ያለች ፤ በመንፈሳዊና ፡ በሥጋዊ ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ድልና ፡ ዕድል ፡ ያላት ፡ አገር ፡ መኾኗ ፡ ሲታወቅ ፤ ለዚሁም ፡ ኑኀ ፡ ዘመን ፤ የታሪክ ፡ ስፋት ፤ ያልተለወጠ ፡ ይዞታ ፤ ከዚህም ፡ በላይ፡ ያልተቋረጠ ፡ ሐረገ ፡ ትውልደ ፡ መንግሥትና ፡ ዘወትር ፡ ኪዳኑን ፡ ፍቅሩን ፡ በማጽናት፡ አብሯት ፡ የሚኖረው ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወትር ፡ ምስክርነታቸውን ፡ ሲሰጡ፡ኢትዮጵያ ፡ በወፍ ፡ በዛፍ ፡ በዘንዶ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አራዊት ፡ በሰማይ ፡ ሰራዊትና ፡ በክፉ ፡ መናፍስት ፡ ታመልክ ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ ማውራት ፡ መድን ፡ የሌለው ፡ ወሬ ፡ ነው ።

ጸሐፊዎች ፡ ለዚሁ ፡ ሐሰተኛ ፡ ወሬ ፡ ምስክር ፡ የሚያደርጉት ፡ በደንጊያ ፡ በዕንጨት ፡ ወይም ፡ በአንዳንድ ፡ የገንዘብ ፡ ቍርጥራጮች ፡ ተገኘ ፡ የሚሉት ፡ ሥዕል ፡ ነው ። ይህ ፡ ዐይነት ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ዐዋቂዎች ፡ ሊሠራ ፡ የሚችል ፡ ነው ። በገንዘብ ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ምልክትም ፡ ላንዳንድ ፡ ልዩ ፡ መታሰቢያ ፡ እንጂ ፤ አምልኮትን ፡ ለማመልከት፡የሚደረግ ፡ አይደለም ። ይህንኑም ፡ በአጭሩ፡በጊዜው፡ በሚገኘው ፡ ገንዘብና ፡ በየሐውልቶች ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ አይተን፡ ልንረዳው ፡ እንችላለን ።

እንግዲህ ፡ አዲስ ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለዕለት ፡ ጕብኝት ፡ መጥቶ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በጠቀስናቸው ፡ ያሉትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ፡ምልክቶች፡አይቶ፡ ትርጓሜውን ፡ ባለማወቅ ፡ ወደ ፡ አምልኮት ፡ ቢለውጠውና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጣዖት ፡ ታመልካለች ፡ ብሎ ፡ ቢጽፍ ፡ እንቀበለው ፡ ይኾን ? አንቀበለውም ።

ረ) ሰብአ ፡ ሰገል ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ለመኾናቸው ፡ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ ይገንዩ ፡ ቅድሜሁ ፡ ኢትዮጵያ ፤ ነገሥተ ፡ ሳባ ፡ ወዐረብ ፡ ጋዳ ፡ ያመጽኡ ። መዝ ፡ ፸፪ ፡ ቍ ፡ ፲፩—፲፫ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፷ ፡ ቍ ፡ ፮ ። ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፤ ወያመጽኡ ፡ እምሳባ ፡ ወርቀ ፡ ወስኂነ ፤ ወይዜንዉ ፡ መድኀኒተ ፡ ዘእምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ተናገሩላቸው ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታቸው ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ለመንግሥቱ ፤ አባታቸው ፡ ካህኑ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ለክህነቱ ፡ ምሳሌዎች ፡ የኾኑለትን ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክርስቶስን ፡ ለማየት ፤ ለመንግሥቱ ፡ የሚገባ ፡ ወርቅን ፤ ለአምላክነቱ ፡ የሚገባ ፡ ዕጣንን ፤ ለዕለተ ፡ ሞቱ ፡ የሚኾን ፡ ከርቤን ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ አድርገው ፡ ለማቅረብ ፤ በረከተ ፡ ልደቱን ፡ ለመሳተፍ ፡ የተጠሩ ፡ የተቀጠሩ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሳባውያን ፡ ነገሥታት ፡ እንደ ፡ መኾናቸው ፡ መጠን ፡ የተወለደው ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ወዴት ፡ ነው ? ከምሥራቅ ፡ አፍሪቃ ፡ ኮከቡን ፡ አይተን ፡ ልንሰግድለት ፡ መጥተናል ፡ እያሉ ፡ ወደ፡ቤተ፡ ልሔም ፡ ደርሰው ፡ እንደ ፡ ታዘዙ ፡ አደረጉ ። ይህን ፡ ወርቅና ፡ ዕጣን ፡ ከርቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአዳም ፡ የሰጠው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከአዳም ፡ ለሴት ፤ ከሴት ፡ በልጅ ፡ ልጅ፡ተላልፎ፡ ለኖኅ ፤ ከኖኅ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ፤ ከመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ለአብርሃም ፤ ከአብርሃም ፡ በልጅ፡ ልጅ ፡ ተላልፎ ፡ ለዳዊት ፤ ከዳዊት ፡ ለሰሎሞን ፤ ከዚያም ፡ ለቀዳማዊ ፡ ምኒልክ፡ተላልፎ ፡ በሳባ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ሲኖር ፡ ኮከቡ ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ መልክተኞቹ ፡ ለክርስቶስ ፡ አቅርበውለታል ።



ይህንንም ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ሊቅ ፡ ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ከምሥራቅ ፡ እየመራ ፡ ያመጣቸው ፡ ኮከብ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ አድርሷቸው ፡ አንቺና ፡ ልጅሽ ፡ ባላችሁበት ፡ ዋሻ ፡ ላይ ፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ ኮከቡን ፡ አይተው ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ ዋሻው ፡ ገብተው ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡ ሰገዱለት ፤ ሣጥናቸውን ፡ ከፍተው ፡ ኮረጆቻቸውን ፡ ፈትተው ፡ እጅ ፡ መንሻውን ፡ ወርቅ ፡ ዕጣን ፡ ከርቤ ፡ አቀረቡለት ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ሕዝብኽ ፡ ኀጢአት ፡ ሰው ፡ የኾንኽ ፡ የሕዝብኽን ፡ ኀጢአት ፡ ለማስተስረይ ፡ ጸሎታቸውን ፡ መሥዋዕታቸውን ፡ ለመቀበል ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ የመጣኽ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ ካንተ ፡ ያገኘነውን ፡ ካንተ ፡ የተቀበልነውን ፡ ሀብት ፡ ለቅዱስ፡ስምኽ ፡ እጅ፡መንሻ፡ አድርገን ፡ አቅርበንልሃል ፡ አሉት ፡ ብሎ ፡ የረቀቀውን ፡ አኰልቶ ፡ መስክሯል ።

እንግዲህ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አይደሉም ፡ ድንገተኞች ፡ አረመኔዎች ፡ ናቸው ፡ የሚሉት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ ይዘው ፡ ነው ? በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ንግሥተ ፡ ሳባን ፡ ከሰብአ ፡ ሰገል ፤ ጕዞዋቸውን ፡ ከጕዞዋ ፤ ሥራቸውን ፡ ከሥራዋ ፡ አስማምቶ ፡ ተመልክቶ ፡ ታሪክን ፡ ለባለታሪኳ ፡ ( ኢትዮጵያ ) ፡ መመለስ ፡ ይጠቅማል ።

ሰ) ኢትዮጵያ ፡ በትንቢት ፡ ያጠናችውን ፡ የክርስቶስን ፡ ሃይማኖት ፡ በሙሉ ፡ ልቧ ፡ የተቀበለችና ፡ በጥምቀትም ፡ የፈጸመችው ፤ ሥጋዊ ፡ ዘውዱዋ ፡ የጸና ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፡ በአክሊለ ፡ መንግሥቷና ፡ በአክሊለ ፡ ክህነቷ ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለወዳጆቹ ፡ ያዘጋጀውን ፡ የክብር ፡ አክሊል ፡ ለመደረብ ፤ በመንፈስ ፡ ረድኤት ፡ ላይ ፡ መንፈስ ፡ ልደትን ፡ ለመቀበል ፡ የቻለችው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በሾመላት፡በሐዋርያው፡ በፊልጶስ ፡ እጅ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለነበረችው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንተኛዋ ፡ ነበረች ፤ እንዲያውም ፡ በትንቢት ፡ የደነደነች፡እንደ፡መኾኗ፡መጠን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ እንደ ፡ መሰከረላት ፡ መምህር ፡ ልትኾን ፡ በቻለች ፡ ነበር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይህን ፡ አልፈው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ክርስትና ፡ መሠረቱ ፡ ግብጽ ፡ ናት ፡ ማለታቸው ፡ ትክክለኛ ፡ ነውን ? አይደለም ! ምክንያቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ክርስትናን ፡ በተቀበለችበት ፡ ጊዜ ፤ እንኳን ፡ ግብጽ ፡ ክርስትና ፡ ልትቀበል ፡ አስተማሪዎቹዋ ፡ ዐቢያን ፡ ሐዋርያት ፡ ማርቆስና ፡ ጴጥሮስም ፡ ገና ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ያልወጡ፡በመኾናቸው ፡ ነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ ፡ ይህን ፡ መቅድም ፡ ባጭር ፡ ስጠቀልልና ፡ ስፈጽም ፤ እግዚአብሔር ፡ ለፍጡራኑ ፡ ሳያስቡት ፡ የሚያሻቸውን ፡ መስጠት ፡ ልማዱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ኹሉንም ፡ በመውደድ ፡ ፍጹም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ለድኻው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ዐስቦ ፡ በኀቡእ ፡ እንዲሠራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በግልጥ ፡ እንዲከፍለው ፡ የተናገረውን ፡ ተከትለው ፡ ለሚያምን ፡ ኹሉ ፡ ይቻላል ፡ በሚለው ፡ ቃል ፡ ዘወትር ፡ የሚሠሩበት ፡ በሥራ ፡ የሚያስተምሩበት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በሰፊው ፡ ልግስናቸውና ፡ በታላቅ ፡ ቸርነታቸው ፡ ስለ ፡ አሳተሙልኝ ፡ ለሕዝብ ፡ ማቅረቤን ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ኹሉ ፡ እየገለጥሁ፡ እኔ ፡ በበኩሌ ፡ እግዚኦ ፡ አምላከ ፡ ኀያላን፡ ስምዐኒ ፡ ጸሎትየ ። ወአጽምዐኒ ፡ አምላኩ ፡ ለያዕቆብ ። ወርእየኒ ፡ እግዚኦ ፡ ተአምኖትየ ። ወነጽር ፡ ኀበ ፡ ገጸ ፡ መሢሕከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ እንደምለው ፡ እናንተም ፡ አምላከ ፡ ኀያላን ፡ ተመየጥሶ ። ሐውጽ ፡ እምሰማይ ፡ ወርኢ ። ወተሣሀላ ፡ ለዛ ፡ ዐጸደ ፡ ወይን ፡ ( ኢትዮጵያ ) ። አስተናሥአ ፡ ወአጽንዓ ፡ ዘተከለት ፡ የማንከ ። በወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ « ኃይለ ፡ ሥላሴ » ፡ ዘአጽናዕከ ፡ ለከ ። ለይኩን ፡ እዴከ ፡ ላዕለ ፡ ብእሲ ፡ (አም፦ ፡ ሥላሴ) ፡ የማንከ ፡ በወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ (ኃይለ ፡ ሥላሴ) ፡ ዘአጽናዕከ፡ ለከ ። እያላችሁ ፡ እንድትጸልዩላቸው ፡ እለምናችኋለሁ ።

እንዲሁም ፡ በአባትነታቸው ፡ እየጠበቁ ፡ እየረዱ ፡ ላሳደጉኝና ፡ ማንኛውንም ፡ የዕውቀት ፡ ፍሬ ፡ ለማግኘት ፡ በቡራኬያቸውና ፡ በሀብታቸው ፡ በልግስናቸው ፡ ለደገፉኝ ፡ ለብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ ፓትረያርክ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሐዋርያዊት ፡ ርስትን ፡ እንዲያድልልኝ ፡ ፈጣሪዬን ፡ እለምነዋለሁ ።



የዲማ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

በጐጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በስተ ፡ ምሥራቅ ፡ የሚገኘው ፡ የአራቱ ፡ ጉባኤያት ፡ ምንጭ ፡ የተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ መሠረት ፡ ዲማ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፤ ፩ኛ ፤ በግራኝ ፤ ፪ኛ ፤ በሱስንዮስ ፡ ዘመን ፡ የነበረውን ፡ ሃይማኖታዊ ፡ ትግል ፡ ያሸነፈና ፡ በዐምስቱ ፡ የጠላት ፡ ወረራ ፡ ዘመን ፡ ለፈጣሪውና ፡ ለሀገሩ ፡ ፍቅር ፡ ለመሪው ፡ ክብር ፡ በተቀዳሚነት ፡ የጀግኖች ፡ ማኅበር ፡ አቋቁሞ ፡ የተከራከረ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያውያን ፡ ሆይ ፡ አንደኛ ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የኢትዮጵያ ፡ እምነት ፡ በሦስቱ ፡ ሕግጋት ፡ ተብሏል ። ምክንያቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ በወፍ ፡ በዛፍ ፡ በዘንዶ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አራዊት ፡ በሰማይ ፡ ሰራዊትና ፡ በክፉ ፡ መናፍስት ፡ ታመልክ ፡ ነበረ ፡ የሚለውን፡ ታሪክ ፡ ሽሮ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ በሕገ ፡ ወንጌል ፡ ማመኗንና ፡ የጣዖት ፡ አምልኮት ፡ ሳትቀላቅል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ብቻ ፡ ስታመልክ ፡ መኖሯን ፡ የሚገልጥ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ። በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ መሠረታዊ ፡ ታሪክ ፡ ተጣምሮ ፡ ይገኝበታል ።

ኹለተኛ ፤ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ተዘርቶ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ በቅሎ ፡ በሕገ ፡ ወንጌል ፡ ፍሬ ፡ የኾነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንጌላዊ ፡ ምስጢረ ፡ ሃይማኖት ፡ በሰባት ፡ ዐዕማድ ፡ ተከፍሎ ፡ ተገልጦበታል ።

ሦስተኛ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖትን ፡ መሠረት ፡ አድርጋ ፡ ስትሠራበት ፡ የኖረችው ፡ ታሪኳን ፡ ነጻነቷን ፡ ጠብቆ ፡ ያኖረላት ፡ ፍሬ ፡ ምግባሯ ፡ በአጭር ፡ ተዘርዝሮበታል ።

እኔ ፡ ሳዘጋጀው ፡ ይበቃል ፡ በማለት ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ መኑ ፡ ይትዐደዎ ፡ ለወልድ ፡ እጓየ ፡ እስመ ፡ ልዑል ፡ መዝራዕተ ፡ የማኑ ፤ (ሥልጣኑ ፡ ጽኑ ፡ ነውና ፡ ልጅ ፡ ወንድሜን ፡ ማን ፡ ይቃወመዋል)፡ ብላ ፡ እንደ ፡ ተናገረችው፡ከኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ኀይለ ፡ ቃልና ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ እስካሁን ፡ አልታጣም ። ቢኾንም ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በጀኔብ ፡ ጉባኤ ፡ እንደ ፡ ተናገሩት ፡ ያለ ፡ ደካሞችን ፡ አበርትቶ ፤ ኀያላኑን ፡ አዋርዶ ፤ ያዋቂዎችን፡ዕውቀት ፡ የመካሪዎችን ፡ ብልኀት ፡ ከንቱ ፡ አድርጎ ፤ እግዚአብሔርን ፡ አስመስግኖ ፤ ሀገርን ፡ ወገንን ፡ ደግፎ ፤ ያለፈውን ፡ አጽንቶ ፤ የሚመጣውን ፡ መሥርቶ ፡ የተገኘ ፡ ኀያል ፡ ቃል ፡ የለም ። ይህን ፡ ላስታውሳችሁ ፡ የምፈልግበት ፡ ምክንያት ፡ የጃንሆይ ፡ ድካም ፡ ካራት ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የኾነውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነጻነት ፡ ጠብቆ ፡ ለማስጠበቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ቃላቸውን ፡ ተቀብለን ፤ መሪነታቸውን ፡ ተከትለን ፡ ብንሠራ ፡ ያደረባቸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸጋውን ፡ ስለሚሰጠንና ፡ ሥራውንም ፡ ስለሚያከናውንልን ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ፡ ሳበረክታችሁ ፡ ይህን ፡ እላይ ፡ የጠቀስኩላችሁን ፡ ተስፋ ፡ ተደግፋችሁ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ሙሉነት ፡ እንድታስቡና ፡ እኔ ፡ ያሳነስኩትን ፡ መልታችሁ ፡ አስተካክላችሁ ፡ መጻሕፍትን ፡ እንድታዘጋጁ ፡ ስል ፡ ነው ።

እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ በሥራ ፡ ይርዳን ።

ይህችን ፡ መጽሐፍ ፡ እንኩ ፡ ብሏዋት ፡ በአፋችሁ ፡ እንደ ፡ ማር ፡ ትኹንላችሁ ፤ ኾዳችሁን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ታቃጥላችሁ ፡ እንደ ፡ ኮሶ ፡ ትምረራችሁ ። ራዕ ፡ ዮሐ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፱ ።

www.ethiopianorthodox.org

## የኢትዮጵያ ፡ እምነት ፡ በሦስቱ ፡ ሕግጋት ፡፡

፩፤ ኢትዮጵያ ፡ በሦስቱ ፡ ሕግጋት ፡ ማለት ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ በሕገ፡ ወንጌል ፤ በሦስቱም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡ ያላቋረጠች ፡ አገር ፡ ናት ፤ ስለ ዚህም ፡ ሰው ፡ በአርኣያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተፈጥሮ ፡ በአርአያ ፡ እግዚአብሔር ፡ በራሪውንም ፡ ኾነ ፡ ተሽከርካሪውን ፡ ሊገዛ ፡ ከፈጣሪው ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የተቀበለውን ፡ የገዥነት ፡ ዘንግ ፡ ሰብሮ ፡ በመጣሉ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ የሞት ፡ ተገዥ ፡ ቢኾን ፡ በጕልበት ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ ብቻ ፡ የበላይነትን ፡ ለመውሰድ ፡ ይቀዳደምበት ፡ ከነበረው፡ ከመጀመሪያው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ኢትዮጵያ ፤ የገዥነት ፡ ዘንግ ፡ ከእጇዋ ፡ ሳይ ወድቅ ፡ ልዕልና ፡ መንግሥትን ፡ የተጐናጸፈው ፡ የጌትነት ፡ ዘውድ ፡ ከራሱዋ ፡ ሳይወልቅ ፤ ብዙ ፡ ሺሕ ፡ ዓመታት ፡ አሳልፋ ፡ እነሆ ፡ ዛሬም ፡ አለች ፡፡ ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፮—፴ ፡፡ መዝ ፡ ፰ ፡ ቍ ፡ ፭—፱ ፡፡

፪ ፤ ይህንንም ፡ ክብርና ፡ ጌትነት ፡ ሊያስገኝላት ፡ የቻለው ፡ በባሕርዩ፡ሞት ፡ በመ ንግሥቱ ፡ ኅልፈት ፡ የሌለበት ፡ የማይለወጥ ፡ ዘለዓለም ፡ ኗሪ ፤ የኾነውን ፡ የሥልጣን ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመከተሏ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡፡

፫ ፤ ጌታውን ፡ ሲከተል ፡ የዋለ ፡ አሽከር ፡ ጕልበት ፡ ገበታውን ፡ ( ጕርሻውን ) ፡ ለማግኘት ፡ እንዲችል ፤ ኢትዮጵያም ፡ የጌታዋን ፡ ፍለጋ ፡ ስትከተል ፡ እንደ ፡ መኖሯ ፡ መጠን ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥትን ፡ ከጠላው ፡ ሰው ፡ ነሥቶ ፡ ለወደደው ፡ በሚሰጥበት ፡ ሥልጣኑ ፡ የብዙዎችን ፡ አህጉር ፡ መብትና ፡ መንግሥት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲገለባብጥና ፡ ሲለዋውጥ ፡ ከላይ ፡ እንደ፡ ጠቀስነው ፡ በ፫ቱ ፡ ሕግጋት ፡ አሰረ ፡ ሃይማኖትን ፡ ኹል ፡ ጊዜ፡ የምትከተል ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመከተሏን ፡ ዋጋ ፡ እንድታገኝ፡ስለ፡ፈቀደ ፤ በጽላሎተ ፡ ረድኤቱ ፡ ውስጥ ፡ የተመሠረተውን ፡ ዘመኑም ፡ ሰማይ ፡ ጸንቶ ፡ የኖረውን ፡ ያኽል ፡ ኾኖ ፡ የሚገመተውን ፡ ሰፊ ፡ መንግሥት ፡ አዘጋጀላት ፤ ስለዚህም ፡ ምስጋና ፡ ለእርሱ ፡ ይኹን ፡ መዝ ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፭ ፡ ፱ ፡፡

፬ ፤ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ በዓለም ፡ ያሉት ፡ አፈ ፡ ብልጦች ፡ እንደ ፡ መብዛታቸው ፡ መጠን ፤ የኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ በሌላው ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ የተዘረጋና ፡ ሰፊ ፡ መንግሥ ቷም ፡ በዚያው ፡ በኩል ፡ የተመሠረተ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፤ እኛ ፡ የዛሬዎቹ ፡ ወጣቶች ፡ ኢት ዮጵያውያን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ክብር ፡ ለመቀነስ ፡ የምናደርገውን ፡ ድካም ፤ ሌሎችም ፡ ሕዝቦች ፡ ስለ ፡ ሀገራቸው ፡ እድገት ፡ ሰፊ ፡ ታሪክ ፡ በመጻፍ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ጥረት ፡ በማወዳደር ፡ ስንመለከተው ፡ ለጽሑፋቸው ፡ ማስደገፊያ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የቆመችበትን ፡ የመሰለ ፡ የታሪክ ፡ መሰላል ፡ ቢያገኙ ፡ ኖሮ ፡ እንኳን ፡ ሰውን ፡ የዕውቀት ፡ ኹሉ ፡ ባለ ቤት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናስረዳኽ ፡ ለማለት ፡ በሞከሩ ፡ ነበር ፡፡

፭፤ ይህንንም ፡ ለመረዳት ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ በብዙ ፡ ሚሊ ያርድ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ዓመታት ፡ አልፈዋል ፡ የሚለውንና ፡ ከፍጥረትም ፡ ተቀዳሚ ፡ የኾ

www.ethiopianorthodox.org

ነች ፡ የመጀመሪያዪቱ ፡ ፍጥረት ፡ ሕይወት ፡ ሳይኖራት ፡ ራሱዋን ፡ በራሱዋ ፡ ለማደስና፡ ለማንቀሳቀስ ፡ ለመፍጠርም ፡ እንደ ፡ ቻለች ፡ ከገደልም ፡ ተፈርፍራ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ከወደቀች ፡ በኋላ ፡ እኩሌታዋ ፡ ዕንጨትን ፡ ወይም ፡ ዛፍን ፡ መኾንን ፡ ስትመርጥ ፤ እኩሌታዋ ፡ ደግሞ ፡ በባሕር ፡ ዘቅጣ ፡ ቈይታ ፡ ግዝፈቱ ፡ ብዙ ፡ ኪሎ ፡ ቁመቱም ፡ ብዙ ፡ ሜትር ፡ የሚገመት ፡ አካል ፡ ያላቸው ፡ ታላላቅ ፡ ፍጥረታት ፡ ለመኾን ፡ እንደ ፡ መረጠች ፡ የሚያትተውን ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ (ሳይንስ) ፡ ምርመራ ፡ ጽሑፍ ፡ ቢመለከትና ፡ ቢመረምር ፡ እኔ ፡ የተናገርኩት ፡ ከዚህ ፡ ሐሳብ ፡ ቅርብ ፡ ወይም ፡ ሩቅ ፡ መኾኑን ፡ ሊያውቀው ፡ ይችላል ።

፯ ፤ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እምነት ፡ ታሪክ ፡ የጻፉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የአምላክ ፡ አገር ፡ ተብላ ፡ የምትጠራ ፡ መኾኑዋን ፤ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ እንዳልነበራት ፡ እያመኑ ፤ ደግሞ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ከመቀበሏ ፡ በፊት ፤ ባዕዳን ፡ አማልክትን ፡ ታመልክ ፡ ነበር ፡ እያሉ ፡ በማተታቸው ፡ ሊወሐዱ፡ የማይችሉ ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ዘርና ፡ መልክ ፡ ያላቸው ፡ ዐሳቦች፡ በጽሑፋቸው ፡ ውስጥ፡ አስቀምጠዋል ፤ ማለት ፡ እምነትና፡ ክሕደት ፡ አውርተዋል ። መዝ ፡ ፷፩ ፡ ቍ ፡ ፲፩ ፡ መ ፡ ፶፭ ፡ ቍ ፡ ፫ ።

፰ ፤ እንግዲህ ፡ እነዚህ ፡ ኹለቱ ፡ ተከራካሪዎች ፡ እምነትና ፡ ክሕደት ፡ በቆሙበት ፡ የጽሑፍ ፡ ዐደባባይ ፡ ላይ ፡ ሕሊናችንን ፡ ዳኛ ፡ አድርገን ፡ ፍርድ ፡ ብንጠይቀው ፡ ወይም ፡ ስሚን ፡ ከግብሯ ፡ ነሥታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ብቻ ፡ በማምለኳ ፡ የአምላክ ፡ አገር ፡ ተብላ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ እስራኤል ፤ አባታቸው ፡ አብርሃም ፡ ከአባቶቹ ፡ (ከለዳውያን) ፡ አገርና ፡ አምልኮት ፡ ወጥቶ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ ተከተለና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከአብራምነትም ፡ ስሙ ፡ ወደ ፡ አብርሃምነት ፡ ከተለወጠ፡ በኋላ ፡ ባተረፈላቸው ፡ የአምልኮት ፡ ቅርስ ፡ ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተባሉ ፡ ለኢትዮጵያም ፡ አምልኮትን ፡ ያተረፈላትና ፡ ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሰኛት ፡ ሰው ፡ እንዳለ ፡ ፍርዱን ፡ ሊያጣራልን ፡ ይችላል ።

፱ ፤ ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ መባል ፡ አብሯት ፡ የኖረ ፡ ከኾነ ፡ ግን ፡ ታሪኳን ፡ አጣርተን ፡ መርምረን ፡ እንናገር ፡ እንጂ ፤ ነውር ፡ በሌለበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ለንጹሑ ፡ ሙሽራ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዕጮኛ ፡ በኾነችው ፡ በታላቂቱ ፡ ሙሽራ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላይ ፤ ከሌሎች ፡ ጎረምሶች ፡ ጋራ ፡ ታመነዝር ፡ ነበር ፤ ማለት ፡ ባዕዳን ፡ አማልክትን ፡ ትከተል ፡ ነበር ፡ የሚለውን ፡ የሐሜት ፡ ወሬ ፡ እንሰርዘው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በሦስቱ ፡ ሕግጋት ፡ እንዴት ፡ ነበረች ?
፪ ፤ ሦስቱ ፡ ሕግጋት ፡ ማን ፡ ማን ፡ ናቸው ?
፫ ፤ ሰው ፡ በማን ፡ አርአያ ፡ ተፈጠረ ? ምንስ ፡ ተቀበለ ? የተቀበለውንስ ፡ ከማን፡ አገኘው ?



፬ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዘመን ፡ እንዴት ፡ ነበረች ፡ ? ዛሬስ ፡ እንዴት ፡ ናት ?
፭ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ክብር ፡ ከማን ? በምን ፡ ተገኘ ?
፮ ፤ አሽከር ፡ ከጌታው ፡ ምን ፡ ያገኛል ?
፯ ፤ እግዚአብሔር ፡ መንግሥትን ፡ ከማን ፡ ለማን ፡ ይሰጣል ?
፰ ፤ እግዚአብሔር ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሌሎች ፡ ያደረገው ፡ የሥራ ፡ ልዩነት ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፱ ፤ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዕድል ፡ ቢያገኙ ፡ ኖሮ ፡ ምን ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ?
፲ ፤ ስለ ፡ ዓለም ፡ የተፈጥሮ ፡ ዘመንና ፡ ስለ ፡ መጀመሪያዪቱ ፡ ፍጥረት ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ምርመራ ፡ እንዴት ፡ ይነገራል ?
፲፩ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እምነት ፡ የጻፉ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ ብለዋል ?
፲፪ ፤ በጽሑፋቸውስ ፡ ስንት ፡ ዐይነት ፡ ዐሳቦች ፡ ይገኛሉ ?
፲፫ ፤ ስለ ፡ ጽሑፎች ፡ ሕሊናችንን ፡ ብንጠይቀው ፡ ምን ፡ ይመልስልናል ?
፲፬ ፤ አብርሃም ፡ ምንን ፡ ተወ ? ማንንስ ፡ ተከተለ ?
፲፭ ፤ አብርሃም ፡ ፊት ፡ ማን ፡ ይባል ፡ ነበር ? በኋላስ ፡ ማን ፡ ተባለ ?
፲፮ ፤ እስራኤል ፡ ከአብርሃም ፡ ምን ፡ አተረፉ ? በሱስ ፡ ምን ፡ ተባሉ ?
፲፯ ፤ በኢትዮጵያስ ፡ እንደ ፡ አብርሃም ፡ ያለ ፡ አውራሽ ፡ ነበር ፡ ወይ ?
፲፰ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ልንናገረው ፡ የማይገባን ፡ ምን ፡ ዐይነቱ ፡ ነው ?
፲፱ ፤ ልናደርገውስ ፡ የሚገባን ፡ ምድን ፡ ነው ?

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ኢትዮጵያ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ።

፩ ፤ ሕገ ፡ ልቡና ፤ ሕገ ፡ ልቡና ፡ ለሰው ፡ በጥንተ ፡ ተፈጥሮ ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የተሰጠው ፡ የመጀመሪያ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

፪ ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ ብርዕ ፡ መቅረጥ ፡ ቀለም ፡ መበጥበጥ ፡ ብራና ፡ መድመጥ ፡ በጠቅላላው ፡ የጽሕፈት ፡ መሣሪያዎችን ፡ የማይሻ ፡ ነው ።

፫ ፤ ሕግነቱም ፡ በመላእክት ፡ ዘንድ ፡ የተጠና ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከተፈጥሮዋቸው ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ አልተለወጠም ።

፬ ፤ ሰውም ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ሃይማኖቱን ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ዐውቆና ፡ ጠብቆ ፡ ፈጣሪውን ፡ ፈርቶ ፡ አክብሮ ፡ ሊኖር ፡ እንጂ ፤ በደብተርና ፡ በእርሳስ ፡ ሊመራ ፡ አልተፈጠረም ፡ ነበር ። ሄኖክ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፷፪ ።

፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፡ በተፈጥሮ ፡ የተሰጠውን ፡ ዕድል ፡ ዐውቆ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ክብሩን ፡ ጠብቆ ፡ መኖር ፡ ቢሳነውና ፡ ጠባቂ ፡ እንደሌለው ፡ በግ ፡ በሞት ፡ መን

www.ethiopianorthodox.org

ገዶች ፡ ላይ ፡ ሲቅበዘበዝ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢያየው ፡ በቀለምና ፡ በወረቀት ፤ የተ
ጻፈ ፡ ሕግን ፡ ረዳት ፡ አድርጎ ፡ ሰጠው ። መዝ ፡ ፹፱ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፰ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ፡

፮ ፤ ሕገ ፡ ልቡና ፤ በሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ የተቃረበ ፡ ግምት
ባለው ፡ ዘመን ፡ ሠርቶዋል ። ይኸውም ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡ ነው ፡

፯) ምንም ፡ እንኳን ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፤ የበደሉትንም ፡ ያልበደሉትንም ፡ ሞት
አንድ ፡ አድርጎ ፡ ቢገዛቸው ፤ ሕገ ፡ ልቡናን ፡ ጠብቀው ፡ በተገኙ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የእግ
ዚአብሔር ፡ ብርሃን ፡ ረድኤቱ ፡ አልጠፋም ፡ ሮሜ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ።

፰ ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሪነት ፡ ዘመን ፤ ከላይ ፡ እንደ ፡ ጠቀስነው ፡ ኹሉ ፡ ሰው ፡ ከእግ
ዚአብሔር ፡ የተሰጠውን ፡ ሕግ ፡ ጥሶ ፡ በተፈረደበት ፡ ፍርድ ፡ መጠን ፡ ዕውርነቱ ፡ እ
ከበደ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ለማግኘት ፡ የተቅበዘበዘባቸው ፡ የሞት ፡ መን
ዶች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።

፱ ፤ እነዚህም ፡ በሰማይ ፡ ሰራዊት ፤ በፀሐይ ፡ በጨረቃ ፡ በኮከብ ፡ በሰው ፡ በአ
ዕዋፍ ፡ በእንስሳት ፡ በአራዊት ፡ ምሳሌ ፡ የተቀረጡና ፡ የተሠሩ ፡ ጣዖታት ፡ ናቸው ።

፲ ፤ እነዚህ ፡ የሞት ፡ መንገዶች ፤ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ መምጣት ፡ ድረስ ፡ በስፋት ፡
ላይ ፡ ስፋት ፡ እየጨመሩ ፡ መኖራቸውን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስና ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍት ፡
አስፋፍተው ፡ ስለሚመሰክሩ ፤ ብዙ ፡ ማተት ፡ አያሻም ።

፲፩ ፤ ስለዚህም ፡ አሞን ፡ ቤል ፡ ዳጎን ፡ አጵሎን ፡ ሞሎክ ፡ የተባሉትንና ፡ እነሰ
ንም ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሰፋፊ ፡ የሞት ፡ መንገዶች ፤ ተከትለው ፡ የሄዱ ፡ ኹሉ ፡ ብዙዎች ፡
ፈተናዎች ፡ ሲደርሱባቸው ፤ ረዳት ፡ ባለማግኘታቸው ፡ በኑሮዋቸው ፡ መለዋወጥ ፡ በመ
ንግሥታቸው ፡ መገለባበጥ ፡ ምክንያት ፡ ዛሬ ፡ ካሉት ፡ የሌሉት ፡ ይበዛሉ ።

፲፪ ፤ ሸማኔ ፡ በቍጢቱ ፤ ጸሓፊ ፡ በጽሕፈቱ ፤ ደጓሽ ፡ በድጕሰቱ ፤ ሠሪ ፡ ኹሉ ፡
በሥራው ፡ እንዲታወቅ ፤ የማይታይ ፡ የማይመረመር ፡ እግዚአብሔር ፡ በፍጥረቱ ፤ ለፍ
ጥረቱ ፡ ስለሚገለጽና ፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ በውስጣቸውም ፡ የሚገኙት ፡ ፍጥረታት ፡
ኹሉ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ አምላክነት ፡ ለፈላጊው ፡ ማስረዳት ፡ ስለሚችሉ ፤ ሰፊውን ፡
መንገድ ፡ ትታ ፡ ወደ ፡ ጠባቡ ፡ መንገድ ፡ ገብታ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ። በአእምሮ፡
ጠባይዕ ፡ መምህርነት ፤ በሕገ ፡ ልቡና ፡ መሪነት ፤ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ምስክርነት ፡ ፈጣሪ
ዋን ፡ ዐውቃ ፡ የተከተለችና ፡ እጆቿዋን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዘረጋች ፡ ኢትዮጵያ ፡
ግን ፤ የወለደውን ፡ የማይክድ ፡ አባቷ ፡ እግዚአብሔር ፤ ልጅነቷን ፡ ዐውቆ ፡ አጽድቆ ፡
ስለ ፡ አቀፋትና ፡ ስለ ፡ ደገፋት ፤ የሞትን ፡ መንገድ ፡ የተከተሉ ፡ ዘመናውያን ፡ ጓደኞቿ፡
ከወደቁበት ፡ ፈተና ፡ አልፋ ፡ በዘር ፡ በሃይማኖት ፡ በቋንቋ ፡ ልዩነት ፡ የሌለበትን ፡
ክብር ፡ ተጐናጽፋ ፤ በኑሮዋ ፡ መለዋወጥ ፡ በመንግሥቷ ፡ መገለባበጥ ፡ ሳይደርስባት ፡
ከብዙ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ፡እመቤትነቷ ፡ ሳይሻር፡ክብሯ ፡ ሳይደፈር ፤ እነሆ ፡ እስከ ፡
ዛሬ ፡ አለች ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፷፰ ፡ ቍ ፡ ፴፩ ።



## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ለሰው ፡ የተሰጠ ፡ የመጀመሪያ ፡ ሕግ ፡ የትኛው ፡ ነው ?
፪ ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ የጽሕፈት ፡ መሣሪያዎችን ፡ ይሻል ፡ ወይ ?
፫ ፤ በመላእክት ፡ ዘንድ ፡ ሕግነቱ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፬ ፤ ሰው ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ በደብተርና ፡ በእርሳስ ፡ ሊመራ ፡ ተፈጥሮ ፡ ነበር ፡ ወይ ?
፭ ፤ ይህ ፡ ሕግ ፤ ስንት ፡ ዘመን ፡ ሠርቶዋል ? የዘመኑን ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ ግለጽ ።
፮ ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ዘመን ፡ የበደሉና ፡ ያልበደሉ ፡ እንዴት ፡ ነበሩ ?
፯ ፤ ሰው ፡ ሕግን ፡ በመጣሱ ፡ ምን ፡ ደረሰበት ?
፰ ፤ የሞት ፡ መንገዶች ፡ የትኞዎቹ ፡ ናቸው ? እስከ ፡ መቼስ ፡ ነበሩ ?
፱ ፤ አሞን ፡ ሞሎክ ፡ ቤል ፡ ዳጎን ፡ የተባሉትንና ፡ ሌሎችንም ፡ የተከተሉ ፡ ምን ፡ ኾኑ ?
፲ ፤ እግዚአብሔር ፡ በምን ፡ ለማን ፡ ይገለጻል ? ምሳሌዎችን ፡ ስጥ ።
፲፩ ፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ በውስጣቸውም ፡ የሚገኘው ፡ ፍጥረት ፡ ለምን ፡ ይጠቅማል ?
፲፪ ፤ ኢትዮጵያስ ፤ የቱን ፡ ትታ ፡ የቱን ፡ ተከተለች ?
፲፫ ፤ በዚህስ ፡ ምን ፡ ደሰረባት ? ምን ፡ ደረሰላት ?
፲፬ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ከጥንት ፡ የዘር ፡ የሃይማኖት ፡ የቋንቋ ፡ ልዩነት ፡ ነበረን ?
፲፭ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ክብሯን ፡ ያጣችበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ፡ ወይ ?

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ኢትዮጵያና ፡ ዜናዋ ።

፩ ፤ ከሕገ ፡ ኦሪት ፡ በፊት ፤ ኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ነበረችበት ፡ እምነት ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ በጻፉት ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እምነትና ፡ ክሕደት ፡ ይወራሉ ።

፪ ፤ ባንድ ፡ በኩል ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገር ፡ መባሏ ፡ ሲታመን ፤ ባንድ ፡ በኩል፡ ደግሞ ፡ ፍጡራንን ፡ ታመልክ ፡ ነበር ፡ የሚባለው ፡ ወሬ ፡ ከታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ምንጭነት ፡ ሲፈልቅ ፡ እውነተኛ ፡ ስሟን ፡ የሚሰርዝ ፡ ምክንያት ፡ ተፈጥሯል ።

፫ ፤ በውነቱ ፡ ባለፈው ፡ እንደ ፡ አስረዳነው ፡ ኹሉ ፡ አስተዋይ ፡ ሰው፡ሕሊናውን ፡ ዳኛ ፡ አድርጎ ፤ በኹለት ፡ ዐይነት ፡ መልክ ፡ የሰፈረውን ፡ ጽሑፍ ፡ ቢመረምረው ፡ አንዱን ፡ ለመምረጥ ፡ እንደሚችል ፡ እርግጥ ፡ ነው ።

፬ ፤ እንዲህም ፡ ማለት ፡ ፀሐይን ፡ ጨረቃን ፡ ከዋክብትን ፡ እንስሳትን ፡ አራዊትን ፡ ክፉ ፡ መናፍስትን ፡ ታመልክ ፡ ነበረ ፡ በማለት ፤ የተጻፈውንና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የአምላክ ፡ ሀገር ፡ ተብላ ፡ ትጠራ ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ የተጻፈውን ፡ ቢያመዛዝን ፡ ሊደርስበት ፡ ይችላል ።

www.ethiopianorthodox.org

፭ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በአነስተኛው ፡ አእምሮዬ ፡ ያዘጋጀኹትን ፡ ትንሽ ፡ ጽሑፍ ፡ ሰፊ ፡ አእምሮና ፡ ታላቅ ፡ አንጐል ፡ ላላቸው ፡ ሰዎች ፡ ሳበረክት ፤ ያጠበብኩትን ፡ እንዲያሰፉልኝ ፤ የጠመመውን ፡ እንዲያቀኑልኝ ፡ የጐደለውን ፡ እንዲሞሉልኝ ፤ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

፮ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ፈጣሪን ፡ እንጂ ፤ ከቶ ፡ ፍጡርን ፡ ያመለከችበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ። ነገር ፡ ግን ፤ የጽሑፍ ፡ ውሳኔ ፡ በሌለው ፡ ሕግ ፤ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ እየተመራመረች ፡ ፈጣሪዋን ፡ መፈለጓና ፡ መከተሏ ፡ እርግጥ ፡ ነው ።

፯ ፤ እንግዲህ ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ እየተመሩና ፡ እየተመራመሩ ፤ ፈጣሪን ፡ መፈለግ ፤ ጣዖት ፡ ማምለክ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ጣዖት ፡ እንደ ፡ ማምለክ ፡ ይቈጠራል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ሰማዮች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋና ፡ ይናገራሉ ፤ ሰማዮች ፡ የእጆቹን ፡ ሥራ ፡ ይመሰክራሉ ፤ ቀን ፡ ለቀን ፡ ወሬ ፡ ታወራለች ፤ ሌሊትም ፡ ለሌሊት፡ጥበብን ፡ ትናገራለች ፤ ከቃላቸው ፡ ያልተሰማ ፡ ነገር ፡ የለም ፤ ነገራቸው፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ወጣ ፤ ወሬያቸውም ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ዳርቻ ፡ ደረሰ ፤ የማይታይ ፡ የማይመረመር ፡ እግዚአብሔር ፡ በፍጥረቱ ፡ ለፍጥረቱ ፡ ይታወቃል ፡ ያለውን ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፤ በመጽሐፍ፡ ቅዱስ ፡ አንብቦ ፡ ይረዳ ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳ ። መዝ ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፩—፱

፰ ፤ የሰው ፡ ምስክርነት ፡ በዓለም ፡ የተለመደ ፡ ነው ፤ ከሰው ፡ ምስክርነትም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስክርነት ፡ እንዲበልጥ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ሲያስረዳ ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ እየተመሩና ፡ እየተመራመሩ ፡ ፈጣሪን ፡ መሻት ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚያሳማት፡ባለመኾኑ ፡ ከማይጠቅም ፡ ማንጐራጐር ፡ እንራቅ ፤ አንደበታችንንም ፡ ከሐሜት ፡ እንጠብቅ ።

፱ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ በነበረችበት ፡ ጊዜ ፡ ፈጣሪዋን ፡ ለመከተል ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ያደረገችው ፡ ምርመራ ፡ በጊዜው ፡ ካስገኘላት ፡ ጥቅም ፡ ሌላ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ ዚህ ፡ ዓለም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤ በረከቱ ፡ ልደቱን ፡ ለመሳተፍ ፡ ብርሃነ ፡ ልደቱን ፡ ለማየት ፡ ስላበቃት ፡ ባለተስፋዬቱ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያላገኘችውን ፡ ዕድል ፡ በወሰደች ፡ ጊዜ ፡ ሃይማኖቷ ፡ በግልጽ ፡ ተመስክሯል ፤ የምርመራዋም ፡ ውጤት ፡ በቂ ፡ ግምት ፡ አግኝቷል ። ማቴ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፩—፲፪ ።

፲ ፤ እንግዲህ ፡ ለፍጡራን ፡ ያልተንበረከከች ፤ የፍጡራንን ፡ ስም ፡ በአምልኮት፡ ያልጠራች ፡ ስለ ፡ ኾነች ፤ ሐሜቱን ፡ ትተን ፡ የአምላክ ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ መኾኗን ፡ እንወቅላት ።

፲፩ ፤ ስለዚህም ፡ የሚከተሉትን ፡ ማስረጃዎች ፡ እንመልከት ።

፲፪ ፤ ፩ኛ ፤ ታላቁ ፡ አባት ፡ አብርሃም ፡ የፈለገውን ፡ በረከት ፡ ከነገዱዋ ፡ ተወልዶ፡ የወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ ከኾነው ፡ ከመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ለማግኘት ፡ የቻለው ፤ ኢትዮጵያ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ፈጣሪዋን ፡ ስትከተል ፡ በተሰጣት ፡ የዕድል ፡ ምርጫ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፡ ፲፰ና ፡ ፲፱ ።

፲፫ ፤ ፪ኛ ፤ ንግሥት ፡ ሳባና ፡ ሰሎሞን ፡ በያሉበት ፡ መንግሥትን ፡ ከመውረሳቸው ፡ በፊት ፡ ለእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ የአጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ ኾኖ ፡ የተነሣው ፡ ንጉሥ ፡ እስራኤል ፡ ዳዊት ፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ከነመምህራኖቿ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተቀ



ብላ ፤ የሰጣትን ፡ ክብር ፡ አቃላ ፤ ያደረገላትን ፡ ረድኤት ፡ ትታ ፤ የሠራላትን ፡ ውለታ ፡ ዘንግታ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ መጽናት ፡ ተስኗት ፡ ስትርገደገድ ፤ በአፍም ፡ በመጣፍም፡ ያጠናችውን ፡ ፈጣሪዋን ፡ ትታ ፤ በሞአብ ፡ በዐሞን ፡ በከንዓን ፡ ጣዖታት ፡ ስታመነዝር ፡ ባየበት ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ እንኳን ፡ መምህር ፤ የቀለምና ፡ የወረቀት ፡ ማስታወሻ፡በሌለው ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ፈጣሪዋን ፡ አጥንታ ፡ ከፍጡራን ፡ በላይ ፡ የአማልክት ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ ኾነው ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በማስተካከል ፡ እጆቿዋን ፡ ዘርግታ ፡ ስለ፡ አያት ፡ ኢትዮጵያ ፡ እጆቿዋን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትዘረጋለች ፡ ሲል ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሰማውን ፡ ተናገረ ፤ እውነትም ፡ መሰከረ ። መዝ ፡ ፷፰ ፡ ቍ ፡ ፴፩ ።

፲፬ ፤ ነቢይ ፡ ዳዊት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጐብኝቶ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ በተፈጠረ ፡ ነበር ።

፲፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያን ፡ በዐይነ ፡ ሥጋ ፡ ሳያይ ፡ በእግረ ፡ ሥጋ ፡ ሳይጐበኝ ፡ በዐይነ ፡ ሕሊና ፡ እንዳያት ፡ በእግረ ፡ ሕሊና ፡ እንደ ፡ ጐበኛት ፡ ያስቀረው ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

፲፮ ፤ ነቢይ ፡ ዳዊት ፤ እግዚአብሔር ፤ ዳዊት ፡ እንደ፡ ልቤ፡ የታመነ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ መሰከረለት ፡ ኹሉ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በጣዖታት ፡ አምልኮት ፡ ያልተዳደፈችና ፡ ያልረከሰች ፡ መኾኗን ፡ በግልጽ ፡ አስረዳ ።

፲፯ ፤ ፫ኛ ፤ ስለ ፡ ሳባ ፡ ንግሥት ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተጻፈውን ፡ እንመልከት ። የሳባ ፡ ንግሥት ፤ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የወጣለትን ፡ የሰሎሞንን ፡ ወሬ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ በእንቆቅልሽ ፡ ልትፈትነው ፡ መጣች ። ከብዙም ፡ ጓዝ ፡ ጋራ ፡ ኹና ፡ ብዙ፡ከብት ፡ ይዛ ፡ በግመልም ፡ ያማረ ፡ ያማረ ፡ ሽቱና ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ የከበረም ፡ ዕንቍ ፡ አስጭና ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገባች ፤ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ መጣች ፤ በልብዋም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ አጫወተችው ።

፲፰ ፤ ሰሎሞንም ፡ የጠየቀችውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ተረጐመላት ፡ ከንጉሡም ፡ የተሰወረ ፡ ነገር ፡ አልነበረምና ፡ መልስ ፡ ያልሰጠበት ፡ ነገር ፡ የለም ።

፲፱ ፤ የሳባም ፡ ንግሥት ፤ ሰሎሞን ፡ የሠራውን ፡ ቤት ፡ መንግሥትና ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የማዕዱንና ፡ የብላቴኖቹን ፡ አቀማመጥ ፡ የሎላልቱን ፡ መሠራትና ፡ የአለባበሳቸውን ፤ የጠጅ ፡ አሳላፊችንም ፡ ደንበኛ ፡ አቋቋም ፡ ከቤት ፡ መንግሥትም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወጣበት ፡ የነበረውን ፡ መንገድ ፡ በጠቅላላውም ፡ ጥበቡንና ፡ ብልኀቱን ፡ እግዚአብሔርም ፡ የሰጠውን ፡ ክብሩንና ፡ ጌትነቱን ፡ ኹሉ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ አደነቀች ፤ ሕሊናዋም ፡ በአንክሮ ፡ ተማረከ ።

፳ ፤ ንጉሡንም ፡ እኔ ፡ መጥቼ ፡ በዐይኔ ፡ እስካይ ፡ ድረስ ፡ የነገሩኝን ፡ አላመንኩም ፡ እንጂ ፤ በሀገሬ ፡ ሳለሁ ፡ ስለ ፡ ነገርኽ ፡ ስለ ፡ ጥበብኽም ፡ የሰማኹት ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ ነው ። እነሆ ፡ እኩሌታውንስ ፡ እንኳ ፡ አልነገሩኝም ። ከሰማኹት ፡ ወሬ ፡ ሥራኽና ፡ ጥበብኽ ፡ ይበልጣልና ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፩ ፤ ሰዎችኽ ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ፤ እለዚህ ፡ ዘወትር ፡ በፊትህ ፡ የሚቆሙ ፡
ባሮችኽ ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ፤ አንተን ፡ የወደደህ ፡ በእስራኤልም ፡ ዙፋን ፡ ያስቀመ
ጠኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ የተባረከ ፡ ይሁን ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ ለዘለ
ዓለም ፡ ወዷልና ፡ ቅን ፡ ፍርድ ፡ ትፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ አድርጎ ፡ አስነሣኽ ፡ አለ
ችው ።

፳፪ ፤ ለንጉሡም ፡ መቶ ፡ ኻያ፡ቅንጣር ፡ ወርቅና ፡ እጅግ ፡ ብዙ፡ሽቱ ፡ የከበረም ፡
ዕንቊ ፡ ሰጠችው ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ሰጠ
ችው ፡ ያለ ፡ የሽቱ ፡ ብዛት ፡ ከቶ ፡ አልመጣም ። ፩ኛ ፡ ነገ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡

፳፫ ፤ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማስረጃ ፡ እናገኛለን ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የወጣለትን ፡ የሰሎሞንን ፡ ወሬ ፡ ሰምታ ፡ በእንቆቅልሽ ፡ ልትፈት
ነው ፡ መጣች ፡ ሲል ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እየመሰከረ ፡ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ በእግዚአብሔር ፡
ስም ፡ የወጣለትን ፡ የሰሎሞንን ፡ ወሬ ፡ ሰምታ ፡ መጣች ፡ ቢል ፡ ከሕገ ፡ ኦሪት ፡ በፊት ፡
ኢትዮጵያ ፡ ፍጡራንን ፡ ታመልክ ፡ ነበር ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሂዳ ፡
ከተመለሰች ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አመነች ፤ ስለዚህም፡ የኢትዮ
ጵያ ፡ እምነት ፡ ከእስራኤል ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ በአፍም ፡ በመጣፍም ፡ መመስከር ፡
በነቢያት ፡ አድሮ ፡ የተናገረ ፤ መጻሕፍትን ፡ ያጻፈ ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ቅዱስ ፡ ቃሉን ፡
ማስተባበል ፡ አይኾንምን ? ብዙ ፡ ባሕር ፡ ተሻግራ ፡ ብዙ ፡ በረሃ ፡ ቈርጣ ፡ እንድትሄድና ፡
ገንዘቧንም ፡ በቅዱሱ ፡ ቦታ ፡ በረከተ ፡ ገጽ ፡ አድርጋ ፡ እንድታቀርብ ፡ ያስገደዳት ፡
በፍቅር ፤ በሃይማኖት ፡ ከጥንት ፡ ያወቀችው ፡ የለመደችው ፡ ከአባቷ ፡ ከካህኑ ፡ መልከ ፡
ጼዴቅ ፡ የተማረችው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ፍጡራንን ፡ የምታመልክ ፡ ቢኾ
ንማ ፡ ኖሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቃ ፡ ለማን ፡ ስም ፡ ትደነግጥና ፡ ትጨ
ነቅ ፤ የማንን ፡ ስም ፡ ትናፍቅ ፤ በማንስ ፡ ሥራ ፡ ትደነቅ ፤ በምንስ ፡ ምክንያት ፡ ገናና ፡
የታወቀ ፡ ዙፋን ፡ ያላት ፡ የሳባ፡ንግሥት ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ቍጥሩ ፡ ከኹለት ፡ ቤት ፡ ላልወ
ጣው ፡ ላልበሰለውና ፡ ለለጋው ፡ ለሰሎሞን ፡ ( ለእስራኤል ) ፡ ዙፋን ፡ ትታጠቅ ፡ ነበር ?

፳፬ ፤ ኢትዮጵያዊ ፡ ሆይ ! ኢትዮጵያ ፡ ፍጡራንን ፡ ታመልክ ፡ ነበር ፡ በማለት ፡
ፈንታስ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በአባቶች ፡ መምህርነት ፤ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ምስክርነት ፡ ያጠና
ችው ፡ ያወቀችው ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፤ የጠለቀውን ፡ የረቀቀውን ፡ ልብ ፡ ያሰበ
ውን ፡ ኵላሊት ፡ ያመላለሰውን ፡ ሰው ፡ ሳይነግረው ፡ የሚያውቅ ፡ ጎቡእ ፡ ማእምረ ፡
ኅቡአት ፡ መኾኑን ፡ ስለምታውቅ ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የወጣለ
ቱን ፡ የሰሎሞንን ፡ ወሬ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ በእውነት ፡ ሰሎሞን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚ
ያውቅ ፡ የሚያመልክ ፡ ከኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለባሮቹ ፡ ምስጢር ፡ ይገልጻልና ፡ የተሰወ
ረውን ፡ ያውቅ ፡ ይኾናል ፡ ስትል ፡ አንደኛ ፡ በእንቆቅልሽ ፡ ጥያቄ ፡ ልትፈትነውና ፡ ሃይ
ማኖቱን ፡ ልትረዳ ፤ ኹለተኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኳ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ምን ፡ ሥራ ፡
እንደ ፡ ሠራና ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ አሉት ፡ ምን ፡ ዐይነትስ ፡ የአምልኮት ፡



ንግሥተ ፡ ዐዜብ ፡ ትትነሣእ ፡ አመ ፡ ዕለተ ፡ ደይን ፡ ወትትፋታሕ ፡ ምስለ ፡ ዛ ፡
ትውልድ ፡ እስመ ፡ መጽአት ፡ እምአጽናፈ ፡ ምድር ፡ ትስማዕ ፡ ጥበቢሁ ፡ ለሰ
ሎሞን ። ማቴዎስ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፵፪ ።

www.ethiopianorthodox.org

ሥርዐት ፡ እንዳለ ፡ ለማወቅ ፡ ሦስተኛ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በዓለም ፡ የአምላክ ፡ አገር
የምትባል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ ነበረችና ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚመለክበት ፡ ሌላ ፡ አገር
እንዳለ ፡ ብትሰማ ፡ በጆሩዋ ፡ የሰማችውን ፡ በዐይኗ ፡ ለማየት ፡ ምስክርነት ፡ ለማረጋ
ጥና ፡ የሃይማኖት ፡ ወገን ፡ ለማብዛት ፡ ሄደች ፡ ብለኸ ፡ ተርክ ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ም ፡ ፲፮
ቍ ፡ ፯ ። መገ ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፱ ።

፳፫ ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የወጣለትን ፡ የሰሎሞንን ፡ ወሬ
በሰማች ፡ ጊዜ ፤ እግዚአብሔር ፡ ማነው ፡ ብላ ፡ አልጠየቀችም ። ምክንያቱም ፡ ይህ
ገናና ፡ ስም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ከኢትዮጵያነቷ ፡ ጀምሮ ፡ አብሯት ፡ የኖረ ፡ እንጂ ፤ አዲስ
ስም ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ድንገተኛ ፡ ደራሽ ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ ድንገተኛ ፡ ፈሳሽ፡ባለመኾኑ
ነው ።

፳፬ ፤ እንግዳና ፡ አዲስ ፡ ስምስ ፡ ቢኾንባት ፡ ኖሮ ፡ ከግብጻውያን ፡ ነገሥታት
አንዱ ፡ በሙሴ ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ፡ ፈርዖን ፤ ሙሴና ፡ አሮን ፡ በፊቱ ፡ ቆመው ፡ የእስረ
ኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ ያደርጉልኝ ፡ ዘንድ ፡ ወገኖቼን ፡ ላክ ፡ ብሎሀል
ቢሉት ፤ ባሮቼን ፡ እለቅ ፡ ዘንድ ፡ የሚያዝዘኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማነው ? እግዚአብሔርን
አላውቀውም ። ባሪያዬን ፡ እስራኤልንም ፡ አለቅም ፡ እንዳለ ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፤ እግዚአ
ብሔር ፡ ማነው ? ሰሎሞንስ ፡ ማነው ? ብላ ፡ ብትጠይቅ ፡ ተገቢ ፡ በኾነ ፡ ነበር
ዘፀ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ እስከ ፡ ፯ ።

፳፭ ፤ ከጥያቄዋም ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅሩ ። ባይማርካ
ትና ፡ ሕጉን ፡ ለመከተል ፡ ባትሻ ፡ ኖሮ ፡ ሩቅ ፡ መንገድ ፡ ለመሄድና ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ
ለማበላሸት ፡ ባልፈለገችም ፡ ነበር ።

፳፮ ፤ ወደ ፡ ሰሎሞንም ፡ ደርሳ ፡ የሠራውን ፡ ቤተ፡ መንግሥትና ፡ ቤተ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ የቤቱንም ፡ ጠቅላላ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ካየችና ፡ የነገረችውንም ፡ ተርጕሞላት
ጥበቡንና ፡ ዕውቀቱን ፡ ከተረዳች ፡ በኋላ ፤ በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ያስቀመጠኸ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ የተባረከ ፡ ይኹን ፡ ስትል ፡ አመሰገነች ፡ እንጂ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክንና
ሥራውን ፤ የአምልኮትንም ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ለማጥናት ፡ የደቂቃ ፡ ጊዜ፡ አልፈለገችም

፳፱ ፤ ሙሴ ፡ እንኳ ፡ በምድያም ፡ በተገለጸለት ፡ ጊዜ ፤ ብዙ ፡ ምልክት ፡ አስፈለ
ገው ፡ እንጂ ፤ በቶሎ ፡ ሊረዳው ፡ አልቻለም ። ዘፀ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ እስከ ፡ ፲ ።

፴ ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ ግን ፡ ያዕቆብ ፡ በፍኖተ ፡ ሎዛ ፡ ተገልጾ ፡ ለተነጋገረው
አምላክ ፡ ምክንያት ፡ እንዳልፈጠረ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከአባቶች ፡ ያጠናችውን ፡ ሃይማኖት
በኢየሩሳሌም ፡ በግልጽ ፡ መሰከረች ፡ እንጂ ፤ ምክንያት ፡ አልፈጠረችም ። ዘፍ ፡ ም
፳፰ ፡ ቍ ፡ ፳፪ ።

፴፩ ፤ ከምስጋናዋም ፡ ጋራ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ ለዘለዓለም ፡ ወዷልና
ቅን ፡ ፍርድ ፡ ትፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ አድርጎ ፡ አስነሣኸ ፡ በማለቷ ፤ እግዚአብሔር
የአባቱን ፡ የዳዊትን ፡ ዙፋን ፡ ይሰጠዋል ። ለያዕቆብም ፡ ወገን ፡ ለዘለዓለም ፡ ነግሦ ፡ ይኖ



ራል ፡ ያለውን ፡ የመሰለ ፡ ቃለ ፡ ትንቢት ፡ ተናግራለች ። ፩ ፡ ነገ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፱ ።
ሉቃ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፴፪ና ፡ ፴፫ ።

፴፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስራኤል ፡ በመስማት ፡ በማየት ፡ በዘወ
ትር ፡ ታምራት ፡ ያጠናችውን ፡ ሃይማኖት ፡ ጠብቆ ፡ መኖር ፡ ተስኗት ፡ እግዚአብሔርን ፡
በጣዖት ፡ ስታስቀና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ ስትፈልግ ፡ አይቶ ፤ ለኢትዮጵያና ፡ ለእስ
ራኤል ፡ ሃይማኖት ፡ ሚዛን ፡ የኾነ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ተናገረ ።

፴፫ ፤ ይኸውም ፡ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ ሰምታ ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ መጥታለችና ፤
የሳባ ፡ (የዐዜብ) ፡ ንግሥት ፡ ይህችን ፡ ትውልድ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ተነሥታ ፡ ትፋረዳታ
ለች ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፵፪ ።

፴፬ ፤ እነሆ ፡ ከሰሎሞን ፡ የሚበልጥ ፡ ከዚህ ፡ አለ ፡ ያለው ፡ ቃሉ ፡ ነው ። ጌታ
ችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሲያስታውሳት ፡ እንደ ፡ ሰዶምና እንደ ፡ ገሞራ፡
ፍርድ ፡ እንዲሻሻልላት ፡ አይደለም ፤ ሀይማኖቷ ፡ የጸናላት ፡ የታወቀች ፡ እንደ ፡ መኾኗ ፡
መጠን ፤ እንቢተኛዋን ፡ ትውልድ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ተነሥታ ፡ እንድትፋረዳት ፡ ነው ፡
እንጂ ፤ ኹለቱ ፡ አገሮች ፡ የሚፋረዱባቸው ፡ ነገሮች ፡ ሦስት ፡ ዐይነቶች ፡ ናቸው ።

፴፭ ፤ አንደኛ ፡ እንቢተኛዪቱ ፡ ትውልድ ፤ በማየት ፡ በመስማት ፡ ባጠናችው ፡
ሃይማኖት ፡ መሠረትነት ፤ እንደ ፡ አባቶቿ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ያይደለ ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡
በአምሳለ ፡ ንጉሥ ፡ ተገልጾ ፡ ከሕገ ፡ አረሚ ፡ የምትለይበትን ፡ ሕገ፡ኦሪትን ፡ ሠርቶላት ፤
ዘፀአት ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፩—፳፭ ። ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ የምትለይበትን ፡ ቅዱስ ፡ ስሙን ፡
አስታውቋት ፤ ትእዛዙንና ፡ ሕጉን ፡ በጽላት ፡ ጽፎ ፡ ሰጥቷት ፤ መምህራን ፡ ነቢያትን ፡
ሾሞላት ፤ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ትታ ፡ ከጣዖታት ፡ ጋራ ፡ ስታመነዝር ፤ ዘዳግም ፡ ም ፡ ፴፪ ፡ ቍ ፡
፳፩ ። ኢትዮጵያ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ያጠናችው ፡ ፈጣሪዋን ፡ በመከተል ፡ ስሙ ፡ የሚጠራ
በት ፡ መቅደስ ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ ቦታ ፡ ሂዳ ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ መሳሳት ፡ እንደ ፡ እስ
ራኤል ፡ እንቢተኝነት ፡ በቃል ፡ መዘለፍ ፡ በመቅሠፍት ፡ መገረፍ ፡ ሳያገኛት ፤ ከዚያ ፡
በፊት ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ልዩ ፡ በኾነው ፡ በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡
ጸናች ፡ ከሕገ ፡ አረሚ ፡ የተለየ ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ተቀብላ ፡ በትእዛዙ ፡ ጸንታ ፡ ሕጉ ፡ በተ
ጻፈባት ፡ በታቦተ ፡ ጽዮን ፡ አማካይነት ፡ ለቅዱስ ፡ ስሙ ፡ ስትሰግድ ፡ መኖሯ ፡ ነው ።

፴፮ ፤ ከፍርድ ፡ መቀበያዎች ፡ አስተያየቶች ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ሲኾን ፡ ኹለቱን ፡
ደግሞ ፡ በየቦታቸው ፡ እናመጣቸዋለንና ፡ ልብ ፡ አድርጎ ፡ መመልከት ፡ ነው ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ከሕገ ፡ ኦሪት ፡ በፊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ነበረችበት ፡ እምነት ፤ ከታሪክ ፡
ጸሐፎች ፡ ምን ፡ ይወራል ?

፪ ፤ ከታሪክ ፡ ጸሐፎች ፡ የመነጨው ፡ ወሬ ፡ በእውነተኛ ፡ ስሟ ፡ ላይ ፡ ምን ፡
ፈጥሯል ?

፫ ፤ አስተዋይ ፡ ሕሊና ፡ ስለ ፡ አምልኮቷና ፡ ስለ ፡ ስሟ ፡ አጠራር ፡ የሰፈሩትን ፡
ጽሑፎች ፡ ሊያመዛዝን ፡ አይችልምን ?

www.ethiopianorthodox.org

፬ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ፍጡራንን ፡ ታመልክ ፡ ነበር ፡ ወይ ? በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ምስክርነት ፡ ማንን ፡ ትከተል ፡ ነበር ?

፭ ፤ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ተመራምሮ ፡ ፈጣሪን ፡ ማወቅ ፡ ጣዖት ፡ ማምለክ ፡ ነው ፡ ለሚል ፡ ሰው ፡ ማስረጃው ፡ ምድን ፡ ነው ?

፮ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ሳለች ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ያደረገችው ፡ ምርመራ ፡ ምን ፡ አስገኝቷል ? ሃይማኖቷስ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተገለጸ ?

፯ ፤ ሃይማኖቷ ፡ ተተገለጸ ፡ የአምላክ ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ መኾኗን ፡ ልናውቅላት ፡ አይገባምን ? ሐሜትንስ ፡ አንተውምን ?

፰ ፤ አብርሃም ፡ በረከትን ፡ ከማን ፡ አገኘ ? መልከ ፡ ጼዴቅስ ፡ ከማን ፡ ወገን ፡ ነው ?

፱ ፤ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተመርቶ ፡ ምን ፡ መሰከረ ? በዚያ ፡ ዘመን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ሀይማኖት ፡ የምትመራበት ፡ ጽሑፍ ፡ ነበራትን ?

፲ ፤ ዳዊት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጐብኝቷልን ? ጐብኝቶ ፡ ቢኾንሳ ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ ይፈጠር ፡ ነበር ?

፲፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ መሰከረ ?

፲፪ ፤ ስለ ፡ ሳባ ፡ ንግሥት ፤ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍሎች ፡ በየትኛው ፡ ጽሑፍ ፡ እናገኛለን ?

፲፫ ፤ ስለ ፡ ሳባ ፡ ንግሥት ፡ የተጻፈው ፡ ምን ፡ ይላል ? ባነበብነውስ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ይገባናል ? ያለ ፡ ማስረጃ ፡ የኢትዮጵያ ፡ እምነት ፡ ከእስራኤል ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማሳበል ፡ አይኾንምን ?

፲፬ ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ በማን ፡ ስም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሄደች ? የማያውቋት ፡ ይናፍቃልን ?

፲፭ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ፍጡራንን ፡ ታመልክ ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ምን ፡ ማለት፡ ይገባል ? እግዚአብሔር ፤ ሰው ፡ ነገርን ፡ ሊያስረዳው ፡ ይፈልጋልን ? ለባሮቹስ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ? የሳባ ፡ ንግሥትስ ፡ ስለ ፡ ስንት ፡ ነገሮች ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሄደች ? ከነምክንያታቸው ፡ ባጭር ፡ አስረዳ ።

፲፮ ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ማነው ፡ ብላ ፡ ጠየቀችን ? ምክንያቱስ ።

፲፯ ፤ የግብጽ ፡ ፈርዖን ፤ ሙሴና ፡ አሮን ፡ ላቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ ምን ፡ መለሰ ?

፲፰ ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አደረገች ? ምንስ፡ ተናገረች ? የአምልኮትን ፡ ትምህርት ፡ ከሰሎሞን ፡ ተምራለችን ?

፲፱ ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ በሀይማኖት ፤ ከሙሴና ፡ ከያዕቆብ ፡ ማንን ፡ ትመስላለች ? የሳባ ፡ ንግሥት ፡ ከምስጋናስ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ ተናገረች ?

፳ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ምን ፡ ተናገረ ?



፳፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሲያስታውሳት ፡ እንደ ፡ ሰዶምና ፡ እንደ ፡ ገሞራ ፡ ነውን ? ልዩነቱን ፡ አስረዳ ፡ ኹለቱ ፡ አገሮች ፡ የሚፋረዱባቸው ፡ ስንት ፡ ናቸው ?

፳፪ ፤ እንቢ.ተኛዪቱ ፡ ትውልድ ፡ ምን ፡ አደረገች ? ኢትዮጵያሳ ?

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ኢትዮጵያና ፡ ማስረጃዎቿዋ ።

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፤ በቅን ፡ ለሚያገለግሉት ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፤ የሚኖር ፡ የማይሻር ፡ የማይደፈር ፤ የማይጣስና ፡ የማይደመሰስ ፡ ኗሪ ፡ መታሰቢያ ፡ መስጠትና ፡ ማቆም ፡ ልማዱ ፡ ነው ።

፪ ፤ ይኸውም ፡ ለኖኅ ፡ ቀስተ ፡ ደመናን ፤ ለአብርሃም ፡ ግዝረትን ፤ ለያዕቆብ ፡ ብኵርናን ፤ ለሙሴ ፡ ጽላትን ፤ ለአሮን ፡ ክህነትን ፤ ለዳዊት ፡ መንግሥትን ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ ያለ ፡ ስጦታ ፡ ነው ።

፫ ፤ ኢትዮጵያም ፡ በአባቶች ፡ መምህርነት ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ምስክርነት ፤ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ በተለየ ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ተከተለችውና ፡ ስለ ፡ አመነችው ፤ እንደ ፡ አእምሮዋ ፡ ስፋት ፤ እንደ ፡ ሃይማኖቷ ፡ ጽናት ፡ የምድር ፡ አሕዛብ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፤ በየወገናቸው ፡ በየቋንቋቸው ፡ በየዕጣቸው ፡ ምድርን ፡ ተካፍለው ፡ በየርስታቸው ፡ መኖር ፡ ከጀመሩበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፤ ከአበው ፡ የወረደውን ፡ ያልተሻረ ፡ ያልተደፈረ ፡ ያልተጣሰና ፡ ያልተደመሰሰ ፡ ነጻነትን ፤ በነጻነትም ፡ መሠረትነት ፡ የሚገኙትን ፡ ሰባቱን ፡ ሀብታት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተቀብላለች ።

፬ ፤ እነዚህም ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የሐሜት ፡ ወሬና ፡ ጥርጣሬ ፡ መለወጥና ፡ መናወጥ ፡ የሌለበት ፤ የአምልኮቷ ፡ ፍሬዎችና ፡ ማስረጃዎች ፡ ናቸው ።

፭ ፤ እነዚህም ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

፩ኛ ፤ ሃይማኖት ፡
፪ኛ ፤ ፍቅር ፡
፫ኛ ፤ ስም ፡
፬ኛ ፤ መንግሥት ፡
፭ኛ ፤ ክህነት ፡
፮ኛ ፤ ቋንቋ ፡
፯ኛ ፤ ልምላሜ ፡ ናቸው ።

፮ ፤ ፩ኛ ፤ ሀይማኖት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በአለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ እንደ ፡ ዘረዘርነው ፡ ኹሉ ፤ እግዚአብሔርን ፡ እንጂ ፤ ከቶ ፡ ፍጡራንን ፡ አላመለከችም ።

፯ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ተመራምራ ፡ ፈጣሪዋን ፡ መከተሏና ፡ እሱንም ፡ በማምለክ ፡ መጽናቷ ፡ እርግጥ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፰ ፤ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፤ ፍጡራንን ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብትን ፤ ታመልክ ፡ ነበረ ፡ ማለታቸው ፤ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ መመራመሯን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፡ ይሁዳ ፡ ይሁዳ ፡ በጐልቄ ፡ አህጉሪከ ፡ ብዙኃን ፡ አማልክቲከ ፤ ከማሁ ፡ አጋንንቲከ ። ወበአምጣነ ፡ ስነ ፡ ምድሩ ፡ ሐነጸ ፡ ሐውልተ ። « ይሁዳ ! አማልክቶችኽ ፡ በሀገርህ ፡ ቍጥር ፡ ብዛት ፡ እንደ ፡ መኾናቸው ፤ አጋንንትኽ ፡ በዚያው ፡ ልክ ፡ ናቸው ። ኤር ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ። »

፱ ፤ እስራኤል ፡ በምድሩ ፡ ማማርና ፡ መበጀት ፡ መጠን ፡ ሐውልቱን ፡ አቆመ ፡ እንዳለው ፡ ኹሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ፍጡራንን ፡ የምታመልክ ፡ ብትኾን፡ኖሮ ፤ በየሜዳውና ፡ በየሸንተረሩ ፤ በየኰረብታውና ፡ በየተራራው ፡ የጣዖታትና ፡ የመስገጃቸው ፡ ምልክት ፡ በተገኘ ፡ ነበር ። ሆሴዕ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፲ ፤ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፤ ኢትዮጵያ ፡ በፀሐይ ፡ በጨረቃ ፡ በከዋክብት ፡ በዛፍ ፡ በዘንዶ ፡ በክፉ ፡ መናፍስትም ፡ ታመልክ ፡ ነበረ ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፤ ጽሑፍን፡ከተጠያቂነት ፡ ለመለየየት ፤ ከዕንጨት ፡ የተቈረጡ ፡ ከድንጋይ ፡ የተቀረጡ ፡ ጣዖታትን ፡ አላመለከችም ፡ ሲሉ ፤ የሰባሪው ፡ ቅናሽ ፡ የመስጊዱ ፡ ፍራሽ ፡ የት ፡ አለ ፡ የሚል ፡ ጥያቄ፡ቢመጣ ፡ ተጠያቂነትን ፡ ከራስ ፡ ለማውረድ ፡ ያኽል ፡ የሰጡት ፡ ወሬ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በአንዱ ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ የጣዖት ፡ ውሽማ ፡ እንዳልጨመረች ፤ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ሆኗታል ። ይህንንም ፡ ቃል ፡ ፊታቸውን ፡ ጸፍቶ ፡ አፋቸውን ፡ ከፍቶ ፡ ለአናገረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንክሮ ፡ ይገባል ።

፲፩ ፤ ስለ ፡ ክፉ ፡ መናፍስት ፤ ሁከተኛው ፡ መልአከ ፡ ጽልመት ፡ መኰንነ ፡ ጽልመት ፡ ዲያብሎስ ፡ በመላእክት ፡ መካከል ፡ ሐሰትን ፡ ከራሱ ፡ አንቅቶ ፡ ከልቡ ፡ አመንጭቶ ፡ በመናገሩና ፡ ሁከትን ፡ በማንሣቱ ፡ ከሚካኤልና ፡ ከገብርኤል ፤ ከሰራዊቱም፡ጋራ፡ ተዋግቶ ፡ የተቀባ ፡ ኪሩብ ፡ ኾኖ ፡ በውበት ፡ በክብርና ፡ በጌትነት ፡ ሊኖርበት ፡ እግዚአብሔር ፡ ካዘጋጀለት ፡ ቦታ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ስለ ፡ ወደቀ ፤ ከወደቀባት ፡ ቀን ፡ ወዲህ ፤ በመላእክት ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ባለጋርነት ፡ ስለ ፡ ድካሙ ፡ ትቶ ፤ ጸቡን ፡ ከአዳምና፡ከልጆቹ፡ጋራ፡አድርጓል።ሕዝ፡ም፡፳፰፡ቍ፡፲፫—፳።ራዕ፡ም፡፲፪፡ቍ፡፯—፱ ።ዮሐ፡ም፡፰፡ ቍ፡፵፬ ። ፪ኛ ፡ ጴጥ ፡ ም፡፪ ፡ ቍ፡፬ ። ፩፡ዮሐ ፡ ም፡፫ ፡ ቍ፡፰—፲ ። ይሁ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

፲፪ ፤ በአዳምና ፡ በልጆቹ ፡ በዲያብሎስና ፡ በሰራዊቱ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ጠንካራ ፡ ጥልና ፡ ትግል ፤ አዳም ፡ ከገነት ፡ ከወጣባት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ተጋጋለ ፡ አለ ።

፲፫ ፤ ክርስቶስም ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ነግሦ ፡ ከሥልጣኑ ፡ ስለ ፡ ሻረው ፡ አስገዳጅነቱ ፡ ቢቀርም ፡ እንኳ ፡ ሌብነቱና ፡ ጠላትነቱ ፡ አልቀረም ። ወደ ፡ ፊትም ፡ ክርስቶስ፡በጌትነት ፡ መጥቶ ፡ ፍርድን ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፤ በኹለቱም ፡ መካከል ፡ የነደደው ፡ የጥላቻ ፡ እሳት ፡ መብረጃ ፡ ሳያገኝ ፡ ይኖራል ።

፲፬ ፤ ዲያብሎስና ፡ ሰራዊቱ ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ በሚያደርጉት ፡ ያጥቂነት ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፤ በሥጋ ፡ በኩል ፡ ከሚያመጡባቸው ፡ ጉዳት ፡ የሚበልጠው ፤ ፈጣሪያቸውን ፡ ትተው ፤ ጓደኞቻቸውን ፡ ወዳጆቻቸውን ፡ ትተው ፤ ጠላታቸውን ፡ ሰጪያቸውን ፡



ትተው ፡ ነሻቸውን ፤ ሕይወታቸውን ፡ ትተው ፡ ሞታቸውን ፡ እንዲወዱ ፡ እንዲመርጡ ፡ እንዲያመልኩ ፡ የራሳቸውን ፡ ወይም ፡ የወንድማቸውን ፡ ሕይወት ፡ እስከ ፡ መሠዋት ፡ ደርሰው ፡ ለሰይጣን ፡ እንዲታዘዙና ፡ ራሳቸውን ፡ እንዲያዋርዱ ፤ ከአምላካቸውም ፡ እንዲለዩ ፡ ለማድረግ ፡ በነፍስ ፡ በኩል ፡ የሚያመጡባቸው ፡ ጦርነት ፡ ነው ። መዝ ፡ ፻፭ ፡ ቍ ፡ ፴፯—፴፱ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ሰው ፡ ከአምላኩ ፡ ስለ ፡ ተለያየና ፡ ጠባቂ ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ በግ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ « ክርስቶስ » ፡ ድረስ ፡ የበደሉትንም ፡ ያልበደሉትንም ፡ ሞት ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ገዝቷቸዋል ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ፡፲፬ ።

፲፭ ፤ በሞትም ፡ ገዥነት ፡ ዘመን ፡ ከዲያብሎስና ፡ ከሰራዊቶቹ ፡ የሚዘጋጀው ፡ የኀጢአት ፡ መሰናዶ ፡ እንደ ፡ መሻሻሉ ፡ መጠን ፤ ለዝግጅቱ ፡ ተባባሪዎች ፡ የኾኑት ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ከአምላክ ፡ ፍርድ ፡ ለማምለጥ፡ ስለ፡አልቻሉ ፤ በዘመነ ፡ ኖኅ ፡ የነበረው፡ ትውልድ፡በፍል፡ውሃ፡ተቀቀለ ። ዘፍ፡ም፡፯፡ቍ፡፩—፳፬ ። በዘመነ፡አብርሃምም፡የነበረው ፡ የሰዶምና፡የገሞራ፡ትውልድ፡በእሳት ፡ ተቃጠለ ። ዘፍ፡ም፡፲፱፡ ቍ፡፩—፴፰ ። ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በኋላ ፡ ለሰይጣን ፡ ታዛዦችና ፡ ለግብሩ ፡ ተባባሪዎች ፡ ባለመኾናቸው ፡ በአምላክ ፡ ታዳጊነት ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ የዳኑ ፡ ኖኅና ፡ ልጆቹ ፡ ሚስቱና ፡ የልጆቹ ፡ ሚስቶች ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። የኖኅም ፡ ልጆች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ መብዛትና ፡ መስፋፋት ፡ በጀመሩ ፡ ጊዜ ፤ ዲያብሎስና ፡ ሰራዊቱም ፡ የሰውን ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መተንኰልና ፡ መታገል ፡ ጀመሩ ። ስልፋቸውም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ሥጋን ፡ ለመጉዳት ፡ የተሰለፉት ፡ በወረወሩት ፡ የጦር ፡ ስለትና ፡ በረጩት ፡ የመርዝ ፡ ርጭት ፡ ከሰው ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ ግማሾቹ ፡ ዕውር፡ ዲዳ ፡ ደንቆሮ ፡ አንካሳ ፡ ቈራጣ ፡ ሲኾኑ ፤ ግማሾቹ ፡ በእብደት ፤ አእምሮ ፡ በማጣት ፡ ከእሳት ፡ ከገደል ፡ እየወደቁ ፤ ከባሕር ፡ እየጠለቁ ፡ አለቁ ።

፲፮ ፤ እንዲሁም ፡ ነፍስን ፡ ለመጉዳት ፡ ከተዘጋጁት ፡ ሰልፈኞች ፡ ባደረጉት፡ልዩ፡ የረቂቅ ፡ ጦርነት ፡ ብርታት ፡ ሰው ፡ በመጀመሪያው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ራሱ ፡ ሕያው ፡ ለሌላውም ፡ ሕይወትን ፡ የሚያድል ፡ አምላክን ፡ ለመኾን ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ የገመተውን ፡ ያኽል ፤ ከሰማይ ፡ ወርደው ፡ ከአዋልደ ፡ ቃኤል ፡ ጋራ ፡ በመቀላቀል ፡ የተሳሳቱ ፤ የኀጢአትን ፡ በር ፡ አሻሽለውና ፡ አስፋፍተው ፡ ለዓለም ፡ የከፈቱ ፡ ትጉሃን ፡ ሰማይ ፡ የተባሉ ፡ ክፉዎች ፡ መናፍስትን ፡ ተከትሎ ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በፊት ፡ ይሠራ ፡ የነበረውን፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኀጢአት ፡ ሥራ ፤ እንደ ፡ ገና ፡ አቋቋመና ፡ ጀመረ ። ዘፍ፡ም፡፮፡ ቍ፡፩—፲፫ ።

፲፯ ፤ ዕንጨት ፡ ጦርቦና ፡ ድንጋይ ፡ አለዝቦ ፤ ራሱ ፡ ባቆመው፡ ንብብ፡አእምሮ ፡ በሌለው ፡ጣዖት ፡ አመነዘረ፤ ዝሙትን፡ መግደልን፡ አዘወተረ፤ ከዚህም፡ የበለጠ፡ እስከ፡ ሰማይ፡ የደረሰ ፡ ግንብ ፡ ሠርቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመቃወም፡ሞከረ ። ኩፋ፡ም፡፲፡ቍ፡፲፫—፳፯ ።

፲፰ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ከሰው ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ የራቀ ፤ ዐሳቡም ፡ ከሰውና ፡ ከመላእክት ፡ አእምሮ ፡ የረቀቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ መንገዱን ፡ ስለ ፡ ቈረጠበት ፡ ሥራው ፡ በጅምር ፡ ቀረ፤ ግንቡ ፡ በነፋስ ፡ ፈረሰ ፤ ከንቱ ፡ ምኞቱም ፡ እስከ፡ መጨረሻው ፡ ተደመሰሰ ። ዘፍጥ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፭—፱ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፱ ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ በቋንቋ ፡ መለያየትን ፡ ያኽል ፡ የቢስ ፡ በሽታ ፡ ስለ ፡
ወደቀበት ፡ በቅርጽና ፡ በአቋቋም ፡ ተመሳስሎ ፡ የሚታየው ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ዝምድና ፡
ብርቱ ፡ መለያየትን ፡ እየፈጠረ ፡ በመሄዱ ፡ ሰው ፡ ከወንድሙ ፡ ይልቅ ፡ ገንዘብን ፡ እየወ
ደደ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ እንደ ፡ ዱባ ፡ ሲቃደድ ፤ እንደ ፡ ጐመን ፡ ሲቀራደድ ፤ እንደ ፡ በግና ፡
እንደ ፡ ፍየል ፡ ሲተራረድ ፡ ይኖራል ።

፳ ፤ የሰው ፡ ልጆች ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ክፉዎች ፡ መናፍስት ፡ በሥጋም ፡ ኾነ ፡ በነ
ፍስ ፡ የሚያደርጉባቸው ፡ ግፍና ፡ በደል ፤ ተንኰልና ፡ ትግል ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ እየጨ
መረ ፡ መሄዱን ፡ ስለ ፡ አዩና ፡ በትግልም ፡ ሊገፏቸው ፡ ሊያሸንፏቸው ፡ የማይችሉ ፡
መኾናቸውን ፡ ስለ ፡ ዐወቁ ፡ የደረሰባቸውን ፡ ኹሉ ፡ ላባታቸው ፡ ለኖኅ ፡ ነገሩት ።

፳፩ ፤ ኖኅም ፤ ልጆቹ ፡ የነገሩትን ፡ ሰምቶ ፡ ብዙ ፡ ካዘነ ፡ በኋላ ፤ ከእግዚአብሔር ፡
በቀር ፡ ታዳጊ ፡ ጌታ ፤ ከረድኤቱም ፡ በቀር ፡ ሰግደድ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፤ ከሃይማኖት ፡ የበለጠ ፡
ጋሻ ፤ ከጸሎት ፡ የበለጠ ፡ አምባ ፡ መጠጊያ ፡ መሸሻ ፡ እንደሌለው ፡ ዐውቆ ፡ ከጥፋት ፡
ውሃ ፡ ለመዳን ፡ በፊት ፡ መርከብን ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ አደረገለት ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡
ልጆቹ ፡ ለሰይጣን ፡ ከመገዛት ፡ ነጻ ፡ የሚወጡበትን ፡ ከወጥመዱ ፡ የሚያመልጡበትን ፡
ምክንያተ ፡ ድኅነት ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ የዘለዓለም ፡ ምሕረቱንም ፡ ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ያደ
ርግለት ፡ ዘንድ ፡ ልመናውን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቀረበ ።

« እነሆ ፡ ጸሎቱንም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ በግእዝና ፡ በአማርኛ ፡ ጥፈነዋል ።

፳፪ ፤ ወጸለየ ፡ ኖኅ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩ ፤ ወይቤ ፡ አምላክ ፡ መናፍ
ስት ፡ ዘውስተ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ዘገበርከ ፡ ምሕረተከ ፡ አድኀንከኒ ፤ ወውሉድየኒ ፡ እምነ
ማያተ ፡ አይኅ ፤ ወኢገበርከኒ ፡ ከመ ፡ እኅልቅ ፡ ከመ ፡ ገበርኮ ፡ ለወልደ ፡ ህጕል ፡ እስመ ፡
ዐቢይ ፡ ሣህልከ ፡ ላዕሌየ ፤ ወዐብየት ፡ ምሕረትከ ፡ ላዕለ ፡ ነፍስየ ፤ ይትለዐል ፡ ሣህልከ ፡
ላዕለ ፡ ውሉድየ ፤ ወኢይሙብሉ ፡ መናፍስት ፡ እኩያን ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢያማስን
ዎሙ ፡ እምነ ፡ ምድር ። ወአንተኒ ፡ ባርከኒ ፡ ኪያየ ፡ ወወሉድየ ፡ ንልሐቅ ፡ ወንብዛኅ ፡
ወንምልአ ፡ ለምድር ፤ ወአንተ ፡ ተአምር ፡ ዘከመ ፡ ገብሩ ፡ ትጉሃኒከ ፡ አበዊሆሙ ፡ ለእሉ ፡
መናፍስት ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ በሕይወት ፡ ዕፅዎሙ ፡ ወአኅዞሙ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ ደይን ፡
ወኢያማስኑ ፡ ውሉደ ፡ ገብርከ ፡ አምላኪየ ፡ እስመ ፡ ጸዋጋን ፡ እሙንቱ ፡ ወለአማስኖ ፡
ተፈጥሩ ፤ ወኢይሙብሉ ፡ ለመንፈሰ ፡ ሕያዋን ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ባሕቲትከ ፡ ተአምር ፡
ኵነኔሆሙ ፤ ወኢይትበውሑ ፡ ላዕለ ፡ ውሉደ ፡ ጻድቃን ፡ እምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፡
መጽሐፈ ፡ ኩፋሌ ፡ ምዕ ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፫—፳ ።

፳፫ ፤ « ኖኅም ፡ ወደ ፡ ፈጣሪው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመነ ። ይቅርታኽን ፡ አድር
ገኽ ፡ ያዳንኸኝ ፡ ልጆቼንም ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ ያዳንኻቸው ፤ ጥፋት ፡ የሚገባው ፡ ቃየል
ንም ፡ እንደ ፡ አጠፋኸው ፡ እንድጠፋ ፡ ያላደረግኸኝ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ይቅርታኽ ፡ ብዙ ፡
ነውና ፡ ቸርነትኽም ፡ በሰውነቴ ፡ ተገልጣለችና ፡ በሥጋ ፡ ኹሉ ፡ ያሉ ፡ የነፍሳት ፡ ፈጣሪ ፡
ይቅርታኽ ፡ በልጆቼ ፡ ላይ ፡ ይገለጥ ። ክፉዎች ፡ አጋንንትም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እንዳያጠ



ፏቸው ፡ በላያቸው ፡ አይሠልጥኑ ፡ አለ ። አንተም ፡ እኔን ፡ አክብረኝ ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ምድርንም ፡ እንመላት ፡ ዘንድ ፡ ልጆቼን ፡ አብዛቸው ፤ አንተም ፡ የእነ ዚህ ፡ ፍጥረቶች ፡ አባቶቻቸው ፡ ያደረጉትን ፡ ታውቃለህ ፤ በሕይወት ፡ ያሉ ፡ እነዚህ ፡ ረቂቃን ፡ አጋንንትን ፡ ይዘኽ ፡ መቻያ ፡ በሚደረግበት ፡ በገሃነም ፡ አግዛቸው ፤ ክፉዎች ፡ ናቸውና ፡ ለማጥፋት ፡ ተፈጥረዋልና ፡ ፈጣሪዬ ፡ የኔን ፡ የባሪያኽን ፡ ልጆች ፡ አያጥፉ ፤ በሕይወት ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ነፍስም ፡ አይሠልጥኑ ፤ አንተ ፡ ብቻ ፡ መቻያቸውን ፡ ታውቃለህና ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ በጻድቃን ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ አይ ሠልጥኑ ፡ አለ ። መጽሐፈ ፡ ኩፋሌ ፡ ምዕ ፡ ፲ ፡ ቍጥር ፡ ፫—፳ ።

፳፬ ፤ እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በመጽሐፈ ፡ ኩፋሌ ፡ ጠቅሰን ፡ ባሳየነው ፡ መሠረት ፡ ኖኅ ፡ ባቀረበው ፡ ጸሎት ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፤ የሰው ፡ ልጆችን ፡ በምሕረቱ ፡ ጐበኘ ፤ ይረዱዋቸውም ፡ ዘንድ ፡ ለይቅርታ ፡ የተዘጋጁ ፡ የምሕረት ፡ መላእክት ፡ ሲልክላቸው ፡ ከሚካኤልና ፡ ከሰራዊቱ ፡ ኀይል ፡ ድል ፡ ተነሥተው ፡ ከሰማይ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ የወደቁ ፡ ዲያብሎስና ፡ ሰራዊቱን ፡ ይዘው ፡ ለሰይጣንና ፡ ለመልክተኞቹ ፡ በተዘጋጀ ፡ የደይን ፡ ቦታ ፡ ( ገሃነም ) ፡ እንዲያግዙዋቸው ፤ ዐሥረኛውን ፡ እጅ ፡ ግን ፡ በዓለም ፡ እንዲተዋ ቸው ፡ አዘዘ ።

፳፭ ፤ ስለዚህ ፡ የታዘዙት ፡ መላእክት ፡ እንደ ፡ ትእዛዙ ፡ ፈጸሙ ፡ ማለት ፡ ዘጠ ኙን ፡ እጅ ፡ በደይን ፡ ቦታ ፡ አሰሩዋቸው ፤ ዐሥረኛውን ፡ እጅ ፡ በዓለም ፡ ተዉአቸው ።

፳፮ ፤ እዚህ ፡ ላይ ፡ ለሰሚዎቹ ፡ ከባድ ፡ መስሎ ፡ የሚታይ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ከባድነቱ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ክፉዎች ፡ አጋንንትን ፡ ከዓለም ፡ ጨርሶ ፡ ቢያጠ ፉቸው ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ በሰላም ፡ ይኖሩ ፡ ነበረ ፤ ብዙዎችን ፡ አስሮ ፡ ጥቂቶችን ፡ ለምን ፡ ተዋቸው ? የሚል ፡ ጠያቂ ፡ ሕሊና ፡ በገጠመ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

፳፯ ፤ ቀላልነቱም ፡ ሰው ፡ በክብር ፡ በጌትነት ፡ ኹሉን ፡ ሊገዛ ፡ ከተፈጠረ ፡ በኋላ ፡ የሚጠፉ ፡ ከተማ ፤ ዐዋጅ ፡ ቢነግሩበት ፡ አይሰማ ፡ እንደ ፡ ተባለ ፤ እግዚአብሔር ፡ አም ላክ ፤ ክፉና ፡ መልካም ፡ የምታስታውቀውን ፡ ዕፅ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ እንዳይነካ ፤ እንዳይ በላ ፡ ቢበላ ፡ ግን ፡ ሞት ፡ እንዲመጣበት ፡ ሲያስጠነቅቀውና ፡ በሕገኛ ፡ ዐዋጁ ፡ ሲከለክ ለው ፡ ትእዛዙን ፡ ስለ ፡ ጣሰ ፤ ሕጉን ፡ ስለ ፡ አፈረሰ ፡ የሞት ፡ ፍርድን ፡ ለመቀበል ፡ የወ ደቀበትን ፡ ግዴታ ፡ ስንረዳው ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፭—፲፰ ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፩—፳ ፡

፳፰ ፤ በዚህም ፡ ላይ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ስንፍናው ፡ ከአባያ ፡ በሬ ፡ የበለጠ ፡ በመ ኾኑ ፤ እንደ ፡ ወረንጦ ፡ የሚቈነጥጡት ፡ እንደ ፡ አልቃሾ ፡ ( . . . . . . . . ) የሚቀሰቅሱት ፡ እነዚህ ፡ ጠላቶች ፡ በአጠገቡ ፡ ባይኖሩ ፡ በፈጣሪው ፡ ፊት ፡ የታዛዥነት ፡ መልክ ፡ ሊያ ሳይ ፡ የማይፈቅድ ፡ ኵሩ ፡ ትቢተኛ ፡ ሙያ ፡ የጐደለው ፡ ጋኛ ፡ (ጌኛ) ፡ ጋጠ ፡ ወጥ ፡ እረኛ ፡ መኾኑን ፡ ስንገነዘበው ፡ ነው ።

፳፱ ፤ ደግሞም ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የዘነጉ ፡ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ሞትን ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ ጠርተው ፡ ወዳጅ ፡ አደረጉት ፡ እንጂ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሞትን ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ገዢ ፡ አድርጎ ፡ አልፈጠረምና ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ መከራ ፡ የመጣበት ፡ እግ

www.ethiopianorthodox.org

ዚአብሔርን ፡ ጠልቶ ፡ ሰይጣንን ፤ ሕይወትን ፡ ጠልቶ ፡ ሞትን ፡ ስለ ፡ ወደደ ፡ ነውና ፡ «ወደሽ ፡ ከተደፋሽ ፤ ቢረግጡሽ ፡ አይክፋሽ» ፡ እንደ ፡ ተባለ ፤ ሰው ፡ ወዶ ፡ ባደረገው ፡ እግዚአብሔር ፡ አይታማም ፡ ብሎ ፡ እውነትን ፡ የሚመሰክር ፡ እንደበት ፡ ሲኖረን ፡ ነው ። ጥበበ ፡ ሰሎ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፲፫—፲፮ ።

፴ ፤ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ዋና ፡ ነገራችን ፡ እንመለስ ። በሰናዖር ፡ ሜዳ ፡ የተሠራው ፡ ግንብ ፡ ከፈረሰና ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ በየነገዳቸው ፡ በየርስታቸው ፡ ከተለያዩ ፡ በኋላ ፤ በየሀገራቸው ፡ ክፉ ፡ መናፍስት ፡ አጋንንትን ፡ እየተከተሉ ፤ በትእዛዛቸውም ፡ እየተመሩ ፤ አጋንንትንና ፡ በስማቸው ፡ የተቀረጡ ፡ ጣዖታትን ፡ ማምለክ ፡ ጀመሩ ።

፴፩ ፤ አምላክን ፤ ከዕንጨት ፡ ወገን ፡ ቄርጦ ፡ ፈልጦ ፡ ጠርቦ ፡ ቀርጦ ፡ ልጎ ፡ ፈልፍሎ ፡ ድንጋይ ፡ ፈንቅሎ ፡ ፈልጦ ፡ ቀርጦ ፡ አለዝቦ ፤ በገዛ ፡ እጅ ፡ ንድፉን ፡ ቅቡን ፡ አከናውኖ ፡ ማምለክ ፡ የተጀመረበት ፡ አገር ፡ ዑር ፡ ዘከላውዴዎን ፤ ዘመኑም ፤ የአብርሃም ፡ ቅድመ ፡ አያት ፡ ሴሩግ ፡ ( ሴሩህ ) ፡ በተወለደበት ፡ ዘመን ፡ ነው ፤ በኋላ ፡ ከኹሉም ፡ ደርሷል ።

፴፪ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ካም ፡ ልጆቹን ፡ ኩሳን ፡ (ኩሺን) ፡ ሚዝራይምን ፡ ይዞ ፡ በመልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዳኘነት ፡ በአባቱ ፡ በኖኅ ፡ ፊት ፡ በዕጣ ፡ ወደ ፡ ወጣችለት ፡ ርስቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲገባ ፡ ከኖኅ ፡ በወረሰችው ፡ የአምልኮት ፡ ሥርዐት ፡ ኖኅንና ፡ ልጆቹን ፡ መጀመሪያ ፡ ከውሃ ፡ ጥፋት ፤ ኹለተኛ ፡ ለአጋንንት ፡ ከመገዛት ፡ ያዳነ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ብቻ ፡ ስታመልክ ፤ ለኖኅም ፡ የሰጠውን ፡ ቃለ ፡ ኪዳን ፡ በማስታወስ ፡ አረንጓዴ ፡ ቢጫ ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ወይም ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ በፊቷ ፡ አድርጋ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ በእሱ ፡ ብቻ ፡ ስተገዛ ፡ ኖራለች ።

፴፫ ፤ ይህም ፡ ሃይማኖታዊው ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀስቱን ፡ በደመና ፡ ባኖረ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፤ ለኖኅ ፡ የሰጠውን ፡ ቃለ ፡ ኪዳን ፡ ወይም ፡ የማለለትን ፡ መሐላ ፡ እንደሚያስብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በአካል ፡ ሦስት ፡ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ ብላ ፡ የምታምነው ፡ የምታመልከው ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኳን ፡ በሌሎች ፡ አማልክት ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳለወጠችው ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ እንደማትለውጠው ፡ ለዓለም ፡ ሲመሰክር ፤ ሲያስተምርና፡ሲሰብክ፡ይኖራል ። ዘፍ ፡ ም፡፱ ፡ ቍ፡ ፲፫—፲፯ ። ኩፋ፡ም፡፲፡ ቍ፡፲፫—፲፯ ።

፴፬ ፡ እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ሃይማኖታዊው ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ የዐይን፡ምስክር፡ኾኖ፡ ሲገኝ ፡ የሌላውን ፡ አገር ፡ ስሕተተኛ ፡ አምልኮት ፤ ለኢትዮጵያ ፡ መስጠት ፡ ብልኅ ፡ በልቶ ፡ በሞኝ ፡ አፍ ፡ አበሰ » ፡ እንደተባለው ፡ መኾኑ ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እምነት ፤ ታሪክ ፡ እጽፋለሁ ፡ ወይም ፡ አስተምራለሁ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፤ ነገር ፡ ከሥሩ ፡ ውሃ ፡ ከጥሩ ፡ የተባለውን ፡ ቃል ፡ መሪ ፡ አድርጎ ፡ ጥንተ ፡ ነገሩን ፡ ከአበውና ፡ ከመጻሕፍት ፡ ቢመረምር ፡ መልካም ፡ ነው ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለአገልጋዮቹ ፡ ምን ፡ ይሰጣል ? ስጦታውስ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ነው ?



፪ ፤ ኢትዮጵያሳ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ምን ፡ አገኘች ?

፫ ፤ ሰባቱ ፡ ሀብታት ፡ ምን ፡ ምን ፡ ናቸው ?

፬ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሌላ ፡ ጣዖታትን ፡ ታመልክ ፡ ነበረን ? በሥነ ፡ ፍጥረትስ ፡ ማንን ፡ ትፈልግ ፡ ነበር ?

፭ ፤ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ፍጡራንን ፡ ታመልክ ፡ ነበረ ፡ ማለታቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተራሮች ፡ የጣዖታትና ፡ የመስጊዳቸው ፡ ምልክት ፡ ይገኛልን ?

፮ ፤ ይሁዳ ፡ እስራኤል ፡ ምን ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ?

፯ ፤ ታሪክ ፡ ጸሐፎች ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ ጽፈዋል ? ምክንያቱስ፡ምንድን ፡ ነው ? ታሪክ ፡ ጸሐፎች ፡ ከጥያቄ ፡ ለመዳን ፡ የሰጡት ፡ ወሬ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ ጠቅሚታል ?

፰ ፤ ስለ ፡ ክፉ ፡ መናፍስት ፡ በመጻሕፍት፡ምን ፡ ተነግሮዋል ? ሁከተኛው ፡ መልአክ ፡ ማነው ? ምንስ ፡ አደረገ ? ሁከተኛው ፡ መልአክ ፡ በፊት ፡ ምን ፡ ነበረ ? በኋላስ ፡ ምን ፡ ኾነ ? ሁከተኛው ፡ በፊት ፡ የት ፡ ነበረ ? በኋላ ፡ የት ፡ ሄደ ?

፱ ፤ በሰውና ፡ በሰይጣን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ኹኔታ ፡ እንዴት ፡ ነው ?

፲ ፤ ክርስቶስ ፡ በመስቀሉ ፡ ከሻረው ፡ ወዲህ ፡ የሰይጣን ፡ ሥራው ፡ እንዴት ፡ ነው ?

፲፩ ፤ ዲያብሎስና ፡ ሰራዊቱ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ በሚያደርጉት ፡ የአጥቂነት ፡ ሥራ ፡ ከሥጋውና ፡ ከነፍሱ ፡ ማነኛው ፡ ይበልጣል ? ልዩነቱን ፡ አስረዳ ።

፲፪ ፤ ሰው ፡ በኀጢአቱ ፡ ከአምላኩ ፡ ከተለየ ፡ ወዲህ ፡ በጻድቃንና ፡ በኃጥአን ፡ መካከል ፡ ምን ፡ ልዩነት ፡ ተደረገ ?

፲፫ ፤ ሰው ፡ በኀጢአት ፡ ከዲያብሎስ ፡ ጋራ ፡ በመተባበሩ ፤ በኖኅና ፡ በአብርሃም ፡ ዘመን ፡ የነበረው ፡ ትውልድ ፡ ከአምላክ ፡ ምን ፡ ተፈረደበት ?

፲፬ ፤ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ የዳኑ ፡ እነማን ፡ ናቸው ?

፲፭ ፤ የኖኅም ፡ ልጆች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ መብዛት ፡ በጀመሩ ፡ ጊዜ ፡ ዲያብሎስና ፡ ሰራዊቱ ፡ ምን ፡ አደረጉ ?

፲፮ ፤ ዲያብሎስና ፡ ሰራዊቱ ፡ በሥጋ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ጉዳት ፡ ያመጡ ፡ ነበር ?

፲፯ ፤ ሰው ፡ ራሱ ፡ አምላክ ፡ ለመኾን ፡ ያሰበውን ፡ ያኸል ፡ ማንን ፡ ይከተል ፡ ጀመር ? ምን ፡ ይከተል ፡ ጀመር ?

፲፰ ፤ ሰው ፤ እግዚአብሔርን ፡ ለመቃወም ፡ ምን ፡ አደረገ ? እግዚአብሔርሳ ፡ ምን ፡ አደረገ ? የእግዚአብሔር ፡ ዕውቀት ፡ ከሰውና ፡ ከመላእክት ፡ ዕውቀት ፡ ያንሳልን ፡ ወይስ ፡ ይበልጣል ?

፲፱ ፤ የቋንቋ ፡ መለያየት ፡ መቼ ፡ ተጀመረ ? እሱስ ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ አመጣ ?



www.ethiopianorthodox.org

፳ ፤ የሰው ፡ ልጆች ፡ ክፉዎች ፡ መናፍስት ፡ የሚያደርጉባቸውን ፡ ትግል ፡ ባየ
ጊዜ ፡ ምን ፡ አደረጉ ?

፳፩ ፤ አባታቸው ፡ ኖኅሳ ፡ የሰው ፡ ልጆችን ፡ በምን ፡ ረዳቸው ? ኖኅ ፡ ስለ
ሰው ፡ ልጆች ፡ የጸለየው ፡ ጸሎት ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ ይ
ኛል ?

፳፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ በኖኅ ፡ ጸሎት ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ምን ፡ አደረገ ? ማንንስ
ላከላቸው ?

፳፫ ፤ መላእክት ፡ እንደ ፡ ታዘዙ ፡ ፈጸሙን ?

፳፬ ፤ ለሰሚዎች ፡ ከባድ ፡ መስሎ ፡ የሚታየው ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ምንድን ፡ ነው
ክብደቱንና ፡ ቅለቱን ፡ ባጭሩ ፡ ግለጽ ።

፳፭ ፤ የሰው ፡ ልጆች ፡ በየሀገራቸው ፡ ከተበታተኑ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ አደረጉ ?

፳፮ ፤ ዕንጨት ፡ ጠርቦ ፡ ድንጋይ ፡ አለዝቦ ፡ ማምለክ ፡ የተጀመረበት ፡ አገር
የት ፡ ነው ? ዘመኑስ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ?

፳፯ ፤ ኢትዮጵያ ፤ የአምልኮትን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ከማን ፡ ወረሰች ? ማንንስ
ስታመልክ ፡ ኖረች ?

፳፰ ፤ በኢትዮጵያ ፡ የኖኅ ፡ ቃለ ፡ ኪዳን ፡ መታሰቢያ ፡ ምንድን ፡ ነው ?

፳፱ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፤ ስንት ፡ ነገሮች ፡ ያስተምረናል ? እነሱስ
ምን ፡ ምን ፡ ናቸው ?

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ፍቅር ፡ የጋራ ፡ ነው ።

፩ ፤ ይዞታችን ፡ የሃይማኖት ፡ ነገር ፡ ሲኾን ፤ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ሃይማኖትና
ፍቅር ፡ እንደ ፡ ዐልጋና ፡ እንደ ፡ ጠገግ ፤ እንደ ፡ እጅና ፡ እንደ ፡ ፍንጅ ፡ የተያያዙ፡የማይ
ለያዩ ፡ መኾናቸውን ፡ ለማስታወስ ፡ ከዚያውም ፡ ዘንድ ፡ በሃይማኖት ፡ የተመሠረተው
የእግዚአብሔርና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍቅር ፡ በየጊዜው ፡ እየጨመረ ፡ የሄደ ፡ መኾኑን፡ ለመ
ግለጥ ፤ ፍቅር ፡ የጋራ ፡ ነው ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ተነሥቼ ፡ ዐሳቤን ፡ እዘረዝራለሁ ፡

፪ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ መጀመሪያ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ እጅ ፡ ቀድሞ ፤ ማለት
ከኢምንት ፡ ፈጥሮ ፡ በጸጋው ፡ አክብሮ ፡ መርጦ ፡ ወደድኩኽ ፡ ወይም ፡ ወደድኳችሁ
ባለ ፡ ጊዜ ፤ እነዚያ ፡ ተመራጮቹ ፡ ፍጡራን ፡ ሊወዱት ፤ ወዳጆቹም ፡ ሊባሉ ፡ ይሞ
ራሉ ፡ እንጂ ፤ ከቶ ፡ ለልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀዶ ፡ አልብሶ ፡ ፈትፍቶ፡አጕርሶ ፡ እጅ
ቀድሞ ፡ ወዳጅ ፡ የኾነው ፡ ፍጡር ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ አልተገኘም ፤ ወደ ፡ ፊትም ፡ አይ
ገኝም ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፲ ።

፫ ፤ እንዲህም ፡ ማለት ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ እሱ ፡ ራሱ ፡ ሀብቱን ፡ ሰጥቶ
ይወድደናል ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ እጅ፡መንሻ ፡ በማቅረብ ፤ ገጸ ፡ በረከት፡ በማግባት
እንደ ፡ ካህናት ፡ የአትርሱኝ ፡ በመስጠት ፤ እንደ፡ሹማምት፡ መታያ ፡ መቅቡጥ ፡ (ጉቦ ፡)



በማብዛት ፤ እንደ ፡ ጠንቋዮች ፡ የአውድ ፡ መግለጫ ፡ የሥር ፡ መማሻ ፡ በማለት ፡ የሚ
ተዋወቁት ፡ የሚወዱት ፡ የሚዛመዱት ፡ ወዳጅ ፤ ዘመድ ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ ነው ።

፬ ፤ ስለዚህ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ወዶ ፡ ከሚያደርገው ፡ ስጦ
ታው ፡ (ሀ) የሀይማኖት ፡ ፈለግን ፤ (ለ) ወረት ፡ የሌለው ፡ ፍቅርን ፤ (ሐ) ማንም ፡ የማይ
ወዳደረው ፡ ስምን ፤ (መ) ቢገፉት ፡ የማይወድቅ ፡ መንግሥትን ፤ (ሠ) ምስጢራዊ ፡
ክህነትን ፤ (ረ) ጓደኛ ፡ የሌለው ፡ ቋንቋን ፤ (ሰ) ድርቅ ፡ የማያሸንፈው ፡ ልምላሜን ፡ አስ
ቀድሞ ፡ ሰጥቶ ፡ ስለ ፡ ወደዳትና ፡ ፍቅሩን ፡ ስለ ፡ ገለጸላት ፤ ኢትዮጵያም ፤ ከቀን ፡ ወደ፡
ቀን ፡ ፍቅሩን ፡ እየጨመረች ፡ በመሄዱዋ ፤ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ተጣብቃ ፡ ትኖራለች ።

፭ ፤ ስለዚህ ፤ እኔ ፡ በልቤ ፡ አምናለሁና ፡ ሞትም ፡ ቢኾን ፡ ሕይወት ፡ መላእክ
ትም ፡ አለቆችም ፡ ኀይላትም ፡ የኾነውም ፡ (ያለው) ፡ የሚኾነውም ፡ (የሚመጣውም) ፡
የበላይም ፡ የበታችም ፡ ሌላም ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፤ ከቶ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ፍቅር ፡ ሊለያት ፡ አይችልም ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፰ ፡ ቍ ፡ ፴፰—፴፱ ።

፮ ፤ እግዚአብሔር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውደዱ ፤ በየጊዜው ፡ የሚያደርግላት ፡ የም
ሕረት ፡ ጕብኝት ፡ የዐይን ፡ ምስክር ፡ ከመኾኑም ፡ በላይ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ብዙ ፡
ማስረጃ ፡ ይገኛል ።

፯ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ጥቅሶች ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በየምዕራፉና ፡ በየክፍሉ፡
ተበታትነው ፡ እንጂ ፤ ካንድ ፡ ቦታ ፡ ተሰብስበው ፡ አይገኙምና ፤ በየተራው ፡ ጠንቅቆ ፡
መመልከት ፡ ነው ።

፰ ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ሀይማኖትዋ ፡ መዝሙር ፡ ፷፰ ፡ ቍ ፡ ፴፩ ፡ የተጻፈውን ፡
ጠቅሰን ፡ እንደ ፡ አስረዳነው ፤ ከዚህም ፡ ስለ ፡ ፍቅሩዋ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ማስረጃ ፡
እንሰጣለን ።

፱ ፤ እናንት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለእኔ ፡ እንደ ኢትዮጵያ ፡ ( ኩሽ) ፡ ልጆች ፡
አይደላችሁም ። አሞጽ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

፲ ፤ ይህ ፡ ጥቅስ ፤ በልዑል ፡ እግዚአብሔርና ፡ በታማኝቱ ፡ አገልጋዩ ፡ በኢትዮ
ጵያ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ብርቱ ፡ ፍቅር ፡ ከዓለም ፡ ኹሉ ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ የማይሽረው ፤
ዘመን ፡ የማይለውጠው ፡ መኾኑን ፡ ያስረዳናል ።

፲፩ ፤ ይህስ ፡ ባይኾን ፤ እስራኤል ፡ የበኵር ፡ ልጄ ፡ ነው ፤ ከምድር ፡ አሕዛብ ፡
ኹሉ ፡ አንተን ፡ ብቻ ፡ ወደድኩ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እናንት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች፤
ለእኔ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ አይደላችሁም ፡ ባላለም ፡ ነበር ።

፲፪ ፤ ኢትዮጵያ ፤ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔርና ፡ ፍቅረ ፡ ቢጽ ፡ የማይለያዩ ፡ መኾናቸ
ውን ፡ ዐውቃ ፡ ገንዘብንና ፡ ራስን ፡ መውደድን ፡ ሳትቀላቅል ፤ ጠንቅቃ ፡ ጠብቃ ፡ ይዛ
ቸው ፡ ትኖራለች ።

፲፫ ፤ ምክንያቱም ፡ አንድ ፡ ባሪያ ፡ ለኹለት ፡ ጌታ ፡ መገዛት ፡ እንደማይቻለው ፤
ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ለእግዚአብሔርና ፡ ለገንዘብ፡መገዛት፡የማይቻል፡ስለ፡ኾነና፡ራስን ፡ መውደ
ድና ፡ ወንድምን ፡ መውደድ ? ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ስለ ፡ ኾኑ፡ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፳፬።

www.ethiopianorthodox.org

፲፬ ፤ ኢትዮጵያ ፤ የሚያየውን ፡ ወንድሙን ፡ የማይወድ ፡ ሰው ፤ የማያየውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዴት ፡ ይወደዋል ፤ ወንድሙን ፡ የሚወድ ፡ ሕግን ፡ ኹሉ ፡ ፈጸመ ፤ የምትወዱኝ ፡ ከኾነ ፡ ትእዛዜን ፡ ጠብቁ ።

« አዲስ ፡ ትእዛዝ ፡ እሰጣችኋለሁ ፤ ርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ትዋደዱ ፡ ዘንድ ፤ እንደ ፡ ወደድኋችሁ ፡ እላንትም ፡ ደግሞ ፡ ርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ትዋደዱ ፡ ዘንድ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቴ ፡ እንደ፡ኾናችሁ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ያውቃል ፤ ርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ፍቅር ፡ ቢኖራችሁ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፴፬-፴፭ ። ም ፡ ፲፭ ፡ ቍ ፡ ፲፪ ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፭ ። በእነዚህና ፡ እነዚህንም ፡ በመሳሰሉ ፡ ትእዛዛት ፤ መሠረት ፤ ፍቅር ፤ ሕግ ፡ ኾና ፡ በዐዋጅ ፡ ከመገለጧ ፡ በፊት ፤ በሕገ ፡ ልቡና ፤ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔርንና ፡ የምትመስላትን ፡ ፍቅረ ፡ ቢጽን ፡ ትፈጽም ፡ ነበረች ።

፲፭ ፤ እንዲሁም ፡ እንደ፡ ዛሬው ፡ ለሰው ፡ እያንዳንዱ ፡ በመኝታ ፡ ጊዜ ፤ የከፈኑን ፡ በምታኽል ፡ በሜትር ፡ የተለካች ፡ ጨርቅ ፡ ( አንሶላ ) ፡ እስክትሰጠውና ፡ በምግብም ፡ ጊዜ ፡ መብሉ ፡ እንደ ፡ ገዳማውያን ፡ መቍነን ፡ በሣህን ፡ ተለክቶለት ፤ በባልና ፡ በሚስት ፡ መካከልም ፡ ቢኾን ፡ መቀላቀል ፡ ሳይኖር ፡ ማነኛው ፡ ሰው ፡ ለየብቻው ፡ መብላት ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፤ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ እንጀራ ፡ ተቋርሶ ፤ አንድ ፡ ልብስ ፡ ተላብሶ ፡ መኖር ፤ ተካፍሎ ፡ መብላት ፤ ተካፍሎ ፡ መጠጣት ፡ ዋና ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነበረ ።

፲፮ ፤ ስለዚህም ፡ ተረት ፤ የሞሰብ ፡ ዳር ፡ ድንበር ፡ የለውም ። መብል ፡ ለኹለት ፡ የኑሮ ፡ ገነት ፤ አብሮ ፡ የበላን ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ አይሽረውም ፤ መብል ፡ አንድ ፡ ለአንድ ፤ የጋኔን ፡ ማዕድ ፤ ብቻውን ፡ የበላ ፡ ብቻውን ፡ ይሞታል ፡ ተብሎ ፡ ይነገራል ።

፲፯ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ እንደ ፡ አጠናችው ፡ ኹሉ ፤ ሰው ፡ ያለውን ፡ ሳይነፍግ ፤ ማነኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የእናት ፡ አገሩን ፡ ሕገኛ ፡ ልማድ ፡ በሙሉ ፡ ልቡ ፡ ተቀባይና ፡ አጽዳቂ ፤ አክባሪና ፡ ጠባቂ ፡ ከመኾኑ ፡ የተነሣ ፤ ኢትዮጵያ ፤ እንግዳ ፡ በመቀበል ፡ ለድኾች ፡ በመራራት ፡ የፈጸመችው ፡ ተግባር ፤ በሰውና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፤ የተቀደሰ ፡ አስታራቂ ፡ መሥዋዕት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታሪክ ፡ ምስክር ፡ ነው ።

፲፰ ፤ ለአንድ ፡ ያሉት ፡ ለኹለት ፡ ይበቃል ፡ እያለች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ትሠራበት ፡ የነበረው ፡ ልማድ ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚወደው ፤ ሀብተ ፡ በረከት ፡ የሚገኝበት ፡ መኾኑን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሲጨነቁና ፡ ሲሰቀቁ ፤ ዐምስት ፡ ዕንጀራ ፡ ቈርሶ ፡ ለዐምስት ፡ ሺሕ ፤ ሰባት ፡ ዕንጀራ ፡ ቈርሶ ፡ ለአራት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ በመስጠቱና ፡ የበሉትም ፡ ከጠገቡ ፡ በኋላ ፤ ከዐምስቱ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ የተረፈ ፡ ፲፪ ፡ ሞሰብ ፡ ሙሉ ፡ እንፍርፋሪ ፡ (ቍራሽ) ፤ ከአራቱ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎችም ፡ የተረፈ ፡ ፯ ፡ ሞሰብ ፡ ሙሉ ፡ ፍትፍት ፡ እንዲነሣ ፡ በማድረጉ ፤ በዚህም ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ያልተደረገ ፡ የማይደረግ ፡ ሀብተ ፡ በረከትን ፡ በማሳየቱ ፤ ወሀቤ ፡ በረከት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ገልጾታል ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፡ ፲፯-፳፩ ። ም ፡ ፲፭ ፡ ቍ ፡ ፴፪—፴፱ ። ፩ ፡ ነገ ፡ ም፡፲፯፡ቍ፡፲፬ ። ፪ ፡ ነገ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ፡፵፪—፵፬ ።



፲፱ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ራሱዋን ፡ ወንድሙዋን ፤ ያለ ፡ አድልዎ ፡ አስተካክላ ፡ በመውደድ ፡ ፍቅረ ፡ ቢጽን ፡ የምትፈጽመውን ፡ ያኽል ፡ ፈጣሪዋን ፡ ከራሱዋ ፡ አብልጣ ፡ ትወድ ፡ ነበር ።

፳ ፤ ስለዚህም ፡ ለገንዘብ ፡ ሲሉ ፡ መሞት ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ የተለመደ ፡ መኾኑን ፡ ተረድቶት ፡ ማንም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወታደር ፤ ቤትን ፡ ንብረትን ፡ እርሻን፡ ልጅን፡ ሚስትን ፡ ወንድምን ፡ እኅትን ፡ አባትን ፡ እናትን ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ የተወ ፡ ኹሉ ፤ በዚህ፡ ዓለም ፡ መቶ ፡ ዕጥፍ ፡ ዋጋን ፤ በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ ይወስዳል ፡ ብሎ ፡ ክርስቶስ ፡ ታላቁን ፡ ተስፋ ፡ ከመስጠቱና ፡ ሊከተለኝ ፡ የሚወድ ፡ ነፍሱን ፡ ይካድ ፡ ብሎ ፡ ጠንካራውን ፡ ዐዋጅ ፡ ከማወጁ ፡ በፊት ፤ ከደሙ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ የኖረው ፡ ሃይማኖቱ ፡ እያስገደደው ፤ ከግል ፡ ሀብቱና ፡ ንብረቱ ፡ ይበልጥ ፤ ለሀገሩ ፡ ለክብሩ ፡ ለሃይማኖቱ ፡ ለውጥ ፡ አድርጎ ፡ ሰውነቱን ፡ በመሠዋት ፡ ያገለግል ፡ ነበር ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ቍ ፡ ፳፬ ። ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፳፱ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ሃይማኖትና ፡ ፍቅር ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ናቸው ? ምሳሌውን ፡ ስጥ ።
፪ ፤ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ ወዳጅነት ፡ ውለታ ፤ ሰው ፡ ይቀድማል ፡ ወይስ ፡ እግዚአብሔር ?
፫ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅነቱ ፡ እንደ ፡ ፍጡራን ፡ ነውን ?
፬ ፤ ኢትዮጵያ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከስጦታው ፡ ምን ፡ ስለ ፡ ሰጣት ፡ ትወደዋለች ?
፭ ፤ ኢትዮጵያን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ሊለያት ፡ የሚችል ፡ አለን ?
፮ ፤ እግዚአብሔር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውደዱ ፡ ምን ፡ ማስረጃ ፡ ይገኛል ?
፯ ፤ አሞጽ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፯ ፡ የተጠቀሰው ፡ ምን ፡ ያስረዳናል ?
፰ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ፍቅረ ፡ ቢጽን ፡ እንዴት ፡ አድርጋ ፡ ጠብቃ ፡ ትኖራለች ?
፱ ፤ አንድ ፡ ባሪያ ፡ ለኹለት ፡ መገዛት ፡ ይቻለዋልን ? ለእግዚአብሔርና ፡ ለገንዘብሳ ?
፲ ፤ ኢትዮጵያ ፤ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ፍቅረ ፡ ቢጽን ፡ ስትፈጽም ፡ ፍቅር ፡ በሕግነት ፡ ተሰጥታ ፡ ነበርን ?
፲፩ ፤ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ ዋናው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ነበር ? ካማርኛ ፡ ምሳሌ ፡ ተመሳሳይ ፡ ማስረጃ ፡ ስጥ ።
፲፪ ፤ ኢትዮጵያ ፤ እንግዳ ፡ ለመቀበሏ ፡ ለድኾች ፡ ለመራራቷ ፡ ምስክሩ ፡ ማነው ?
፲፫ ፤ ክርስቶስ ፡ የገለጸው ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚወደው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልማድ ፡ ምን ፡ ዐይነቱ ፡ ነው ?
፲፬ ፤ ማንም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወታደር ፡ ስለ ፡ አገሩ ፡ ክብርና ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ምን ፡ ያደርግ ፡ ነበር ?

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

ታ ላ ቅ ፡ ስ ም ።

፩ ፡ ስም ፡ ኹሉ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የኾነው ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ተገ ቷል ። ይኸውም ፡ ብርሃኑን ፡ ዕለት ፡ ጨለማውን ፡ ሌሊት ፡ ጠፈርን ፡ ሰማይ ፡ ሰውን አዳም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ጠራው ፡ ማለት ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፭—፰ ። ፭ ፡ ፪ ።

፪ ፤ ከዕለተ ፡ ፍጥረት ፡ በኋላ ፤ ሰዓታት ፡ በዕለታት ፡ ዕለታት ፡ በአውራኅ ፡ አወ ራኅ ፡ በዓመታት ፡ አበው ፡ በውሉድ ፡ እየተባዙ ፡ መሄድ ፡ ከጀመሩ ፡ ወዲህ ፡ ግን ጊዜው ፡ እንደሚሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ከሰውም ፡ የሰውና ፡ የቦታ ስሞች ፡ መገኘት ፡ ጀምረዋል ።

፫ ፤ ምሳሌ ፤ የሰው ፡ ስም ፤ አዳም ፡ ሔዋን ፡ ቃየል ፡ ሴት ፡ ያሬድ ፡ ኖኅ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ እስራኤል ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በጠቅላላው ፤ በግዝረት ፡ በጥምቀት በሹመት ፡ የሚወጣ ፤ በግዝረት ፤ ይስሐቅ ፡ ዮሐንስ ። በጥምቀት ፤ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ። በሹመት ፤ ጴጥሮስ ፡ ታዴዎስ ፡ ባ ልዮስ ፡ አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ምኒልክ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፬ ፤ የሀገር ፡ ስም ፤ ኤዶም ፡ ( ኤደን ) ፡ አራራት ፡ (ጥ) ፡ ባቢሎን ፡ ነነዌ ፡ ኤፍ ራታ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፭ ፤ አወጣጡ ፡ ግን ፤ በትንቢት ፡ ወይም ፡ በመታሰቢያነት ፡ ነው ።

፮ ፤ በትንቢት ፡ ሲወጣ ፤ ለብዙዎች ፡ አባት ፡ አደርግሀለኹና ፡ በዘርኽም ፡ አሕ ዛብ ፡ ኹሉ ፡ ይባረካሉና ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አብርሃም ፡ ትባላለህ ፡ እንጂ ፤ አብራም አትባልም ። ዘፍ ፡ ፲፯ ፡ ፭ ።

፯ ፤ በመታሰቢያነት ፡ ሲወጣ ፤ በኤፍራታ ፤ ኤፍራታ ፡ በእስክንድር ፡ እስክን ድርያ ፡ ፍኖተ ፡ ሰላም ፡ ይላል ።

፰ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ስያሜ ፡ ከመታሰቢያ ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ በቤቴል ፡ አንጻር ይጠራል ። ቤቴል ፡ ማለት ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ኢትዮጵያ ማለት ፡ ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፳፰ ፡ ቍ ፡ ፲፱ ።

፱ ፤ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከመጀመሪያዎቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ነገሥታት ፡ ፳፯ኛ ኾኖ ፡ በነገሠው ፡ ንጉሥ ፤ በኢትዮጲስ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተብላለች ፡ ብለው ፡ ይተር ካሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ማን ፡ ትባል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ማስረጃ ፡ አልሰጡም ። ምክንያቱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መታሰቢያ ፡ የሰው ፡ መታሰቢያ ፡ አድርጎ ፡ ለመለ ወጥ ፡ የሚያስችል ፡ በቂ ፡ ነገር ፡ ባለመገኘቱ ፡ ነው ።

፲ ፤ ወደ ፡ እውነተኛውስ ፡ መንገድ ፡ ስንመለስ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ መታሰቢ ያነቱ ፡ ኢትዮጵያ ፤ (በጊዜው ፡ ኹሉ ፡ ስም ፡ አጠራሬ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡) እያለች ፡ በጸሎት ፡ በአምልኮት ፡ የምትጠራው ፤ የእግዚአብሔር ፡ (አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡) ብቻ ፡ መኾኑን ፡ ማወቅ ፡ ነው ።



፲፩ ፤ ስምነቱንም ፡ ስንመረምር ፤ ትርጓሜው ፤ ኢ ፡ ማለት ፡ እግዚአብሔር ፡ ት ፡ ማለት ፡ ታው ፤ ትጉህ ፡ አብ ፤ ዮ ፡ ማለት ፤ ዮድ ፡ የማን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፤ ጵ ፡ ማለት ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያ ፡ ማለት ፤ ያንዱ ፡ አምላክ ፡ የአብ ፡ የወልድ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አገር ፡ ማለት ፡ ኹኖ ፡ እናገኘዋለንና ፡ የፊደላትን ፡ ትርጓሜ ፡ ከመ ሠረታዊ ፡ ቋንቋው ፡ ከግእዝ ፡ መርምረን ፡ እንረዳ ።

፲፪ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ በሦስት ፡ አካላት ፤ በአንድ ፡ መለኮት ፡ ሲሠለስ ፡ ሲቀ ደስ ፡ የነበረ ፡ ያለ ፡ የሚኖር ፡ የአንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ መታሰቢያ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፤ ዘመን ፡ ሳይለውጠው ፤ ጊዜ ፡ ሳይሽረው ፤ በክብር ፡ ላይ ፡ ክብርን ፡ በታሪክ ፡ ላይ ፡ ታሪክን ፡ እየጨመረ ፡ ይኖራል ።

፲፫ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የተሰመየ ፡ (የተሰየመ) ፤ መኾ ኑን ፡ ለመረዳት ፡ የሚፈልግ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በኹለትና ፡ በሦስት ፡ ምስክር ፡ ይጸናልና ፤ አን ደኛ ፡ ወደ ፡ መሠረታዊ ፡ ቋንቋው ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፤ ኹለተኛ ፡ ለኖኅ ፡ የማለለትን ፡ መሐላ ፡ ለማሰብ ፤ ምሕረቱንም ፡ ለመፈጸም ፡ እግዚአብሔር ፡ በደመና ፡ ወደሚገልጸው ፡ ቀስት ፤ ሦስተኛ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኖኅ ፡ አምልኮት ፡ ጸንታ ፡ አማላጅነቱም ፡ ዘመን ፡ የማይሽረው ፡ መኾኑን ፡ አምና ፡ ለኖኅ ፡ ስለ ፡ ማለ ፤ ለልጆቹ ፡ ሊያደርግላቸው ፡ የተናገረውን ፡ ምሕ ረቱን ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ እንዳያርቅባት ፡ ለአምልኮቷ ፡ ምስክር ፡ አድርጋ ፤ በእግዚአብ ሔር ፡ ፊት ፡ ዘወትር ፡ የምታውለበልበውን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ይመልከት ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፱ ፡ እስከ ፡ ፲፰ ።

፲፬ ፤ ስም ፡ ወደ ፡ ግብር ፡ ይመራል ፡ እንደሚባለው ፤ ኢትዮጵያ ፡ ስሟ ፡ ከአም ልኮቷ ፡ የተመሠረተ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፤ በቅዱስ ፡ አምልኮት ፡ ላይ ፡ የተመሠ ረተው ፡ ቅዱስ ፡ ስሟ ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ግብር ፡ ስለሚመራት ፡ አረንጓዴ ፡ ብጫ ፡ ቀይ ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማዋን ፡ በነገሥታቷና ፡ በጦር ፡ ሰራዊቶቿ ፡ ፊት ፡ እያ ስቀደመች ፤ ፈጣሪዋን ፡ አብ ፡ ወልድ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ እያሰበች ፤ ንጹሕ ፡ ሃይማ ኖቷን ፡ በሥራ ፡ ገልጻ ፡ እየመሰከረች ፤ በምትሰለፍበትና ፡ በምትሰማራበት ፡ ቦታ ፡ ኹሉ ፤ በባቢሎን ፡ በሰናዖር ፡ ( ሰናዓር ) ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ለኀጢአት ፡ የተሠራውን ፡ ግንብ ፡ በኀ ይለ ፡ ነፋስ ፡ ያፈረሱ ፤ የዐመፀኞችን ፡ ዐሳብ ፡ የደመሰሱ ፡ ሥላሴ ፤ ድል ፡ አድራጊነ ትን ፡ ከዘውዱዋ ፡ ጋራ ፡ አቀዳጅተዋታል ።

፲፭ ፤ በዚህ ፡ ሥልጣን ፡ ሥጋዊ ፡ ጠላትንና ፡ መንፈሳዊ ፡ ጠላት ፡ ዲያብሎስን ፡ በእጁዋ ፡ ጨብጣበት ፤ በእግሯ ፡ ረግጣበት ፡ ትኖራለች ።

፲፮ ፤ በማን ፡ ሥልጣን ፡ ይህን ፡ የድል ፡ ሥራ ፡ ትሠሪያለሽ ፡ ብሎ ፡ የሚጠይ ቃት ፡ ቢኖር ፡ ኀይሌ ፡ ጕልበቴ ፡ ስሜም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፤ ኹሉን ፡ በሚችል ፡ በሥላሴ ፡ ኀይል ፡ ኹሉን ፡ እሠራለሁ ። የማን ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብረት ፡ ኀይለ ። የማን ፡ እግዚአብሔር ፡ አልዐለተኒ ። የማን ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብረት ፡ ኀይለ ። ብላ ፡ ትመልስ ለታለች ፡ መዝ ፡ ፻፲፯ ፡ ፲፭—፲፯ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፯ ፤ ይህን ፡ ስም ፡ በጠራን ፡ ጊዜ ፤ ሳይረዱት ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስ
የሌለ ፡ በሌላ ፡ ቋንቋ ፡ የማይገኝ ፡ እንግዳና ፡ አዲስ ፡ ስም ፡ ያመጣን ፡ አስመስለው ፡ የ
ያወሩ ፡ ሐሜተኞች ፡ አሉ ።

፲፰ ፤ እጅግም ፡ የሚያስደንቀው ፤ አንደኛ ፡ ልብ ፡ ኹለተኛ ፡ ዐይን ፡ ሦስተ
መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ አሉን ፡ እንመረምራለን ፡ እናስተውላለን ፡ እናነባለን ፡ እያለ
ሥላሴ፡የተባለው ፡ ስም፡ ከጥንታዊው ፡ የባቢሎናውያን ፡ አረመኔነት ፡ አምልኮት ፡ የ
መሠረት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ የለም ፡ ብለው ፡ ሥላሴ ፤ በነ
ያት ፡ ያልታወቀ ፤ በሐዋርያት ፡ ያልተሰበከ ፤ አስመስለው ፡ ማውራታቸው ፡ ነው ።

፲፱ ፤ እንዲሁም ፤ ሌዋውያን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከገቡበት ፡ ከቀዳማዊ ፡ ም
ልክ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፤ ታላቁ ፡ ሊቀ ፡ ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ እስከ ፡ ተነሣበት ፡ እስከ ፡ አጼ
ገብረ ፡ መስቀል ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ትምህርት ፡ ቤት
ዕብራይስጢና ፡ ግእዝ ፡ ተባብረው ፡ ተጣምረው ፡ የኖሩትን ፡ ያኽል ፡ ዛሬ ፡ ዕብራ
ስጡ ፡ ጠፍቶ ፡ ግእዙ ፡ ብቻውን ፡ ቀርቶ ፤ ለዚያውም ፤ ወራት ፡ ብሶት ፤ ቀን፡ጥሎት
አባቱ ፡ እንደ ፡ ሞተበት ፡ ልጅ ፡ ብቻውን ፡ ሲንገላታ ፡ ቢያዩት ፤ አሪተ ፡ ግእዝ ፤ ከአሪተ
ሌዋውያን ፡ የተለየ ፤ ዐዋቂዎችም ፡ እልም ፡ ድርግም ፡ ብለው ፡ የጠፉ ፡ መስሏቸው
በዕብራስጢው ፡ የሆዋ ፡ ( የሆባ ) ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፤ ሦስትነትን
የሚያመለክት ፡ ቃል ፡ የለም ፡ እያሉ ፡ በክርስትና ፡ ላይ ፤ እስልምናንና ፡ ይሁዳዊ ፡ እ
ነትን ፡ ቀላቅለው ፡ በማስተማር ፡ በትምህርት ፡ ያልጐለመሱ ፤ በዕውቀት ፡ ያልታደሰ
ልጆችን ፡ ማሳሳታቸው ፡ ነው ።

፳ ፤ ለእነሱ ፡ ስለ ፡ መሰላቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ለኢትዮጵያስ ፡ በአንድነቱ፡ም
ታዌ ፤ በሦስትነቱ ፡ ርባዔ ፡ ሳትቀላቅል ፡ የምታምነው ፡ የምታመልከው ፡ የምትሰ
ድለት ፡ የምትገዛለት ፡ ፈጣሪዋ ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ እስጢፋኖስን ፡ ጳ
ሎስን ፡ ቄርሎስን ፡ ዮሐንስን ፡ የመሰሉ ፡ እንደ ፡ መዶሻ ፡ የሚቀጠቅጡ ፤ እንደ ፡ ሠም
የሚያቀልጡ ፤ ሊቃውንትን ፡ ከልጆቹዋ ፡ አላሳጣትም ።

፳፩ ፤ ስለዚህ ፤ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፤ ስለ ፡ አንድነትና ፡ ስለ ፡ ሦስ
ነት ፤ ከዕብራይስጥ ፡ የጠቀሱት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ተጽፏልና ፡ አንባቢዎች ፡ ልብ፡አ
ርጋችሁ ፡ ተመልክታችሁ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖትና ፡ በሐሜተኞች ፡ ወሬ
መካከል ፡ የእውነተኛ ፡ ምስክርነት ፡ ቃላችኹን ፡ እንድትሰጡ ፡ ትለመናላችሁ ።

፳፪ ፤ ከዕብራይስጥ ፡ የተጠቀሱ ፡ ቃላት ። ኤል ፤ ኤሉሃ ፤ ኤሎሄ ፤ ኤሎሂም
አዶን ፡ አዶኒ ፡ አዶናይ ፡ አዶኒም ፡ የሆዋ ፡ ሻዳይ ፡ ባራእ ፡ አማር ፡ አቴም ፡ ሱሩና ፡

ከእነዚህም ፡ ኤል ፡ ኤሎሃ ፡ ኤሎሄ ፡ ኤሎሂም ፡ አዶን ፡ አዶኒ ፡ አዶናይ ፡ አ
ኒም ፡ የሆዋ ፡ ሻዳይ ፡ ስሞች ። ባራእ ፡ አማር ፡ አቴም ፡ ሱሩና ፡ አንቀጾች ፡ ናቸው ።

ሲነገሩም ፡ ኤል ፡ ኤሎሃ ፤ አምላክ ፤ ፈጣሪ ። አዶን ፡ እግዚእ፡ጌታ፡እንደ፡ማለት
በነጠላ ። ኤሎሂም ፤ አማልክት ፡ አምላኮች ። አዶናይ ፤ አዶኒም ፡ አጋእዝት ፡ ጌቶች
እንደ ፡ ማለት ፡ በብዛት ። ባራእ ፡ ፈጠረ ፡ ፈጠረ ። አማር ፡ ይቤ ፡ አለ ፤ እንደማለት፡በ



ጠላ ። አቴም ፤ አንትሙ ፤ እናንተ ፤ ሱሩና ፤ ገሐሡ ፡ ግቡ ፤ እንደ ፡ ማለት ፡ በብዛት ። ኤሎሄ ፤ አምላኪየ፡አምላኬ ። አዶኒ ፤ እግዚእየ ፡ ጌታዬ ፤ አዶናይ ፤ አጋእዝትየ ፡ ጌቶች ፡ እንደማለት ፡ በዝርዝር ፡ ይነገራሉ ። እነዚህ ፡ አዶናይ ፤ ኤሎሂም ፤ የተባሉ ፡ ስሞች ፡ ለፈጣሪ ፡ ሲነገሩ ፤ በአንድ ፡ አንቀጽ ፤ ባራእ ፤ ኤሎሂም ፡ አማር ፡ አዶናይ ፡ ተብለው ፡ ይነገራሉ ። ትርጓሜውም ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዓለምን ፡ ፈጠረ ፡ አለ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እግዚአብሔር ፡ በአካል ፡ ሦስት ፤ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ መኾኑን ፡ ያስረዳል ።

፳፫ ፤ የሆዋ ፤ ሻዳይ ፤ የተባሉት ፡ ስሞች ፤ እግዚአብሔር ፡ በባሕርይ ፡ ስሙ ፡ የሚጠራባቸው ፤ አንድነቱ ፡ የሚገለጽባቸው ፡ ስሞች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በብዛት ፡ አይነገሩም ። ትርጓሚያቸውም ፤ የሆዋ ፡ ማለት ፡ እግዚአብሔር ፡ ገባሬ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡ ሰማይን ፡ ምድርን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ። ሻዳይ ፡ ማለት ፡ ከሃሌ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥሉጥ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ። ኹሉን ፡ የሚችል ፤ በኹሉ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፳፬ ፤ እንግዲህ፡ኤሎሂም ፡ አዶናይ ፡ በአካሉ ፡ በሦስትነቱ ፤ የሆዋ ፡ ሻዳይ ፡ በባሕርዩ ፡ በአንድነቱ ፡ የሚጠራባቸው ፡ ስሞች ፡ መኾናቸውንና፡ትርጓሜያቸውም ፤ ኤሎሂም ፡ አምላክ ፤ አዶናይ ፡ አጋእዝት ፤ የሆዋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገባሬ ፡ ኵሉ ። ሻዳይ ፡ እግዚአ ፡ ኵሉ ፡ ዘሀሎ ፡ ወይሄሉ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማወቅ ፡ ነው ።

፳፭ ፤ ኤሎሂምና ፡ አዶናይ ፡ እንደ ፡ ትርጓሜያቸው ፡ ኹኔታ፡አንቀጽ ፡ ለውጠው፡ በብዛት፡አንቀጽ ፤ አቴም ፡ አንትሙ ፤ ሱሩና ፡ ገሐሡ ፤ በተባሉት ፡ አናቅጽ ፡ በተነገሩ፡ ጊዜ ፡ ለመላእክት ፡ ለካህናት ፡ ይነገራሉና ፤ በአንድ ፡ አንቀጽ ፡ ሲነገሩ ፡ ለፈጣሪ ፤ በብዛት ፡ አንቀጽ ፡ ሲነገሩ ፡ ለፍጡራን ፡ የሚነገሩ ፡ መኾናቸውን ፡ ጠንቅቆ ፡ በሕግ፡ ማወቅ ፡ ነው ። የቋንቋው ፡ አካሄድ ፡ ባጭሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ በሦስት ፡ ልሳን ፡ በግእዝ ፡ ፊደል ፡ እናሳያለን ።

| ፳፮ ፡ ዕብራይስጥ ። | ግእዝ ። | አማርኛ ። |
|---|---|---|
| ባራእ ፡ | ፈጠረ ፡ | ፈጠረ ። |
| ኤሎሂም ፡ | አምላክ ፡ | አምላክ ። |
| አማር ፡ | ይቤ ፡ | አለ ። |
| አዶናይ ፡ | አጋእዝት ፡ | ሥላሴ ። |
| የሆዋ ፡ | እግዚአብሔር ፡ | እግዚአብሔር ፡ ያንድነት፡ስም ። |
| ሻዳይ ፡ | ከሓሊ ፡ | ኹሉን ፡ ቻይ ። |
| ኤሎሄ ፡ | አምላኪየ ፡ | አምላኬ ። |
| ላማ ፡ | ለምንት ፡ | ለምን ። |
| ሰበቅታኒ ፡ | ኀደገኒ ፡ | ተውኸኝ ። |

ይኸ ፡ ለአምላክ ፡ ሲነገር ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፯ ፡ ለፍጡራን ፡ ሲነገሩ ፡ ግን ፡ በብዛት ፡ አንቀጽ ፡፡

| ዕብራይስጥ ፡ | ግእዝ ፡፡ | አማርኛ ፡፡ |
|---|---|---|
| ኤሎሂም ፡፡ | አማልክት ፡ | አማልክት ፡፡ |
| አቴም ፡፡ | አንትሙ ፡ | እናንተ ፡ ናችሁ ፡፡ |
| አዶናይ ፡፡ | አጋእዝትየ ፡ | ጌቶቼ ፡፡ |
| ሱሩና ፡፡ | ገሐሡ ፡ | ግቡ ፡ እያለ ፡ ይነገራል ፡፡ |

፳፰ ፤ እዚህ ፡ በአጭሩ ፡ የዘረዘርነውን ፡ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ ዕብራይስጥን ፡ ከግእዝ ፡ አስማምተው ፡ በዚያውም ፡ የምስጢረ ፡ ሥላሴን ፡ ነገር፡ አጕልተው፡ አስፍተው ፡ ጽፈውታልና ፡ ገጽ ፡ ፶፱ ፡ እስከ ፡ ፷ ፡ ተመልከት ፡፡

፳፱ ፤ እንግዲህ ፡ የምስጢረ ፡ ሥላሴን ፡ ነገር ፡ በቦታው ፡ እናመጠዋለንና ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ነገራችን ፡ እንመለስ ፡፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ እንደ፡ ተናገርነው ፤ ኢትዮጵያ፡ሦስትነትን ፡ ካንድነት ፤ አንድነትን ፡ ከሦስትነት ፡ ሳትለያይ ፤ ተጠንቅቃ ፡ ተጠብቃ ፡ በምታመልከው ፡ ስም ፡ የተጠራች ፡ አገር ፡ ናት ፡ እንጂ ፤ በፍጡራን ፡ ስም ፡ የተጠራች ፡ አይደለችም ፡፡

፴ ፤ ኢትዮጵያ ፤ እሱዋ ፡ በፈጣሪዋ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ መጠራቷ ፡ መጠን ፤ ይህንኑ ፡ ስም ፡ ትምህርት ፡ አድርጋ ፡ ለመስጠት ፤ ልጆቿንም ፡ በሱዋ ፡ ስም ፡ ጦቢያው ፡ ጦቢያ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እያለች ፡ ትጠራለች ፡፡

፴፩ ፤ ኢትዮጵያ ፤ በኢትዮጲስ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተብላለች ፡ የሚለው ፡ ታሪክ፤ ከዘመነ ፡ ካም ፡ ጀምሮ ፡ ከሳባውያን ፡ ነገሥታት ፡ ፭ኛ ፡ ኾኖ ፡ የነገሠው ፡ ኢትዮጲስ ፡ የተባለው ፡ ንጉሥ ፡ እስከ ፡ ነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ነገሥታት ፡ የነገሡባትን ፤ ብዙ ፡ ዘመናተ ፡ መንግሥት ፡ ያሳለፈችውን ፡ አገር ፡ ያለ ፡ ስም ፡ አስቀርቷታል ፡፡

፴፪ ፤ ስለዚህ ፡ አንደኛ ፡ ኢትዮጲስ ፡ የተባለው ፡ ንጉሥ ፡ ከመንገሡ ፡ በፊት ፡ ማን ፡ ትባል ፡ ነበር ? ብሎ ፡ ለሚጠይቅ ፡ መልስ ፡ ከማጣት ፤ ኹለተኛ ፡ ለዘለዓለም ፡ ክብር ፡ ኾኗት ፡ የሚኖረውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በፍጡራን ፡ ስም ፡ ለመለወጥ ፡ ከመጣጣር ፤ በጕላው ፡ በተረዳው ፡ ነገር ፤ ኢትዮጵያ ፡ በምታመልከው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የአምላክ ፡ አገር ፡ ተብላ ፡ ትጠራለች ፤ ልጆቿንም ፡ በስሟ ፡ ትጠራለች ፤ ማለት ፡ ይበልጣል ፡፡ ስለዚህም ፡ ልጆቿ ፡ በእናታቸው ፡ ስም ፤ ጦቢያው ፡ ጦቢያ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እየተባሉ ፡ ይጠራሉ ፤

## ጥ ያ ቄ ፡፡

፩ ፤ ስም ፡ መጀመሪያ ፡ ከማን ፡ ተገኝቷል ? ምሳሌ ፡ ስጥ ፡፡
፪ ፤ ሰው ፡ መብዛት ፡ ከጀመረ ፡ ወዲህሳ ፡ ስሞች ፡ ከማን ፡ ይገኙ ፡ ጀመር ?
፫ ፤ ምሳሌውን ፡ ለይተህ ፡ ለይተህ ፡ ስጥ ፡፡
፬ ፤ የግዝረት ፡ የጥምቀት ፡ የሹመት ፡ ስም ፡ እንዴት ፡ ያለው ፡ ነው ?
፭ ፤ የሀገር ፡ ስም ፡ የሚወጣው ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ ነው ?
፮ ፡ የትንቢትና ፡ የመታሰቢያ ፡ ስም ፡ እንዴት ፡ ያለው ፡ ነው ?



፯ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ስያሜ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ነው ? ማነንስ ፡ ይመስላል ?
፰ ፤ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ ምን ፡ ይላሉ ?
፱ ፤ ከኢትዮጲስ ፡ በፊት ፡ ማን ፡ ትባል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አስረድተዋልን ? ምክንያቱስ? እውነተኛው ፡ ነገርስ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፲ ፤ ስምነቱን ፡ ስንመረምር ፡ ምን ፡ ኾኖ ፡ እናገኘዋለን ? ትርጓሜውስ ፡ በማነኛው ፡ ቋንቋ ፡ ይገኛል ?
፲፩ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለማወቅ ፡ የሚፈልግ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይገባዋል ?
፲፪ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ ወደ ፡ ግብር ፡ ስለሚመራት ፡ ምን ፡ ታደርግ ፡ ነበር ? በዚህስ ፡ ምን ፡ አግኝታበታለች ?
፲፫ ፤ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ ይጠቅማታል ?
፲፬ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ሥልጣኗ ፡ ለሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ምን ፡ ትመልሳለች ?
፲፭ ፤ ሐሜተኞች ፡ የሥላሴን ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ይላሉ ?
፲፮ ፤ ከሌዋውያን ፡ እስከ ፡ ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ዘመን ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ ትምህርት ፡ ምን ፡ ይደረግ ፡ ነበር ? ዛሬሳ ?
፲፯ ፤ ሥላሴን ፡ የሚክዱ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ ያወራሉ ? ምን ፡ ያስተምራሉ ?
፲፰ ፤ ከዕብራይስጥ ፡ የተጠቀሱ ፡ ቃላት ፡ ማን ፡ ማን ፡ ናቸው ? ልዩነታቸውስ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፲፱ ፤ ለፈጣሪና ፡ ለፍጡር ፡ ሲነገሩ ፡ አገባባቸው ፡ እንደ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፳ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በፍጡር ፡ ስም ፡ ተጠርታለችን ?

## ምዕራፍ ፡ ፰ ፡፡

## ገናና ፡ መንግሥት ፡፡

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፤ ጥንቱን ፡ ሰውን ፡ በመልኩና ፡ በምሳሌው ፡ ሲፈጥረው ፤ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ለሚበሩትና ፡ ለሚሽከረከሩት ፤ በባሕርና ፡ በየብስ ፡ ለሚንቀሳቀሱት ፤ ከሚስቱም ፡ ጀምሮ ፡ ለቤተ ፡ ሰብእ ፡ ኹሉ ፡ የጸጋ ፡ ገዥ ፡ አድርጎ ፡ ፈጥሮታል ፡፡ ማስረጃውም ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ተስፋፍቶ ፡ ይገኛል ፡፡ ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፮—፴ ፡፡ መዝ ፡ ፰ ፡ ቍ ፡ ፭—፱ ፡፡ ዘፍ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ፡፡ የሹመቱም ፡ ዐይነት ፡ መንግሥት ፡ ክህነት ፡ ተብሎ ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ ይመደባል ፡፡

፪ ፤ ክህነት ፤ መብቱም ፡ ቅጣቱም ፡ መንፈሳዊውን ፡ የተደገፈ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ በዐይን ፡ ከሚታየው ፡ የማይታየው ፡ ሥራው ፡ ይበልጣል ፡፡ የሐዋ ፡ ሥራ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፩—፲፩ ፡፡ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፯—፲፪ ፡፡

፫ ፤ መንግሥት ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰው ፡ ልጆች ፡ ለመዓትም ፡ ኾነ ፡ ለምሕረት ፤ ለአስፈላጊው ፡ ሥራ ፡ ታማኞች ፡ የኾኑትን ፡ መርጦ ፤ ለቤቱ ፡ መጋቢ፡ባደረጋቸው ፡ ነገሥታት ፡ አድሮ ፤ ሥጋዊውን ፡ ዓለም ፡ የሚያስተዳድርበት ፤ ሥጋዊውን ፡ መሥመር ፡ የተከተለ ፡ በመኾኑ ፤ መብቱም ፡ ቅጣቱም ፡ ግልጽ ፡ ነው ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፬ ፤ እንዲህም ፡ ማለቴ ፤ የያዝኩት ፡ መሥመር ፤ የምድራዊውን ፡ መንግሥት
ነገር ፡ የተከተለ ፡ በመኾኑ ፡ ምድራዊውን ፡ ኹኔታ ፡ ስገልጽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሰማይ
ምድርን ፤ በውስጣቸውም ፡ የሚገኙትን ፡ ኹሉ ፡ የሚታየውንና ፡ የማይታየውን፡ ከሰ
ይና ፡ ከምድር ፡ ውጪም ፡ ቢኾን ፤ የወሰን ፡ ክልል ፡ የዘመን ፡ ልክ ፡ መጀመሪያና
መጨረሻ ፡ በሌለበት ፡ ሥልጣን ፡ ኹሉን ፡ ፈጥሮ ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ብቻ ፡ የሚወሰን ፡ ኾኖ ፤ እሱም ፡ መንግሥቱም ፡ ረቂቃን፡መኾናቸው
መካዶ ፡ አይደለምና ፡ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ እንዳትሳሳት ።

፭ ፤ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ሥረ ፡ ነገራችን ፡ እንመለስ ። ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ አ
ምን ፡ ነቢይ ፡ ካህን ፡ ንጉሥ ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ሾመው ፤ ምንም ፡ እንኳን ፤ ከቃዔል
ልጆች ፤ ቱባልቃይን ፡ የተባለው ፡ የጀመረው ፡ የማዕድን፡ሥራ ፤ ተስፋፍቶ ፤ ዘውድን
ሉልን ፡ በትረ ፡ ወርቅን ፡ የመሳሰሉት ፡ የመንግሥት ፡ መሣሪያዎች ፡ ተዘጋጅተው፡ባ
ገኙም ፤ አበው ፤ አንደኛ ፡ ለልጆቻቸው ፤ ኹለተኛ ፡ ለክፍለ ፡ ሀገራቸው ፤ በጠቅላ
ውም ፤ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፤ በራሪውን ፡ ተሽከርካሪውን፡ ተላዋሹን ፡ ተንቀ
ቃሹን ፡ የሚገዙ ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፰ ። ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፩—፫

፮ ፤ በዚህ ፡ መሠረት ፤ የሰው ፡ ልጆች ፡ ከአዳም ፡ በዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ት
ልድ ፡ ተለያይተው ፡ በየአገራቸው ፡ መንግሥት ፡ እስኪያቋቁሙ ፡ ድረስ ፤ ገዢዎች
አበው ፡ ነበሩ ።

የዛሬው ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ መንግሥት ፤ ከካም ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፤ ከኩሽ ፡ ልጅ
ከስመ ፡ ጥሩው ፡ ከናምሩድ ፤ በባቢሎን ፡ ተጀምሮዋል ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፯—፲ ።

፯ ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ከአዳም ፡ በኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሰማኒያ ፡ ዐምስት
ዓመት ፤ በተደረገው ፡ የምድር ፡ ክፍያ ፡ ካምና ፡ ልጆቹ ፡ ወደ ፡ ክፍለ፡ሀገራቸው፡ሲገ
የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ በመሠረቱ ፡ እያሳደጉትና ፡ እያስፋፉት ፡ ስለ ፡ ሄዱ፤ከዚ
ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ መብቱ ፡ ሳይቀነስ ፤ ሥልጣኑ ፡ ሳይደመሰስ ፤ ሕጉ ፡ ሳይጣስ ፤ ፩ሺ፯
፷፰ ፡ ዘመን ፡ ሠርቶ ፡ እነሆ ፡ ደርሰንበታል ።

፰ ፤ ከላይ ፡ እንደተናገርነው ፡ እስከ ፡ ናምሩድ ፡ ዘመን ፡ የነበሩ፡አባቶች ፤ መ
ቱን ፡ ይዘው ፡ ይሠሩ ፡ ይቀጡ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፤ የሥልጣናቸው ፡ ልዩ ፡ ሥጋዊ ፡ ም
ክት ፡ አልነበረውም ። በኋላ ፡ ግን ፡ የማዕድን ፡ ሥራ ፡ እየተስፋፋ ፡ ሄደ ። በናምሩድ
ዘመን ፡ የበላይነትን ፡ ላገኘው ፡ ሰው ፤ የሥልጣን ፡ ምልክቶች ፡ የሚኾኑ ፡ ዘውድና
በትረ ፡ መንግሥት ፤ ጋሻና ፡ ጦር ፤ ሌሎችም ፡ መሣሪያዎች ፤ እንዲሁም ፡ ጋሻጃግ
ዎችና ፡ አጃቢዎች ፡ ተለይተዋል ።

፱ ፤ ነገደ ፡ ካም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከገቡ ፡ ጀምሮ ፤ አግዓዝያን፡እስከ ፡ ተባሉት
ሳባውያን ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፤ በዚሁ ፡ ሲሠራ ፡ ቈይቷል ። አግዓዝያን ፡ የተባሉት
ሳባውያን ፡ አርበኞች ፤ ጠላትን ፡ አሸንፈው ፤ መንግሥቱን ፡ ከወረሱ ፡ ጀምሮ ፤ የመ
ግሥት ፡ መዓርጋትና ፡ ስሞች ፡ ተለይተው ፤ ንጉሥ ፡ መባልና ፡ አጼ ፡ መባል ፡ ተጀ
ሮዋል ። ልዩነቱም ፡ ንጉሥ ፤ ልዑላን ፡ መሳፍንትንና ፡ መኳንንትን ፡ የሚያዝ ፡ ሲኾን



ዘውድ ፡ ጭኖ ፤ በቀኝ ፡ እጁ ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ በግራ፡እጁ፡ሉል፡ጨብጦ ፤ አጼ ፡ የሚ
ባለው፡ነገሥታቱን፡ይገዛል ፤ ያዝዛል ። በአጠራርም፡አጼ ፡ ጃንሆይ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

፲ ፤ አጼ ፡ ማለት ፤ አርዐደ ፤ ጸብአ ፤ ብሎ ፡ አርዓዲ ፡ ጸባኢ ፤ አንቀጥቃጭ ፡ አሸ
ባሪ ፡ ጦረኛ ፡ ቀስተኛ ፡ ጀግና ፡ ወታደር ፤ ተብሎ ፡ የሚጠራበት ፡ የግርማ ፡ ስሙ ፡ ነው ።
በግርማ ፡ የሚገለጽበት ፡ ልብሰ ፡ መንግሥቱም ፤ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ አርድ፡ አንቀጥቅጥ፡
ይባል ፡ ነበር ።

፲፩ ፤ ጃንሆይ ፡ ማለት ፤ በዘመን ፡ ብዛት ፡ ፊደሉ ፡ ተለውጦ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ዳን ፡
ሆይ ፡ ማለት ፡ ነው ። ትርጓሜውም ፡ ዳንኤል ፡ እንደ፡ማለት ፤ ዳን ፤ ዳኛ ፡ ሆይ ፤ ህልው፡
እግዚአብሔር ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የነበረ ፤ ዓለሙን ፡ አሳልፎ ፡ የሚኖር ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ የሰጠኝ ፡ ዳኛ ፤ የእግዚአብሔር ፡ እንደራሴ ፡ ተብሎ ፡ በፈራጅነቱ ፡ የሚጠራ
በት ፡ ስም ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ ገል
ጠውታል ። ኹለተኛም ፡ በፈራጅነቱ ፡ ዐይን ፡ እጅ ፡ እግር ፡ መቅጣት ፡ የሚችል፡ስለ ፡
ኾነ ፤ ኀያል ፡ ተብሎ ፡ ይተረጐማል ፤ ዳን ፡ ማለት ፡ ኀያል ፡ ማለት ፡ ነውና ።


፲፪ ፤ አንድ ፡ አንድ ፡ ተራኪዎች ፡ አጼ፡ መባልን ፤ ዕጼ ፡ ከተባለው፡ቃል፡የመጣ፡
ነው ፡ ሲሉ ፤ ጃንሆይ ፡ መባል ፡ ደግሞ ፤ በዳር ፡ አገር ፡ የነበሩ ፡ ገበሬዎች ፤ ዝኖን ፡
የተባለው ፡ የበረሃ ፡ እንስሳ ፤ አዝመራቸውን ፡ ሊያጠፉ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤ በመለማ
መጥ ፡ የሚያቀርቡለት ፡ የቁልምጫ ፡ ስም ፡ ነበረ ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ለነገሥታት ፡ ኾኖዋል፡
ብለው ፡ በቃል ፡ ሲተርኩ ፤ ግማሾቹ ፡ ደግሞ ፤ ጅን ፡ ከተባለው ፡ የጋኔን ፡ ስም ፤ ጅኒ ፡
እንደ ፡ ማለት ፡ የተወረሰ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በአፍም ፡ በመጽሐፍም ፡ ያወራሉ ። እንዲ
ህም ፡ ማለታቸው ፤ ኢትዮጵያ ፡ በዘንዶ ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አራዊትና ፡ እንስሳት ፤ በክፉ ፡
መናፍስትም ፡ ታመልክ ፡ ነበረ ፡ የሚለውን ፡ የሐሰት ፡ ወሬ ፡ ለመደገፍ ፡ ነው ።

፲፫ ፤ ኢትዮጵያስ ፤ እንኳን ፡ ነገሥታቶቿን ፡ በጋኔን ፡ ስም ፡ ልትጠራ፡ይቅርና፡
ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኾኑ ፡ የአሕዛብ ፡ ነገሥታት ፡ አማልክት ፡ ነን ፡ ለማለት ፡ የጣዖታትን ፡
ስም ፡ ወርሰው ፤ ለራሳቸው ፡ አድርገው ፤ ክርስትና ፡ እንኳን ፡ ሳያገዳቸው ፤ ለእግዚአ
ብሔር ፡ የሚገባውን ፡ የክብር ፡ ሰላምታ ፡ ለማይገባው ፡ እንዲሰጥ ፡ ሌላውን ፡ ሲያስገ
ድዱ ፤ ሌሎችም ፡ አሕዛብ ፤ ልጆቻቸውን ፡ ለጣዖታት ፡ ሲሠዉ ፡ በማየቷ ፡ ተደንቃበ
ታለች ። መዝ ፡ ፷፯ ፡ ቍ ፡ ፴፩—፴፪ ።

፲፬ ፤ እንግዲህ ፡ ኢትዮጵያ ፤ ስሙ ፡ በማይለወጠው ፤ ክብሩ ፡ በማይናወጠው ፡
በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ እንጂ ፤ ራሱዋንም ፡ ኾነ ፡ ልጆቿዋን ፤ በጋኔን ፡ ስም ፡ የጠራች
በትና ፡ ያስጠራችበት ፤ የተጠራችበትም ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የለም ፤ እንግዲህም ፡
አይመጣምና ፤ ወጣት ፡ ልብ ፡ አድርገህ ፡ ተመልከት ። ብዙ ፡ መርምር ፤ መርጠህ፡ ተና
ገር ፤ ክብርህን ፡ ለሌላ ፡ አትስጥ ፤ ልዕልናህን ፡ በውርደት ፡ አትለውጥ ።

፲፭ ፤ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፤ ብዙ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፤ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡
በፊት ፡ እንደ ፡ ነበረና ፡ ከጥፋት ፡ ውሃም ፡ በኋላ ፤ በካም ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ተመሠረት ፤

www.ethiopianorthodox.org





ይናገሩና ፡ የሰው ፡ ልጆች፡ብዛት ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ አይደ(
ስም ፤ ይህ ፡ ታሪክ ፡ እውነተኛ ፡ ታሪክ ፡ አይመስልም ። ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ የነበሩት
እንኳን ፡ ቢኾኑ ፤ እንደ ፡ አንድ ፡ መንደር ፡ ባላባትና ፡ ባለርስት ፡ ነበሩ ፡ ማለት ፡ ነው
እንጂ ፤ ነገሥታት ፡ ለማለት ፡ አያስደፍርም ፡ ብለው ፤ መልሰው ፡ በትች ፡ ያፈርሱታል፡

፲፯ ፤ ይህም ፡ አነጋገር ፤ እግዚአብሔር ፤ ሰውን ፡ በወገኑ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በም
ድርና ፡ በባሕር ፤ በማነኛውም ፡ በራሪና ፡ ተሽከርካሪ ፤ ተላዋሽና ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ላይ
የሾመው ፡ ብዙ ፡ ተባዙ ፤ ምድርን ፡ ምሉዋት ፡ ሲል ፡ ያዘዘው፡መኾኑ፡ሲታወቅ ፤ መ(
ቱን ፤ ከመቃወሙ ፡ በላይ ፡ ብዙ፡ተባዙ፡ያለ፡እግዚአብሔርን ፤ ፪ሺ፪፻ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ
ያልነበረ ፤ ቢኖርም ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ አድርጎታል ። የጥፋትንም ፡ ውሃ ፡ በእስያ ፡ ክፍል
ብቻ ፡ ያዘነመ ፡ አስመስሎ ፡ ስለሚያሳይ ፤ ነበረ ፡ ማለት ፡ የሚያሳፍር ፡ መስሎ፡ አይታ
ይም ። ነገር ፡ ግን ፡ አያያዛችን ፡ መንፈሳዊውን ፡ መሥመር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ዐሳባችንን
ባጭር ፡ ወስነን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በገናናው ፡ በልዑል ፡ እግዚአብሔር፡አም
ልኮት ፡ ተመሥርቶ ፤ በገናናው ፡ በልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ተጠርቶ ፤ በቸርነቱ
ተደግፎ ፡ የኖረ ፡ የሚኖር ፡ መኾኑንና ፤ በተለየም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሉል
ጨብጦ ፡ በመታየቱ ፤ መንግሥቱን ፤ የመንግሥትን ፡ ሥልጣን ፡ ከጠላው ፡ ነሥቶ ፡ ለ(
ደደው ፡ መስጠት ፡ ከሚቻለው ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ፡ማ(
ረዳት ፡ ብቻ ፡ ይበቃል ። ዳን ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፲፯ና ፡ ፳፭ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ሰውን ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ፈጠረው ?
፪ ፤ የሹመቱ ፡ ዐይነት ፡ ምን ፡ ምን ፡ ተብሎ ፡ ይመደባል ?
፫ ፤ ክህነት ፡ የሚባለው ፡ ምን ፡ ዐይነቱ ፡ ነው ? መብቱስ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፬ ፤ መንግሥት ፡ የተባለው ፡ የትኛው ፡ ነው ? መብቱስ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፭ ፤ አዳም ፡ ምን ፡ ተብሎ ፡ ተሾመ ? ልጆቹስ ?
፮ ፤ አበው ፡ ገገርዎች ፡ የኾኑ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ?
፯ ፤ ኢትዮጵያዊው ፡ መንግሥት ፡ ከማን ፡ ተጀመረ ?
፰ ፤ ካምና ፡ ልጆቹ ፡ ምን ፡ አደረጉ ? በእነሱ ፡ የተመሠረተው ፡ መንግሥት ፡ ስንት
ዓመት ፡ ሠራ ?
፱ ፤ እስከ ፡ ናምሩድ ፡ የነበሩ ፡ አባቶች ፡ ለሥልጣናቸው ፡ ሥጋዊ ፡ ምልክት
ነበረውን ?
፲ ፤ የንጉሥ ፡ የሥልጣኑ ፡ ምልክቶች ፡ ምን ፡ ምን ፡ ናቸው ?
፲፩ ፤ የመንግሥት ፡ መዓርጋት ፡ ልዩነት ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፲፪ ፤ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ማን ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ?
፲፫ ፤ አጼ ፤ የምን ፡ ስሙ ፡ ነው ? ጃንሆይ ፡ ማለትሳ ?
፲፬ ፤ ባለታሪኮች ፡ ስለ ፡ አጼና ፡ ስለ ፡ ጃንሆይ ፡ ስምነት ፡ ምን ፡ ይላሉ ?

www.ethiopianorthodox.org

፲፭ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሌላ ፡ የተጠራችበት ፡ ልጆቿንስ ፡ የጠራች
በት ፡ አለን ?

## ምዕራፍ ፡ ፰ ።

## ክ ህ ነ ት ።

፩ ፤ በአለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ጠቀስነው ፡ ኹሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፤ አዳምን ፡ ከኹለት ፡ ነገሮች ፡ ማለት ፡ ከሚሞትና ፡ ከማይሞት ፡ ፈጥሮ ፤ ሞት ፡ የማይስማማት ፡ ነፍስን ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ አዋሕዶ ፤ ሞት ፡ የሚስማማው፡ ሥጋን፡በነፍስ፡ሕያው ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አድርጎ ፤ በልጅነት ፡ አክብሮ ፤ ነቢይ ፡ ካህን ፡ ንጉሥ ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ሾመው ፤ በኦሪት ፡ በወንጌል ፡ ሥርዐት ፡ እስኪወሰን ፡ ድረስ ፤ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ የነበሩ ፡ አበው ፤ በበረከተ ፡ አበው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እየተሾሙ ፤ ትንቢትን ፡ ክህነትን ፡ መንግሥትን ፡ ከቅዱስ ፡ መንፈሱ ፡ እየተቀበሉ ፤ በነቢይነታቸው ፤ ያለፈውን ፡ የሚመጣውን ፡ ሲገልጡ ፤ ሲያስተምሩ ፤ በካህንነታቸው ፡ መሥዋዕት ፡ ሲያቀርቡ ፤ በጸሎታቸው ፡ አምላካቸውን ፡ ሲጠሩና ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ሲነጋገሩ ፤ በንጉሥነታቸውም ፡ ልጆቻቸውን ፡ ሲሠሩ ፡ ሲቀጡ ፡ ኖረዋል ።

፪ ፤ በዚህም ፡ መሠረት ፡ ወዐጠነ ፡ አዳም ፡ ምስለ ፡ ትንግሔ ፡ ፀሓይ ፡ በከርቤ ፤ ወሚዓ ፡ ወሰሊክ ፡ እንዲል ፤ አዳም ፡ ከገነት ፡ በወጣ ፡ በማግሥቱ ፤ በሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ተጠጥቶ ፡ እያዘነና ፡ እያለቀሰ ፤ ቸርነት ፡ ምሕረት ፡ የባሕርዩ ፡ ከኾነው፡አምላክ፤ዕርቅ ፡ ለመጠየቅ ፡ የመዓዛ ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ። ኩፋሌ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፩—፫ ።

፫ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ አዳም ፤ እንደ ፡ ዲያብሎስ ፡ ትዕቢቱን ፡ ከልቡናው ፡ አንቅቶ ፤ ሐሰትን ፡ ከባሕርዩ ፡ አመንጭቶ ፡ አለመበደሉን ፤ ከዚህም ፡ የበለጠ ፡ በሥራው ፡ ደንግጦ ፡ ተጠጥቶ ፡ ምሕረት ፡ መለመኑን ፡ ንስሐ ፡ መግባቱን ፡ አይቶ ፤ ተመልክቶ ፤ አዘነለት ፡ ራራለት ፡ ማረው ፡ ይቅር ፡ አለው ።

፬ ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በኀሙስ ፡ ዕለት ፡ ወበመንፈቃ ፡ ለዕለት ፡ እትወለድ ፡ እምወለተ ፡ ወለትከ ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ማርያም ። ወእድኅክ ፡ ውስተ ፡ መርኅብከ ፤ ወእትቤዘወከ ፡ በመስቀልየ ፡ ወበሞትየ ፤ ( በዐምስት ፡ ቀን ፡ ተኩል ፡ ማለት ፤ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት፡መቶ ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፤ ማርያም ፡ ከምትባለው ፡ የልጅ ፡ ልጅኽ ፡ ተወልጄ ፤ በሚዳህ ፡ ድኼ ፤ ተሰቅዬ ፤ ሞቼ ፡ አድንሀለኹ) ፡ ብሎ ፤ አዳም ፡ ወዴት፡አለህ፤እንዳትበላ፡ያዘዝኩኽን ፡ በላኽን ? አዳም ፡ ከእኛ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ኾነ ፡ ሲል ፡ የተናገረ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፤ በቃሉ ፡ የተዘጋጀውን ፡ የመድኀኒት ፡ ተስፋ፡ ሰጠው ። ቀሌምንጦስ ፡ ተመልከት ።

፭ ፤ አዳምም ፤ ይህን ፡ ለጊዜው ፡ የማያልቅ ፤ የማይበላሽና ፡ የማይጠፋ፡የተስፋ፡ሥንቅ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተቀብሎ ፤ በተቀበለበት ፡ ዕለት፡ ሌሊቱን ፡ ማለት ፤ ሺሑን፡ ዘመን ፡ እንኳን ፡ ሳይፈጽም ፡ በ፱፻፴ ፡ ዓመት ፡ ስለ ፡ ሞተ ፤ ልጆቹ፡ ተስፋውን ፡ ተቀ



ካህኑ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ።

አብርሃም ፡ ዐሥራት ፡ የሰጠው ፡ የሰላም ፡ ንጉሥ ፡ ታላቁ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ካህን ፡ ይህ ፡ ነው ። ክህነቱ ፡ የወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ ኾኖ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ። ዕብ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፩—፬ ።

www.ethiopianorthodox.org

ብለው ፡ ጊዜውን ፡ ሲጠብቁ ፤ እንደ ፡ ተማሩትም ፡ የመዓዛ ፡ መሥዋዕት ፡ እያቀረበ
ከእግዚአብሔር ፡ የተሰጠውን ፡ ተስፋ ፡ በቃል ፡ ኪዳን ፡ ሲያጸድቁ ፡ ኖረዋል ።

ከነዚህም ፡ አበው ፤ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፤ የተስፋው ፡ ማረፊያ ፤ የእግዚአብሔር፡ መ
ለጫ ፤ የሕጉ ፡ መምህራን ፡ የነበሩት ፤ ሄኖክ ፡ ኖኅ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ አብርሃም
ይስሐቅ ፡ ያዕቆብ ፡ ሙሴ ፡ ዳዊት ፡ ናቸው ።

፮ ፤ ከነሱም ፡ መካከል ፡ ካህን ፡ መባል ፡ በአሪት ፡ ከመገለጹ ፡ በፊት ፤ የወል
እግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ የወንጌል ፡ ሥርዐተ ፡ ቍርባን ፡ መምህርና ፡ ሰባኪ ፤ የብፁዓ
ሐዋርያት ፡ መሪና ፡ ፈታውራሪ ፡ ሆኖ ፡ በቀራንዮ ፡ ሊያገለግል ፤ ታላቁ፡ካህን ፡ ሊ
ካህናት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመምጣቱና ፡ ለመሥዋዕት ፡ ከመቆሙ ፡ በፊት ፤ ቤተ
መቅደሱን ፡ ሊጠብቅ ፤ ንዋያተ ፡ ቅድሳት ፡ ጾምን ፡ ጸሎትን ፡ ተባሕትዎን ፡ ድንግ
ናን ፡ ከዊነ ፡ ሰማዕትን ፡ ሊያዘጋጅ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ተመርጦ ፡ የተላከው ፡ በታማኝ
ሽማግሌ ፡ በሴም ፡ አማካይነት ፤ ከእግዚአብሔር ፡ የተሾመው ፤ ኢትዮጵያዊው ፡ ካህን
መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፡ ፲፰—፳፫ ። መዝ ፡ ፻፲ ፡ ቍ ፡ ፬ ።

፯ ፤ ይህ ፡ ካህን ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፤ በኑሮው ፡ ኹሉ ፡ ከዓለም
ልዩ ፡ ኾኖ ፤ ክፋቷንም ፤ በጎነቷንም ፤ በግል ፡ ዐሳቧ ፡ ትሠራ ፡ ዘንድ ፡ በመላእክት፡አ
ሳል ፡ በተፈጠረችው ፡ በነፍስ ፡ ግብር ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፤ ንጹሕ ፡ ድንግል ፡ ጸዋሚ
ተሐራሚ ፡ ባሕታዊ ፡ ነበር ።

፰ ፤ ታላቁ ፡ ካህን ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፤ የወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፤ የሰላም
ንጉሥ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፤ ሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ የማይተካከሉትና ፡ የማይወ
ደሩት ፤ መዓርገ ፡ ክብሩ ፡ ምጡቅ ፡ ምስጢረ ፡ ክህነቱ ፡ ረቂቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ የሌዋውያን
አባት ፡ አብርሃም ፤ ሌዊ ፡ ገና ፡ በወገቡ ፡ ሳለ ፤ በረከተ ፡ ገጽ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ አቀረበለት
ዐሥራት ፡ አወጣለት ።

፱ ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ምላቱ ፡ እየጨመረ ፡ እንደሚሄድ ፡ ብርቱ፡ምንጭና፡እንደ
ውሃ ፡ መሸረብ ፡ ( ቧንቧ ) ፡ የበረከተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምንጭ ፡ ካህኑ ፡ መልከ
ጼዴቅ ፤ ኅብስተ ፡ አኰቴቱን ፡ ጽዋዐ ፡ በረከቱን፡ባርኮ ፡ ቀድሶ ፡ በመስጠት ፤ ከቍርባነ
ኦሪት ፡ ልዩ ፡ የኾነችውን ፤ ከመሥዋዕተ ፡ እንስሳ ፡ የከበረችውን ፡ ቍርባነ ፡ ወንጌል
ከሰበከለት ፡ በኋላ ፤ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባረክኽ ፡ ፍጥረቱ ፡ አብርሃም ፡ ሆይ
ቡሩክ ፡ ነህ ፤ ጠላቶችኽን ፡ በእጅኽ ፡ የጣለልህ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጉን
አምላክ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ባረከው ። ዕብ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፩-፲፬ ።

፲ ፤ አብርሃምም ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ በረከት ፡ ተቀብሎ ፡ ዘንባባ ፡ ይዞ ፡ በዓለ ፡ እ
ዚአብሔርን ፡ አከበረ ። አብርሃም ፤ የሰዶም ፡ ንጉሥ ፡ ወደሱ ፡ መጥቶ ፤ ከምርኮ፡ውስጥ
ሀብቱ ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ፡ ሰዎችን ፡ መልስልኝ ፡ በአለው ፡ ጊዜ ፤ የጦር ፡ ጓደኞቹ
ኤስኬልና ፡ መምሬ ፡ ከወሰዱት ፤ ወታደሮቼ ፡ የዕለት ፡ ምግብ ፡ ካደረጉት ፡ በቀር
እኔ ፡ አብርሃምን ፡ አከበርኩት ፡ እንዳትል ፤ ከገንዘብህ ፡ የጫማ ፡ ክር ፡ ስንኳ ፡ አል
ስድም ፡ ሲል ፡ የተናገረ ፤ እግዚአብሔርም ፤ አብራም ፡ ለአንተ ፡ ጋሻኽ ፡ እኔ ፡ ነኝና



አትፍራ ፤ ዋጋኽም ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ሲል ፤ ለአብርሃም፡ ተስፋውን ፡
ያጸናለት ፤ እንዲሁም ፡ የሦስት ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ እንስሳት ፡ በመሠዋት ፤ የክህነትን ፡
ሥራ፡ይሠራ፡ዘንድ፡መዓርገ፡ክህነትን ፡ የፈቀደለት ፤ በረከቱን ፡ ከታላቁ ፡ ካህን ፡ መልከ፡
ጼዴቅ ፡ በተቀበለበት ፡ ቀን ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፡ ፳፩-፳፬ ። ም ፡ ፲፭ ፡ ቍ ፡ ፩-፲ ።

፲፩ ፤ ሙሴ ፤ ለአሮንና ፡ ለአልዓዛር ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሐዋርያት፡
ከመስጠቱ ፡ በፊት ፤ ክህነትን ፡ በመምህራን ፤ ቡራኬ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ለማግኘትና ፡
ለመሾም ፡ መሠረቱና ፡ መጀመሪያው ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፤ አብርሃምን ፡ የባረከበት ፡ አብ
ርሃም ፡ ከመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ የተባረከበት ፡ ያ ፡ ቡሩክ ፡ ሰዓት ፡ ነው ። ሉቃስ ፡ ም ፡ ፳፬ ፡
ቍ ፡ ፶፩ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ ፡ ፳፩—፳፬ ።

፲፪ ፤ የመልከ ፡ ጼዴቅን ፡ ነገር ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ ከፍ ፡ አድርገው፡ይናገራሉ ።
ይልቁንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምርጥ ፡ ዕቃ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የንጋት ፡ ጨረቃ ፡
ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፤ ስለ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ሐሊና ፡ መርምሮ ፡
አንደበት ፡ ተነጋግሮ ፡ የማይፈጽመው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በዕፁብ ፡ ብቻ ፡ ይወሰናል ።

፲፫ ፤ የመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ኢትዮጵያዊነቱ ፤ ከነገደ ፡ ካም ፡ በመወለዱ ፤ በስም ፡
አጠራሩ ፡ በኑሮ ፡ ድርጅቱ ፡ ይታወቃል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፤ የማዕርጉን፡
ምጡቅነት ፤ የምስጢረ ፡ ክህነቱን ፡ ረቂቅነት ፤ ከሌዋውያን ፡ ነገድ፡ ከሴማውያን፡ሐረገ፡
ትውልድ ፡ አለመወለዱን ፤ ክህነቱ ፡ የወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ ኾኖ ፡ ለዘለዓ
ለም ፡ ይኖራል ፤ ከወገናቸው ፡ ላልተወለደው ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ አባታቸው ፡ አብር
ሃም ፡ ዐሥራት ፡ ሰጠው ፡ የዚህን ፡ ካህን ፡ ልዕልናውን ፡ አያችሁን ? ብሎ ፡ ካስረዳ ፡
በኋላ ፤ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡ መወለዱ ፡ እየታወቀ ፤ አባት ፡ የለውም ፤ እና
ትም ፡ የለችውም ፤ ዘመኑ ፡ አይቈጠርም ፤ የተወለደበት ፡ የሞተበት ፡ አይታወቅም ፡
ሲል ፡ ዘግቶታል ።

፲፬ ፤ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ የመልከ ፡ ጼዴቅን ፡ ሰውነት ፡
ረስቶ ፡ ወይም ፡ ተሳስቶ ፡ አይደለም ።

ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ አባት ፡ እናት ፡ የለውም ፡ ዘመኑ፡አይ
ቈጠርም ፤ የተወለደበት ፡ ጊዜ ፡ አይታወቅም ፡ ማለቱ ፤ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ካህን ፡ የሌ
ዋውያን ፡ አባት ፤ አብርሃም ፡ ዐሥራት ፡ ሰጪ ፡ ኾኖ ፡ ሲገኝ ፤ ነገሩን ፡ አጋኖ ፡ ባይሰው
ረውና ፡ ከዚህ ፡ ነገድ ፡ ከዚህ ፡ ትውልድ ፡ የተወለደ ፡ ነው ፡ ቢላቸው ፡ ኖሮ ፤ ዕብራው
ያን ፤ ሱባኤ ፡ ትውልድ ፡ የሄኖክ ፡ ሱባኤ ፡ ዕለት ፡ የኤርምያስ ፡ ሱባኤ፡ዘመን፡የዳንኤል፡
በጠቅላላው ፡ ኦሪት ፡ ነቢያት ፡ የተናገሩት ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፤ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ እያወ
ወቁ ፤ እልክ ፡ መስሎዋቸው ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በመሢሑ ፡ ላይ ፡ በጠላትነት፡ ተነሥ
ተው ፡ መድኀኒታቸውን ፡ እንደ ፡ ካዱ ፤ ይህንንም ፡ እልክ ፡ መስሎዋቸው፡ትምህርቱን ፡
አንቀበልም ፡ ባሉ ፡ ነበርና ፡ ከክርስቶስ ፡ እስከ ፡ መለየት ፡ ደርሶ ፡ ሕይወቱን ፡ ሊለውጥ
ላቸው ፡ የሚያስብላቸው ፡ ወገኖቹ ፡ እስራኤል ፡ እንዳይሰናከሉ ፡ የመልከ ፡ ጼዴቅ ፡
ነገር ፡ ጭንቅ ፡ ነው ፡ ሊመረምሩት ፡ ሊተረጕሙት ፡ አይቻልም ፡ በማለት ፡ ወሰነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

እንጂ ፤ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ሐዋርያዊ ፡ ቀሌምንጦስ ፡ ዘእምነገዱ ፡ ለካም ፡ ብሎ ፡ ገል
ታል ።

፲፭ ፤ ይኸውም ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ለሰው ፡ ምክንያት ፡ የሚኾነውን ፡ ነገ
መሰወር ፡ መሻር ፡ አራቆ ፡ መናገር ፡ ልማዱ ፡ ስለ፡ኾነ ፤ በየመልእክቶቹ ፡ የታወቀው
ምልክት ፡ በዕብራውያን ፡ መልእክቱ ፡ እንደ ፡ ተወው ፡ ያለ ፡ ነገር፡ነው ። እሱም ፡ ጳ
ሎስ ፡ ሐዋርያሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እያለ ፡ በየመልእክቶቹ ፡ መጀመሪያ ፡ የሚ
ፈው ፡ ቃል ፡ ነው ።

፲፮ ፤ ባለፈው ፡ እንደ ፡ ጠቀስነው ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ለመኾ
ትውልዱ ፡ ስም ፡ አጠራሩ ፡ የኑሮ ፡ ድርጅቱ ፡ ያስታውቃል ፡ ያልነውን ፡ ስንዘረዝር
ስለ ፡ ትውልዱ ፤ ጳውሎስ ፡ የሰወረውን ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ቀሌምንጦስ ፡ ዘእምነገዱ
ለካም ፡ ብሎ ፡ ገልጦታል ፡ ባልነው ፡ ትውልዱ ፡ ነገዱ ፡ ከነገደ ፡ ካም ፡ መኾኑን ፡ አስ
ድተናል ።

፲፯ ፤ ስለ ፡ ስሙ ፡ አጠራር ፡ በኢትዮጵያ ፡ መለከ ፡ ካለው ፡ ግሥ ፡ የሚገኙት
መልክ ፡ መለክ ፡ የሚባሉት ፡ ቃላት ፡ የክብር ፡ ስሞች ፡ ኾነው ፡ ይገኛሉ ።
በዚህም፡ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታትና ፡ ገገርዎች ፡ መሊኩ ፡ መለክ ፡ ሰገ
እየተባሉ ፡ ይጠሩ ፡ ነበር ። ትርጓሜውም ፡ ገዥ ፡ ገዥን ፡ የሚያሰግድ ፡ ማለት ፡ ሲኾን
መልከ ፡ ጼድቅ ፡ ማለት ፡ ንጉሥ ፡ ጽድቅ ፡ ንጉሥ ፡ ሰላም ፡ የሰላም ፡ የጽድቅ ፡ ንጉሥ
ማለት ፡ ነውና ፡ ከቋንቋው ፡ ከግእዝ ፡ የተመሠረተው ፡ ስሙ ፡ ኹለተኛ ፡ ምስክር
ሊኾን ፡ ችሏል ።

፲፰ ፤ ሦስተኛውም ፡ የኑሮ ፡ ድርጅት ፡ በአዳምና ፡ በሔዋን ፡ ተመሥርቶ ፤ በኢ
ዮጵያውያን ፡አበው ፡ ጸንቶ ፡ እንደሚኖረው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የላመ ፡ የጣመ ፡ አለ
ቅመስ ፤ ዳባ ፡ መልበስ ፤ ጠጕርን ፡ አለ ፡ መላጨት ፤ ጥፍርን ፡ አለመቍረጥ ፤ ከአንድ
ቦታ ፡ በጸሎት ፡ ተወስኖ ፡ መኖር ፡ ከሱ ፡ ተወርሶ ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ደርሶ ፡ በኢት
ጵያ ፡ አድባራትና ፡ ገዳማት ፡ ሲሠራበት ፡ ስናየው ፤ ሦስተኛውን ፡ የዐይን ፡ ምስክር
ሊኾነን ፡ ችሎዋል ።

፲፱ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኪዳነ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅን ፡ ለማጽናት
ወደ ፡ ግብጽ ፡ በተሰደደበት ፡ በሕፃንነቱ ፡ ወራት ፡ የግብጽን ፡ በረሃ ፡ ዘልቆ ፡ በኢት
ጵያ ፡ ጠረፍ ፡ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ምድር ፡ ሦስት ፡ ዓመት፡ከመንፈቅ ፡ በ
ሳለፉ ፤ በረከቱ ፡ ፍቅሩን ፡ በኢትዮጵያ ፡ በማሳረፉ ፤ ኋላም ፡ ካህኑ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ
ይላክበትና ፡ ያገለግልበት ፡ በነበረው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ የክህነት ፡ ሥራውን ፡ በመፈጸሙ
በመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ክህነት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ዕንቍ ፡ ፈርጥ ፡ ቦግ ፡ ብሎ ፡ የሚታየው ፡ የ
ልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክህነት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዕድል ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጎታል ።

፳ ፤ ዛሬም ፡ አንደኛ ፡ አባታቸው ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ሲላክና ፡ ሲያገለግል፡በነ
ረበት ፤ ኹለተኛ ፡ ለጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምኃ ፡ ካቀረቡት ፡ አንዱ፡መሊኩ
( ሚሊኪዩር ፡ ) እንግዳ ፡ ኾኖ ፡ በአደረበት ፤ ሦስተኛ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ



በተቀበረበት ፡ ቦታ ፡ በጎልጎታ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሠርቶ ፡ ኢት
ዮጵያውያን ፡ ካህናት ፡ የክህነት ፡ ሥራ ፡ ሲፈጽሙበት ፡ ይህ ፡ ሥራ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ፡
ክርስቶስ ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ ያይደሉ ፡ ሌሎች ፡ በጎች ፡ አሉኝ ፡ አመጣቸዋለሁ ፤ ቃሌንም ፡
ይሰሙኛል ፡ ያለውንና ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ የመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ክህነቱ፡የወልደ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ ኹኖ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ፡ ያለውን ፡ አጽድቆታል ። ዮሐ ፡ ም፡
፲ ፡ ቍ ፡ ፲፮ ። ዕብ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፫ ። ለኢትዮጵያ ፡ ይህን ፡ ዕድል ፡ የሰጣት ፡ አምላክ ፡
ይክበር ፡ ይመስገን ። አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ የነበሩ ፡ አበው ፡ ምን ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ?
፪ ፤ አዳም ፡ ከገነት ፡ በወጣ ፡ በማግሥቱ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፫ ፤ አዳም ፡ በጠየቀው ፡ ዕርቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ መለሰለት ?
፬ ፤ አዳም ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ? በኋላስ ፡ ልጆቹ ፡ ምን ፡ ሲያደርጉ ፡ ኖሩ ?
፭ ፤ ከአበው ፡ የተስፋው ፡ ማረፊያ ፡ የኾኑት ፡ ማን ፡ ማን ፡ ናቸው ?
፮ ፤ የአሪት ፡ ካህናት ፡ ከመሾማቸው ፡ በፊት ፡ የተነሣው ፡ ካህን ፡ ማን ፡ ነው ?
፯ ፤ የመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ኑሮው ፡ እንዴት ፡ ነበር ?
፰ ፤ መልከ ፡ ጼዴቅን ፡ ሌዋውያን ፡ ይተካከሉታልን ?
፱ ፤ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ለአብርሃም ፡ ምን ፡ አደረገለት ? አብርሃምስ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፲ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ ተስፋውን ፡ ያጸናለት ፡ መቼ ፡ ነው ?
፲፩ ፤ ክህነትን ፡ በመምህራን ፡ ለመሾም ፡ የተጀመረው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ?
፲፪ ፤ የመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ኢትዮጵያዊነቱ ፡ በምን ፡ ይታወቃል ?
፲፫ ፤ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ስለ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ምን ፡ ጽፎዋል ?
፲፬ ፤ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ እናት ፡ አባት ፡ የለውም ፡ ያለ ፡
በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ?
፲፭ ፤ ቀሌምንጦስስ ፡ ምን ፡ ብሎዋል ?
፲፮ ፤ የጳውሎስ ፡ የመልእክቶቹ ፡ ምልክት ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፲፯ ፤ የመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ የስሙ ፡ አጠራር ፡ ትርጓሜው ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፲፰ ፤ የመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ የኑሮ ፡ ድርጅቱ ፡ እንዴት ፡ ነበር ?
፲፱ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኪዳነ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅን ፡ ለማጽናት ፡ ምን ፡
አደርገ ?
፳ ፤ በጎልጎታ ፡ የሚፈጸመው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሥራ ፡ ምን ፡ ሊያስረዳን ፡ ይችላል ?

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

## ቋ ን ቋ ።

፩ ፤ ምንጊዜም ፡ ቢኾን ፡ ለቋንቋ ፡ ሥሩ ፡ መገለጫው ፡ ምንጩና ፡ መፍለቂያው ፡
ፊደል ፡ መኾኑ ፡ የታወቀ፡ስለ፡ኾነ ፤ በዚህ፡ምዕራፍ፡የጽሑፋችን፡መሠረት፡ ፊደል ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ ፤ ፊደል ፤ ከአዳም ፡ በሦስተኛው ፡ ትውልድ ፡ በሄኖስ ፡ ከእግዚአብሔር
ለሰው ፡ ልጆች ፡ የተሰጠ ፡ በልሳን ፡ ተውጦና ፡ ተሰውሮ ፡ የነበረው ፡ አካሉ ፡ በሰማይ
ገበታነት ፡ ተጥፎ ፡ ተቀርጦ ፡ የተገለጠ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ነው ። ኵፋ ፡ ም ፡ ፫፡ ቍ ፡ ፲፰

፫ ፤ ቋንቋ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተገኝቶ ፡ በመላእክትና ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ተጠንቶ
መልኩ ፡ በሕሊና ፡ ሲታወስ ፤ ረቂቅ ፡ አካሉ ፡ በልሳን ፡ ሲዳሰስ ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ሄኖ
ኖሮ ፡ በኋላ ፡ በቀለምና ፡ በወረቀት ፡ ሳይኾን ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ በተፈጥሮው ፡ ዐዋ
ሊኾን ፡ የተፈጠረ ፡ ሰው ፡ ዕውቀቱ ፡ እየደከመ ፡ ስለ ፡ ሄደና ፡ ሊጠቀምበት ፡ ስለ ፡ አ
ቻለ ፡ ዐይን ፡ በመመልከት ፡ እጅ ፡ በጥፈት ፡ ሕሊናውን ፡ እየረዱለት ፡ ዐሳቡን ፡ በ
ሑፍ ፡ በማሳረፍ ፡ ይጠቀም ፡ ዘንድ ፡ የሰላም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ የቋንቋን
ኹኔታ ፡ የፊደልን ፡ መልክና ፡ ቅርጥ ፡ በሰማይ ፡ ገበታነት ፡ ጥፎና ፡ ቀርጦ ፡ ለሰው
ልጅ ፡ አስተማረ ።

፬ ፤ የእነዚህም ፡ ፊደላት ፡ መደበኛ ፡ ቍጥራቸው ፡ ከእሑድ ፡ እስከ ፡ ዐርብ ፡ በ
ፈጠሩት ፡ ፍጥረታት ፡ ልክ ፡ ፳፪ ፡ ናቸው ።

ለነዚህም ፡ በመጥበቅና ፡ በመመሳሰል ፡ ምክንያት ፡ ተደራቢዎች ፡ አራት
ፊደላት ፡ አሉዋቸው ፤ ከተደራቢዎቻቸውም ፡ ጋራ ፡ ፳፮ ፡ ይኾናሉ ፤ ምክንያቱም ፡ ኻያ
ኹለቱን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ በ፳፬ ፡ ሰዓት ፡ በኹለት ፡ ክፍላተ ፡ ዕለት ፡ ( ሌሊትና ፡ መ
ልት ፡ ) የፈጠረ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርና ፡ ፍጥረቶቹ ፡ የሚጠሩበት ፡ የሚነጋገሩበት
ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ።

፭ ፤ ኹለተኛውም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ወይም ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ በኻያ ፡ ኹለቱ ፡ ፊ
ላት ፡ መሠረትነት ፤ ባራቱ ፡ ድምፅ ፡ ሰጭዎች ፡ አዋሐጅነት ፡ በ፳፮ ፡ ዝግጅቶች ፡ የ
ገለጥና ፡ የሚነገር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ።

፮ ፤ የፊደላት ፡ መልክ ፡ በሄኖስ ፡ ዘመን ፡ ታይቶ ፡ ተለይቶ ፡ ዐይንና ፡ ሕሊና ፡ እየተ
ዳዱ ፡ በሰጡት ፡ ውጤት ፤ የሰው ፡ ልጆች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ መጥራት ፤ የፊደላትን
መልክ ፡ ለይቶ ፡ ማወቅና ፡ ማጥናት ፡ ሲጀምሩ ፡ የሕሊና ፡ ዐሳብ ፡ ኹሉ ፡ በአፍ ፡ በ
ጣፍ ፡ የታወቀ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰባተኛው ፡ ትውልድ ፡ በ
ኖክ ፡ ዘመን ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ጥፈትን ፡ አስተማረ ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፳፮ ።

፯ ፤ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ በቃል ፡ ያለ ፡ ይረሳል ፤ በመጣፍ ፡ ያለ
ይወረሳል ፡ እያለ ፡ ክፉም ፡ በጎም ፡ ኾነ ፡ ማነኛውንም ፡ ዐሳቡን ፡ በብራና ፡ በወረቀት
ጥፎ ፡ አፍሮ ፡ በዕንጨት ፡ በድንጋይ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በኾኑት ፡ የመዓድን ፡ ዐይ
ቶች ፡ ዐንጦ ፡ ቀርጦ ፡ ያስቀምጥ ፡ ጀመረ ።

፰ ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጣፎች
ከመንፈሳዊው ፡ ወገን ፡ መጽሐፈ ፡ ሄኖክ ፡ . . . . . በትውልድ ፡ ተላልፎ ፡ ደርሶናል ። ከዚ
ህም ፡ ሌላ ፡ ሥጋዊው ፡ ወገን ፡ በየፈላስፎች ፡ እጅ ፡ የሚገኘው ፡ የፍልስፍና ፡ መጣፍ ፡ ከአ
ልደ ፡ ቃኤል ፡ ተጋብተው ፡ ዓለምን ፡ ሲያስቱ ፡ ከነበሩ ፡ አጋንንት ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ ተ



ና ፡ ተቀርጦ ፡ ኖሮ ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በኋላ ፡ ከሴም ፡ በ፫ኛው ፡ ትውልድ ፡ በቃይናን ፡
መን ፡ የተገኘ ፡ ነው ።

፱ ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ቦታ ፡ ለመመርመር ፡ ሲዘዋወር ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ ያገኘውን ፡
ፍልስፍና ፡ ትምህርት ፡ በጽሑፍ ፡ ገልብጦ ፡ ኖኅ ፡ እስኪሞት ፡ ደብቆ ፡ አኑሮ ፡ በኋላ ፡
ለ ፡ ገለጠው ፤ ከዚያ ፡ አያይዞ ፡ ዓለም ፡ በየፈላስፎች ፡ እጅ ፡ እያዘዋወረ ፡ እያቃዳና ፡
ያበዛ ፡ ከጥቅሙ ፡ ይልቅ ፡ የጉዳቱን ፡ መሥመር ፡ ሲያስፋፋበት ፡ ይኖራል ።

፲ ፤ አዳም ፡ በገነት ፡ ሳለ ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ቋንቋ ፡ ነበር ፡ አዳም ፡ ዕፀ ፡
ለስን ፡ ከበላ ፡ በኋላ ፡ ከገዥነቱ ፡ ስለ ፡ ተሻረና ፡ የኹሉ ፡ ገዥ ፡ አንድ ፡ እግዚአብሔር ፡
መኾኑ ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ እየራሱ ፡ መተዳደር ፡ ስለ ፡ ጀመረ ፤ ቋንቋውም ፡ ኑሮውም ፡
ተለያየ ፡ ኾነ ።

፲፩ ፤ እባብና ፡ ሔዋን ፤ በዐሳብ ፡ ለመገናኘት ፡ የቻሉ ፡ ቋንቋው ፡ አንድ ፡ ቢኾን ፡
ው ፡ እንጂ ፡ የእባብ ፡ ትምህርት ፡ በዐይን ፡ ጥቅሻ ፡ በከንፈር ፡ ንክሻ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፤
በቀን ፡ ብዛት ፡ ሔዋን ፡ እስክታጠናው ፡ ድረስ ፡ በነገሩ ፡ አዳም ፡ በደረሰበት ፡ ነበር ።

፲፪ ፤ አዳም ፡ ከገነት ፡ ከወጣ ፡ በኋላም ፡ በሰናዖር ፡ ግንብ ፡ መፍረስ ፡ ሥላሴ ፡
እስኪለያዩት ፡ ድረስ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ቋንቋ ፡ አንድ ፡ መኾኑ ፡ የታወቀ ፡ ስለ ፡ ኾነና ፡
ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ መለያየቱና ፡ መብዛዛቱ ፡ የጐላ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ብዙ ፡ ማተት ፡ አያሻም ።

፲፫ ፤ እንግዲህ ፡ ከዚህ ፡ ከደረስን ፡ የግል ፡ ዕጣችንን ፡ ይዘን ፡ መሄድ ፡ አለብን ።
ዕጣችንም ፡ ከሰው ፡ ሳይኾን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ያገኘነው ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ነጻ ፡
ኾኖ ፡ የነጻነታችን ፡ ምስክር ፡ የኾነው ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ።

፲፬ ፤ ግእዝ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተገኝቶ ፡ ተቀዳሚ ፡ ቋንቋ ፡ ለመኾኑ ፡ የምንሰጣ
ቸው ፡ ማስረጃዎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

፲፭ ፡ አንደኛ ፤ ፊደሉ ፡ ጥፈቱ ፡ ቅርጡ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ኾኖ ፤ ድምጡንም ፡
በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ያናግራል ፡ እንጂ ፤ ረዳት ፡ የማይሻ ፡ ስለ ፡ ኾነና ፡
ሌሎችም ፡ የዓለም ፡ ቋንቋ ፡ ፊደሎች ፡ ግእዝኛውን ፡ ድምፅ ፡ በመስጠት ፡ የማይመሳሰ
ሉት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ አ ፤ ኸ ፡ በ ፡—ገ ፡—ደ ፡— እንደ ፡ ማለት ፡ በአማ
ካይ ፡ አፍ ፡ አከፋፈት ፡ የሚሰጠው ፡ ድምጥ ፡ ነው ።

፲፮ ፤ ኹለተኛ ፤ የግእዝ ፡ ፊደል ፡ በኻያ ፡ ኹለት ፡ ተመድቦ ፡ በሰባት ፡ ስልት ፡
ሲነገር ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ኻያ ፡ ኹለቱን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ፈጥሮ ፡ በሰባቱ ፡
ዕለታት ፡ ዐሳቡን ፡ እንደ ፡ ፈጸመ ፡ ስለሚያስረዳ ፡ ነው ።

፲፯ ፤ ሦስተኛ ፡ ኻያ ፡ ኹለተኛው ፡ ፍጥረት ፡ አዳም ፡ ባራት ፡ የሥጋ ፡ ጠባዮች ፡
በሦስት ፡ የነፍስ ፡ ግብሮች ፡ ግዘፍ ፡ ፍጥነት ፡ ሙቀት ፡ ቍረት ፡ ለባዊነት ፡ ነባቢነት ፡
ሕያውነት ፡ በ፯ ፡ ነገራት ፡ ጸንቶ ፡ ጕድለት ፡ የሌለበት ፡ የጸጋ ፡ ገዥ ፤ የእግዚአብሔር ፡
የክብር ፡ ወራሽ ፡ መኾኑን ፡ በምላቱ ፡ ሕጸጽ ፡ የሌለበት ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡
ማደሪያ ፡ መገለጫ ፡ መኾኑን ፡ ስለሚያስረዳ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፰ ፤ አራተኛ ፤ ኻያ ፡ ኹለቱን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ የፈጠረ፡እግዚአብሔር ፡ ኻ
ኹለተኛውን ፡ ፍጡር ፡ አዳምን ፡ በልጅነት ፡ አክብሮ ፡ በሰባቱ ፡ ሀብታት ፡ በጥበብ
በማስተዋል ፤ በዕውቀትና ፡ በእውነት፡በምክርና፡በኀይል ፤ እግዚአብሔርን፡ በመፍራ
እንደ ፡ አስጌጠውና ፡ እንደ ፡ አበለጠገው ፡ ስለሚያስረዳ ፡ ነው ።

፲፱ ፤ ዐምስተኛ ፤ በባቢሎን ፡ የተመሠረቱ ፡ ቋንቋዎች ፡ በየወገኑ ፡ የፍጡራን
ስም ፡ ተደግፈው ፡ ይሄዳሉ ።

<u>ማስረጃ ።</u>

| <u>ስም ።</u> | <u>ቋንቋ ።</u> |
|---|---|
| ኤቦር ፡ (ኤበር) ፤ | ዕብራይስጥ ፤ |
| ጽርዕ ፤ | ጽርዕ ፤ |
| ሮም ፤ | ሮማይስጥ ፤ |
| ዐረብ ፤ | ዐረብ ፤ |

የመሰለው ፡ ኹሉ ፡ ነው ።

፳ ፤ ግእዝ፡ ግን፤እግዚእ፡እግዚአብሔር፡ አግዓዚ ፤ለኀጢአት፡ ለጣዖት ፡ ከመገዛት
ነጻ፡አውጥቶ ፡ ግዕዛን ፡ የሥጋ ፡ የነፍስ ፡ ነጻነትን ፡ ከሚሰጥ ፡ ጌታ ፤ ከልዑል ፡ እግዚአብሔ
ተገኝቶ ፤ ለአግዓዝያን ፡ ለአዳምና ፡ ለልጆቹ ፤ የተሰጠ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ግ ፤ ጋሜል ፡ ግሩም
ዕ ፡ ዔ ፡ ዐቢይ ፤ ዝ ፡ ዛይ ፡ ዝኩር ፡ እግዚአብሔር ፡ ግእዝ ፡ ተብሎ ፡ በልዑል ፡ እግዚአ
ሔር ፡ ስም ፡ ይጠራል ፡ እንጂ ፤ በፍጡራን ፡ ስም ፤ እንዲሁም ፡ ባለቋንቋዎቹ ፡ አግዓ
ያን ፡ ተብለው ፡ በስሙ ፡ ይጠሩበታል ፡ እንጂ ፤ ቋንቋው ፤ በባለቋንቋዎቹ ፡ ስም ፡ አይ
ራምና ፡ ለቀዳማዊነቱ ፤ ጠቅላላ ፡ ማስረጃ ፡ ሊኾነን ፡ ችሎዋል ።

፳፩ ፤ አባቶቻችን ፡ ስለ ፡ ግእዝ ፡ ሲተርኩ ፤ ድምፁ ፡ በአማካይ ፡ አፍ ፡ አከፋፈ
መነገሩ ፤ በአርአያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከማዕከለ ፡ ምድር ፡ (ቀራንዮ) ፡ ለተፈጠረው ፡ በ
ማይና ፡ በምድር ፡ መካከል ፡ ላለው ፡ በራሪና ፡ ተሽከርካሪ ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፤ የጸጋ
ገዥ ፡ ኹኖ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ በታች ፡ ከፍጡራን ፡ በላይ ፤ ማዕከላዊ ፡ ማዕርግ ፡ ክብር
ለተሰጠው ፡ ለአዳም ፡ የተሰጠ ፡ ቋንቋ ፡ በመኾኑ ፡ ነው ።

፳፪ ፤ በሰናዖር ፡ ሜዳም ፤ የሰው ፡ ልጆች ፡ ግንብ ፡ ለመሥራት ፡ በጀመሩ ፡ ጊዜ
የተስማሙበት ፡ የውል ፡ ጽሑፍ ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይተርኩ
ነበር ። አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌም ፡ የግእዝን ፡ ነገር ፤ ጠልቀው ፡ ጠንቅቀው
ያወቁ ፡ የጀርመን ፡ ሊቃውንት ፡ ግእዝ ፤ አዳምና ፡ እግዚአብሔር ፡ ይነጋገሩበት ፡ የ
በረ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ ብለው፡ የግእዝን ፡ ነገር ፤ ከኢትዮጵያውያን ፡ ይልቅ ፡ አው
ፓውያን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ እርግጡን ፡ እንዲተርኩ ፤ በወሬ፡ሳይኾን ፡ ያዩትን ፡ የሰመ
ትን ፡ መስክረዋልና ፡ የአለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌን ፡ መጽሐፍ ፡ ተመልከት ።

፳፫ ፤ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፤ የግእዝን ፡ ፊደሎች ፡ እንደ ፡ አቀማመጣቸው ፤ በፊተ
ውና ፡ በኋለኛው ፡ ተራ ፡ እንጥፋለን ።



<u>ቀዳማዊ ፡ ፊደለ ፡ ግእዝ ።</u>

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አ—አሌፍ ፡ አልፍ ፡ አብ ፡ | አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| በ—ቤት ፡ ባዕል ፡ | በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ገ—ጋሜል ፡ ገምል ፡ | ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ደ—ዳሌጥ ፡ ድ ፡ ( ን ፡ ) ልት ፡ ድልው ፡ | ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ሀ—ሄ ፡ ሆይ ፡ ሀወይ ፡ | ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ወ—ዋው ፡ ዋዌ ፡ ዋሕድ ፡ | ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዘ—ዛይ ፡ ዛይን ፡ ዝኩር ፡ | ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ሐ—ሔት ፡ ሐውት ፡ ሕያው ፡ ሕይወት ፡ | ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| ኀ—ኀርም ፡ ኄር ፡ | ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ጠ—ጤት ፡ ጠይት ፡ ጠቢብ ፡ | ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| የ—ዮድ ፡ የማን ፡ ቀኝ ፡ እጅ ፡ | የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ከ—ካፍ ፡ ከሃሊ ፡ | ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ለ—ላሜድ ፡ ለዊ ፡ ልዑል ። | ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| መ—ሜም ፡ ማይ ፡ ምዑዝ ፡ | መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ነ—ኖን ፡ ነሐስ ፡ ንጉሥ ፡ | ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ሠ—ሣምኬት ፡ ሠውት ፡ | ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ዐ—ዔ ፡ ዐይን ፡ ዐቢይ ፡ | ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ፈ—ፌ ፡ ፈፍ ፡ ፍቁር ፡ | ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ጸ—ጻዴ ፡ ጸደይ ፡ ጽድቅ ፡ | ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ—ፀጸ ፡ ፀጳ ፡ | ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ቀ—ቆፍ ፡ ቅዱስ ፡ | ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| ረ—ሬስ ፡ ርእስ ፡ | ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ—ሳን ፡ ስቡሕ | ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ተ—ታው ፡ ታዊ ፡ ትጉህ ፡ | ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ጰ—ጳይት ፡ ጴት ፡ | ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ፐ—ፒ ፡ ፔ ፡ ፌ ፡ | ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| | | ዲ | ቃ | ሎ | ች | ። | |
| ገ— | | ጐ | ጕ | ጓ | ጔ | ጕ | |
| ኀ— | | ኈ | ኍ | ኋ | ኌ | ኍ | |
| ከ— | | ኰ | ኵ | ኳ | ኴ | ኵ | |
| ቀ— | | ቈ | ቍ | ቋ | ቌ | ቍ | |

<u>ዋየሎቹም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።</u>

ዉ ዩ ኣ ዮ ህ ዎ

www.ethiopianorthodox.org

## ኹለተኛው ፡ ፊደል ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

## ዲቃሎች ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ኈ | ኊ | ኍ | ኋ | ኌ |
| ቈ | ቊ | ቍ | ቋ | ቌ |
| ኰ | ኲ | ኵ | ኳ | ኴ |
| ጐ | ጒ | ጕ | ጓ | ጔ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |



| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |

፳፩ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፤ የዘረዘርናቸው ፤ በግእዝ ፡ ፊደላት ፤ ኹለት ፡ አ ፡ ዐ ፡ ሦስት ፡ ሀ ፡ ሐ ፡ ኀ ፡ ኹለት ፡ ሠ ፡ ሰ ፤ ሁለት ፡ ጸ ፡ ፀ ፡ ይገኙባቸዋል ።

፳፪ ፤ ምስጢሩም ፤ ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፤ አ ፡ አልፋ ፡ ዐ ፡ ዐይን ፡ ያሜጋ ፡ ብላ ፡ እግዚአብሔር ፤ ከፍጡራን ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ ቀዳማዊ ፡ ጥንት ፡ ፍጡራንን ፡ አሳልፎ ፡ በማይቈጠር ፡ ዘመን ፡ የሚኖር ፤ ደኃራዊ ፡ ተፍጻሜት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

፳፫ ፤ ሀ ፡ ሃሌ ፡ ሆይ ። ሐ ፡ ሐውት ፡ ሐመር ። ኀ ፡ ኀርም ፡ ኄር ፤ ብላ ፡ ልዩ ፡ ቅርጥ ፡ ያላቸውን ፡ ሦስት ፡ ፊደላት ፡ በአንድ ፡ ድምጥ ፡ በመናገሯ ፡ ቀዳማዊ ፡ ደኃራዊ ፡ እግዚአብሔር ፤ መጠቅለል ፡ መቀላቀል ፡ በሌለባቸው ፡ በሦስት ፡ አካላት ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፤ እንደ ፡ አካላት ፡ ከሦስት ፡ በማይከፈል ፡ በአንድ ፡ መለኮት ፤ የሚታመን ፡ የሚመለክ ፤ በአንድነቱ ፡ ምንታዌ ፤ (መንታነት) ፤ በሦስትነቱ ፡ ርባዔ ፡ (አራትነት) ፡ የሌለበት ፤ በልዩ ፡ ሦስትነት ፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ።

፳፬ ፤ ሠ ፡ . . ሣምኬት ፡ ሰ ፡ . . ፡ ሳን ፡ ብላ ፡ ልዩ ፡ ቅርጥ ፡ ያላቸው ፡ ኹለት ፡ ፊደላት ፡ በአንድ ፡ ድምጥ ፡ መናገሯ ፤ ከተዋሕዶ ፡ በፊት ፤ እየራሳቸው ፡ ልዩ ፡ አካል ፤ ልዩ ፡ ባሕርይ ፤ የነበራቸው ፡ መለኮትና ፡ ሰውነት ፤ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ከኾነበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፤ መንታነት ፡ ስለ ፡ ጠፋ ፤ አንድነት ፡ ስለ ፡ ጠና ፤ እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ መኾኑ ፡ ቀርቶ ፤ እንደ ፡ ሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ነቅ ፡ የሌለበት ፡ ፍጹም ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

፳፭ ፤ ጸ ፡ ጻድቅ ፤ ፀ ፡ ፀሐይ ፡ ብላ ፤ ልዩ ፡ ቅርጥ ፡ ያላቸውን ፡ ፊደላት ፡ በአንድ ፡ ድምጥ ፡ መናገሯ ፤ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኹለቱ ፡ ጡቶቿ ፤ ማለት ፤ ኹለቱ ፡ ሕግጋት ፡ ኦሪትና ፡ ወንጌል ፤ ከአንድ ፡ አምላክ ፡ ተገኝተው ፤ አንድ ፡ ክርስቶስን ፡ የሚሰብኩ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፤ ራሱዋ ፡ የምታምን ፤ ለሌላው ፡ የምታስተምር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ።

፳፮ ፤ እንግዲህ ፡ ኦሪት ፡ ነቢያት ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክህን ፤ በፍጹም ፡ ዐሳብኽ ፤ በፍጹም ፡ ልብኽ ፡ ውደድ ፡ በሚለውና ፤ ወንድምህን ፡ እንደ ፡ ራስኽ ፡ አድርገኽ ፡ ውደድ ፡ በሚለው ፤ በእነዚህ ፡ ኹለት ፡ ትእዛዛት ፡ ጠንተው ፡ እንዲኖሩ ፡ በቅርጥ ፤ በቦታ ፡ ተለያይተው ፡ ተነጣጥለው ፡ በድምጥ ፤ ተጣምረውና ፡ ተዋሕደው ፡ በሚነገሩት ፡ በእነዚህ ፡ ዘጠኝ ፡ ፊደላት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖትና ፡ እውነት ፡ ሰላምና ፡ ሕይወት ፡ ክብርና ፡ ፍቅር ፡ ክህነትና ፡ መንግሥት ፡ ታሪክን ፡ የተጐናጠፈ ፡ ስም ፤ እነዚህ ፡ ዘጠኙ ፡ የክብር ፡ ደረጃዎች ፡ በነጻነት ፡ ጠንተው ፡ ይኖራሉ ። ማር ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፳፱—፴፩ ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፵ ፤ ስለዚህም ፡ ከእነዚህ ፡ ትእዛዛት ፤ አንዷቱ ፡ ታንሳለች ፡ ብሎ ፡ ራሱ ፡ የሚ
ሽር ፤ ለሌላው ፡ የሚያስተምር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ውጭ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ከእ
ነዚህም ፡ ፊደላት ፡ አንዷቱ ፡ ታንሳለች ፡ ብሎ ፡ ራሱ ፡ የሚሽር ፡ ለሌላው ፡ የሚያስተ
ምር ፡ ከኢትዮጵያዊነት ፤ ውጭ ፡ ክብሩን ፡ የጠላ ፡ መኾኑ ፡ ነውና ፤ ፊደላትን ፡ ከመ
ፋቅ ፤ ምስጢራቸውን ፡ እንወቅ ።

ይህን ፡ ታላቅ ፡ ቋንቋ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዕድል ፡ አድርጎ ፡ የሰጠ ፡ እግዚአብሔር
አምላክ ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ የቋንቋ ፡ መሠረት ፡ ምንድን ፡ ነው ?

፪ ፤ ፊደል ፡ ምንድን ፡ ነው ? የተገኘስ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ?

፫ ፤ ቋንቋ ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ሄኖስ ፡ እንዴት ፡ ነበረ ? በኋላስ ፡ ምን ፡ ተገኘ

፬ ፤ የፊደላት ፡ መደበኛ ፡ ቊጥራቸው ፡ ስንት ፡ ነው ?

፭ ፤ ተደራቢዎች ፡ ፊደላት ፡ ስንት ፡ ናቸው ?

፮ ፤ ፊደላት ፡ በጠቅላላው ፡ ስንት ፡ ይኾናሉ ፡ ? ምክንያቱስ ፡ ምንድን ፡ ነው

፯ ፤ ጥፈት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተጀመረ ?

፰ ፤ ሰው ፡ በጥፈት ፡ ምን ፡ ጥቅም ፡ አገኘ ?

፱ ፤ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ መጣፎች ፡ መጽሐፈ ፡ ሄኖክ ፡ እን
ዴት ፡ ተገኘ ?

፲ ፤ የፍልስፍናን ፡ መጽሐፍ ፡ ማን ፡ አገኘው ?

፲፩ ፤ ቃይናን ፡ የፍልስፍናውን ፡ ትምህርት ፡ ምን ፡ አደረገ ? በዚህስ ፡ ትም
ርት ፡ ዓለም ፡ ምን ፡ ተጠቀመ ?

፲፪ ፤ አዳም ፡ በገነት ፡ ሳለ ፡ ቋንቋ ፡ እንዴት ፡ ነበረ ? ከዚያስ ፡ በኋላ ፡ እን
ዴት ፡ ኾነ ?

፲፫ ፤ ከቋንቋ ፡ ዕጣችን ፡ ማነው ?

፲፬ ፤ ግእዝ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ሊያናግር ፡ አይችልምን ? የዓለም ፡ ፊደላትስ
ይመስሉታልን ?

፲፭ ፤ ኹለተኛው ፡ ማስረጃ ፡ ምን ፡ ይገልጥልናል ?

፲፮ ፤ አዳም ፡ ስንት ፡ ዐይነት ፡ ነገሮች ፡ ያሉት ፡ ፍጥረት ፡ ነው ?

፲፯ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለአዳም ፡ የሰጠው ፡ ሀብታት ፡ ስንት ፡ ናቸው ?

፲፰ ፤ በባቢሎን ፡ የተመሠረቱ ፡ ቋንቋዎች ፡ እንዴት ፡ ይነገራሉ ? ምሳሌ
ዎችን ፡ ስጥ ።

፲፱ ፤ ግእዝ ፡ ከሌሎቹ ፡ ቋንቋዎች ፡ ልዩነቱ ፡ ምንድን ፡ ነው ?

፳ ፤ በፊደላት ፡ ውስጥ ፡ በመልክ ፡ በቅርጥ ፡ የሚለያዩ ፤ በስም ፡ አንድ
የኾኑ ፡ ማን ፡ ማን ፡ ናቸው ?

፳፩ ፤ የአ ፡ ዐ ፡ ምስጢር ፡ ምንድን ፡ ነው ?



፳፪ ፤ የሀ ፡ ሐ ፡ ኀ ፡ ምስጢር ፡ ምንድን ፡ ነው ?

፳፫ ፤ የ ፡ ሠ ፡ ሰ ፡ ምስጢር ፡ ምንድን ፡ ነው ?

፳፬ ፤ የጸ ፡ ፀ ፡ ምስጢር ፡ ምንድን ፡ ነው ?

፳፭ ፤ ኢትዮጵያ ፤ ልዩ ፡ ቅርጥ ፡ ያላቸውን ፡ ፊደላት ፡ በአንድ ፡ ስም ፡ መጥ
ራቷ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ?

፳፮ ፤ አሪት ፡ ነቢያት ፡ በምን ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ? የዘጠኙ ፡ ፊደላት ፡ ፍሬ ፡
ምንድን ፡ ነው ?

፳፯ ፤ ፊደላትን ፡ ከመፋቅ ፡ የሚሻል ፡ ምን ፡ ነገር ፡ አለ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

## ልምላሜ ።

፩ ፤ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ኖኅ ፡ በነበረው ፡ ዘመን ፤ ምድርን ፡ ለማጠጣት ፤ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ የሚሄድ ፡ የመስኖ ፡ ውሃ ፡ ወይም ፡ ጉም ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ዝናም ፡ አልነበረም ።

፪ ፤ ከማየ ፡ አይኅ ፡ በኋላ ፡ በኖኅ ፡ ዕድሜ ፡ በ፮፻ ፡ ዓመት ፡ ኖኅ ፡ ከመርከብ ፡ ወጥቶ ፤ ከአባቶቹ ፡ እንደ ፡ ተማረው ፤ ከንጹሓን ፡ እንስሳት ፡ ወገን ፤ መሥዋዕት ፡ በአቀረበ ፡ ጊዜ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ መልካሙን ፡ መዓዛ ፡ ተቀብሎ ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ መዝራት ፡ ማጨድ ፡ ብርድ ፡ ትኩሳት ፡ በጋ ፡ ክረምት ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ የማይቋረጥ ፡ መኾኑን ፡ ከተናገረ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፤ ምድር ፡ በመስኖ ፡ ውሃ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፤ የሰማይ ፡ ዝናም ፡ ጠጥታ ፤ ልዩ ፡ ልዩውን ፡ ዘርና ፡ ተክል ፡ የምታስገኝ ፡ ኹናለች ።

፫ ፤ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማይን ፡ በደመና ፡ በጋረደ ፡ ጊዜ ፡ አረንጓዴ ፡ ቢጫ ፡ ቀይ ፡ የኾነ ፡ ቀስቱን ፡ በደመና ፡ ላይ ፡ ሲገልጽ ፤ በሱና ፡ በፍጡራን ፡ መካከል ፡ ያቆመውን ፡ ጽኑ ፡ ኪዳን ፤ ዐስቦ ፤ ምሕረቱን ፡ የማያርቅ ፡ መኾኑን ፡ ለኖኅ ፡ ስለ ፡ ነገረው ፤ የአራሹና ፡ የእርሻው ፡ ተስፋ ፡ በዝናም ፡ ላይ ፡ የጸና ፡ ኾነ ።

፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፤ ዓለምን ፡ በአደሰበትና ፡ የሕይወትን ፡ በር ፡ በከፈተበት ፡ ዘመን ፤ ከኖኅ ፡ ጋራ ፡ ጽኑ ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ። መታሰቢያነቱም ፡ የማይደመሰሰውን ፤ አረንጓዴ ፡ ቢጫ ፡ ቀይ ፡ የኾነ ፡ ቀስቱን ፡ ለኪዳኑ ፡ ምልክት ፤ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ሰጠ ፤ ይህ ፡ መታሰቢያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ኀምሳ ፡ ዘመን ፡ ሲሠራ ፡ ኖሮ ፡ እነሆ ፡ ደርሰንበታል ።

፭ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ መዝራት ፡ ማጨድ ፡ ብርድ ፡ ትኩሳት ፡ በጋ ፡ ክረምት ፤ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ አይቋረጥም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፤ ዓለም ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ ተስፋውን ፡ አጽንቶ ፡ እርሻን ፡ በማስፋፋቱ ፤ በመስኖ ፡ ከሚያገኘው ፡ ጥቅም ፡ በበለጠ ፡ በበጋና ፡ በክረምት ፡ ሲጠቀምባቸው ፡ ይኖራል ።

፮ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ክረምት ፡ ከሌላው ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ ልዩ ፡ መኾኑን ፡ ማንም ፡ ስለሚያውቀው ፤ ብዙ ፡ ማተት ፡ ባያሻም ፡ ቅሉ ፤ የልምላሜዋን ፡ ነገር ፡ በምንናገርበት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ ፤ ለልምላሜዋ ፡ መሠረት ፡ የኾነውን ፡ የክረምት ፡ ጊዜዋን ፡ ሳናስታውስ፡በቸልታ ማለፍ ፡ ስለ ፡ አልተገባን ፤ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ክረምት ፡ በአጭሩ ፡ እናትታለን ።

፯ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ክረምት ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ ከኖኅ ፡ እጅ፡ መልካሙን መዓዛ ፡ መሥዋዕት ፡ ተቀብሎ ፡ የማይሻር ፡ የማይለወጥ ፡ ኪዳኑን ፡ ባቆመበት ፤ ለመ መሪያ ፡ ጊዜ ፡ ሰማይን ፡ በደመና ፡ በጋረደበት ፡ ለኪዳኑ ፡ ምልክት ፡ የኾነው ፡ ቀስቱን በደመና ፡ በአኖረበት ፤ ዝናመ ፡ ምሕረት ፡ ጠለ ፡ በረከት ፡ መስጠትን ፡ በጀመረበት በሰኔ ፡ ወር ፡ ተጀምሮ ፡ በመስከረም ፡ ወር ፡ ይፈጸማል ።

፰ ፤ በዚህም ፡ መሠረት ፡ ጊዜውን ፡ ሳይለውጥ ፤ ወራቱን ፡ ሳያናውጥ ፡ በዚያው በጥንቱ ፡ መሠረቱ ፡ ሲመላለስ ፡ ይኖራል ።

፱ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማይን ፡ በደመና ፡ በጋረደ ፡ ጊዜ ፤ በደመና ፡ ላይ የተሣለውን ፡ ቀስቱን ፡ አይቶ ፡ የኖኅን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሲያስብ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ለ ስቱ ፡ ተመሳሳይ ፡ የኾነውን ፡ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፤ በሰማይና ፡ በምድር ፡ መካከል ፡ እያው በለበች ፤ በኖኅ ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ ያላትን ፡ እምነት ፡ እየገለጸች ፡ ለኖኅ ፡ የሰጠውን ፡ መሐላ ( ኪዳን ) ፡ እንዲያጸናላት ፤ ምሕረቱንም ፡ እንዳያስቀርባት ፤ ስለምታማፅነው ፤ መዝራት ማጨድ ፡ብርድ ፡ ትኩሳት ፡ በጋ ፡ ክረምት ፡ ሳይለወጡ ፡ ሳይቋረጡ ፤ እንደ ፡ እግዚ ብሔር ፡ ቃል ፡ እነሆ ፡ አሉ ፡ ወደፊትም ፡ ይኖራሉ ።

፲ ፤ ኢትዮጵያ ፤ የነፋስ ፤ የእሳት ፡ የመሬት ፡ የውሃ ፡ ምግብና ፡ የምታገኝባቸው ባንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፤ አራት ፡ ክፍላተ ፡ ዘመን ፡ አሉዋት ። አከፋፈላቸውም ፡ እንደሚ ከተለው ፡ ነው ።

፲፩ ፤ አንደኛ ፡ ከመስከረም ፡ ፳፮ ፡ እስከ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፭ ፡ መጸው ፡ ይባላል የነፋስ ፡ ወራት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፤ ቅጠል ፡ የነበረው ፡ ያብባል ፤ አበባ ፡ የነበረው ያፈራል ፤ ያላደገውም ፡ ያድጋል ።

፲፪ ፤ ኹለተኛ ፡ ከታኅሣሥ ፡ ፳፮ ፡ እስከ ፡ መጋቢት ፡ ፳፭ ፡ ሐጋይ ፡ ( በጋ ) ይባላል ፤ የሙቀት ፡ ወራት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያላፈራው ፡ ያፈራል ፤ ያፈራው ( ጮርቃው ) ፡ ይበስላል ፤ የበሰለው ፡ ይደርቃል ፤ ይታጨዳል ፡ ይወቃል ።

፲፫ ፤ ሦስተኛ ፤ ከመጋቢት ፡ ፳፮ ፡ እስከ ፡ ሰኔ ፡ ፳፭ ፡ ጸደይ ፡ (ለቆ) ፡ ይባላል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፤ ጉል ፡ ቢያነሡ ፡ ድንጋይ ፡ ቢፈነቅሉ ፡ ገቦ ፡ ቡቃያ ፡ ይገኛል ። ዝናምም ( አዘንም ፡ ለክሙ ፡ ጸደየ ፡ ወመጸወ ) ፡ የለቆውን ፡ የገፋን ፡ ዝናም ፡ እሰጣችኋለሁ ባለው ፡ መሠረት ፡ በመጠኑ ፡ ይዘንማል ፡ ከአዝርእትም ፤ የአገዳ ፡ እኽል ፡ ዐይነቶች ዘንጋዳን ፡ ማሽላን ፡ የባሕር ፡ ማሽላን ፡ የመሰሉት ፡ ይዘራሉ። ዱባን ፡ ቅልን ፡ የመሰሉ ተክሎች ፡ ይተከላሉ ። በበልግ ፡ የተዘሩትም ፡ ፍሬያቸውን ፡ ይሰጣሉ ። ኢዩ ፡ ፪፡፳፫-፳፭፡

፲፬ ፤ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ክፍላተ ፡ ዘመን ፤ መጸው ፡ ሐጋይ ፡ ጸደይ ፤ በዐማርኛ፡ ገፍ በልግ ፡ ለቆ ፡ ይባላሉ ። ትርጓሜውም ፤ መጸው ፡ ገፍ ፡ መባሉ ፤ ክረምቱ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ጠል ፡ ለመከር ፡ እየገፋ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ነው ።



፲፭ ፤ ሐጋይ ፤ በልግ ፡ መባሉ ፤ በሙቀቱ ፡ ወራት ፡ የሚገኘው ፡ ዝናም፡ በከፊል፡ በጥቂት ፡ አገሮች ፡ ብቻ ፡ ፍሬውን ፡ ስለሚሰጥና ፡ ያለ ፡ ዘመኑ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ ነው ።

፲፮ ፤ ጸደይ ፤ ለቆ ፡ መባሉ ፡ በዚህ ፡ ወራት ፡ የሚገኘው ፡ ዝናም ፤ ለክረምቱ ፡ እንደ ፡ ዋዜማ ፡ ተቀዳሚ ፡ ኾኖ ፡ በመገኘቱ ፡ የፀሐይ ፡ ኀይል ፡ ለጎዳው ፡ መሬት ፤ የመ ጀመሪያውን ፡ ልምላሜ ፡ ስለሚሰጥ ፤ ለቈጽል ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፲፯ ፤ አራተኛ ፤ ከሰኔ ፡ ፳፮ ፡ እስከ ፡ መስከረም ፡ ፳፭ ፡ ክረምት ፡ ይባላል ፤ የውሃ ፡ ወራት ፡ ማለት ፡ ነው ።

፲፰ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሰማይ ፡ በደመና ፡ ይጋረዳል ፤ ተራራው ፡ ኮረብታው፡ በጉም፡ ይሸፈናል ፤ ሌት ፡ ቀን ፡ ሳይለይ ፡ ይዘንማል ፤ ወንዞች ፡ ታላቁም ፡ ታናሹም ፡ ይመላሉ ።

፲፱ ፤ ጐርፎች ፤ ከልካቸው ፡ ከወሰናቸው ፡ አልፈው ፤ ተራራውን ፡ ኮረብታውን ፡ ይንዳሉ ፤ ድምጣቸው ፤ ልብን ፡ ያናውጣል ፡ ምላታቸውም ፡ ለዐይን ፡ ያስደነግጣል ፤ መብረቅ ፡ ብልጭ ፤ ብልጭ ፡ ይላል ፤ ነጐድጓድም ፡ የግርማ ፡ ድምጡን ፡ ይሰጣል ። ምድርም ፡ እንደ ፡ ሠም ፡ ትቀልጣለች ። መዝ ፡ ፸፬፡ቍ ፡ ፭-፱ ። መዝ ፡ ፸፴፭ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

፳ ፤ ወመንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጼልል ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ፡ እንዲል፤ ውሃን፡ የፈጠረ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፤ በውሃ ፡ ላይ ፡ ባያጸናት ፡ ኖሮ ፤ በውስጧ ፡ ያሉ ፡ ኹሉ ፡ ተስፋ ፡ በቈረጡ ፡ ነበር ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፪ ። ነገር ፡ ግን ፡ በኖኅ ፡ ኪዳን ፡ አማካይነት ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በተመደበው ፤ ኢትዮጵያዊው ፡ ክረምት ፡ የሚገኘው ፡ ዝናም ፤ ለምሕረትና ፡ ለበረከት ፤ ለመዝራትና ፡ ለማጨድ ፡ እንዲኾን ፡ የተ ነገረ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምነው ፤ ኢትዮጵያውያን ፡ ገበሬዎች ፤ በሐምሌ ፡ በነ ሐሴ ፡ ከላይ ፡ ዝናም ፡ ተግብ ፡ ውሽንፍር ፡ እያጠናፈራቸውና ፡ እያማታቸው ፤ ከታች ፡ ጐርፍ ፡ ድጥ ፡ ወልቅ ፡ ጭቃ ፡ እያላጋቸውና ፡ እያንገላታቸው ፡ ዘርን ፡ ይዘራሉ ።

፳፩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ ትክሻቸው ፡ ዘር ፤ በአንድ ፡ ትክሻቸው ፡ ቀንበር ፡ ተሸክመው ፤ እነሱ ፡ እንዲዘሩ ፡ እንዲተክሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲያሳድግ ፡ ልምላሜ ፡ ፍሬ ፡ እንዲሰጥ ፡ አምነው ፤ በዕንባ ፡ የዘሩትን ፤ በመከር ፡ ወራት ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ያጭ ዳሉ ፡ ይወቃሉ ፤ ምርቱን ፡ ያፍሳሉ ። በእግዚአብሔር ፡ በረከትም ፡ አንዱ ፡ ቅንጣት ፡ ፍሬ ፡ ሠላሳ ፡ ስሳ ፡ መቶ ፡ ቅንጣት ፡ ስለሚያፈራላቸው ፤ ከዘሩት ፡ በላይ ፡ መቶ ፡ ዕጥፍ ፡ ያገኛሉ ። መዝ ፡ ፻፳፯ ፡ ቍ ፡ ፭ ፡ ፮ ። ዕብ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

፳፪ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በኖኅ ፡ ቃለ ፡ ኪዳን ፡ የመሠረተውን ፡ ክረምት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዕድል ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ሰጣት ፤ ኢትዮጵያ ፤ ከሌላው ፡ ክፍል ፡ በበለጠ ፡ ልምላሜ ፡ አጊጣና ፡ አሸብርቃ ፤ ውበት ፡ ባላቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አበባዎች ፡ ደምቃ ፡ ትታ ያለች ።

፳፫ ፤ እርሻዎቿ ፡ ፍሬዎቻቸውን ፡ በመቶ ፡ ዕጥፍ ፡ ይሰጣሉ ። ምንጮቿ ፡ የሕይ ወት ፡ ውሃን ፡ ያፈልቃሉ ። ወንዞቿ ፡ አድልዎ ፡ እንደ ፡ ሌለበት ፡ መልካም ፡ አዳይ ፡ በያ ውራጃዎቿ ፡ ያከፋፍላሉ።ደጋዎቿና ፡ ቆላዎቿ ፤ ዋንዛ ፡ ዘግባ ፡ ጥድ ፡ ዞጲ ፡ እነሱንም ፡ የመሳሰሉ ፡ የማይነቅዙ ፡ ዕንጨቶች ፡ ያበቅላሉ ። ዕጣን ፡ ከርቤ ፡ እነሱንም ፡ የመሳሰሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሽቱ ፡ ዐይነቶች ፡ ያስገኛሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፬ ፤ በጠቅላላው ፡ ሞት ፡ ኀዘን ፡ ሕማም ፡ ድካም ፡ ባይኖሩ ፡ ኖሮ ፤ ኢትዮጵያን ገነት ፡ ናት ፡ ለማለት ፡ የሚያሳፍር ፡ አልነበረም ።

ይህችን ፡ ለምለም ፡ አገር ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ የሰጠን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ኖኅ ፡ ስለ ፡ ልምላሜ ፡ ምድር ፡ በምን ፡ ትጠቀም ፡ ነበር ?

፪ ፤ ኖኅ ፡ ከመርከብ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ መሥዋዕት ፡ ቢሠዋ ፡ እግዚአብሔር ምን ፡ አለው ?

፫ ፤ ምድርሳ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ምን ፡ አገኘች ?

፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰማይን ፡ በደመና ፡ በጋረደ ፡ ጊዜ ፡ የአራሽ ፡ ተስፋ ፡ ምድን ፡ ነው ?

፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ ዓለምን ፡ ባደሰ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አደረገ ? መታሰቢያውስ ስንት ፡ ዘመን ፡ ሠርቶዋል ?

፮ ፤ ዓለም ፤ ከመስኖ ፡ ውሃ ፡ በበለጠ ፡ በክረምት ፡ ዝናም ፡ ምን ፡ ይጠቀማል ?

፯ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ክረምትና ፡ የሚፈጸሙት ፡ ወራቶች ፡ ማን ፡ ማን ፡ ናቸው ?

፰ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በኖኅ ፡ አምላክ ፡ ስለምታመልክ ፡ ምን ፡ አገኘች ?

፱ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ስንት ፡ ክፍላተ ፡ ዘመን ፡ አሉዋት ?

፲ ፤ መጸው ፡ የሚባለው ፡ ከመቼ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ? ምንስ ፡ ይገኝበታል ?

፲፩ ፤ ኹለተኛውስ ፡ ክፍል ፡ ማነው ? በሱስ ፡ ምን ፡ ይገኛል ? ከ ፡ እስከ አስረዳ ።

፲፪ ፤ በለቆ ፡ ከአዝርዕት ፡ ምን ፡ ምን ፡ ይዘራሉ ? ከአትክልት ፡ ምን ፡ ምን ፡ ይተከላሉ ?

፲፫ ፤ አራተኛውስ ፡ ምን ፡ ይባላል ? በክረምት ፡ ምን ፡ ምን ፡ እንደሚገኙበት አስረዳ ።

፲፬ ፤ ገበሬዎች ፡ በፊት ፡ ምን ፡ ይደርስባቸዋል ፡ በኋላሳ ፡ ምን ፡ ያገኛሉ ?

፲፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለኖኅ ፡ የሰጠውን ፡ ክረምት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በማድረጉ ምን ፡ አግኝታበታለች ?

## ሕገ ፡ ኦሪት ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

## ኢትዮጵያ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ።

፩ ፤ ሰው ፡ በተፈጥሮ ፡ በተሰጠው ፡ ዕውቀቱ ፡ ፈጣሪውን ፡ ዐውቆ ፡ ሕጉን፡ጠብቆ በመላእክት ፡ አምሳል ፡ ሊኖር ፡ እንጂ ፤ በቀለም ፡ በወረቀት ፡ ሊመራ ፡ የተፈጠረ አለመኾኑን ፡ መላልሰን ፡ ባለፈው ፡ አስረድተናል ።



፪ ፤ ስለዚህም ፡ ሰው ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፤ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፤ በዚህ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፤ በተፈጥሮ ፡ ዕውቀቱ ፡ ሊጠቀምበት ፡ ስለ ፡ አልቻለ፤ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ በአምሳለ ፡ ንጉሥ፡ ተገልጦ ፤ ለዕውቀቱ ፡ አጋዥ ፡ ረዳት ፡ ይኾነው ፡ ዘንድ ፤ ሕግን ፡ በገበታ ፡ ላይ ፡ ጽፎ ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ ሰጠው ፡ ዘፀአ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፲፮ና ፡ ፲፯ ።

፫ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፤ ዓለም ፡ በሕግ ፡ እየተመራ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መከተል ፡ ጀመረ ።

፬ ፤ ከኖኅ ፡ ዕድሜ ፡ በኋላ ፡ ከፋሌግ ፡ እስከ ፡ አብርሃም ፡ ፭፻፵፩ ፡ ዓመት ፡ በሕገ ፡ ጣዖት ፤ ከአብርሃም ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ ፬፻፲፭ ፡ ዓመት ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የቈየች ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፤ ከኖኅ ፡ በኋላ ፡ በሺሕ ፡ ፭፻፹፰ ፡ ዓመት ፡ የሕገ ፡ መጽሐፍ ፡ ርዳታ ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ አግኝታለች ።

፭ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ግን ፤ ከኖኅ ፡ ዕድሜ ፡ በኋላ ፡ ፪ሺ ፡ ፩፻፹፩ ፡ ዓመት ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስትመራ ፡ ቈይታ ፤ ከእስራኤል ፡ በኋላ ፡ ፭፻ ፶፫ ፡ ዓመት ፡ በሊቀ ፡ ካህናት ፡ አዛርያስ ፡ እጅ ፤ በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቈየችበት ፡ ሕገ ፡ ልቡና ፤ ክፉና ፡ በጎን ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ ለማጥናትና ፡ ለመጠበቅ ፤ አጋዥ ፡ ይኾናት ፡ ዘንድ ፤ በልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ የተጻፈውን ፡ የሕገ ፡ መጽሐፍ ፡ ርዳታ ፡ አግኝታለች ።

፮ ፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የምትቀድመው ፤ መጽሐፍን ፡ በመቀበል ፡ እንጂ ፤ በእምነት ፡ አይደለም ።

፯ ፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሃይማኖት ፡ የምትቀድም ፡ ቢኾን ፡ ኖሮስ፡ ለነገደ ፡ ሮቤል ፤ ለነገደ ፡ ጋድና ፡ ለነገደ ፡ መንፈቀ ፡ ምናሴ ፤ በዮርዳኖስም ፡ ለሰፈሩ ፤ ወገኖቿ ፡ መሠዊያ ፤ ወይም ፡ መማፀኛ ፡ መሥራትን ፤ እንዲሁም ፤ ደብተራ ፡ ኦሪት ፡ ከቆመችበት ፡ ከአንዲት ፡ ቦታ ፡ በቀር ፤ በቀሩት ፡ አህጉረ ፡ ምስካይ ፤ መሥዋዕት ፡ መሠዋትን ፡ ስትከለክል ፤ ሙሴም ፤ ኢትዮጵያዊት ፡ ሚስት ፡ በማግባቱ ፡ ስታንጐራጕር ፡ የነበረችውን ፡ ያኽል ፤ (ኢይባእ፡ ሞአባዊ ፡ ወዐምናዊ ፡ እስከ ፡ ሣልስ፡ወራብዕ፡ ትውልድ)፡ በምትላቸው ፡ አንጻር ፡ ትመለከታት ፡ ለነበረችው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጽላትን ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ከነሊቀ ፡ ካህናታቸው ፡ በግልጥ ፡ በወፌሴል ፡ ባልሰጠችም ፡ ነበር ። ዘኁ ፡ ም፡፲፪፡ ቍ፡ ፩ ። ኢ.ያ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ቍ፡፲—፴፬ ።

፰ ፤ ነገር ፡ ግን ፤ ኢትዮጵያ ፡ ለአጠናቸው ፡ ሃይማኖት ፡ አጋዥ ፡ የሚኾናት ፡ ትምህርት ፡ እንጂ ፤ አዲስ ፡ ሃይማኖት ፡ ፈላጊ ፡ ባለመኾኗ ፤ ኪዳኑ ፡ አብርሃምን ፡ በማሰብ ፤ ከግብጽ፡ ባርነት ፡ ነጻ ፡ አውጥቶ ፤ ለሱ ፡ ገንዘብ ፡ እንድትኾን ፡ ቤተ፡እስራኤልን፡ የመረጠ ፡ እግዚአብሔር ፤ ኪዳኑ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅን ፡ በማሰብ ፤ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ በአምልኮት ፡ ትከተለው ፡ ለነበረች ፡ አገሩ ፡ ኢትዮጵያ ፤ በሊቀ ፡ ካህናት ፡ አዛርያስ ፡ እጅ ፡ ኪዳኑ ፡ የጸናባት ፡ ጽሌን ፡ (ታቦተ ፡ ጽዮንን) ፡ ሕጉ ፡ ትእዛዙ ፡ የተጣፈበት ፡ መጽሐፈ ፡ ኦሪትን ፡ ሰጣት ።

www.ethiopianorthodox.org

፱ ፤ የኢትዮጵያን ፡ ሃይማኖት ፡ ሰው ፡ አላወቀውም ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔ
ሕጉ ፡ የተጻፈባቸውን ፡ ኹለቱን ፡ ጽላት ፡ ገበታውን ፡ በእጁ ፡ ቀርጦ ፤ ቃሉን ፡ በጣቱ
ጥሮ ፤ ለሙሴ ፡ ሲሰጥ ፤ የአብርሃምና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሀይማኖት ፡ ሚዛኑ ፡ አንድ ፡ መ
ኑን ፡ በረቂቅ ፡ ጥበቡ ፡ ገልጦዋል ።

፲ ፤ ይኸም ፡ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፡ የእግዚአብሔር፡የሥራ፡መሣሪያ፡የኾነውን ፡ ጊ
ሲጠብቅ፡፫፻፺፫፡ዓመት፡ከቈየ፡በኋላ ፤ አንዱቱን ፡ ጽሌ ፤ አማናዊት ፡ ድንግል ፡ ካህኑ ፡ ሳዶ
ንጉሥ፡ሰሎሞን ፡ በያዙት ፡ ዕጣ ፡ ለቤተ ፡ እስራኤል ፡ አንዱን ፡ ጽሌ ፤ ካህኑ ፡ አዛርያስ ፡
ማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በያዙት ፡ ዕጣ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አካፍሎ ፡ በመስጠቱ ፤ የተደበቀውን፡ገል
የረቀቀውን ፡ አጕልቶ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሃይማኖት ፤ በሱና ፡ በኢትዮጵያ ፡ መካከል ፡
ውን ፡ ጥኑ ፡ ፍቅር ፡ ለዓለም ፡ አስረድቶአል ። በዚህ፡ጊዜ ፡ ዕጣ፡ያልነው ፡ ዕድል ፡ ነው

፲፩ ፤ ኢትዮጵያ ፤ እግዚአብሔር ፡ በቸርነቱ ፡ የሰጣትን ፡ ይህንን ፡ ዕድል ፡ ከተ
በለችበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፤ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ትከተለው ፡ የነበረ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብ
ርን ፡ በሕገ ፡ መጽሐፍ ፡ እያጠበቀች ፡ ሀይማኖቷን ፡ እያጠናች ፡ በግልጥ ፡ እየመሰከረች
ተስፋ ፡ እየጨመረች ፡ ሄደች ፡ እንጂ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አ
ችም ፡ ለጣዖታትም ፡ ከቶ ፡ አልተንበረበከችም ።

፲፪ ፤ ባለፈው ፡ እንዳስረዳነው ፡ ኹሉ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተ
ገረው ፡ መሠረት ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከእንቢተኛዪቱ ፡ ትውልድ ፡ ጋራ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከ
ትፋረድባቸው ፡ ሦስት ፡ ነገሮች ፤ ኹለተኛው ፡ ቀጥሎ ፡ የተገለጠው ፡ ነው ።

፲፫ ፤ ይኸውም ፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ በጠላቶቿ ፡ ላይ ፡ ፱ ፡ መቅሠፍት ፡ ፲ኛ ፡ ሞ
በኵር ፤ ፲፩ኛ ፡ ስጥመት ፡ አድርጎ ፡ ከባርነት ፡ ቤት ፡ ያወጣት ፡ በግል ፡ ዕድል ፡ የነ
ላት ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ በደብረ ፡ ሲና ፡ ተገልጦ ፡ መተዳደሪያዋን ፡ ለመሪዋ
ለሙሴ ፡ አስጠንቶ ፡ ሳይጨርስ ፤ ፊት ፡ ለፊት ፡ እያየችው ፡ ከዐይኗ ፡ ሳይሰወር ፤ ለወር
ጥኛ ፡ ስትለውጠውና ፡ ስታሳዝነው ፤ በየጊዜውም ፡ ስታስቈጣው ፡ ኢትዮጵያ ፤ አሪት
በወንጌል ፡ እስክትለወጥላት ፡ ድረስ ፤ ከተቀበለችው ፡ ትእዛዝ ፡ ማንኛውንም ፡ ሳት
ውጥ ፤ ሕጉን ፡ ትእዛዙን ፡ ጠብቃ ፤ አምልኮቱን ፡ አጥንታ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መ
ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ኾና ፡ መኖሯ ፡ ነው ። ዘፀ ፡ ም
፴፪ ፡ ቍ ፡ ፩—፳፫

በውነቱ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ልጅ ፡ ካባቱ ፡ ባይበልጥ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖት ፡ እን
ከቤተ ፡ እስራኤል ፡ ከአዳም ፡ ሃይማኖት ፡ ይበልጣል ፡ ቢባል ፡ የሚያሳፍር ፡ አይደለም

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ሰው ፡ በተፈጥሮ ፡ ዕውቀቱ ፡ ሊጠቀምበት ፡ ስለ ፡ አልቻለ ፡ እግዚአብሔር
ምን ፡ አደረገ ?

፪ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዓለም ፡ ምን ፡ አደረገ ?

፫ ፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ከፋሌግ ፡ እስከ ፡ አብርሃም ፡ በምን ፡ ሕግ ፡ ነበረች ? ከአ
ርሃም ፡ እስከ ፡ ሙሴሳ ?



፬ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ቈይታ ፡ ሕገ ፡ መጽሐፍ ፡ ምን ፡
ጊዜ ፡ አገኘች ።

፭ ፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ኢትዮጵያን ፡ የምትቀድማት ፡ በምን ፡ ነው ?

፮ ፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ኢትዮጵያን ፡ ብትቀድም ፡ ምን ፡ ባደረገች ፡ ነበር ?

፯ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሃይማኖት ፡ ፈላጊ ፡ ነበረችን ? ወይስ ፡ ትምህርት ?

፰ ፤ እግዚአብሔር ፤ ኹለቱን ፡ ጽላት ፡ ለሙሴ ፡ በሰጠ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አስረዳ ?

፱ ፤ በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ እግዚአብሔር ፤ የኢትዮጵያን ፡ ሃይማኖትና ፡ ፍቅር ፡
በምን ፡ አስረዳ ?

፲ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ኦሪትን ፡ ከተቀበለች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትታ ፡ ጣዖትን ፡ ተከት
ላለችን ?

፲፩ ፤ ኢትዮጵያና ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ከሚፋረዱባቸው ፡ ነገሮች ፡ ኹለተኛው ፡
የትኛው ፡ ነው ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

## ኢትዮጵያ ፡ በኦሪት ፡ ያገኘችው ፡ ሀብት ።

፩ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ በየጊዜው ፡ ለሰው ፡ የልግስና ፡ ዐዋጅ ፡ ያደርግለ
ታል ።

፪ ፤ በፊተኛው ፤ አዳምን ፡ ፈጥሮ ፡ በነፍስ ፡ ሕያው ፡ አድርጎ ፡ በልጅነት ፡ አከ
በሮ ፤ በራሪውን ፡ ተሽከርካሪውን ፡ ተላዋሹን ፡ ተንቀሳቃሹን ፡ ግዛ ፡ ኹሉን ፡ ብላ ፡ ነገር ፡
ግን ፡ ክፉና ፡ መልካም ፡ ከምታስታውቀው ፡ ዕንጨት ፡ አትብላ ፡ ብሎታል ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡
ቍ ፡ ፳፮-፴ ። ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፭-፲፯ ። በኋላም ፡ ኖኅንና ፡ ልጆቹን ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ አድኖ ፤
ዓለሙን ፡ አድሶ ፡ ኪዳኑን ፡ ከእነሱ ፡ ጋራ ፡ ሲያጠና ፤ ኹሉን ፡ እንደ ፡ እኽል ፡ እንደ ፡
ተክል ፡ ብሉ ፡ ሰጥቻችኋለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ደም ፡ ወይም ፡ ደሙን ፡ ከነፍሱ ፡ ጋራ ፡
ማለት ፤ በክት ፡ አትብሉ ፡ ብሏቸዋል ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፩—፭ ።

፫ ፤ እንዲሁም ፡ ሰው ፡ ወንድሙን ፡ አራዊትን ፡ እንስሳትን ፡ አዕዋፍንም ፡ ወይም ፡
አራዊት ፤ ሰውን ፡ በግፍ ፡ እንዳይገድሉ ፤ ቢገሉ ፡ ግን ፡ የሚቴን ፡ ደም ፡ ከገዳዩ ፡ እኔ ፡
እፈልገዋለሁ ፡ ሲል ፤ በጥብቅ ፡ አዝዟቸዋል ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፭-፰ ። በዐማርኛ ፡ ቅሉ ፤
እግዚአብሔር ፡ በፍርዱ ፡ አድልዎ ፡ የሌለበት ፡ መኾኑን ፡ ለማስረዳት ፤ የውሻ ፡ ደም ፡
የማያስቀር ፡ ጌታ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ነው ።

፬ ፤ በዚህ ፡ መሠረት ፤ በፊት ፡ ለአዳም ፤ በኋላም ፡ ለኖኅና ፡ ለልጆቹ ፡ ትእዛዙን ፡
እንዲጠብቁ ፡ ካስታወቃቸው ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ተባዙ ፤ ምድርን ፡ ምሏት ፤ ኹሉንም ፡
ምግብ ፡ ሊኾናችሁ ፡ ሰጥቻችኋለሁ ፡ ሲል ፡ ትእዛዙን ፡ በመጠበቅ ፡ የሚገኘውን ፡
ታላቅ ፡ በረከት ፡ ሰጣቸው ።

፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፤ ቃል ፡ በቃል ፡ ያጠናውን ፡ በመዘንጋቱና ፡ በመግደፉ ፤
ማስታወሻ ፡ መከለሻ ፡ መጣፍ ፡ ስለ ፡ አስፈለገው ፤ በኦሪት ፡ ሰባቱን ፡ ሕግጋት ፡ ሦስ

www.ethiopianorthodox.org

ቱን ፡ ትእዛዛት ፤ (ዐሥሩን ፡ ቃላት) ፡ በእነሱም ፡ መሠረትነት ፡ የመሰሏቸውን ፡ ኹሉ
በጥፊት ፡ ገልጠ ፡ አፍርጦ ፡ ትእዛዙን ፡ አስታውቆ ፡ አስጠንቅቆ ፡ ኦሪትን ፡ ብትጠብ
የዘራኸው ፡ የተከልከው ፡ ያምርልሀል ፤ የድልብ ፡ ድልብ ፡ ትበላለህ ፤ የልጅ ፡ ልጅ ፡
ለህ ፡ ብሎ ፡ የኦሪትን ፡ ትእዛዝ ፡ የፈጸመ ፡ ኹሉ ፤ ጻድቅ ፡ ባለበረከት ፡ መኾኑን ፡ አ
ድቷል ። ዘሌዋ ፡ ም ፡ ፳፮ ፡ ቍ ፡ ፲ ።

፯ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ባትጠብቅ ፤ ሰማይ ፡ ብረት ፡ ምድር ፡ ብርት
ይሆንብሀል ፡ ማለት ፡ ሰማይ ፤ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ አይሰጥኽም ፤ ምድር
የዘራኸባትን፡አታበቅልም ፤ የተከልክባትን ፡ አታጽድቅም ፡ ብሎ ፡ ትእዛዙን፡በማይፈጽ
ሰው፡ላይ፡ከፍ፡ያለ፡ቅጣት፡የሚደርስበት፡መኾኑን፡ገልጿል ። ዘሌዋ፡ም፡፳፮፡ቍ፡፲፱፡ተረ
የለመደ ፡ ልማድ ፤ ያሰርቃል ፡ ከማድ ፤ ሌባ ፡ ለዐመሉ ፡ ዳቦ ፡ ይልሳል ፤ ዘር ፡ ከልጓ
ይጠቅሳል ፡ እንደሚባለው ፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፤ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ሳለች ፡ በጥንታውያን
አባቶቿ ፤ በሴሩህ፡ (ግ) ፡ በናኮር ፡ በታራ ፡ የለመደችውን ፡ የጣዖት ፡ ውሽማነት ፤ በሕ
ኦሪትም ፡ ስለ ፡ አልተወች ፤ በዚህም ፡ የውሻ ፡ ዐይነት ፡ ተልከፍካፊ ፡ ልማድ ፡ ባን
ዕጮኛዋ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ተወስኖ ፡ መኖር ፡ ስለ ፡ አልተቻላት ፤ ከ
ከት ፡ ወጥታ ፡ ወደ ፡ መርገም ፡ ገብታ ፤ ያ ፡ የጣዖት ፡ ውሽማነት ፤ በፋርስ ፡ በባቢሎ
ኋላም ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ንባቡን ፡ አጥብቆ ፤ ውሽማ ፡ (ውሻ ፡ ዐይነት ፡ ) አደረጋት

፰ ፤ ሥሩ ፡ መራራ ፡ ከኾነ ፡ ጫፉ ፡ መራራ ፡ እንዲኾን ፡ ሥሩ ፡ የሚጣፍጥ፡ከኾ
ጫፉም ፡ ስለሚጣፍጥ ፤ ኢትዮጵያ ፤ በሕገ ፡ ልቡና ፡ የጥንታዊ ፡ አባቷ ፡ የኖኅን ፡ ዐሥ
ፍኖት ፡ ስትከተል ፡ በመቈየቷ ፤ በሕገ ፡ ኦሪትም ፡ ቀዳማዊ ፡ እምነቷን ፡ በትምህርት
አጐልምሳ ፤ ዕውቀቷን ፡ አድሳ ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፤ ከመርገም ፡ ወጥታ ፤ ወደ ፡ በረከ
ገብታ ፤ በኪዳነ ፡ ኖኅ ፡ ላይ ፡ ኪዳነ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅን ፡ ኪዳነ ፡ አብርሃምን ፡ አዋሕ
ለመውረስ ፡ ሃይማኖቷ ፡ ስለ ፡ አገዛት ፡ መጽሐፈ ፡ ኦሪትን ፡ ከነትምህርቱ ፤
ነተ ፡ ኦሪትን ፡ ከነሥራቱ ፤ ጽሌ ፡ ኦሪትን ፡ ከነመሥዋዕቱ ፤ ተስፋ ፡ ዳዊትን ፡ ከነትንቢ
ዘርዐ ፡ ዳዊትን ፡ ከነበረከቱ ፤ በረከተ ፡ ይሁዳን ፡ ከነምልክቱ ፤ ብኵርናን ፡ ከነቅብዐ
ባለፉት ፡ አንጻር ፡ እነዚህን ፡ ሰባቱን ፡ ሀብታት ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቀብላለች

፱ ፤ እነሱም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በአለፈው ፡ ዐይነት ፡ ኹኔታቸውን ፡ ባጭሩ ፡ እ
ስረዳለን ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ዝርዝር ፡ ከመግባታችን ፡ በፊት ፡ ልናስረዳው ፡ የምን
ደው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ።

፲ ፤ ይኸውም ፤ እነዚህማ ፡ ሀብታት ፡ ለቤተ ፡ እስራኤል ፡ የተሰጡ ፡ ናቸው
እንጂ ፤ ለኢትዮጵያ ፡ የተሰጡ ፡ ናቸውን ፡ ብሎ ፡ የሚጠይቅ ፡ ቢኖር ፤ የእስራኤልነ
ቸውን ፡ ስም ፡ እንዳይጠሩ ፤ ከአሕዛብ ፡ ለይተን ፡ እናጥፋቸው ፡ ብለው ፡ የተማከሩባቸው
ፋርሳውያንና ፡ ባቢሎናውያን ፡ በጠላትነት ፡ ከመነሣታቸው ፡ በፊት ፡ እስራኤል ፡ ከ
ሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ መርጬ ፤ ርስት ፡ አደረግሁኽ እያለ ፡ የሚያቆላምጣት ፡ እግዚአብሔር
ከፊቷ ፡ ሳይርቅ ፤ ከዐይኗ ፡ ሳይሰወር ፤ (ኢይትናገረነ ፡ እግዚአብሔር ፤ አላ ፡ ይትናገረ
ሙሴ ) ፡ ሙሴ ፡ እንጂ ፤ እግዚአብሔር ፡ አይናገረን ፡ ማለትን ፡ ከተናገረችበት ፡ ጊዜ



ምሮ ፤ ተዘከርነ ፡ ዓሣተ ፡ ዘንበልዕ ፡ በምድረ ፡ ግብጽ ፤ ብፁዕ ፡ ዘይበልዕ ፡ እምፍርፋ
ተ ፡ ማዕዱ ፡ ለፈርዖን ፤ ወብፁዕ ፡ ዘይሰቲ ፡ እማየ ፡ ዐይጋቲሃ ፡ ለግብጽ ፤ ይክልኑ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ሠሪዐ ፡ ማዕድ ፡ በገዳም ፤ ይዝብጥ ፡ ኰኵሐ ፡ ወያውኅዝ ፡ ማየ ። አታንጐ
ጕሪ ፡ ቢሏት ፤ በምድረ ፡ ግብጽ ፡ እንበላው ፡ የነበረ ፡ ዓሣ ፡ ምን ፡ ያምር ፤ ከፈ
ዖን ፡ ማዕድ ፡ ፍርፋሪ ፡ የሚበላ ፡ ከግብጽ ፡ ምንጮች ፡ ውሃ ፡ የሚጠጣ ፡ ሰው፡
ስጉን ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እኽል ፡ ውሃ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላልን ?
ያለች ፡ እያንጐራጐረች ፤ አትፈታተኝ ፡ ቢሏት ፡ እየተፈታተነች፤ አታመንዝሪ ፡ ቢሏት፡
ጣዖት ፡ እያመነዘረች ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሊነግሯት ፡ ከተላኩትም ፡ ድንጉጦ
ን ፡ ከበር ፡ እያባረረች ፤ ገፍተው ፡ የመጡትን ፡ በሰይፍ ፡ እየመተረች ፤ በመጋዝ ፡
የተረተረች ፤ በድንጋይ፡እየወገረች ፡ የመቤት ፡ ልጅ ፡ ስትኾን ፡ ያልዘሩ ፡ በቀል፡ ኾና ፤
ባሪያ ፡ ዐመል ፡ ይዛ ፤ አልበላም ፤ አላበራም ፡ እንቢ ፡ ስለ ፡ አለች ፤ ሀብት ፡ በረከት ፤
እንቢተኛዪቱ ፡ ትውልድ ፡ ተነሥቶ ፤ ለታማኝቱ ፡ ለቅን ፡ ታዛገርቱ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ተሰ
ቷል፡ብለን ፡ እንመልስለታለን።ዘኍ፡ም፡፲፩ቍ፡፬-፮።መዝ፡፸፰፡ቍ፡፳።ዘፀ፡ም፡፳፡ቍ፡፲፱።

፲ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ የተገኙ ፡ ፯ቱ ፡ ሀብታት ፤ ቀጥሎ ፡ በፊደል ፡ የተዘረዘሩት ፡
ናቸው ።

ሀ) ፤ መጽሐፈ ፡ ኦሪትና ፡ ትምህርቱ ።

፲፩ ፤ ኦሪት ፤ ዘፍጥረት ፡ (ዘልደት) ፡ ሥነ ፡ ፍጥረትን ፡ ልደተ፡ አበውን ፡ ይሰብካል ።

፲፪ ፤ ኦሪት ፡ ዘፀአት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ተአምራቱን ፡ ጌትነቱን ፡ ይነግራል ።

፲፫ ፤ ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፤ ሥርዐቱን ፡ ሕጉን ፡ ያስረዳል ። ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፡
የቤተ ፡ መንግሥት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ አገልግሎት ፡ ተገቢ ፡ መኾኑንና ፡ በዚህም ፡ አገ
ልግሎት ፡ ተገቢ ፡ የሚኾነው ፤ ምን ፡ ያኽል ፡ ዕድሜ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ መኾኑን ፤ የእግ
ዚአብሔርንም ፡ ፍርድ ፡ ያሳያል ።

፲፬ ፤ ኦሪት፡ዘዳግም፤ከዚህ ፡ በላይ ፡ በአራቱ ፡ ክፍሎች ፡ በሰፊው ፡ የተዘረዘረውን፡
በአጭሩ ፡ እየጠቀለለ ፤ ዐሳቡን ፡ በኢታምልክ ፡ ማለት ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡
ጣዖታት ፡ አምልኮትን ፡ አትጨምር ፡ በማለት ፡ እያጸና ፡ ሃይማኖትን ፡ ያስተምራል ።

፲፭ ፤ ኦሪት ፡ አሁን ፡ በዘረዘርናቸው ፡ በዐምስቱ ፡ ክፍሎች ፡ ተጽፎ ፤ መጽሐፈ ፡
ሙሴ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ትምህርቱም ፡ ይኸ ፡ ነው ።

## ሕ ግ ጋ ት ።

፩ ፤ ከእኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አታምልክ ።
፪ ፤ በሐሰት ፡ አትማል ።
፫ ፤ ነፍስ ፡ አትግደል ።
፬ ፤ አትስረቅ ።
፭ ፤ አታመንዝር ።
፮ ፤ የወንድምኽን ፡ ገንዘብ ፡ አትመኝ ።
፯ ፤ በሐሰት ፡ አትመስክር ።

www.ethiopianorthodox.org

፰ ፤ ትእዛዛት ፡፡ — የእግዚአብሔር ፡ የአምላክህን ፡ ሰንበት ፡ አክብር ፡፡
፱ ፤ እናትህንና ፡ አባትህን ፡ አክብር ፡፡
፲ ፤ ወንድምህን ፡ እንደ ፡ ራስኽ ፡ አድርገኽ ፡ ውደድ ፡፡

መጽሐፈ ፡ ኦሪት ፤ የሚሰጣቸው ፡ ዐይነተኞቹ ፡ የትምህርት ፡ መሪዎች ፡ እነዚ
ናቸው ፡፡ ዘፀ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ ፡ ፫—፲፯ ፡፡ ዘሌዋ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፲፰ ፡፡

፲፮ ፤ በእነዚህ ፡ ቃላት ፡ በተለይም ፡ ከእኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አታምል
በሚለው ፡ ሕግና ፡ ወንድምኽን ፡ እንደራስኽ ፡ አድርገኽ ፡ ውደድ ፡ በሚለው ፡ ትእዛ
ኦሪት ፡ ነቢያት ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፡፡

፲፯ ፤ ስለ ፡ ዐሥሩ ፡ ቃላት ፡ ሰፊውን ፡ ዝርዝር ፡ ነገር ፡ ወደፊት ፡ እናመጣዋለን
ከነሱም ፡ ሌላ ፡ በመጽሐፈ ፡ ኦሪት ፤ በያይነቱ ፡ በየስልቱ ፡ የሚሰጥ ፡ ብዙ ፡ ትምህርት
ስለ ፡ አለ ፡ በየቦታው ፡ እናመጣዋለንና ፡ ልብ ፡ አድርጎ ፡ መመልከት ፡ ነው ፡፡

ለ ) ክህነተ ፡ ኦሪት ፡ ከነሥርዐቱ ፡፡

፲፰ ፤ ክህነት ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ አስረዳነው ፡ ኹሉ ፡ የወልደ ፡ እግዚአ
ሔር ፡ ምሳሌ ፡ አድርጎ ፡ በልዩ ፡ ምስጢር ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሾመው ፤ የልዑል
እግዚአብሔር ፡ ካህን ፡ ተብሎ ፡ ከተጠራው ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ በቀር ፤ ከአዳም ፡ እስከ
ሙሴ ፡ የነበሩ ፡ አበው ፤ ትንቢትን ፡ ክህነትን ፡ መንግሥትን ፡ በበረከተ ፡ አበው ፡ ወ
ሰው ፡ ከመሥራታቸው ፡ በቀር ፡ የተወሰነ ፡ ሥርዐት ፡ አልነበራቸውም ፡፡

፲፱ ፤ ከፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ በ፫ ፡ ሺሕ ፡ ፬፻፹፩ ፡ ዘመን ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ
ደብረ ፡ሲና ፡ ላይ ፡ በአምሳለ ፡ ንጉሥ ፡ ተገልጾ ፤ በታመነ ፡ አገልጋዩ ፡ በሙሴ ፡ አማ
ይነት ፡ ሕግን ፡ ሲወስን ፤ ክህነት ፡ ከቤተ ፡ ሌዊ ፡ የበላይነቱም ፡ ከቤተ ፡ አሮን ፡ እን
ይወጣ ፡ ወስኖዋል ፡፡

፳ ፤ በዚህ ፡ መሠረት ፤ በሙሴ ፡ አማካይነት ፡ እግዚአብሔር ፡ አሮንን ፡ ከሾ
በት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፤ ለኢትዮጵያ ፡ ታላቅ ፡ ካህን ፡ አድርጎ ፡ አዛርያስን ፡ እስከ ፡ ሾመበት
ቀን ፡ ድረስ ፤ አሮን፡አልዓዛር ፡ ፊንሐስ ፡ ኤሊ፡ ሳሙኤል ፡ አብያታር ፡ ሳዶቅ ፡ የሚባሉ
ሰባት ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ በእስራኤል ፡ ተሹመዋል ፡፡

፳፩ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፤ በሰባተኛው ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ ለሰ
አዊ ፡ ተፈጥሮዋቸው ፡ በተሰጠው ፡ ሕግ ፡ ጸንተው ፤ እሱን ፡ ብቻ ፡ ሲያመልኩና ፡ በስመ
ሲያምኑ ፤ እንደ ፡ ተፈጥሮው ፡ ፍጹምነት ፤ በሰባት ፡ የድምጥ ፡ ስልቶች ፡ ፍጹማን ፡ም
ጢራትን ፡ ዐውቆ ፡ ሊናገርበት ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ በተሰጠው ፡ ግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ እሱን፡ ብቻ
ሲያመሰግኑ ፡ ለኖሩ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ክህነተ ፡ ኦሪትን ፡ ከነሥርዐቱ ፡ ሰጣቸው ፡፡

፳፪ ፤ ሥርዐቱም ፤ አንደኛ ፡ ሌዋውያን ፤ ከእስራኤል ፡ መካከል ፡ በእግዚአብሔር
ትእዛዝ ፡ ለክህነት ፡ ሲመረጡ ፤ ደቂቀ ፡ አሮን ፡ ተቀብተው ፤ መሥዋዕት ፡ በመ
ዋት ፡ ውሳጣዊውን ፡ ሥርዐተ ፡ ምስጢር ፡ በማከናወን ፤ ኹለተኛ ፡ ደቂቀ ፡ ቀአት
ንዋየ ፡ ቅድሳቱን ፡ በጠቅላላውም ፡ የአሮን ፡ ልጆች ፡ የሚሠሩበትን ፡ የመሥዋዕት ፡ ዕቃ



ኹሉ ፡ በመሸከም ፤ ሦስተኛ ፡ ደቂቀ ፡ ጌድሶር ፤ ድንኳኒቱንና ፡ መጋረጃዎቿን ፡ በመሸከም፤
ራተኛ ፤ ደቂቀ ፡ ሜራሪ ፡ የድንኳኒቱን ፡ ተራዳዎቿን ፡ አዕማዶቿን ፡ ደገፋዎቿን ፡ ካስ
ማዎቿን ፡ ገመዶቿንም ፡ ኹሉ ፡ በመሸከም ፡ እንዲያገለግሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ አዘዘ ፤
ቀባት ፡ መሠዋት ፡ ድንኳን ፡ መትከል ፡ መንቀል ፡ መጫን ፡ መሸከም ፡ ነበር ፡፡ ልቅና
ውም ፡ ለአሮን ፡ ልጅ ፡ ለአልዓዛር ፡ ነበር ፡፡ ዘኍ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፩—፶፩ ፡፡ ም ፡ ፬ ፡
ቍ ፡ ፩—፵፱ ፡፡

፳፫ ፤ ይህ ፡ ክህነተ ፡ ኦሪት ፤ ክርስቶስ ፡ ለአዲሲቱ ፡ ሕግ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ለሰ
በካት ፡ መልእክተ ፡ ሕይወት ፡ የካህናት ፡ አለቃ ፡ ኾኖ ፡ እስኪመጣላቸው ፡ ድረስ ፤
እንደ ፡ ዳረጎት ፡ ኾኖ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፩ ፡ ሺሕ ፡ ፬፻ ፡ ዓመት ፡ ለኢትዮጵ
ያውያን ፡ ተሰጠ ፡፡

፳፬ ፤ ሐ ) ጽሌ ፡ ኦሪት ፡ ከነመሥዋዕቱ ፡፡

የሰው ፡ ልጅ ፤ ሁል ፡ ጊዜም ፡ ክፋት ፡ በባሕርዩ ፡ የመላበት ፡ በመኾኑ ፡ ስቶ ፡
ተሳስቶ ፡ ከመንገድ ፡ ወጥቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ በደለና ፡ በጣዖታት ፡ ስለ ፡ ተሰና
በለ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ በሚታይ ፡ በሚዳሰስ ፡ ነገር ፡ ወደሱ ፡ ሊያቀርበው ፤ በየቀ
ኑም ፡ ወደ ፡ ረቂቅነት ፡ ወደ ፡ ጥልቅነት ፡ ሊራመድ ፡ ይገባው ፡ የነበረው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡
ዕውቀት ፤ እርምጃውን ፡ እየለቀቀ ፤ ወደ ፡ ግዙፍነትና ፡ ወደ ፡ ድንቍርና ፡ እየተንፏቀቀ፡
ወደ ፡ ኋላው ፡ ስለ ፡ ሄደ ፤ ትእዛዝ ፡ ባለማክበር ፤ ከእንስሳትና ፡ ከአራዊት ፡ ከአዕዋፍም ፡
ከጥቃቅን ፡ ፍጥረቶች ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ስለ፡ ተዋረደ ፤ ግዙፍ ፡ አእምሮው ፡ በሚፈቅድ
ለት ፡ መጠን ፡ ወደ ፡ አምልኮቱ ፡ ሊስበው ፡ ወዶ ፤ መሥዋዕቱን ፡ ጸሎቱን ፡ ስግደቱን ፡
ፍጹም ፡ አገልግሎቱን ፡ ሊያቀርብባት ፡ ትእዛዙ ፡ የተጻፈባትን ፡ የድንጋይ ፡ ገበታ ፡
ሰጠው ፡፡ እሱዋም ፡ ጽዮን ፡ ትባላለች ፡፡

፳፭ ፤ ጽሌ ፡ ማለት ፡ በግእዙ ፡ የነጠላነት ፤ ጽላት ፡ የብዛት ፡ ስም ፡ ነው ፡፡ ነገር ፡
ግን ፡ በልማድ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ ይነገራል ፡፡

፳፮ ፤ እንዲሁም ፡ በጽላትና ፡ በታቦት ፡ መካከል ፤ የኹኔታና ፡ የአነጋገር ፡ ልዩ
ነት ፡ ሲኖር ፤ ልማደኛው ፡ ሰው ፤ ታቦተ ፡ ጽዮን ፡ ጽላተ ፡ ሙሴ ፡ ናት ፡ በማለት ፡ ሲና
ገር ፡ ይሰማል ፡፡

፳፯ ፤ ጽሌ ፡ ኦሪት ፡ ጽዮን ፤ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንድትገባ ፡ የፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ጽላት ፤ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ዘጠና፡ሦስት ፡ ዓመት ፡ በደብተራ ፡ ኦሪት ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ እምነ ፡
ጽዮንን ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሲፈልገውና ፡ ሲናፍቀው ፡ ለነበረ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሕዝቡ ፡ ሰጠ ፡፡

፳፰ ፤ በዚህች ፡ ጽሌ ፡ ፊት ፤ ይቀርብ ፡ የነበረው ፡ መሥዋዕት ፤ እግዚአብሔር ፡
ለሙሴ ፡ እንደ ፡ አዘዘው ፤ ከተቀደሱት ፡ እንስሳት ፡ ወገን ፤ የበሬ ፡ የበግ ፡ የጠቦት ፡ የወ
ይፈን ፡ የጊደር ፡ ስብና ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ በሙሴ ፡ አማካይነት ፡ ኪዳኑን ፡ ያጸ
ናበት ፡ ደማቸው ፡ ነበር ፡፡

፳፱ ፤ ይህም ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ የተፈጸመው ፡ ነገር ፤ ሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ለጸናበት ፡
ለክርስቶስ ፡ ደም ፤ መንገድ ፡ ጠራጊው ፡ ነበር ፡፡

www.ethiopianorthodox.org




የውጣ ፡ የተጻፈባት ፡ ምሳሌዪቱ ፡ ጽዮን ፡ ወደ ፡ ገባችባት ፡ አገር ፡ አማና
ዊት ፡ ጽዮን ፡ ማርያም ፡ አካላዊ ፡ ቃልን ፡ አዝላ ፡ ተሰደደች ፤ ስለዚህ ፡
እምነ ፡ ጽዮን ፡ እያልን ፡ እንጠራታለን ።



፴ ፤ ስለዚህ ፡ አሪት ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ መሪ ፡ ትኾነን ፡ ዘንድ ፤ ሕጉ ፡ የተፃ
ባት ፡ ጽዮንን ፤ ኪዳኑ ፡ የጸናበት ፡ መሥዋዕተ ፡ አሪትን ፡ ለእኛ ፡ ለኢትዮጵያውያ
ሲሰጥ ፤ እምኵሉ ፡ ተዓይኒሁ ፡ ለያዕቆብ ። ነኪር ፡ ነገሩ ፡ በእንቲአኪ ፡ ሀገረ ፡ እግዘ
ብሔር ። ከያዕቆብ ፡ ከተሞች ፡ ከሴሎ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ይልቅ ፡ ሀገረ ፤ እግዚአብሔ
ኢትዮጵያ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ አንቺ ፡ የሠራው ፡ ነገሩ ፡ ልዩ ፡ ነው ፤ ድንቅ
ነው ፡ ሲል ፡ ነቢይ ፡ ዳዊት ፡ የገለጸው ፡ የልቡና ፡ አድናቆትና ፡ ውዝዋዜ ፤ በጐ
ታወቀ ፡ ተረዳ ።

፴፩ ፤ ይልቁንም ፡ እግዚአብሔር ፤ ታምራቱን ፡ የገለጸባቸውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡
ሮች ፤ ከአስታወሰ ፡ በኋላ ፤ በዚያው ፡ ከተወለዱት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፤ ሰው ፡ ኹ
እምነ ፡ ጽዮን ፡ ይላል ፡ ሲል ፤ የተናገረው ፡ ቃለ ፡ ትንቢት ፡ ጊዜውን ፡ ሲጠብቅ ፡ ኖ
ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ እንደመኾናቸው ፤ ቤ
እግዚአብሔር ፡ ሊሠሩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተፈቀደላቸው ፡ ተስፋ ፡ በ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ.
መስከረም ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ የአኵስም ፡ ጽዮንን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲመሠርቱ ፡ በተ
ሩት ፡ ቃል ፡ የተደበቀው ፡ ተገልጧል ፤ የረቀቀው ፡ ጐልቶ ፡ ተተርጉሞዋል ።

፴፪ ፤ ንግግሩንም ፡ ለተመልካቾቹ ፡ ጉልህ ፡ መነጥር ፡ ይኾንላቸው ፡ ዘንድ ፡
ለን ፡ ጥፈነዋል ።

ሞአ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ።

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵ

፴፫ ፤ በአኰቴተ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ አነ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይ
ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፤ እምአመ ፡ አንገሠኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዕሥ
ወሠለስቱ ፡ ዓመት ፤ ሐወፅክዋ ፡ ለእምነ ፡ ጽዮን ፡ ገበዘ ፡ አኵስም ፤ ወርኢኩ ፡ ስ
ሕንጼሃ ፡ ዘቀዳሚ ፡ አክበርክዋ ፡ ወአልዐልክዋ ።

፴፬ ፤ ወናሁ ፡ ጸውዐተኒ ፡ መፍቅድ ፡ ከመ ፡ እሕንጽ ፡ ቤታ ፡ ለእምነ ፡ ጽዮን ፡
ዳስ ፡ ንድቅ ፤ እስመ ፡ ፈተውኩ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዘይሄኒ ፡ ደኃሪታ ፡ እምቀዳሚታ ፡
ጸጋሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አስተናደፍኩ ፡ ካልአ ፡ መሠረተ ፡ ሕንጻ ፤ ወአንበር
እብነ፡ማዕዘንት ፡ አመ ፡ ዕሥራ ፡ ወሰኑዩ ፡ ለወርኀ ፡ መስከረም ፡ በዕለተ ፡ ኀሙስ ፤
ሠርቱ ፡ ወተስዐቱ ፡ ምእት ፡ አርብዓ ፡ ወኀምስቱ ፡ ዓመት ፡ እምልደተ ፡ እግዚእነ ፡
ሱስ ፡ ክርስቶስ ። በዘመነ ፡ ማቴዎስ ፡ ወንጌላዊ ።

፴፭ ፤ ወወሀብኩ ፡ ለመፍቅደ ፡ ሕንጻሁ ፡ ዐሠርተ ፡ ወሠለስተ ፡ ምእተ ፡ እል
መክሊተ ፡ ብሩር ፡ ዘኢትዮጵያ ፤ ዘውእቱ ፡ አሐዱ ፡ ሚልዮን ፡ ወሠለስቱ ፡ ምእ
ሺሕ ፡ መክሊተ ፡ ብሩር ።

፴፮ ፤ ወካዕበ ፡ ወሀብኩ ፡ ለእምነ፡ጽዮን ፡ ሠላሳ ፡ (፴) ጋሻ ፡ ምድረ፡እምርስ
ዚአየ ፡ በጥቃሃ ፡ ለባሕረ ፡ ዝዋይ ፤ ዘሀለዉ ፡ ውስቴታ ፡ ኀምስቱ ፡ ደስያት፡እስመ ፡
ሐፈ ፡ ታሪክ ፡ ይነግር ፡ ወያየድዕ ፡ ከመ ፡ በመዋዕሊሃ ፡ ለጉዲት ፡ ተንሥአት ፡ እም
ጽዮን ፡ እምአኵስም ፡ ወነገደት ፡ ብሔረ ፡ ሸዋ ፡ ወነበረት ፡ በአሐቲ ፡ ደሴት ፡ እም

www.ethiopianorthodox.org

ያቲሃ ፡ ለባሕረ ፡ ዝዋይ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ፡ እስከነ ፡ ገብአት ፡ ወተመይጠት ፡ ኅበ ፡ አ
ስም ፡ ወለይእቲኒ ፡ ደሴት ፡ ይሰምይዋ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ ሰብአ ፡ ብሔር ፡ በነገሮሙ
ደብረ ፡ ጮን ፤ ዘውእቱ ፡ ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ብሂል ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ሠመርኩ ፡ አነሂ
ከመ፡ይኩን ፡ ለዝክር ፡ እስከ ፡ ደኀሪ ፡ መዋዕል።በእንተ ፡ ንግደታ ፡ ወግብአታ ፤ ወዓዲ
በእንተ ፡ ተአንግዶታ ፡ በደሴተ ፡ ዝዋይ ።

ወሊተኒ ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ይኩነኒ
ለተዝካረ ፡ ስምየ ፡ ወለመድኀኒተ ፡ ነፍስየ ። አሜን ።

## መሠረታዊ ፡ ቃል ።

፴፯ ፤ ለአኰስም ፡ ጽዮን ፡ ይህን ፡ የአዲሱን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕንጻ ፡ ስንመ
ሠርትላት ፡ ከዚህ ፡ ሰዓት ፡ ላደረሰን ፡ አምላካችን ፡ ውለታውን ፡ ለመመለስ ፡ የሚበቃ
ዐቅም ፡ የለንም ። በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ ሀገራችን ፡ ነጻነት ፡ እየተዋጋን ፡ በች
ግሬ ፡ ላይ ፡ በነበርንበት ፡ ጊዜያት ፡ ከሰላማዊ ፡ ሰዓት ፤ ይህን ፡ ሥራ ፡ እንድንሠራው
ያበቃን ፡ ዘንድ ፡ ፈጣሪያችንን ፡ በሃይማኖት ፡ ለምነነው ፡ ነበር። ሀገራችን ፡ በጠላት
ከተወረረች ፡ በኋላ ፤ በስደት ፡ አገር ፡ በነበርንበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፤ ስለዚሁ ፡ ነገር
ሃይማኖትና ፡ ተስፋ ፡ ከሕሊናችን ፡ አልተለዩንም ።

፴፰ ፤ አምላካችን ፡ በይቅርታው ፡ በጐበኘን ፡ ጊዜ ፤ አገራችንን ፡ ከጠላት ፡ ቀን
በር ፡ አውጥቶ ፡ እኛን ፡ ከዚህ ፡ ሰዓት ፡ አድርሶ ፡ የሐልዮውን ፡ በገቢር ፡ እንዲፈጸም
አደረገልን ።

፴፱ ፤ አኰስም ፡ በሐውልቶቹዋ ፡ ስመ ፡ ጥሩነት ፤ በቤተ ፡ ክርስቲያንዋ ፡ ጥንታ
ዊነት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የታሪክ ፡ ፋና ፡ ናት ። ሲያያዝ ፡ በመጣው ፡ ታሪክ ፡ እንደሚገኘው
በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ የመጣችው ፡ ቅድስት ፡ ጽዮን ፡ በጥንቱ ፡ ዘመን ፤ አንሰባ
ደግሞም ፡ መዝበር ፡ እየተባለ ፡ የሚጠራው ፡ በዚሁ ፡ አቅራቢያ ፡ በሚገኘው ፡ ቦታ
በምኵራብ ፡ አሪት ፡ ነበረች ።

፵ ፤ የክርስትናን ፡ ሥርዐት ፡ የጀመሩት ፡ አብርሃና ፡ አጽብሐ ፡ በነገሡበት
ዘመን ፡ ግን ፡ ውሃ ፡ ሰፍሮበት ፡ የነበረው ፡ ይኸ ፡ ስፍራ ፡ ባሕሩ ፡ በተአምራት ፡ ደርቆ
ላቸው ፡ መጀመሪያዪቱን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሳነጹላት ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዐሥራ
ሁለቱ ፡ የመቅደስ ፡ ክፍሎች ፡ እንደ ፡ ነበሩባት ፡ ይነገራል ።

፵፩ ፤ የጥንቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡በጉዲት ፡ ከተቃጠለ ፡ በኋላ፤አንበሳ ፡ ውድም
ባለሰባት ፡ ክፍል ፡ አድርጎ ፡ አሳንጾት ፡ ነበር ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ባ፲፰፻፳፯ ፡ ዓ ፡ ም
በግራኝ ፡ ሰራዊት ፡ ስለ ፡ ተመዘበረች ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ቈይቶ ፡ የተነ
ሣው ፡ አጼ፡ ፋሲል ፡ ይህን ፡ አሁን ፡ ያለውን ፡ ሕንጻ ፡ አሠርቶላት ፤ በየዘመኑም ፡ የነ
በሩ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ እያደሱላት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ቈይታለች ።

፵፪ ፤ እኛም ፡ በዚህች ፡ ቀን ፡ የዛሬ ፡ ፳፯ ፡ ዓመት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ተነጥላ ፡ የነ
በረች ፡ ኤርትራ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንድትመለስ ፡ ባደረግንበት ፡ በመጀመሪያው
ዓመት ፡ ለእምነ ፡ ጽዮን ፤ የዚህን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የመሠረቱን ፡ ደንጊያ ፡ ስናኖር



ስለታችን ፡ ከመፈጸሙ ፡ በላይ ፤ የደረሰው ፡ ድርብ ፡ ዕጽፍ ፡ ደስታ ፡ የሚኾን ፡ የኤር
ትራ ፡ መመለስ ፡ አጋጣሚነት ፡ በፈጣሪያችን ፡ ፈቃድ ፡ የተፈጸመ ፡ ነው ።

፵፫ ፤ በአብርሃ ፡ ወአጽብሓ ፡ ጊዜ ፡ የነበሩትም ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ ክፍሎች፡አሁ
ንም ፡ እንዲኖሩ ፡ ምኞታችን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ መካከሉ ፡ የእምነ ፡ ጽዮን ፡ መቅደስ ፡ ኾኖ ፡
በግራና ፡ በቀኝ ፡ ፯ ፡ ፯ ፡ መቅደሶች ፡ እንዲገኙበት ፡ አድርገናል ።

፵፬ ፤ የጥንቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለሴቶች ፡ የተከለከለ ፡ ነበር ። ይህ ፡ እኛ ፡
የምናሠራው ፡ መቅደስ ፡ ግን ፡ ሳይከለከሉ ፡ እንደ ፡ ወንዶቹ ፡ ምእመናን ፡ ጸሎታቸውን ፡
ለማድረስ ፡ የተፈቀደላቸው ፡ እንዲኾኑ ፡ አድርገናል ።

፵፭ ፤ የጥንቱም ፡ ሕንጻ ፡ በየዘመናቸው ፡ ላሠሩት ፡ ለጥንታውያን ፡ ነገሥታት ፡
መታሰቢያነቱን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ እንዲኖር ፡ ትተነዋል ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ አንደኛው ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ግዛታችን ፡ ትግሬ ፡ ለመ
ጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ደረስን ፡ የሥራ ፡ መጀመሪያ ፡ ያደረግነው ፡ ይህ ፡ የጽዮን ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ሕንጻ ፡ መሠረት ፡ መጣል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ አንድ ፡ የተከበረና ፡ የተቀደሰ ፡
ታላቅ ፡ ነገር ፡ ለመፈጸም ፡ ፈጣሪያችን ፡ አበቃን ። ስለዚህም ፡ ለዘወትር ፡ እናመሰግነ
ዋለን ።

፵፮ ፤ ይህችም ፤ የሕዝብና ፡ የአሕዛብ ፡ ተስፋ ፡ የተመሠረተባት ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ ሕጉ ፡ የተጻፈባት ፡ አምልኮቱ ፡ የታወቀባት ፡ ኪዳኑ ፡ የጸናባት ፡ ጽሌ ፤ የሥግው ፡
ቃል ፡ እናት ፡ የእመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ምሳሌ ፡ ስለ ፡ ኾነች ፤ መታሰቢያነቷ ፡ ሳይለ
ወጥ ፡ ጽዮን ፡ በጽዮንነቷ ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ።

፵፯ ፤ ኢትዮጵያውያንም ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ሊጠሩባት ፡ በተፈቀደላቸው ፡
በጽዮን ፡ እየተማፀኑ ፡ ልጇዋን ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ እያሉ ፡ እንደሚጠሩ ፤ እናቱን ፡
እናታቸውን ፡ እምነ ፡ ጽዮን ፡ ማርያም ፡ እያሉ ፡ ይጠሩዋታል ። በምስጋናም ፡ ጊዜ ፡ ለዘ
ለዓለም ፡ ማረፊያዬ ፡ ይህች ፡ ናት ፡ መርጫታለሁና ፡ አድርባታለሁ ፡ ብሎ ፤ ስለ ፡ መረ
ጣትም ፤ የአሸናፊ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እናት ፡ ሆይ ፡ ከሴቶች ፡ ተለይተሽ ፡ አንቺ ፡
የተባረክሽ ፡ ነሽ ። የማሕፀንሽ ፡ ፍሬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ምስጉን ፡ አምላክ ፡ ነው ፡
እያሉ ፡ ከማመስገን ፡ ለዘለዓለም ፡ አያቋርጡም ።

፵፰ ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፤ የዐዜብ ፡ ንግሥት ፡ ማርያም ፤ ሰይጣን ፡ በሚያመ
ጣው ፡ ምክንያት ፡ ኹሉ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፤ እንደ ፡ ወጥመድ ፡ በድንገት ፡ እንዳ
ትደርስባቸው ፡ ለኢትዮጵያውያን ፤ በአማላጅነት ፡ ከልጇዋ ፡ ፊት ፡ መሐር ፡ ሊተ ፡ ወል
ድየ ፤ ተዘከር ፡ ኪዳንየ ፡ በማለት ፡ ስለምትቆምላቸው ፤ ኢትዮጵያና ፡ ልጆቿ ፡ በነጻነታ
ቸው ፡ በክብራቸው ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ።

፵፱ ፤ እንግዲህ ፡ በራስኽ ፡ የማልክላቸው ፡ ወዳጆችኽን ፡ ዐስብ ፡ በማለት ፡
ፊንታ ፤ ከወዳጅነት ፡ በበለጠ ፡ ደረጃ ፡ ቆማችሁ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ በጸሎት ፡ በተ
ገናኛችሁ ፡ ጊዜ ፤ በተሰቀለው ፡ በተቸነከረው ፡ ልጅኽ፡በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ስም ፤ አቤቱ ፡ ማረን ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ እያላችሁ ፤ ከልጁ ፡ ጋራ ፡ በተገናኛችሁ ፡ ጊዜ
በመረጥኻት ፡ በወደድኻት ፡ በወለደችኽ ፡ በድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፤ አቤቱ ፡ እዘ
ልን ፡ ራራልን ፡ እያላችሁ ፡ የልጁን ፡ ስም ፡ ለአባቱ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፤ የእናቱን ፡ ስም
ለልጁ ፡ መማለጃ ፡ አድርጋችሁ ፤ ጸሎታችሁን ፡ የምታቀርቡ ፤ በመሣሪያነቱም ፡ አ
ኣዊና ፡ ውስጣዊ ፡ ሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ ጠላትን ፡ አጥቅታችሁ ፤ ክብራችሁን ፡ ነጻ
ታችሁን ፡ ጠብቃችሁ ፡ የኖራችሁ ፡ የምትኖሩ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጀግኖች ፡ ብፁዓን
ናችሁ ።

፶ ፤ መ) ተስፋ ፡ ዳዊት ፡ ከነትንቢቱ ።

ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ የሚገባውን ፡ ትቶ ፡ ተሳስቶ ፡ ወደ
ሞት ፡ ጕድጓድ ፡ ከወደቀ ፡ ወዲህ ፡ ኀጢአት ፡ የጣለችባቸውን ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ለማ
ለል ፤ ለሞት ፡ ከመገዛት ፡ ነጻ ፡ ለመውጣት ፡ እሱን ፡ ለአመኑ ፤ በአምልኮቱ ፡ ለጸኑ
ሰዎች ፡ ፍጻሜው ፡ ሙሉ ፡ ሕይወት ፡ የኾነ ፡ ተስፋን ፡ ሰጥቷል ።

፶፩ ፤ ይኸውም ፡ ኹለተኛ ፡ ምድርን ፡ በፍል ፡ ውሃ ፡ አላጠፋትም ፡ ብሎ ፡ ለኖኅ
ይህችን ፡ ምድር ፤ ለአንተ ፡ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ለልጆችኽ ፡ እሰጣታለሁ ፡ ብሎ ፡ ለአ
ርሃም ፤ እንደ ፡ ሰጠው ፡ ያለ ፡ በቃል ፡ ኪዳን ፡ የተመሠረተ ፡ ጽኑ ፡ ተስፋ ፡ ነው ።

፶፪ ፤ እንዲሁ ፡ ለመረጠው ፤ እንደ ፡ ልቤ ፡ የታመነ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መሰከረለት
ለነቢይ ፡ ዳዊት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡ አድርጎለታል ።

፶፫ ፤ ይኸውም ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ እሱ ፡ የነበሩ ፡ አበው ፤ ከሩቅ ፡ አይተው ፡ የ
መኟት ፡ በመዓዛ ፡ ትንቢት ፡ የናፈቋት ፡ የሥጋዊና ፡ የመንፈሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ሥር
ኾኖ ፡ መገኘቱ ፡ ነው ።

ለዳዊት ፡ የተሰጠው ፡ ተስፋ ፤ ይህ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘረው ፡ ነው ።

፶፬ ፤ «ባሪያዬ ፡ ዳዊትን ፡ እንደ ፡ ልቤ ፡ የታመነ ፡ ኾኖ ፡ ስላገኘኹት ፤ ከወገኖቹ
መካከል ፡ መርጬ ፡ አነገሥኩት ። ለንጉሥነቱ ፡ የተለየ ፤ የከበረ ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥ
ትን ፡ ቀባኹት ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፳፪—፳፬ ።

፶፭ ፤ እጄ ፡ ትረዳዋለች ፡ ክንዴ ፡ ታበረታዋለች ፡ ማለት ፤ ሥልጣኔ ፡ ትደግፈ
ዋለች ፤ ረድኤቴ ፡ ድልን ፡ ትሰጠዋለች ፤ አሸናፊ ፡ ታደርገዋለችና ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ የሚነሣ
ጠላት ፡ አይረባም ፤ አይጠቀምም ፤ በሱ ፡ ላይም ፡ በቂ ፡ ሥልጣን ፡ አያገኝም ፤ የአመጽ
ልጅም ፡ ሊቃወመው ፡ አይችልም ።

፶፮ ፤ የዕለት ፡ ጠላቶቹን ፡ ከፊቱ ፡ አጠፋቸዋለሁ ፤ ጥንተ ፡ ጠላቶቹንም ፡ አዋር
ዳቸዋለሁ ፡ አንሳቀላቸዋለሁ ። ይቅርታዬ ፡ ቸርነቴ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ነው ።

፶፯ ፤ በስሜ ፡ ሥልጣኑ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ። እጁን ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ክንዱንም
በፈሳሾች ፡ ላይ ፡ እዘረጋለሁ ፤ ማለት ፡ ሕዝብን ፡ አሕዛብን ፡ እንዲገዛ ፡ አደርጋለሁ ።



፶፰ ፤ እሱ ፤ አባቴ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ረዳቴ ፡ መድኀኒቴ ፡ ይለኛል ። እኔም ፡ የበኵር ፡ ል
አደርገዋለሁ ። ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ በላይ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ነ
ሊምሉለት ፡ የታመነ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ቸርነቴን ፡ ለዘለዓለም ፡ አጸናለታለሁ ። ዘሩ ፡ በ
ግሥት ፡ ሳይናወጥ ፤ ዙፋኑ ፡ ሳይለወጥ ፤ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ እንዲኖር ፡ አደርጋለ

፶፱ ፤ ልጆቹ ፤ ሕጌን ፡ ቢተዉ ፡ በፍርዴ ፡ ጸንተው ፡ ባይኖሩ ፡ ሥርዐቴን ፡ ቢ
ርሱ ፡ ማለት ፤ አምልኮቴን ፡ ቢያጐሉ ፡ ፍርድ ፡ ቢያደሉ ፡ መማለጃ ፡ ቢበሉ ፡ ኀጢ
ቸውን ፡ በበትር ፡ በደላቸውን ፡ በጨንገር ፡ እጐበኛታለሁ ። ማለት ፤ እንደ ፡ አባትነ
ባያፍሩኝ ፤ እንደ ፡ ጌትነቴ ፡ ባይፈሩኝ ፤ በኀላፊ ፡ ጦር ፡ አስደነግጣቸዋለሁ ። በረኃ
በቸነፈር ፡ እቀጣቸዋለሁ ፡ እንጂ ፤ ጨርሰው ፡ እንዲጠፉ ፡ ቸርነቴን ፡ ከእነሱ ፡ አ
ቅም ። እውነተኛነቴን ፡ በሐሰት ፡ አልለውጥም ። መሐላዬን ፡ (ኪዳኔን) ፡ አላፈርስ
፷ ፤ ልጁ ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፤ ክብሮ ፡ ገኖ ፡ ዙፋኑ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ሞቆ ፤ አባትነ
እንደ ፡ ጨረቃ ፡ ደምቆ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዲኖር ፤ ለዳዊት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በቅዱስነ
ምየለታለኹና ፡ ከአንደበቴ ፡ የወጣውን ፡ አላጥፍም ። መዝ ፡ ፹፱ ፡ ቍ ፡ ፲፱—፴፯ ።

፷፩ ፤ «ከአብራክኽ ፡ የተገኘውን ፤ በዙፋንኽ ፡ አነግሥልሀለኹ ፡ ብሎ ፡ እግዚ
ሔር ፡ ለዳዊት ፡ በውነት ፡ ማለ» ፡ መዝ ፡ ፻፴፪ ፡ ቍ ፡ ፲፩ ። ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘረ
ታላቅ ፡ ተስፋ ፤ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዳዊት ፡ ሲሰጥ ፤ አንደኛ ፡ መታመን ፤ ኹ
ተኛ ፡ ማመን ፡ ( ሃይማኖት ) ፡ ሦስተኛ ፡ መንግሥት ፡ አራተኛ ፡ ረድኤት ፡ ዐምስተ
ቅጣት ፡ ስድስተኛ ፡ ምሕረት ፡ ፯ኛ ፡ ዐልጋ ፡ ወራሽነት ፡ እነዚህ ፡ ሰብዐቱ ፡ ነገሮ
አሉበት ።

፷፪ ፤ ትንቢቱም ፤ « ኢይወፅእ ፡ ምስፍና ፡ እምይሁዳ ፤ ወምልክና ፡ እምአባ
ከይሁዳ ፤ የመንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ አይጠፋም ። ግዛትም ፡ ከወገኖቹ ፡ አይወጣ
በትር ፡ ከዕሴይ ፡ ሥር ፡ ትወጣለች ። በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ የሚቀመጥ ፡ ሰው ፤ ለዘለዓለ
አይታጣም» ፡ ያለው ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፵፱ ፡ ቍ ፡ ፲ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፩ ። ይህን
የመሰለ ፤ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ በብዙ ፡ ገጽ ፡ ይገኛል ።

፷፫ ፤ ሠ ) ዘርዐ ፡ ዳዊት ፡ ከነበረከቱ ።

የሰው ፡ ዘር ፤ በመጀመሪያ ፡ ቅድስናው ፡ በሙሉ ፡ ፍጹም ፡ ኾኖ ፡ አል
ኝም ።

፷፬ ፤ እባብና ፡ ሔዋን ፤ ተስማምተውና ፡ ተያይተው ፡ ባመጡት ፡ ጣጣ ፤
ሬው ፡ ላይ ፡ የኀጢአት ፡ ዋግ ፡ የመታው ፤ የመቅሠፍት ፡ የሞት ፡ ትል ፡ የበላው ፡ ጠ
የዘራው ፡ እንክርዳድም ፡ ተገኘበት ። በዚህ ፡ ምክንያት ፤ ዘሩ ፡ ኹሉ ፡ ቅድስናን ፡
ገኘ ፡ አልቻለም ።

፷፭ ፤ ስለዚህ ፡ ከኀጢአት ፡ ንጹሕ ፡ ኾነው ፡ የተገኙትን ፡ ኖኅን ፡ አብርሃም
ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ባረካቸው ። ዘራቸውንም ፡ ለበረከት ፡ አደረገ ። ክቡር ፡ ዘ
ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለሚጠይቅ ፡ ሕሊና ፤ ክቡር ፡ ዘር ፡ የሚባለው ፡ እግዚአብሔርን ፡
ፈሩ ፤ የምእመናን ፡ ዘር ፡ መኾኑን ፡ ማወቅ ፡ ይበቃዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

፺፮ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በኋላ ፤ ዓለምን ፡ ኹለተኛ ፡ ሲ
ድስ ፡ የፍጥረትንም ፡ ዘር ፡ ሲያራባ ፤ ለኖኅ ፡ ለአብርሃም ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ምክንያት
በማድረግ ፡ ቀዋሚ ፡ ዘር ፡ ሰጣቸው ።

በኖኅ ፡ ዘር ፡ ውስጥ ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ጠቀስነው ፤ መልካምና ፡ መጥፎ ፡ ግርድና
ምርትነት ፡ ያለበት ፡ ዐይነት ፡ ይገኛል ። ይኸውም ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔርና ፡ በስመ
ጣዖት ፡ የተለያየው ፡ ነው ።

፺፯ ፤ በቀዳማይ ፡ ምኒልክ ፡ ላይ ፡ ለተወሐደው ፤ ለኢትዮጵያዊና ፡ እስራኤላዊ
ዘርም ፤ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ልዩነት ፡ ነበረበት ።

፺፰ ፤ በአብርሃምና ፡ በመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ዘመን ፤ ከተደረገው ፡ መቀራረብ፡ወዲህ
ግን ፤ ምንም ፡ እንኳን ፡ አብርሃም ፡ ለልጆቹ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፤ የማይካድ፡ርስት
አድርጎ ፡ በማውረሱና ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የልብ ፡ ድካም ፡ የሚበዛባቸውን ፡ የአ
ብርሃምን ፡ ልጆች ፡ በሽታ ፡ ለማቃለል ፤ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ በመስጠት ፡ በኩል ፡ በእስ
ኤል ፡ መካከል ፡ በመገለጹ ፤ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ታሪክ ፡ ለሚተርኩ ፡ ሰዎች ፡ ቤተ ፡ እ
ራኤል ፡ አስቀድማ ፡ የሠለጠነች ፡ ቢመስላቸውም ፡ ቅሉ ፤ ከጣዖት ፡ ቤት ፡ ገብታ ፡ የ
ጣችው ፡ ቤተ ፡ እስራኤልና ፡ ወደ ፡ ጣዖት ፡ ቤት ፡ ያልገባችው ፡ ኢትዮጵያ ፤ በየበኩ
ቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተመረጡ ፡ ዕቃዎች ፡ ነበሩ ።

፺፱ ፤ ይህንንም ፤ የመንፈስ ፡ ተዋሕዶዋቸውን ፤ ከሥጋ ፡ ተዋሕዶዋቸው፡በፊት
ለኹለቱም ፡ ወገን ፡ ሕዝቦቹ ፡ የነበረውን ፡ ፍቅር ፡ ለመግለጥ ፤ ኹለት ፡ የድንጋይ ፡ ገ
ቶች ፡ ጽላትን ፤ በእጁ ፡ ቀርጦ ፤ ቃሉን ፡ በጣቱ ፡ ጥፎ ፤ የሰጠ ፡ እግዚአብሔር ፤ በሰለ
ሞን ፡ ዘመን ፡ እስኪገልጠው ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ አያውቀውም ፡ ነበር ።

፻ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ የተመረጡ ፡ ዘሮች ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ፡አምሳል
እንዲኾኑ ፡ የፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፤ በዘርኽ ፡ የምድር ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ፡ይባረካሉ ፡ ሲል
የተናገረለትን ፡ ዘርዐ ፡ አብርሃምንና ፡ ዘርዐ ፡ ኢትዮጵያን ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፤ አዋሕዶ
ላሳየው ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ፡ እብነ ፡ መለክ ፡ ቀድሞ ፡ ኹሉን ፡ የሚገዛ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ የተከለው ፡ የዘለዓለም ፡ ሐውልት ፡ ኾነ ።

፻፩ ፤ ክቡር ፡ ዘርዐ ፡ አብርሃም ፤ በትውልድ ፡ ሐረግ ፤ በይስሐቅ ፡ በያዕቆብ ፡ በ
ሁዳ ፡ ዘምዮ ፤ ከዳዊት ፡ ከሰሎሞን ፡ ሲደርስ ፤ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣትነቱን ፡ ገለጠ ።

፻፪ ፤ በቡቃያነቱ፤ በከነዓናውያን፡መካከል፡ ዝቀተኛ፡ ኾኖ፡ የታየውን፡ ያኽል፡አሕ
ዛብ ፡ ኹሉ ፤ ከቅርንጫፎቹ ፡ በታች ፡ ማረፊያ ፡ መጠለፊያ ፡ እስኪያገኙ ፡ ድረስ ፤ ከፍ ፡ ያለና
ገናና ፡ ኾነ ።

፻፫ ፤ በረከቱም ፤ ኖኅ ፡ ለሴም ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ለአብርሃም ፡ አብርሃም ፡ ለይስ
ሐቅ ፡ ይስሐቅ ፡ ለያዕቆብ ፡ በቃል ፡ ከሰጡት ፡ ሌላ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከኖኅ ፡ ከአ
ብርሃም ፡ ከያዕቆብ ፡ ጋራ ፡ በቃል ፡ ኪዳን ፡ ያጸናው ፤ በሥራ ፡ የገለጠው ፡ ሀብተ ፡ ትን
ቢት ፡ ሀብተ ፡ ክህነት ፡ ሀብተ ፡ መንግሥት ፡ ነው ።



፻፬ ፤ ስለዚህ ፤ ኪዳነ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅንና ፡ ኪዳነ ፡ አብርሃምን ፤ ለማዋሐድ ፡
ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የሀብታት ፡ የምስጢራት ፡ ቦይ ፡ ባደረገው ፡ በነቢዩ ፡ ዳዊት ፡
አድሮ ፤ ወይከውን ፡ ቡሩክ ፡ ስሙ ፡ ለዓለም ። እምቅድመ ፡ ፀሐይ ፡ ሀሎ ፡ ስሙ ። ወይት
ባረኩ ፡ ቦቱ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛበ ፡ ምድር ።. . . ስሙ ፡ ለዘለዓለም ፡ የተባረከ ፡ ይኾናል ፡
እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ሞቆ ፡ እንደ ፡ ጨረቃ ፡ ደምቆ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ። የምድር ፡ አሕ
ዛብ ፡ ኹሉ ፡ ይመራረቁበታል ፡ ሲል ፤ በሰሎሞን ፡ የተናገረውን ፡ በምኒልክ ፡ ፈጸመ ፡

፻፭ ፤ የዳዊት ፡ ተስፋውና ፡ ትንቢቱ ፡ ዘሩና ፡ በረከቱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ተሰጥቶአል
ባልን ፡ ጊዜ ፡ አይሁድ ፤ አንተ ፡ ካህኑ ፡ ያለውን ፡ ለአብርሃም ፤ ነገረ ፡ መሢሕን ፤ መቅ
ደስ ፡ ትትሐነፅ ፡ እስከነ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ ያለውን ፤ ለአግሪጳስ ፡ ወይም ፡ ገና
ለሚመኙት ፡ እንደ ፡ ሰጡትና ፡ እንደሚያስቡት ፡ ለክርስቶስ ፡ የተባለውን ፡ በመቀማት
አይደለም ።

የሚመስለውም ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፤ በእነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ ምክ
ንያት ፡ እንደ ፡ አለባቸው ፡ ይወቅ ። መዝ ፡ ፸፪ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ።

፻፮ ፤ ስለዚህ ፡ ክርስቶስ ፤ ከዳዊት ፡ ዘር ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፤ እኔ ፡ አባት ፡ እኾንባ
ለሁ ፤ እሱም ፡ ልጅ ፡ ይኾነኛል ። ከአብራክኽ ፡ የተገኘውን ፡ በዙፋንኽ ፡ አነግሥልሀለሁ ፡
ሕፃን ፡ ተወልዶልናልና ፡ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ተሰጠን ፤ አለቅነቱም ፡ በጫንቃው ፡ ላይ
ይሆናል ፡ ስሙም ፡ ድንቅ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። መካርም ፡ ብርቱም ፡ አምላክ ፡ የዘለ
ለም ፡ አባት ፤ የሰላም ፡ አለቃ ፤ እኔ ፡ ለአለቆች ፡ ሰላምን ፡ አመጣለሁና ፤ ጌትነት ፡ ሕይ
ወት ፡ የግሉ ፡ ነው ። ለሰላሙ ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ። በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ መንግሥቱ
ትጸናለች ። በሃይማኖት ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ የመጡትን ፤ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም
በእውነትና ፡ በቅንነት ፡ ይቀበላል ፡ ተብሎ ፡ ቢነገርለትም ፡ ቅሉ ፤ ብርቱ ፡ አምላክ
ጌትነት ፡ ሕይወት ፡ የግል ፡ ገንዘቦቹ ፡ ናቸው ። እኔ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ያየኹት ፡ ኢየሱስ ፡ የአም
ላክ ፡ ልጅ ፡ ነው ። ጌታ ፤ ጌታዬን ፡ በቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ። እግዚአብሔር ፡ አምላክ
የአባቱ ፡ የዳዊትን ፡ ዙፋን ፡ ይሰጠዋል ። ለያዕቆብ ፡ ወገን ፡ ለዘለዓለም ፡ ነግሦ ፡ ይና
ራል ። ለመንግሥቱም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ። እሱ ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ይ
ላል ፡ የሚል ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ አለው ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ም፡፯ ፡ ቍ፡ ፲፪—፲፬ ። ኢሳ ፡ ም፡ ፱
ቍ ፡ ፮ና ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፻፴፪ ፡ ቍ ፡ ፲፩ ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፴፩—፴፬ ።

፻፯ ፤ መንግሥቱም ፡ ትምህርቱም ፤ ሰማያውያን ፡ እንጂ ፤ ምድራውያን ፤ መን
ሳውያን ፡ እንጂ ፤ ሥጋውያን ፡ ላለመኾናቸው ፤ ምድራዊው ፡ መምህር ፡ ምድራዊ ፡ ነገር
ይናገራል ። ከሰማይ ፡ የመጣ ፡ እሱ ፡ የሰማዩን ፡ ይናገራል ። ባየውም ፡ በሰማውም ፡ ይመ
ሰክራል ። ምስክርነቱንም ፡ የሚቀበላት ፡ የለም ። ምስክርነቱንም ፡ የተቀበለ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ እውነተኛ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ዐተመ ። መንግሥቴስ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በኾነች ፡ ኖሮ
አሽከሮቼ ፡ በተዋጉልኝ ፡ ነበር ፡ የሚል ፡ ልዩ ፡ መታወቂያ ፡ ተሰጥቷቸዋል ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፫
ቍ ፡ ፴፩—፴፬ ። ም ፡ ፲፰ ፡ ቍ ፡ ፴፮ና ፡ ፴፯ ። እንግዴህ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚኾነውን ፡
በጊዜው ፡ እናመጣዋለንና ፡ በቦታው ፡ መመልከት ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፸፫ ፤ ከኹለቱ ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱን ፡ መንፈሳዊውን ፡ በአጭር ፡ አስረድ
ናል ። እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ ሥጋዊውን ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ እንገልጣለን ።

፸፬ ፤ የዳዊት ፡ ተስፋውና ፡ ትንቢቱ ፡ ዘሩና ፡ በረከቱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሲሰጥ
ኢትዮጵያዊና ፡ እስራኤላዊ ፡ ዘር ፡ ለተወሐዱበት ፡ ለምኒልክ ፡ በሥጋ ፤ የዳዊትን ፡ ተ
ፋውን ፡ ትንቢቱን ፡ በረከቱን ፡ በዘርነት ፡ ለመውረስና ፡ ስሙንም ፡ በልጅነት ፡ ለማ
ናቱ ፤ የመንግሥቱም ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ዕድሜ ፡ ማለት ፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ እስ
ያልፉ ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ለመኾኑ ፤ ዘርኽን ፡ ለዓለም ፡ በመንግሥት፡ አዘጋጃለሁ
ዙፋንኽንም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ አጸናለሁ ፡ ብዬ ፡ ለዳዊት ፡ ምያለኹና ፡ ዘሩ ፡ ለዘለዓለም
በመንግሥት ፡ ይኖራል ። ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ በላይ ፡ ነው ፡ ማለት ፤ ንጉሠ ፡ ነገሥት
ነው ። ጽድቅኽንም ፡ ለንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ስጠው ። ኢትዮጵያውያን ፡ ይገዙለታል ። ስሙ
ከፀሓይ ፡ ፊት ፡ አለ ፡ የሚል ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ አለው ። ይኽስ ፡ ባይኾን ፤ እግዚአብሔር
የዳዊትን ፡ ዙፋን ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ አጸናለሁ ፤ ዙፋኑም ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ዕድሜ ፡ ማለት
ሰማይ ፡ የሚኖረውን ፡ ያኽል ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ይኖራል ፡ ሲል ፤ በይሁዳ ፡ የተ
ረጋው ፡ የዳዊት ፡ ዙፋን ፤ ከዳዊት ፡ እስከ ፡ ዘሩባቤል ፡ በነገሡት ፡ ነገሥታት ፡ ብቻ
መንግሥቱ ፡ ተፈጽሞ ፡ ሲታጠፍ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ለሚታመኑ ፡ ሰዎች፡ኹሉ
የሕሊና ፡ ዕንቅፋት ፡ በኾናቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከሐሜት
ንጹሕ ፡ ነው ።

፹ ፤ ክቡር ፡ ዳዊት ፤ ወትሠይመኒ ፡ ውስተ ፡ ርእሰ ፡ ሕዝብ ። ሕዝብ፡ዘኢየአም
ተቀንየ ፡ ሊተ ። የሕዝብ ፡ ራስ ፡ አድርገኽ ፡ ትሾመኛለህ ። የማያውቀኝ ፡ ወገን ፡ ተገ
ልኝ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ትንቢታዊ ፡ ቃል ፡ ይፈጸምለት ፡ ዘንድ ፡ ልጁ ፡ ሰሎሞን ፡ በ
ፋኑ ፡ በተቀመጠበት ፡ ቀን ፤ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ምሕረት ፡ ለአደረገለት ፡ ፈጣሪው ፤ በመ
ታው ፡ ላይ ፡ ሰግዶ ፤ ዐይኑ ፡ ሲያይ ፡ ከዘሩ ፡ በዙፋኑ ፡ የሚቀመጥ ፡ ስለ ፡ ሰጠው ፤ ም
ጋና ፡ ካቀረበ ፡ በኋላ ፤ አቤቱ ፡ ፍርድኽን ፡ ለንጉሡ ፡ (ለሰሎሞን) ፡ ጽድቅኽንም ፡ ለ
ጉሡ ፡ ልጅ ፡ ስጥ ። በማለት ፡ የመጨረሻ ፡ ጸሎቱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቀረበ ። መዝ
፲፰ ፡ ቍ ፡ ፵፫ ። መዝ ፡ ፸፪ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፹፩ ፤ በዚህ ፡ ቅዱስ ፡ ጸሎት ፡ ምክንያት ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ራሱ ፡ አባቴ
አምላኬ ፡ ረዳቴ ፡ መድኀኒቴ ፡ ይለኛል ። እኔም ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ አደርገዋለሁ ። እሱ
ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ በላይ ፡ ነው ፡ ማለት ፤ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ነው ። ቸርነቴን ፡ ለዘ
ዓለም ፡ አጸናለታለሁ ፡ ስለ ፡ አለ ፤ ፍርዱን ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፤ እው
ተኛ ፡ ኪዳኑን ፡ ለንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ለቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ሰጠ ።

፹፪ ፤ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ (3016) ፫ሺሕ ፡ ፲፮ ፡ ዓመት ፡ ኢትዮጵያዊውን
ዙፋን ፡ የተወሐደው ፡ የዳዊት ፡ ዙፋን ፤ በክብር ፡ ላይ ፡ ክብር ፡ እየጨመረ ፡ ኖሮዋል
ወደፊትም ፡ ይኖራል ። የነምር ፡ ዋሻ ፡ የአንበሳ ፡ ጕድጓድ ፡ ከኾነው ፡ ሉዓላዊ ፡ ትው
ልደ ፡ መንግሥት ፡ የወጡት ፡ የአንበሳ ፡ ደቦሎች ፡ ነገሥታት ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ
እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፪፻፹፯ ፡ ናቸው ።



፹፫ ፤ ከአብራክኽ ፡ የተገኘውን ፡ በዙፋንኽ ፡ አነግሥልሀለሁ ፡ ባለውም ፡ መሠ
ረት ፤ በልዑል ፡ ዐልጋ ፡ ወራሽ ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤
ለ ፡ መንግሥቱ ፡ አወራረስ ፡ በተፈጸመው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
ዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

፹፬ ፤ እንድረዳችሁ ፡ እኔን ፡ መለመን ፡ ትታችሁ ፤ ሊረዱዋችሁ ፡ የማይችሉትን ፡
ማይጠቅሙአችሁን ፡ አሕዛብን ፡ ትለማመጣላችሁ ፡ ብሎ ፡ የወቀሳቸው ፡ የይሁዳና ፡
እስራኤል ፡ ነገሥታት ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ረድኤት ፡ የአብርሃምን ፡ በረከት ፡ ትተው ፤
አሕዛብ ፡ ጌሻነት ፤ በትውስት ፡ መሣሪያ ፡ ብዛት ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለማጽናት ፡
ጣጣሩ ፤ ዐመፅን ፡ ሲመክሩ ፤ በኪዳን ፡ ኖኅ ፡ በኪዳን ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ላይ ፡ ኪዳን ፡
አብርሃምን ፡ ኪዳን ፡ ዳዊትን ፡ መከዳዎች ፡ አድርጋ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚገኘውን ፡
ጥፍ ፡ ጕልበት ፡ ለማግኘት ፤ ተስፋዋንም ፡ ከፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፤ ዘሯን ፡ ከዳዊት፡ ዘር፡
ማዋሐድ ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ በሕሊናዋ ፡ ያሰበቻት ፡ የፈጸመቻት ፡ ምክር ፤ ድንቅ ፡ ጥልቅ፡
ታላቅ ፡ ጥበብ ፡ ናት ፤ ይህች ፡ ምክር ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ። ኢሳ ፡ ፴ ፡ ፩-፲፩ ።

፹፭ ፤ በዚህች ፡ ጥበብ ፤ ኀያላኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ይነግሣሉ።ታላቂቱን ፡
አገር ፡ ይይዛሉ ፤ ሰፊ ፡ ግዛት ፡ ይገዛሉ ፤ ረቂቅ ፡ ፍርድ ፡ ይፈርዳሉ ፤ በዚህች ፡ ጥበብ ፡
ላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ሰብዐቱን ፡ ሀብታት ፡ ይወርሳሉ ። ምሳ ፡ ፰ ፡ ፩—፳፩ ።

፹፮ ፤ አንደኛ ፡ በእናት ፡ በአባታቸው ፡ ቤት ፤ በሞግዚቶቻቸው ፡ እጅ ፤ ለነገሥ
ታት ፡ በተወሰነላቸው ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፤ ተስፋ ፡ አበውን ፡ የሀገር ፡ ፍቅርን ፡ ሥርዐተ ፡
መንግሥትን ፡ ምስጢረ ፡ ሃይማኖትን ፡ እየተማሩ ፡ ሲያድጉ ፤ የመልካም ፡ አስተዳደግን ፡
ርኣያ ፡ ሲያሳዩ ፤ የጸጥተኛነት ፡ የአስተዋይነት ፡ መልክ ፡ ሲታይባቸው ፤ በንጉሠ ፡ ነገ
ሥት ፡ አባታቸውና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ መመረጥን ፡ መወደድን ፡ ለሥራ ፡ መታ
መንን ፡ ያገኛሉ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ያልጋ ፡ ወራሽነት ፡ ተስፋ ፡ ይጣልባቸዋል ።

፹፯ ፤ ኹለተኛ ፡ የጥበብና ፡ የኀይል ፡ መንፈስ ፡ በተሟላው ፡ የአስተዳደግ ፡ ጊዜ
ያቸው ፤ ከሊቃውንት ፡ ጋራ ፡ እየዋሉ ፤ ምስጢር ፡ ሲያደላድሉ ፤ በሃይማኖት ፡ ያባቶቻ
ቸውን ፡ አምላክ ፡ ሲከተሉ ፤ ለሀገር ፡ ፍቅር ፡ መቈርቈር ፡ ሲያድርባቸው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡
በእግዚአብሔር ፡ መራጭነትና ፡ ሰጭነት ፤ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አባታቸው ፡ ተከታይ ፡
ዐልጋ ፡ ወራሽ ፡ ይኾናሉ ፤ ለዘውድ ፡ ይታጫሉ ።

፹፰ ፤ ሦስተኛ ፡ በዐልጋ ፡ ወራሽነት ፡ ጊዜያቸው ፡ አገራቸውን ፡ አምላካቸውን፡
በመውደድ ፤ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ በበጎ ፡ ምግባር ፡ ሕግ ፡ ጠባቂነትን ፤ አስተዳደር ፡
ዐዋቂነትን ፤ ፍርድ ፡ ጠንቃቂነትን ፡ ይዘው ፡ ሲገኙና ፡ በመከላከያም ፡ በኩል ፡ ካባቶቻ
ቸው ፡ በታሪክ ፡ ከወረሱት ፡ ከኢትዮጵያዊው ፡ የተፈጥሮ ፡ ጀግንነት ፡ ጋራ፤ ብልኀነትን፡
አስታዋይነትን ፡ ቅልጥፍናን ፡ በጠቅላላው ፡ የጦር ፡ አመራር ፡ ሙያን ፡ ሲያከናውኑ ፤
እንደ ፡ አእምሮዋቸው ፡ ስፋት ፤ እንደ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ጽናት ፤ በልዑል ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ አምላካቸው ፤ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አባታቸው ፤ በተወዳጅ ፡ ሕዝባቸው ፡ ፈቃድ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከአባቶቻቸው ፡ በኋላ ፡ የመንግሥቱን ፡ ዙፋን ፡ ይወርሳሉ ። ዘውድ ፡ ጭነው ፡ ሉል ፡ ጨብጠው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ይኾናሉ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዳዊት፡እንደ ፡ ሰጠው ፡ ኪዳንና ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ዙፋን ፡ ወግ ፤ ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ በላይ ፡ ስለሚኾኑ ፡ አጼ ፡ በሚባል ፡ ስም ፡ ይጠራሉ ።

፹፱ ፤ አራተኛ ፤ እግዚአብሔርን፡አባት ፡ ረዳት ፡ መድኀኒት ፡ እንደ፡ኾነ፡አምነው፡ አባታችን ፡ አምላካችን ፡ ረዳታችን ፡ መድኀኒታችን ፡ ብለው ፡ በጸሎተ ፡ ሃይማኖት ፡ ሲጠሩት ፡ በበኵር ፡ ልጅነታቸው ፡ ስለሚረዳቸው ፤ በረድኤቱ ፡ ግዛታቸውን ፡ ያሰፋሉ ፤ ጠላታቸውን ፡ ይገፋሉ ። በልግስና ፡ ሕዝባቸውን ፡ ይገድፋሉ ። ራስ ፡ ቍር ፡ ሸልመው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መዓርጋት ፡ ሰጥተው ፡ ልዑላን ፡ መሳፍንትን ፤ ክቡራን ፡ መኳንንትን ፡ ይሾማሉ ። ዘውድ ፡ ጭነው ፡ የንጉሥነት ፡ ዙፋን ፡ በአለባቸው ፡ አገሮች ፡ ነገሥታቱን ፡ ያነግሣሉ ። የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ኹለት ፡ ልሳን ፡ ሰይፍ ፡ ያለ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ቤተ ፡ መንግሥትንና ፡ ቤተ ፡ ክህነትን ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ አጣምረው ፡ አዋሕደው ፡ ያስተዳድራሉ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፤ ከወሰን ፡ ክልላቸው ፡ አንድ ፡ ጫማ ፡ አንድ ፡ ስንዝር ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ጋት ፡ ሳያሰርቁ ፡ ሳያስነጥቁ ፡ ከትምህርተ ፡ ሃይማኖታቸው ፤ አንድ ፡ ነቍጥ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ነጥብ ፡ ሳያስፍቁ ፡ ከሥጋዊና ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ጠላት ፡ ጋራ ፡ ሲታገሉ ፡ ሲጋደሉ ፡ ይኖራሉ ። እግዚአብሔርም ፡ ድሉን ፡ ስለሚሰጣቸው ፤ ተጋዳይ ፡ አርበኛ ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ። ለአገራቸውም ፡ የታሪክ፡ድልብ፡ ያኖራሉ ።

፺ ፤ ዐምስተኛ ፤ እግዚአብሔር ፡ በሰጣቸው ፡ የመንግሥት ፡ አስተዳደር ፡ ላይ ፤ የቸልታ ፡ መንፈስ ፡ ቢያመጡ ፡ ሕጉን ፡ ቢለውጡ ፡ ወሰን ፡ ክልላቸውን ፡ ትምህርተ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ባይጠብቁ ፡ የአምላካቸውን ፡ የአገራቸውን ፡ ክብር ፡ ቢንቁ ፡ ፍርድ ፡ ቢያደሉ ፡ መማለጃ ፡ ቢበሉ ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ የሚሠራውን፡ግፍ ፡ እንዳያዩ ፡ ዐይናቸውን ፡ ቢሸፍኑ ፡ የድኾችን፡ ጩኸት ፡ እንዳይሰሙ ፡ ጆሮዋቸውን ፡ ቢደፍኑ ፡ የግል ፡ ጥቅማቸውን ፡ ፈላጊዎች ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ ወዳጆች ፡ ቢኾኑ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አደራ ፡ ቢያቃልሉ ፡ አፈ ፡ ጻድቅ ፡ ኾነው ፡ በልቡናቸው ፡ ቢክዱ ፡ በእሱ ፡ ላይ ፡ የሰው ፡ ወይም ፡ የጋኔን ፡ ውሽማ ፡ ይዘው ፡ ጐድን ፡ ጐድን ፡ ቢሄዱ ፡ ከቤት ፡ ወይም ፡ ከጎረቤት ፡ ጠላት ፡ አስነሥቶ ፡ ያስደነግጣቸዋል ፤ ያንቀጠቅጣቸዋል ። ከክብራቸው ፡ ከቤታቸው ፡ ያወጣቸዋል ። በደዌ ፡ በጦር ፡ በረኃብ ፡ በቸነፈር ፡ በስደት፡በሞት ፡ ይቀጣቸዋል ። ዘሌዋ ፡ ም ፡ ፳፮ ፡ ፩—፵፮ ።

፺፩ ፤ ስድስተኛ ፤ በሠሩት ፡ በደል ፡ ደንግጠው ፤ ኀጢአታቸውን ፡ አምነው ፡ ተጠጥተው ፡ አንተን ፡ ትተን ፡ ሌላ ፡ የተከተልን ፡ ትእዛዝኽን ፡ ያልሰማን ፡ ሕግኽን ፡ ያፈረስን ፡ አደራኽን ፡ ያጠፋን ፡ ስምኽን ፡ የካድን ፡ እኛ ፡ ኀጢአተኞች ፡ ነን ፤ ሕጌን ፡ ብትጠብቁ ፡ እጠብቃችኋለሁ ፤ ሕጌን ፡ ባትጠብቁ ፡ አጠፋችኋለሁ ፤ ለሚጠሉኝ፡ እስከ፡ሦስት፡



ትውልድ ፡ ድረስ ፡ የአባቶችን ፡ ኀጢአት ፡ በልጆች ፡ የምቈጥርና ፡ የማስከፍል ፡ ተኛ ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ ያልክ ፡ አንተ ፡ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡ ነህ ። እኛ ፡ ስለ ፡ ኀጢአ ችን፡ብዛት፡በአፋችን፡ስምኽን፡ለመጥራት፡ወደ፡አንተ ፡ አንገታችን ፡ አቅንተን ፡ ሰማይ ዙፋንኽን ፡ በዐይናችን፡ለማየት፡የሚገባን፡አልኾንም ። ነገር ፡ ግን ፡ አንተ፡ዘፀ ፡ ፴፬ ፡ ስምየኒ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፤ ስሜ ፡ መሐሪ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ይባላል ፡ ብለኽ ፡ ስ ነገርከን ፡ ስለ ፡ ስምኽ ፡ ብለኽ ፡ የኖኅን ፡ የመልከ ፡ ጼዴቅን ፡ የአብርሃምን ፡ የዳዊት ኪዳን ፡ አትለውጥብን ፤ ምሕረትኽን ፡ አታርቅብን ፤ በደላችንን ፡ አታስብብን ፤ ርታኽ ፡ ፈጥኖ ፡ ይደረግልን ፡ ብለው ፡ ቢለምኑት ፡ ንስሓቸውን ፡ ተቀብሎ ፡ ምሕረቱ ያበዛላቸዋል ። በጦር ፡ ሜዳም ፡ ኀይሉን ፡ እንደ ፡ ዝናር ፡ ያስታጥቃቸዋል ። እንደ ፡ ባሽ ፡ አግሬ ፡ ከመከራው ፡ ይሰውራቸዋል ። ከወደቁበት ፡ ያነሣቸዋል ። ክብራቸውን ስማቸውን ፡ ያድስላቸዋል ። የጠላቶቻቸውን ፡ ፊታቸውን ፡ መልሶ ፡ ጀርባቸውን ፡ ቀል ኀይላቸውን ፡ ደምስሶ ፡ ድሉን ፡ ይሰጣቸዋል ። በቤት ፡ በጎረቤት ፡ በቅርብ ፡ በሩቅ ፡ ያ ጠላታቸውን ፡ በእጃቸው ፡ ጭብጥ ፡ በእግራቸው ፡ እርግጥ ፡ አድርጎ ፡ ያስገዛላቸዋል ፡

፺፪ ፤ ሰባተኛ ፤ ኢትዮጵያውያን ፡ ነገሥታት ፡ ገና ፡ በሕይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ ጆቻቸው ፡ በኵሩን ፡ ለመንግሥታቸው ፡ ወራሽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ገልጸው ፡ የመስፍንነቱ አክሊል ፡ ሰጥተው ፡ ዐልጋ ፡ ወራሽ ፡ ብለው ፡ ይሾሙታል ። ይህ ፡ ልማድ ፡ ከዳዊት ከንግሥተ ፡ ሰባ ፡ የተወረሰ ፡ ነው ።

፺፫ ፤ የዳዊት ፡ ልጆች ፡ ብዙዎች ፡ ስለ፡ነበሩ ፤ ዳዊት ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔ ባገኘው ፡ ተስፋ ፡ በግልጽ ፡ ለሕዝቡ ፡ ባያስታውቅም ፡ ቅሉ ፤ ዐልጋ ፡ ወራሽነትን ፡ በ ሊናው ፡ ወስኖ ፡ ይህንኑ ፡ ለሰሎሞን ፡ እናት ፡ ለቤርሳቤህ ፡ (ባትሸባ) ፡ ገልጾ ፡ በመሐ አጸንቶላት ፡ ነበረ ።

፺፬ ፤ የመንግሥቱን ፡ አወራረስ ፡ ቍርጥ ፡ ባለማወቃቸውም ፡ ከልጆቹ ፡ አቤሎምና ፡ አዶንያስ ፡ የተባሉት ፡ በአባታቸው ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ዐመፅ ፡ ሠርተዋል ።

፺፭ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፤ ንጉሡ ፡ ዳዊት ፡ ይህን ፡ የዐመፅ ፡ መንፈስ ፡ የተከተሉ ልጆቹ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾኑ ፡ የእስራኤል ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ ካህናቱም ፡ ጭምር መኾናቸውን ፡ ዐውቆ ፤ የዐልጋ ፡ ወራሽነቱን ፡ መብት ፡ መስጠት ፡ ብቻ ፡ ባይበቃው ልጁን ፡ ሰሎሞንን ፡ ራሱ ፡ ገና ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አነገሠው ፤ በዙፋኑ ፡ ተካው ።

፺፮ ፤ ሰሎሞንም ፡ ዘውድ ፡ ጭኖ ፡ በዙፋን ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፤ አንደኛ ፡ ስለ ሰሎሞን ፤ ኹለተኛ ፡ ስለ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፤ ሦስተኛ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰባ፡ ኹለተውን ፡ ትንቢታዊ ፡ መዝሙር ፡ ዘምሮዋል ፡ ተናግሮዋል ። ፩፡ነገ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፩—፵፱

፺፯ ፤ የሳባ ፡ ንግሥትም ፤ ይህንን ፡ የዳዊትን ፡ መንፈሳዊ ፡ አርአያ ፡ ከአባቶቿ ልማድ ፡ ጋራ ፡ በማዋሐድ ፡ ገና ፡ በሕይወት ፡ ሳለች ፡ ልጇዋን ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክን በኢትዮጵያ ፡ አነገሠችው ፤ በአባቶቿ ፡ መንግሥት ፡ ተካችው ።

www.ethiopianorthodox.org

፺፰ ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ነቢይ ፡ ዳዊት ፤ ፍርድህን ፡ ለንጉሥ ፤ (ሰሎሞን) ፡ እውነተኛነትህንም ፡ ለንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ስጥ ፡ ሲል ፡ የተናገረው ፡ ጸሎት ፡ በረከት ፡ በልጁ ፡ በሰሎሞን ፡ ተጀምሮ ፡ በልጅ ፡ ልጁ ፡ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ተፈጽሟል ።

፺፱ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ይህን ፡ የተቀደሰ ፡ ሥራ ፡ አክብራ ፡ ስለ ፡ ያዘችውና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በኢትዮጵያዊው ፡ ዙፋን ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፤ ከእሱ ፡ በኋላ ፡ ዘውዱን ፡ የሚቀበለው ፡ በኵሩ ፡ ዐልጋ ፡ ወራሹ ፡ በግልጥ ፡ ስለሚታወቅ ፡ ይህ ፡ ሥርዐት ፡ ታላቅ ፡ ዳኛ ፡ ኾኖ ፡ የእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ የታሪካቸው ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሚመሰክረው ፤ የእስራኤል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በየጊዜው ፡ ካፈሰሰችው ፡ ደም ፡ ኢትዮጵያን ፡ አንጽቷት ፡ ይኖራል። ..እምቅድመ ፡ ፀሐይ ፡ ሀሎ ፡ ስሙ ..ፀሐየ፡ዓለም ፡ ክርስቶስ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ከመምጣቱና ፡ በሥጋ ፡ የዳዊት ፡ ልጅነቱን ፡ ከማስረዳቱ ፡ በፊት ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ልትተላለፍ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ጸንታ ፡ ልትኖር ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽኑዕ ፡ ኪዳን ፡ የተደረገላት ፡ መንግሥተ ፡ ዳዊት ፡ በዘር ፡ መንግሥተ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ተዋሕዳ ፡ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መሠረቷን ፡ አጠበቀች ።

፻ ፤ ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ኹሉ ፡ ወዘልፈ ፡ ይጼልዩ ፡ በእንቲአሁ ፡ ዘወትር ፡ ስለ ፡ እሱ ፡ ይጸልያሉ ፡ በሚለው ፡ ቃለ ፡ ትንቢት ፡ መሠረት ፤ እግዚኦ ፡ ኵነኔከ ፡ ሀቦ ፡ ለንጉሥ ። ጽድቀከኒ ፡ ለወልደ ፡ ንጉሥ ። እያሉ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ ለዐልጋ ፡ ወራሹ ፤ ዘወትር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይጸልያሉ ። በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተስፋ ፡ ዳዊትን ፡ ከነትንቢቱ ፤ ዘርዐ ፡ ዳዊትን ፡ ከነበረከቱ ፡ ከወረሰችበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡ ኢትዮጵያዊነቱን ፡ ሳይለቅ ፡ መንበረ ፡ ዳዊት ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

ረ) በረከተ ፡ ይሁዳ ፡ ከነምልክቱ ።

፻፩ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ በሚሠራቸው ፡ ሥራዎች ፡ ውስጥ ፤ ዕፁብ ፡ ድንቅ ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ የሚወሰን ፡ የፍጡር ፡ ሕሊና ፡ መርምሮ ፡ የማይደርስበት ፡ ጥልቅ ፤ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ በማንኛውም ፡ አድሮ ፡ የሚሠራው ፡ ኀይሉ ፡ ነው ።

፻፪ ፤ አበው ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የነበራቸው፡እምነት ፡ ፍጹም ፡ ምሉዕ ፡ የተቃና ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፤ በረከትን ፡ ለልጆቻቸው ፡ ሲሰጡ ፤ በዐይን ፡ የማይታየውን ፡ ሀብት ፡ እንደሚታይ ፡ ኹሉ ፤ እጅ ፡ በእጅ ፡ እንደ ፡ መስጠት ፡ ያኽል ፡ ይቈጥሩት ፡ ነበረ ። ይህንንም ፡ ለመረዳት ፡ ከይስሐቅ ፡ ታሪክ ፡ በአጭሩ ፡ መጥቀስ ፡ ያስፈልጋል ። ይስሐቅ ፡ በሸመገለ ፡ ጊዜ ፤ የታደነ ፡ የአውሬ ፡ ሥጋ ፡ እንዲበላ ፡ ተመኘ። አምሮቱንም፡ ለማስወገድ ፤ የታወቀ ፡ አዳኝና ፡ ቀስተኛ ፡ የነበረውን ፡ የበኵር ፡ ልጁን ፡ ኤሳውን ፡ ጠርቶ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፤ እነሆ ፡ እኔ ፡ ሸመገልኩ ፡ የታደነ ፡ የአውሬ ፡ ሥጋ ፡ መብላት ፡ አምሮኛል ፡ አድነህ ፡ አምጣልኝና ፡ ከሞቴ ፡ በፊት ፡ በልቼ ፡ ልባርክኽ ፡ ልመርቅኽ ፡ አለው ። ኤሳው ፡ ወደ ፡ አደን ፡ በሄደበት ፡ የበረከት ፡ ዕድለኛ ፡ ያዕቆብን ፡ እናቱ ፡ ከጠቦቶች ፡ መልካሙን ፡ መርጦ ፡ እንዲያርድላት ፤ ምግቡንም ፡ እንድታዘጋጅለትና ፡ ወስዶ ፡ ለአባቱ ፡ እንዲሰጥ ፡ አዘዘችው ።



፻፫ ፤ ያዕቆብ ፡ ግን ፡ በወንድሙ ፡ በኤሳው ፡ ጸጕራምነት ፡ በእሱ ፡ ለስላሳነ
መሐከል ፡ ያለውን ፡ ርቀት ፡ አስታውሶ ፤ ምንም ፡ እንኳን ፡ በሽምግልና ፡ ምክንያ
ዐይኖቹ ፡ ቢፈዙ ፤ አባቱ ፡ ዳስሶ ፡ የለየው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ እንደ ፡ አታላይ፡ወይም ፡ እን
ባለጌ ፡ እንዳይቈጥረውና ፡ በረከት ፡ ሲሻ ፡ መርገም ፡ እንዳይመጣበት ፡ ፈርቶ ፡ ነበ
ቢኾንም ፤ እናቱ ፡ በጥልቅ ፡ ምክር ፡ ስለ ፡ አረጋጋችውና ፡ ስለ ፡ አጽናናችው ፡ ትእዛ
ፈጸመ ። ወደ ፡ አባቱም ፡ ሂዶ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፤ ከሞትኽ ፡ በፊት ፡ በልተኽ ፡ ትመርቀ
ዘንድ ፡ የምትሻውን ፡ አምጥቼልሀለሁና ፡ ተነሥ ፡ ተመገብ ፡ አለው ። ይስሐቅም ፡ ል
አንተ ፡ ማነህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ ያዕቆብም ፡ አባባ ፡ እኔ ፡ የበኵር ፡ ልጅኽ ፡ ኤሳው ፡ ነ
ብሎ ፡ መለሰለት ። ይስሐቅም ፡ ድምጡን ፡ ስለ ፡ ጠረጠረ ፤ ልጄ ፡ እስኪ ፡ ወደ ፡ ን
ቅረብ ፡ ልዳስኽ ፡ አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይስሐቅ ፡ ያዕቆብን ፡ በዳሰሰው ፡ ጊዜ ፤ ርብቃ
ያዕቆብ ፡ በብልኀት ፡ የሠሩት ፡ ሥራ ፤ የጠጕራሙን ፡ የኤሳውን ፡ ሥዕልነትና ፡
ሌነት ፡ ይዞ ፡ በመገኘቱ ፤ ዕውሩ ፡ ሽማግሌ ፡ ይስሐቅ ፡ ጠበቅ ፡ አድርጎ፡ዳሶ ፡ እርግጡ
በማግኘት ፡ ፈንታ ፤ ሥዕሉን ፡ እንደ ፡ ዋና ፡ አምኖ ፡ በድምፁ ፡ ምክንያት ፡ አድሮበ
የነበረውን ፡ ጥርጣሬ ፡ ከሕሊናው ፡ አውጥቶ ፡ ስለ ፡ ጣለው ፤ ያዕቆብ ፡ እንደ ፡ ፈራ
መኾኑ ፡ ቀርቶ ፤ ያቀረበለትን ፡ በልቶ ፡ ጠጥቶ ፡ አቅፎ ፡ ስሞ ፡ ልጄ ፡ የተባረክ ፡ ነ
አሕዛብ ፡ ይገዙልኽ ፤ ወገኖችህ ፡ ይስገዱልኽ ፤ ለወንድምኽ ፡ ጌታ ፡ ኹን ፤ የእናት
ልጆች ፡ ይሰገዱልኽ ፡ ብላ ፤ ጠጣ ፤ ግዛ ፡ ንዳ ፡ ብሎ ፡ ባረከው ፡ መረቀው ።

፻፬ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፤ ኤሳው ፡ መጥቶ ፡ አባቱ ፡ የፈለገውን ፡ ለማቅረብ ፡ እሱ
የተመኘውን ፡ በረከት ፡ ለማግኘት ፡ ቢፈልግ ፤ አሁን ፡ በተንኰል ፡ ወንድምኽ ፡ መጥ
በረከትን ፡ ወሰደብህ ፡ ብሎ ፡ አባቱ ፡ መለሰለት ።

፻፭ ፤ ኤሳውም ፡ በብስጭት ፡ በለቅሶና ፡ በጩኸት ፤ ጥቂት ፡ እንኳን ፡ አላስቀ
ልኝምን ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፤ ወንድምኽን ፡ ለአንተ ፡ ጌታ ፡ አድርጌዋለሁ ፡ እንግዴ
ለአንተ ፡ ምን ፡ እሰጥሀለኹ ፡ ብሎ ፡ መልሶለታል ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፳፯ ፡ ፩-፵፩ ፡ ተመልከ

፻፮ ፤ እንግዴህ ፡ ይስሐቅና ፡ ኤሳው ፡ በተነጋገሩበት ፡ ንግግር ፤ ይስሐቅ ፡ ለ
ቆብ፡በቃል ፡ የሰጠውን ፡ በረከት ፡ እጅ ፡ በእጅ ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ በዙፋን ፡ እንደ ፡ አ
መጠው ፡ ሉል ፡ እንደ ፡ አስጨበጠው ፡ ዘውድ ፡ እንደ ፡ ጫነለት ፡ መንግሥትን ፡ እን
አረጋገጠለት ፡ አስመስሎ ፤ ወንድምኽን ፡ ለአንተ ፡ ጌታ ፡ አድርጌዋለሁ ፡ ያለውን ፡ ቃ
ስንመረምረውና ፡ ይህ ፡ ቃለ ፡ ትንቢት ፡ በያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ በነገሥታት ፡ ላይ ፡
ጽሞ ፡ ስንመለከተው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጥበቡ ፤ ምን ፡ ይረቅ ! ምን ፡ ይደንቅ ! ም
ይጠልቅ ! በማለት ፡ ዐሳባችንን ፡ እንወስናለን ።

፻፯ ፤ በዚህ ፡ ታላቅ ፡ ተስፋ ፡ መሠረትነት ፤ ያዕቆብ፡ በሚሞትበት፡ጊዜ፡ከልጆ
መካከል ፡ ይሁዳን ፤ ይሁዳ ፡ ወንድሞችኽ ፡ አንተን ፡ ያመሰግናሉ ። እጅኽ፡በጠላቶች
ደንደስ ፡ ላይ ፡ ነው ። የአባትኽ ፡ ልጆች ፡ ይገዙልሀል ። የአንበሳ ፡ ግልገል፡ይሁዳ ፡ ል
ሆይ ፤ ከምርኮ ፡ ወጣኽ ። እንደ ፡ አንበሳ ፡ እንደ ፡ ሴት ፡ አንበሳ ፡ ተንበረከከ ፡ ተኛ ። ለ

www.ethiopianorthodox.org

ሰቅሰው ፡ የሚችለው ፡ ማን ፡ ነው ። በትር ፡ ከይሁዳ ፤ የገዥም ፡ ዘንግ ፡ ከእግሮቹ ፡ መካከል ፡ አይወጣም ፡ ብሎ ፡ ባርኮታል ።

፻፰ ፤ ይህ፡በረከት ፡ ለይሁዳ ፡ ቢሰጥም ፡ ቅሉ ፤ለጊዜው ፡ በሱ፡ላይ ፡ ምስክር ፡ አላሳየም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሥራ ፤ እግዚአብሔር ፡ የወሰነለትን ፡ ጊዜ ፡ ሲያገኝ ፤ የበጎች ፡ እረኛ፡ የነበረው ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ እስራኤልና ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ በተሰላለፉበት ፡ የጦር ፡ ሜዳ ፡ እስራኤልን ፡ ይገዳደር ፡ የነበረውን ፡ ጐልያድ ፡ የተባለውን ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ አርበኛ ፡ ገድሎ ፡ ወገኖቹን ፡ ነጻ ፡ ባወጣ ፡ ጊዜ ፤ ኋላም ፡ በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፤ ይሁዳን ፡ ወንድሞቹ ፡ እንዲያመሰግኑት ፡ እጁም ፡ በጠላቱ፡ደንደስ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፤ የአባቱም፡ልጆች ፡ እንዲሰግዱለት ፡ አባቱ ፡ የተናገረለት ፡ ትንቢታዊው ፡ ቃለ ፡ በረከት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተፈጸመ ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ቍ ፡ ፩-፶፰።ም ፡ ፲፰ ፡ ቍ፩-፰።

፻፱ ፤ ዳዊት ፡ ከአለፈ ፡ በኋላ ፤ ይህ ፡ የአንበሳዊነት ፡ ዕድልና ፡ ኀይል ፡ ድልም ፡ የአግዓዚነት ፡ ሥር ፡ ለአለው ፡ ለመንግሥተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሰጭነት ፡ ተጨመረለት ። ስለዚህም ፡ ታሪካዊ ፡ ለኾነው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ መሠረትና ፡ ቀዋሚ ፡ ዐምድ ፡ በኾነው ፡ ዕብነ ፡ መለክ ፡ ( ምኒልክ ) ፡ ላይ ፤ ሞዐ ፡ አንበሳ ፡ የሚል ፡ ምልክት ፡ ( አርማ ) ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ወጣላቸው ።

፻፲ ፤ ከዚያም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤ አግዓዚ ፡ ወልደ፡ አግዓዚ ፡ በመባል ፡ ላይ ፡ አንበሳ ፡ ወልደ ፡ አንበሳ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራ ፡ ጀመር ።

፻፲፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ፡እንደ ፡ አዘዘውና ፡ እንደ፡ወሰነላቸው፤ለጦር ፡ የተቈጠሩት ፡ ኀያላን ፡ እስራኤል ፤ ከነገደ ፡ ይሁዳ ፡ የተመረጠው ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ጠቅላይ ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ ኾኖ ፡ ሦስት፡ሦስቱ ፡ በአንድ፡ወገን ፡ ተደልድለው ፤ በአራት ፡ ተከፍለው፡ በሚሰፍሩበትና ፡ በሚጓዙበት ፡ ጊዜ ፤ ለአራቱም ፡ ክፍል ፡ አራት ፡ ዐይነት ፡ ዐላማ ፡ ነበራቸው ። ከእነዚህም ፡ ሦስቱ ፡ ሥዕለ ፡ ሰብእ ፡ ሥዕለ ፡ ተመን ፡ ሥዕለ፡ንስር ፡ ሲኾኑ ፤ አራተኛው ፡ የጠቅላይ ፡ ጦር ፡ መሪው ፡ የነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ዐላማ ፡ ሥዕለ ፡ አንበሳ ፡ ነበር። ዘኍ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፩—፴፫ ።

፻፲፪ ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፤ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መታሰቢያ ፡ የኾኑ ፡ ነገሮች ፡ የአንበሳ ፡ ሥዕል ፡ ይመለከትባቸዋል ። እንዲሁም ፡ አንበሳ ፡ ዘውድ ፡ እንደ ፡ ጫነ፡ በሥዕል ፡ ይታያል ። ዐዋጅ ፡ በመስጠት ፡ ጊዜም ፤ ኀያላኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፤ ሞዐ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ብለው ፤ የንግግራቸው ፡ በር፡ መክፈቻ ፡ ያደርጉታል።

ስለዚህ ፡ ለማስረጃ ፡ ያኽል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ዐዋጅ፡ ጽፈናል ።

ሞዐ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ።

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ዐ ዋ ጅ ።

መኳንንትም ፡ የሻለቃም ፡ በየሰጠንህ ፡ ግዛት ፡ የነፍስ ፡ ደኅንነት ፡ የሰላም፡ ኑሮ፡ ዕረፍት ፡ የሚለመንበት ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳይሠራ ፡ የመኖሪያ ፡ ቤትኽን ፡ በማደራጀት ፡ ባላገሩም ፡ ተጐዳን ፡ ብሎ ፡ ይጮኻል ፡ እንጂ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመፍረሱ ፡ የተሠራውም ፡ ከተበላሸ ፡ በኋላ ፡ ባለመታደሱ ፡ ተቈርቋሪ፡ ስላላገኘ፤ለነፍሱም ፡ ጉዳት ፡ ለሥጋውም ፡ መቅሠፍት ፡ የሚያመጣ ፡ ኾኖአልና ፡ በያውራጃህ ፡ የተተከሉትን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የፈረሰውን ፡ አሠራ ፤ ያረጀውን ፡ አሳድስ ፤ የሃይማኖት ፡ መሠረቱ፡ የክርስቲያን ፡ ምልክቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሥራት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ባላገሩን ፡ አለወገን ፡ አዘኸ ፡ ድኻ ፡ አትበድልብኝ ፤ አጥቢያውም ፡ በገንዘቡም ፡ በጕልበቱም ፡ ረድቶ ፡ ካወጣና ፡ ከሠራ ፡ በኋላ ፤ ከጕልበቱና ፡ ከገንዘቡ ፡ የሚተርፈውን ፡ ሥራ ፡ እኔ ፡ ረዳለሁና ፡ ችግርኽን ፡ በደጃዝማች ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ፡ በኩል ፡ አስታውቀኝ ።

ከዚህ ፡ ዐዋጅ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሳይሠራ ፡ ቀርቶ ፡ መፍረሱንም ፡ አለመታደሱንም ፡ የሰማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የሚፈጀውን ፡ የሥራ ፡ አጠፌታ ፡ መቀጫ ፡ እየከፈልክ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሥራና ፡ ጕዳይ ፡ ይገባል ።

ሐምሌ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ።



፻፲፫ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከይስሐቅ ፡ በያዕቆብ ፡ ከያዕቆብ ፡ በይሁዳ ፡ ያሳደረውን ፤ በዳዊት ፡ የገለጠውን ፡ ኀይል ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ከነ ፡ ምልክቱ ፡ ስለ ፡ ሰጣቸው ፤ በሥዕል ፡ እንደሚያሳዩት ፡ በአነጋገርም ፡ እንደሚገልጹት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ዘወትር ፡ ከኀይል ፡ ወደ ፡ ኀይል ፡ ስለሚሔዱ ፡ ባለፈው ፡ እንደ ፡ ጠቀስነው ፡ በሥጋዊ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ጥቃት ፡ ሳያስገቡ ፡ ድል ፡ አድራጎች ፡ ኾነው ፡ ይኖራሉ ። ወገኖቻቸው ፡ ይገዙላቸዋል ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ ያመሰግኑዋቸዋል ፤ እጃቸውም ፡ በጠላታቸው ፡ ደንደስ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ይማርካሉ ፡ እንጂ ፤ አይማረኩም ።

## ሰ) ብኵርና ፡ ከነ ፡ ቅብዐቱ ።

፻፲፬ ፤ ብኵርና ፡ ማለት ፤ ቀዳሚነት ፡ ወይም ፡ አለቅነት ፡ ማለት፡ነው።ይኸውም፡ በልደት ፡ ወይም ፡ በሀብት ፡ የሚገኝ ፡ ነገር ፡ ነው ። መገኛውና ፡ ምንጩ ፡ ግን ፤ ራሱ ፡ ሰጪው ፡ ባለቤቱ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ኹኔታውን ፡ ፍጡር ፡ ሊያውቀው ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ የዚህ ፡ ታላቅ ፡ ጸጋ ፡ ምስጢር ፡ ይደነቃል ፡ እንጂ ፤ አይመረመርም ።

፻፲፭ ፤ ብኵርና ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ነው።አንዱ ፡ የአምላክ፡ አንዱ ፡ የፍጡር ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ኀያል ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ለአባቱ ፡ በኵር ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ነገር ፡ ግን ፡ ብኵርናው ፡ አባቱን ፡ የማያስቀድም ፤ እሱን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የማይል ፤ ከሱም ፡ በኋላ ፡ ተመሳሳይ ፡ የማያስከትል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ የሰው ፡ ቀርቶ ፡ የመላእክት ፡ ሕሊና ፡ መርምሮ ፡ አይደርስበትም ።

፻፲፮ ፤ በሥላሴ ፡ መቅደም ፡ መቀዳደም ፡ መከተል ፡ መከታተል ፡ ሳይኖር ፤ አብ ፡ ስለ ፡ ወለደ ፡ ወልድ ፡ ስለ ፡ ተወለደ ፡ ብቻ ፤ የፍጡራን ፡ አእምሮ ፡ በሚችለውና ፡ በሚ

www.ethiopianorthodox.org

ገምተው ፡ መጠን ፤ ከሦስቱ ፡ አንዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፤ ወልድ ፡ በኵር ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ይህን ፡ በቦታው ፡ እናመጣዋለን ።

፻፲፯ ፤ የፍጡራን ፡ ብኵርና ፡ ግን ፤ በልደት ፡ በሀብት ፡ ተቀዳሚ ፡ የኾነው ፡ ለተከታዩ ፡ በኵር ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ጠቀስነው ፡ ኹሉ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚያደርገው ፡ የረቂቅ ፡ ስጦታ ፡ መንገድ ፤ ታናሹ ፡ ታላቅ ፡ ታላቁ ፡ ታናሽ ፡ ይኾናል ። ይህነንም ፡ በሚከተለው ፡ መረዳት ፡ ይቻላል ።

፻፲፰ ፤ መላእክት ፡ በተፈጥሮ ፡ ከሰው ፡ ቅድሚያ ፡ አላቸው ። በተፈጥሮዋቸውም ፡ ረቂቃን ፡ መንፈሳውያን ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ በሥራቸው ፡ ከነሱ ፡ በኋላ ፡ ለተፈጠሩት ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ሊወርሱ ፡ ለተዘጋጁት ፡ ሰዎች ፡ መልእክተኞች ፡ ናቸው ። ዕብ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ። መዝ ፡ ፻፬ ፡ ቍ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፺፩ ፡ ቍ ፡ ፲፩—፲፪ ።

፻፲፱ ፤ የሰው ፡ ልጆች ፡ የአዳም ፡ የበኵር ፡ ልጁ ፡ ቃየል ፤ ወንድሙን ፡ ገድሎ ፡ ከብኵርናው ፡ ከወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፤ ብኵርና ፡ ቦታዋን ፡ የምትለቅበት ፡ ቦታዋን ፡ የምታገኝበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ ይገኛል ።

፻፳ ፤ በዚህም ፡ መሠረት ፡ ሴት ፡ የቃየልን ፡ ብኵርና ፡ ስለ ፡ ወሰደ ፡ ብኵርና ፡ በሴት ፡ በይስሐቅ ፡ በያዕቆብ ፡ በይሁዳ ፡ በዳዊት ፡ በሰሎሞን ፡ ቦታዋን ፡ ከመጀመሪያ ፡ ልጅ ፡ ለቃ ፡ በታናሽ ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ተገኝታለች ።

፻፳፩ ፡ ከሄኖስ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሴም ፡ በነበሩ ፡ አበው ፤ በኋላም ፡ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ቦታዋን ፡ ይዛለች ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ ኤሳውና ፡ ያዕቆብ ፡ በተወለዱ ፡ ጊዜ ፤ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ተደረገ ። ኹለቱም ፡ ገና ፡ በማሕፀን ፡ ሳሉ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ኹለት ፡ ወገኖች ፡ በማሕፀንሽ ፡ አሉ ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ይበልጣል ፤ ታላቁ ፡ ለታናሹ ፡ ይገዛል ፡ ሲል ፡ ለርብቃ ፡ ነገራት ። ከተወለዱም ፡ በኋላ ፡ በአስተዳደግ ፡ ጊዜያቸው ፡ ውስጥ ፡ ኤሳው ፡ አዳኝ ፡ ከበረሃ ፡ ዋይ ፤ ያዕቆብ ፡ ድልድል ፡ ቅምጥል ፡ ከቤት ፡ ዋይ ፤ በመኾናቸው ፤ ኤሳው ፡ ከዕለታት ፡ በአንድ ፡ ቀን ፤ በድካምና ፡ በረኃብ ፡ ምክንያት ፡ ብኵርናውን ፡ ከዕለት ፡ ምግብ ፡ በታች ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ገመታትና ፡ በምስር ፡ ንፍሮ ፡ ለያዕቆብ ፡ ስለ ፡ ሸጠለት ፡ ብርኵና ፡ ለታናሹ ፡ ለያዕቆብ ፡ ተሰጠች ። ዘፍጥ ፡ ም ፡ ፳፭ ፡ ቍ ፡ ፳—፴፬ ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፲—፲፬ ።

፻፳፪ ፤ እንዲሁ ፡ ሮቤል ፡ ከአባቱ ፡ ዕቅብት ፡ ስለ ፡ ደረሰና ፡ የአባቱን ፡ ምንጣፍ ፡ ስለ ፡ አረከሰ ፡ ብኵርናው ፡ ለይሁዳ ፡ ተሰጠ ። ዘፍጥ ፡ ም ፡ ፵፱ ፡ ቍ ፡ ፫—፭ ። ፰—፲፫ ።

፻፳፫ ፤ በኋላም ፡ መልክ ፡ ቁመት ፡ የማያታልለውና ፡ የማይሸነግለው ፤ ልቡና ፡ ያሰበውን ፡ ኵላሊት ፡ ያመላለሰውን ፡ መርምሮ ፡ የሚያውቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከኤልያብ ፡ መርጦ ፡ ለዳዊት ፤ ከአቤሴሎም ፡ ከአዶንያስ ፡ መርጦ ፡ ለሰሎሞን ፡ ብኵርናን ፡ ሰጠ ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ፭—፲፫ ። ፩ ፡ ነገ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፩—፵፱ ።

፻፳፬ ፤ ሕግ ፡ ከመሠራቱ ፡ በፊት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውድ ፡ በመጫን ፡ ብቻ ፡ ይነግሡ ፡ ነበር ፤ ሕግ ፡ ከተሠራ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ እንደ ፡ አዘዘው ፡ ከርቤ ፡ ቀንሞ ፡ ቀጺመት ፡ አበሜ ፡ የሚባሉት ፡ ፬ ፡ ዐይነት ፡ ሽቱዎች ፡ ዐምስተኛ ፡ ዘይት ፡



ገብቶባቸው ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ከጸለየባቸው ፡ በኋላ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ በዚ ዐይነት ፡ የተዘጋጀውን ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብተው ፡ የሚነግሡ ፡ ኾነዋል ። ... አት ፡ ም ፡ ፴ ፡ ቍ ፡ ፳፪ — ፳፯ ።

፻፳፭ ፤ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ዳዊት ፡ ሰሎሞን ፤ ከአበው ፡ የወረሱትን ፡ ከእግዚአብሔ... የተቀበሉትን ፡ ብኵርናን ፡ ከነቅብዐቱ ፡ በሊቀ ፡ ካህናት ፡ አዛርያስ ፡ እጅ ፡ በቀዳማ... ምኒልክ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ሰጣት ፤ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጀምሮ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነ... ታት ፤ በክብራቸው ፡ በቀደመ ፡ ብኵርናቸው ፡ ላይ ፡ የእስራኤልን ፡ ብኵርና ፡ ሀብ... ሴምን ፡ በረከተ ፡ አብርሃምን ፡ በትረ ፡ ይሁዳን ፡ ደርበው ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ተ... ተው ፡ ሉል ፡ ጨብጠው ፡ ዘውድ ፡ ጭነው ፡ የሚነግሡ ፡ ኾነዋል ።

፻፳፮ ፡ ኢትዮጵያ ፤ ሰባት ፡ አዕጹቅ ፡ እንደ ፡ አሏት ፡ መቅረዝ ፡ በሕግ ፡ አማካይነ... ከእግዚአብሔር ፡ ባገኘቻቸው ፡ ሰባት ፡ ሀብታት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የነበራት ፡ እምነት ፡ እያጠነከረች ፤ በጕልበት ፡ ላይ ፡ ጕልበት ፡ እየጨመረች ፤ ክብሯን ፡ እያ... ፋች ፤ በነጻነት ፡ ዘውዷ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ሞቃ ፡ እንደ ፡ ጨረቃ ፡ ደምቃ ፡ እንደ ፡ ... ማዝና ፡ እንደ ፡ ዕንቍ ፡ ፈርጥ ፤ በሀብታት ፡ በምስጢራት ፡ አጊጣ ፡ አሸብርቃ ፡ ት... ለች ።

ለኢትዮጵያ ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ሀብትን ፡ የሰጠ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበ... ይመስገን ። አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ በፊት ፡ ለአዳም ፡ ምን ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠው ?

፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በኋላ ፡ ለኖኅና ፡ ለልጆቹ ፡ ምን ፡ አዘዘ ? ለ... ዊትሳ ?

፫ ፤ እግዚአብሔር ፡ በኦሪት ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ምን ፡ ሰጠ ? ኦሪትን ፡ የጠበቀ ፡ ም... ዋጋ ፡ ያገኛል ?

፬ ፤ ኦሪትን ፡ ያልጠበቀ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ይመጣበታል ?

፭ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ ያገኘቻቸው ፡ ሀብታት ፡ ስንት ፡ ናተቸው ? እነሱ ምን ፡ ምን ፡ ናቸው ?

፮ ፤ መጽሐፈ ፡ ኦሪት ፡ ስንት ፡ ክፍሎች ፡ አሉት ?

፯ ፤ በመጽሐፈ ፡ ኦሪት ፡ የትምህርቱ ፡ መሪዎች ፡ ቃላት ፡ ስንት ፡ ናቸው ? በነሰ... ስንት ፡ ሕግጋት ፤ ስንት ፡ ትእዛዛት ፡ ይገኙባቸዋል ? ሕግጋትንና ፡ ትእ... ትን ፡ ለይተኽ ፡ ተርክ ።

፰ ፤ ክህነተ ፡ ኦሪት ፡ ለማን ፡ ተሰጥቷል ?

፱ ፤ ከአሮን ፡ እስከ ፡ ሳዶቅ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ስንት ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ተሾመዋ... በሰባተኛው ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ አደረ...

፲ ፤ የክህነተ ፡ ኦሪት ፡ ሥርዐቱ ፡ ምንድነው ? ኹኔታውን ፡ በአጭሩ ፡ አስረዳ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፩ ፤ ክህነተ ፡ኦሪት ፡ ከልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ በፊት ፡ በስንት ፡ ዓመት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ተሰጠ ?

፲፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዙን ፡ የጻፈባት ፡ ገበታ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ለሰው ፡ ተሰጠች ? እሷስ ፡ ማን ፡ ትባላለች ?

፲፫ ፤ ሙሴ ፡ ጽላትን ፡ በተቀበለ ፡ በስንት ፡ ዓመት ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽዮንን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሰጠ ?

፲፬ ፤ የብሉይ ፡ መሥዋዕት ፡ ምንድን ፡ ነበር ?

፲፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለቅዱሳን ፡ የሚሰጣቸው ፡ ተስፋ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ?

፲፮ ፤ የዳዊት ፡ ተስፋ ፡ ምንድን ፡ ነው ? ትንቢቱስ ?

፲፯ ፤ ክቡር ፡ ዘር ፡ ምንድን ፡ ነው ?

፲፰ ፤ ኢትዮጵያና ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምን ፡ ነበሩ ?

፲፱ ፤ እግዚአብሔር ፡ የኹለቱን ፡ አገሮች ፡ ፍቅር ፡ ለመግለጥ ፡ ምን ፡ አደረገ ?

፳ ፤ የዳዊት ፡ ዘር ፡ የትኛው ፡ ነው ? በረከቱስ ?

፳፩ ፤ ከዳዊት ፡ ዘር፡መንፈሳዊው ፡ ንጉሥ ፡ማነው ? ምልክቱስ፡ምንድን ፡ ነው ?

፳፪ ፤ ከዳዊት ፡ ዘር ፡ ሥጋዊ ፡ ዘር ፡ ማነው ? ምልክቱስ ፡ ምንንድ ፡ ነው ?

፳፫ ፤ በይሁዳ ፡ የነበረው ፡ የዳዊት ፡ መንግሥት ፡ በስንት፡ ነገሥታት ፡ ተፈጸመ ?

፳፬ ፤ ሰሎሞን ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ምን ፡ አደረገ ?

፳፭ ፤ የዳዊት ፡ ጸሎት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ ሰጠ ?

፳፮ ፤ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነገሡ ፡ ስንት ፡ ናቸው ?

፳፯ ፤ በዳዊት ፡ ተስፋ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሰባቱ ፡ ሀብታት ፡ ምን ፡ ምን ፡ ናቸው ? ስማቸውን ፡ ከነምክንያታቸው ፡ ግለጥ ።

፳፰ ፡ በረከት ፡ በአበው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ይቈጠር ፡ ነበር ?

፳፱ ፤ በይስሐቅና ፡ በልጆቹ ፡ መካከል ፡ ምን ፡ ማስረጃ ፡ ይገኛል ?

፴ ፤ ያዕቆብ ፤ ለይሁዳ ፡ ምን ፡ ተናግሮ ፡ ነበር ? ነገሩስ ፡ መቼ ፡ ተፈጸመ ?

፴፩ ፤ በይሁዳ ፡ በረከት ፡ ምክንያት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ምን ፡ ስምና ፡ ምልክት ፡ ተሰጣቸው ?

፴፪ ፤ የይሁዳ ፡ ዓላማ ፡ ምን ፡ ነበረ ?

፴፫ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ መታሰቢያዎች ፡ ምን ፡ ምልክት ፡ አለባቸው ?

፴፬ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ንግግራቸውን ፡ «ዐዋጅ» ፡ የሚከፍቱበት፡በምን፡ ቃል ፡ ነው ?

፴፭ ፤ ብኵርና ፡ ማለት ፡ ምንድን ፡ ነው ? ከምንስ ፡ ይገኛል ?

፴፮ ፤ ብኵርና፡ስንት፡ዐይነት ፡ መልክ ፡ አለው ? አንደኛውንና፡ኹለተኛውን ፡ ለይ ።

፴፯ ፤ የልደትና ፡ የሀብት ፡ ብኵርና ፡ እንዴት ፡ ነው ?



፴፰ ፤ ቃየል ፡ ወንድሙን ፡ ስለ ፡ በደለ ፡ በብኵርና ፤ ምን ፡ መለዋወጥ ፡ ተደረ

፴፱ ፤ ኤሳው ፡ ምን ፡ አደረገ ? ያዕቆብስ ፡ ምን ፡ አገኘ ?

፵ ፤ ሮቤል ፡ ምን ፡ አደረገ ? ይሁዳስ ፡ ምን ፡ አገኘ ?

፵፩ ፤ ነገሥታት ፡ ከሕግ ፡ በፊት ፡ እንዴት ፡ ይነግሡ ፡ ነበር ? ከሕግ ፡ በኋላስ

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

## ክፍል ፡ ዘመን ፡ ፫ ።

## ኢትዮጵያ ፡ በሕገ ፡ ወንጌል ።

፩ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ በረቂቅ ፡ ባሕርዩ ፡ የሚሠራቸው ፡ ፃ ጢራት ፡ ኹሉ ፤ የባሕርዩን ፡ ርቀት ፡ እንድናደንቅ ፡ እንጂ፤ለመመርመር ፡ እንዳንሞክ በአፋችንም ፡ ቃለ ፡ ኀይል ፡ እንዳንናገር ፤ ብንመረምርም ፡ ድርስ ፡ ነገሩን ፡ ማግኘ ቢሳነን ፡ ይህ ፡ ሊኾን ፡ እንዴት ፡ ይቻላል ? ብለን ፡ እንዳንጠራጠር ፡ ድካማችንን ፡ አ ቀን ፡ ሕሊናችንን ፡ ወስነን ፡ እንድንኖር ፡ ለዕውቀታችን ፡ ማሠሪያዎች ፡ ለዐሳባች መዝጊያዎች ፡ ናቸው ።

፪ ፤ እንዲሁ ፡ ሥሉስ ፡ አካል ፤ ዋሕደ ፡ ባሕርይ ፤ ረቂቅ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔ እሱ ፡ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ የፍጡር ፡ ባሕርይ ፡ የማይመረምረው ፤ የወደደውን ፡ መኾንና ማድረግ ፡ እንዲቻለው ፤ ሥራውም ፡ ከሥራ ፡ በላይ ፡ እንደ፡ኾነ ፡ እሱን ፡ የመሰለ ፡ ሠ አድራጊ ፡ ፈጣሪ ፡ ሥራውንም ፡ የመሰለ ፡ ሌላ ፡ ተሠሪ ፡ ተደራጊና ፡ ተፈጣሪ ፡ ቀድሞ ዛሬ ፡ ወደፊትም ፡ እንደ ፡ ሌለ ፤ ፍጡር ፡ ኹሉ ፡ እንዲያምን ፡ ለሃይማኖቱ ፡ አስገዳጅ ናቸው ።

፫ ፤ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፤ አምላክነቱን ፡ ለመመርመ ለሚፈልግ ፡ ፍጡር ፡ ኹሉ ፤ እንዳይመረመር ፡ ለመኾን ፤ ቻይ ፡ መኾኑን ፡ ለማስረዳ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ በመጀመሪያው ፡ ሰዓት ፡ በመጀመሪያው ፡ ዕለት ፡ ሥራው በጨለማ ፡ ሠራ ፡ ጀመረ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ የተፈጠረ ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ በጨለማ ፡ ውስ ነበረ ። ጨለማው ፡ አልፎ ፡ ብርሃን ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፤ የሚታይ ፡ መልክ ፡ የሚሰ ድምጥ ፡ አልነበረም ።

፬ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለማንኛውም ፡ ነገር ፤ ምንጩ ፡ መፍለቂያው ፡ መምጫውና ፡ ለ ለጫው ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ ሲያስረዳ ፤ የጨለማው ፡ ሰዓቶች ፡ በሚፈጸሙበ ጊዜ ፤ ብርሃን ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ድምጡን ፡ በማሰማት ፡ ብርሃንን ፡ ፈጠረ ።

፭ ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ከአልነበሩበት ፡ በድንገት ፡ ተጠርተው ፤ አሁን ፡ ባሉበ ቦታ ፡ ተገኝተው ፤ ከየት ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ ወደ፡የት ፡ እንዲሄዱ ፤ ምን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፤ ማ እንዳመጣቸው ፤ የት ፡ እንደ ፡ አሉ ፡ ሳያውቁ ፡ ሲጨነቁ ፤ በጨለማ ፡ ታፍነው ፡ ተ ነው ፡ የነበሩት ፡ እንግዶች ፡ ፍጡራን ፤ ድንገተኛው ፡ የብርሃን ፡ ጐርፍ፡ባጥለቀለቃቸ ጊዜ ፤ የነበራቸው ፡ ደስታ ፤ ይህን ፡ ያኽል ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ለመናገር ፡ ልክ ፡ መጠ ምሳሌ ፡ ሚዛን ፡ ስለማናገኝ ፡ መልሳችን ፡ ዝም ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፯ ፤ የፍጡራንም ፡ ደስታ ፤ ከወደ ፡ የት ፡ እንደ ፡ መጡ ፤ ወደ ፡ የት ፡ እንዲሄዱ የነበራባቸው ፡ ዐሳብ ፡ ባይቃለልላቸውም ፡ ቅሉ ፤ «እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ብርሃን ይኹን» ፡ ብሎ ፡ ፈጣሪያቸው ፡ ድምፁን ፡ በሰጣቸው ፡ ቃሉን ፡ ባሰማቸው ፡ ጊዜ ፤ ያጠ ጣቸው ፡ (የፈጠራቸው) ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ እነሱም ፡ ፍጡራን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ቦታቸው ፡ ሰማይ ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በማወቃቸው ፡ ነበርና ፡ ፈጣሪያቸውን ፤ ቅዱስ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ አመሰገኑት ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፩—፬ ።

፯ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ብርሃንን ፡ በፈጠረ ፡ ጊዜ ፤ ጨለማውን ፡ ሌሊት ብርሃኑን ፡ ቀን ፡ ብሎ ፡ ጠራው ። ትርጓሜውም ፤ ሌሊት ፡ ማለት ፡ ዕረፍት ፡ መዓልት (ቀን) ፡ ማለት ፡ ሥራ ፡ ነው ።

ከእነዚህ ፡ ቃላት ፤ ሌሊት ፡ የተባለው ፡ ቃል ፤ ግእዝነቱን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ሲኾን ቀን ፡ የተባለው ፡ ቃል ፤ ተቀንየ ፡ ከሚለው ፡ የግእዝ ፡ ግሥ ፤ አቃፊዎቹን ፡ ተንና ፡ የን ትቶ ፡ እንደ ፡ ጐድን ፡ አጥንት ፡ ከመሓል ፡ አፈንግጦ ፡ ወጥቶ ፡ መዓልት ፡ በሚለው ቃል ፡ ፈንታ ፡ ትክ ፡ ምትክ ፡ ኾኖ ፡ ቀርቶዋል ።

በቤተ ፡ ክህነት ፡ ግን ፤ መዓልት ፡ በተባለው ፡ ቃል ፤ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ ይሠራበ ታል ።

፰ ፤ መዓልትና ፡ ሌሊት ፤ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሰዓት ፡ ተካፍ ለው ፤ ሥራቸውን ፡ ሲፈጽሙ ፡ ፳፬ቱ ፡ ሰዓት ፡ አንድ ፡ ዕለት ፡ ይባላል ።

፱ ፤ ይህ ፡ ውሳኔ ፤ በግእዙ ፡ የጸና ፡ ነው ። በዐማርኛ ፡ ግን ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ኹለት ፡ ቀን ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ስንት ፡ ቀን ፡ እያለ ፤ ዕለቱ ቀን ፡ ተብሎ ፡ ይነገራል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ስንት ፡ ዕለት ፡ መቼ ፡ (ዕ) ለት ፡ እሑድ ለት ፡ ሰኞ ፡ ለት ፡ እያለ ፡ የግእዙን ፡ ቃል ፡ ይከተላል ።

፲ ፤ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፤ ከፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ ጀምሮ ፡ ሌት ፡ እየቀደመ ቀን ፡ እየተከተለ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ሲያከናውን ፡ ይኖራል ።

በምሳሌነቱ ፤ ሌት ፡ ከፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ልደት ፡ የነበረው ዘመን ፡ ቀን ፤ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ እስከ ፡ መጨረሻዪቱ ፡ የፍርድ ፡ ቀን ፡ ያለው፡ዘመን እንደ ፡ ኾነ ፡ መጻሕፍት ፡ ያረጋግጣሉ ።

፲፩ ፤ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሌሊቱ ፡ ምሽት ፡ ውድቅት ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ አጠባብ ተብሎ ፡ ባራት ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ። እንዲሁ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ያለው ዘመን ፤ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ኖኅ ፤ ከኖኅ ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፤ ከሙሴ ፡ እስከ ፡ ሰሎሞን ፤ ከሰሎ ሞን ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ባራት ፡ ክፍል ፡ የተከፈለ ፡ ነው ።

፲፪ ፤ ከዚህም ፤ ከምሽት ፡ እስከ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ያለው ፡ ግማሹ ፡ ሌሊት ጨለማ ፡ እየጸናበት ፡ ስለሚሄድ ፤ ግርማ ፡ ሌሊት ፡ ድምፀ ፡ አራዊት ፡ እንዲበረታበት ከአዳም ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፤ ሥልጣነ ፡ ሞት ፡ የጸናችበት ፤ ኀጢአት ፡ የበረ ታችበት ፤ ክፉዎች ፡ መናፍስት ፡ የሠለጠኑበት ፤ ክፉና ፡ መልካም ፡ ተለይቶ ፡ የማይታ ወቅበት ፤ የጣዖት ፡ አምልኮት ፡ የተመሠረተበት ፡ ከባድ ፡ የመከራ ፡ ዘመን ፡ ነበረ ።



፲፫ ፤ በዚህ ፡ ዘመን ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ልቡ ፡ እንደ ፡ ወደደው ፡ ይሠራ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ሕጉ ፤ ሕገ ፡ ልቡና ፡ ይባላል ።

፲፬ ፤ ከመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ጀምሮ ፡ ያለው ፡ ግማሹ ፡ ሌሊት ፤ ሌሊቱ ፡ ጊዜውን ፡ እየጨረሰ ፤ ጨለማው ፡ እየተቃለለ ፡ ስለሚሄድ ፤ የብርሃንን ፡ መምጣት ፡ የሚሰብክ ፡ የዶሮ ፡ ድምጥ ፡ እንደሚሰማበት ፤ የአጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ እንዲታይበት ፤ ከሙሴ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ባለው ፡ ዘመን ፡ ክፉና ፡ መልካም ፡ ጽድቅና ፡ ኀጢአት ፡ አምልኮተ ፡ ጣዖትና ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተለይቶ ፡ ታውቆዋል ።

፲፭ ፤ እንደ ፡ ዶሮ ፤ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያስታውቁ ፡ የሚሰብኩ ፡ በደብረሲና ፡ የመብረቅ ፡ የነጐድጓድ ፡ ነጋሪት ፡ ድምጥ ፤ አቅርንተ ፡ መንፈስ ፡ የተባሉ ፡ የነቢያት ፡ ትንቢት ፡ ተሰምቶበታል ።

እንደ ፡ አጥቢያ ፡ ኮከብ ፤ በደብረ ፡ ሲና ፡ በደብተራ ፡ ኦሪት ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የክብሩ ፡ ምልክት ፡ ( ብርሃን ) ፡ ታይቶበታል ።

፲፮ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፤ ሰው ፤ ለአእምሮው ፡ ረዳት ፡ የሕግ ፡ መንገድ ፡ አግኝቶ ፡ መመ ራት ፡ ስለ ፡ ጀመረ ፤ ሕጉ ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ ተብሎዋል ፤ ትርጓሜውም ፤ ብርሃን ፡ ወይም ፡ ቃል ፡ ማለት ፡ ነው ።

፲፯ ፤ በሌሊቱ ፡ መጨረሻ ፤ ለፀሐይ ፡ መንገድ ፡ ጠራጊ ፡ ጎሕ ፡ ሰበከ ፡ ይባላል ።

እንዲሁ ፡ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ መጨረሻ ፡ የፀሐየ ፡ ጽድቅ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መንገድ ፡ ጠራጊው ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፤ ከኔ ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ ከኔ ፡ በኋላ ፡ ይመ ጣል ፤ እኔ ፡ የጫማውን ፡ ክር ፡ ልፈታ ፡ አይገባኝም ።

፲፰ ፤ እኔ ፡ በውሃ ፡ አጠምቃችኋለሁ ፤ ነገር፡ግን ፡ እናንተ ፡ ሳታውቁት ፡ በመካከላ ችሁ ፡ የቆመው ፡ እሱ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡በእሳት፡ ያጠምቃችኋል ፤ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ቀርባለችና ፡ ንስሐ ፡ ግቡ ፡ እያለ ፡ ያስተምር ፡ ጀመር ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፲፭-፴፩ ። ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።

ይህ ፡ ትምህርቱ ፤ ለኦሪትና ፡ ለወንጌል ፡ መገናኛ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፡ ኦሪት ፡ ነቢያት ፡ ወንጌል ፡ የተባበሩበት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መድኀኒት ፡ ተገልጾ ፤ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ኹሉ ፡ ያየው ፡ ዘንድ ፤ ተራራው ፡ ኮረብታው ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፤ ቆላው ፡ መልቶ ፤ ተካክሎ ፡ የቀና ፡ መንገድ ፡ እንዲኾን ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ እንዲጠረግ ፡ የአ ውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ኾነ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፵ ፡ ቍ ፡ ፫—፭ ።ማቴ፡ም፡፫ ፡ ቍ፡፫—፬ ።

፲፱ ፤ ዮሐንስ ፡ በኅሕነቱ ፡ ሳለ ፤ እውነተኛው ፡ ፀሐይ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ ከምሥ ራቅ ፡ ኖኅት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወጥቶ ፡ ብርሃኑን ፡ በዓለም ፡ ዘረጋ ። በጨለማና ፡ በሞት ፡ ጥላ ፡ የነበሩ ፡ ኹሉ ፤ ጨለማን ፡ በብርሃኑ ፡ አርቀው ፤ ቅዝቃዜን ፡ በሙቀቱ ፡ አስ ለቅቀው ፤ እጅግ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አላቸው ። ሌሊት ፡ አለፈ ። ቀን ፡ መጣ ። አውሬ ፡ ወደ ፡ ጕድጓዱ ፡ ገባ ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ለሥራ ፡ ወጣ ። የተዘጋው ፡ ተከፈተ ። ፍቅር፡ተመሠረተ ። በሰውና ፡ በመላእክት ፡ በእግዚአብሔርም ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ የጥል ፡ ግድግዳ፡ፈረሰ ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ገጸ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አየ ። በዚች ፡ ቀን ፤ መላእክትና ፡ ኖሎት፡አብረው ፡ ለምስጋና ፡ በተሰለፉ ፡ ጊዜ ፤ ይህ ፡ መልአክ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ የከብቶች ፡ እረኛ ፡ ነው፡፡ብሎ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሊለይ ፡ የሚችል ፡ ኑሮ ፡ ይኾን ? እንጃ ። ዕፁብ ፡ ድንቅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሥራ፡ረቂቅ ፡ የዚህ ፡ የልደት ፡ በዓል ፡ ደስታ ፡ ተካፋዮች ፡ ኹሉ ፤ ከሰማያውያን ፡ መላእክት ፡ እስከ ፡ እንስሳት፡ድረስ፡በፁዓን፡ናቸው ። ኢሳ፡ም፡፱፡፮።ሕዝ፡ም፡፵፬፡፩-፬ ። ሉቃ፡ም፡፪፡ቍ ፡ ፩፡፳፩ ።

፳ ፤ በዚህ ፡ ቀን ፤ ጥንታዊ ፡ ፍቅሩን ፡ የማይረሳ ፡ አምላክ ፤ በሕገ ፡ ልቡና፡እሱን ፡ መሻቷን ፤ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ በማምለክ ፡ መጽናቷን ፤ መምህሮቿ ፡ አባቶቿ ፡ ኖኅ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ አብርሃም ፡ ዳዊት ፡ የሰጧትን ፡ ትምህርት ፡ ሳትለውጥ ፤ ሃይማኖቷን ፡ ሳታናውጥ ፤ በጎ ፡ ምግባሯን ፡ ሳታበላሽ ፤ ልቡናዋን ፡ በፍቅረ ፡ ጣዖት ፡ ሳታቆሽሽ ፤ በንጽሕና ፡ ስትጠብቀው ፡ መቈየቷን ፡ ያውቃልና ፤ ርዳን ፡ ቢሉት ፡ ርዱኝ ፤ ደግፉን ፡ ቢሉት ፡ ደግፉኝ ፡ ለሚል ፤ ቢያነሡት ፡ ቢጥሉት ፡ ቢቈርጡት ፡ ቢፈልጡት ፡ በያ ነዱት ፡ ይህን ፡ አደረጋችሁኝ ፡ ለማይል ፡ ጣዖት ፤ ራሱዋን ፡ ያላዋረደች ፡ እጇዋን ፡ ያልዘረጋች ፡ ጕልበቷን ፡ ያላንበረከከች ፡ ድንግልናዋን ፡ ያላረከሰች ፡ ቃል ፡ ኪዳኗን ፡ ያላፈረሰች ፡ ድንግሊቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከመላእክትና ፡ ከኖሎት ፡ ጋራ ፡ በዓለ ፡ ልደቱን ፡ እንድታከብር ፤ በረከተ ፡ ልደቱን ፡ እንድትካፈል ፡ ፈቅዶ ፡ በመለኮታዊ ፡ ኀይሉ ፡ ወደ፡ ቤተ፡ ልሔም ፡ ጠራት ።

፳፩ ፤ የሰማያዊ ፡ ልዑል ፡ አምላክ ፤ ሰማያዊ ፡ መልክተኛ ፡ ኮከብ ፤ መልክቱን ፡ በነገራት ፡ ጊዜ ፤ አቅራቢያዬ ፡ መልካሟ ፡ ርግቤ ፡ የእኔ ፡ ሆይ ፤ ወደ ፡ ግንቡ ፡ አጠገብ ፡ ወደ ፡ ዋሻው ፡ ጥላ ፤ እኔ ፡ ወደ ፡ አለኹበት ፡ ወደ ፡ በረት ፡ ነዪ ፡ እያለ ፡ የሚጠራትን ፡ ሰው ፡ የኾነውን ፡ አምላክ ፡ ( አማኑኤልን ) ፡ ለማየት ፤ ቃልኽ ፡ ያማረ ፡ ፊትኽ ፡ የከበረ ፡ ነውና ፡ ቃልኽን ፡ አሰማኝ ፤ ፊትኽን ፡ አሳየኝ ፡ እያለች ፤ የወደቀበትን ፡ ለማየት ፡ ገሥገሠች ፡ እንጂ ፤ ልዋል ፡ ልደር ፡ አላለችም ። የምትናፍቀውንም ፡ ለማየት ፡ ስለ ፡ ቸኰለች ፤ ለጥሪዋ ፡ ምክንያት ፡ አልሰጠችም ። መሐ ፡ ፪ ፡ ፲—፲፬ ።

፳፪ ፤ ይህች ፡ ጥንተ ፡ ስንዱ ፡ እመቤት ፡ ለጕዞ ፡ በተነሣች፡ጊዜ ፤ ነቢዩ ፡ ዳዊት፡ ይገንዩ ፡ ቅድሜሁ ፡ ኢትዮጵያ ። ወጸላእቱሂ ፡ ሐመደ ፡ ይቀምሑ ። ነገሥተ ፡ ተርሴስ ፡ ወደስያት ፡ አምኃ ፡ ያበውኡ ። ነገሥተ ፡ ሳባ ፡ ወዐረብ ፡ ጋዳ ፡ ያመጽኡ ። ወይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎሙ ፡ ነገሥተ ፡ ምድር ። ባለው ፡ ቃለ ፡ ትንቢት ፡ መሠረት ፤ ባለባልትና ዩቱን ፡ ባለሙያዩቱን ፡ ንግሥት ፡ ማክዳን ፡ ተከትላ ፤ ወርቅ ፡ ዕጣን ፡ ከርቤ ፡ የተባሉትን ፡ ገጸ ፡ በረከቶች ፡ አሰናድታ ፤ ጕዞዋን ፡ ቀጠለች ።

፳፫ ፤ በአካሄዷም ፡ ወርቅ ፡ ከርቤ ፡ ዕጣን ፡ የሽቱ ፡ ቅመሞችን ፡ ይዛ ፤ የክረምት፡ ደመና ፡ ወይም ፡ ጢስ ፡ መስላ ፡ የሱዳንን ፡ የግብጽን ፡ በረሃ ፡ ቈርጣ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የምትወጣ ፡ ያች ፡ ማናት ? እንደ ፡ ፀሓይ ፡ የሞቀች ፤ እንደ ፡ ጨረቃ ፡ የደመቀች ፡ እንደ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ የምታስደነግጥ ፤ እንደ ፡ ጎሕ ፡ የምትገነበኝ ፡ ( የምታበራ ) ፡ ያች ፡ ማናት ፡ እያለ ፡ በመደነቅ ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ ድምፀ ፡ ትንቢቱን ፡ ያሰማ ፡ ነበር ። መኃ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፯ ። ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፬—፲ ።

፳፬ ፤ « ያን ፡ ጊዜ ፤ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፤ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ዓለምን ፡ ጭጋግ ፡ ጨለማ ፡ ሸፍኗታል ፤ በአንቺ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ብርሃኑና ፡ ምስጋናው ፡ ጌትነቱም ፡



ተገለጠብሽ ፡ ብሎ ፡ በሌሊተ ፡ ልደቱ ፡ የኾነውን ፡ እንደ ፡ ሉቃስ ፡ ዐሳብ ፡ ከተናገረ በኋላ ፡ ኢሳ ፡ ም ፡ ፷ ፡ ቍ ፡ ፪ ። ወትሬእዪ ፡ ሶቤሃ ፡ ወትፈርሂ ፡ ወይደነግፅኪ ፡ ልብኪ እስመ ፡ ይትመየጥ ፡ ኀቤኪ ፡ ብዕለ ፡ ባሕር ፡ ዘአሕዛብ ፡ ወዘበሓውርት ። ወያመጽኡ መራዕየ ፡ አግማል ፡ ወይከድኑ ፡ አናቅጸኪ ፡ አግማለ ፡ ምድያም ፡ ወያመጽኡ ፡ እምሳባ ወርቀ ፡ ወስሂነ ፡ ወይዜንዉ ፡ መድኀኒተ ፡ ዘእምኀበ ፡ እግዚአብሔር ። ከሳባ ፡ ወርቅና ዕጣን ፡ ያመጣሉ ። ከእግዚአብሔርም ፡ የኾነውን ፡ መድኀኒት ፡ ያወራሉ ።

የግመል ፡ ብዛት ፡ በርሽን ፡ ሲሸፍነው ፡ ብዙ ፡ ግመሎች ፡ እየተነዱ ፡ ወደ አንቺ ፡ ሲመጡ ፡ የአሕዛብ ፡ ሀብት ፡ ወደ፡አንቺ ፡ ሲመለስ ፡ አይተሽ ፡ ልብሽ፡ ይደነ ጥብሻል ። ብዙ ፡ ወገኖች ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ አንች ፡ ይመጣሉ ። በእስራኤል ፡ ስለ ተመሰገነው ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስም ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ አድርገው ፡ ያዘጋጁትን ፡ ወ ቃቸውን ፤ ብራቸውን ፡ ከሳቸው ፡ ( ከእነሱ ፡ ) ጋራ ፡ ያመጣሉ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጰ ያውያን ፤ ነገሥተ ፡ ሳባ ፡ የተናገረው ፡ ደረሰ ፡ ተፈጸመ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፷ ፡ ቍ ፡ ፬—፯ ።

፳፭ ፡ እነዚህ ፡ ነገሥታት ፡ ኮከቡን ፤ በምሥራቅ ፡ አይተን ፡ ልንሰግድለት መጥተናልና፡ የተወለደው ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ፡ የት ፡ ነው ፡ እያሉ ፤ ከኢየሩሳሌም ከተማ ፡ በአፍኣ ፡ በጐልጐታ ፡ ሰፍረው ፡ አድረው ፡ የጥያቄያቸውን ፡ ውጤት ፡ ለማ ኘት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ከተማ ፡ ገቡ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፳፮ ፡ ከደቂቀ ፡ ነቢያት ፡ አንዱ ፡ ሚክያስ ፤ ወተንሥኡ ፡ ሰባቱ ፡ ኖሎት ፡ ወ ምንቱ ፡ ሰራዊት ። ሰባቱ ፡ እረኞች ፤ ስምንቱ፡ አለቆች፡ ይነሡበታል፡ እንዲል ፤ ጊዜው ኢትዮጵያና ፡ ፋርስ ፡ የግዛት ፡ ወሰን ፡ ኩታ ፡ አጋጣሚነት ፡ በነበራቸው ፡ ጊዜ፡በመኾኑ አብረዋቸው ፡ የሄዱት ፡ ነገሥታት ፡ መኳንንት ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ነገር፡ ግን ፤ እጅ መንሻ፡ ለማቅረብ ፤ በረከተ ፡ ልደቱን ፡ ለመሳተፍ ፤ እግዚአብሔር፡የቀጠራቸው ፤ በትን ቢት ፡ የጠራቸው ፤ የወርቅ ፡ የዕጣን ፡ የከርቤ ፡ ባለቤቶች ፤ መሊኩ ፡ ወይም ፡ ሚሊቸር ማንቲ ፡ ሶራ ፡ በዲሳስፋር ፡ የሚባሉት ፡ ሳባውያን ፡ ነገሥታት ፡ ነበሩ ። ሚክ ፡ ም፡፭ ቍ ፡ ፭ ።

፳፯ ፡ ሄሮድስ ፡ ንጉሥና ፡ ኢየሩሳሌም ፤ ሰልፋቸውን ፡ ብዛታቸውን ፡ ቅልጥፍ ናቸውን ፡ አይተው ፤ ጥያቄያቸውንም ፡ ሰምተው ፡ ደነገጡ ፡ ተሸበሩ ።

፳፰ ፡ ሄሮድስ ፡ ንጉሥም ፡ ካህናቱን፡ ለብቻቸው ፡ ጠርቶ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ የተነ ገረውን ፡ ትንቢት ፡ ጠይቆ ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፤ ሰብአ ፡ ሰገልን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ሰደዳቸው ፤ ሲሸኛቸውም ፤ ድርሰ ፡ ነገሩን ፡ ጠይቃችሁ ፤ ያገኛችሁት ፡ እንደ ፡ ኾነ እኔም ፡ መጥቼ ፡ እንድሰግድለት ፡ ተመልሳችሁ ፡ ንገሩኝ ፡ ሲል ፡ በጥብቅ ፡ አደራ ለመናቸው ።

፳፱ ፡ ይህ ፡ ቃል ፤ ክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፤ ነገሥታት ፡ የሚሰግዱ ለት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መኾኑን ፡ ስለሚያስረዳ ፤ ለሰብአ ፡ ሰገል ፡ ታላቅ ፡ የሃይማ ኖት ፡ ምስክር ፡ ኾነላቸው ።

www.ethiopianorthodox.org




መድኅን ፡ ክርስቶስ ፡ በተወለደ ፡ ጊዜ ፡ በመንፈሰ ፡ ትንቢት ፡ የተጠሩት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እንደ ፡ ኢሳይያስ ፡ « እነሆ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ » ፡ በማለት ፡ ጠቅሶ ፡ በሚያሳያቸው ፡ በኮከቡ ፡ ምልክት ፡ ሰገዱለት ። ወርቅ ፡ ዕጣን ፡ ከርቤ ፡ ገበሩለት ። መዝ ፡ ፸፪ ፡ ቍ ፡ ፱—፲፩ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፴ ፡ ቍ ፡ ፲ ። ም ፡ ፷ ፡ ቍ ፡ ፯ ። ሶፎ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፲ ።



፴ ፤ እግዚአብሔር ፤ በፈቀደ ፡ ጊዜ ፡ ሥራውን ፡ ለማስመስከር ፤ ኃጥእ ፡ ጻድቅ ፡ አማነ
መናፍቅ ፡ ሰው ፡ ሰይጣን ፡ እንስሳ ፡ ደንጊያ ፡ ስለማይመርጥ ፤ በአዳም ፡ ጊዜ ፤ ያ ፡ እባብ
ዲያብሎስ ፡ ይህችን ፡ ዕፀ ፡ በለስ ፡ ብትበሉ ፡ ዐይናችሁ ፡ ይከፈታል ፡ መልካምና ፡ ክፉ
ታውቃላችሁ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ትኾናላችሁ ፡ ብሎ ፤ ሰው ፡ አምላክ ፡ እን
ኾን ፡ የተነበየውን ፡ ያኽል ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፫-፭ ። ሄሮድስም ፡ መጥቼ ፡ እሰግድለት ፡ ዘንደ
ርግጡን ፡ ንገሩኝ ፡ ሲል ፡ በተናገረው ፡ ቃሉ ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አስገዳጅነት ፡ ያለ
ልቡ ፡ ምስክርነቱን ፡ ሲሰጥ ፤ በቤተ ፡ ልሔም ፡ የተወለደው ፤ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ የሚፈ
ጉት ፡ ንጉሥ ፡ ክርስቶስ ፤ ምድራዊ ፡ ያይደለ ፡ ሰማያዊ ፤ የአንድ ፡ መንደር ፡ ያይደለ
የዓለም ፡ ኹሉ ፤ የከሐድያን ፡ አይሁድ ፡ ያይደለ ፤ የአይሁድ ፡ የተአማንያን ፡ ንጉሥ
እንደ ፡ ኾነ ፡ እሰግድለታለሁ ፡ ብሎ ፡ በማረጋገጡ ፤ በግድ ፡ ከነቢያት ፡ ውስጥ ፡ ኾነ

፴፩ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ፤ በኮከብ ፡ እየተመሩ ፤ በሄሮድስና ፡ በካ
ናት ፡ ምስክርነት ፡ ልባቸውን ፡ እያጠናከሩ ፤ ሃይማኖታቸውን ፡ እያመሳከሩ ፡ ወደ ፡ ቤተ
ልሔም ፡ ደረሱ ።

፴፪ ፤ ከምሥራቅም ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ የመራቸው ፡ ኮከብ ፤ ዘኍልቍ
ም ፡ ፳፬ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ። የተጻፈውን ፡ በመተርጐምና ፡ የኢሳይያስን ፡ ቃል ፡ በመጥቀስ
ነዋ ፡ አምላክክሙ ፤ ነዋ ፡ ንጉሥክሙ ፡ እነሆ ፡ አምላካችሁ ፤ እነሆ ፡ ንጉሣችሁ ፡ ብሎ
አመለከታቸው ። ወደ ፡ ቤትም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፤ በኮከብ ፡ እንደ ፡ አዩት ፡ አርአያ ፡ ከእና
ከድንግል ፡ ማርያም ፡ ጋራ ፡ ሕፃኑን ፡ አገኙ ።

፴፫ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፤ ሣጥናቸውን ፡ ከፍተው ፤ ኮረጃቸውን ፡ ( ቦርሳቸውን )
ፈተው ፤ ወርቅ ፡ ዕጣን ፡ ከርቤ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ አቀረቡለት ። ምክንያቱም ፤ ወርቁ
ስለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነቱ ፤ ዕጣን ፡ ስለ ፡ አምላክነቱ ፤ ከርቤ ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ነበር ። ማቴ
ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፩—፲፪ ።

፴፬ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፤ ኢየሩሳሌም ፡ መጻሕፍት ፡ መምህራን ፡ እያሏት ፤ ኖሎት
መላእክት ፡ ነቢያት ፡ እየመሰከሩላት ፤ የእግዚአብሔር ፡ የክብሩ ፡ ብርሃን ፡ እያመ
ታት ፡ ወደሱዋ ፡ የመጣውን ፡ ንጉሥ ፤ ሳታውቀው ፡ ሳታየው ፤ ሳትለየው ፡ ኢትዮጵያ
በብዙ ፡ ሺ ፡ ምዕራፍ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ የሚገመት ፡ መንገድ ፡ ሄዳ ፤ እጅ ፡ መንሻውን
በማቅረቧ ፤ በረከተ ፡ ልደቱን ፡ በመሳተፏ ፤ ለመንፈሰ ፡ ትንቢት ፡ በመታዘዟ ፤ ከእግ
አብሔር ፡ ጋራ ፡ ያላትን ፡ ግለኛ ፡ ፍቅር ፤ በግልጽ ፡ አሳይታለች ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡
ናት ፡ ትቀርብ ፡ ሞግዚት ፡ የተባለው ፡ ተረት ፡ ተፈጸመ ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፩—፳፩
ሚክ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፴፭ ፤ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ እጅ ፡ መንሻውን ፡ ካቀረቡ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሄሮድስ ፡ እን
መለሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መላክ ፡ በሕልም ፡ ስለ ፡ ነገራቸው ፤ የፈለጉትን ፡ አግኝተ
የተመኙትን ፡ አይተው ፡ መስማት ፤ በማየት ፡ ተለውጦላቸው ፤ ሃይማኖታቸውን ፡ አ
ንተው ፤ ደስ ፡ እያላቸው ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ በሌላ ፡ ሃይማኖት ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ተ
ለሱ ፤ በአርባ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ደረሱ ።

www.ethiopianorthodox.org

፴፮ ፡ እነዚህም ፡ አርባ ፡ ቀኖች ፡ የእስራኤል ፡ መልክተኞች ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ጐብኝተው ፡ የተመለሱባቸው ፡ አርባ ፡ ቀኖች ፡ እስራኤል ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ እስኪገቡ ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ ለፈጸሟቸው ፡ አርባ ፡ ዘመናት ፡ ምሳሌዎች ፡ እንደ፡ኾኑ ፤ ዘኍ፡ም፡ ፲፬፡ ቍ ፡ ፴፫—፴፬ ፡፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዜና ፡ ጥምቀትን ፡ ሳትሰማ፡ ለቈየችባቸው ፡ አርባ ፡ ዘመኖች ፡ ምሳሌዎች ፡ ኾኑ ፡፡

፴፯ ፤ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፤ ሄሮድስ ፡ እንደ ፡ ተሣለቁበት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፤ እጅግ ፡ ተቈጣ ፤ ከሰብአ ፡ ሰገልም፡በተረዳው ፡ የዘመን ፡ ቍጥር ፡ ልክ ፤ ከዓመት ፡ እስከ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ተመንፈቅ ፡ ዕድሜ ፡ ያላቸውን ፡ ሕፃናት ፡ በማስገደሉ ፤ ከመከራው፡ ጽናት ፡ ከግፉ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፤ ከወላጆቹ ፡ የሚመነጨው ፡ የለቅሶ ፡ የዋይታ ፡ ድምጥ ፤ ኤርምያስ ፡ እንደ፡ተናገረ ፡ እስከ ፡ ራማ ፡ ተሰማ ፡ ማቴ ፡ ም፡ ፪፡ቍ ፡ ፲፮—፲፰ ፡፡ ዘፍ፡ም፡ ፴፭ ፡ ቍ ፡ ፲፱ ፡፡ ኤር ፡ ም ፡ ፴፩ ፡ ቍ ፡ ፲፭ ፡፡

፴፰ ፤ ይህ ፡ ጊዜ ፤ ነቢያትን ፡ ወደሷ፡የተላኩትን፡ ኹሉ፤ የገፈፈች፡የገረፈች፡የሰቀለች፡የገደለች ፤ እንስት ፡ አንበሳዊት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የነቢያትን፡ደም ፡ ከአፈሰሰች፡ በኋላ፤ ከአቤል ፡ ደም ፡ ጀምሮ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ እስከ ፡ ገደለችው ፡ እስከ ፡ ዘካርያስ ፡ ደም ፡ ድረስ ፡ የጻድቃን ፡ የነቢያት ፡ ኹሉ ፡ ደም ፡ ከሷ፡ ይፈለግ ፡ ዘንድ ፤ በመጨረሻው ፡ የነቢያትን ፡ ጌታ ፡ ገድላ ፡ ደሙን ፡ የደማቸው ፡ ፍጻሜ ፡ ማኅተም ፡ ለማድረግ ፤ መንፈሳዊ ፡ ዜግነቷን ፡ ለዲያብሎስ ፤ ሥጋዊ ፡ ዜግነቷን ፡ ለቄሣር ፡ ለውጣ ፡ ለማስመዝገብ ፤ የተሰለፈችበትና ፡ ትጥቋን ፡ ያጠበቀችበት ጊዜ ፡ ነው ፡፡ ማቴ ፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ቍ፡ ፴፭—፴፯ ፡፡

፴፱ ፤ ክርስቶስ ፡ በተወለደ ፡ በአርባ ፡ ዘመን ፤ የንግሥት ፡ ሕንደኬ ፡ ጃንደረባ ፡ እንደ ፡ ኦሪት ፡ ሕግ ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሄዶ ፡ በዓል ፡ አክብሮ ፡ ሲመለስ ፡ በሰረገላው ፡ ተቀምጦ ፡ መጽሐፈ ፡ ኢሳይያስ ፡ እያነበበ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ጋዛ ፡ በምታወርደው ፡ መንገድ ፡ ሲሄድ ፡ ይህን ፡ ሰረገላ ፡ ተከተለው ፡ ብሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፊልጶስን ፡ አዘዘው ፡፡

፵ ፤ ፊልጶስ ፡ ሰረገላውን ፡ እየተከተለ ፡ ሲሄድ ፡ ጃንዳረባው ፤ እንደ፡በግ ፡ ለመታረድ ፡ መጣ ፡ በግ ፡ ጸጕሩን ፡ ሲሸልቱት ፤ ከሌሊት ፡ ቍር ፡ ከመዓልት ፡ ሐሩር ፡ የምድንበትን ፡ ጸጕሬን ፡ ለምን ፡ ትሸልቱኛላችሁ ? ብሎ ፡ በሸላቾች ፡ ፊት ፡ እንዳይናገር ፤ ሲገፉት ፡ ሲገርፉት ፡ ሲሰቅሉት ፡ ሲቸንክሩት ፡ በምን ፡ ዕዳዬ ፡ ነው ? ብሎ ፡ አልተናገረም ፡፡ ሕይወቱ ፡ ከምድር ፡ ተቈርጣለችና ፤ ማለት ፡ ከሰቀልነው ፡ ከገደልነው ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ከአብ ፡ ያለ ፡ እናት ፤ ዓለም ፡ ከተፈጠረ፡በኋላ ፤ ከድንግል ፡ ያለ፡አባት ፡ መወለዱን ፡ ማን ፡ ይናገራል ? ብለው ፡ ይሞት ፡ በቃ ፡ ቢፈርዱበት ፤ ተሰቅሎ ፡ ሙቶ ፡ በሞቱ ፡ ዓለምን ፡ አድኖ ፤ ሞትን ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፤ መግነዝ ፡ ፍቱልኝ ፤ መቃብር ፡ ክፈቱልኝ ፡ ሳይል ፡ ተነሣ ፡ በማለት ፤ ሕማሙን ፡ ሞቱን ፡ ከሐሊነቱን ፡ ሲያመለክት ፡ የተናገረውን ፡ ከነቢዩ ፡ ከኢሳይያስ ፡ ትንቢት ፡ ፶፫ተኛውን ፡ ምዕራፍ ፡ ሲያነብ ፡ ሰምቶ ፤ ይህን ፡ የምታነበውን ፡ ቃል ፡ ታውቀዋለህን ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፡፡ ኢሳ ፡ ም ፡ ፶፫ ፡ ቍ ፡ ፯—፱ ፡፡



፵፩ ፤ ጃንደረባውም ፡ ምስጢሩን ፡ ጠልቆ ፡ ጠንቅቆ ፡ የነገረኝ ፡ የለምና ፡ እ ዴት ፡ ዐውቀዋለሁ ? እንግዲህ ፡ ነቢይ ፡ ይህን ፡ የተናገረ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ነው ? ወይስ ስለ ፡ ሌላ ፡ እባክህ ፡ አስረዳኝ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ፡፡ ለንግግር ፡ እንዲመቸውም ፡ በሰረ ላው ፡ አስቀመጠው ፡፡

፵፪ ፤ ፊልጶስም ፤ በለመደው ፡ ለማስረዳት ፡ ሲል ፤ ከዚሁ ፡ ከኢሳይያስ ፡ ት ቢት ፤ ስለ ፡ ልደቱ ፤ ድንግል ፡ በድንግልና ፡ ፀንሳ ፡ በድንግልና ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ትወ ዳለች ፤ ስሙንም ፡ አማኑኤል ፡ ትለዋለች ፤ ማርና ፡ ቅቤ ፡ ይበላል ፡ ማለት ፤ ኦሪትን ወንጌልን ፡ ያስተምራል ፤ ይህም ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ የሚሰጠው ፡ ም ክት ፡ ነው ፡፡ ኢሳ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ፡፡

፵፫ ፤ ሰውም ፡ ቢኾን ፤ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሲያስረዳ ፤ ሕፃን ፡ ተ ለደልን ፤ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ተሰጠን ፡ ( ወልድ ፡ ለኩነተ ፡ ሥጋ ፡ ተሰጠልን ) ፡ አለቅነቱ በጫንቃው ፡ ነው ፡ ማለት ፤ ሥልጣን ፡ የባሕርዩ ፡ ነው ፤ መካር ፡ ብርቱ ፡ አምላክ ፡ የዘ ዓለም ፡ አባት ፡ የሰላም ፡ አለቃ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ስሙ ፡ ድንቅ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ፡፡ ኢሳ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፮—፯ ፡፡

፵፬ ፤ ይህንና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ቃል ፡ ሲተረጕምለት ፡ ከቈየ ፡ በኋላ ጥምቀት ፡ ከክርስቶስ ፡ ተገኝታ ፡ በስሙ ፡ ለሚጠመቁ ፡ ኹሉ ፡ ልጅነትን ፡ እንድታሰ ቸው ፡ ከመድኀኒት ፡ ምንጭ ፡ በደስታ ፡ ውሃ ፡ ትቀዳለህ ፡፡ አክሊል ፡ እንደ ፡ ለበሰ ወንድ ፡ ሙሽራ ፤ በሽልማቷም ፡ እንደ ፡ አጌጠች ፡ ሴት ፡ ሙሽራ ፤ የሕይወት ፡ ልብስ አልብሶኸኛልና ፤ የጽድቅንም ፡ መጐናጠፊያ ፡ ደርበህልኛልና ፤ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ይለኛል ፡፡ ሰውነቴም ፡ በአምላኬ ፡ በመድኀኒቴ ፡ ደስ ፡ ይላታል ፡፡ ያለውን ፡ እያስረዳወ መንገዳቸውን ፡ ሲሄዱ ፡ ውሃ ፡ ባለበት ፡ ደረሱ ፡፡ ኢሳ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፫ ፡፡ ም ፡ ፷፩ ፡ ቍ ፡ ፲

፵፭ ፤ ጃንደረባውም ፡ ከእናቱ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ባገኘው ፡ የኦሪት ፡ ትምህርት ፡ ል ናው ፡ የታደሰ ፡ አእምሮው ፡ የጐለመሰ ፡ በመኾኑ ፤ ኦሪት ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ መ ችው ፡ ወዲያውኑ ፤ ኦሪት ፡ ነቢያት ፡ ወንጌል ፡ የሚያስተምሩት ፡ ክርስቶስን ፡ ተ ብሎ ፤ ውሃ ፡ ይኸው ፡ ብጠመቅ ፡ ማን ፡ ይከለክለኛል ? ብሎ ፡ ሰረገላውን ፡ አቁሞ ፡ ወ ውሃው ፡ ወረዱና ፡ በፊልጶስ ፡ እጅ ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ ተጠመቀ ፡፡ በኦሪትም ፡ ውጥ የነበረችውን ፡ ሃይማኖቱን ፡ ፍጹም ፡ አደረጋት ፡፡

፵፮ ፤ ጃንደረባውም ፡ የሐዋርያውን ፡ ትምህርት ፡ ተቀብሎ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ገብቶ የወንጌልን ፡ እምነትና ፡ ጥምቀትን ፡ ሰበከ ፡፡ የሐዋ ፡ ሥ ፡ ም ፡ ፰ ፡ ቍ ፡ ፳፮—፵ ፡፡

፵፯ ፤ ኢትዮጵያ ፤ እጅ ፡ መንሻ ፡ አቅርባ ፡ በተመለሰችባው ፡ አርባ ፡ ቀኖች ፡ ቍ ርና ፡ ልክ ፤ አርባ ፡ ዘመን ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ክርስቶስን ፡ ተቀበለች ፡፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ቤ እስራኤል ፤ ከሰቀልነው ፡ ከገደልነው ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ከአብ ፡ ያለ ፡ እናት ፤ ድኅ ዓለም ፡ ከድንግል ፡ ያለ ፡ አባት ፡ መወለዱን ፡ ማን ፡ ይናገራል ፡ ብላ ፤ የሰቀለችው ፡ ደለችው ፡ የሕይወት ፡ ራስ ፡ ክርስቶስ ፡ በትንሣኤው ፡ ስለ ፡ አሳፈራት ፤ በልደቱ ፡ እን ተቈጣች ፡ በትንሣኤውም ፡ ተቈጥታ ፤ ምእመናንን ፡ ለመግደል ፤ ከሞት ፡ የተረፋት

www.ethiopianorthodox.org

ለማሳደድ ፡ ለማባረር ፡ መጻሕፍትን ፡ ለመቈንጠል ፡ የጀመረችውን ፡ እንቢታ ፡ ለመ ፈጸም ፡ ቍርጥ ፡ አድርጋ ፡ የተሰለፈችበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ።

፵፰ ፤ የዐመፅ ፡ ሥራዋንም ፡ ለመፈጸም ፡ ሳውል ፡ የተባለውን ፡ ጀግና ፡ ምእ መናንን ፡ እንዲያድን ፤ የማሰር ፡ የመፍታት ፡ የመደብደብ ፡ የመዝረፍ ፡ መብት ፡ ሰጥታ ፡ ሾመች ። እነ ፡ እስጢፋኖስን ፡ በድንጋይ ፡ ወግራ ፤ እነ ፡ ያዕቆብን ፡ በሰይፍ ፡ መትራ ፡ ገደ ለች ። የሐዋ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ ፪ ። ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፶፰ ።

፵፱ ፤ ስለ ፡ ክርስቶስ ፤ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ገልጠው ፡ አፍርጠው ፡ አበጥ ረው ፡ አንጠርጥረው፡የሚመሰክሩትን ፤ ሄኖክን፡ጥበብን ፡ ተረፈ ፡ ኤርምያስን ፡ መጽሐፈ ፡ ልደትን ፡ እነሱንም ፡ የመሳሰሉትን ፡ ግማሹን ፡ እየፋቀች ፡ አበላሸቻቸው ፤ ግማሹን ፡ እየ ቈነጠለች ፡ አቃጠለቻቸው ።

፶ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከልደት ፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ኢትዮጵያ ፤ ቅዱስ ፡ ፍሬምናጦስን ፡ በፈቃዷ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ልካ ፤ መጻሕፍተ ፡ ሐዲስት ፤ በጠ ቅላላው ፡ ሥርዐተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲመጡላት ፡ በማድረጓ ፤ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አዛርያስ ፡ የተከለላት ፤ ሐዋርያ ፡ ፊልጶስ ፡ ውሃ ፡ አጠጥቶ ፡ ያሳደገላት ፡ ተስፋ ፡ ሕይ ወት ፡ ፍሬውን ፡ ሰጠ ።

፶፩ ፤ ኢትዮጵያ ፤ ሥርዐተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሐዋርያው ፡ ከማርቆስ ፡ መን በር ፡ እንዲመጣላት ፡ መፍቀዱዋ ፤ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ቃለ ፡ ዐዋዲ ፡ ዘይሰብክ ፡ በገዳም ፡ ጺሑ፡ ፍኖተ፡ እግዚአብሔር፡ ወአርዩ፡ መጽያሕቶ ፡ .... የእግዚአብሔርን፡ መንገድ፡ ጥረጉ፡ ጥርጊያውንም ፡ የተዳለደለ ፡ አድርጉ ፡ የሚል ፡ ያዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ድምፅ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ይሰማል ፡ ያለውን ፡ ትንቢት ፡ ጠቅሶ ፡ በወንጌሉ ፡ መጀመሪያ ፡ ስለ ፡ ጻፈ ፤ ኢሳይያስ ፡ በትንቢት ፡ ፊልጶስ ፡ በስብከት ፡ ማርቆስ ፡ በጽሕፈት ፡ ያጣሩትን ፡ የምስጢር ፡ አበባ ፡ እንደ ፡ ንብ ፡ ቀሥማ ፤ አንድ ፡ ዕንጀራ ፡ ማር ፡ አድርጋ ፡ በመጋገሯ ፡ በጣዕሙ ፤ ምረትን፡ በመብራትነቱ ፡ ጨለማን ፡ ለሚያርቅ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፤ በማይጠገብ ፡ መዓር ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖቷ ፡ ባልትዋና ፡ ባለሙያነቷ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ሲመሰክር ፡ ይኖራል ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፵ ፡ ቍ ፡ ፫ ። ማርቆስ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፫ ።

፶፪ ፤ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በም ሳሌ ፡ በዐጸደ ፡ ወይን ፡ እንደ ፡ ነገራት ፤ የወይኑ ፡ ባለቤት ፡ ፍሬውን ፡ ያመጡለት ፡ ዘንድ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ አሽከሮቹን ፡ በመጨረሻ ፡ ልጁን ፡ ቢልክባት ፤ አሽ ከሮቹን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ ፊቷ ፡ ያው ፡ አልበቃት ፡ ብሎ ፡ የደማቸው ፡ መፈጸ ሚያ ፡ የግፋቸው ፡ መደምደሚያ ፡ አድርጋ ፡ ልጁን ፡ በመግደሏ ፤ ክፉዎችን ፡ በክፉ ፡ ሊያ ጠፋቸው ፡ ይገባል ፡ ብላ ፡ እንደ ፡ ፈረደችው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፤ የወይኑ ፡ ባለቤት፡ክፉዎ ችን ፡ በክፉ ፡ አጥፍቶ ፤ መንግሥትን ፡ ከእነሱ ፡ ነሥቶ ፤ ፍሬ ፡ ለሚገኝበት፡ለሌላ፡ሕዝብ፡ ስለ ፡ ሰጣት ፤ መንግሥትን ፡ ክህነትን ፡ ትንቢትን ፡ አጥታ ፤ ከሀብት ፡ ከበረከት፡ተለይታ ፤ ከሀገሯ ፡ ወጥታ ፤ በዓለም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍለ ፡ አገሮች ፤ በስደት ፡ የተበታተነችበት ፤ ስሟም ፡ ካይላ ፡ ፈላሻ ፡ ተብሎ፡የተጠራበት፡ጊዜ ፡ ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ቍ ፡ ፴፫-፵፩ ።



፶፫ ፤ ይህንንም ፡ ያመጣው ፡ ከሕይወት ፡ ሞትን ፡ በመረጠችበት ፡ በዚያ ፡ በ… ሲካ ፡ ቀን ፤ እኛስ ፡ ከቄሳር ፡ በቀር ፡ ንጉሥ ፡ የለንም፡ ስትል ፡ የመሰከረችለት ፤ ቅንአት በሚባለው ፡ ወተት ፡ ያጐለመሰችው ፤ ምቀኝነት ፡ በሚባለው ፡ ቅብዐት ፡ ያለሰለሰችው የቄሳር ፡ በሽታነት ፡ ነው ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፲፭ ።

፶፬ ፤ ኢትዮጵያ ፤ በሕገ ፡ ልቡና ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ በሕገ ፡ ወንጌል ፡ በሦስቱም ሕግጋት ፤ ደም ፡ ማፍሰስ ፡ አጥንት ፡ መከስከስ ፡ ሳይኖርባት ፤ በቅን ፡ ልቡና ፡ በትሑት ሰብእና ፤ ለፈጣሪዋ ፡ ቅን ፡ ታዛዥነቷን ፡ እየገለጸች ፡ ወደሱዋ ፡ የተላኩትን ፡ ኹሉ ፡ በ ላም ፡ በፍቅርና ፡ በክብር ፡ እየተቀበለች ፡ ሃይማኖቷን ፡ ከግቡ ፡ አደረሰች ።

፶፭ ፤ ባለፈው ፡ ከጠቀስናቸው ፤ ኢትዮጵያና ፡ እንቢተኛዪቱ ፡ ትውልድ ፡ ከ… ፋረዱባቸው ፡ ሦስት ፡ ነገሮች ፡ ሦስተኛው ፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ተስፋዋን ፡ እንቢ፡ ስትል ኢትዮጵያ ፡ በኮከብ ፡ እየተመራች ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ድረስ ፡ ሄዳ ፤ ከፈጣሪዋ ፡ ተዋውቃ በዐይነ ፡ መንፈስ ፡ ታየው ፡ ትናፍቀው ፡ የነበረውን ፡ አምላክ ፡ በዐይነ ፡ ሥጋ ፡ አይታ ለይታ ፡ መመለሱዋ ፡ ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፵፪ ።

፶፮ ፤ እንዲሁም ፡ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፤ ይገንዩ ፡ ቅድሜሁ ፡ ኢትዮጵያ ፤ ወጸላእቱሂ ሐመደ፡ ይቀምሑ። .... ኢትዮጵያውያን፡ ይገዙለታል። ጠላቶቹ ፡ ግን ፡ ይዋረዳሉ ፡ ሲል በተናገረላት ፡ ቃል ፡ መሠረት ፤ የተወለደው ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ የት ፡ ነው ? ብ… የጠየቀቻት ፡ ኢየሩሳሌም ፤ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ሄደሽ ፡ ፈልጊ ፡ ብላ ፡ የተዘባበተ… ባትን ፡ ያህል ፤ በበረት ፡ የተኛውን ፡ አምላክ ፡ ሳትንቅ ፡ ሳታቃልል ፤ ከስግደት ፡ ጋራ የተፈቀደላትን ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ በማቅረብ ፤ ሞቱን ፡ መንግሥቱን ፡ አምላክነቱን ፡ መ ክራ ፡ ጠላቶቹን ፡ አሳፍራ ፡ ሃይማኖቷን ፡ አድሳ ፡ ታሪኳን ፡ ቀድሳ ፡ መንበረ ፡ ዳዊትን ከነ ፡ ተስፋው ፡ ወርሳ ፡ መኖሯ ፡ ነው ። መዝ ፡ ፸፪ ፡ ቍ ፡ ፩ - ፲፫ ።

፶፯ ፤ በዚህ ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ ምስጢር ፡ ተደረገ ። ኢየሩሳሌም ፡ በበረት ፡ የተ… ውን ፡ ድኻ ፡ አይታ ፡ ተጸየፈች ። ኢሳይያስ ፡ ያስተማራትን ፡ ረሳች ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፯ ቍ ፡ ፲፬ ።

፶፰ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ግን ፤ በጨርቅ ፡ የተጠቀለለው ፡ በበረት ፡ የተኛው ፡ ንጉሠ ነገሥት ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አምላከ ፡ አማልክት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐወቀች ፤ አመነች ፤ መ… ከረች ።

፶፱ ፤ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ዳዊት ፡ ኢሳይያስ ፡ ሌሎችም ፡ ነቢያት ፡ በአስተማሯት ትምህርት ፡ ሠራችበት ። ስለዚህም ፡ በታላቁ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፤ እንቢተኛዎቹን ፡ ለመ… ረድ ፡ መብት፡ ተሰጣት ። .... ስለዚህ ፤ የገናናዪቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ልጅ ፡ የኾነው ፡ ኹሉ ፤ የ… ናቱ ፡ ታሪክ ፡ የሚታደስበትን ፡ ጽሑፍ ፤ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ ኾነ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ የ… ሪክ ፡ መጻሕፍት ፡ እየለቀመ ፡ ሊሰበስብ ፡ ይገባል ፡ እንጂ ፤ በንጽሕናዋ ፡ ላይ ፤ ልዩ ፡ ል… አሰተኛ ፡ ምክንያት ፡ ሲፈጥር ፡ ቢገኝ ፤ በአባቱና ፡ በእናቱ ፡ ላይ ፡ የድፍረት ፡ ቃል ፡ የ… ናገረ ፡ ይሙት ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈርድበታል ። ዘፀ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ ፡ ፲፪ ም ፡ ፳፩ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ። ማቴዎስ ፡ ም ፡ ፲፭ ፡ ቍ ፡ ፬ ።

www.ethiopianorthodox.org

፹ ፤ ስለዚህ ፡ እኛ ፡ ኹላችን ፤ እንደ ፡ ጫማ ፡ ወይም ፡ እንደሌላው ፡ ዕቃ ፡ የምንቀባው ፡ ልዩ ፡ መልከኛ ፡ ቀለም ፡ ካልተገኘልን ፡ በቀር ፤ ያለ ፡ ቀለማችን ፡ የሚያስጠጋን ፡ የለምና ፡ መጥሮ ፡ መጥሮውን ፡ ዐሳብ ፡ ትተን ፤ ኢትዮጵያነታችንን ፡ ከልብ ፡ እንመን ፡ በአፍም ፡ እንታመን ።

፹፩ ፤ በረከተ ፡ ልደቱን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሰጠ ፡ አምላክ ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።
አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ በረቂቅ ፡ ባሕርዩ ፡ የሚሠራቸው ፡ ምስጢራት ፤ ለእኛ ፡ ምን ፡ ይኾኑናል ? ።
፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ የወደደውን ፡ መኾን ፤ የወደደውን ፡ ማድረግ ፡ ይችላልን ?
፫ ፤ እግዚአብሔርን ፡ የመሰለ ፡ ሌላ ፡ ፈጣሪ ፡ አለን ?
፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አደረገ ? ሥራውስ ፡ ምን ፡ ያመለክታል ?
፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ የጨለማው ፡ ሰዓቶች ፡ በሚፈጸሙበት ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፮ ፤ እንግዶቹ ፡ ፍጡራን ፡ የመጡበትን ፡ ያሉበትን ፡ የሚሄዱበትን ፡ ያውቁ ፡ ነበርን ?
፯ ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የፈጣሪን ፡ ስም ፡ ማን ፡ ገለጸ ?
፰ ፤ ፍጡራኑ ፤ ከቀደመው ፡ ዐሳባቸው ፡ ምን ፡ ተረዱ ? ምን ፡ ቀረባቸው ? በኋላስ ፡ ምን ፡ አደረጉ ።
፱ ፤ እግዚአብሔር ፡ ጨለማን ፡ ብርሃንንስ ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ ጠራ ? የአጠራሩስ ፡ ትርጓሜ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፲ ፤ ሌሊት ፡ ቀን ፤ የተባሉት ፡ ቃላት ፡ በዐማርኛ ፡ እንዴት ፡ ይነገራሉ ?
፲፩ ፤ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ ለምን ፡ ተላከ ?
፲፪ ፤ ከዮሐንስ ፡ በኋላ ፡ ማን ፡ መጣ ?
፲፫ ፤ በጨለማና ፡ በሞት ፡ ጥላ ፡ የነበሩ ፡ ምን ፡ ጥቅም ፡ አገኙ ?
፲፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፲፭ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተጠራች ፡ ጊዜ ፡ ቸል ፡ አለችን ?
፲፮ ፤ ኢትዮጵያ ፤ ለክርስቶስ ፡ ያቀረበችው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፲፯ ፤ ሰብአ ፡ ሰገል ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ጥያቄያቸው ፡ ምንድን ፡ ነበር ?
፲፰ ፤ ሄሮድስና ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ምን ፡ ኾኑ ?
፲፱ ፤ ሄሮድስ ፡ ንጉሥ ፡ ካህናትን ፡ ጠይቆ ፡ ሰብአ ፡ ሰገልን ፡ ምን ፡ አላቸው ?
፳ ፤ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አገኙ ?
፳፩ ፤ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ በመጡበት ፡ መንገድ ፡ ተመለሱን ?
፳፪ ፤ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ሄሮድስ ፡ ምን ፡ አደረገ ?



፳፫ ፤ ፊልጶስ ፡ ሰረገላውን ፡ በተከተለ ፡ ጊዜ ፡ ጃንደረባው ፡ ምን ፡ ያደርግ ነበር ?
፳፬ ፤ ፊልጶስ ፡ ጃንዳረባውን ፡ ስለ ፡ ስንት ፡ ነገሮች ፡ አስተማረው ?
፳፭ ፤ እነሱንስ ፡ ከምን ፡ መጽሐፎች ፡ ጠቅሶ ፡ አስረዳው ?
፳፮ ፤ ከትምህርቱ ፡ በኋላ ፡ ጃንደራባው ፡ ምን ፡ አለው ?
፳፯ ፤ ጃንደራባው ፡ በማን ፡ ስም ፤ በማን ፡ እጅ ፡ ተጠመቀ ?
፳፰ ፤ ጃንደረባው ፤ በአገሩ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፳፱ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ በስንት ፡ ዓመት ፡ ጥምቀትን ፡ ተበለች ? ሳውል ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ በእስራኤል ፡ ምንድን ፡ ነበረ ?
፴ ፤ ቤተ ፡ እስራኤል ፤ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ በግልጥ ፡ የሚመሰክሩትን ፡ ምን ፡ አደገቻቸው ?
፴፩ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ፍሬምናጦስን ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ለምን ፡ ላከች ?
፴፪ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በሦስቱም ፡ ሕግጋት ፤ ወደሱዋ ፡ የተላኩትን ፡ ገድላለችን ?

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

## አንዲት ፡ ሃይማኖት ።

፩ ፤ በሕገ ፡ ልቡና ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ በሕገ ፡ ወንጌል ፡ በሦስቱም ፡ ሕግጋት ፤ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ሃይማኖትም ፡ አንድ ፡ ነው ። ኤፌ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፭ ዘዳ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፬ ።

፪ ፤ እግዚአብሔር ፤ እንደ ፡ ወደደ ፡ መኾንና ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ማድረግ ፡ የግሉ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ። ነበረ ፤ አደረገ ፤ ፈጠረ ፡ የሚባሉት ፡ የመኾንና ፡ የማድረግ ፡ አንቀጾች ይነገሩለታል ።

፫ ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፤ ስለ ፡ እግዚአብሔርነቱ ፤ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተነገረውን ፡ ኹሉ ፡ በልባችን ፡ የምናምንበት ፤ በአፋችን ፡ የምንታመንበት ፡ መግለጫ ፡ ሃይማኖት ፡ ይባላል ።

፬ ፤ ሃይማኖት ፡ ማለት ፤ በዐይን ፡ የማይታየውን ፤ በእጅ ፡ የማይዳሰሰውን ፤ የዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ነገር ፤ ይህ ፡ እንዴት ፡ ይኾናል ? ማለት ፡ ሳይኖር ፤ በሙሉ ልብ ፡ ማመን ፤ በአፍም ፡ በመጣፍም ፡ መመስከር ፡ ነው ።

፭ ፤ ሃይማኖት ፡ እንደ ፡ መሰንቆ ፡ ጭራ ፡ አንዲት ፡ ስለ ፡ ኾነች ፤ እንደ ፡ በገና አውታር ፡ ልዩነት ፡ የለባትም ።

፮ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ጭራው ፡ ኹኔታ ፤ ኹኔታዋ ፡ የሚገለጥባቸው ፡ ዐምስት ወይም ፡ ሰባት ፡ አዕማድ ፡ አሏት ። ምሳ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፯ ፤ ሃይማኖት ፤ የፍጡር ፡ ሕሊና ፡ መርምሮ ፡ የማይፈጽማት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ምጢር ፡ ተብላ ፡ ትጠራለች ።

www.ethiopianorthodox.org

፰ ፤ ይህ ፡ ስም ፤ ጌታችን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይህችን ፡ ምስጢር፡ ከዐዋቆችና፡ ከጠቢባን ፡ ሰውረህ ፡ ለሕፃናት ፡ ገልጠህታልና ፡ የሰማይና፡ የምድር ፡ ገዥ ፡ አባቴ ፡ ሆይ፡ አመሰግንሀለሁ ፡ በአለ ፡ ጊዜ ፤ ያወጣላት ፡ ስም ፡ ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፳፭—፳፯ ።

፱ ፤ ስለ ፡ አገላለጡዋም ፡ ቀድሞ ፡ ስውር ፡ የነበረው ፡ ምስጢር ፡ ዛሬ ፡ ለምእመናን ፡ ስለ ፡ ተገለጠ ፤ ሊታሰብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሊታይ ፡ ሊዳሰስ ፡ አይደለምና ፤ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ በሥጋውያን ፡ ከንፈሮች ፡ ጠንቅቆ ፡ መናገር ፡ አይቻልም ፡ ብሎ ፡ በመጽሐፈ ፡ ኪዳን ፡ በማስተማሩ ፡ ሃይማኖት ፤ በልብ ፡ ተመርምሮ ፡ የሚታመን ፡ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፡ እንጂ ፤ በዐይን ፡ የማይታይ ፤ በእጅ ፡ የማይዳሰስ ፡ መኾኑን ፡ አስረድቷል ።

፲ ፤ ስለዚህ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማመን ፤ ለሃይማኖታችን ፡ ድካምና፡ አጋዥ ፡ ይኾነን ፡ ዘንድ ፤ ስለ ፡ እግዚአብሔርነቱ ፤ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተጻፉትን፡ ቃላት ፡ ከፋፍለን ፡ የምናጠናባቸው ፤ ዐምስቱ ፡ ወይም ፡ ሰባቱ ፡ ክፍሎች ፤ አዕማደ፡ ምስጢር ፡ ይባላሉ ።

፲፩ ፤ እንዲሁ ፤ ለትሑታን ፡ ዕውቀትን ፡ ስለ ፡ ምትገልጥ ፤ ከዕውቀትም ፡ በላይ፡ ስለ ፡ ኾነች ፤ ሃይማኖት ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጥበብ ፡ ተብላ ፡ ትጠራለች ።

፲፪ ፤ ደገኛው ፡ ሰሎሞን ፡ ስለ ፡ እሱዋ ፡ ሲናገር ፤ ጥበብ ፡ ለራሱዋ ፡ ቤት ፡ ሠራች ። ሰባትም፡አዕማድ ፡ አቆመች ። ማዕዷን ፡ አዘጋጀች ። ፍሪዳዋን ፡ አረደች ። የወይን፡ጠጁዋንም ፡ አዘጋጀች ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተጋባዦቹን ፡ ይጠሩ ፡ ዘንድ ፡ ባሮቿን ፡ ላከች ፡ ብሎ ፤ መምህራነ ፡ ወንጌል ፡ ሐዋርያት ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ የጠሩዋቸው ፡ ምእመናን ፤ ሰብዐቱን ፡ አዕማደ ፡ ምስጢር ፡ ተምረው ፤ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ተቀብለው ፡ ከብረው ፡ ሕያዋን ፡ ኾነው ፡ የሚኖሩ ፡ በሃይማኖት ፡ መኾኑን ፡ ገልጾዋል ። ምሳ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፩-፯ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ቍ ፡ ፩—፲፪ ።

፲፫ ፤ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፤ ጥበብ ፡ ከልጆቿ ፡ የተነሣ፡ጸደቀች፡ በአለ ፡ ጊዜ ፤ ሐዋርያት ፡ ለምእመናን ፡ ሲያስተምሩ ፤ ምእመናን ፡ ሰማዕታት ፡ በነገሥታት ፡ በመኳንንት ፡ አደባባይ ፡ ሲመሰክሩ ፤ ዐላውያን ፡ ነገሥታት ፡ ከሐድያን ፡ መኳንንት ፡ በእሳት ፡ ሲያቃጥሏቸው ፤ ከአንበሳ ፡ ጉድጓድ ፡ ሲጥሏቸው ፤ ሃይማኖት ፤ ነበልባለ ፡ እሳት ፡ አብርዳ ፡ አንበሳ ፡ አሰግዳ ፡ በተገለጠች ፡ ጊዜ ፤ መናፍቃን ፡ እያፈሩ ፤ ምእመናን ፡ እየጠነከሩ ፤ ከኀይል ፡ ወደ ፡ ኀይል ፡ በመሄዳቸው ፤ በሃይማኖትም ፡ የክርርቶስ፡ ማደሪያ ፡ በመኾናቸው ፤ ደገኛው ፡ ሰሎሞን ፡ ጥበብ ፡ ለራሱዋ ፡ ቤት ፡ ሠራች ፡ ያለውን፡ ቃል ፤ ጥበብ ፡ ከልጆቿ ፡ ጸደቀች ፡ ያለው ፡ የመድኀኒታችን ፡ ቃል ፡ ተርጕሞታል ። ማቴ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፳ ።

፲፬ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፤ ይህችን ፡ ጥበብ ፡ ቢፈልግ ፤ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ የላከኝ ፡ አብ ፡ ካልሳበው ፡ ማንም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ለመምጣት ፡ አይችልም፡ እንደ ፡ አለ ፤ ቸል ፡ ሳይል ፡ ለኹሉ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ በሰፊው ፡ መስጠት፡የሚቻለው፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ያለ ፡ እርሱ ፡ ሰጭነት ፡ ሊያገኛት ፡ አይችልምና ፤ ሳይጠራጠር ፡ የጥበብ ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይለምን ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፷፭ ።



፲፭ ፤ ጥበብነቷም ፡ ከምድራዊ ፡ ሰው ፤ ወይም ፡ ከመንፈስ ፡ አጋንንት ፡ የተገኘች አይደለችም ። ጥንታዊ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ከኾነው ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ተገኝታ ፤ ከፍጡራን ፡ ኹሉ ፡ ጥበብ ፡ በላይ ፡ ኹና ፤ የፍጡራንን ፡ ዕውቀት ፡ ከንቱ አድርጋ ፡ ትኖራለች ፡ እንጂ ። ያዕ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፭ - ፲፯ ።

፲፮ ፤ ይህች ፡ ጥበብ ፡ ሃይማኖት ፤ ከኖኅ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ነበረች ፤ ከጥፋት ፡ ውሃ አዳነችው ።

፲፯ ፤ መልከ ፡ ጼዴቅን ፡ የወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሳሌ፡የልዑል ፡ እግዚአብሔር፡ ካህን ፡ አደረገችው ። አብርሃምን ፡ በፈተናው ፤ ኢዮብን ፡ በቍስሉ ፡ ረዳችው ። ዳ ትን፡ ከበግ ፡ እረኝነቱ ፡ ጠርታ ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ዙፋን ፡ አወጣችው ። የተቀደሰው ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ቀባችው ። በእሱዋ ፡ ነገሥታት ፡ ይነግሣሉ ፤ በእሱዋ ፡ መኳንንት ይሾማሉ ። ከጻድቃን ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ከሰማዕታት ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ደም ፡ ትሄዳለች ለሰማዕታት ፡ እሳት ፡ እንዲበርድላቸው ፡ አንበሳ፡እንዲሰግድላቸው፡ለባሕታውያን ፡ ቶ እንዲታለብላቸው ፡ ዛፍ ፡ እንዲያፈራላቸው ፡ ታደርጋለች ። ዕብ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፩ - ፴

፲፰ ፤ ሃይማኖት ፤ እባቡን ፡ ለመርገጥ ፡ ጊንጡን ፡ ለመጨበጥ ፡ ዲያብሎስን ድል ፡ ለመንሣት ፡ አጋንንትን ፡ ለመግዛት ፡ በቂ ፡ ሥልጣን ፡ አላት ። ማር ፡ ም ፡ ፲ ቍ ፡ ፲፯ - ፲፱ ።

፲፱ ፤ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ የምታኽል ፡ ሃይማኖት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፤ ሾ ውን ፡ ወርካውን ፡ ነቅሎ ፡ ከወደደው ፡ ቦታ ፡ ሊተክል ፤ ተራራውን ፡ ኮረብታውን ፡ ፈ ቅሎ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ሊጥል ፡ ይችላል ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ቍ ፡ ፳ ።

፳ ፤ ከዚህ ፡ የበለጠ ፤ ክርስቶስን ፡ የተቀበለ ፡ ሃይማኖት ፡ ያለው ፡ ሰው ፤ ከ ጋና ፡ ከደም ፡ ወገን ፡ በባልና ፡ በሚስት ፡ መዋደድ ፡ ከሚገኘው ፡ ልደት ፡ በበለጠ ፡ በ ይመረመር ፡ ምስጢር ፡ በስሙ ፡ የሚያምን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንዲኾን ፡ መ ኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶታልና ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር፡ የነበረው ምስጋናውን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ በአባቱ ፡ ቤት ፡ ይኖራል ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ቍ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ። ም ፡ ፲፯ ፡ ቍ ፡ ፳፬ ።

፳፩ ፤ እንግዲህ ፡ ታላቂቱ ፡ ሃይማኖት ፤ እንደ ፡ ሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ነቅ ፡ ምን ያት ፡ የሌለባት ፡ አንዲት ፡ መኾኗን ፡ ማወቅ ፡ አለብን ።

፳፪ ፤ እሱዋም ፡ አሪት ፡ ነቢያት ፡ ወንጌል ፡ የሰበኩት ፡ ክርስቶስ፤ አንድ ፡ አካ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ የምትናገር ፡ የቀናችው ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ናት ።

፳፫ ፤ ከላይ ፡ እንደ ፡ ጠቀስነው ፤ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ሃይማኖትም ፡ አንደ ስለ ፡ ኾነ ፤ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የምናስተምረው፤ አምላክ ፡ በሰማይ ፡ በምድርም ፡ ከሰማ በላይ ፡ ከምድር ፡ በታች ፤ በመንግሥቱ ፡ ሽረት ፡ በባሕርዩ ፡ ሞት ፡ የሌለበት ፡ ልዑ እግዚአብሔር ፡ መኾኑን ፡ ሃይማኖትም ፡ እርሱ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሰዎች የገለጸውን ፤ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ያጻፈውን ፤ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ በአፍም ፡ በልብም ማመን ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፬ ፤ ስለዚህ ፡ ስንጽፍም ፡ ኾነ ፡ ስናነብ ፤ የሃይማኖት ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር፡ መንገዱን ፡ ይከፍትልን ፡ ዘንድ ፡ ምስጢሩን ፡ ይገልጥልን ፡ ዘንድ ፡ እንለምነው ።

አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ይትቀደስ ፡ ስምከ ፡ ትምጻእ ፡ መንግሥትከ ። አሜን ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስንት ፡ ነው ? ሃይማኖትስ ፡ ስንት ፡ ነው ?

፪ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የሚነገሩ ፡ አንቀጾች ፡ ስንት ፡ ናቸው ? እንሱስ ፡ ማን ፡ ማን ፡ ናቸው ?

፫ ፤ ስለ ፡ እግዚአብሔርነቱ ፡ የምንታመንበት ፡ መግለጫ ፡ ምንድን ፡ ነው ?

፬ ፤ ሃይማኖት ፤ በዐይን ፡ የሚታይ ፤ በእጅ ፡ የሚዳሰስ ፡ ነገር ፡ ነውን ?

፭ ፤ የሃይማኖት ፡ ኹኔታ ፡ የሚገለጽባቸው ፡ አዕማድ ፡ ስንት ፡ ናቸው ?

፮ ፤ ሃይማኖት ፡ ምን ፡ ተብላ ፡ ትጠራለች ?

፯ ፤ ምስጢር ፡ የምትባልበት ፡ ስም ፡ ከየት ፡ ተገኘ ? ጥበብ ፡ የምትባልበትስ ?

፰ ፤ ሃይማኖት ፡ ጥበብ ፡ መባሏ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ?

፱ ፤ ጥበብን ፡ የሚፈልግ ፡ ከማን ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል ?

፲፩ ፤ ጥበብ ፡ ከሰው ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ትገኛለችን ?

፲፪ ፤ በቅዱሳን ፡ ላይ ፡ ከተገለጸው ፡ ሥራ ፡ በአጭሩ ፡ ዘርዝር ።

፲፫ ፤ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ያኽል ፡ ሃይማኖት ፡ ብትኖረን ፡ ምን ፡ ለማድረግ ፡ እን ችላለን ?

፲፬ ፤ ሰው ፡ በሃይማኖት ፡ የሚያገኘው ፤ የበለጠው ፡ ነገር ፡ ምንድን ፡ ነው ?

፲፭ ፤ ሰው ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ የት ፡ ይኖራል ? ምንስ ፡ ያያል ?

፲፮ ፤ እንደ ፡ ሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ምክንያት፡የሌለባት፡ሃይማኖት ፡ ማነኛዪቱ ፡ ናት ?

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

## ፩ኛ ፤ ዐምደ ፡ ሃይማኖት ።

፩ ፤ ዐምድ ፤ ቃልነቱ ፡ የግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በዐማርኛ ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ትርጓሜ ፡ ስለ ፡ አለው ፡ ለቤት ፡ ሲኾን ፤ ቃሉ ፡ ተለውጦ ፡ ምሰሶ ፡ ይባላል ። ለጽሕፈት ፡ ሲኾን ፤ በራሱ ፡ ሳይለወጥ ፡ ዐምድ ፡ ተብሎ፡ይጠራል ። ኹኔታውም ፤ የገጽ፡ ስፋት ፡ መክፈያና ፡ መመጠኛ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ምሰሶ ፡ ከማለት ፡ የራቀ ፡ ነገር ፡ የለውም ።

፪ ፤ በዚህም ፡ ነገር ፤ ሃይማኖትን ፡ ከፍለን ፡ መጥነን ፡ የምናጠናባቸው ፡ ክፍሎች፡ አዕማድ ፡ ይባላሉ ።

፫ ፤ ምክንያቱም ፤ ዐምድ ፡ በገጽ ፡ ስፋት ፡ ላይ፡መክፈያ ፡ መመጠኛ ፡ በመኾኑ፤ ለጽሕፈት ፡ ለንባብ ፡ ደንብ ፡ እንዲሰጥ ፤ ይህም ፡ ሰው ፡ ሰፊ ፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ፡የኾነውን ፡ ባሕርየ ፡ ሥላሴን ፡ ሊመረምር ፡ ቢወድ ፤ በመጠኑ ፡ መርምሮ ፡ ሕሊናውን ፡ እንዲወስን፤ ከዐቅሙ ፡ በላይ ፡ እንዳይመረምር ፡ ሕግና ፡ ደንብ ፡ የሚሰጥ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ።



፬ ፤ እንዲሁም ፡ ዐምድ ፡ በምሰሶነቱ ፡ ቤትን ፡ እንዲያጠና ፤ ይህም ፡ ስለ ፡ ሃይ ኖት ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በተጻፈው ፡ ቃል ፤ የሰውን ፡ ልቡና ፡ የሚያጠና ፡ ስለ ፡ ኾነ ነው ።

፭ ፤ ስለዚህ ፡ ከአዕማድ ፡ ቀዳሚው ፡ መጀመሪያው ፡ እግዚአብሔር ፡ በአካላት በኩነታት ፡ ሦስት ፤ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ ብለን ፡ ማመንን ፡ የምንማርበት ፡ የምናስተ ርበት ፡ ክፍል ፡ ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ይባላል ።

፮ ፤ ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፤ የሦስትነት ፡ ምስጢር ፤ የማይመረመር ፡ መለኮት ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የነበሩ ፤ ዛሬም ፡ ባሉ ፤ ወደፊትም ፡ ዓለምን ፡ አሳልፈው ፡ የሚኖሩ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተባሉ ፡ አካላትን ፡ በማዋሐድ ፡ እንደ ፡ አለ ፡ ዐው እግዚአብሔር ፤ በአካል ፡ በስም ፡ በገጽ ፡ በግብር ፡ በኩነት ፡ (ኹኔታ) ፡ ሦስት ፤ በባሕር በሕልውና ፡ በመለኮት ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማመን ፡ ነው ።

፯ ፤ እግዚአብሔር ፤ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ሲኾን ፡ አንድ ፡ መኾኑን መጻሕፍት ፡ በየገጹ ፡ በየአንቀጹ ፡ አምልተው ፡ አስፍተው ፡ ይናገራሉ ።

፰ ፤ አነጋገራቸውም ፤ እግዚአብሔር ፤ በአካል ፡ ሦስት ፡ ሲኾን ፤ በባሕርይ አንድ ፡ ነውና ፡ ባለቤቱን ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ ይናገራሉ ።

፱ ፤ ስለዚህም ፤ ወይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርአያነ ፡ ወበአም ሊነ ። እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ በመልካችን ፡ በምሳሌያችን ፡ እንፍጠር ፡ አለ ። ዘፍ ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፮ ።

፲ ፤ ወይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዳም ፡ ኮነ ፡ ከመ ፡ አሐዱ ፡ እምኔነ ፡ አዳም ፡ ከእኛ እንደ ፡ አንዱ ፡ ኾነ ፡ አለ ፤ እግዚአብሔር ፡ እያለ፤ ባለቤቱን ፡ አንቀጹን ፡ ያንድ ፤ ዐሳቡ ዝርዝሩን ፡ በብዙ ፡ እያደረገ ፤ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ሲኾ አንድ ፡ መኾኑን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ያስረዳናል ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፮ ። ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፳

፲፩ ፤ እንዲሁ ፡ ዘፍጥረት ፡ ፲፩ ፡ ፯ ። አንዱ ፡ ያንዱን ፡ ነገር ፡ እንዳይሰማ ፤ እንውረድ ፡ ቋንቋቸውንም ፡ እንደባልቅባቸው ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ የላ ውን ፡ የመሰለ ፡ ምስክር ፡ ይሰጣል ።

፲፪ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ አማልክትን ፡ የፈለጉ ፡ ሰዎች ፤ ይልቁንም ፡ የዎ ምር ፡ ሚስዮን ፡ ማኅበር ፤ እነዚህ ፡ ጥቅሶች ፡ አኀዝ ፡ አይወስኑም ፡ እያሉ ፤ በዘፈቀ ብዙ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ነገር ፡ ይናገራሉ ።

፲፫ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለእንቢ ፡ መድኀኒት ፡ የሌለው ፡ በመኾኑ ፤ ከሕግ ፡ ወጥተው በልብ ፡ ወለድ ፡ ሜዳ ፡ እንዲያው ፡ ይፈነጫሉ ። ይፈነጥዛሉ) ፡ እንጂ ፤ መጽሐፍ ፡ ቅዱ አይረዳቸውም ፡ አይመሰክርላቸውም ።

፲፬ ፤ ስለዚህ ፤ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ሲኾን ፡ አን መኾኑን ፤ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጠንቅቆ ፡ ለይቶ ፡ በየስልቱ ፡ በየዐይነቱ ፡ ያስተምረናል ልብ ፡ አድርገን ፡ ትምህርቱን ፡ እንስማው ።

www.ethiopianorthodox.org

ሀ/ የአካልና ፡ የስም ፡ የገጽ ፡ ሦስትነት ፡፡

፲፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ በአካሉ ፡ በገጹ ፡ መጠቅለል ፡ መቀላቀል ፡ የሌለበት ፡ ልዩ ሦስት ፡ ነው ፡፡ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፤ በአካል ፡ በገጽ ፡ ሦስት ፡ መኾኑንም፤ ራሱን በራሱ ፡ መሰወር ፤ ራሱን ፡ በራሱ ፡ መግለጥ ፡ የሚቻለው ፡ ልዑል፡ እግዚአብሔር ፡ ፊት በዘመነ ፡ አብርሃም ፡ ኋላም ፡ በዘመነ ፡ ክርስቶስ ፡ ገልጦታል ፡፡

፲፮ ፤ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፤ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ በዓለም ፡ ከነበሩት ሕዝብ ፡ ፍጹም ፡ ሃይማኖቱና ፡ በጎ ፡ ምግባሩ ፤ በመላእክት ፡ በሰውና ፡ በአጋንንት ፡ ከኹሉም ፡ በላይ ፡ በኾነ ፤ በልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታወቀለት ፡ የተመሰከረለት ርእሰ ፡ አበው ፡ አብርሃም ፡ ነበረ ፡፡

፲፯ ፤ ስለዚህም ፡ አዳምና ፡ እሱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እየተያዩ፤ የሴት ፡ ዘር ፡ እባብን እንዲቀጠቅጥ ፡ ለአዳም ፡ የሰጠውን ፡ ተስፋ ፤ ለዚህ ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ ሊያድስለትና ምንም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በኀጢአቱ ፡ ምክንያት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፊት ፡ ሊያይ ፡ ባይችል ፤ አብርሃም ፡ ብቻ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እንዲያየው ፡ ፈቅዶ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር በፍቅር ፡ ተገለጠለት ፡፡ ዘፍ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቊ ፡ ፲፬ - ፲፯ ፡፡

፲፰ ፤ አብርሃም ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ ከድንኳኑ ፡ ደጅ ፡ ተቀምጦ ፤ አሻግሮ ፡ አሻግሮ ፡ ሲመለከት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ወደሱ ፡ ሲመጡ ፡ አየ ፡፡

፲፱ ፤ እንግዳ ፡ መቀበልን ፤ ከግል ፡ ጥቅሙ ፡ በላይ ፡ አድርጎ ፡ አጥብቆ ፡ ይወድ የነበረው ፡ አብርሃም ፡ ሮጦ ፡ ሄዶ ፡ ሰገደላቸው ፤ እጅ ፡ ከነሣቸውም ፡ በኋላ ፤ አቤቱ በፊትኽ ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባሪያኽን ፡ አትለፈኝ፡፡ ውሃ ፡ እናምጣላችሁና እግራችሁን ፡ ታጥባችሁ ፡ ከጥላው ፡ ዐርፋችሁ ፡ እኽል ፡ ቀምሳችሁ ፡ ከባሪያችሁ ዘንድ ፡ ጥቂት ፡ ካረፋችሁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አሰባችሁት ፡ ትሄዳላችሁ ፡ ብሎ ፡ ቢለምናቸው ፡ እንዳልክ ፡ አድርግ ፡ አሉት ፡፡

፳ ፤ እሱም ፡ እንግዶችን ፡ ከጥላው ፡ ዐሳርፎ ፤ ወደ ፡ ቤት ፡ ተመልሶ ፡ ሚስቱን ፡ ቶሎ ፡ በይ ፡ ሦስቱን ፡ መስፈሪያ ፡ ዱቄት ፡ አቡክተሽ ፡ አንድ ፡ ዳቦ ፡ አድርገሽ ፡ ጋግሪው ፡ ብሎ ፡ አዝዟት ፡ ከብቶቹ ፡ ወደ ፡ ተሰማሩበት ፡ ሄዶ ፤ ከከብቶቹ ፡ ጥፍሩ ፡ ያልዘረዘረውን፡ ቀንዱ ፡ ያልከረከረውን ፡ ንጹሕ ፡ ወይፈን ፡ መርጦ ፡ አምጥቶ ፡ አርዶ ፡ አወራርዶ ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ያቀርብለት ፡ ዘንድ ፡ ለአሽከሩ፡ (ለወጥ ፡ ቤቱ) ፡ ሰጠው ፡፡

፳፩ ፤ ኹለቱም ፡ ታዛገሮች ፡ ሚስቱና ፡ ወጥ ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ ታዘዙ ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፤ በያይነቱ ፡ ያዘጋጀውን ፡ ምግብ ፤ አቅርቦ ፡ ሚስቱ ፡ የራቀውን ፡ ከውስጥ ፡ እያቀረበችለት ፤ እሱ ፡ ከፊታቸው ፡ ቆሞ ፡ እያሳለፈላቸው ፡ ያቀረበላቸውን ፡ በሉ ፡፡

፳፪ ፤ ከምሳም ፡ በኋላ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሰበውን ፡ ተስፋ ፡ ለመፈጸም ፤ ሚስትህ ፡ የት ፡ ናት ? ብሎ ፡ ጠየቀው ፤ አብርሃምም ፡ እነሆ ፡ ከድንካኑ ፡ ውስጥ ፡ አለች፡ ብሎ ፡ ሲመልስ ፤ እንደ ፡ ዛሬ ፡ ኹሉ ፡ ከርሞ ፤ እኔ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ቤት፡እመጣለሁ ፡፡ ሚስትህም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ታገኛለች ፡ ብሎ ፡ የምሥራች ፡ በመንገሩ ፡ አለቅነት፡በጫንቃው፡



የኾነው ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ (ክርስቶስ) ፡ ከአብርሃም ፡ ዘር ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፤ የአብርሃም ፡ አምላክ ፤ ለልጆቹ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ሦስትነቱን ፡ ሲገልጽ ፡ የአብርሃም ፡ ተስፋ ፡ ተፈጸመ ፡፡ ዘፍ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ቊ ፡ ፩—፲ ፡፡ ኢሳ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቊ ፡ ፮—፰ ፡፡

፳፫ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ በ፴፡ዓመት ፡ ኹለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሦስትነቱን ፡ ገለጠ ፡፡ አገላለጡ ፡ ግን ፤ በአብርሃም ፡ ዘመን ፡ ከተደረገው ፡ ልዩ ፡ ነው ፡፡

፳፬ ፤ በአብርሃም ፡ ዘመን ፤ ሦስቱም ፡ አካላት ፡ የተገለጹበት ፡ እግዚአብሔር ፡ በመልኩና ፡ በምሳሌው ፡ በፈጠረው ፡ በሰው ፡ አርአያ ፡ ነበረ ፡፡

፳፭ ፤ በዮርዳኖስ ፡ ግን ፡ ልዩ ፡ ምስጢር ፡ ተገለጠ ፤ ያውም ፡ ከቀደመው፡የበለጠ ፡ ልዩ ፡ ግርማና ፡ ውበት ፡ ያለው ፡ ኾነ ፡፡

፳፮ ፤ ይኸውም ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ ተጠምቆ ፡ ከውሃው ፡ ወጥቶ ፡ ሲጸልይ ፤ አብ ፡ በደመና ፡ ኾኖ ፡ በሱ ፡ ህልው ፡ ኹኜ ፡ ልመለክበት ፡ የምወደው ፡ የምወልደው ፡ የባሕርይ ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነውና ፤ እሱን ፡ ስሙት ፡ ብሎ ፡ ሲያዝዝና ፡ ሲመሰክር ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአምሳለ ፡ ርግብ ፡ ወርዶ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ሲቀመጥ ፡ በመታየቱ ፡ ነው ፡፡ ማቴ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቊ ፡ ፲፫—፲፯ ፡፡

፳፯ ፤ እዚህ ፡ ላይ ፡ የምናስታውሰው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ፡፡ ይኸውም ፡ አብ ፡ በደመና ፡ ኾኖ ፡ ሲመሰክር ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአምሳለ ፡ ርግብ ፡ ሲወርድ ፡ ሣራ ፡ ወንድ፡ ልጅ ፡ ታገኛለች ፡ በተባለው ፡ ትንቢት ፡ የአብርሃም ፡ ተስፋ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በላይ ፤ አምላክ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፤ ጥምቀትን ፡ ለመቀደስ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ተገኝቶ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅነትን ፡ ሲያስመሰክር ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ አዳም ፡ ከእኛ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ኾነ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ሲፈጸም ፡ ማየታችን ፡ ነው ፡፡

፳፰ ፤ ስለ ፡ ገጹትም ፡ ሦስትነት ፤ ነቢይ ፡ ዳዊት ፡ ፊትኽን ፡ ፈለግኹ ፤ አቤቱ ፡ ፊትኽን ፡ እሻለሁ ፡ ፊትኽን ፡ ከእኔ ፡ አትመልስ ፡ ብሏል ፡፡ መዝ ፡ ፳፯ ፡ ቊ ፡ ፰ ፡ ፱ ፡፡

፳፱ ፤ እንግዴህ ፡ መጻሕፍት ፡ በየገጹ ፡ እግዚአብሔር ፡ በባሕርዩ ፡ አንድ ፤ በአካሉ ፡ ሦስት ፡ መኾኑን ፡ ሲያስረዱ ፤ እኛ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ቃል ፡ መውጣት ፡ አይገባንምና ፤ የአብርሃምን ፡ የሙሴን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትምህርት ፡ ምስክርነት ፡ እናጽና ፡፡

ለ) ክፍል ፡ ፪ ፡፡ የስም ፡ ሦስትነት ፡፡

፴ ፤ ቀድሞ ፡ ለአብርሃም ፡ በዐጸደ ፡ መምሬ ፤ ኋላም ፡ ለዮሐንስ ፡ በዮርዳኖስ ፡ የተገለጡት ፡ ሦስት ፡ አካላት ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ናቸው ፡፡

፴፩ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከትንሣኤው ፡ በኋላ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱን፡ ሾሞ ፡ በመምህርነት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሲልካቸው ፤ ሂዱና ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ አስተምሩ ፡ ስታጠምቋቸውም ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በሉ ፡ ብሎ፡ እስኪገልጠው ፡ ድረስ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በባሕርይ ፡ ስሙ ፤ አንድ ፡ እግዚአሔር ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በመባል ፡ ብቻ ፡ ይጠራ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፤ ምንም ፡ አካላት ፡ በሦስትነት ፡ ገጽ ፡ ቢገለጡና ፡ ቢታዩ ፡ እንኳ ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማለት ፡

www.ethiopianorthodox.org

አልታወቀም ፡ አልተገለጠም ፡ ነበር ። ከሕዝብም ፡ ኾነ ፡ ከአሕዛብ ፡ ከቶ ፡ ይህንን ስም ፡ የሚጠራ ፡ አልነበረም ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳፰ ፡ ቍ ፡ ፲፱-፳ ። ዘዳግ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፬

፻፷፪ ፤ ሙሴ ፤ ሦስቱን ፡ ሰዎች ፤ እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ ተገለጠለት ፡ ማለቱ አብርሃም ፡ ሦስቱን ፡ ሰዎች ፤ አቤቱ ፡ በፊትኽ ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባሪያኽን አትለፈኝ ፡ ማለቱ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። ዘፍጥ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ቍ ፡ ፩—፮ ።

፻፷፫ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ጐልቶ ፡ አልታወቀም ፡ እንጂ ፤ ከአንድ ፡ ቦታ ፡ ሳ ሰበሰብ ፡ ተበታትኖ ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ በየአንቀጹ ፡ በየገጹ ፡ ይገኛል ።

፻፷፬ ፤ ይኸውም ፡ ሙሴ ፤ የፈጠረህ ፡ እሱ ፡ አብ፡አይደለምን ፡ ብሎ ፤ ስለ ፡ አብ ናቡከደነጾር ፤ አራተኛው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ልጅ ፡ ይመስላል ፡ ሲል ፡ ስለ ፡ ወልድ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በርብቃ ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ወረደ ፡ ሲል ፡ ስለ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የብሉይ ፡ ኪዳንን ፡ ምስክርነት ፡ ያሳስበናል ። ዘዳ ፡ ም ፡ ፴፪ ፡ ቍ ፮—፰ ። ዳን ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፳፭ ። ኩፋ ፡ ም ፡ ፲፱ ።

፻፷፭ ፤ እንደ ፡ ቀሽመሪ ፡ መታጠቂያ ፡ ጌጥ ፡ በመጽሐፍ፡ ቅዱስ ፡ አልፎ ፡ አልፎ በመገኘታቸው ፡ ለብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ጌጥ ፡ ኾነው ፡ የነበሩትን ፡ እነዚህን ፡ ስሞች ፤ ጌ ችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሂዱና ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ዳርቻ ፡ አስ ምሩ ፡ ስታጠምቋቸውም ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አጥምቋቸው ብሎ ፡ የሦስቱን ፡ ስም ፡ በአንድነት ፡ ጠርተው ፡ እንዲያጠምቁና ፡ እንዲያስተምሩ ፡ በ ዘዙ ፤ ይህን ፡ ስም ፡ እንደ ፡ አልማዝና ፡ እንደ ፡ ዕንቍ ፡ ቀለበት ፡ እንደ ፡ ሲሻን ፡ (ኒሳን) ሽልማት ፡ የሹመታቸው ፡ መታወቂያ ፡ አድርጎ ፡ በመስጠቱ ፤ ስሙና ፡ የአባቱ ፡ ስም የመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ስም ፡ ለተጻፈባቸው ፡ ለአጥማቂዎችና ፡ ለተጠማቂዎች ፡ ክርስ ያን ፤ ልዩ ፡ ሦስት ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብሎ ፡ ማመን ፡ ኾነላቸው ። ራዕ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፩ ። ሥራቸውንም ፡ የኦሪትንና ፡ የወንጌልን ፡ ቃል ፡ በማስማማት ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወ ልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ ብለው ፡ ይጀምራሉ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳፰ ቍ ፡ ፲፱ ። ዘዳ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፬ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፩ ። ግእዙን ፡ ተመልከት ።

፻፷፮ ፡ በዚህችም ፡ ሃይማኖት ፤ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክ ስቶስ ፡ ጸጋ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድነት ፡ ተገባቸው ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፲፫

ሐ) ክፍል ፡ ፫ ። የግብር ፡ ሦስትነት ።

፻፷፯ ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ለያንዳንዳቸው ፡ ልዩ ፡ የአካል ፡ ግብር አላቸው ። የአብ ፡ ግብሩ ፡ መውለድ ፡ ማስረጽ ፤ የወልድ ፡ ግብሩ ፡ መወለድ ፤ የመንፈስ ቅዱስ ፡ ግብሩ ፡ መስረጽ ፡ ነው ።

፻፷፰ ፤ ስለዚህም ፡ ክርስቲያን ፤ አብ ፡ ወላዲ ፤ ወልድ ፡ ተወላዲ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ሰራጺ ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ። ወላዲ ፡ ማለት ፡ ወላጅ ፤ ተወላዲ ፡ ማለት ፡ ተወላጅ ፤ ሰራጺ ማለት ፡ የወጣ ፡ የተገኘ ፡ ማለት ፡ ነው ።



፻፷፱ ፤ ይህም ፤ ራሱ ፡ አብ ፤ ከአጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ በፊት ፡ ማለት ፤ አጥቢያ ፡ ኮከ ሳይፈጠር ፡ ወለድሁኽ ፡ በማለቱ ። መዝ ፡ ፻፲ ፡ ፫ ። ወልድም ፤ ወንዞችን ፡ ሳይፈጥር ፤ የወ ምንጮች ፡ ተራሮች ፡ ኮረብቶች ፡ ሳይፈጠሩ ፤ ወለደኝ ፡ ከአብ ፡ ወጥቼ ፡ (ተወልጄ፡ ወ ዓለም ፡ መጣሁ ፡ በማለቱ ፤ ምሳ - ፰ ፡ ቍ ፡ ፳፭ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ቍ ፡ ፳፰ ።

፻፸ ፤ ስለ፡መንፈስ ፡ ቅዱስም ፤ ከአብ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ለእናንተ ፡ የምልክላችሁ ፡ ከአ የወጣ ፡ መንፈሰ ፡ ጽድቅ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤ እሱ ፡ ይመሰክርልኛል ፡ ብለ በማስረዳቱ ። ዮሐ ፡ ም፡፲፭፡ ቍ፡፳፮።እሱ ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ፤ የገለጠው ፡ ምስጢር ፡ ነ እንጂ ፤ ከፍጡራን ፡ ወገን ፡ መርምሮ ፡ ያገኘ ፡ ያስረዳ ፡ የለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከፍጡ ምስክርነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስክርነት ስለሚበልጥ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክር ያን ፡ ምስክርነቱን ፡ ተቀብላ ፤ እግዚአብሔር ፡ በስም ፡ በአካል ፡ በግብር ፡ ሦስት ፤ ርይ ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብላ ፡ ታምናለች ፡ ታሳምናለች ።

መ) ክፍል ፡ ፬ ። የኩነት ፡ (ኹኔታ) ፡ ሦስትነት ።

፻፸፩ ፤ ኩነታት ፤ በተከፍሎ ፡ በተፈልጦ ፡ ያለመጠቅለል ፡ ያለመቀላቀል ፡ በ ሳቸው ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ አካላትን ፤ በተዋሕዶ ፡ በተጋብኦ ፡ ( በአንድነት ) ፡ በ ውና ፡ (መኗኗር) ፡ እያገናዘቡ ፤ በአንድ ፡ መለኮት ፡ የነበሩ ፡ ያሉ ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው

፻፸፪ ፤ እነሱም ፡ ልብነት ፡ ቃልነት ፡ እስትንፋስነት ፡ ናቸው ። ልብነት ፤ በአ መሠረትነት ፤ ለራሱ ፡ ለባዊ ፡ (ዐዋቂ) ፡ ኾኖ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ልብ ፡ ዕ ቀት ፡ መኾን ፡ ነው ። ቃልነት ፤ በአብ ፡ መሠረትነት ፤ ለራሱ ፡ ነባቢ ፡ ቃል ፡ ኾና ለአብ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ንባብ ፡ ቃል ፡ መኾን ፡ ነው ። እስትንፈስነት ፡ በአብ ፡ መ ረትነት ፡ ለራሱ ፡ ሕያው ፡ ኾኖ ፤ ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ሕይወት ፡ መኾን ፡ ነው ።

፻፸፫ ፤ ስለዚህ ፤ በአብ ፡ ልብነት ፤ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ህልዋን ፡ ናቸወ ያሰቡበታል ። በወልድ ፡ ቃልነት ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ህልዋን ፡ ናቸው ፤ ይናገሩ ታል ። በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እስትንፋስነት ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ ህልዋን ፡ ናቸው ፤ ሕያዋን ኾነው ፡ ይኖሩበታል ።

፻፸፬ ፤ የኩነታትን ፡ ነገር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመጻሕፍት ፡ ሲያስረዳ ፤ የእግዚ ብሔር ፡ ቸርነቱ ፡ በምድር ፡ መላ ። በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሰማዮች ፡ ተፈጠሩ ። ሰራ ዊቶቻቸውም ፡ ኹሉ ፤ በአፉ ፡ እስትንፋስ ፡ ተከናወኑ ፡ ብሎ ፡ አስረድቷል ። መዝ ፡ ፴፫ ቍ ፡ ፭—፮ ።

ስለዚህ ፤ እግዚአብሔር ፡ በአካላት ፡ በኩነታት ፡ ሦስት ፤ በባሕርይ ፡ በህ ውና ፡ በመለኮት ፡ በመፍጠር ፡ በመግዛት ፡ በሥልጣን ፡ በመንግሥት ፡ አንድ ፡ ተብሎ ይታመናል ።

ሠ) የባሕርይ ፡ አንድነት ።

፻፸፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ በባሕርዩ ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ በአንድነት ፡ ፈጥሮ ፡ በሚ ዛበት ፡ በባሕርይ ፡ የግብር ፡ ስሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ይህንም ፡ እሱ ራሱ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክህ ፡ ነኝ ፡ ከኔ ፡ በቀር ፡ ሌሎችን ፡ አማልክት ፡ አታ

www.ethiopianorthodox.org

ልክ ፡ ብሎ ፡ ለሙሴ ፡ በመንገሩና ፡ ሙሴ ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ፡ ስማ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክህ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በማስተማሩ ፡ ተገልጧል ፡፡ ዘፀ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ ፡ ፪ - ፬ ፡፡ ዘዳግ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፬ ፡፡

ረ ) የህልውና ፡ አንድነት ፡፡

፵፮ ፤ ህልውና ፡ ማለት ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ መኖር ፡ ነው ፡፡ ይኸውም ፡ በኩነታት ፡ መገናዘብ ፡ የሚፈጸም ፡ ምስጢር ፡ ነው ፡፡

አካላትን ፡ ቅሉ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ የሚያሰኛቸው ፡ ህልውና ፡ ነው ፡፡ ህልውናቸውም ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፴፰ ፡፡ እኔ ፡ በአብ ፡ እንደ ፡ አለሁ ፡ አብም ፡ በእኔ ፡ እንደ ፡ አለ ፡ ታውቁ ፡ ትረዱ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ሥራዬ ፡ በእኔ ፡ እመኑ ፡ ብሎ ፡ ገልጾ ፡ ያስረዳው ፡ ነው ፡፡

፵፯ ፤ አብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ወልድ ፡ በአብ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ ህልዋን ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፤ በአብ ፡ ልብነት ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ህልዋን ፡ ናቸው ፡ ያውቃሉ ፡፡ በወልድ ፡ ቃልነት ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ህልዋን ፡ ናቸው ፡ ይናገራሉ ፡፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እስትንፋስነት ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ ህልዋን ፡ ናቸው ፡ ይተነፍሳሉ ፡፡

፵፰ ፤ ሐዋርያ ፡ ፊልጶስ ፤ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አብን ፡ አሳየንና ፡ ይበቃናል ፤ ማለት ፡ አንተን ፡ እንደ ፡ አየን ፡ አብን ፡ብናይ ፤ መስማቱ ፡ በማየት ፡ ይፈጸምልናል ፡ ቢለው ፤ ፊልጶስ ፤ ይህን ፡ ያኽል ፡ ዘመን ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፡ አታውቀኝምን ? እኔን ፡ ያየ ፡ አብን ፡ አየ ፡፡ ወይስ ፡ እኔ ፡ በአብ ፡ እንደ ፡ አለሁ ፡ አብም ፡ በእኔ ፡ እንደ ፡ አለ ፡ አታምንምን ? እንዴት ፡ አብን ፡ አሳየን ፡ ትላለህ ? ይህም ፡ እኔ ፡ የምነግራችሁ ፡ ቃል ፤ በእኔ ፡ ህልው ፡ ኾኖ ፡ አብ ፡ ሥራውን ፡ ይሠራል ፡ እንጂ ፤ እኔ ፡ ብቻዬን ፡ ከራሴ ፡ አንቅቼ ፡ የምናገር ፡ አይደለሁም ፡፡ ስለዚህ ፡ እኔ ፡ በአብ ፡ እንደ ፡ አለሁ ፤ አብም ፡ በእኔ ፡ እንደ ፡ አለ ፡ እመኑ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስረድቷል ፡፡ ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፡ ፲ - ፲፪ ፡፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፵፬ ፡፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፴፰ ፡፡

፵፱ ፤ ይህ ፡ የህልውና ፡ ምስጢር ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተናገረው ፡ ቃል ፡ ጸንቶ ፤ ምስክርነቱን ፡ ተቀብሎ ፡ ከማመን ፡ በቀር ፤ የፍጡር ፡ ሕሊና ፡ መርምሮ ፡ የማይደርስበት ፡ መኾኑን ፡ ማወቅ ፡ ይጠቅማል ፡፡ ዮሐ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፴፫ ፡፡

ሰ ) የመለኮት አንድነት ፡፡

የመለኮት ፡ ትርጓሜ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡፡ ከዚህም ፡ ባጭሩ ፡ እናሳያለን ፡፡

ይኸውም ፤

፩ኛ ፤ አገዛዝ ፡

፪ኛ ፤ ጌትነት ፡

፫ኛ ፤ ባሕርይ ፡

፬ኛ ፤ አምላክነት ፡

፭ኛ ፤ ክብር ፡ ነው ፡፡



፶ ፤ አገዛዝ ፡ ሲኾን ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በሓውርት ፡ መለኮቱ ፡፡ አገዛዙ ፡ በአራ
ማዕዘን ፡ ምሉ ፡ ነው ፡ ይላል ፡፡ መዝ ፡ ፻፫ ፡ ቍ ፡ ፳፪ ፡፡

፶፩ ፡ ጌትነት ፡ ሲኾን ፤ ወዘኢያስተርኢ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምፍጥረተ ፡ ዓለ
ይትዐወቅ፡በፍጥረቱ፡ለፍጥረቱ፡በሐልዮ ፤ ወበአእምሮ ፡፡ ወከመዝ ፡ ይትአመር ፡ ኀይሉ፡ወ
ለኮቱ፡ዘለዓለም ፡፡ ዓለም ፡ ከመፈጠሩ ፡ በፊት ፤ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ የማይታ
የማይመረመር፡ እግዚአብሔር ፤ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ በመመርመር ፡ ይታወቃል ፡፡ እንዲ
ከሐሊነቱ ፡ የዘለዓለም ፡ ጌትነቱ ፡ ይታወቃል ፡ ይላል ፡፡ ሮሜ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳ ፡፡

፶፪ ፤ መለኮት ፤ (ባሕርይ) ሲኾን ፤ ዑቁ ፡ ኢይኂጡክሙ ፡ በጥበበ ፡ ነገር ፡ ዘይየው
ለከንቱ ፡ በሥርዐተ ፡ ትምህርተ ፡ሰብእ ፡ ለስሒተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡፡ ወአኮ ፡ በሕገ ፡ ክ
ቶስ ፡ ዘላዕሌሁ ፡ ኀደረ ፡ ፍጹም ፡ መለኮቱ ፡ በሥጋ ፡ ሰብእ ፡፡ . . . . ፍጹም ፡ መለኮ
(ባሕርዩ) ፡ በከዊን ፡ የተዋሐደው ፡ የክርስቶስን ፡ ሕግ ፡ ያይደለ ፡ ሰውን ፡ ለማሳት ፡ ሰ
ሠራሽ ፡ ትምህርት ፡ በማስተማር ፡ ለከንቱ ፡ ነገር ፡ የሚያለዛዝቡ ፡ ሰዎች ፡ በነገር ፡
ምነት ፡ እንዳያታልሏችሁ ፡ ዕወቁ ፡ ይላል ፡፡ ቆላ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፰—፱ ፡፡

፶፫ ፤ አምላክነት ፡ ሲኾን ፤ ሞገስ ፡ ወሰላም ፡ ይብዛኅ ፡ ለክሙ ፡ በአእምሮቱ ፡ ለ
ላክነ ፡፡ ወኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ፡ ዘበኀይለ ፡ መለኮቱ ፡ ወሀበ ፡ ለነ ፡ ኵሎ ፡
ባረ ፡ ዘይወስድ ፡ ኀበ ፡ ሕይወት ፡ ወጽድቅ ፡፡ . . . . በአምላክነቱ ፡ ኀይል ፡ ወደ ፡
ቅና ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ የሚወስደውን ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የሰጠንን ፡ ጌታችን ፡
ሱስ ፡ ክርስቶስን ፤ አምላካችንን ፡ በማወቅ ፡ ሰላምና ፡ ክብር ፡ ይብዛላችሁ ፡ ይላል
፪ ፡ ጴጥ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ ፫ ፡፡

፶፬ ፤ ክብር ፡ ሲኾን ፤ ውእቱ ፡ ዘጸውዐነ ፡ ውስተ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ወውስተ ፡
ይቱ ፡ ዘቦቱ ፡ ነሐዩ ፡ ወነዐቢ ፡ ወንከብር ፡ በተስፋሁ ፡ እንተ ፡ ጸገወነ ፡ ከመ ፡ በእን
ዝንቱ ፡ ትኩኑ ፡ ሱቱፋነ ፡ ለመለኮተ ፡ ዚአሁ ፡ እንዘ ፡ ትጕይይዋ ፡ ለፍትወተ፡ሙስና
ለዝንቱ ፡ ዓለም ፡፡

፶፭ ፤ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ርኵስነት ፡ ተለይታችሁ ፤ የክብሩ ፡ ወራሾች ፡ እንድትኾ
በሰጠን ፡ ተስፋ ፤ በክብር ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ በምንኖር ፡ ገንዘብ ፤ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ወደ፡
ነት ፡ የጠራን ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ይላል ፡፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፬ ፡፡

፶፮ ፤ ከዚህ ፡ ባጭር ፡ ባሳየነው ፡ አኳኋን ፡ እግዚአብሔር ፡ በአካላት ፡ በ
ታት ፡ ሦስት ፤ በባሕርይ ፡ በህልውና ፡ በአገዛዝ ፡ በሥልጣን ፡ በመለኮት ፡ በመንግሥ
በመሰለውም ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፤ ሦስቱን ፡ አካላት ፡ አ
ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብሎ ፡ በማመን ፡ ይፈጸማል ፡፡

፶፯ ፤ ምስጢረ ፡ ሥላሴን ፤ ጠልቆ ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅ ፡ አይቻልም ፡፡ ነገር ፡
የሚቻለውን ፡ ያኽል ፡ በጥቂቱ ፡ ለመረዳት ፤ መጻሕፍት ፡ የሰጡንን ፡ ምሳሌዎች ፤
ስን ፡ ፀሓይን ፡ እሳትን ፡ እንመልከት ፡፡

፶፰ ፤ (ሀ) ነፍስ ፡ አካሏ ፡ ባሕርይዋ ፡ አንድ ፡ ነው ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሦስት ፡ ኹ
ዎች ፡ ልብነት ፡ ቃልነት ፡ እስትንፋስነት ፡ አሏት ፡፡ ልብነቷ ፤ ከሥጋዊ ፡ ልብ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በመዋሐድ ፡ ዕውቀቱን ፡ ይሰጣል ፤ ቃልን ፡ እስትንፋስን ፡ ያስገኛል ። ቃልነቷ ፤ በልብ
ነቷ ፡ መሠረትነት ፡ ሥጋዊውን ፡ አንደበት ፡ (መላስ) ፡ በመዋሐድ ፡ ይገለጣል ። የልቡ
ናንም ፡ ዐሳብ ፡ ይገልጣል ። እስትንፋስነቷ ፤ በልብነቷ ፡ መሠረትነት ፡ ከሥጋዊ ፡ እስትን
ፋስ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ ለሰው ፡ ሕይወት ፡ ይሆናል ። ለሰው ፡ ይህ ፡ የሕይወት ፡ እስትን
ፋስ ፡ ከሌለው ፡ ሬሳ ፡ ይባላል ።

፶፱ ፤ ልብ ፡ ቃል ፡ እስትንፋስ ፡ በመኾን ፡ እየተገናዘቡ ፡ በሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ልዩ
ነት ፡ የለባቸውም ። ነፍስ ፡ በአካሏ ፡ ለአንዲት ፡ ባሕርየ ፡ ሥላሴ ፤ በሦስቱ ፡ ኹኔታዎቿ፡
ለሦስቱ ፡ አካላት ፡ ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምሳሌነቷን ፡ ትሰጠናለች ።

የነፍስ ፡ የአካሏ ፡ አንድነት ፤ የኹኔታዋን ፡ ሦስትነት ፡ እንዳይጠቀልለው ፤ እንዳ
ያቀላቅለው ፤ የኹኔታዋ ፡ ሦስትነት ፡ አካሏን ፡ እንዳይከፍለው ፤ እንዳይነጥለው ፤ ሥላ
ሴም ፤ በልብነቷ ፡ አብ ፡ በቃልነቷ ፡ ወልድ ፡ በእስትንፋስነቷ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሲመ
ሰል ፤ የአንዲት ፡ ባሕርያቸው ፡ ምሳሌ ፡ አንዲት ፡ አካለ ፡ ነፍስ ፡ ናትና ፤ የሥላሴ ፡ የባሕ
ርያቸው ፡ አንድነት ፤ የአካላቸውን ፡ ሦስትነት ፡ አይጠቀልለውም ፤ አይቀላቅለውም ።
የአካላቸውም ፡ ሦስትነት ፤ የባሕርያቸውን ፡ አንድነት ፡ አይከፍለውም ፡ አይነጥለውም ።
ስለዚህም ፡ ነፍስ ፡ አንዲት ፡ ብትባል ፡ እንጂ ፤ ሦስት ፡ እንዳትባል ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስም ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፤ ሦስት ፡ አምላክ ፡ አይባልም ። ምሳ
ሌነቱን ፡ በግልጥ ፡ እንድትረዳ ፤ እግዚአብሔር ፤ ሰውን ፡ በመልኩ ፡ በምሳሌው ፡ ፈጠ
ረው ፡ ሲል ፡ ምስክርነቱን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይሰጥሀል ፡ አምነህ ፡ ተቀበለው ።
ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፮—፳፯ ።

፷ ፤ (ለ) ፀሐይ ፡ አካሉ ፡ አንድ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሦስት ፡ ኹኔታዎች ፡ አሉት ።
እነሱም ፡ ክበብ ፡ ብርሃን ፡ ሙቀት ፡ ናቸው ። ክበብ ፡ በክበብነቱ ፤ ብርሃንን ፡ ሙቀትን ፡
ያስገኛል ። ብርሃንም ፡ በክበብ ፡ መሠረትነት ፡ ከክበብ ፡ ተገኝቶ ፡ ለዓለም ፡ ያበራል ፤
የጨለማን ፡ ሥልጣን ፡ ይሽራል ። ሙቀትም ፡ በክበብ ፡ መሠረትነት ፡ ከክበብ ፡ ተገ
ኝቶ ፤ ቅዝቃዜ ፡ ያስለቅቃል ፤ ርጥቡን ፡ ያደርቃል ። በክበቡ ፡ አብ ፡ በብርሃኑ ፡ ወልድ ፡
በሙቀቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰላል ። ይህ ፡ አንድ ፡ ፀሐይ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፤ ሦስት ፡
ፀሐይ ፡ እንዳይባል ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፤
ሦስት ፡ አምላክ ፡ አይባልም ። ኢሳይያስ ፡ ሚልክያስ ፡ በመንፈስ ፡ ትንቢት ፡ ያዩትን ፡
የፀሐይን ፡ ምሳሌነት ፤ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ አባቴ ፡ ፀሐይ ፡ ነው ። እኔ ፡
ብርሃኑ ፡ ነኝ ። መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ሙቀቱ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተርጕሞታል ። ቀሌምንጦስ ፡
ተመልከት ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፷ ፡ ቍ ፡ ፳ ። ሚልክ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፪ ። ዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡
ቍ ፡ ፴፭ - ፴፯ ።

፷፩ ፤ ይህንንም ፡ የመድኀኒታችንን ፡ ቃል ፡ ተከትሎ ፡ አባ ፡ ሕርያቆስ፡ የተባለ ፡
ሊቅ ፤ አብ ፡ ፀሐይ ፡ ነው ፤ ወልድ ፡ ፀሐይ ፡ ነው ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፀሐይ ፡ ነው ፤
ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ያለ ፤ አንድ ፡ እውነተኛ ፡ ፀሐይ ፡ ነው ፡ ብሎዋል ።



፷፪ ፤ (ሐ) እሳት፡ አካሉ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ሦስት ፡ ኹኔታዎች ፡ አሉት ፤ እነሱም ፡
ነበልባል ፡ ብርሃን ፡ ዋዕይ ፡ (ሙቀት) ፡ ናቸው ። በነበልባሉ ፡ አብ ፡ በብርሃኑ ፡ ወልድ ፡
በሙቀቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰላል ። ይህ ፡ አንድ ፡ እሳት ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፤ ሦስት፡
እሳት ፡ እንዳይባል ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፤
ሦስት ፡ አምላክ ፡ አይባልም ።

፷፫ ፤ ሙሴ ፡ ኢዩኤል ፡ ሚልክያስ ፡ በመንፈስ ፡ ትንቢት፡ የተናገሩትን፡የእሳትን ፡
ምሳሌነት ፤ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባቴ ፡ እሳት ፡ ነው ፤ እኔም ፡ ብርሃኑ፡
ነኝ ። መንፈስ፡ቅዱስም፡ዋዕዩ፡ነው ፡ ብሎ ፡ ገልጦታል ። ዘፀ ፡ ም፡፫፡ቍ ፡ ፪-፯ ። ኢዩ ፡ ም ፡
፪፡ቍ፡፫ ። ዘዳ፡ም፡፬ ፡ ቍ፡፫ ። ሚልክ፡ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፪-፬ ። የሐ ፡ ሥ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፩-፭ ።

፷፬ ፤ ይህንንም ፡ አባ ፡ ሕርያቆስ ፤ አብ ፡ እሳት ፡ ነው ፤ ወልድ ፡ እሳት ፡ ነው ፤
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እሳት ፡ ነው ፡ በልዕልና ፡ ያለ ፤ አንድ ፡ የሕይወት ፡ እሳት ፡ ነው፡ብሎ ፡
አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ ተናግሮታል ። የምስጢረ ፡ ሥላሴን ፡ ነገር ፡ ከረኸርሙ ፡ በአጭሩ ፤
ከሩቁ ፡ በቅርቡ ፡ ለመረዳት ፡ የሚፈልግ ፡ በነፍስ ፡ በፀሐይ ፡ በእሳት ፡ ምሳሌነት ፡ ሕሊና
ውን ፡ ይወስን ። መለኮት ፡ ይህን ፡ ያኽላል ፡ ይህን ፡ ይመስላል ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ፤
ምሳሌም ፡ የለውም ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፵ ፡ ቍ ፡ ፲፰ ።

፷፭ ፤ ለመለኮት ፤ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ እንደ ፡ ጨረቃ ፡ የተወሰነ ፡ ክበብ ፡ የለውም ።
እንደ ፡ ሰውም ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ ከስንዝር ፡ አይደለም ። የሰውና ፡ የመላእክት ፡ አእም
ሮ ፡ መርምሮ ፡ የማይደርሰው ፡ በልዕልና ፡ የሚኖር ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ መዝ ፡
፻፲፫ ፡ ቍ ፡ ፭ - ፮ ። ፻፲፭ ፡ ቍ ፡ ፫ ።

፷፮ ፤ ለመለኮት ፤ ላይ ፡ ታች ፡ ቀኝ ፡ ግራ ፡ የለውም ፤ በዓለም ፡ ኹሉ ፡ ምሉ ፡ ነው፡
እንጂ ። መዝ ፡ ፻፫ ፡ቍ፡ ፳፪ ። ፳፬ ፡ ቍ ፡ ፩ ።ለመለኮት ፡ ለግዛቱ ፡ የተወሰነ ፡ ቦታ ፡ የለውም፤
ኹሉን፡ይገዛል ፡ እንጂ ። ለመለኮት ፡ ከላይ ፡ ጣሪር ፤ ከታች ፡ መሠረት ፡ የለውም ፤ ጣሪ
ሩም ፡ መሠረቱም ፡ እሱ ፡ ነው ፡ እንጂ ። መዝ ፡ ፻፴፱ ፡ ቍ ፡ ፯ - ፲፩ ።

፷፯ ፤ ለመለኮት ፡ ከምድር ፡ የወደቀውን ፡ ለማንሣት ፤ ወገብ ፡ ጐንበስ ፡ አንገት፡
ቀለስ ፡ ማድረግ ፡ የለበትም። ኹሉ ፡ በእጁ ፡ እንደ ፡ ዕንቍላል ፡ የተጨበጠ ፡ ነው ፡ እንጂ።
ዕብ፡ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፫ ። መዝ ፡ ፺፭ ፡ ቍ፡፬ ። መለኮት ፡ ለዐይን ፡ እንደሚመች ፡ ተወስኖ ፡ ይታይ፡
ዘንድ ፡ ከፊት ፡ ደረት ፡ ከኋላ ፡ ጀርባ ፡ አለው ፡ አይባልም ፡ የለውም ። ለእሳት ፡ ጀርባው፡
ፊቱ ፡ ቀኙ ፡ ግራው ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ እንዳይባል ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእሳት ፡ የተሸፈነ ፡
ራሱ ፡ እሳት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ በዐይን ፡ በሕሊና ፡ የተወሰነ ፡ ግምት ፡ ሊሰጠው ፡ አይቻልም ።
በባሕርዩ ፡ ኀጢአት ፡ በአምልኮቱ ፡ ሐሰት ፡ የሌለበት ፤ በሀብቱ ፡ ድኽነት ፤ በኀይሉ ፡
ደካምነት ፡ የማይገኝበት ፡ ኹሉን ፡ ፈጥሮ ፡ የሚገዛ ፤ ከኹሉ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፤ ኹሉን ፡
አሳልፎ ፡ የሚቀር ፤ ሦስቱ ፡ ስም ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ነው ። ከወልድ ፡ በቀር ፡ አብን ፡ የሚያውቅ ፤ ከአብም ፡ በቀር ፡ ወልድን ፡ የሚያ
ውቅ ፡ የለም ። ወልድ ፡ ግን ፡ ለወደደው ፡ ይገልጥለታልና ፤ ምስጢሩን ፡ በቸርነቱ ፡ ሊገ
ልጥልን ፡ ፈቃዱ ፡ ይሁን ። አሜን ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፳፪ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ዐምድ ፡ የምን ፡ ቃል ፡ ነው ? ትርጓሜውስ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፪ ፤ ነገረ ፡ ሀይማኖትን ፡ የምናጠናባቸው ፡ ክፍሎች ፡ ምን ፡ ይባላሉ ? ምክን
ቱስ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፫ ፡ ከአዕማድ ፡ መጀመሪያው ፡ ማን ፡ ይባላል ?
፬ ፡ ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ማለት ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ በአካል ፡ ሦስት ፤ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ መኾኑን ፡ ማን ፡ ይናገራል
፮ ፤ በአካላት ፡ በገጻት ፡ መጠቅለል ፡ መቀላቀል ፡ አለን ?
፯ ፤ እግዚአብሔር ፡ በአብርሃም ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፰ ፤ አብርሃም ፡ ከድንኳኑ ፡ ተቀምጦ ፡ ምን ፡ አየ ?
፱ ፤ አብርሃም ፡ ስንት ፡ ሰዎች ፡ አየ ፡ ምንስ ፡ አላቸው ?
፲ ፤ አብርሃም ፡ ለእንግዶቹ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፲፩ ፤ አብርሃም ፡ ከእንግዶቹ ፡ ምን ፡ ተስፋ ፡ አገኘ ?
፲፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ ሲገለጥ ፡ በምን ፡ መልክ ፡ ነው ?
፲፫ ፤ እግዚአብሔር ፡ በዮርዳኖስ ፡ የገለጠው ፡ ምስጢር ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፲፬ ፤ የአብርሃም ፡ የሙሴ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስክርነት ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፲፭ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከማስተማሩ ፡ በፊት ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚባለው ፡ ስም ፡ ይታወቅ ፡ ነበርን ?
፲፮ ፤ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ስለ ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምስክር ፡ ይገኛልን
፲፯ ፤ የክርስቲያን ፡ ምልክት ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፲፰ ፤ ክርስቲያን ፡ ሥራቸውን ፡ በምን ፡ ይጀምራሉ ?
፲፱ ፤ በዚህ ፡ ሀይማኖት ፡ ለክርስቲያን ፡ ምን ፡ ተገባቸው ?
፳ ፤ የግብር ፡ ሦስትነት ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፳፩ ፤ ስለ ፡ ግብር ፡ ሦስትነት ፡ ማስረጃ ፡ አለኽን ?
፳፪ ፤ የኩነት ፡ ሦስትነት ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፳፫ ፤ የኩነታትን ፡ ነገር ፡ በአጭር ፡ አስረዳ ። ማስረጃውንም ፡ ስጥ ።
፳፬ ፡ የባሕርይ ፡ ግብር ፡ ስሙ ፡ ማነው ?
፳፭ ፤ ህልውና ፡ ማለት ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፳፮ ፤ ፊልጶስ ፡ ምን ፡ ጠየቀ ? ጌታስ ፡ ምን ፡ መለሰለት ?
፳፯ ፤ የክርስቶስ ፡ መልስ ፡ ምን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነበር ?
፳፰ ፤ የህልውና ፡ ምስጢር ፡ በምርመራ ፡ ሊገኝ ፡ ይቻላልን ?
፳፱ ፤ የመለኮት ፡ ትርጓሜው ፡ ስንት ፡ ነው ?
፴ ፤ ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፡ በምን ፡ ይፈጸማል ?
፴፩ ፤ መጻሕፍት ፡ ለሦስነትነት ፡ የሰጧቸው ፡ ምሳሌዎች ፡ ማን ፡ ማን ፡ ናቸው
፴፪ ፤ የነፍስ ፡ ምሳሌነት ፡ እንዴት ፡ ነው ? ማስረጃውስ ፡ በየት ፡ ይገኛል ?



፴፫ ፤ የፀሓይ ፡ ምሳሌነት ፡ እንዴት ፡ ነው ? ማስረጃውስ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡
በየት ፡ ይገኛል ?
ስለ ፡ ፀሓይ ፡ ምሳሌነት ፡ መድኀኒታችን ፡ ምን ፡ ተናሯል ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

## ኹለተኛ ፡ ዐምድ ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ።

፩ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ ይህን ፡ ዓለም ፡ ከመፍጠሩ ፡ በፊት ፤ አንድነቱ ፡
ሦስትነቱን ፡ ሳይጠቀልለው ፤ ሦስትነቱ ፡ አንድነቱን ፡ ሳይከፍለው ፡ ሳይነጥለው ፤ በአ
ንድነት ፡ በሦስትነት ፡ ሲሠለስ ፡ ሲቀደስ ፡ ክብሩ ፡ ጌትነቱ ፡ ሳይቀነስበት ፤ ምስጋናው ፡
ሳይጐድልበት ፤ በክብር ፡ በጌትነት ፡ ነበረ ።

፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ ራሱ ፡ ለኹሉ ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ መገኛ ፡ ኹሉን ፡ አምጪ ፡
ፈጣሪ ፡ ከመኾኑ ፡ በቀር ፤ ለሱ ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ መገኛ ፡ ወይም ፡ አምጪ ፡ ፈጣሪ ፡
ስለሌለው ፤ የኹሉ ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ እሱ ፡ ነው ። በዚህም ፡ የፍጥረታት ፡ ፈጣሪ ፡
ተብሎ ፡ ይጠራል ።

፫ ፤ ለሥራውም ፤ ሰማይንና ፡ ምድርን ፤ በውስጣቸውም ፡ የሚገኙትን ፡ ኹሉ ፤
ካለመኖር ፡ ወደ ፡ መኖር ፡ በሥልጣኑ ፡ አምጥቶ ፡ መፍጠሩ ፤ በቂ ፡ ምስክር ፡ ኾነው ።
ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፩—፳፯ ።

፬ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ቀድሞ ፡ የተገኘ ፡ ሌላ ፡ ስለ ፡ ሌለና፡
ከኹሉ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ ቀዳማዊ ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከፍጡራን ፡ ወገን ፡ አንደኛ ፡
መገኛውን ፤ ኹለተኛ ፡ የተገኘበትን ፡ ዘመን ፤ ሦስተኛ ፡ የዕድሜውን ፡ ልክ ፡ መጠን ፡
ያወቀ ፡ የሚያውቅም ፡ የለም ።

፭ ፤ እሱ ፡ ብቻውን ፤ ዓለም ፡ ምድር ፡ ሰማይ ፡ ሳይፈጠሩ ፡ የነበረ ፡ ነው ። ምን
ጮች ፡ ሳይመነጩ ፤ ቀላያት ፡ ሳይገኙ ፤ አብሕርት ፡ ሳይወሰኑ ፤ ተራሮች ፡ ኮረብቶች ፡
ሳይከናወኑ ፡ የነበረ ፡ ቀዳማዊ ፡ ነው ። መዝ ፡ ፺ ፡ ቍ ፡ ፪ ።

፮ ፤ መዓልትና ፡ ሌሊት ፡ ቀንና ፡ ወራት ፡ ዘመንና ፡ ዓመት ፡ ክረምትና ፡ በጋ
ገፍና ፡ በልግ ፡ (ለቆ) ፡ ተለይተው ፡ ሳይታወቁ ፡ የነበረ ፡ ቀዳማዊ ፡ ነው ።

፯ ፤ ጨለማና ፡ ብርሃን ፡ ነፋስና ፡ ዝናም ፡ ደመናና፡ጉም ፡ መብረቅና ፡ ነጐድጓድ
ውሃና ፡ እሳት ፡ ብርድና ፡ ትኵሳት ፡ ሳይፈጠሩ ፡ የነበረ ፡ ቀዳማዊ ፡ ነው ።

፰ ፤ ማጣትና ፡ ማግኘት ፡ ድካምና ፡ ብርታት ፡ ክብርና ፡ ኀሳር ፡ ታናሽና፡ታላቅ
ግዙፍና ፡ ረቂቅ ፡ ገዥና ፡ ተገዥ ፡ አዛዥና ፡ ታዛዥ ፡ ሕይወትና ፡ ሞት ፡ ጽድቅና ፡ ኀጠ
አት ፡ ክፋትና ፡ ደግነት ፡ የሚታየውና ፡ የማይታየው ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፤ ሳይፈጠር ፡ የ
በረ ፡ ቀዳማዊ ፡ ነው ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፩—፬ ።

፱ ፤ ቀዳማዊነቱ ፤ አባት ፡ ከልጁ ፡ ታላቅ ፡ ከታናሹ ፡ አዳም ፡ ከልጆቹ ፡ ሰማይና
ምድር ፡ ከሌላው ፡ ፍጥረት ፡ እንደ ፡ አገኙት ፡ ቅድሚያ ፤ በደቂቃና ፡ በሰዓት ፡ በዕለትና
በወራት ፡ በዘመንና ፡ በዓመት ፡ በጥቂት ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ጊዜያት ፤ እነሱንም ፡ በመ

www.ethiopianorthodox.org

ስሉ ፡ መስፈሪያዎችና ፡ መለኪያዎች ፡ የተለካና ፡ የተደካ ፤ የተመጠነ ፤ የተሰፈረና ፡ የተቈጠረ ፡ አይደለም ።

፲ ፤ ከርሱ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ዛሬ ፡ ያለንበት ፡ ዓለም ፡ ከመፈጠሩ ፡ በፊት ፤ የነበረና ፡ የነበረውንም ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ፡ እንጂ ፤ የነበረ ፡ ሰው ፡ ኑሮ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ተደረገ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ተሠራ ፡ ብሎ ፡ ታሪክ ፡ የሚነግር ፡ ቢገኝ ፡ ኖሮ ፤ ፍጥረት ፡ ያለፈጣሪው ፡ ስለማይገኝ ፤ ከኹሉ ፡ በፊት ፡ ራሱ ፡ መገኘትና ፡ ሌላውንም ፡ ማስገኘት ፡ የማሉ ፡ ስለ ፡ ኾነ፡ ታሪኩ ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ይወሰናል። ስሙም ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ብሉየ ፡ መዋዕል ፡ (በዘመን ፡ ያረጀ) ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። በአስተያየትም ፤ የጸጕሩ ፡ ሽበት ፤ የነጭ ፡ ሐር ፡ መልክ ፡ የያዘ ፡ መስሎ ፡ በታላቅ ፡ ሽማግሌ ፡ መልክ ፡ ለቅዱሳኑ ፡ ስለሚታይ ፤ ያዩት ፡ ኹሉ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእሱ ፡ ጸዓዳ ፡ ከመ ፡ ፀምር ። የራስ ፡ ጠጕሩ ፤ እንደ ፡ ብዝት ፡ ግምጃ ፤ ማለት ፡ እንደ ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መስክረዋል ። ዳን ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፱ ።

፲፩ ፤ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ስምና ፡ ይህ ፡ ልዩ፡ መልክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሲሰጥ ፤ ዘመኑ ፡ የማይቈጠር ፡ መኾኑን ፡ ባጭሩ ፡ ለመረዳት ፡ ያኽል ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ ሽማግሌዎቻችን ፡ ወግ ፡ ዘመን ፡ የሚያልቅበት ፤ እርጅና ፡ የሚመጣበት ፡ ኾኖ ፡ አይደለም ።

፲፪ ፤ እግዚአብሔርንም ፡ በዘመን ፡ ያረጀ ፡ ሽማግሌ ፡ ብሎ ፡ ለመጥራትና ፡ ቅድምናውንም ፤ በሽምግልና ፡ መልክ ፡ በዐይነ ፡ ሕሊና ፡ ለመመልከት ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእግዚአብሔርነቱ ፤ ከፍጡራን ፡ ልማድ ፡ የሚወረሰውን ፡ የሽማግሎችን ፡ ወግ ፡ እንደማይጠብቅ ፡ ይወቅ ።

፲፫ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ በጥንትነቱና ፡ በቀዳማዊነቱ ፤ የማይለይና ፡ የማይነግ ፡ የማይከፈል ፡ የማይቀነስ ፡ ዕውቀት ፡ ጥበብም ፡ የባሕርዩ ፡ ነው ።

፲፬ ፤ የፍጡር ፡ ሕሊና ፡ መርምሮ ፡ በማይደርሰው ፡ በዚህ ፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ፡ ዕውቀቱ ፤ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፤ ለኹሉ ፡ መስፈሪያ ፡ መለኪያ ፡ ሚዛን ፡ የኾነውን ፡ ሰዓት ፡ ዕለት ፡ ወር ፡ ዓመት ፡ የሚገኙበትን ፡ ጊዜ ፡ የተባለውን ፡ ታላቅ ፡ መሣሪያ ፤ ለሥራው ፡ ማሰናጃ ፡ ማዘጋጃና ፡ ማደራጃ ፡ አድርጎ ፡ ፈጥሮ፤ በጊዜ ፡ መደብነት ፤ ሌላውን ፡ ፍጥረት ፡ እያከታተለ ፡ ፈጠረ ። መዝ ፡ ፻፲፱ ፡ ቍ ፡ ፻፳፮ ።

፲፭ ፤ አንደኛ፤ጊዜን፡ሰማይን፡ምድርን፡ጨለማን ፡ ውሃን ፡ ነፋስን ፡ እሳትን ፡ ብርሃንን ፡

ኹለተኛ ፤ በኹለተኛ ፡ ቀን ፡ ጠፈርን ፤

ሦስተኛ ፤ በሦስተኛ ፡ ቀን ፤ አዝርዕትን ፡ አትክልትን ፡ ዕፀዋትን ፤

አራተኛ ፤ በአራተኛ ፡ ቀን ፤ ፀሓይን ፡ ጨረቃን ፡ ከዋክብትን ፤

አምስተኛ ፤ ባምስተኛ ፡ ቀን ፤ ከባሕር ፡ በልብ ፡ የሚሳቡትን ፡ በእግር ፡ የሚሽከረከሩትን ፡ በክንፍ ፡ የሚበሩትን ፡ ወፎችን ፡ ዓሦችን፡ሌሎችንም ፡ ጥቃቅን፡ፍጥረቶች ፤

ስድስተኛ ፤ በስድስተኛው ፡ ቀን ፤ ከየብስ ፡ ማለት ፡ ከምድር ፤ አራዊትን ፡ እንስሳትን ፡ አዕዋፍን ፡ በየወገን ፡ በየወገኑ ፤ በየዐይነት ፡ በየዐይነቱ ፡ ፈጠረ ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፩ - ፳፯ ።



፲፮ ፤ ከዚህም ፡ ኹሉ ፡ በኋላ፤ ሰውን ፡ በመልኩና ፡ በምሳሌው ፡ ከምድር ፡ ፈጥ

በምድር፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ እንዲገዛ ፡ አደረገው ። በነፍስ ፡ ሕይወት ፤ በመንፈስ ፡ ቅዳ

ልጅነት ፡ አከበረው ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፰ ፡ ቍ ፡ ፭ - ፰ ።

፲፯ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሥጋው ፡ ሞት ፡ የሚስማማው ፡ በመኾኑ ፤ ከመላእክ

ጥቂት ፡ ያነሰ ፡ ኾነ ።

ሰባተኛ ፤ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ዕረፍትን ፡ ፈጠረ ። መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚ

ሔር ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ይሠራው ፡ ዘንድ ፡ ከጀመረው ፡ ሥራ ፡ ዐረፈ ፡ ይላል ። ዘ

ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፩ - ፬ ።

፲፰ ፤ ስለዚህም ፡ ሊቃውንት ፤ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ዐረ

ማለቱንና ፤ ሰውም ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ሥራውን ፡ ሠርቶ ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ እን

ርፍ ፡ ማዘዙን ፡ ተመልክተው ፤ እግዚአብሔር ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ሥራውን ፡ ሠርቶ ፡

ባተኛው ፡ ቀን ፡ ዐረፈ ፤ ፍጥረት ፡ በስድስት ፡ ቀን ፡ ተፈጽሞዋል ፤ በሰባተኛው ፡ ቀ

ምንም ፡ የተፈጠረ ፡ የለም ፡ እያሉ ፡ የሥራ ፡ መጀመሪያ ፡ ጊዜን ፤ የሥራ ፡ መጨረ

ዕረፍትን ፡ ከፍጥረት ፡ ውጭ ፡ አድርገው ፡ ይናገራሉ ። ዘፀ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ ፡ ፰ - ፲፩ ።

፲፱ ፤ እንዲያውም ፤ ከሚሲዮናውያን ፡ ማኅበር ፡ አድቤንቲስት ፡ የተባሉ

አንዱ ፡ ክፍል ፡ ማኅበር ፤ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ ሙታንን ፡ ለመርዳ

ወደ ፡ መቃብር ፡ ወርዶ ፡ የፈጸመውን ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ከሥራ ፡ ውጭ ፡ አድርገው ፤

ስቶስ ፡ እንኳ ፡ በቅዳሜ ፡ ቀን ፡ በመቃብር ፡ ዐርፎ ፡ ዋለ ፡ እያሉ ፡ የቅዳሜን ፡ ክብር ፡

ልጉ ፤ በክርስቶስ ፡ ላይ ፡ ያልታማበትን ፡ የሥራ ፡ ጕድለት ፡ ያወራሉ ።

፳ ፤ ተሳስተው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ይህ ፡ በመቃብር ፡ ተኝቶ ፡ መዋልና ፡ ማያ

ክርስቶስ ፡ ከፈጸማቸው ፡ ሥራዎቹ ፡ አንዱ ፡ የሞት ፡ ሥልጣን ፡ የተሻረበት ፤ ሃ

ሞት ፡ የጠፋበት ፡ እሱ ፡ መኾኑን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይናገራል ። መዝ ፡ ፹ ፡ ቍ ፡

፹፰ ፡ ፹ - ፯ ።

፳፩ ፤ ለመኾኑ ፤ የመቃብር ፡ ኑሮ ፤ ለክርስቶስ ፡ የዘመናዊ ፡ ዕረፍትና ፡ ምቾ

ኾኖ ፡ ከተቈጠረለት ፤ ውርደት ፡ ኾኖ ፡ የሚቈጠርበት ፡ ትንሣኤውና ፡ ዕርገቱ ፡ ይኾ

እንኳን ፡ መቀበሩ ፡ ትንሣኤውና ፡ ዕርገቱም ፡ ቢኾኑ፤ ለክርስቶስ ፡ ከሥራ ፡ ውጭ ፡

ቈጠሩለት ፡ አይደለም ።

፳፪ ፤ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ቃል ፡ ትኩር ፡ አድርጎ፡ለሚመለከተው ፤ በቀዳ

ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፤ እግዚአብሔር ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በ

መሪያ ፡ ሰዓት ፡ በፊት ፤ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ፈጠረ ፡ ብሎ ፡ የሥራ ፡ መጀመሪያ ፡

ኾኖ ፤ በጊዜ ፡ መደብነት ፡ የተከናወኑትን ፡ የፍጥረታት ፡ ተራ ፡ ሲያከታትል ፡ መና

ሰማይና ፡ ምድር ፡ ሠራዊታቸውም ፡ ኹሉ ፡ ማለት ፤ በውስጣቸው ፡ የሚገኙት ፡ ፍ

ታት ፡ ኹሉ ፡ ተፈጸሙ ፡ ተከናወኑ ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፩ ። ፪ ፡ ቍ ፡ ፩—፬ ።

፳፫ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይሠራው ፡ ዘንድ ፡ የጀመረውን ፡ ሥራ ፤ በሰባተኛው ፡

ፈጸመ ፡ በማለቱ ፤ ዕረፍት ፡ የፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ መጨረሻ ፡ አክሊል ፡ መኾኗን ፡ ስ

www.ethiopianorthodox.org

ያስረዳ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፤ ሠራና ፡ ዐረፈ ፡ በማለት ፡ መካከል ፡ ልዩ ነት ፡ አለመኖሩን ፡ ማወቅ ፡ ነው ።

፳፬ ፤ የተፈጠረውም ፡ ፍጥረት ፤ በሦስት ፡ ክፍል ፡ ቦታ ፤ በሰማይ ፡ በምድር ፡ በባሕር ፡ እንዲኖር ፡ አደረገ ።

፳፭ ፤ በፍጥረታት ፡ ጠባይ ፤ መምረርና ፡ መጣፈጥ ፡ ክፋትና ፡ ደግነት ፡ ድካምና ፡ ብርታት ፡ ይገኙበታል ።

፳፮ ፤ ይህ ፡ የፍጥረታት ፡ ጠባይ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ከሐሊነቱን ፡ ጌትነቱን ፡ የሚመረምር ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፤ የሥራውን ፡ ጣዕም ፡ በየዐይነቱ ፡ ቀምሶ ፤ መንክር ፡ ግብርከ ፡ ወነፍስየ ፡ ትጤይቆ ፡ ጥቀ ። ሥራህ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፤ ልቡናዬም ፡ ትረዳዋለች ፡ ብሎ ፡ እንዲመሰክር ፡ ያስገድደዋል ። መዝ ፡ ፻፴፱ ፡ ፲፬ ።

፳፯ ፤ በዚህም ፡ ስሙ ፤ ኹሉን ፡ ቻይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። አዲስ ፡ ጨርቅ ፤ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ጥቍር ፡ ቀለም ፡ ቢያገቡት ፡ ኹሉን ፡ እንዲቀበል ፤ የፍጡር ፡ ባሕርይ ፡ ጽድቅም ፡ ኀጢአትም ፡ ይስማማዋል ።

፳፰ ፡ ነገር ፡ ግን ፤ ለእሳት ፡ ሙቀት ፡ እንጂ ፡ ቅዝቃዜ ፤ ለውሃ ፡ ቅዝቃዜ ፡ እንጂ ፡ ሙቀት ፡ እንዳይስማማው ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ እንጂ ፡ ኀጢአት ፡ አይስማማ ውም ፤ ኀጢአት ፡ የሌለበት ፡ ንጹሕ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በመጻሕፍት ፡ ስሙ ፤ ዮሴዴቅ ፡ ይባላል ። ትርጓሜውም ፡ ንጉሠ ፡ ጽድቅ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፳፱ ፤ የፍጡራን ፡ ባሕርይ ፤ ቍጣና ፡ ጭካኔ ፡ ይስማማዋል ። እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ትዕግሥትና ፡ ርኅራኄ ፡ የግሉ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፤ ስሙ ፤ መሓሪ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። መዝ ፡ ፻፫ ፡ ቍ ፡ ፰ ።

፴ ፤ ፍጡር ፤ ሐሰት ፡ ድካም ፡ ንዴት ፡ ድኽነት ፡ ከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ፍርድ ፡ ማድ ላት ፡ ሽረት ፡ ሞት ፡ ይስማማዋል ።

፴፩ ፤ እሱ ፡ ግን ፤ በአምላክነቱ ፡ ሐሰት ፡ በኀይለኛነቱ ፡ ድካም ፡ በጌትነቱ ፡ ጕድ ለት ፡ በብልጥግናው ፡ ድኽነት ፡ በፍርዱ ፡ ማድላት ፡ በመንግሥቱ ፡ ሽረት ፡ ኀልፈት ፡ በባሕርዩ ፡ ሞት ፡ ስለሌለበት ፤ የአማልክት ፡ አምላክ ፤ አሸናፊ ፤ የጌቶች ፡ ጌታ ፤ ለድ ኾች ፡ ምግብ ፤ ለገበሬዎች ፡ ዘር ፡ ልስጥ ፡ ቢል ፡ የማይሳነው ፡ ኹሉ ፡ የሚቻለው ፡ ባለ ጠጋ ፡ እውነት ፡ ፈራጅ ፡ ሠሪ ፡ ቀጪ ፡ የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተብሎ ፡ በሰውና ፡ በመላእክት ፡ አንደበት ፡ ይመ ሰገናል ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፫ ።

፴፪ ፤ አንድነትን ፡ ከሦስትነት ፡ ሦስትነትን ፡ ከአንድነት ፡ የሚያስተባብረው ፤ ቅድስናን ፡ የተመላው ፡ ይህ ፡ ምስጋና ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የነበረ ፡ ዛሬም ፡ ያለ ፡ ወደ ፊትም ፡ ከቅዱስ ፡ ባሕርዩ ፡ ጋራ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ።

፴፫ ፤ ከአዳም ፡ ሰባተኛው ፡ ትውልድ ፡ ሄኖክ ፤ በመንፈስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመ ስጦ ፡ ዓለመ ፡ መላእክት ፡ ገብቶ ፡ ከማኅበረ ፡ መላእክት ፡ መካከል ፡ ተገኝቶ ፡ መላእክት ፤



ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ እያሉ ፡ እግዚአብሔርን ፤ በአንድነቱ ፡ በሦስት ነቱ ፡ ሲያመሰግኑ ፡ ሰምቶ ፤ የመናፍስት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፤ የማያንቀላፉ ፡ ትጉሃን ፡ መላእ ክት ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ በፊትኽ ፡ ቆመው ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጹሕ ፡ እምኀጢአት ፡ ጽኑዕ ፡ በአምልኮት ፡ ልዩ ፡ እምአማልክተ ፡ ሐሰት ፡ እኩት ፡ በአፈ ፡ መላእክት ፡ ወሰብእ ፡ ነህ ፡ እያሉ ፡ ያመሰግኑሀል ፡ ብሎ ፤ ያየውን ፡ የሰማውን ፡ መስክ ረዋል ። ሄኖክ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፴፰ ። ይህንንም ፡ የመሰለው ፡ ብዙ ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፩ - ፬ ።

፴፬ ፤ ይህ ፡ ምስጋና ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ለመኖሩ ፡ እንደ ፡ ዕውር ፡ ዐይን ፡ ጭልጭልታ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የክብሩን ፡ ጨረር ፡ አይተው ፡ ምስክር ፡ ከኾኑት ፡ ከፍ ጡራን ፡ ይልቅ ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ከአባቱ ፡ ጋራ ፡ በክብር ፡ በመንግሥት ፡ በዘ መን ፡ ቀዳማዊነት ፡ እኩል ፡ ትክክል ፡ የነበረው ፤ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ እኛን ፡ ለማ ዳን ፡ በሥጋ ፡ የተገለጠው ፡ የሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ እኔ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ልሠራው ፡ የሰጠኸኝን ፡ ሥራ ፡ ፈጽሜ ፡ አመሰገንኩኽ ፡ አሁንም ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በነበረኝ ፡ ምስጋና ፡ አመስግነኝ ፡ ሲል ፤ ባየው ፡ በሰማው ፡ ማለት ፡ እውነተኛ ፡ ምስክር ፡ ኹኖ ዋል ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ቍ ፡ ፭ ።

፴፮ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከዓለም ፡ በፊት ፤ ምስጋናውም ፡ ከዓለም ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ አንድ ፡ አምላክ ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡ ዘእንበለ ፡ ይቁም ፡ አድባር ፤ ወይትፈጠር ፡ ዓለም ፡ ወምድር ። እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፡ አንተ ፡ ክመ። ተራሮች ፡ ኮረብቶች ፡ ሰማይ ፡ ምድር ፡ ሳይፈጠሩ ፤ ከዓለም ፡ በፊት ፡ የነበርክኽ ፡ ለዘለ ዓለምም ፡ የምትኖር ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህ ፡ እያልን ፤ ከነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ ጋራ ፡ እናመስግ ነው ። መዝ ፡ ፺ ፡ ቍ ፡ ፪ ። ፺፫ ፡ ቍ ፡ ፪ ።

ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እያልን ፡ እንድናመሰግነው ፤ በቸርነቱ ፡ የበቃን ፡ ያድ ርገን ። አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ እንዴት ፡ ነበር ?

፪ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ አለውን ? የኹሉ ፡ አምጪ ፡ ፈጣሪ ፡ ማነው ? ስሙስ ፡ ማን ፡ ይባላል ?

፫ ፤ ለእግዚአብሔርነቱ ፡ ምስክር ፡ ምንድን ፡ ነው ?

፬ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መገኛ ፡ ያወቀ ፡ አለን ? የሚያውቅስ ፡ ይገኛልን ?

፭ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ቀዳማዊነት ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ዘመን ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ዓመት ፡ ተብሎ ፡ ይታወቃልን ?

፮ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ታሪክ ፡ ምን ፡ በማለት ፡ ይወሰናል ? በቀዳማዊነቱስ ፡ ማን ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ?

www.ethiopianorthodox.org

፯ ፤ እግዚአብሔር ፡ በምን ፡ መልክ ፡ ለቅዱሳን ፡ ይታይ ፡ ነበር ?
፰ ፤ ከእሑድ ፡ እስከ ፡ ቀዳሚት ፡ የተፈጠሩትን ፡ ፍጥረታት ፡ ዘርዝር ።
፱ ፤ ለፍጡራን ፡ ገዥ ፡ እንዲኾን ፡ የፈቀደለት ፡ ለማነው ?
፲ ፤ እግዚአብሔር ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ፈጠረ ?
፲፩ ፤ ሊቃውንት ፡ ስለ ፡ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ይላሉ ፤
፲፪ ፤ የእግዚአብሔር ፡ የሥራ ፡ መጀመሪያው ፡ ምንድን ፡ ነው ? የሥራ ፡ መጨረሻ ውስ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፲፫ ፤ ሚስዮኖች ፤ በሰንበት ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ መድኀኒታችን ፡ ምን ፡ ይላሉ ?
፲፬ ፤ ፍጥረት ፤ በስንት ፡ ክፍል ፡ ቦታ ፡ ይኖራል ?
፲፭ ፤ በፍጥረት ፡ ጠባይ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ይገኛል ?
፲፮ ፤ የፍጥረታት ፡ ጠባይ ፡ ለመርማሪ ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ?
፲፯ ፤ እግዚአብሔር ፡ በከሐሊነቱ ፡ ማን ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ?
፲፰ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እውነተኛነቱ ፡ ማን ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ?
፲፱ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ርኅራኄው ፡ ማን ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ?
፳ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከምስጋና ፡ የተለየበት ፡ ጊዜ ፡ አለን ?
፳፩ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ምስጋናው ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ለመኖሩ ፡ ምስክሩ ፡ ማን ፡ ነው ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

## ሦስተኛ ፡ ዐምድ ፡ ድኅረ ፡ ዓለም ።

፩ ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ በአንድነቱ ፡ በሦስትነቱ ፡ ጸንቶ ፤ በአንድነቱ ፡ መንታነት ፤ በሦስትነቱ ፡ አራትነት ፡ ሳይኖርበት ፡ የነበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ካለመኖር ፡ ወደ ፡ መኖር ፡ አምጥቶ ፡ ለመፍጠር ፡ ዐሰበ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፵ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ።

፪ ፤ ሲፈጥርም ፤ ምክር ፡ ያካፈለው ፡ ወይም ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ (ፕላን) ፡ የሰጠው ፡ የለም ። ለመፍጠር ፡ ያሰበበትንም ፡ ያወቀ ፡ የለም ። ኢሳ፡ም፡፵፡ቍ፡፲፪—፲፭።

፫ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ለመፍጠር ፤ ያሰበው ፡ ዐሳብ ፡ ሰውን ፡ በመውደድ ፡ ለሰው ፡ ክብር ፡ ለቅዱስ ፡ ስሙ ፡ መመስገኛ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ለሰው ፡ በጸጋ ፡ የሚሰጠውን ፡ ክብር ፡ ከማዘጋጀቱ ፡ ይልቅ ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ለእኛ ፡ ክብር ፡ ያዘጋጀውን ፡ እውነተኛውን ፡ ተስፋ ፡ ለመፈጸም ፡ በልጁ ፡ ተዋሕዶ ፤ ሥጋን ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ባደረገው ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተገለጠ ።

፬ ፤ ይህ ፡ ምስጢር ፡ እውነተኛ ፡ ረቂቅ ፡ ጥበብ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ዓለምና ፡ አለቆቹ ፡ ሊያውቁት ፡ አይችሉም ።

፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ በባሕርይ ፡ ጥበቡ ፡ ዓለሙን ፡ ፈጥሮ ፡ ሲገዛ ፤ ለአምላክነቱ ፡ ምስክሩ ፤ ሥራውና ፡ ራሱ ፡ ሠሪው ፡ ናቸው ።



፮ ፤ የሥራው ፡ ምስክርነት ፤ ፍጥረት ፡ በየወገኑ ፡ በያይነቱ ፡ ቦታውን ፡ ይዞ እስከ ፡ አሁን ፡ ስለ ፡ አለና ፡ ወደፊትም ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ስለሚኖር ፤ መጻ ፍት ፡ እንደ ፡ ተናገሩት ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ መርማሪው ፡ በምስክርነቱ ፡ ሊጠቀምበት ይችላል ። መዝ ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፩—፭ ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳ ። የራሱ ፡ ምስክርነት ፤ ብ ሃን ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፤ ድምፁን ፡ ከሰጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ አ ቋረጥም ። መዝ ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፯ ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፫ ።

፯ ፤ ስለዚህም ፤ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ በነቢያት ፡ አድሮ ፤ ለአባቶቻችን ፡ በብዙ ዐይነት ፡ ምሳሌ ፡ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ አነጋገር ፡ ነገራቸው ። በኋለኛውም፡ዘመን ፤ ኹሉን በፈጠረበት ፡ ለኹሉ ፡ ገዥ ፡ በኾነው ፤ በመልክ ፡ በሚመስለው ፡ በባሕርይ፡ በሚተካ ለው ፡ በኀያል ፡ ቃሉ ፡ በልጁ ፡ ለእኛ ፡ ነገረን ። ዕብ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፩—፬ ። ዘኍ ፡ ም ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፮—፰ ።

፰ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ በመንግሥት ፡ በሥልጣን ወደረኛ ፡ ኣደኛ ፡ ሳይኖረው ፤ ቍጥሩ ፡ ባልታወቀ ፡ ግምቱ ፡ ባልተወሰነ ፡ ዘመን ፡ እንደ ነበረ ፤ ወደፊትም ፡ ባለፈው ፡ ኹኔታ ፡ በማይቈጠር ፡ በማይሰፈር ፡ ዕድሜ ፡ ለዘለዓለም ይኖራል ። ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ያልፋል ፤ ይጠፋል ። እሱ ፡ ግን ፡ ኀልፈት ፡ ውላጤ ፡ ሳይ ርበት ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ።

፱ ፤ ስለ ፡ ዘለዓለማዊነቱ ፤ አንተ ፡ አስቀድሞ ፡ ምድርን ፡ መሠረትካት ። ሰማ ትም ፡ የእጆችህ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ። እነሱ ፡ ያልፋሉ ፡ ይጠፋሉ ። አንተ ፡ ግን፡አታልፍም አትለወጥም ። ኹሉ ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ያረጃል ። እንደ ፡ መጋረጃ ፡ ትለዋውጣቸዋለህ እንደ ፡ ብራና ፡ እንደ ፡ ወረቀት ፡ ትጠቀልላቸዋለህ ። አንተ ፡ ግን ፡ መቼም ፡ መች፡አንተ ነህ ። ዘመንህም ፡ (ዕድሜህም) ፡ አይፈጸምም ። መንግሥትኽ ፡ የዘለዓለም ፡ መንግሥ ናት ። ግዛትህም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ናት ። ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ለዘለዓለም ፡ አምላ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህ ። አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡ ዙፋንኽ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ መ ሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እውነተኛ ፡ ምስክርነቱን ፡ ይሰጣል ፤ ሥልጣኑ ፡ የማትነሣ ፤ መንግሥ የማታልፍ ፡ የማትለወጥ ፡ ናትና ፡ መንግሥት ፡ ሕዝብና ፡ ነገድ ፡ ልሳናትም ፡ ኹሉ ፡ ያ ሰግኑታል ። ዕብ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፰—፲፪ ። መዝ ፡ ፵፭ ፡ ቍ ፡ ፮ ። ፺ ፡ ቍ ፡ ፪ ። ፺፫ ፡ ቍ ፡ ፪ ። ፻፪ ፡ ቍ ፡ ፳፭—፳፯ ። ፻፵፭ ፡ ቍ ፡ ፲፩—፲፬ ። ዳን ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፲፫—፲፬ ።

፲ ፤ የፍጡራን ፡ ባሕርይ ፤ ኀልፈት ፡ ውላጤ ፡ የሚስማማው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ እንደ ጥላ ፡ ያልፋሉ ፤ እንደ ፡ ሣር ፡ አበባ ፡ ይረግፋሉ ።

፲፩ ፤ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ኹሉ ፡ እንደ፡ሣር ፡ ነው ። ክብሩም ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ አበባ ፍሬ ፡ ነው ። ሣሩ ፡ ይደርቃል ። አበባውም ፡ ይረግፋል ። ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ፍጥረት፡ኹ እንዲሁ ፡ ነው ። የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ ተብሎ ተጽፎዋልና ፤ የበሉ ፡ እንዳልበሉ ፤ የገዙ ፡ እንዳልገዙ ፤ ያገኙ ፡ እንዳላገኙ ፡ ይኾናሉ መዝ ፡ ፻፵፬ ፡ ቍ ፡ ፬ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፵ ፡ ቍ ፡ ፮—፱ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፱ ፡ ንጉሥ ፡ ኹሉ ፡ በሞት ፡ ይሻራል ። መኰንን ፡ ኹሉ ፡ ይሻራል ። ገዥ ፡ ኹሉ ፡ ያልፋል ። መካር፡በምክሩ ፡ ጠቢብ ፡ በጥበቡ ፡ ፈላስፋ ፡ በዕውቀቱ ፡ ፈጣን ፡ በሩጫው ፡ ኀይለኛ ፡ በጉልበቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ ሊያመልጥ ፡ አይችልም ።

፲፫ ፡ በመንግሥታቸው ፡ አንዱን ፡ ሲያከብሩ ፡ አንዱን ፡ ሲያደኸዩ ፡ የነበሩ ፡ ኀያላን ፡ ነገሥታት ፤ ስማቸውን ፡ በጕልበታቸው ፡ ያሳወቁ ፤ ጊዜ ፡ ያነሣቸው ፡ ዐባይ ፡ (አምባ) ፡ ገነኖች ፡ (ዲክታተሮች) ፡ የምድርን ፡ ፊት ፡ በብዛት ፡ ሸፍነው ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብና ፡ አሕዛብ ፡ አራዊትና ፡ እንስሳት ፡ የሰማይ ፡ ወፎችና ፡ የባሕር ፡ ዓሣዎች ፡ በራሪና ፡ ተሽከርካሪ ፡ ተሳዋሽና ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ኹሉም ፡ እንዳልነበሩ ፡ ይኾናሉ ። ኹሉም፡ከሞት፡ እጅ ፡ በታች ፡ ይገዛሉ ። በሥልጣኑም ፡ ይያዛሉ ።

፲፬ ፡ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፤ በቅን ፡ ታዛዥነቱ ፡ በትክክል ፡ ዳኝነቱ ፡ ኹሉን ፡ ለእግዚአብሔር፡ሲያስገዛ፡የኖረው ፡ የኋለኛው፡ ጠላት፡ሞት ፡ ይሻራል ፡ ያልፋል ። መዝ ፡ ፻፫ ፡ ቍ ፡ ፯—፲፰ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፵ ፡ ቍ ፡ ፲፭-፲፰ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፲፭ ፡ ቍ ፡ ፳፬-፳፯ ።

፲፭ ፡ ከሱም ፡ በኋላ ፡ ሰማይ ፡ ምድር ፡ ያልፋሉ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳፬ ፡ ቍ ፡ ፴፭ ።

ከፍጥረቱ ፡ በላይ ፡ የኾነ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፤ ኹሉን፡አሳልፎ ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ጠቀስነው ፤ ከዓለም ፡ በፊት ፡ በነበረበት ፡ ኹኔታ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ። ዘመኑም ፡ ይህን ፡ ያኽላል ፡ ሊባልና ፡ ሊወሰን ፡ አይቻልም ።

፲፮ ፡ ለጥንትነቱ ፡ ጥንት ፡ የሌለው ፡ በመኾኑ ፤ የጥንትነቱ ፡ ታሪክ ፡ ነበረ ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ እንዲወሰን ፤ ለፍጻሜነቱም ፡ ፍጻሜ ፡ የሌለው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ የፍጻሜነቱ ፡ ታሪክ ፡ ዘለዓለም ፡ ይኖራል ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ይወሰናል ፡ እንጂ ፤ ሕሊና ፡ መርምሮ ፡ አይደርስበትም ። መዝ ፡ ፻፬ ፡ ቍ ፡ ፮ ። ፺፫ ፡ ቍ ፡ ፪ ።

፲፯ ፡ ስለዚህ ፡ ስሙ ፡ አልፋ ፡ ወኦ ፡ ቀዳማዊ ፡ ደኃራዊ ፡ ፊተኛ ፡ ኋለኛ ፡ መጀመሪያ ፡ መጨረሻ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ራዕ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ። ፪ ፡ ፰ ። ፳፪ ፡ ፲፫ ።

፲፰ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ያንድነቱን ፡ የሦስትነቱን ፡ የጥንትነቱን ፡ የፍጻሜነቱን፡ ነገር ፤ ለማወቅ ፡ የፈለጉ ፡ አባቶቻችን ፡ ዕውቀቲቱ ፡ ስለ ፡ ጸናችባቸውና ፡ ስለ ፡ በረታችባቸው ፤ ከሱዋ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ መኖር ፡ እሱዋንም ፡ መመርመር ፡ ስለ ፡ ተሳናቸው ፤ እምትካት ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፡ አንተ ፡ ክመ ። ጥንት ፡ የነበርክ ፡ ለዘለዓለም ፡ የምትኖር ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህ ፡ በማለት ፡ ቃላቸውን ፡ ወስነዋል ፤ ዐሳባቸውን ፡ ዘግተዋል ። እኛም ፡ ከአባቶቻችን ፡ አንሻልምና ፤ በሰው ፡ ልብ ፡ ያለውን ፡ ከተዋሐደችው ፡ ነፍሱ ፡ በቀር ፡ የሚያውቅ ፡ እንደሌለ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ራሱን ፡ ራሱ ፡ ይመረምራል ፡ እንጂ ፤ ፍጡር ፡ ሊመረምረው ፡ የማይችል ፡ መኾኑን ፡ ዐውቀን፤አንድነቱን ፡ ሦስትነቱን ፡ ጥንትነቱንና ፡ ዘለዓለማዊነቱን ፡ በአፍም፡በልብም ፡ አምነን ፤ ልዩ ፡ ሦስት ፡ አንድ ፡ አምላክ፡ አብ ፡ ወልድ፡ መንፈስ፡ቅዱስ ፡ ሆይ ፤ ዛሬም፡ዘወትርም፡ለዘለዓለም፡ክብር፡ምስጋና ፡ የአምልኮት፡ስግደት፡ ለአንተ፡ይኹን ፡ እያልን ፡ እናመስግነው ። ፩ ፡ ነገ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፬ ። ፩ ፡ ቆሮ፡ም፡፪፡ቍ ፡ ፲፩ ።

ከአብ ፡ ተመሥርታ ፤ ከወልድ ፡ የምታደርሰውን ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የምትፈጸመውን ፡ የተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ፈጣሪያችን ፡ በቸርነቱ ፡ ይግለጥልን ። አሜን ።



አልቦ ፡ ዘዐርገ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘወረደ ፡ እምሰማይ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ዘውእቱ ፡ ይነብር ፡ በየማነ ፡ እግዚአብሔር ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ ዐሰበ ።

፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ ዓለምን ፡ ሲፈጥር ፡ አማካሪ ፤ ወይስ ፡ ፕላን ፡ ያሳየው ፡ አለን ?

፫ ፤ እግዚአብሔር ፡ ዓለምን ፡ ፈጥሮ ፡ ለመግዛቱ ፡ ምስክሩ ፡ ማነው ?

፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለአባቶቻችን ፡ በማን ፡ ተናገረ ? ለእኛስ ፡—በማን ፡ ነገረን ?

፭ ፤ ፍጥረት ፡ ዘለዓለም ፡ ይኖራልን ? እግዚአብሔርሳ ?

፮ ፤ ስለ ፡ ዘለዓለማዊነቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ምን ፡ ይላል ?

፯ ፤ የሰው ፡ ምሳሌው ፡ ምንድን ፡ ነው ?

፰ ፤ እግዚአብሔር ፡ ጥንት ፡ ፍጻሜ ፡ በመኾኑ ፡ ማን ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

### አራተኛ ፡ ዐምድ ፡ ምስጢረ ፡ ሥጋዌ ፡ (ሰው ፡ የመኾን ፡ ምስጢር) ።

፩ ፤ ምስጢረ ፡ ሥጋዌ ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ አምላክ፡ብለን፡ ከምናምንባቸው ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፡ ብለን ፡ የአምላክን ፡ ሰው ፡ መኾን ፤ የሰውን ፡ አምላክ ፡ መኾን ፡ የምናምን በት ፡ የምናሳምንበት ፡ ነው ።

፪ ፤ አዳም ፤ የፈጣሪውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመተላለፉ ፤ ሞት ፡ ያልተፈጠረበትን ፡ ሲያ ውቅ ፡ ሞትን ፡ በፈቃዱ ፡ ስቦ ፡ ጐትቶ ፡ በማምጣቱ ፤ ሞት ፡ እንዲፈረድበት ፡ ኾነ ።

፫ ፤ ቸርነት ፡ የባሕርዩ ፡ የኾነው ፡ አምላካችን ፤ አዳም ፡ ከክብሩ ፡ ተዋርዶ ፡ ከል ብሱ ፡ ተራቁቶ ፡ ከቆመበት ፡ ወድቆ ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፤ አባት ፡ ለልጁ ፡ እንደሚራራ ፤ አዘ ነለት ፡ ራራለት ።

፬ ፤ አዳም ፤ በሚስቱ ፡ አማካይነት ፤ ከእባብ ፡ የተቀበለውን ፡ ምክር ፡ ሲፈጽም ፤ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊኾንና ፡ ክፉንና ፡ መልካምን ፡ ሊያውቅ ፡ ነበር ።

፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መኾን ፡ ብቻ ፡ ቀረበት ፡ እንጂ ፤ ክፉ ንና ፡ መልካምን ፡ ለማወቅ ፡ ቻለ ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቊ ፡ ፲፯ ። ኩፋሌ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቊ ፡ ፮ ።

፮ ፤ አዳምና ፡ ሚስቱ ፤ ክፉና ፡ መልካም ፡ ከምታስታውቀው ፡ ዕንጨት ፡ ፍሬ ፡ ቈርጠው ፡ በበሉ ፡ ጊዜ ፤ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ራቁታቸውን ፡ ሲኖሩ ፡ አይተፋፈሩ ፡ የነበረ ፤ ዐይኖቻቸው ፡ ተከፈተውላቸው ፡ በፊት ፡ መልበሳቸውን ፤ ዛሬ ፡ መራቆታቸውን ፡ ያለ ፈውን ፡ ክብር ፡ የመጣውን ፡ ኀሳር ፡ ያለፈውን ፡ ጌትነት ፡ የመጣውን ፡ ባርነት ፡ ያለፈ ውን ፡ ጤናና ፡ ሰላም ፡ የመጣውን ፡ ሕማምና ፡ ድካም ፡ ያለፈውን፡ሕይወት ፡ የመጣውን ፡ ሞት፡በጠቅላላው ፡ ክፉንና ፡ መልካምን ፡ ለይተው፡ዐወቁ ፡ ተጨነቁ ። ዘፍ፡ም፡፪፡ቊ፡፳፭ ።

፯ ፤ በራሪውን ፡ ተሽከርካሪውን ፡ አራዊትን ፡ እንስሳትን ፡ አዕዋፍን ፡ ዓሣትን ፡ በምድር ፡ በባሕር ፡ ያለውን ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ሊገዙ ፡ በተሾሙበት ፡ ቀን ፤ ለልጅነት ፡ ለጌትነት ፡ ሊኾናቸው ፡ የተሰጣቸውን ፡ የክብርና ፡ የሞገስ ፡ የጸጋና ፡ የሰላም ፡ ልብስ ፡ አወለቁ ። ለአገልጋይነት ፡ የሚገባውን ፡ ሌላ ፡ ጨርቅ ፡ ቢያጡ ፡ የበለስ ፡ ቅጠል ፡ ቈር



ጠው ፡ ሰፍተው ፡ ሽርጥ ፡ (ግልድም) ፡ አድርገው ፡ ታጠቁ ። አዳም ፡ የፈጣሪውን ፡ ፊት፡ ማየት ፡ ስለ ፡ አፈረ ፤ ከገነት ፡ ዛፎች ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ ተሰወረ ። በዚያ ፡ ቀን ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ኀፍረትና ፡ ኀሳር ፤ ተመሳሳይ ፡ ስለሌለው ፤ እንዲህ ፡ ነበር፡ሊባል ፡ አይቻልም ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቊ ፡ ፰—፲፩ ።

፰ ፤ አዳም ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መኾን ፡ ቢቀርበት ፤ እሱ ፡ እግዚአብሔርን፡ እንዳያይ ፡ ከመፍራቱ ፡ ይልቅ ፤ እግዚአብሔር ፡ እሱን ፡ እንዳያየው ፡ ከዛፎች ፡ መካከል፡ በመደበቁ ፡ ኹለተኛ ፡ ተሳሳተ ።

፱ ፤ እግዚአብሔር ፡ አዳምን ፡ እየፈለገ ፡ መጣ ፤ ባኖረበት ፡ ቦታ ፡ ባላገኘውም ፡ ጊዜ ፤ አዳም ፡ ወደ ፡ የት ፡ አለኽ ፡ ብሎ ፡ በከፍታ ፡ ድምፅ ፡ ጠርቶ ፡ ጠየቀው ።

፲ ፤ አዳምም ፤ በገነት ፡ ስትመላለስ ፡ የእግርኽን ፡ ዳና ፡ ( ነጐዳ ) ፡ ሰምቼ ፡ ራቁ ቴን ፡ ነኝና ፡ ስለ ፡ ፈራሁ ፤ ከዚህ ፡ ተሰውሬያለሁ ፡ አለው ።

፲፩ ፤ ኹለተኛም ፤ ምናልባት ፡ አትብላ ፡ ያልኩኽን ፡ በልተኽ ፡ ይኾን ? ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዳምን ፡ ጠየቀው ። አዳምም ፤ ትርዳኽ ፡ ብለኽ ፡ የሰጠኸኝ ፡ ሴት ፡ ሰጠችኝና ፡ በላኹ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

፲፪ ፤ ሦስተኛም ፤ አንቺሳ ፡ ይህን፡ለምን፡ሠራሽ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሔዋንን ፡ ጠየቃት ። ሴቲቱም ፡ እባብ ፡ አሳተችኝ ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቊ ፡ ፰-፲፫ ።

፲፫ ፤ በእነዚህ ፡ ሦስት ፡ ጥያቄዎችና ፡ መልሶች ፤ እግዚአብሔር ፤ እሱ ፡ የማያው ቀውን ፡ ነገር ፡ ከአዳም ፡ ጠይቆ ፡ የሚረዳ ፤ አዳምም ፤ እግዚአብሔር ፡ የሱን ፡ ሥራ፡ የማ ያውቅ ፡ ኾኖ ፡ ሥራውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚያስረዳ ፡ የሚያስመስል ፡ አስተያየት ፡ አለባቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ አዳም ፤ እግዚአብሔር ፡ ላቀረበለት ፡ ጥያቄ ፤ አቤቱ ፡ አንተ ፡ ኹሉን ፡ ታውቃለህ ፡ እኔ ፡ ለአንተ ፡ ምን ፡ አስረዳሀለሁ ፡ ብሎ ፡ ሊመልስለት፡ይገባው ፡ ነበር ። ኾኖም ፡ አዳም ፤ ከገናናው ፡ ባለሥልጣን ፡ ለቀረበለት ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ እንዲ ሰጥ ፡ ሲገደድ ፤ የዳኝነትን ፡ መልክ ፡ ከማወቁ ፡ ይልቅ ፤ በሥራው ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ሊኾን ፡ አለመቻሉን ፡ ሲያውቅ ፤ ኹሉን ፡ ቻይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ፡ አዳ ምን ፡ ሊኾን ፡ የሚችል ፡ መኾኑን ፡ በማስረዳታቸው ፤ የጥያቄዎቹ ፡ ቃላት ፡ ለሰው ፡ ልቡና ፡ የተስፋ ፡ ሥንቅ ፡ ኾነውታል ።

፲፬ ፤ «አዳም ፡ ወዴት ፡ አለኽ ። ምናልባት ፡ አትብላ ፡ ያልኩኽን፡ በላኽን»፡የሚ ሉት ፡ ቃላተ ፡ ጥያቄ ፤ አዳም ፡ አንተ ፡ ኹሉን ፡ ቻይ ፡ ንጹሐ ፡ ባሕርይ ፡ እኔን ፡ መኾን ፡ አትችልም ፡ እንጂ ፤ ሠሪ ፡ ከሠራው ፡ ቤት ፡ ሊገባ ፡ ችሎታ ፡ እንደ ፡ አለው ፤ እንዲሁ ፡ እኔም ፡ አንተን ፡ መኾን ፡ እችላለሁ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ያሉ ፡ በመኾናቸው ፤ አምላክ ፡ ሰው ፡ ለመኾኑ ፡ የትንቢት ፡ በር ፡ ከፋች ፡ ኾነዋል ።

፲፭ ፤ ከዚህም ፡ አያይዞ ፤ ስለ ፡ እባብና ፡ ስለ ፡ ሔዋን፡ልጅ ፡ ኗሪ ፡ ክርክር ፤ እባብ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ሰኰና ፡ እንድትጠብቅ ፤ የሔዋንም ፡ ልጅ ፡ የእባብን ፡ ራስ ፡ እንዲቀጠ ቅጥ ፡ በማዘዙ ፤ አዳምን ፡ የፈለገ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥጋ፡በኾነ ፡ ጊዜ ፤ ያለ፡አባት ፡ ከሴት ፡ ብቻ ፡ ተወልዶ ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ በጠላትነት ፡ የኖረውን ፤ በኋላም ፡

www.ethiopianorthodox.org

አንደኛ ፡ በዘመነ ፡ ሄሮድስ ፡ ኹለተኛ ፡ በገዳመ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ሦስተኛ ፡ በዐውደ ፡ ጲላጦስ ፡ የተፈታተነውን ፡ ዲያብሎስን ፤ በሰውነቱ ፡ በተቀበለው ፡ መከራ ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ አዳምን ፡ ከነልጆቹ ፡ እንዲያድን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጽኑውን ፡ ኪዳን ፡ መሠረተ ።

፲፮ ፡ አዳም ፡ ከገነት ፡ ሲወጣ ፤ አዳም ፡ ከእኛ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ኾነ ፡ በማለቱ ፤ በቃላቱ ፡ ጥያቄዎች ፡ አምላክ ፡ ሰው ፡ መኾኑን ፡ እንደ ፡ ሰበከ ፤ ከእኛ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ኾነ ፡ ባለውም ፡ ሰው ፡ አምላክ ፡ መኾኑን ፡ ተናገረ ።

፲፯ ፡ ከዚህ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለአዳም ፡ የሰጠው ፡ ተስፋ ፡ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ አነጋገር ፡ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ ምሳሌ ፡ በነቢያት ፡ አፍ ፡ ለአባቶቻችን ፡ ሲነግራቸው ፡ ኖሮ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ አዳም ፡ ወደ ፡ የት ፡ አለኽ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾኖ ፤ አዳም ፡ ከኛ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ኾነ፡ያለውን ፡ ፈጸመ ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፱ና ፡ ፳፪ ።

፲፰ ፡ አዳም ፡ በስድስተኛው ፡ ቀን ፡ ተፈጥሮ ፡ የእግዚአብሔርን፡ትእዛዝ ፡ ሊጠብቅ ፡ በገነት ፡ ከተሾመ ፡ በኋላ ፤ ክፉና ፡ መልካም ፡ ከምታስታውቀው ፡ ዕንጨት ፡ ፍሬ፡ አትብላ ፤ ብትበላ ፡ ግን ፡ በዚያው ፡ በበላኽበት ፡ ቀን ፡ ትሞታለህ ፡ ሲል ፡ እግዚአብሔር፡ እንደ ፡ ነገረው ፡ ባለመጠበቁ ፤ ተስፋ ፡ ሞት ፡ ተፈጸመበት ። ማለት ፤ ሺሕ፡ዘመን ፡ ሳይሞላ ፤ በዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜው ፡ የሞትን ፡ ጽዋ ፡ ተቀበለና፡ወደ ፡ መሬትነቱ ፡ ተመለሰ ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲—፲፯ ። ፫ ፡ ቍ ፡ ፲፯—፲፱ ።

፲፱ ፡ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ለኀጢአት ፡ ለሞት ፡ ተገዛ ። በአዳም ፡ ኀጢአት ፡ ምክንያት ፤ የዓለም ፡ ጕዳና ፡ ኹሉ ፡ ወጣ ፡ ገብ ፡ ስለ ፡ ኾነ፤ ማለት ፡ ጽኑት ፡ ክፉት ፡ ከሰው ፡ ልቡና ፡ የማይለይ ፡ ስለ፡ኾነ ፤ ኦሪትም፡እንኳ፡ብትኾን ፡ ኀጢአትን ፡ አነገሠቻት ፡ እንጂ ፤ ልትሽራት ፡ አልተቻለም ። ሮሜ ፡ ም፡፭ ፡ ቍ ፡ ፲፩-፳ ።

፳ ፡ ነገር ፡ ግን ፤ ኀጢአትን ፡ የሚሽር ፡ ሌላ ፡ እንዲመጣ ፡ በተስፋ ፡ ይጠበቅ ፡ ነበር ። ከኀጢአት ፡ ቀንበር ፡ በታች ፡ ሲጨነቁና ፡ ሲማረሩ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፤ በመልክተኛና ፡ በአማላጅ ፡ ሳይኾን፡እሱ ፡ ራሱ፡ሰው ፡ ኾኖ ፡ እንዲያድናቸው ፡ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ፡ ተናገረ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ቍ ፡ ፳ ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ ፡ ፫ ። ዕብ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፬-፲፮ ።

፳፩ ፡ ትንቢቱንም ፡ ለሚጠራጠሩ ፡ ሰዎች ፤ እናንት ፡ የዳዊት ፡ ወገኖች ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምታሳዝኑት ፡ እንኳን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሰውን ፡ ማሳዘን ፡ ቀላል ፡ ነገር፡ ኾኖ ፡ ነውን ? እነሆ ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ ምልክት ፡ ይሰጣችኋል ። እነሆ ፡ ድንግል ፡ በድንግልና ፡ ፀንሳ ፡ በድንግልና ፡ ትወልዳለች ። ስሙንም ፡ አማኑኤል ፡ ትለዋለች ፡ ብሎ ፤ ስሙን ፡ ከነግብሩ ፡ አስረዳቸው ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ።

፳፪ ፤ የአዳምን ፡ የመድኀኒት ፡ ተስፋ ፡ ለሚጠባበቁ ፡ ሰዎች ፤ ሺሕ፡ዘመን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ኾኖ ፡ እንደ ፡ መቈጠሩ ፡ መጠን ፤ ከዕለተ ፡ ፍጥረት ፡ እሑድ ፡ አዳም ፡ እስከ ፡ ተፈጠረባት ፡ ዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ድረስ ፡ በነበሩት ፡ በስድስቱ ፡ ዕለታት ፡ ምሳሌነት ፤ ድኅነቱ ፡ በስድስተኛው ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ዓለም ፡ እንዲደረግለት ፡



የእግዚአብሔርን ፡ ቍርጥ ፡ ዐሳብ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፤ ሱባኤ ፡ ትውልድ ፡ በሄኖክ ፡ ሱባኤ ፡ ዕለት ፡ በኤርምያስ ፡ ሱባኤ ፡ ዓመት ፡ በዳንኤል ፡ ተቈጠረላቸው ፡ ተወሰነላቸው ።

፳፫ ፤ ቀን ፡ ቢደርስ ፡ አምባ ፡ ይፈርስ ፡ እንዲሉ ፤ ቀኑ ፡ ዘመኑ ፡ ዕለቱ ፡ ሰዓቱ ፡ ሲደርስ ፤ ከዓመቱ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፤ ከዕለቱ ፡ አንድ ፡ ዕለት ፤ ከሰዓቱ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሳይጐድል ፤ በጽኑ ፡ ቀጠሮው ፡ በእሱ ፡ ያመነው ፡ ኹሉ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ እንዲያገኝ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቀዳሚና ፡ ተከታይ ፡ የሌለው ፡ አንድ ፡ ልጁን ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ላከው ። ገላ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፬ ።

፳፬ ፤ ዐምስት ፡ ቀን ፡ ተኩል ፡ ማለት ፤ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ፡ዘመን ፡ ሲፈጸም ፤ ከልጅ ፡ ልጅኽ ፡ ተወልጄ ፡ አድንሀለኹ ፡ ብሎ ፡ ለአዳም ፤ ከርሞ ፡ እንደ፡ዛሬ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እመለሳለሁ ፡ ብሎ ፡ ለአብርሃም ፡ መጀመሪያ ፡ በሰው ፤ በኹለተኛው፡ግን፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ ሰው ፡ ኾኜ ፡ ሥጋ ፡ ለብሼ ፡ ዓለምን ፡ እጐበኛለሁ ፡ ብሎ ፡ ለዕዝራ፡የተናገረ፡ ወልድ ፡ ዋሕድም ፤ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ከአብ ፡ ያለ ፡ እናት ፡ እንደ፡ተወለደ ፤ ድኅረ፡ዓለም፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ በቃልነቱ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ያለ ፡ አባት ፡ ከሴት ፡ ብቻ ፡ ተወለደ ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ቍ ፡ ፲ ።

፳፭ ፤ ይህችውም ፤ ኢሳይያስና ፡ ሕዝቅኤል ፡ የመሰከሩላት ፡ የዘወትር፡ድንግል ፡ ማርያም ፡ ናት ። ሕዝ ፡ ም ፡ ፵፬ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

፳፮ ፤ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፤ በእኛም ፡ አደረ ፤ የባሕርይ ፡ ክብሩን ፡ በጸጋ ፡ ለሰው ፡ የሚሰጥ ፡ የተናገረውን ፡ የማይለውጥ ፡ እሱ ፡ ለአባቱ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፤ ከአብ ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ ትክክል ፡ የኾነ ፡ ክብሩን ፡ አየንለት ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፲፬-፲፮ ።

፳፯ ፤ ሕፃን ፡ ተወልደ ፡ ለነ ፤ ወልድ ፡ ተውህበ ፡ ለነ ፤ ወቅድመት ፡ ኮነ ፡ ዲበ ፡ መትከፍቱ ። ሕፃን ፡ ተወለደልን ፡ ወልድ ፡ ለኩነተ ፡ ሥጋ ፡ ተሰጠልን ። ስለዚህም ፡ አምላክ ፡ ሰው ፡ ሰው ፡ አምላክ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ቀዳማዊ ፡ ቃል ፡ ደኃራዊ፡ሥጋን ፤ ደኃራዊ ፡ ሥጋ ፡ ቀዳማዊ ፡ ቃልን ፡ በመዋሐዱ ፤ ሥጋ ፡ ጥንትነትን ፡ ጥንታዊ ፡ ልደትን፡ገንዘብ ፡ አደረገ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፮ና ፡ ፯ ።

፳፰ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተ ፡ ልጄ ፡ ነህ ። እኔ ፡ ዛሬ፡ ወለድኩኽ ፡ ሲል ፡ መሰከረለት ። መዝ ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፯ ። ዕብ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፭ ።

፳፱ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፤ በሥጋና ፡ በቃል ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ ልዩነት ፡ ቀረ ። አንድነት ፡ ጸና ። መንታነት ፡ ጠፋ ። ቃል ፡ ወይም ፡ ሥጋ ፡ ተብሎ ፡ በልዩነት ፡ መጠራት ፡ ቀርቶ ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ስሙ ፡ አማኑኤል ፡ ተባለ ። ትርጓሜውም ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ አምላክ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፴ ፤ አንድነት ፤ መንታነትን ፡ ስለ ፡ አጠፋውና ፤ የቃል ፡ ገንዘብ ፡ ለሥጋ ፡ የሥጋ ፡ ገንዘብ ፡ ለቃል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፤ ኹለት ፡ ግብር ፡ ( ሥራ ) ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ መኾኑ ፡ ቀርቶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ግብር ፡ አንድ ፡ ፈቃድ ፡ ኾነ ። ስለዚህ ፡ ስሙ

www.ethiopianorthodox.org

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተባለ ። ትርጓሜውም ፡ አዳኝ ፡ ጌታ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፴፩ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ፡ ፵፪ ።

፴፩ ፤ አማኑኤል ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተባሉት ፡ ስሞች ፤ ለቃል ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ ለሥጋ ፡ ብቻ ፡ የሚሰጡ ፡ ስሞች ፡ አይደሉም ። ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሲኾን ፤ ከኹለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፤ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በመኾኑ ፤ በተዋሕዶ ፡ የሚጠራባቸው ፡ ስሞች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ።

፴፪ ፤ በዚህ ፡ መሠረት ፤ ለመድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ ኹለት ፡ ልደት ፡ እንደ ፡ አለው ፡ እናምናለን ። አንደኛው ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፤ ጊዜው ፡ ሰዓቱ ፡ ቀኑ ፡ ወሩ ፡ ዘመኑ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ በማይባል ፡ ዕድሜ ፤ ከጥንት ፡ ከዘለዓለም ፡ በማይመረመር ፡ ምስጢር ፤ ያለ ፡ እናት ፡ ከአብ ፡ የተወለደው ፡ ልደት ፡ ነው ። መዝ ፡ ፻፲ ፡ ቍ ፡ ፫ ። ሚክ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፪ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ።

፴፫ ፤ ኹለተኛው ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፤ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ያላባት ፡ የተወለደው ፡ ልደት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በምስጢረ ፡ ሥጋዌ ፤ ወልደ ፡ አብ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፤ ቃል ፡ ለተዋሐደው ፡ ሥጋ ፡ ራሱ ፡ ክብር ፡ ሆነው ፡ ብለን ፡ እናምናለን ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፯ ። ቍ ፡ ፩—፲ ። ገላ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፬ ።

፴፬ ፤ አምላካችን ፡ ክርስቶስ ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ግብር ፡ አንድ ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናምናለን ፤ እንታመናለን ፤ እናስተምራለን ፤ ዝርዝር ፡ ነገራቸውንም ፡ በየተራው ፡ እንመልከት ።

፴፭ ፤ ፩ኛ ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ።

አምላካችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ከመኾኑ ፡ አስቀድሞ ፤ የመለኮት ፡ አካልና ፡ ባሕርይ ፤ የሰው ፡ አካልና ፡ ባሕርይ ፡ ልዩነት ፡ ነበረባቸው ።

፴፮ ፡ ስለዚህም ፤ አምላክ ፡ ለብቻው ፡ ወልድ ፡ ቃል ፤ ሥጋም ፡ ለብቻው ፡ ሰው ፡ ሥጋ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራ ፡ ነበር ። በአኗኗርም ፡ ቃል ፡ ወልድ ፡ ቀዳማዊ ፡ ሥጋ ፡ ደኃራዊ ፡ ነው ።

፴፯ ፡ ስለዚህ ፡ ቀዳማዊ ፡ ቃል ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ በኀያል ፡ ቃልነቱ ፡ ኹሉን ፡ ካለመኖር ፡ ወደ ፡ መኖር ፡ አምጥቶ ፡ እንደ ፡ ፈጠረ ፤ የማይመረመር ፡ ጥንታዊ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ በመልካችን ፡ በምሳሌያችን ፡ ሰውን ፡ እንፍጠር ፡ ብሎ ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ ፈጠረው ፡ አስፋፍቶ ፡ በመግለጽ ፤ የቃልን ፡ ቀዳማዊነት ፡ የሥጋን ፡ ደኃራዊነት ፡ የቃልን ፡ አምላክነት ፡ የሥጋን ፡ ፍጡርነት ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ለይቶ ፡ ጠንቅቆ ፡ ያስረዳናል ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፮ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፩—፬ ።

፴፰ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ በሦስትነቱ ፡ ለአብርሃም ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፤ የዛሬ ፡ ዓመት ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እመለሳለሁ ፡ ብሎ ፡ በቃልነቱ ፡ ሲናገር ፡ ሥጋ ፡ በአብርሃምነት ፡ ቆሞ ፡ ተስፋውን ፡ ይቀበል ፡ ነበር ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ቍ ፡ ፱ ፡ ፲ ።

፴፱ ፡ ከተዋሐደው ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ ተስፋው ፡ ስለ ፡ ተፈጸመ ፤ አምላክ ፡ ሰው ፡ ሰው ፡ አምላክ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በመኾኑ ፤ ከድንግል ፡ የተወለደውን ፡



በበረት ፡ የተኛውን ፤ ኢሳይያስ ፡ አማኑኤል ፡ ዳንኤል ፡ ክርስቶስ ፡ ገብርኤል ፡ ኢየሱስ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ፤ ኖሎት ፡ መላእክት ፡ አመሰገኑት ። የምድር ፡ ነገሥታት ፡ ሰገዱለት ፤ ገበሩለት ። እናቱም ፡ አውራ ፡ ጣቱን ፡ አሰረችው ፤ በጨርቅ ፡ ጠቀለለችው ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ። ዳን ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፳፭ ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፴፩ ።

፵ ፤ ከተዋሕዶ ፡ በፊት ፤ አምልኮት ፡ ምስጋና ፡ ለፈጣሪ ፡ እንጂ ፤ ለፍጡር ፡ አይሰጡም ፡ ነበር ። ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚለው ፡ የቅድስና ፡ ምስጋና ፡ ለአምላክ ፡ ብቻ ፡ ከሰውና ፡ ከመላእክት ፡ አፍ ፡ ይቀርብለት ፡ ነበር ። ለዚህም ፡ ሄኖክ ፡ ኢሳይያስ ፡ ምስክር ፡ ናቸው ።

፵፩ ፤ ከተዋሕዶ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፤ ከድንግል ፡ የተወለደው ፡ ኢየሱስ ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንዲባልና ፡ ቅዱስ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ የምስጢር ፡ መልእክተኛው ፡ ገብርኤል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ተልኮ ፡ ምስክርነቱን ፡ ከሰጠበት ፡ ከዕለተ ፡ ፅንስ ፡ ጀምሮ ፡ አምላክ ፡ ለኾነው ፡ ሥጋ ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ተገባው ። ዳን ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፳፬ ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፮—፴፭ ።

፵፪ ፤ ለዚህም ፡ በዕለተ ፡ ፅንሱ ፡ በዕለተ ፡ ልደቱ ፡ ለተደረገው ፡ ምስጢር ፤ ታማኞች ፡ በኾኑት ፡ በመላእክት ፡ በኖሎት ፡ በዳንኤልና ፡ በዮሐንስ ፡ ቃል ፡ ከተገኘው ፡ ምስክርነት ፡ በላይ ፤ አንደኛ ፡ በሱ ፡ ህልው ፡ ኾኜ ፡ የምመለክበት ፡ የምወደው ፡ የምወልደው ፡ የባሕርይ ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነውና ፡ እሱን ፡ ስሙት ፡ ያለው ፡ አባቱ ፤ ኹለተኛ ፡ እኔና ፡ አብ ፡ አንድ ፡ ነን ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ራሱ ፤ ሦስተኛ ፡ ሞቶ ፡ ተነሥቶ ፡ በአብ ፡ ቀኝ ፡ የተቀመጠው ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ለሐዋርያት ፡ የሰጠው ፡ እሱ ፡ ኢየሱስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ በጴጥሮስ ፡ አፍ ፡ የመሰከረው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነግረውናል ፤ አስተምረውናል ፤ መስክረውልናል ። ስለዚህ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከሰው ፡ ምስክርነት ፡ በላይ ፡ የኾነውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስክርነት ፡ ተቀብላ ፡ አምና ፡ በእግዚአብሔር ፡ አንድነት ፡ መንትኛ ፤ በሦስትነቱ ፡ አራተኛ ፡ ሳትቀላቅል ፤ ጠንቅቃ ፡ ለይታ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ታምናለች ፤ ታስተምራለች ። ማቴ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፴ ። የሐ ፡ ሥ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፳፫—፴፬ ።

፵፫ ፤ በምስጢረ ፡ ሥላሴ ፤ እግዚአብሔር ፡ በአካሉ ፡ ሦስት ፤ በመለኮት ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ተናግረናል ። በምስጢረ ፡ ሥጋዌም ፤ በመለኮት ፡ አንድ ፡ ብለን ፡ ከምናምንባቸው ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ በቃልነቱ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስረድተናል ። ሰውም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ፍጹም ፡ መለኮቱ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፤ በመለኮት ፡ ተከፍሎ ፡ የለበትም ። ቈላ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፱ ።

፵፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ በአካል ፡ ሦስት ፡ በመለኮት ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ ሲባል ፤ መለኮት ፡ እንደ ፡ አካላት ፡ ከሦስት ፡ አይከፈልም ። ወይም ፡ ሦስቱ ፡ ኹሉ ፡ ሰው ፡ ኾኑ ፡ አያሰኝም ። ለዚህም ፡ በምስጢረ ፡ ሥላሴ ፡ የገለጥነውን ፡ የኩነታትን ፡ ምስጢር ፡ ማወቅ ፡ ይጠቅማል ።

www.ethiopianorthodox.org

፵፭ ፤ ከዚህም ፡ ባለፉት ፡ ምሳሌዎች ፡ ኹኔታ ፡ ምስጢሩን ፡ እናስረዳለንና፡ልብ፡ አድርጎ ፡ መመልከት ፡ ነው ።

፵፮ ፤ ፩ኛ ፡ ነፍስ ። ነፍስ ፡ በአካሏ ፡ ከሦስት ፡ የማትከፈል ፡ አንዲት ፡ ስትኾን ፤ ሦስት ፡ ኹኔታዎች ፡ ልብነት ፡ ቃልነት ፡ እስትንፋስነት ፡ አሏት ።

፵፯ ፤ ሰው ፡ ዐሳቡን ፡ ሊገልጽ ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፤ ቃልነቷ ፡ ከሥጋዊ ፡ ምላስ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ ይገለጣል ፤ ድምጡን ፡ ይሰጣል ። በአንደበትም ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፤ ከልብ ፡ አይጠፋም ። ልብ ፡ ቃል ፡ እስትንፋስ ፤ በተዋሕዶ ፡ እያሉ ፡ ቃል ፡ ሥጋዊ ፡ ምላስን ፡ ተዋሕዶ ፡ በተገለጠና ፡ ድምጡን ፡ በሰጠ ፡ ጊዜ ፤ ይህ ፡ የቃልነት ፡ ሁኔታ ፤ ልብን ፡ እስትንፋስን ፤ ወደ ፡ ቃልነት ፡ ሊለውጣቸው ፡ ወይም ፡ የነፍስን ፡ አካል ፡ ከሦስት ፡ ሊከፍለው ፡ አይችልም ። ስለዚህም ፤ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ በቃልነቱ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፤ የቃል ፡ ሰው ፡ መኾን ፡ መለኮትን ፡ እንደ ፡ አካላት ፡ ከሦስት ፡ አይከፍለውም ። ወይም ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ኾኑ ፡ አያሰኘውም ።

፵፰ ፤ ፪ኛ ፡ ፀሐይ ፡ ፀሐይ ፡ አካሉ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፤ ሦስት ፡ ኹኔታዎች ፡ ክበብ፡ ብርሃን ፡ ዋዕይ ፡ አሉት ።

ብርሃን ፤ ከክበብና ፡ ከዋዕይ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ እያለ ፤ ከብንተ ፡ ዐይን ፡ ጋራ ፡ ይወሐዳል ። በተዋሕዶውም ፤ ብንተ ፡ ዐይን ፡ ሩቁን ፡ ቅርቡን ፡ እንድትመረምር ፡ ያደርጋታል ። ይህ ፡ ከብንተ ፡ ዐይን ፡ ጋራ ፡ የብርሃን ፡ መዋሐድ ፡ ክበብንና ፡ ዋዕይን ፡ ከኹኔታቸው ፡ ወደ ፡ ብርሃንነት ፡ አይለውጣቸውም ። ወይም ፡ ፀሐይ ፡ ከሦስት ፡ አይከፈልም ። እንዲሁም ፡ የሰው ፡ ሕይወትና ፡ ብርሃን ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሥጋን ፡ በተዋሐደ ፡ ጊዜ ፤ ተዋሕዶው ፡ መለኮትን ፡ እንደ ፡ አካላት ፡ ከሦስት ፡ አይከፍለውም ፡ ወይም ፡ አብ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ኾኑ ፡ አያሰኝም ።

፵፱ ፤ ወዳጄ ፡ ምእመን ፡ ሆይ ፤

በምስጢረ ፡ ሥላሴና ፡ በምስጢረ ፡ ሥጋዌ ፡ መሐከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ እንድታውቅ ፤ የኩነታትን ፡ ምስጢር ፡ ጠንቅቅና ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፡ ብለኽ ፡ እመን ።

ቃል ፡ ከመላስ ፤ ብርሃን ፡ ከብንተ ፡ ዐይን ፡ ጋራ ፡ ሲዋሐዱ ፤ ሳይጠፉፉ ፡ ተዋሕደው ፡ ይኖራሉ ፡ እንጂ ፤ አንዱ ፡ አንዱን ፡ አይሽረውም ፤ አንዱ ፡ አንዱን ፡ አይውጠውም ።

፶ ፤ የቃልና ፡ የመላስ ፡ የብርሃንና ፡ የዐይን ፡ መዋሐድ ፤ እንደ ፡ ዘይትና ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ተዋሕዶ ፡ ልዩነት ፤ እንደ ፡ ወተትና ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ተዋሕዶ ፡ መደባለቅ ፡ መቀላቀል ፡ መሻሻርና ፡ መጠፋፋት ፡ የለበትም ። ተዋሕዶዋቸው ፡ እንደ ፡ ነፍስና ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፶፩ ፤ ነፍስና ፡ ሥጋ ፤ መለያየት ፡ መንታነት ፡ ወይም ፡ መጠፋፋት ፡ ሳይኖርባቸው ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾነው ፡ ስለሚኖሩ ፤ አንድ ፡ ሰው ፤ ኹለት ፡



አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ አካል፡ኹለት፡ባሕርይ ፡ አይባልም ። ኹለት ፡ ግብር ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ የለውም ።

፶፪ ፤ ስለዚህም ፤ እገሌ ፡ ተወለደ ፡ እገሌ ፡ አደገ ፡ በዚሁ ፡ አንጻር፡ተራበ ፡ ጠገበ ፡ በረታ ፡ ደከመ ፡ ሞተ ፡ ዳነ ፡ ይባላል ። እንዲሁም ፤ ደንቆሮ ፡ ዐዋቂ ፡ ሰነፍ ፡ ልባም ፡ ሕያው ፡ ሬሳ ፡ የሚባሉት ፡ ቃላት ፤ የነፍስና ፡ የሥጋን ፡ ተዋሕዶ ፡ በማጽናት ፡ ይነገሩለታል ።

፶፫ ፤ የነፍስ ፡ ገንዘብ ፡ ለሥጋ ፤ የሥጋ ፡ ገንዘብ ፡ ለነፍስ፡ስለ፡ሆነ ፤ ሰው ፤ እንደ፡ ዕውቀቱ ፡ መጠን ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሳለ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፤ በወዲህም ፡ ዓለም ፡ ኾነ ፤ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ይህ ፡ የነፍስ ፡ ሥራ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ የሥጋ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሳይለይ ፡ ጥቅሙንም ፡ ኾነ ፡ ጉዳቱን ፡ በአንድ ፡ መልክ ፡ ያገኛል ።

፶፬ ፤ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሆነ ፡ ባልን ፡ ጊዜም ፤ የመለኮትና፡የሰውነት፡ተዋሕዶ ፤ እንደ፡ ቃልና ፡ እንደ ፡ መላስ ፡ እንደ ፡ ዐይንና ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ነፍስና ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ መለያየት ፡ ወይም ፡ መደባለቅ ፡ የለበትም ።

፶፭ ፤ ስለዚህ ፡ አምላካችን ፡ ክርስቶስ ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ፡ ግብር ፡ አንድ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፤ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፤ ኹለት ፡ ግብር ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ አለው ፡ አንልም ።

፶፮ ፤ የተዋሕዶ ፡ ሀይማኖት ፤ በምስጢረ ፡ ሥላሴ ፤ እግዚአብሔር ፡ በአካል ፡ ሦስት ፡ በመለኮት ፡ አንድ ፡ ነው ፤ በምስጢረ ፡ ሥጋዌ ፤ ከሦስቱ ፡ አካላት፡አንዱ፡አካል፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ በቃልነቱ ፤ ሰው ፡ ከኾነ ፡ በኋላ ፤ በመለኮቱና ፡ በሰውነቱ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ የለም ። ፍጹም ፡ መለኮቱ ፡ በከዊን ፡ ስለ ፡ ተዋሐደ ፤ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፡ በእኛም ፡ አደረ ።

፶፯ ፤ ቃል ፡ ራሱን ፡ በራሱ፡ ስለ ፡ አከበረ ፤ ለተዋሐደው ፡ ሥጋ ፡ ራሱ ፡ ክብር ፡ ስለ፡ ኾነው ፤ ጸጋ ፡ እውነትም ፡ የመላበት ፡ ማለት ፤ ሥጋውን ፡ ቈርሶ ፡ ደሙን ፡ አፍሶ ፡ ብሉ ፡ ጠጡ ፡ ብሎ ፡ የሚሰጥ ፤ የተናገረውን ፡ የማይለውጥ ፤ አማኑኤል ፡ አምላካችን ፤ በመለኮቱ ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፤ ከአብ ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ ትክክል ፡ የኾነ ፡ ክብሩን ፡ አየነ ፡ ብሎ ፡ ማመን ፡ ናት ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፲፬—፲፮ ።

፶፰ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላካችን ፤ የክርስቲያን ፡ ሕይወት ፡ እሱና ፡ የላከው ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ትክክል ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ማመን ፡ ናትና ፤ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ማመንን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይግለጽልን ። አሜን ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ቍ ፡ ፫ ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ አራተኛ ፡ ዐምድ ፡ ማን ፡ ነው ?

፪ ፤ ምስጢረ ፡ ሥጋዌ ፡ ምን ፡ የምናስተምርበት ፡ ምን ፡ የምናምንበት ፡ ነው ?

፫ ፤ አዳም ፡ የፈጣሪውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመተላለፉ ፡ ምን ፡ መጣበት ?

www.ethiopianorthodox.org

፬ ፤ ቸርነቱ ፡ የማያልቅበት ፡ አምላክሳ ፡ ምን ፡ አደረገለት ?

፭ ፤ አዳም ፡ የእባብን ፡ ምክር ፡ ሲፈጽም ፡ ለምን ፡ ነበር ? ታዲያሳ ፡ ምን ፡ አገኘ ? ምን ፡ ቀረበለት ?

፮ ፤ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ በለስን ፡ በልተው ፡ ምን ፡ አወለቁ ? ምን ፡ ታጠቁ ?

፯ ፤ አዳም ፡ ከፈጣሪው ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡ ምን ፡ አደረገ ?

፰ ፤ እግዚአብሔር ፡ አዳምን ፡ ምን ፡ አለው ? አዳምሳ ፡ ምን ፡ መለሰ ?

፱ ፤ እግዚአብሔር ፡ ኹለተኛ ፡ አዳምን ፡ ምን ፡ ጠየቀው ? አዳምሳ ፡ ምን ፡ አለ ?

፲ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሔዋንን ፡ ምን ፡ አላት ፤ ሔዋንሳ ፡ ምን ፡ መለሰች ?

፲፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ በሔዋንና ፡ በእባብ ፡ ዘር ፡ መካከል ፡ በተናገረው ፡ ኗሪ ፡ ንግግር ፡ ምን ፡ መሠረተ ?

፲፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ አዳም ፡ ከኛ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ኾነ ፡ ባለው ፡ ቃሉ ፡ ምን ፡ ሰበከ ?

፲፫ ፤ አዳም ፡ በስንት ፡ ዘመኑ ፡ ሞተ ? ምክንያቱስ ?

፲፬ ፤ ኦሪት ፡ ኀጢአትን ፡ ለመሻር ፡ ችላለችን ?

፲፭ ፤ ኀጢአትን ፡ ለመሻር ፡ የሚጠበቀው ፡ ማን ፡ ነበር ? ምልክቱስ ፡ ምን ፡ ነበር ?

፲፮ ፤ ቃል ፡ ምን ፡ ኾነ ? ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሲኾን ፡ ሥጋ ፡ ምን ፡ አገኘ ?

፲፯ ፤ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ አማኑኤል ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተባሉት ፡ ስሞች ፡ ለቃል ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ ለሥጋ ፡ ብቻ ፡ ይነገራሉን ?

፲፰ ፤ የመድኀኒታችን ፡ ስንት ፡ ልደት ፡ አለው ? አንደኛውንና ፡ ኹለተኛውን ፡ ለይ ።

፲፱ ፤ ከተዋሕዶ ፡ በፊት ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ አንድነት ፡ ነበራቸውን ? ልዩነቱን ፡ አስረዳ ።

፳ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ አደረገ ? ሥጋስ ፡ ምን ፡ ተቀበለ ?

፳፩ ፤ ከተዋሕዶ ፡ በኋላሳ ፡ ምን ፡ ተደረገ ?

፳፪ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ምስክሩ ፡ ማነው ?

፳፫ ፤ ኢትዮጵያ ፡ የምትከተል ፡ የማንን ፡ ምስክርነት ፡ ነው ?

፳፬ ፤ ፍጹም ፡ መለኮት ፡ ሰው ፡ አልኾነምን ?

፳፭ ፤ የቃል ፡ ሰው ፡ መኾን ፡ መለኮትን ፡ ሊከፍለው ፡ ይችላልን ?

፳፮ ፤ የነፍስና ፡ የፀሓይ ፡ ምሳሌነት ፡ ለምን ፡ ይጠቅመናል ?

፳፯ ፤ የቃልና ፡ የመላስ ፡ የዐይንና ፡ የብርሃን ፡ የነፍስና ፡ የሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ መለየት ፡ መደባለቅና ፡ መጠፋፋት ፡ አለበትን ?

፳፰ ፤ የመለኮትና ፡ የትስብእት ፡ ተሕዋዶሳ ?

፳፱ ፤ የተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዴት ፡ ናት ?



ኢየሱስ ፡ ተጠምቆ ፡ ሲጸልይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወረደ ። አብ ፡ የምወድኽ ፡ ልጄ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ብሎ ፡ መሰከረ ። የኢየሱስም ፡ ዕድሜ ፡ ፴ ፡ ዘመን ፡ ነበር ። ሉቃስ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፳፩—፳፫ ።

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

## ዐምስተኛ ፡ ዓምድ ፡ ምስጢረ ፡ ጥምቀት ።

፩ ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተወለደ ፡ በሠላሳ ፡ ዘመኑ ፡ በዮርዳ ኖስ ፡ ወንዝ ፡ በዮሐንስ ፡ እጅ ፡ ተጠመቀ ፤ ስለ ፡ ጥምቀቱም ፤ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጊእየ ፡ እገብእ ፤ ወእትመየጥ ፡ እንተ ፡ ቀላየ ፡ ባሕር ፤ እግዚእብሔር ፡ እስራኤልን ፡ አሻግሬ ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡ ከወጣሁ ፡ በኋላ ፤ ወደ ፡ ጥልቁ ፡ ባሕር ፡ እመለሳለሁ ፡ አለ ። ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕለ ፡ ማያት ። አምላከ ፡ ስብሐት ፡ አንጐድጐደ ። እግዚ አብሔር ፡ ላዕለ ፡ ማያት ፡ ብዙኀ ። የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በውሆች ፡ ላይ ፡ ነው ፤ የምስጋና ፡ አምላክ ፡ ድምፁን ፡ ሰጠ ፤ እግዚአብሔር ፡ በውሆች ፡ ላይ ፡ ታየ ።

፪ ፡ ወመንፈስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጼልል ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ ይሰፋል ፡ የሚል ፡ መሪ ፡ ቃለ ፡ ትንቢት ፡ ተጽፎለት ፡ ነበረ ። ይህ ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ በጥምቀቱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወልድ ፡ በውሃ ፡ ሲጠመቅ ፤ አብ ፡ ለምስክርነት ፡ ድምፁን ፡ ሲሰጥ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአምሳለ ፡ ርግብ ፡ ሲወርድ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተፈጸመ ። መዝሙር ፡ ፳፯ ፡ ቍ ፡ ፳፪ ። ፳፱ ፡ ቍ ፡ ፫ ።

፫ ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከገሊላ ፡ ከናዝሬት ፡ ዮሐንስ ፡ ወደ ፡ አለ በት ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ በዮሐንስ ፡ እጅ ፡ ሊጠመቅ ፡ መጣ ። ዮሐንስ ፡ ከሱ ፡ ሊጠመቅ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ልመጣ፡በአንተ ፡ እጅ ፡ ልጠመቅ ፡ ይገባኛል ፡ እንጂ ፤ አንተ ፡ ወደኔ ፡ ልትመጣ ፡ በኔ ፡ እጅ ፡ ልትጠመቅ ፡ ይገባኛልን ? አይኾንም ፡ አለው ።

፬ ፤ መድኀኒታችንም ፡ አምላካዊውን ፡ ምክር ፡ ብታውቅስ ፡ አምላኩን ፡ ማጥመቅ ፡ ለአንተ ፡ በባርያው ፡ እጅ፡መጠመቅ፡ለኔ ፡ ሲኾን ፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ለኛ ፡ ስለ፡ኾነ ፡ ዛሬ ፡ ጽድቅን ፡ ኹሉ፡ልንፈጽም ፡ ይገባናልና ፡ እንቢ ፡ አትበል ፡ አለው።ከዚህ፡ በኋላ ፤ መድኀኒታችን ፡ በዮንሐስ ፡ እጅ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡ ተጠመቀ ።

፭ ፤ መድኀኒታችን ፡ ኀጢአት ፡ ኖሮበት ፡ ንስሐ ፡ ሊገባ ፡ አልተጠመቀም ። የሰው ፡ ሁሉ ፡ ጽድቅ ፡ እንደ ፡ መርገም ፡ ጨርቅ ፡ ኾኖ ፡ ነበርና ፡ በጽድቁ ፡ ጽድቃች ንን ፡ ሊያድስልን ፤ በጥምቀቱ ፡ ጥምቀታችንን ፡ ሊቀድስልን ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፮ ፤ ስለዚህ ፡ ተጠምቆ ፡ ከውሃው ፡ ወጥቶ ፡ ሲጸልይ ፡ ሰማዮች ፡ ተከፈቱ ፤ መን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ ወርዶ ፡ ተቀመጠበት ። እንዲሁም ፡ በሱ ፡ ህልው ፡ ኾኜ ፡ የምመለክበት ፡ የምወደው ፡ የምወልደው ፡ የባሕር ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ከሰማይ ፡ መጣ ። በዚህ ፡ የማይመረመር ፡ ምስጢር ፡ እናያለን ። መድኀኒታችን ፡ እንደ ፡ ጸለየ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይነግረናል ። ግን ፡ ጸሎቱ ፡ ምን ፡ ወይም ፡ ለምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አይገልጥም ። ነገር ፡ ግን ፡ በመድኀኒታችን ፡ ጸሎት ፤ ሰማዮች ፡ እንደ ፡ ተከፈቱ ፤ መን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ፡ወረደ ፡ አብ ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ መሰከረ ፤ ይህንንም ፡ ኹሉ ፡ ዮሐንስና ፡ ኢየሱስ ፡ እንደ፡አዩ ፡ ስናነብ ፤ የመድኀኒታችን ፡ ጸሎት ፡ በሰ ውና ፡ በእግዚአብሔር ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ የጥል ፡ ግርግዳ ፡ ለማፍረስ ፤ ሰውና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማቀራረብ ፡ ለማዋሐድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታወቀ ፡ ተረዳ ።



፯ ፤ የመድኀኒታችን ፡ ጥምቀት ፡ በሠላሳ ፡ ዘመኑ ፡ ኾነ ፤ አይሁድ ፡ እንደሚያደርጉት ፡ የመንጻት ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ ኃጥኣን ፡ መጸብሐን ፡ ከዮሐንስ ፡ እንደ ፡ ተጠመቁት ጥምቀት ፡ አልነበረም ፤ በሠላሳ ፡ ዘመኑ ፡ ፈጸመው ፡ እንጂ ፤ ምክንያቱም ፡ ለክህነት መመረጥና ፡ መሾም ፡ በሠላሳ ፡ ዘመን ፡ ዕድሜ ፡ ነበር ።

፰ ፤ ስለዚህ ፡ ማንኛውም ፡ ካህን ፡ ወይም ፡ የካህናት ፡ አለቃ ፡ በሠላሳ ፡ ዘመን ዕድሜው ፡ እንደ፡ብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ሕግ ፡ ይሾም ፡ ነበር። ታማኙ ፡ ሊቀ ፡ ካህናታችን ፡ ኢ[...] ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከአብ ፡ የተሰጠችውን ፡ መልእክት ፡ ሲጀምር ፡ በሠላሳ ፡ ዘመን ፡ ዕ[...] ሜው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ በጥምቀት ፡ መሠረተ ። ከዚህ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራስ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፤ የመምህርነቱን ሥራ ፡ እያከታተለ ፡ ፈጸመ ።

፱ ፤ ሙሴ ፡ አባቶቻችንን ፡ በደመና ፡ በባሕር ፡ አጠመቃቸው ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፪ ዮሐንስም ፡ በውሃ ፡ አጠመቀ ። የሐዋ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፭ ። በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማጥመቅ ፡ ግን ለሙሴና ፡ ለዮሐንስ ፡ ጌታ ፡ ለመድኀኒታችን ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ጥ[...] ቀትን ፡ ሲመሠርት ፤ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ገሮምሮ ፡ ከቶ ፡ ለማንም ፡ ያልታየ ፡ መንፈስ ቅዱስ ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ ወርዶ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፴፫

፲ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ልብነቱ ፡ የወደደችው ፡ የመረጥሁት ፡ ወዳጄ ፡ ልጄ ፡ እነኾ[...] በሱ ፡ ላይ ፡ መንፈሴን ፡ ሰጠሁ ፤ ሲል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በልጁ ፡ ለምእመናን ፡ እን[...] ሰጥ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ተፈጸመ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፵፪ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፲፩ ፤ ሙሴ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ዮሐንስም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ ጠ[...] ጊና ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ መልእክተኛ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ተጽፏል ። ሙሴ ፡ የመሰከረለት ፡ ዮ[...] ንስ ፡ መንገዱን ፡ የጠረገለት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፤ ከነቢያት ፡ ኹሉ ፡ በላይ አዳኝ ፡ ጌታ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ የምወደው ፡ የምወልደው ፡ የባሕርይ ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነወ[...] እሱን ፡ ስሙት ፡ የሚል ፡ ምስክርነት ፡ ስለ ፡ ልጅነቱ ፡ ስለ ፡ ጌትነቱ ፡ ስለ ፡ መምህርነ[...] ከሰማይ ፡ መጣለት ። ይህም ፡ ታማኝ ፡ ምስክር ፡ በባሕርዩ ፡ ኀጢአት ፡ በቃሉ ፡ ሐሰ[...] የማይገኝበት ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፲፫—፲፯ ።

፲፪ ፤ መድኀኒታችን ፡ በስሙ ፡ የሚያምኑ ፡ ኹሉ ፡ በጥምቀት ፡ የእግዚአብሔ[...] ልጆች ፡ እንዲሆኑ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ በመሠረተባት ፡ የመምህርነት ፡ ሥ[...] ውን ፡ በከፈተባት ፡ ሕገ ፡ ወንጌልን ፡ በጀመረባት ፡ በጥምቀቱ ፡ ጥምቀታችንን ፡ በ[...] ሰባት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ወልድ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ ሲጠመቅና ፡ ተጠምቆ ፡ በስሙ ፡ ለሚ[...] መቁት ፡ ሲጸልይ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በክስርቶስ ፡ ለክርስቲያን ፡ ሊሰጥና ፡ ሰዎች[...] ወደ ፡ ንጽሕና ፡ ወደ፡የውሀት ፡ በጠቅላላው ፡ ቀድሞ ፡ ወደ ፡ ነበሩበት ፡ ጠባይ ፡ ሊመ[...] ቸው ፡ በርግብ፡ አምሳል ፡ ሲወርድ ፤ አብ ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሲ[...] ክር ፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ፡ የኾነ ፡ ምስጢር ፡ ተገለጠ ።

፲፫ ፤ ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፡ በምስጢረ ፡ ሥጋዌ ፡ ተተረጐመ ። ምስጢረ ፡ ሥጋ[...] በምስጢረ ፡ ጥምቀት ፡ ተፈጸመ ። አምላክ ፡ ሰው ፡ ሰው ፡ አምላክ ፡ ከኾነ ፡ በኋላ ፤ አ[...]

www.ethiopianorthodox.org

ነት፡ በመጽናቱ፡ አማኑኤል፡ አምላካችን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ፡ ነውና ፡ እንደ፡ ንስጥሮስ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ያደረው ፤ እንደ ፡ ልዮን ፡ ከሱ ፡ ጋራ፡ ያለው ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ሳይል፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ አዋሕዶ ፡ ዮሐንስ ፡ ያጠመቀውን ፡ በዮርዳኖስ ፡ ላይ ፡ የቆመውን ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እሱን ፡ ስሙት ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሰከረ ።

፲፬ ፤ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ አንድ ፡ ነቢይ ፡ መሢሕ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ እንዲመጣ ፤ የሰውን ፡ ልጆችም ፡ በመልክተኛና ፡ በአማላጅ ፡ ሳይኾን ፤ እሱ ፡ ራሱ ፡ እንዲያድና ቸው ፡ ተጽፎ ፡ ነበር ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፵፫ ፡ ቍ ፡ ፫ ። ዳን ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፳፬—፳፭ ። መሢ ሕም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ መንገድ ፡ ጠራጊ ፡ ዐዋጅ ፡ነጋሪ ፡ ኾኖ ፡ ኤልያስ ፡ እንዲመጣ ፡ ነቢዩም ፡ ኾነ ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪው ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያጠምቁ ፡ ተነግሮ ፡ ነበር ። ኢሳ፡ ም ፡ ፵፫ ፡ ቍ ፡ ፫ ። ሚል ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፩ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፭ ።

፲፭ ፤ ስለዚህ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ ለማጥመቅ ፡ ከእግዚአብ ሔር ፡ ተላከ ፤ ትንቢቱን ፡ የሚያውቁ ፡ ጊዜውን ፡ የሚጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ነገሩን ፡ ለመረ ዳት ፡ መልክተኞች ፡ ላኩበት ፡ መልክተኞቹም ፡ ወደ ፡ ዮሐንስ ፡ ሂደው ፡ ክርስቶስ ፡ ነህን ፡ ኤልያስ ፡ ነህን ፡ ወይስ ፡ ነቢይ ፡ ነህን ፡ አንተ ፡ ማነህ ፡ አሉት ።

፲፮ ፤ ዮሐንስም ፡ ክርስቶስ ፡ ኤልያስም ፡ ነቢይም ፡ አይደለሁም ፡ ብሎ ፤ ክርስ ቶስ ፡ ነቢይም ፡ መኾንን ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ኤልያስነትን ፡ ጨምሮ ፡ ካደ ።

ዮሐንስ ፡ ክርስቶስነትንና ፡ ነቢይነትን ፡ ለባለቤቱ ፡ ሲሰጥ ፤ ለራሱ ፡ የሚገባ ውን ፡ ኤልያስነትን ፡ ጨምሮ ፡ መካዱና ፡ ክርስቶስ ፡ ኤልያስ ፡ ነቢይም ፡ አይደለሁም ፡ ማለቱ፤የዮሐንስ ፡ ኑሮ ፡ ከሰው ፡ የተለየ ፡ ስለ፡ኾነ ፤ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ይጠራጠሩ፡ የነበሩት ፡ ሕዝቡ ፡ ኤልያስነትን ፡ ቢያምንላቸው ፡ ኑሮ ፡ ክርስቶስነትን ፡ በሚኑበት ፡ ነበርና ፡ ይህን ፡ ስለ ፡ ፈራ ፤ ዕንቅፋትን ፡ ከሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ለማስወገድ ፡ ክርስቶስ ፡ ኤል ያስ ፡ ነቢይም ፡ አይደለሁም ፡ አለ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፲፱—፳፮ ።

፲፯ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ ኤልያስ ፡ ነቢይም ፡ ካልኾንክ ፡ ለምን ፡ ታጠምቃ ለህ ፡ ሲሉ ፡ ባቀረቡለት ፡ ጥያቄ ፡ እኔ ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ነኝ ፡ ስለዚህም ፡ እኔ ፡ በውሃ ፡ አጠምቃለሁ ፡ ግን ፡ እናንተ ፡ የማታውቁት ፡ እኔም ፡ የጫማውን ፡ ክር ፡ ልፈታ ፡ የማይገ ባኝ ፡ መምህር ፡ በመካከላችሁ ፡ አለ ።

፲፰ ፤ ይህ ፡ ከኔ ፡ በኋላ ፤ የሚመጣው ፡ መምህር ፡ ከኔ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እሱ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያጠምቃችኋል ፡ ብሎ ፡ በውሃ ፡ የሚያጠምቅ፡እሱ ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ የመሢሕ ፡ መንገድ፡ ጠራጊ ፡ ኤልያስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ከሱ ፡ በኋላ ፡ የሚ መጣው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በሚያጠምቀው ፡ ነቢይ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ አስረ ድቷል ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፯—፴፫ ።

፲፱ ፤ ምስክርነቱንም ፡ ሲሰጥ ፡ እኔ ፡ የማውቀው ፡ አልነበርኩም ፡ ለእስራኤል ፡ ሊገለጥ ፡ በውሃ ፡ አጠምቅ ፡ ዘንድ ፡ የላከኝ ፡ እግዚአብብሔር ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚያጠምቅ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወርዶ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ሲቀመጥበት ፡ የምታየው ፡



እሱ ፡ ነው ፡ አለኝ ፡ እንጂ ፡ ብሎ ፡ ምስክርነቱን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ መኾኑን ገልጧል ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፴፪—፴፬ ።

፳ ፤ ከርኩስነታችሁ ፡ ትነጹ ፡ ዘንድ ፡ በቅዱስ ፡ ውሃ ፡ አጥባችኋለሁ ፡ ሲል የተናገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጥምቀቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አውርዶ ፡ በስሙ ፡ ተጠም ቀው ፡ ከውሃና ፡ ከመንፈስ ፡ የሚወለዱ ፡ ኹሉ ፡ የመንጻትንና ፡ የማንጻትን ፡ ጸጋ ፡ ያገኙ ዘንድ ፡ የጥምቀትን ፡ ውሃ ፡ ቀደሰላቸው ። ሕዝ ፡ ም ፡ ፴፮ ፡ ቍ ፡ ፳፭ ።

፳፩ ፤ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የመንጻት ፡ ሥርዐት ፡ ሲኖር ፤ ብልጫ ያለው ፡ በደምና ፡ በውሃ ፡ የሚደረገው ፡ ነበር ። ዘፀ ፡ ም ፡ ፴ ፡ ቍ ፡ ፲ ። ዘኍ ፡ ም፡ ፲፱ ቍ ፡ ፱ ። ፴፩ ፡ ፳፫ ። ዕብ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፯ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የመንጻት ፡ ሥርዐት ለተቀባዮቹ ፡ ጠቃሚ ፡ አልነበረም ። ምክንያቱም ፡ መንፈስ ፡ ስለሌለበት ፡ ነው ። በ ዲስ ፡ ኪዳን ፡ የክርስቲያን ፡ ጥምቀት ፡ እንደ ፡ ብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ሥርዐት ፡ እንዳይኾን ከውሃ ፡ ጥምቀት ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጥምቀት ፡ ስለሚበልጥ ፤ ኦሪት ፡ ነቢያት፡እስከ ዮሐንስ ፡ ሠርተው ፡ ሥራቸውን ፡ ሲፈጽሙ ፤ በዘመነ ፡ ሙሴና ፡ በዘመነ ፡ ክርስቶስ መኻከል ፡ እንደ ፡ ዳኛ ፡ የነበረው ፡ ዮሐንስ ፡ የኦሪትን ፡ መንጻት ፡ በውሃ ፡ ጥምቀት ካሳለፉትና ፡ የዕንቅፋትን ፡ ድንጋይ ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ ካነሣት ፡ በኋላ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ፡ የሚያጠምቀው ፡ መምህር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በጥምቀት ፡ ወደ ፡ ሥራው ሲገባ ፤ የክርስቲያን ፡ ጥምቀት፡በመንፈስ፡በደም ፡ በውሃ ፡ ኾነ ። ፩፡ ዮሐ ፡ ም፡ ፭፡ቍ፡፮-፰

፳፪ ፤ ለመድኀኒታችን ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ልደት ፡ እንዳለው ፡ በ ስጢረ ፡ ሥጋዌ ፡ ተናግረናል ። አንደኛው ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፤ ኹለተኛው ፡ ከእመቤታችን ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ መድኀኒታችን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ይባላል ዮሐ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፳፯ ። ዳን ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፲፫ - ፲፬ ።

፳፫ ፤ እንዲሁ ፡ ሰውን ፡ የሚወድ ፡ የመድኀኒታችን ፡ ቸርነቱ ፡ በተገለጠ ፡ ጊዘ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ከሥጋዊው ፡ ልደት ፡ ሌላ ፡ ኹለተኛ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከእግዚአ ሔር ፡ መወለድ ፡ እንዲሆንላቸው ፡ ስለ ፡ ፈቀደ ፤ አምላካችን ፡ መድኀኒታችን ፡ ለኛ ፡ ጥቅ ሲጠመቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈሱን ፡ በልጁ ፡ ለክርስቲያን ፡ በመስጠቱ ፡ በስመ ለሚያምኑ ፡ ኹሉ ፡ በውሃ ፡ ተጠምቀው ፤ ሥጋውን ፡ ደሙን፡ተቀብለው፤ከውሃና ፡ ከመ ፈስ ፡ ቅዱስ፡ተወልደው፤በውሃ ፡ በደም ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ምስክርነት ፡ የእግዚአብሔ ልጆች ፡ እንዲኾኑ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥልጣን፡ሰጣቸው።ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፲፪

፳፬ ፤ ኦሪት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ እንደ፡መኾኗ ፤ በሙሴ፡ ተሰጥታለችና ፡ በ ሪነቷ ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ አደረሰችን ። ጸጋና ፡ እውነት ፡ ግን ፡ ማለት፡ራሱን ፡ ለወገኖ ለውጥ ፡ አድርጎ፡መስጠትና ፡ እንደተናገረው፡መፈጸም ፡ አለመጠጠትም፡እግዚአብሔር በምሳሌ፡ካየው፡ከሙሴ ፡ ይልቅ ፤ እግዚአብሔርን ፡ በህልውናው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ዘወት በሚያየው ፡ በመልክ፡በሚመስለው ፡ በባሕርይ ፡ በሚተካከለው ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶ ስለ፡ኾነ ፤ ከምልዓቱ ፡ ከለጋስነቱ ፡ እኛ ፡ ኹላችን ፡ ስለ ፡ ጸጋ ፡ ፈንታ ፡ በጸጋ፡ላይ ፡ ጸጋ

www.ethiopianorthodox.org

አገኘን፤ማለት፡በኦሪት፡ፈንታ፡ወንጌልን፤በውሃ፡ጥምቀት ፡ ፈንታ፡የመንፈስ፡ቅዱስ፡ጥምቀትን ፤ በመንፈስ ፡ ረድኤት፡ላይ፡መንፈስ ፡ ልደትን ፡ ተቀበልን ። ዮሐ ፡ ም፡፩፡ቍ፡፲፭-፲፰ ።

፳፭ ፤ መድኀኒታችን ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ ለወጠ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ፍቅሩን። እንዳስታወቀ ፤ በጥምቀቱ ፡ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፡ እናያለን ። መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እኛን ፡ ለማዳን ፡ ከአብ ፡ የተሰጠውን ፡ መልእክት ፡ ሲጀምር ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ለመግባት ፡ ተጠመቀ ። ስለዚህ ፡ ጥምቀቱ ፡ ለእኛ ፡ ጥቅም ፡ እንደ፡ኾነና ፡ በጥምቀታችን፡ በሃይማኖት ፡ የጥምቀትን ፡ ኀይልና ፡ ጸጋ ፡ እንዲሰጠን ፡ እንለምናለን ፡

፳፮ ፤ የክርስትና ፡ ጥምቀት ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ በአብና ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ለሚጠመቅ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ አብ ፡ በክርስቶስ ፡ የተጠመቀ ፡ ልጄ ፡ ብሎ ፡ ይመሰክርለታል ። ወልድም ፡ ኀይልን ፡ ይሰጠዋል ።

፳፯ ፤ ከአብና ፡ ከወልድ ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ የሚኖር ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ፍጥረቱን ፡ መድኀኒታችንንና ፡ ማኅበሩን ፡ የሚያዋሕድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይወርድበታል ። ኢትዮጵያ ፡ መድኀኒታችን ፡ ለኛ ፡ ጥቅም ፡ ሲጠመቅ፡በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚያጠምቅ ፡ እሱ ፡ በጥምቀቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመውረዱ ፡ ጥምቀታችንን ፡ እንደ፡ ቀደሰልን፡ያመነ፡የተጠመቀ ፡ ይድናል ። ያላመነ ፡ ያልተጠመቀ ፡ ይፈረድበታል ። ማር ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ቍ ፡ ፲፮ ። ባለው ፡ ቃሉ ፡ በስሙ ፡ ለሚያምንና ፡ ለሚጠመቅ ፡ ሕይወት ፡ እንዲሆንለት ፡ አምና ፡ የክርስቶስ ፡ ጥምቀት ፡ ለክርስቲያን ፡ ጥቅም ፡ እንደ፡ኾነ ፤ ታምናለች ፡ ታስተምራለች ፡ ልጆቿንም ፡ በስሙ ፡ ታስጠምቃለች ።

፳፰ ፡ ጌታችን ፡ መድኀኒታችን ፡ አምላካችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በጥምቀቱ ፡ በተሰጠው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምስክርነት ፡ ያጽናን ። አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ምስጢረ ፡ ጥምቀት ፡ ማለት ፡ ምንድ ፡ ነው ?
፪ ፤ መድኀኒታችን ፡ በስንት ፡ ዓመት ፡ ተጠመቀ ?
፫ ፡ ስለ ፡ ጥምቀቱ ፡ በብሉይ ፡ ምን ፡ ቃል ፡ ነበረ ?
፬ ፤ ቃሉስ ፡ በምን ፡ ጊዜ ፡ ተፈጸመ ? ማስረጃውስ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፭ ፤ መድኀኒታችን ፡ በማን ፡ እጅ ፡ በየትኛው ፡ ወንዝ ፡ ተጠመቀ ?
፮ ፤ የመድኀኒታችን ፡ ጥምቀት ፡ ስለ፡ምን ፡ ነበረ ?
፯ ፤ መድኀኒታችን ፡ ተጠምቆ ፡ ሲጸልይ ፡ ምን ፡ ተደረገ ?
፰ ፤ የመድኀኒታችን ፡ ጸሎት ፡ ለምን ፡ ነው ?
፱ ፤ ሙሴ ፡ አባቶችን ፡ በምን ፡ አጠመቀ ?
፲ ፤ ዮሐንስ ፡ በምን ፡ አጠመቀ ? ክርስቶስስ ?
፲፩ ፤ ስለ ፡ ሙሴና ፡ ስለ ፡ ዮሐንስ ፡ በብሉይ ፡ ምን ፡ ተጽፏል ?
፲፪ ፤ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ መሰከረ ?
፲፫ ፤ ስለ፡ዓለም ፡ ተስፋ ፡ ምን ፡ ተጽፎ ፡ ነበረ ?



፲፬ ፤ መንገድ ፡ ጠራጊው ፡ ማነው ?
፲፭ ፤ ዮሐንስ ፡ ለጠያቂዎቹ ፡ ምን ፡ መለሰ ?
፲፮ ፤ በኦሪት ፡ የመንጻት ፡ ሥርዐት ፡ እንዴት ፡ ነበረ ?
፲፯ ፤ የክርስቲያን ፡ ጥምቀት ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፲፰ ፤ ክርስቶስ ፡ በስሙ ፡ ለሚያምኑ ፡ ምን ፡ ሰጣቸው ?
፲፱ ፤ የክርስቶስ ፡ ጥምቀት ፡ ለማን ፡ ጥቅም ፡ ነው ?
፳ ፤ ኢትዮጵያስ ፡ ስለ ፡ ጥምቀት ፡ ምን ፡ ታስተምራለች ?

## ምዕራፍ ፡ ፳ ።

### ስድስተኛ ፡ ዐምድ ፡ ምስጢረ ፡ ቍርባን ፡ (የቍርባን ፡ ምስጢር) ፤


፩ ፤ አሐተ ፡ መሥዋዕተ ፡ ገብረ ፡ እንተ ፡ ለግሙራ ፡ ለእለ፡ይትቄደሱ ። ዕብ፡ም ፲ ፡ ቍ፡ ፲፬ ። የቍርባን ፡ ምስጢር ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ በኹለት ፡ ዐይነት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ስልት ፡ ይሠራ ፡ ነበር ፤ ይህም ፡ ባጭሩ ፡ ሲዘረዘር ፡ ከሥጋ ፡ ከደም ፡ ወገን ፡ የኾነው መሥዋዕት ፤ ከእኽል ፡ ወገን ፡ የኾነው ፡ ቍርባን ፡ ይባል ፡ ነበር፡ ማለት ፡ ነው ። መዝ ፵ ፡ ቍ ፡ ፰ ። አሠራሩም ፡ የሠርቀ ፡ ወርኀ ፡ (መባቻ) ፡ የሰንበት ፡ (ቅዳሜ) ፡ የታላላቅ በዓላት ፡ የፊቃድ ፡ የምስጋና ፡ የበደል ፡ የመድኀኒት ፡ የንስሐ ፡ የብፅዐት ፡ የቅንአት እየተባለ ፡ ይጠራ ፡ ነበር ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ።

፪ ፤ ሠራተኞችም ፡ ቦታውም ፡ ልዩነት ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፤ ከመጋረጃ ፡ ውጭ ቦታው ፡ ቅድስት ፡ መሥዋዕት ፡ አቅራቢዎቹ ፡ ካህናት ፤ ከመጋረጃው ፡ ውስጥ ፡ ቦታው ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ መሥዋዕት ፡ አቅራቢው ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ይባል ፡ ነበር ።

፫ ፤ ጊዜውም ፡ እንዲሁ ፡ ልዩ ፡ ስለ፡ኾነ ፡ ካህናት ፡ ዘወትር ፡ ሲሠዉ ፡ የካህናቱ አለቃ፡በዓመት፡አንድ፡ቀን፡ይሠዋ ፡ ነበር ። ዕብ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፮-፯ ። ለክርስቲያን ፡ ክብር ኾና ፡ የተዘጋጀችው ፡ ሕግ ፡ ባልተገለጠችባቸው ፡ ከሙሴ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ በነበሩት ዘመናት ፡ የሰው ፡ ጽድቅ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መርገም ፡ ጨርቅ ፡ ስለ ፡ ኾነና ፡ ኹሉም ፡ በደል ፡ ስለ ፡ ተካከለ ፤ ካህናቱም ፡ ኾኑ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ ራሳቸው ፤ በ፡ ላም ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ኀጢአት ፡ ይሠዉ ፡ ነበር ። ዕብ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፳፯ ።

፬ ፤ መሥዋዕቱም ፡ የማንጻት ፡ ኀይል ፡ አልነበረውም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዐምስት ሺሕ ፡ ከዐምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ የምሠራላቸው ፡ ሥራት ፡ ይች ፡ ናት ፡ ያለ ፡ እ ዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ የሚያቀርቡትን ፤ በኦሪት ፡ ሕግ ፡ የሚሠዉትን ፡ መሥዋ ትና ፡ ቍርባን ፡ አልወደድሁም ፡ ሥጋህን ፡ ንጹሕ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርግልኝ ፡ እንጂ በማለቱ ፤ ኦሪትን ፡ የሚሽረው ፤ ወንጌልን ፡ የሚያጸናው ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ በሚፈጸምበት ጊዜ ፡ በዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ቃሉን ፡ ላከ ። ከሞት ፡ አዳናቸው ። በመጽሐፍ ፡ ራስ ፡ በ ሪት ፡ የወገኖቼን ፡ ጩኸት ፡ ሰምቼ ፡ ከሚያስጨንቋቸው፡እጅ ፡ ላድናቸው ፡ ወረድኹ ዘፀ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፯—፰ ። መዝሙር ፡ ፵ ፡ ቍ ፡ ፯ ። ፻፯ ፡ ፳ ። ኤር ፡ ም ፡ ፴፩ ፡ ቍ ፴፫—፴፬ ። ዕብ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፬—፲፮ ።

www.ethiopianorthodox.org



ኢየሱስ ፡ አንገቱን ፡ ዘንበል ፡ አደረገ ። ነፍሱንም ፡ ከሥጋው ፡ ለየ ።
ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፴፩ ።



፳ ፤ እስራኤል ፡ ሕይወትኽን ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ታያታለህ ፡ ተብሎ ፡ ስለኔ
ተጽፏልና ፡ እሺ ፡ በጀ ፡ እነሆ ፡ መጣኹ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ። ኢየሱስ ፡ ክር
ቶስ ፡ ባባቱ ፡ ፈቃድ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈቃድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወዶ
ባቀረበልን ፡ በሥጋው ፡ በደሙ ፡ ቅዱስ ፡ ቊርባንነት ፡ እኛ ፡ ኹላችን ፡ እንከብር ፡ ዘን
ለሚያምኑ ፡ ኹሉ ፡ መንጻት ፤ ስርየተ ፡ ኀጢአት ፡ ክብርና ፡ ሕይወት ፡ የሚገኝባትን
አንዲት ፡ መሥዋዕት ፡ ለዘለዓለም ፡ የማትሻር ፡ የማትለወጥ ፡ አድርጎ ፡ ሠራ ።

፳፩ ፤ ይህችውም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አድሮበት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አዳኝ
ጌታ ፡ ብሎ ፡ ከሚያምን ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ የማያገኛት ፤ ከፈጣሪ ፡ በቀር ፡ ፍጡር ፡ መ
ምሮ ፡ የማይደርስባት ፡ መሥዋዕት ፡ ወንጌል ፡ ናት ።

፳፪ ፤ አይሁድ ፡ ለራሳቸው ፡ ሳይኾን ፡ ለአባቶቻቸው ፡ በተደረገው ፡ ነገር ፡ ይመኩ
ነበርና ፡ ስለ ፡ ኀላፊው ፡ መብል ፡ ብቻ ፡ አጥብቀው ፡ ሲፈልጉት ፡ መድኀኒታችን
ለኀላፊው ፡ መብል ፡ ሳይኾን ፡ ዘለዓለም ፡ ለሚኖረው ፡ ምግብ ፡ ዐስቡ ፡ ቢላቸው ፤ ባር
የሰጣቸውን ፡ ስጦታ ፡ አቃለው ፡ አባቶቻችን ፡ ከሰማይ ፡ ዕንጀራ ፡ በሉ ፡ አንተስ ፡ ከዚ
የተሻለ ፡ ምን ፡ የዐይን ፡ ምስክር ፡ ታሳያለህ ፡ ምን ፡ ተኣምራት ፡ ታደርጋለህ ፡ አሉት

፳፫ ፤ ዐሳቡና ፡ ነገሩ ፡ ጠባዩና ፡ ግብሩ ፡ የማይመረመረው ፡ ጌታችን ፡ አምላካችን
መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሙሴ ፡ የሰጣችሁ ፡ ዕንጀራ ፡ አይ
ለም ።

ይህ ፡ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ ኅብስት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ ነው ፤ እኔም ፡ የ
ሰጣችሁ ፡ ኅብስት ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፡ አላቸው ።

፲፱ ፤ አይሁድ ፡ ይህን ፡ ሰምተው ፡ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ እኔ ፡ የምሰጣችሁ ፡ ይህ
ኅብስት ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፡ በማለቱ ፡ እያወቅነው ፡ እንዴት ፡ ከሰማይ ፡ ወረድኹ ፡ ይለናል
ሥጋውንስ ፡ እንዴት ፡ ሊሰጠን ፡ ይችላል ፡ ብለው ፡ አንጐራጐሩ ።

አይሁድ ፡ በትውልድ ፡ መጽሐፋቸው ፡ የሌለ ፡ ልማድ ፡ በክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ነ
ቱንና ፡ እናቱን ፡ እናውቃለን ፡ ብለው ፡ ሲመሰክሩ ፡ ተሳሳቱ ።

፲ ፤ በእውነቱ ፡ ያመፀኞች ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ መኾናቸው ፡ መጠን ፡ የአባቶ
ቸውን ፡ ዐመፅ፡ለመፈጸም ፡ አባቶቻቸው ፡ በሙሴ ፡ ላይ ፡ በሚስቱ ፡ ምክንያት ፡ እንዳን
ራጐሩ ፤ እነሱ ፡ ደግሞ ፡ በክርስቶስ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ስለ፡አጡ ፡ አባቱንና ፡ ነ
ቱን ፡ እናውቃለን ፡ በማለት ፡ አንጐራጐሩ ፡ እንጂ ፤ እንኳን ፡ አባቱን ፡ እናቱንም ፡ እ
ማያውቋት ፡ በንግግራቸው ፡ ዘሯን ፡ ሥራዋን ፡ አድራሻዋን ፡ ባለመጥቀሳቸው ፡ ይታ
ቃል ።

፲፩ ፤ ሥጋውን ፡ እንዴት ፡ ሊሰጠን ፡ ይችላል ፡ ማለታቸውም ፡ አባቶቻቸው
እግዚአብሔር ፡ መና ፡ ከደመና ፡ አውርዶ ፤ ውሃ ፡ ከድንጋይ ፡ አፍልቆ ፡ እየመገባቸው
እግዚአብሔር ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ማዕድ ፡ መሥራት ፤ ውሃ ፡ ከድንጋይ ፡ ማፍለቅ ፡ ለ
ዝቡ ፡ እኽል ፡ ውሃ ፡ መስጠት ፡ ይቻለዋልን ፡ በማለት ፡ የጀመሩትን ፡ የሐሜተኛ ፡ አ
ልማድ ፡ ውጥን ፡ ለመጨረስ ፡ መኾኑ ፡ አያጠራጥርም ። መዝ ፡ ፸፰ ፡ ቍ ፡ ፲፱—፴ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪ ፤ ኹል ፡ ጊዜ ፡ የሚታገሥ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ የአባቶቻቸውንም ፡ የነሱንም ፡ ማንጐራጐር ፡ ሰምቶ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ታገሣቸው ።

በኔ ፡ የሚያምን ፡ አይራብም ፡ አይጸማም ፤ አባቶቻችሁ ፡ በምድረ፡ በዳ፡ዕንጀራ፡ በሉና ፡ ሞቱ ፤ ከዚህ ፡ ኅብስት ፡ የበላ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፤ አይሞትም ።

፲፫ ፤ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ የሕይወት ፡ ዕንጀራ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ስለ ፡ ዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ የምሰጠው ፡ ምግብ ፡ ሥጋዬ ፡ ነውና ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ሥጋ ፡ ካልበላችሁ፡ ደሙንም ፡ ካልጠጣችሁ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ የላችሁም ፡ እውነት ፡ እነግራችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ አባትነቱ ፡ መከራቸው ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፳፮—፶፰ ።

፲፬ ፤ አይሁድ ፡ በአፋቸው ፡ አባቱን ፡ እናቱን ፡ እናውቃለን ፡ እንደ፡ማለታቸው፤ ከነቢያትና ፡ ከነቢያት ፡ መምህር ፡ እግዚአብሔር ፤ የተማሩ ፡ ቢኾኑ ፡ ኖሮ ፡ እንደ፡ሚክያስ ፡ እንደ ፡ ኢሳይያስ ፡ ትምህርት ፤ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የወለደው ፡ አባቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ድኅረ ፡ ዓለም ፡ ያለ ፡ ዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ ያለ ፡ ሩካቤ፡ (ወንድ ፡ ሳታውቅ) ፡ የወለደችው ፡ እናቱ ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ እንደ ፡ ኾነች ፤ የአብ ፡ ልጅ ፡ የማርያም ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አማኑኤል ፡ መካር ፡ ብርቱ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባወቁና ፡ ትምህርቱን ፡ በሰሙት ፡ ምክሩን ፡ ትእዛዙን ፡ በተቀበሉት ፡ ነበር ። ሚክ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፪ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ። ፱ ፡ ፯—፰ ።

፲፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እናውቃለን ፡ እያሉ ፡ ለሕይወት ፡ የሚፈልጋቸውን ፡ ሰው ፡ በፋሲካ ፡ ቀን ፡ ለሞት ፡ በመፈለጋቸው ፡ አለዋቂዎች ፡ መኾናቸው ፡ ተገለጠ ።

፲፮ ፤ መድኀኒታችን ፡ በመዋዕለ ፡ ስብከቱ ፡ በወልድ ፡ የሚያምን ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ አለው ፡ እያለ ፡ ክርስቲያንን ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ሲጠራ ፡ ምእመናኑም ፡ በውሃ ፡ ተጠምቀው ፡ ሥጋውን ፡ በልተው ፡ ደሙን ፡ ጠጥተው ፡ ጥበብና ፡ ዕውቀት፡ማስተዋልና፡እውነት፡ኀይልና ፡ ምክር ፤ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ የሚገኙበት፡መንፈስ፡ቅዱስን ፡ ተቀብለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ከላይ ፡ ልትወለዱ ፡ ይገባችኋል ፡ ሥጋዬን ፡ የበላ ፤ ደሜን ፡ የጠጣ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ አለው ፡ እያለ ፡ ሲያስተምር ፡ የሰሙ ፡ ኹሉ ፡ ሩቅ ፡ አድርገው ፡ ይመለከቱት ፡ ነበርና ፤ አይሁድ፡ ሲያንጐራጕሩ ፡ ሐዋርያት ፡ ሲጠራጠሩ ፡ ሕይወትን ፡ የሚሰጥ ፡ መንፈስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሊያስረዳቸው ፡ ስለኛ ፡ ጥቅም ፡ በጥምቀቱ ፡ የጀመረውን ፡ ቸርነት ፡ በሞቱ ፡ ፈጸመው ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፯ ፡ ፴፯ ።

፲፯ ፤ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ የነበረውን ፡ የፋሲካ ፡ በዓል ፡ አከባበር፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ አይሁድ ፡ እንደሚገባ ፡ አላደረጉትም ፡ ያም ፡ ቀን ፡ ዐሙስ ፡ ነበረ ።

ማታ ፡ ጊዜ ፡ በጉን ፡ በመቅደስ ፡ አርደው ፡ ሲመሽ ፡ ወሰደው፡ በቤታቸው ፡ ተካፍለውታል ። ምሳሌ ፡ የነበረው ፡ የፋሲካ ፡ በግ ፡ ሥራውን ፡ ጨርሶ ፡ ቦታውን ፡ ሲለቅ ፤ በመጽሐፍ ፡ ራስ ፡ ስለሱ ፡ የተጻፈለት ፡ የዓለሙን ፡ ኀጢአት ፡ የሚያስወግደው ፡ እውነተኛው ፡ የእግዚአብሔር ፡ በግ ፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ መጣኹ ፡ ብሎ ፡ ሥራውን ፡ ጀመረ ። ዘፀ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፫ - ፲፭ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፱ ።



፲፰ ፤ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ስለ ፡ ፋሲካ ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ በሚያደርጉት ፡ ማዕ[...] ልዩ ፡ ሥርዐት ፡ ነበራቸው ።

፲፱ ፤ መጠጡ ፡ ደም ፡ ከሚመስል ፡ ቀይ ፡ ወይን ፡ ይዘጋጃል ፤ እንዲሁም ፡ [...] ጹሕ ፡ ስንዴ ፡ ዳቦ ፡ ይሠራል ፤ ሦስት ፡ ጽዋ ፡ ከወይኑ ፡ ያቀርባሉ ፤ ከዳዊት ፡ መዝመ[...] ከመቶ ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ በግብዣው ፡ ጊዜ ፡ መዘመር ፡ [...] ዳቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ መጀመሪያ ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ሦስተኛውንና ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ [...] ተኛውን ፡ ኹለቱን ፡ መዝሙር ፡ ዘምረው ፡ ራት ፡ ሲጀመር ፤ ከኹሉ ፡ በፊት ፡ ባለቤ[...] ከዳቦው ፡ አንዱን ፡ አንሥቶ ፡ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡ ከምድር ፡ ይህንን ፡ ምግብ ፡ ስ[...] ሰጠኸን ፡ ምስጋና ፡ ይገባሀል ፡ ብሎ ፡ ቈርሶ ፡ መጀመሪያ ፡ እሱ ፡ ይበላል ፤ ኹሉ ፡ ከ[...] ይበላሉ ።

፳ ፤ እንዲሁም ፡ የፊተኛውን ፡ ጽዋ ፡ አንሥቶ ፤ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡ ይ[...] መጠጥ ፡ ከወይን ፡ ስለ ፡ ሰጠኸን ፡ ምስጋና ፡ ይገባሀል ፡ ብሎ ፡ አመስግኖ ፡ በፊት፡እ[...] ይጠጣል ፤ ኹሉም ፡ ከዚያ ፡ ይጠጣሉ ።

፳፩ ፤ እንዲሁም ፡ በኹለተኛው ፡ ጽዋዕ ፤ መቶ ፡ ዐሥራ፡ዐምስተኛውንና፡መ[...] ዐሥራ ፡ ስድስተኛውን ፡ መዝሙር ፤ በሦስተኛው ፡ ጽዋውን ፡ ከጠጡ ፡ በኋላ ፤ ባለቤ[...] እስራኤል ፡ በግብጽ ፡ በእንግድነት ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ በታላቅ ፡ ኀይል ፡ [...]ኑዕ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳወጣቸው ፤ ሲወጡም ፡ በችኰላ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ሥንቃቸው ፡ ቂ[...] እንደ ፡ ነበረ ፡ ይህም ፡ በዓል ፡ ከግብጽ ፡ የወጡበት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ በዚህም ፡ ምክን[...] በበዓሉ ፡ ቀን ፡ ቂጣ ፡ መጣጣ ፡ እንዲበላ ፡ አስረድቶ ፡ ሲጨርስ ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ሰ[...] ኛውንና ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንተኛውን ፡ መዝሙር ፡ ዘምረው ፡ ራት ፡ ይፈጸም ፡ ነበ[...]

፳፪ ፤ መድኀኒታችን ፡ በፋሲካ፡ልማድ ፡ ለራት ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፤ ከኹለተኛ[...] ጽዋዕ ፡ በኋላ ፡ ከራት ፡ ተነሥቶ ፡ የደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ እግር ፡ አጠበ ። ዮሐ ፡ ም፡ [...] ቍ ፡ ፬—፲፩ ።

፳፫ ፤ ሥርዐተ ፡ ሕፅበቱን ፡ ፈጽሞ ፤ እናንተ ፡ ጌታችን ፡ መምህራችን ፡ ትለ[...] ችሁ ፡ በእውነት ፡ መምህራችሁ ፡ ጌታችሁ ፡ ነኝ ፤ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ መምህራችሁ ፡ [...] ችሁ ፡ ስኾን ፡ እግራችሁን ፡ ካጠብኋችሁ ፤ እናንተም ፡ ለባልንጀሮቻችሁ ፡ እንዲ[...] አድርጉ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፲፪—፲፬ ።

፳፬ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ ተቀመጠና ፡ ኅብስቱን ፡ አንሥቶ ፡ አ[...] ግኖ ፡ ባርኮ ፡ ቈርሶ ፡ ስለ፡ናንተና ፡ ስለ ፡ ብዙዎች ፡ ቤዛ፡የሚፈተት ፡ የሚሰጥ፡ ሥ[...] ይህ ፡ ነው ፡ እንኩ ፡ ብሉ ፡ ብሎ ፡ ሰጣቸው ።

፳፭ ፤ እንዲሁም ፡ ጽዋውን ፡ አንሥቶ ፡ አመስግኖ ፡ አክብሮ ፡ ስለናንተ ፡ [...] ዓለም ፡ ሕይወት ፡ የሚፈሰው ፡ አዲስ ፡ ሥርዐት ፡ ኾኖ ፡ የሚሰጠው ፡ ደሜ ፡ ይህ ፡ [...] እንኩ ፡ ጠጡ ፡ ብሎ ፡ ሰጣቸው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳፮ ፡ ቍ ፡ ፳፮—፳፰ ።

፳፮ ፤ እነሱም ፡ አክብረው ፡ ተቀብለው ፤ ሥጋውን ፡ በሉ ፤ ደሙን ፡ ጠጡ ፤ ከ[...] እንደ ፡ ጠቀስነው ፡ በፋሲካ ፡ ራት ፡ ላይ ፡ ባለቤቱ ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ እንግድነትና ፡

www.ethiopianorthodox.org

ብጽ ፡ ስለ ፡ መውጣታቸው ፡ የኾነውን ፡ ታሪክ ፡ ይዘረዝር ፡ ነበር ። መድኀኒታችን ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ለራት ፡ በተቀመጠበት ፡ ቀን ፡ ግን ፤ በመጀ
መሪያው ፡ ጽዋዕ ፡ ከእናንተ ፡ አንዱ ፡ ያሲዘኛል ፡ አላቸው ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፳፩ ።

በኹለተኛው ፡ ጽዋዕ ፤ የሚያሲዘኝ ፡ እጁን ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ወጭቱ ፡ (ማህን) ፡ የሚያወርደው ፡ ከኔ ፡ ጋራም፡ከወጡ ፡ የሚጠቅሰው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ የሰው፡ልጅ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ይሞታል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አሳልፎ ፡ ለሚሰጠው ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ ወዮለት ፡ ብሎ ፡ ከማስጠንቀቅ ፡ ጋራ ፡ የሚያሲዘው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ በልዩ ፡ ምልክት ፡ አሳ ያቸው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳፮ ፡ ቍ ፡ ፳፩—፳፭ ።

፷፯ ፤ በሦስተኛውም ፡ መሥዋዕተ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ መሥዋዕተ ፡ አሮን ፡ ካለፉ፡ በኋላ ፤ ብሉይ ፡ ኪዳን ፡ የተፈጸመበትን ፤ ሐዲስ፡ኪዳን ፡ የጸናበትን ፡ የሐዲስ ፡ ሥርዐት ፡ መሥዋዕት ፤ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ በዮሐንስ ፡ ወንጌል፡ምዕራፍ ፡ ፲፯ ፡ በተጻፈው፡ጸሎቱ፡ አክብሮ ፡ ቀድሶ ፡ ሰጣቸው ።

፷፰ ፤ እንዲሁም ፡ ሥርዐተ፡ ምስጢርን ፡ ሠርቶ፡አሳይቶ ፡ መታሰቢያዬን ፡ እንደ ዚህ ፡ አድርጉ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ አዘዛቸው ፡ ሐዋርያት ፡ ከክርስቶስ ፡ የተቀበሉትን ፡ ትእ ዛዝ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመስጠታቸው ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የክርስቶስን ፡ ሕማሙን፡ ሞቱን ፡ ትንሣኤውን ፡ ዕርገቱን ፡ ዳግም ፡ ምጽአቱን ፡ በልብ ፡ እያሰበች ፤ በአፏ ፡ እየመ ሰከረች ፤ በሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ለሐዲስ ፡ ሥርዐት ፡ የተሰጠውን ፤ የዓለሙን ፡ ኀጢአት፡ ለማስወገድ ፡ ችሎታ ፡ ያለውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በግ ፡ ስትሠዋ ፤ ሥጋውን ፡ ደሙን፡ ስትሰጥና ፡ ስትቀበል ፡ ኖራለች ፤ ትኖራለች ።

፷፱ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይህ ፡ ኅብስት ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፤ ይህ፡ ጽዋዕ፡ ደሜ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በተናገረና ፡ ኅብስቱን ፡ ወይኑን ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ አድርጎ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ በመስጠቱ ፤ የሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ቃሉን ፡ በደሙ ፡ ባተመው ፡ ጊዜ ፤ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ የሚሠዉትን ፡ መሥዋዕትና ፡ ቍርባን፡አልወደድሁምና፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ መጣሁ ፡ ብሎ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ ላይ ፡ የተናገረውን ፡ ዐዋጅ፡ሲፈጽም ፤ ይህ፡ ኅብስት ፡ ስለ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ቤዛ ፡ የሚፈተት ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ጽዋዕ፡ ስለ፡ዓለም፡ ሕይወት ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ ስርየት ፡ የሚፈሰው ፡ የሐዲስ ፡ ሥርዐት፡ደሜ ፡ ነው ፡ ያለው፡ ኀያል ፡ ቃሉ ፡ ኦሪትን ፡ ሻረ ፤ ወንጌልን ፡ ሾመ ። ዕብ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፫—፱ ።

፸ ፤ ብሉይ ፡ ኪዳንን ፡ በሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ፈጸመ ። መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ በመጽሐፍ ፡ ስለሱ ፡ የተጻፈውን ፡ ለመፈጸም ፡ ኅብስቱንና ፡ ወይኑን ፡ ሥጋ ውን ፡ ደሙን ፡ አድርጎ ፡ ልንበላውና ፡ ልንጠጣው ፡ ሰጠን ፤ ስለዚህም፡ በማይመረመር፡ ልግስናው ፡ መሐሪ ፡ ርኅሩኅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለጌትነቱ ፡ መታሰቢያ ፡ አደረገ ።

፸፩ ፤ ዘለዓለማዊ ፡ ኪዳኑን ፡ ዐስቦ ፡ ለሚፈሩት ፡ ለሚያመልኩት ፡ ምግባቸውን፡ ሰጣቸው ። ለአሕዛብ ፡ ርስቱ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፤ ለወገኖቹ፡ (ለሐዋርያት) ፡ የሥራውን ፡ ኀይል ፡ ማለት ፡ ኅብስቱን ፡ ሥጋ ፤ ወይኑን ፡ ደም ፡ አድርጎ፡ አምነው ፡ ለሚቀበሉት ፡ ኀይል ፡ ጽንዕ ፡ የሚኾን ፡ ምስጢረ ፡ ቍርባንን ፡ አሳያቸው ።



፸፪ ፤ የወልድ ፡ ሥራው ፡ እውነትና ፡ ቅንነት ፡ ናቸው ። ማለት ፡ ሕያው ፡
እንደ ፡ ላከኝ ፡ እኔም ፡ ሕያው ፡ ነኝ ፡ የበላኝም ፡ ስለኔ ፡ ሕያው ፡ ኾኖ ፡ ይኖራል ፡
ውን ፡ ቃል ፤ ሥጋዬን ፡ ብሉ ፡ ደሜን ፡ ጠጡ ፡ ብሎ ፡ በመስጠቱ ፡ አጠናው ። ሥ
እውነተኛ ፡ መብል ፡ ነውና ፤ ደሜም ፡ እውነተኛ ፡ መጠጥ ፡ ነውና ፡ ሥጋዬን ፡ የ
ደሜን ፡ የጠጣ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ አለው ።

፸፫ ፤ እኔም ፡ በኋለኛዩቱ ፡ ቀን፡ አስነሣዋለሁ ፡ ሲል ፡ የተናገረው፡ ትእዛዙ፡ የታ
ነው ። ለዘለዓለምም ፡ የጸና ፡ ነው ። ሰው ፡ ለሕይወቱ ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ ስለሚፈ
እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፡ የሰው ፡ ሥጋ ፡ መብላትም ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ በመ
አማኑኤል ፡ አምላካችን ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ በኅብስት ፡ በወይን ፡ ሰጠን ። መዝ ፡ ፻
ቍ ፡ ፩- ፰ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፶፩—፶፯ ።

፸፬ ፤ ምሳሌ ፤ ወይም ፡ መታሰቢያ ፡ ወይም ፡ ለውጥ ፡ አይደለም ፡ ሕያው ፡
ዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ይህ ፡ ኅብስት ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ጽዋዕ ፡ ደሜ ፡ ነው ፡
እንደ ፡ ነገረን ፤ እውነተኛ ፡ ሥጋው ፡ እውነተኛ ፡ ደሙ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፸፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ መድኀኒት ፡ ልጁን ፡ ሲልክ ፡ ጸ
እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ በስሙ ፡ ለሚያምኑ ፡ ኹሉ ፡ እንጂ ፤ በሐዋርያት ፡ ብቻ ፡ ስ
ወሰን ፤ ክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ የክርስቶስን ፡ ሥጋ ፡ በልቶ ፡ ደሙን ፡ ጠጥቶ ፡ የዘለዓ
ሕይወትንና ፡ የክብር ፡ ትንሣኤን ፡ ይወርስ ፡ ዘንድ ፤ መታሰቢያዬን ፡ አድርጉ ፡
የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ አዘዘ ።

ይህን ፡ ያደረገ ፡ ስሙ ፡ ቅዱስ ፤ ግሩም ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ
ላል ። መዝ ፡ ፻፲፩ ፡ ቍ ፡ ፱ ።

፸፮ ፤ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኅብስቱን ፡ ወይኑን ፡ በምስጋና
ብሮ ፡ ቀድሶ ፡ ማለት ፡ ራሱን ፡ ኅብስት ፡ ወይን ፡ ኅብስቱንና ፡ ወይኑንም ፡
ውን ፡ ደሙን ፡ አድርጎ ፡ በፍጹም ፡ ሃይማኖትና ፡ በንጽሕና ፡ ልንበላውና ፡ ልንጠ
ሲሰጠን ፤ መታሰቢያዬን ፡ አድርጉ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝህ ፡ መሥዋ
ልጅህ ፡ እነሆ ፡ እያለች ፡ ልጁን ፡ ለአባቱ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ መሥዋዕት ፡ አድ
በምታቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኅብስቱን ፡ ወይኑን ፡ አሐዱ ፡
ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ ወልድ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብላ ፡ በምስ
ታከብረዋለች ፡ ትቀድሰዋለች ።

፸፯ ፤ እንዲሁም ፡ አቤቱ ፡ ራስኽን ፡ ለሞት ፡ አሳልፈህ ፡ በሰጠህባት ፡ ቀን
ስቱን ፡ ወይኑን ፡ ቀድሰኽ ፡ ቈርሰኽ ፡ ባርከኽ ፡ አክብረኽ ፡ ቀምሰኽ ፡ ለሐዋርያት ፡
ሰጠሀቸው ፤ ዛሬም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ አድርገህ ፡ ሥጋኽን ፡ ደምኽን ፡
ብላ ፡ በጸሎት ፡ ትባርከዋለች ፡ ትቈርሰዋለች ።

፸፰ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥጋውን ፡ በምትፈትትበትና ፡ ደሙን ፡ በም
ስበት ፡ ጊዜ ፤ መገረፉን ፡ መሰቀሉን ፡ መቸንከሩን ፡ መወጋቱን ፡ ሕማሙን ፡ ሞ

www.ethiopianorthodox.org

ታስባለች ፤ ታሳስባለች ። በቍርባን ፡ ጊዜም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምትፈጽመው ፡ ጸሎትና ፡ ምስጋና ፡ ቅዳሴ ፡ ዝማሬ ፡ ይባላል ።

፴፱ ፤ ምክንያቱም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ አመስግኖ ፡ ከሰጣቸውና ፡ ማኅበሩም ፡ አመስግነው ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ፤ ከመቶ ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ እስከ ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ያለውን ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ዘምረው ፡ እሱ ፡ ወደ ፡ ሞት ፤ እነሱ ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ ስለ ፡ ተሰነባበቱ ፡ ነው ።

፵ ፤ መድኀኒታችን ፡ የሊቀ ፡ ካህናትነቱን ፡ ሥራ ፡ በፈጸመባት ፡ ቀን ፡ የብሉይ፡ ኪዳን ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ መጋረጃ ፡ ገልጦ ፡ እንዲሠራ ፤ በሥጋ ፡ ተገልጦ ፡ መጋረጃ ፡ ጋርዶ ፡ እንዲሠራ ፡ ሥጋውን ፡ መጋረጃ ፡ አድርጎ ፡ የእውነትና ፡ የሕይወት ፡ መንገድን ፡ ማለት ፤ ሕገ ፡ ተስፋን ፡ ልደትን ፡ አድሶልናልና ፡ ወንድሞቻችን ፡ የነፍስ ፡ የሥጋ ፡ ሕይወት ፡ የሚኾን ፡ የክርስቶስን ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ይዘን ፡ ለማቅረብ ፡ ለመቀበል ፡ ለማቀበል ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በምንገባበት ፡ ጊዜ ፤ መፈራት ፡ መወደድ ፡ ባለልሟነት ፡ አለን ። ዕብ ፡ ፲ ፡ ፲፱ና ፡ ፳ ።

፵፩ ፤ ስለዚህም ፡ አንደኛ ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዐሙስ ፡ ማታ ፡ ሥጋዬን ፡ ደሜን ፡ ብሉ ፡ ጠጡ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ሰጠን ፤

ኹለተኛ ፡ ካህናት ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዘወትር ፡ የሚያቀርቡት ፡ ኅብስቱ ፡ ወይኑ ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋው ፡ ደሙ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

፵፪ ፤ ሦስተኛ ፡ በኅብስት ፡ በወይን ፡ መልክ ፡ ቢታይም ፤ ካህናት ፡ የሚሰጡን ፡ እኛም ፡ የምንቀበለው ፡ ኅብስቱ ፡ ወይኑ ፡ በእውነት ፡ የአምላካችን ፡ የአማኑኤል ፡ ሥጋው ፡ ደሙ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናምናለን ።

ከክርስቲያን ፡ ወገን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የክርስቶስን ፡ ሥጋውን ፡ በልቶ ፤ ደሙን ፡ ጠጥቶ ፤ ሕይወቱን ፡ ትንሣኤውን ፡ ሊወርስ ፡ ቢወድ ፤ ልቡናውን ፡ ከቂም ፡ ከበቀል ፤ ሥጋውን ፡ ነፍሱን ፡ ከበደል ፡ ንጹሕ ፡ አድርጎ ፡ ሥጋውን ፡ ይብላ ፤ ደሙን ፡ ይጠጣ ፤ ከኀጢአት ፡ ሳይነጻ ፡ ቢቀበል ፡ ግን ፡ የጌታ ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አላወቀምና ፤ እንደ ፡ ምድራዊ ፡ ምግብ ፡ አቃሎታልና ፡ በኀጢአት ፡ ሳለ ፡ ያለ ፡ ኀፍረት ፡ በድፍረት ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ በመቀበሉ ፡ ፍትሑ ፡ ርቱዐ ፡ ሥላሴ ፡ ይፈርዱበታል ። ፩፡ቆሮ፡ም፡፲፩፡ ቊ፡፳፫-፳፱።

እንዲህ ፡ ማለቴ ፤ ሰው ፡ የሚያውቀው ፡ ኀጢአቱን ፡ ተናዞ፤ ስለማያውቀው ፡ ኀጢአቱ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ እያለ ፡ በንጹሕ ፡ ልብ ፡ እንዲቀርብ ፡ ሳሳስብ ፡ ነውና ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ፡ በእውነተኛ ፡ ልቡናው ፡ በፍጹም ፡ ሃይማኖት ፡ ወደሱ ፡ እንቅረብ ፤ ክርስቶስን ፡ በልተን ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕያዋን ፡ እንኹን ።

፵፫ ፤ አቤቱ ፡ የዘለዓለም ፡ ምግብ ፡ ሊኾነን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ አድርገህ ፡ ሥጋኸን ፡ ደምኸን ፡ ስጠን ። አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ የብሉይ ፡ ኪዳን ፡ መሥዋዕት ፡ ስንት ፡ ዐይነት ፡ ነበር ?
፪ ፤ የእንስሳውና ፡ የእኽሉ ፡ ልዩነት ፡ ምንድነው ?



፫ ፤ መሥዋዕቱ ፡ የምን ፡ የምን ፡ ይባል ፡ ነበር ?
፬ ፤ የቦታው ፡ ልዩነት ፡ ምንድነው ?
፭ ፤ ዘወትር ፡ የሚሠዉት ፡ እነማን ፡ ናቸው ?
፮ ፤ በዓመት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የሚሠዋው ፡ ማነው ?
፯ ፤ ስለ ፡ ወንጌል ፡ መሥዋዕት ፡ ምን ፡ ተጽፎ ፡ ነበረ ?
፰ ፤ የወንጌል ፡ መሥዋዕት ፡ ስንት ፡ ናት ?
፱ ፤ አይሁድ ፡ ክርስቶስን ፡ ለምን ፡ ፈለጉት ?
፲ ፤ አይሁድ ፡ ስለ ፡ መብል ፡ ምን ፡ ተናገሩ ?
፲፩ ፤ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ሰማያዊ ፡ መብል ፡ ምን ፡ አለ ?
፲፪ ፤ አይሁድ ፡ ለምን ፡ አንጐራጐሩ ?
፲፫ ፤ አባቶቻቸው ፡ አመስጋኞች ፡ ነበሩን ?
፲፬ ፤ ክርስቶስ ፡ ሰውን ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚጠራበት ፡ ቃል ፡ የትኛው ፡ ነው ?
፲፭ ፤ ክርስቶስ ፡ በጥምቀቱ ፡ የጀመረውን ፡ መቼ ፡ ጨረሰው ?
፲፮ ፤ በፋሲካው ፡ በግ ፡ ማን ፡ ተተካ ?
፲፯ ፤ በብሉይ ፡ የፋሲካ ፡ ሥርዐት ፡ እንዴት ፡ ነበር ?
፲፰ ፤ ክርስቶስ ፡ በፋሲካ ፡ ራት ፡ ላይ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፲፱ ፤ ክርስቶስ ፡ በፋሲካ ፡ ራት ፡ ላይ ፡ ምን ፡ አዘዘ ?
፳ ፤ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ ምን ፡ ተናገረ ?
፳፩ ፤ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ቍርባን ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፳፪ ፤ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ቍርባን ፡ ምን ፡ አዘዘ ?
፳፫ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የክርስቶስን ፡ መታሰቢያ ፡ ታደርጋለችን ?
፳፬ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ የምታከብርበት ፡ ጸሎት ፡ ምን ፡ ይባላል ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

## ሰባተኛ ፡ ዐምድ ፡ ምስጢረ ፡ ትንሣኤ ።

፩ ፤ ወተንሥአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ዘንቃህ ፡ እምንዋም ። ወከመ ፡ ኀያል ፡ ወኅዳገ ፡ ወይን ። መዝ ፡ ፸፰ ፡ ቊ ፡ ፷፭ ።

እግዚአብሔር ፡ ለባሮቹ ፡ ላገልጋዮቹ ፡ ለነቢያት ፡ ያልገለጠው ፡ ምስጢር ፡ የለምና ፡ ነቢያት ፡ ኹሉ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየተመሩ ፡ ሰው ፡ መኾኑን ፡ ከድንግል ፡ ያለ፡ አባት ፡ መወለዱን ፡ ሞቱን ፡ ትንሣኤውን ፡ ዕርገቱን ፡ ዳግም ፡ ምጽአቱን ፡ ፍጹም ፡ አምላክነቱን ፡ ተናገሩ ። አሞ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቊ ፡ ፯ ።

፪ ፤ ሲናገሩም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ አነጋገር ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምሳሌ ፡ አስረድተዋል ። ትምህርታቸውም ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ተመሥርቶ ፤ በአበው ፡ ተስፋ ፡ ጸንቶ ፤ የሰላም ፡ ንጉሥ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስኪመጣ ፡ ባለተስፋዎችን ፡ በሥንቅነት ፡ ይረዳቸው ፡ ነበር ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፵፱ ። ቊ ፡ ፲ ።

www.ethiopianorthodox.org



ክርስቶስ ፡ እነሣለሁ ፡ እንዳለ ፡ ተነሣ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፪፡፲፱-፳፩፡ማቴ፡ም፡፲፮፡ቊ፡፳፩።ም፡፳፰፡ቊ፡፮፡



፫ ፤ ፍሬ ፡ ነገሩም ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በየገጹ ፡ በየአንቀጹ ፡ ይገኛልና ፡ ልብ
አድርጎ ፡ መመልከት ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ለማስረጃ ፡ ያኽል ፡ ባጭሩ ፡ እንጠቅሳለንና ፡ ማ
ተዋል ፡ ነው ።

፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ለአብርሃም ፡ ከይስሐቅ ፡ ዘር ፡ ይጠራልሀል፡በዚ
ዘር ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ይባረካሉ ፡ ያለውን ፡ ይስሐቅ ፡ ከያዕቆብ ፡ ጋራ ፡ ሲታገል፡አይ
ልጄ ፡ አንበሳ ፡ ነው ፤ ልጄ ፡ እንደ ፡ ደቦል ፡ አንበሳ ፡ ተኛ ፤ አንቀላፋ ፤ ሊቀሰቅሰው ፡ የ
ችል ፡ የለም ፤ በፈቃዱ ፡ ተኛ ፤ በፈቃዱ ፡ ተነሣ ፡ ብሎ ፡ መሰከረ ። ዘፍ ፡ ም፡ ፲፮፡ቊ፡፲፱

፭ ፤ አወጣጡ ፡ ከጥንት ፡ ከዘለዓለም ፡ የኾነ ፡ ማለት ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር፡ያለ፡እና
ከአብ ፡ የተወለደው ፡ አንበሳው ፡ የይስሐቅ ፡ ልጅ ፡ ከጫካው ፡ ወጥቶ ፡ በበረት ፡ ተኛ

እረኞችና ፡ መንጋቸው ፡ ከበቡት ፤ ላሞችና ፡ አህዮች ፡ ዐወቁት ፤ ስለ፡ጌትነቱም
እስትንፋሳቸውን ፡ ገበሩለት ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቊ ፡ ፫ ።

፮ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በአንበሳውና ፡ በላሞች ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ ጥንታዊ ፡ ጠብ
ስለ፡ተሻረ ፤ የሰላም ፡ ኑሮ ፡ ስለ ፡ ተጀመረ ፡ ከኢሳይያስ ፡ ጋራ ፡ ይህን ፡ ድንቅ፡ነገር፡ ያየ
ብዙ ፡ የሰማይ ፡ ጭፍሮች ፤ ሰውን ፡ በመውደድ፡በምድር፡ዕርቅ፡ስለ፡ ተጀመረ ፤ በሰማይ
ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ፡ አሉ ። ኢሳ፡ም፡፲፩ ፡ ቊ፡፮ ። ሉቃ ፡ ም፡፪ ፡ ቊ ፡ ፲፬

፯ ፤ በማርና ፡ በቅቤ ፡ የከበረው ፡ የአንበሳው ፡ እናት ፡ ማርያም ፡ ዝናውን
ሰምታ ፡ ታሪኩን ፡ ዐይታ ፡ ስሙን ፡ አማኑኤል ፡ አለችው ። ትርጓሜውም ፡ እግዚአ
ሔር ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቊ ፡ ፳፫ ። አማኑኤል ፤ ለእናቱ
ለዘመዶቹ ፡ እየታዘዘ ፤ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ በቁመት፡በዕውቀት ፡ አደገ
ሉቃ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቊ ፡ ፶፩ ፡ ፶፪ ።

፰ ፤ አማኑኤል ፡ ዳግመኛ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይባላል ። ለሕዝብና ፡ ለአሕዛ
አለቃ ፡ ሊኾን ፤ ላሞችን ፡ ከአናብስት ፡ ጋራ ፡ ፍየልን ፡ ከነምር ፡ በጎችን ፡ ከጅብ ፡ ከ
ኰላ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ ጥፋት ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ሊጠብቅ ፡ የታጨው ፡ ሕፃኑ ፡ ኢየሱ
በአስተዳደጉ ፡ የተዋበና ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ የመላበት ፡ ኾነ ።

ጭምትና ፡ ጸጥተኛ ፡ ከመኾኑ ፡ የተነሣ ፤ የተቀጠቀጠ ፡ መቃ ፡ አይሰበርበት፡
ነበር ፤ ከአነጋገሩም ፡ ልዝብነት ፡ የሚጤስ ፡ የጧፍ ፡ ኵስታሪ ፡ አይጠፋበትም ፡ ነበ
ኢሳ ፡ ም ፡ ፵፪ ፡ ቊ ፡ ፪—፬ ።

፱ ፤ በንግግሩ ፡ ማማር ፡ በአንደበቱ ፡ ቅልጥፍና ፡ በመልኩ ፡ ውበት ፡ ያዩት ፡
ሙት ፡ ኹሉ ፡ በፍቅሩ ፡ ይማረኩ ፡ ነበር ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡በዕቅመ ፡ አዳ
አካለ፡መጠን ፡ ሲያደርስ ፤ ማለት ፤ ሠላሳ፡ዘመን፡ሲመላው፡በዮርዳኖስ ፡ ሥራውን ፡ በጀመ
ጊዜ ፤ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ገዥ ፡ አባቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፤ የምወደው ፡ ል
ይህ ፡ ነው ፡ እሱን ፡ ስሙት ፡ ብሎ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኾ
መሰከረ ። ማቴ ፡ ም፡፫፡ቊ፡፲፯ ። ዮሐ ፡ ም፡ ፫፡ ቊ፡፳፯ ። እሱን፡ስሙት፡በማለቱ፡ንጉሥ፡
መው፡ንጉሥ ፡ ነው ፡ እንደሚባለው ፡ ሳይኾን ፤ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ፡ነው፡ብሎ፡ ራ
እንደ ፡ መሰከረለት ፤ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ንጉሥ ፡ የአምላክ ፡ ልጅ ፡ አምላክ ፡ ስለ ፡ ኘ

www.ethiopianorthodox.org

በሥጋ ፡ ተገልጦ ፡ መግዛት ፡ ተገልጦ፡መፍረድ፡የሚቻለው፡የሰማይና፡የምድር፡ገዥ፡እሱ ፡ ነውና ፤ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰሙት፡ትእዛዙን፡እንዲቀበሉት ፡ በዐዋጅ ፡ አዘዘ ።

፲ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፤ በሀገር ፡ በመንደር ፡ በከተማ ፡ በገጠር ፡ እየተዘዋወረ፡ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ ነገረ ፡ መንግሥቱን ፡ ሥርዐተ ፡ መንግሥቱን ፡ አስተማረ ።

በፍርዱም ፡ የተሳለ ፡ ኹለት ፡ ልሳን ፡ ሰይፍ ፡ በኾነው ፡ ሥልጣኑ ፤ ከአንደበቱ፡ በሚወጣው ፡ የፍርድ ፡ ቃል ፡ ወድጃለሁ ፡ ንጻ ፤ አንተ ፡ ርኩስ ፡ መንፈስ፡ ውጣ ፤ ኀጢአትኽ ፡ ተሰረየልኽ፤ኀጢአትሽ፡ ተሰረየልሽ ፤ አንተ ፡ ጕልማሳ ፡ ተነሥ ፤ አልዓዛር ! ና ፡ ከመቃብር ፡ ውጣ ፡ እያለ ፡ ደዌን ፡ ሰይጣንን ፡ ኀጢአትን ፡ ሞትን ፡ መቃብርን ፡ ሲኦልን ፡ እንደ ፡ በደላቸው ፡ ቀጣቸው ። ያጠፉትንም ፡ አስከፈላቸው ። ባሕርን ፡ ነፋሳትን ፡ ከትእዛዙ ፡ እንዳያልፉ ፡ ገሠጻቸው ።

፲፩ ፤ እንደ ፡ ሙሴ ፡ በመጋቢነት ፡ ደንብ ፡ ሳይኾን ፤ ከሙሴ ፡ የበለጠ ፡ ባለቤት ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ልግስናው ፡ ወገኖቹን ፡ ረዳቸው ፤ ሕይወት ፡ ለሚፈልጉት ፡ ሕይወቱን ፤ ለኀጢአተኞች ፡ ስርየተ ፡ ኀጢአትን ፤ ለርኁባነ ፡ ሥጋ ፡ ምግብን ፤ ለርኁባነ ፡ ነፍስ ፡ ትምህርትን ፡ ሰጥቶ ፡ አጠገባቸው ። ከሚሹት ፡ ኹሉ ፡ አንዳች፡ ነገር ፡ አላሳጣቸውም ። መዝ ፡ ፸፫ ፡ ቍ ፡ ፳፱ ፡ ፴፩ ። ማር ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፫-፴፪ ። ፪-፬ ። ፰ ፡ ፴፱ ። ሉቃስ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፵፩—፵፰ ።

፲፪ ፤ እነሆ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንወጣለን ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ በኀጢአተኞች ፡ እጅ ፡ ይሰጣል ፤ ይሰቀሉታል ፤ ይገሉታል ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ይነሣል ፡ ብሎ ፡ የሚሄድበትን ፡ አገር ፡ የሚሄድለትን ፡ ግብር ፡ የሚፈጸመውን ፡ ነገር ፡ ካስረዳቸው ፡ በኋላ ፤ አባቶቻቸው ፡ እስራኤል ፡ መናውን ፡ በልተው ፡ በዚያው ፡ ሳያመሰግኑ ፡ በሥጋ ፡ ምኞት ፡ ምክንያት ፡ ክፉ ፡ ፍትወት ፡ እንደ ፡ ተነሣባቸው ፤ ብርቱ ፡ ጥፋት ፡ እንደ ፡ ደረሰባቸው ፡ ስለ፡መብል ፡ በጥብቅ ፡ ይፈልጉት ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ በአባቶቻቸው፡ወጥመድ፡ እንዳይያዙ ፤ ዘለዓለም ፡ ለሚኖረው ፡ ለሕይወት ፡ ምግብ ፡ እንጂ ፤ ለኀላፊው ፡ መብል ፡ እንዳይጥሩ ፡ እንዳይግሩ ፡ እንዳይጨነቁና፡እንዳይቸገሩ ፡ ክፉ ፡ እንዳይሠሩ፡ወደ፡ ፈተና ፡ እንዳይገቡ ፡ የካህናት ፡ አለቃነቱን ፡ ሲፈጽም ፤ የሕይወት ፡ ምግብ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ሰጣቸው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ቍ ፡ ፳፩ ። ፳፯ ፡ ፳፯ ። መዝ ፡ ፸፫ ፡ ፴፩—፴፬ ።

፲፫ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሦስቱ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ጋራ ፡ ጌቴሴማኒ ፡ ወደሚባል ፡ የተክል ፡ ቦታ ፡ ገብቶ ፡ ይጸልይ ፡ ጀመረ ። ወዙ ፡ እንደ ፡ ደም ፡ ነጠብጣብ ፡ ኢየወረደ ፡ ሲሰግድና ፡ ሲጸልይ ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ የሚቻል ፡ ቢኾን ፡ ይች ፡ ጽዋዕ ፡ ከኔ ፡ ትለፍ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የአንተ ፡ ፈቃድ ፡ ከኔ ፡ ፈቃድ ፡ ልዩ ፡ አይደለምና ፡ ፈቃድኽ ፡ ይኹን ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በጸሎቱ ፡ ውስጥ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳፮ ፡ ቍ ፡ ፴—፴፱ ።

፲፬ ፤ የኛን ፡ ደዌ ፡ የወሰደው ፡ የኛን ፡ ሕማም ፡ የተሸከመው ፡ ጌታችን ፡ አምላካችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተክል ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ የፈጸመው ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ በሥጋው ፡ ለሥጋችን ፡ በነፍሱ ፡ ለነፍሳችን ፡ ለመካስ ፡ ካሰበው ፡ የመጀመሪያውን ፡ ክፍል ፡ የያዘ ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፶፫ ፡ ቍ ፡ ፫—፲ ።



፲፭ ፤ በአስተያየቱም ፡ በትምህርቱም ፡ ከኛ ፡ ልዩ ፡ ነው ፤ ሥራው ፡ ከሥራችን
ኑሮው ፡ ከኑሮዋችን ፡ አይስማማም ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ የእግዚአብሔርነት
ዕውቀት ፡ አለኝ ፡ ይላል ፤ የኛን ፡ ሥራ ፡ ይቃወማል ፤ በማንኛውም ፡ እኛን ፡ አይመስ
ምና ፡ ጻድቅ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንግደለው ፡ ብለው ፡ የተማከሩበት ፡ ወደሰ
ከመምጣታቸው ፡ በፊት ፡ በፈቃዱ ፡ ከሥጋው ፡ ሊለያት ፡ ኋላም ፡ አዋሕዶ፡ሊያስነሣት
በሚቻለው ፡ በነፍሱ ፡ ክርስቶስ ፡ የመጀመሪያውን ፡ የሕማም ፡ ጽዋዕ ፡ ጠጣ ። ጥበ
ሰሎ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፪—፳፩ ።

፲፮ ፤ የነፍስ ፡ ሕማም ፡ ፍርሃት ፡ ሁከት ፡ ድንጋጤ ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ አዳ
እግዚአብሔር ፡ ያዘዘውን ፡ በተላለፈ ፡ ጊዜ ፤ ከገነት ፡ ዛፎች ፡ መሓከል ፡ በመደበቅ ፡
ለስ ፡ ቅጠል ፡ ሰፍቶ ፡ ግልድም ፡ አድርጎ ፡ በመታጠቅ ፡ በቃልም ፡ በሥራም ፡ የፈጸ
ቸው ፡ ናቸው ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፳ ።

፲፯ ፤ ስለዚህ ፡ በቀዳማዊ ፡ አዳም ፡ ኀጢአት ፡ የተጐዳው ፡ ዓለም ፡ በዳግማ
አዳም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጽድቅ ፤ ከሕማሙ ፡ ሊድን ፡ ከስብራቱ ፡ ሊጠገን ፡ ክ
ቶስ ፡ ሕማማተ ፡ ነፍስን ፡ ሲፈጽም ፡ ፈራ ፤ ተከዘ ፤ አዘነ ፤ ዕንባውንም ፡ እያፈሰሰ፡ጸለ
ማር ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፡ ፴፪—፵፪ ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ቍ ፡ ፵፩ ፡ ፵፫ ። ዕብ ፡ ም ፡
ቍ ፡ ፯ ።

፲፰ ፤ ክርስቶስ ፡ በጌቴሴማኒ ፡ የተቀበለው ፡ መከራ ፡ ዐይን ፡ ያላየው ፡ ጆ
ያልሰማው ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ ያልታሰበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዳጆቹ ፡ ሊድኑበት ፡ ያ
ጀው ፡ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፤ ዐቢይ ፡ ክቡር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ንባቡን ፡ እንጂ ፤ ትርጓሜው
ሊያውቅ ፡ የሚችል ፡ የለም ።

፲፱ ፤ እባብና ፡ ዲያብሎስ ፡ አዳምና ፡ ሚስቱ ፡ በድቡሽት ፡ ላይ ፡ የሠሩት
የጥል ፡ ግድግዳ ፡ አፍርሶ ፤ ፊት ፡ ተጣቍረው ፡ ተዟዙረው ፡ የነበሩትን ፡ ሰውና ፡ እግዚ
ብሔርን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሊያስተያያቸው ፡ የቻለው ፤ በጌቴሴማኒ ፡ ከሕይወት ፡ ምንጭ
ክርስቶስ ፡ ያለ ፡ መጠን ፡ የወረደው ፡ የደሙ ፡ ወዝ ፡ የፈሰሰው ፡ የዕንባ ፡ ጐርፍ ፡ ነወ

፳ ፤ ከጸሎቱም ፡ በኋላ ፤ ከተክል ፡ ቦታ ፡ ሲወጣ ፡ በሱ ፡ ድካም ፡ ዕረፍት ፡ በሰ
ሕማም፡ ሕይወት ፡ ተሟልቶ ፡ ተሰጥቷቸው ፤ ዐሳብ ፡ ጠፍቶላቸው ፡ ወደ ፡ ፈተና ፡ እ
ትገቡ ፡ ትጉ ፤ ጸልዩ ፡ ቢላቸው ፡ ሳይሰሙ ፡ ያንቀላፉ ፡ የነበሩትን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ
ቀስቅሶ ፡ ጊዜው ፡ ደርሷልና ፡ ተነሡ ፡ ከዚህ ፡ እንሂድ ፡ አላቸው ። ክርስቶስ ፡ ጊዜ
ደረሰ ፡ ሲል ፡ ጨለማ ፡ ወይም ፡ ብርሃን ፡ ሌሊት ፡ ወይም ፡ ቀን ፡ ሊባል ፡ የማይቻለ
እረኛው ፡ ሊሞትበት ፡ በጎቹ ፡ ሊበተኑበት ፡ የተቀጠረው ፡ በሰውና ፡ በእግዚአብሔ
ዘንድ ፡ የታወቀው ፡ ያ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ያመለክት ፡ ነበር ። ዘካ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡

፳፩ ፤ ከተክል ፡ ቦታም ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ አይሁድና ፡ የሮማ ፡ ጭፍሮች ፡ ከ
ቸው ። ክርስቶስም ፡ ማንን ፡ ትሻላችሁ ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ል
የናዝሬቱን ፡ ኢየሱስን ፡ እንሻለን ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፤ ኀይሉን ፡ ምልክት ፡ ከማድረግ ፡ ጋ
እኔ ፡ ነኝ ፡ ሲላቸው ፡ በጀርባቸው ፡ በግንባራቸው ፡ ወደቁ ።

www.ethiopianorthodox.org

፷፪ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እኔን ፡ የምትሹ ፡ ከኾነ ፡ እነዚህን ፡ ተዋቸው ፡ ብሎ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ አስለቅቆ ፡ ሊያስሩት ፡ ሊደበድቡት ፡ ሊገፉት ፡ ሊገርፉት ፡ ሊተፉበት ፡ ሊያፌዙበት፡ራሱን ፡ በዘንግ ፡ ፊቱን ፡ በጥፊ፡ ሊመቱት ፡ ሊሰቅሉት ፡ ሊገድሉት ፡ በጠቅላላው ፡ እሱና ፡ እነሱ ፡ የወደዱትን ፡ ሊያደርጉበት ፡ በፈቃዱ ፡ ራሱን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ቍ ፡ ፬—፲ ።

፷፫ ፤ አይሁድ ፡ ፋኑስና ፡ ፋና ፡ ጐመድና ፡ ሾተል ፡ ይዘው ፡ መጡበት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ በማለቱ ፡ ብቻ ፡ ጠጠር ፡ ሳይጣልባቸው ፤ ጦር ፡ ሳይወረወርባቸው ፡ ቃሉ ፡ ጦር ፡ ኾኖ ፡ ስለ ፡ ወጋቸው ፤ በጀርባቸው ፡ ወደቁ ። በመሣሪያዎቻቸውም ፡ ሳይጠቀሙባቸው ፡ ቀሩ ። ይህ፡ጦሩም ፡ ኀይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክርስቶስ፡የእግዚአብሔር፡ኀይል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሊያምኑ ፤ ክርስቲያን ፡ የክርስቲያን፡ኀይል ፡ በኾነው ፡ መስቀሉ ፡ የጠላትን፡ ኀይል ፡ ይሰብሩ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጣቸው ። ያላመኑ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ስንፍና ፡ በሚቈጥሩት ፡ መከራውም ፡ በጨለማና ፡ በሞት ፡ ጥላ ፡ ለነበሩ ፡ ብርሃን ፡ ወጣላቸው ።

፷፬ ፤ ክርስቶስ ፡ እኔን ፡ የምትሹ ፡ ከኾነ ፡ እነዚህን ፡ ተዋቸው፡ይሂዱ ፡ አለ ። ከምእመናን ፡ አንድ ፡ እንዳይጠፉ ፡ በሚጠባበቀው ፡ በዚህ ፡ ቃል፡የኀጢአት ፡ የሞት ፡ እስረኞች ፡ ተፈቱ ፤ የኀጢአት ፡ የሞት ፡ ማሠሪያን፡የሚፈታ፡እሱ፡ግን፡ስለኛ፡ኀጢአት ፡ ታሰረ ። በእስራትም ፡ የሞትን ፡ እግር ፡ ብረት ፡ ከነቍልፉ፡ ሰበረው፤ማለት፡ፍዳ፡ መርገምን ፡ ሻረ ።

፷፭ ፤ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ክርስቶስና ፡ አይሁድ ፡ በዐሳብም ፡ በሥራም ፡ አልተስማሙም ፡ ነበር ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ግን ፡ የሞት ፡ መንገዶች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኾኑ፤ አይሁድ ፡ ሊገሉት ፡ ሲመጡ ፤ ክርስቶስም ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ሊታረድ ፡ ሲመጣ ፡ በፍኖተ ፡ መስቀል ፡ ተገናኙ ። መገናኘታቸውም ፡ የጻድቃን ፡ ቀጠሮ ፡ በመኾኑ ፤ ክርስቶስ ፡ የአይሁድን ፡ ዐሳብ ፡ ሳይለውጥ ፤ አይሁድም ፡ የክርስቶስን ፡ ፈቃድ ፡ ሳይለውጡ፡ በዐሳብም፡ በሥራም ፡ ተስማምተው ፡ ዋሉ ።

፷፮ ፤ አይሁድ ፡ ክርስቶስን ፡ ይዘው ፡ ከሐና ፡ ወደ ፡ ቀያፋ ፡ ከቀያፋ ፡ ወደ፡ሐና ፡ ቤት ፡ ኢያመላለሱ ፡ ሲገርፉት ፡ ሲያዳፉት ፡ አድረው ፡ ሲነጋ፡ወደ፡መስፍኑ ፡ ቤት ፡ ወሰዱት ። መስፍኑም ፡ ጰንጤናዊ፡ ጲላጦስ ፡ ነበረ ። . . . መስፍኑም ፡ ባደረገው ፡ ምርመራ፡ ኹሉ ፡ ከከሳሾቹም ፡ ኾነ ፡ ከተከሳሹም ፡ ከቶ ፡ ክርስቶስን ፡ ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ ወንጀል፡ አልተገኘም ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ምንም ፡ ክርስቶስ ፡ በሰውነቱ ፡ ኀጢአት ፡ ያልሠራ ፡ በአንደበቱ ፡ ሐሰት ፡ ያልተገኘበት ፡ ቢኾንም ፡ ቅሉ ፤ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ሕዝብና ፡ ስለ፡ አሕዛብ፡ ለውጥ ፡ መድኀኒት ፡ ኾኖ ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ በሰው ፡ ዐሳብ ፡ ሳይኾን ፡ በእግዚአብሔር፡ ዐሳብ ፡ የተቈረጠ ፡ ነበርና ፤ ወንበዴው ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ በርባን ፡ እንዲፈታ ፤ ጻድቅ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲሞት ፤ ሕዝብ ፡ አሕዛብ ፡ ካህናት ፡ ነገሥታት፡ባሉበት ፤ በኢየሩሳሌም ፡ ዐደባባይ ፡ ፍርድ ፡ ተፈጸመ ። በዚህም ፡ ፍርድ ፡ ሰውና ፡ እግዚአብሔር ፡ ተስማሙ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፵፱—፶፪ ።

፷፯ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ሰጪው ፡ ፍርድ ፡ ተቀባዩ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰውነቴን ፡ አሳልፌ ፡ ለሞት ፡ ልሰጣት ፡ በመቃብር ፡ ልጥላት ፡ ዳግመኛም ፡ ላስነሣት ፡



ሥልጣን ፡ አለኝና ፡ በፈቃዴ ፡ ሰውነቴን ፡ ለበጎች ፡ ቤዛ ፡ አድርጌ ፡ ለሕማም ፡ ለሞት ፡ እሰጣታለሁ ፤ ዳግመኛ ፡ አስነሣታለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲፈርድ ፤ በሞቱና ፡ በትንሣኤው ፡ ፍ( ዱን ፡ ሲፈጽም ፡ እግዚአብሔርነትን ፡ ቀምቶ ፡ አልወሰደምና ፡ በጲላጦስ ፡ ዐደባባይ ፡ ፍርድ ፡ ሲቀበል ፡ አስገዳጅ ፡ ሳይኖርበት ፡ በሰውነቱ ፡ የወደደውን ፡ ሊያደርግ ፤ ያሰ( ውን ፡ የተናገረውን ፡ ለመፈጸም ፡ በባሪያው ፡ መልክ ፡ ፊቱን ፡ በጥፊ ፡ ሊመቱትና ፡ ሊተፉበት ፡ ጀርባውን ፡ ለግርፋት ፡ ራሱን ፡ በበትር ፡ ለመመታት ፡ የሾኽ ፡ አክሊል፡ለ( ቀዳጀት ፡ አፉን ፡ ለመራር ፡ ሐሞት ፡ እጁን ፡ እግሩን ፡ ለችንካር ፡ ጐኑን ፡ ለጦር ፡ በ( ቅላላው ፡ ሰውነቱን ፡ ለመስቀልና ፡ ለሕማማት ፡ መስቀል ፡ ለሞት ፡ ለመቃብር ፡ ለት( ሣኤ ፡ ለዕርገት ፡ ለነቢረ ፡ የማን ፡ ሰጠ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፲፬—፲፰ ። ፊል ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፯—፱ ።

፷፰ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ ተናገሩለት ፡ የሰውን ፡ ተስፋ ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ቀይ ፡ ግምጃ ፡ ለብሶ ፤ የሾኽ ፡ አክሊል ፡ ተሸክሞ ፤ ከምርመራ ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ዐደባባይ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፤ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ስቀለው ፡ ስቀለው ፡ እያሉ፡ጮሁ ፡ ጲላጦስም ፡ ገርፎ ፡ ሊሰቅሉት ፡ ስለ ፡ ሰጣቸው ፡ ቀራንዮ ፡ ወደሚባል ፡ ስፍራ ፡ ወ( ደው ፡ በኹለት ፡ ወንበዴዎች ፡ መካከል ፡ ሰቀሉት ።

፷፱ ፤ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተሰቀለበት ፡ ቀኑ ፡ ዐርብ ፡ ጊዜው ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከስድስት ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ዓለም ፡ ጨለማ ፡ ኾነ ። ፀሐይ ፡ ጨለመ ። ጨረቃ፡ደም ፡ ኾነ ። ከዋክብት፡ብርሃናቸውን ፡ ነሱ ። በዘጠኝ ፡ ሰዓትም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተጠማኹ ፡ አለ ፤ ከዚያም ፡ ሐሞት ፡ የተደባለቀበት ፡ መጣጣ ፡ የያዘ ፡ ዕቃ ፡ ነበረ ፤ እዚያ ፡ ከቆሙት ፡ አንዱ ፡ ከመጣጣው ፡ ነገር ፡ በዘንግ ፡ አስሮ ፡ ወደ ፡ አፉ ፡ አቀረበለት ። እሱም ፡ ቀምሶ ፡ አል( ጣም ፡ አለ ፤ ወዲያውኑ ፡ እነሆ ፤ ልጅሽ ፡ ብሎ ፡ ዮሐንስን ፡ ለእመቤታችን ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፤ እነኋት ፡ እናትኽ ፡ ብሎ ፡ እመቤታችንን ፡ ለዮሐንስ ፡ ከሰጠና ፡ ለአመኑት ፡ አምላኪየ ፡ አምላኪየ ፡ ለምን ፡ ተውከኝ ፡ ብሎ ፤ ለካዱት ፡ ለሰቀሉት ፡ በማያውቁት ፡ የማያውቁትን ፡ ባለማወቅ ፡ ይሠራሉና ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ በ( ቸው ፡ ብሎ ፡ ከጸለየላቸው ፡ በኋላ ፤ አባት ፡ ሆይ ፡ ነፍሴን ፡ በአንተ ፡ እጅ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምጥ ፡ ጮሆ ፤ ቅድስት ፡ ነፍሱን ፡ ከቅዱስ ፡ ሥጋው ፡ በገዛ ፡ ሥ( ጣኑ ፡ ለየ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፩—፴ ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ቍ ፡ ፴፬—፵፮ ።

፸ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ምድር ፡ ተናወጠች ፤ አዕባን ፡ ተፈተቱ ፤ መቃብራት፡ተከፈተ( ከቅዱሳን ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ ሙታን ፡ ተነሡ ፤ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ መጋረጃ ፡ ተቀደደ ፡ ማቴ ፡ ም ፡ ፳፯ ፡ ቍ ፡ ፵፯—፶፫ ።

፸፩ ፤ በዚህ ፡ አስደናቂ ፡ ነገር ፡ እናያለን ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ የሚሠሩትን ፡ አያው( ምና ፡ ይቅር ፡ በላቸው ፡ በማለት ፡ ሕዝቡን ፡ ከአባቱ ፡ ሊያስታርቅ ፡ አምላኪየ ፡ አ( ላኪየ ፡ ለምን ፡ ተውኸኝ ፡ በማለት ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ በግ ፡ በእሳትና ፡ በዲን ፡ ጕድጓደ ፡ ወድቆ ፡ ተረስቶ ፡ የነበረ ፡ አዳምን ፡ ለቸር ፡ አባቱ ፡ ሲያሳስብ ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ነፍሴ(

www.ethiopianorthodox.org

በእጅህ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብሎ ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ መኾኑ፡መጠን ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ቅድስት ፡ ነፍሱን ፡ ከቅዱስ ፡ ሥጋው ፡ ሲለይ ፡ ለኛ ፡ ለክርስቲያን ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ክብርና ፡ ጌትነትን ፡ ያስገኘውን ፡ መከራ ፡ መስቀልን ፡ በመቀበሉና ፡ ለኛ ፡ ቤዛ ፡ ኾኖ ፡ በመሞቱ ፤ የመላእክት ፡ ፈጣሪ ፡ በፈቃዱ ፡ ከመላእክት ፡ ያነሰ ፡ ኾኖ ፡ በመገኘቱ ፡ ከሰው ፡ በቀር ፡ ፍጥረቱ ፡ ኹሉ ፡ ተጨነቀ ፤ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ ብርሃናት ፡ ብርሃናቸውን ፡ ነሡ ፤ ጨለማ ፡ ለበሱ ፤ በምድርም ፡ ያሉ ፡ ፍጥረታት ፡ ኹሉ ፡ ተንቀጠቀጡ ፤ መሠረቶቹም ፡ ተናወጡ ። መዝ ፡ ፹ ፡ ቍ ፡ ፰ ።

፴፪ ፤ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም፡ተገልጦ፡በኖረባቸው፡ ፴፫ ፡ ዓመታት ፡ ከአንደበቱ ፡ የገነታ ፡ ድምጥ ፡ እንዳልተሰማበት ፤ የሚጤስ ፡ የጧፍ ፡ ኩስታሪ ፡ እንዳልጠፋበት ፤ የተቀጠቀጠ ፡ መቃ ፡ እንደ ፡ አልተሰበረበት ፡ መጻሕፍ ፡ ቅዱስ ፡ ምስክር ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፶፪ ፡ ቍ፡፪ - ፬ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰማይን ፡ ከነግሡ ፡ ምድርን ፡ ከነልብሱ ፡ የፈጠረ ፡ ኀያል ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥጋ ፡ ኾኖ ፡ ሕማማት ፡ መስቀልን ፡ ፈጽሞ ፡ ነፍሱን፡ከሥጋው ፡ በለየ ፡ ጊዜ ፤ አባት ፡ ሆይ ፡ ነፍሴን ፡ በጅኽ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ድምጡን ፡ ሲያሰማ ፤ ሰማይን ፡ ምድርን ፡ እስከ ፡ ሲኦል ፡ መሠረት፡ድረስ ፡ አናወጣቸው ። በያለበት ፡ የሰማው ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሠም ፡ ቀልጦ ፡ በነፋስ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ አለ ፡ ዛፍ ፡ ተናወጠ ። ድምጡም፡የፀሓይን ፡ የጨረቃን ፡ የከዋክብትን ፡ ብርሃን ፡ አጠፋው ፤ ሻረው ። ዐለቱን ፡ ሠነጠቀው ። ያንቀላፉ ፡ ሙታንን ፡ ከእንቅልፋቸው ፡ ቀሰቀሳቸው ።

፴፫ ፤ ሞትን ፡ መቃብርን ፡ ኀጢአትን ፡ ሰይጣንን ፡ ከሥልጣናቸው ፡ ሻራቸው ። አዳምንና ፡ ልጆቹን ፡ ከእስራታቸው ፡ ፈታቸው ።

፴፬ ፤ ያ ፡ ቃል ፡ ዓለምን ፡ ሲፈጥር ፡ ብርሃን ፡ ይኹን ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፤ ኀላፊ፡ብርሃን፡ ተገለጠ ። ዛሬ ፡ ግን ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ነፍሴን ፡ በጅኽ ፡ እሰጣለሁ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ኀላፊ፡ ብርሃን ፡ ተሽሮ ፡ የማያልፍ ፡ ብርሃን ፡ መጣ ፤ ይህ ፡ ብርሃን ፡ ጨለማ ፡ አይፈራረቀውም ፤ ደፈር ፡ ጠፈር ፡ አይከለክለውም ። ኀልፈት ፡ ውላጤ ፡ አይሰማማውም ። በሰማይ ፡ ላሉ ፡ መላእክት ፡ በመቃብር ፡ ላሉ ፡ ሥጋት ፡ በሲኦል ፡ ላሉ ፡ ነፍሳት ፡ አንድ ፡ ብርሃን ፡ ኾነላቸው ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፪ ።

፴፭ ፤ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ፱ ፡ ሰዓት ፡ ነበር ፤ አዳም ፡ በገነት ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ካሳለፈ ፡ በኋላ፡ የተከለከለውን ፡ በበላበት ፡ ቀን ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ አዳም ፡ ወዴት ፡ አለኽ ፡ የሚል ፡ ፈላጊ ፡ ቃል ፡ በገነት ፡ ተሰምቶ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ያ ፡ ቃል ፡ ሥግው ፡ ኾኖ፡ በአፈሰሰው ፡ ደሙ ፡ አዳምን ፡ ከኀጢአት ፡ ካጠበው ፡ በኋላ ፤ እንደ ፡ ፈለገ ፡ ከእስራቱ ፡ ፈታው ። በኋላም ፡ በ፲፩፡ሰዓት ፡ ወደ ፡ ቀዳማዊ ፡ ርስቱ ፡ መለሰው ። ክርስቲያናዊ ፡ ሆይ ፡ መጽሐፍ፡ ቅዱስ፡ ክርስቶስ ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ የኾነው ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ዐውቀኽ ፡ እነሆ፡ በዳዊት፡ ሀገር ፡ መድኀን ፡ ተወልዶላችኋል ፡ ይህም ፡ ቡሩክ ፡ አምላክ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በልደቱ ፡ ደስታውን ፡ እንዳበሰረ ፤ ክርስቶስ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ሞተ ፡ ብሎ ፡ በአስረዳኽ ፡ ጊዜ ፤ ሞቱ ፡ እንደኛ ፡ ሞት ፡ የነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ መለየት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ጠንቅቀህ ፡



እመን ፡ እንጂ ፤ አምላካችን ፡ ለአንተ ፡ ቤዛ ፡ ኾኖ ፡ መሞቱን ፡ አትጠራጠር ። ሉቃ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ፊል ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፰ ።

፴፮ ፤ በአእምሮ ፡ ያልበሰሉትን ፡ ሰዎች ፡ አምላክ ፡ እንዴት ፡ ይሞታል ፡ እያሉ የሚያሳብሉና ፡ የሚያጠራጥሩ ፡ ወሬኞች ፡ እንዳሉ ፡ ዕወቅ ። ሥግው ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኀያል ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባለማመናቸው ፡ ምክንያት ይጠራጠራሉ ፡ እንጂ ፤ እውነተኛውን ፡ ሃይማኖት ፡ ከተቀበሉና ፡ ከተከተሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ኹሉን ፡ ቻይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ በመሞትና ፡ ባለመሞት ፡ በመተኛትና ፡ በመንቃት መሐከል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምንም ፡ ችግር ፡ እንደማይገጥመው ፡ ቢያውቁ ፡ ቢረዱ ቢያምኑ ፡ ኑሮ ፤ ቃሉን ፡ ላከ ፤ ከሞትም ፡ አዳናቸው ፡ በሚለው ፡ ተስፋ ፡ መሠረት በክርስቶስ ፡ ሞት ፡ ወደ ፡ ዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ በተሸጋገሩበት ፡ ነበር ። መዝ ፡ ፲፯ ቍ ፡ ፳ ።

፴፯ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ተሞትኩ ፡ ሰርዶ ፡ አይብቀል ፡ በሚል ፡ አስተያየት የተመራውን ፡ ከንቱ ፡ ሐሳብ ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ትተኽ ፡ ቢያውቁስ ፡ የምስጋና ፡ ጌታን ባልሰቀሉም ፡ ነበር ፡ ኢያለ ፡ የሚመራኽን ፡ መምህር ፡ ተከትለህ ፡ አምላክህ ፡ ለአንተ ቤዛ ፡ ኾኖ ፡ መሞቱን ፡ አምነኽ ፡ ተጠቀምበት ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፱ ።

፴፰ ፤ እኔም ፡ የምነግርኽ ፡ ይኸው ፡ ነው ፤ አምላካችን ፡ በመስቀል ፡ እንደ ሞተ ፤ በሥጋ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ወርዶ ፡ ሙስና ፡ መቃብርን ፡ አጠፋ ። በነፍስም ፡ ወደ ሲኦል ፡ ወርዶ ፡ በኀጢአታቸው ፡ ታስረው ፡ የነበሩ ፡ ነፍሳትን ፡ ከእስራት ፡ ፈታቸው ነጻነትን ፡ ሰበከላቸው ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፲፰—፳ ።

፴፱ ፤ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ነፍሴን ፡ በፈቃዴ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለሁ ፤ ሰውነቴን በመቃብር ፡ ልጥላት ፡ ላስነሣትም ፡ ሥልጣን ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፤ መግንዝ ፍቱልኝ ፡ መቃብር ፡ ከፈቱልኝ ፡ ሳይል ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ተነሣ ። ዮሐ ፡ ም፡፲፡ ቍ፡፲፰

፵ ፤ ኀያል ፡ አምላክ ፡ ስለ፡ ኾነ ፤ ሞት ፡ ይዞ ፡ ሊያስቀረው ፡ አልቻለም ። ሙስና መቃብርም ፡ አላገኘውም ። በተነሣ ፡ በአርባ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ። በአብ ፡ ቀኝ ተቀመጠ ። ዳግመኛም ፡ በሙታንና ፡ በሕያዋን ፡ ሊፈርድ፡በጌትነት ፡ ይመጣል ። የሐዋ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፱—፲፩ ።

፵፩ ፤ እኛም ፡ በትንሣኤው ፡ ያመነው ፡ ኹሉ ፡ እኔም ፡ ከምድር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ባልኩ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉን ፡ ወደኔ ፡ እስባለሁ ፡ ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ፡፴፪ ። ባለው ፡ ተስፋ፡መሠረት ፡ የክብር ፡ ትንሣኤ ፡ ተነሥተን ፡ በዘለዓለም ፡ ሕይወትና ፡ ክብር ፡ ከሱ ፡ ጋራ፡እንኖር ፡ የሙታንን ፡ ትንሣኤና ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ በሃይማኖት ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ። ፩ ፡ ተሰ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፲፭—፲፯ ።

፵፪ ፤ አምላካችን ፡ በትንሣኤው ፡ እንዲያስነሣን ፡ ፈቃዱ ፡ ይኹንልን ። አሜን

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ትንሣኤ ፡ በመጽሐፍ ፡ ምን ፡ ምስክር ፡ አለ ?

፪ ፤ ጌታ ፡ በተወለደ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ታየ ?

www.ethiopianorthodox.org

፫ ፤ የጌታችን ፡ አስተዳደጉ ፡ እንዴት ፡ ነበር ?
፬ ፤ አማኑኤል ፡ ለናቱና ፡ ለዘመዶቹ ፡ ይታዘዝ ፡ ነበር ፡ ወይ ?
፭ ፤ ክርስቶስ ፡ ዐቅመ ፡ አዳም ፡ አደረሰ ፡ ሲባል ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ?
፮ ፤ ክርስቶስ ፡ በ፴ ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፯ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ምን ፡ ተናገረ ? ቃሉስ ፡ ምን ፡ ያመለክተናል ?
፰ ፤ ክርስቶስ ፡ ከጥምቀት ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፱ ፤ ክርስቶስ ፡ ከጥምቀቱ ፡ በኋላ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ ቈየ ።
፲ ፤ ክርስቶስ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ የሞቱን ፡ ነገር ፡ ይገልጥላቸው ፡ ነበር ፡ ወይ ? ምን ፡ ብሎ ?
፲፩ ፤ ክርስቶስ ፡ በጌቴሴማኒ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፲፪ ፤ ክርስቶስ ፡ ሊይዙት ፡ የመጡትን ፡ ምን ፡ አላቸው ?
፲፫ ፤ ክርስቶስ ፡ ሊሞት ፡ ሲፈረድበት ፡ ኀጢአቱ ፡ ምን ፡ ኖሮዋል ?
፲፬ ፤ ክርስቶስ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ምን ፡ ኀይል ፡ አደረገ ?
፲፭ ፤ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ጠላቶቹ ፡ ምን ፡ አለ ፡ ስለ ፡ ወዳጆቹስ ?
፲፮ ፤ በመስቀል ፡ የሞተው ፡ ምንድነው ፡ እሱስ ፡ ማነው ?
፲፯ ፤ በሞቱ ፡ ሞትን ፡ ያጠፋ ፡ ማነው ?
፲፰ ፤ የሞተው ፡ አልተነሣምን ?
፲፱ ፤ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ያረገው ፡ የት ፡ ደረሰ ?
፳ ፤ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ያረገው ፡ ዳግመኛ ፡ አይመጣ ፡ ይኾን ?
፳፩ ፤ ሙታንና ፡ ሕያዋን ፡ እነማን ፡ ናቸው ?
፳፪ ፤ በሙታንና ፡ በሕያዋን ፡ ላይ ፡ የሚፈርድ ፡ ማነው ?
፳፫ ፤ የሙታንን ፡ ትንሣኤና ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ታምናለህን ?

## ክፍል ፡ ፬ ። አርእስተ ፡ ምግባር ።

### ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

### ኹለቱ ፡ ትእዛዛት ።

፩ ፤ በእላ ፡ ክልኤ ፡ ትእዛዛት ፡ ተሰቅሉ ፡ ኦሪት ፡ ወነቢያት ፡ ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፴፬-፵። በእነዚህ ፡ ኹለት ፡ ትእዛዛት ፡ ኦሪት ፡ ነቢያት ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፤ እነዚህም፡ ሃይማኖትና ፡ ምግባር ፡ ናቸው ።

ሃይማኖት ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽን ፡ በፍጹም ፡ ልብ ፡ በፍጹም ፡ ዐሳብ ፡ በፍጹም ፡ ኀይል ፡ መውደድ ፡ ነው ።

፪ ፤ ምግባር ፡ ወንድምን ፡ እንደ ፡ ራስ ፡ አድርጎ ፡ መውደድ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በእነዚህ ፡ በኹለቱ ፡ በሃይማኖትና ፡ በምግባር ፡ ሰው ፤ አንደኛ ፡ ከፈጣሪው ፡ ኹለተኛ ፡ ከራሱ ፡ ሦስተኛ ፡ ከወገኑ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ ይኖራል ።

፫ ፤ እንግዲህ ፡ የሚቻለውን ፡ ያኽል ፡ በየዐይነቱ ፡ በየስልቱ ፡ የምንሰጠውን ፡ ሃይ ዐሳብ ፡ አንባቢዎች ፡ በፍቅርና ፡ በማስተዋል ፡ ይመለከቱልን ፡ ዘንድ ፡ እያሳሰብን ፡ ሃይ



ማኖት ፡ ምንም ፡ ውስጠ ፡ ምስጢሯ ፡ ለትምህርትና ፡ ለአነጋገር ፡ እንደሚመች ፡ በአ ማድ ፡ የተከፋፈለ ፡ ቢኾን ፡ ዕዝል ፡ ቅጥል ፡ የሌላት ፡ ዘለዓለም ፡ አንዲት ፡ ናት ። ኤፌ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፭ ።

፬ ፤ ምግባር ፡ ግን ፡ እንደበገና ፡ አውታር ፤ እንደ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድምጡም ፡ ልዩ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ስልት ፡ ያለው ፡ ነውና ፡ ብዙት ፡ ልዩነት ፡ አለው ።

ስለዚህ ፡ አሁን ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ ባጭሩ ፡ እናስረዳለን ።

ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ባለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ አስረድተናል ። ከዚህ ፡ የምናሳየው ፡ … ይማኖትን ፡ አንድነት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፭ ፤ ሃይማኖት ፡ ከአብ ፡ ትጀመራለች ፡ ወደ ፡ ወልድ ፡ ታደርሳለች ፡ በመንፈ… ቅዱስም ፡ ትፈጽማለች ፡ ማለት ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡በ… ለት ፡ ትወስናለች ።

ሦስቱ ፡ ስም ፡ አንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ። እግዚአብሔ… ፡ የሦስቱ ፡ ስም ስለ ፡ ኾነ ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል እውነተኛ ፡ ክርስቲያን ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ሦስቱን ፡ አካላት ፡ እግዚአብሔር ፡ እ… ይጠራል ፤ ይኸውም ፡ ባጭሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፮ ፤ ሃይማኖት ፡ ከእኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አታምልክ ፡ በሰማይ ፡ ካሉ ፡ …ሓይ ፡ ከጨረቃ ፡ ከከዋክብት ፡ ከመላእክት ፤ በምድር ፡ ካሉ ፡ ከሰው ፡ ከእንስሳትና ፡ …ራዊት ፡ ከአዕዋፍና ፡ ከዓሣት ፤ ከዕንጨትና ፡ ከደንጊያ ፡ ከመሰላቸውም ፡ ኹሉ ፡ ለአን… ሥዕልና ፡ ምሳሌ ፡ አቁመህ ፡ አዘጋጅተህ ፡ አታምልክ ፡ አትስገድ ፡ በሚል ፡ ትእዛ… ትጀመራለች ፡ ትፈጸማለች ። ዘፀ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ ፡ ፩ — ፫ ።

፯ ፤ በሰማይና ፡ በምድር ፡ በባሕርና ፡ በየብስ ፡ ያለው ፡ የሚታየውና ፡ የማ… …የው ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ፈጣሪውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ብቻ ፡ ያመልካል ፤ ለእግዚአብ… ብቻ ፡ ይገዛል ፤ እሱን ፡ ብቻ ፡ ያመሰግናል ።

፰ ፤ ከአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጥቶ ፡ ዕንጨት ፡ ጠርቦ ፡ ደንጊያ ፡ አለዝ… …ወርቅ ፡ ብር ፡ አቅልጦ ፡ ናስ ፡ መዳብ ፡ ብረት ፡ ገል ፡ ቀጥቅጦ ፡ አፍ ፡ እያለው ፡ የማ… …ገረውን ፤ ዐይን ፡ እያለው ፡ የማያየውን ፤ ጆሮ ፡ እያለው ፡ የማይሰማውን ፤ አፍንጫ… …ለው ፡ የማያሸተውን ፤ እጅ ፡ እያለው ፡ የማይዳስሰውን ፤ እግር ፡ እያለው ፡ የማይሄደ… የሕይወት ፡ እስትንፋስ ፡ የሌለበትን ፡ የእጁን ፡ ሥራ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጣዖትን ፡ የ… …መልክ ፡ ሰው ፤ ከእውነተኛዪቱ ፡ ሃይማኖት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ከአ… …ሃም ፡ በረከት ፡ የወጣ ፡ ነው ። መዝ ፡ ፻፲፭ ፡ ቍ ፡ ፬ - ፰ ።

፱ ፤ ሃይማኖት ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ኹሉን ፡ቻይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የወደደ… …መኾን ፡ የወደደውን ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ በማመን ፡ ይፈጸማል ። እግዚአብ… የወደደውን ፡ መኾን ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ ለሚያምን ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ በአካሉ… በባሕርዩ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ከሦስቱ ፡ አካል ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለየ ፡ አካሉ ፡ በቃልነቱ ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ። በ፴ ፡ ዘመኑ ፡ ተጠመቀ ። በሰውነቱም ፡ ሞቶ ፡ ዓለሙን ፡ አዳነ ። ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ክርስቲያን ፡ ሊመገቡትና ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ሊያገኙበት ፡ ሰጠ ። ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ ተነሣ ። በአርባ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ። በአባቱ ፡ ቀኝ ፡ ተቀመጠ ።

፲ ፤ ዳግመኛ ፡ ለጻድቃን ፡ ሊፈርድላቸው ፡ በኀጥአን ፡ ሊፈርድባቸው ፡ ይመጣል ። አንድነቱን ፡ ሦስትነቱን ፡ ሥጋዌውን ፡ ሞቱን ፡ ትንሣኤውን ፡ ዕርገቱን ፡ ዳግም ፡ ምጽአቱን ፡ ለሚያምን ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የሕይወቱና ፡ የትንሣኤው ፡ ወራሽ ፡ ለመኾን ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፡ ብለው ፡ ቢነግሩት ፡ ቢያስተምሩት ፡ ከባድና ፡ ሩቅ ፡ ነገር ፡ አይሆንበትም ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቊ ፡ ፲፰ - ፳፪ ።

ታላቁ ፡ ሊቅ ፡ መምህር ፡ ሰው ፡ አገኘሁ ፡ የምስጢረ ፡ ሥላሴን ፡ ነገር ፤ ነው ፡ ብሎ ፡ ከማመን ፡ በቀር ፡ እንዴት ፡ ብሎ ፡ ማወላወል ፡ ከጨመሩበት ፡ ሊረዳ ፡ አይቻልም ፡ ብለዋል ።

፲፩ ፤ እንዲሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ የወደደውን ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ ለሚያምን ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ነበረ ፤ ዓለምን ፡ አሳልፎ ፡ ይኖራል ፤ ፍጥረቱን ፡ ኹሉ ፡ ካለመኖር ፡ ወደ ፡ መኖር ፡ አምጥቶ ፡ ፈጠረ ፤ ኋላም ፡ ያሳልፈዋል ፤ እንደ ፡ ልብስ ፡ ይለውጠዋል ፤ እንደ ፡ መጋረጃ ፡ ይጠቀልለዋል ፡ ብለው ፡ ቢነግሩት ፤ ቢያስተምሩት ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ የሚያዳግተው ፡ ነገር ፡ የለም ። መዝ ፡ ፻፪ ፡ ቊ ፡ ፳፭-፳፯ ።

፲፪ ፤ ሃይማኖት ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በስውርና ፡ በግልጥ ፡ ማለት ፡ በሥጋ ፡ ተገልጠ ፡ በነቢያት ፡ በሐዋርያት ፡ በመምህራን ፡ በሊቃውንት ፡ አድሮ ፡ ተሰውሮ ፡ ያስተማረው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ብሉያት ፡ ሐዲሳት ፡ በተባሉት ፡ መዝገቦች ፡ ንቅዝ ፡ የማይበላው ፡ ብል ፡ ዝገት ፡ የማያበላሸው ፡ ሌባ ፡ አጥር ፡ ጥሶ ፡ ግድግዳ ፡ ምሶ ፡ የማይወስደው ፡ ድልብ ፡ ኾኖ ፡ ለሚፈልጉት ፡ ሰዎች ፡ ተዘጋጅቶላቸዋል ።

፲፫ ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ሳያፍር ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ አካሉና ፡ ስለ ፡ ባሕርዩ ፤ ስለ ፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ፡ ሥራው ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የገለጠው ፤ በመምህራን ፡ ያናገረው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢያምን ፤ እግዚአብሔር ፡ ደግሞ ፡ በሰማያዊ ፡ መንግሥቱ ፡ በቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ ፊት ፡ ያንን ፡ ሰው ፤ የሱ ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያምነዋል ፤ የእምነቱንም ፡ ዋጋ ፡ ይሰጠዋል ።

፲፬ ፤ በቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ከሀሊነቱም ፡ የተጻፈውን ፡ እውነተኛ ፡ ምስክር ፡ የማያምነውን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ የሚያፍርበትንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ደግሞ ፡ በሰማያዊ ፡ መንግሥቱ ፡ በክብሩና ፡ በጌትነቱ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤ በአባቱ ፡ ፊትና ፡ በቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ ፊት ፡ ይክደዋል ፡ ያፍርበታል ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲ ።

፲፭ ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በክርስትናው ፡ ምክንያት ፡ ሳይፈጥር ፤ በሃይማኖቱ ፡ ክሕደትን ፡ ሳይጨምር ፤ ያለ ፡ ሃይማኖት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ማሰኘት ፡ የማይቻል ፡ መኾኑን ፡ ዐውቆ ፡ ተጠንቅቆ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በባሕርዩም ፡ ኾነ ፡ በሥራው ፡ ወደረኛ ፡ ጓደኛ ፡ የሌለው ፡ መኾኑን ፡ አምኖ ፤ በፍጹም ፡ ሃይማኖቱ ፡ በበጎ ፡ ምግባሩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ አሰኝቶ ፡ ሊያገለግለው ፡ ይገባዋል ። የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ የምታኽል ፡ ሃይ



ማኖት ፡ ያለችው ፡ እውነተኛ ፡ ክርስቲያን ፡ ሾላውን ፡ ወርካውን ፡ ከበቀለበት ፡ ነቅሎ ፡ ወደ ፡ ወደደው ፡ ሊተክል ፤ ተራራውን ፡ ኮረብታውን ፡ ፈንቅሎ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ሊጥል ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የሚቻለው ፡ ሃይማኖትና ፡ ምግባር ፡ ሲስማሙ ፡ ነው ።

፲፮ ፤ ምግባር ፡ የሌላት ፡ ሃይማኖት ፡ ነፍስ ፡ እንደ ፡ ተለየው ፡ ሬሳ ፡ ናት ። ነፍስ ፡ የተለየው ፡ ሬሳ ፡ መላወስ ፡ መንቀሳቀስ ፡ እንደማይቻለው ፡ ምግባርም ፡ የሌላት ፡ ሃይማኖት ፡ ከቶ ፡ ሰውን ፡ ልትጠቅም ፡ አትችልም ። ያዕ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቊ ፡ ፲፯—፳፮ ።

የእግዚአብሔርን ፡ አምላክነት ፡ ማመን ፡ የግድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ አጋንንትም ፡ ያምናሉ ፤ ስሙም ፡ ሲጠራ ፡ ይደነግጣሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ እምነት ፡ ቅዱሳን ፡ ሊያሰኛቸው ፡ አይችልም ። ክርክሱነትም ፡ አያወጣቸውም ። ሃይማኖት ፡ በምግባር ፡ ፍጹም ፡ ካልሆነ ፡ ሰውን ፡ ሊረዳውና ፡ ሊጠቅመው ፡ እንዳይችል ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይህ ፡ የሥጋ ፡ ዘመድ ፡ ሰይጣን ፡ ያለጾምና ፡ ያለ ፡ ጸሎት ፡ አይወጣም ፡ በማለቱ ፡ አስረድቶናል ።

፲፯ ፤ ወንድሞቻችን ፡ እስኪ ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ አባት ፡ ወደ ፡ አብርሃም ፡ እንመልከት ። አብርሃም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመነ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ከሀገርኽ ፡ ውጣ ፡ ከዘመድኽ ፡ ተለይ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ማሳይህ ፡ አገር ፡ ና ፡ ቢለው ፡ እንደ ፡ ታዘዘ ፡ አደረገ ፤ ልጅህ ፡ ይስሐቅ ፡ ዘር ፡ ይኾንህል ፤ ስምኽም ፡ በሱ ፡ ይጠራል ፡ ካለው ፡ በኋላ ፤ አብርሃም ፡ አብርሃም ፡ የምትወደውን ፡ አንዱን ፡ ልጅኽን ፡ እኔ ፡ በማሳይህ ፡ ተራራ ፡ ሠዋልኝ ፡ ቢለው ፤ መቅረምረም ፡ መሸኮርመም ፡ ማንጐራጐር ፡ መጠራጠር ፡ ሳይኖርበት ፡ እሺ ፡ በጄ ፡ ብሎ ፡ ልጁን ፡ ለመሥዋዕት ፡ አቀረበ ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቊ ፡ ፩ ። ፲፯ ፡ ፲፱—፳፩ ። ፳፪ ፡ ፩—፲ ።

፲፰ ፤ እግዚአብሔር ፡ አብርሃምን ፡ በሀገር ፡ በዘመድ ፡ በአጋር ፡ በእስማኤል ፡ በይስሐቅ ፡ ፍቅር ፡ ፈተነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሃይማኖቱ ፤ በምግባሩ ፡ ተፈጽማ ፡ መልታ ፡ ስለ ፡ ተገኘች ፤ በታዘዘበትም ፡ ኹሉ ፡ የታመነ ፡ ኾኖ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፤ አብርሃም ፡ ከፈተናው ፡ አለፈ ፤ ማመኑም ፡ ጽድቅ ፡ ኾኖ ፡ ተቈጠረለት ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ቊ ፡ ፲፪—፳ ።

፲፱ ፤ ሃይማኖት ፡ ለሥራ ፡ ስለምትረዳ ፤ በጎ ፡ ምግባርም ፡ የሃይማኖትን ፡ ጒድለት ፡ ስለ ፡ ምትመላ ፤ በእኔ ፡ እመኑ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ እመኑ ፤ እኔ ፡ ጌታችሁ ፡ መምህራችሁ ፡ ስኾን ፡ እግራችሁን ፡ እንዳጠብኋችሁ ፤ እናንተም ፡ ለወንድሞቻችሁ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጉ ፡ ብሎ ፡ ያዘዘን ፡ የሃይማኖትና ፡ የምግባር ፡ መምህራችን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ሄደ ፡ ልንሄድ ፤ ማለት ፡ እንደ ፡ ኖረ ፡ ልንኖር ፤ በሥራ ፡ በቃል ፡ እንዳስተማረን ፡ ልንሠራ ፡ እኛ ፡ ኹላችን ፡ ይገባናልና ፡ ሃይማኖትን ፡ ከበጎ ፡ ምግባር ፡ አስማምተን ፡ እንያዝ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቊ ፡ ፩ ። ፲፫ ፡ ፲፪—፲፬ ። ለዚሁ ፡ አምላካችን ፡ በፈቃዱ ፡ ይርዳን ። አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ኹለቱ ፡ ትእዛዛት ፡ ማን ፡ ማን ፡ ናቸው ?
፪ ፤ ሃይማኖትን ፡ ምግባርን ፡ ለይ ?
፫ ፤ ሃይማኖትና ፡ ምግባር ፡ ለሰው ፡ ምን ፡ ይጠቅማሉ ?
፬ ፤ ሃይማኖት ፡ ብዙ ፡ ናትን ፡ ምግባርሳ ?
፭ ፤ ሃይማኖት ፡ በማን ፡ ተጀምራ ፡ በማን ፡ ትፈጸማለች ?
፮ ፤ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ፡ የትኛው ፡ ነው ?
፯ ፤ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ማንን ፡ ያመልካል ?
፰ ፤ እግዚአብሔር ፡ የወደደውን ፡ መኾን ፡ ይችላልን ?
፱ ፤ የወደደውን ፡ ማድረግሳ ?
፲ ፤ ለሚያምን ፡ ሰው ፡ ምን ፡ አለው ?
፲፩ ፤ ሃይማኖትን ፡ ያስተማረ ፡ ማነው ?
፲፪ ፤ በሃይማኖት ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ማፈር ፡ ይገባልን ?
፲፫ ፤ በክርስትና ፡ ምክንያት ፡ መፍጠር ፡ ይገባልን ?
፲፬ ፤ ያለ ፡ ሃይማኖት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ማሰኘት ፡ ይቻላልን ?
፲፭ ፤ ምግባር ፡ የሌላት ፡ ሃይማኖት ፡ ትጠቅማለችን ?
፲፮ ፤ ሃይማኖት ፡ የውድ ፡ ናትን ?
፲፯ ፤ የአጋንንት ፡ እምነት ፡ ቅድስናን ፡ ይሰጣልን ?
፲፰ ፤ አብርሃም ፡ በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ጸደቀ ፡ ታምናላችሁን ?
፲፱ ፤ እግዚአብሔር ፡ አብርሃምን ፡ በምን ፡ በምን ፡ ፈተነው ?
፳ ፤ ሃይማኖቱ ፡ በምግባሩ ፡ አልተፈጸመችምን ?
፳፩ ፤ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ሄደ ፡ ልንሄድ ፡ አይገባንምን ?

### ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

## ት ው ክ ል ት ።

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከሰው ፡ የሚሻው ፡ ሃይማኖትና ፡ መሠረት ፡ ምግባር ፡ ሲኾን ፡ ሃይማኖት ፡ መሠረት ፤ ምግባር ፡ ጣራ ፡ ግድግዳ ፡ ነው ።

፪ ፤ ምግባር ፡ በሃይማኖት ፡ መሠረትነት ፡ ላይ ፡ ሲጸና ፤ ሃይማኖትም ፡ በምግባር ፡ ስትገለጽና ፡ ስትፈጸም ፡ ሃይማኖትንና ፡ ምግባርን ፡ የሚያዋሕድ ፡ ትውክልት ፡ ነው ። የትውክልት ፡ ትርጓሜው ፡ መታመን ፡ ነው ፤ ትውክልት ፡ ከሃይማኖት ፡ ልዩነት ፡ አለው፡ ወደፊት ፡ ተመልከት ።

፫ ፤ ስለ ፡ ትውክልት ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የምናገኘው ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ትእዛዝ ፡ ተወከል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወግበር ፡ ሠናየ ። ወያኀድረከ ፡ ዲበ ፡ ምድር ። ወይሬእየከ ፡ ዲበ ፡ ብዕላ ። በእግዚአብሔር ፡ እመን ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ እንዲህ ፡ ያደረግኽ ፡ እንደ፡



ኾነ ፡ ፀመልካሚቱ ፡ ምድር ፡ ያኖርሀል ፤ በሀብተ ፡ ሥጋ ፡ በሀብተ ፡ ነፍስ ፡ ያበለጥግሀል፡ የሚለው ፡ ነው ። መዝ ፡ ፴፮ ፡ ቍ ፡ ፫ ።

፬ ፤ ይህ ፡ ቃል ፡ ተስፋን ፡ የተደገፈ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ በሃይማኖትና ፡ በምግባር ላይ ፡ እንደ ፡ ማገር ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ጭቃና ፡ እንደ ፡ ሲሚንቶ ፡ ኾኖ ፡ ሃይማኖትንና ምግባርን ፡ ያስማማል ። ምግባርን ፡ ያጸናል ። ሃይማኖትን ፡ ይፈጽማል ። ሃይማኖት መሠረት ፡ ትውክልት ፡ ማገር ፡ ምግባር ፡ ጣራና ፡ ግድግዳ ፡ ሲኾኑ ፡ ልዩነቱን ፡ ባጭሩ በዚህ ፡ መረዳት ፡ ይቻላል ።

፭ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ አምላክነት ፡ ማመን ፡ ግድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ሰው ፡ ብቻ ፡ ሳ ኾን ፡ አጋንንትም ፡ ያምናሉ ። ትውክልት ፡ ግን ፡ ለኹሉ ፡ የሚሰጥ ፡ አይደለም ።

አፍንም ፡ ልብንም ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ አምላክ ፡ በመምራትና በማሰማራት ፡ ሃይማኖትን ፡ ፍጹም ፡ የሚያደርገው ፡ ይህ ፡ ትውክልት ፡ የተባለው፡ ነገር የሚሰጠው ፡ ለፍጹማን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፮ ፤ የሚሠራውም ፡ በፍጹማን ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ማመን ፡ የሚያውቁትን ነገር ፡ አዎን ፡ ማለት ፡ ነው ። ተቃዋሚውም ፡ ክሕደት ፡ ነው ። ይህም ፡ የኾነውን ፡ አ ደለም ፡ ማለት ፡ ነው ።

መታመን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ አደርጋለሁ ፡ አሸንፋለሁ ፡ ብሎ ፡ የራስን ጕልበት ፤ እንደ ፡ ገበሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደርግልኛል ፡ ብሎ ፡ ለቀለብ ፡ የሚኾነውን አውጥቶ ፡ መዝራት ፡ ነው ፤ ተቃዋሚውም ፡ ኑፋቄ ፡ ( ጥርጥር ) ፡ ነው ። ይህም ፡ ራስን ወይም ፡ አምላክን ፡ ይኾን ፡ አይኾን ፡ የማለት ፡ መጠራጠር ፡ ነው ።

፯ ፤ የትውክልትን ፡ ነገር ፡ ለመረዳት ፡ የሚከተለውን ፡ እንመልከት ። ገበሬ ከላይ ፡ ዝናም ፡ ከታች ፡ ጐርፍ ፡ ጭቃ ፡ እያላጋው ፤ ባንድ ፡ ትክሻው ፡ ቀንበር ፡ ባንድ ትከሻው ፡ ዘር ፡ ተሸክሞ ፡ ለእርሻ ፡ ይወጣል ። እያለቀሰ ፡ ይዘራል ። ዘሩን ፡ ከጐተራ እያወጣ ፡ ከጭቃ ፡ ላይ ፡ ሲያፈስ ፤ ዐሳቡ ፡ አጠፌታውን ፡ ከምርቱ ፡ ላይ ፡ ለማግኘት ስለ ፡ ኾነ ፤ ከቶ ፡ ያስቀርብኛል ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አይጠራጠርም ። ስለዚህ ፡ መ መሪያ ፡ በቡቃያው ፡ ቀጥሎ ፡ በአበባው ፡ ኋላም ፡ በሸቱ ፡ በምርቱ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ። መ ፻፳፯ ፡ ፭ ።

፰ ፤ ለትውክልት ፡ ተቃዋሚው ፡ ኑፋቄ ፡ (ጥርጥር) ፡ ነው ። ሰው ፡ አገኛለሁ ፡ በ ለት ፡ አጣለሁ ፡ ማለትን ፡ ከቀላቀለው ፤ በእግዚአብሔር ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ተስፋ ፡ ሊ ጸምለት ፡ አይችልም ።

በትውክልት ፡ ብዙ ፡ ቅዱሳን ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎችን ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ፡ ተጽፏል ። ከእነዚህም ፡ ለማስረጃ ፡ ያኽል ፡ ጥቂቶችን ፡ እንጠቅሳለን ።

፱ ፤ ኤልያስ ፡ እንደኛ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ አምላኩ ፡ በሚያደርገ ቅንአት ፡ ከእኛ ፡ ቀርቶ ፡ በሥራ ፡ ከሚመስሉት ፡ ብልጫ ፡ አለው ።

www.ethiopianorthodox.org

በዘመኑ ፡ የእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ አምልኮት ፡ የሚገባውን ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ፈጣሪ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፤ ዕንጨት ፡ ጠርበው ፡ ድንጊያ ፡ አለዝበው ፡ ሲያመልኩ ፡ አይቶ ፤ ሰማይ ፤ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ እንዳይሰጥ ፤ ምድርም ፡ የዘሩባትን ፡ እንዳታበቅል ፡ የተከሉባትን ፡ እንዳታጸድቅ ፡ የፈጣሪውን ፡ ስም ፡ ጠርቶ ፡ ሰማይን ፡ ምድርን ፡ አወገዘ ።

፲ ፤ ሳይጠራጠር ፡ ባቀረበው ፡ ጸሎቱም ፡ እስራኤል ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ በረኃብ ፡ ተቀጡ ፤ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ በኀጢአታቸው ፡ ስላዘኑና ፡ ስለ ፡ ደነገጡ፤ መሥዋዕት ፡ ሠውቶ ፡ ኀጢአታቸውን ፡ አሰረየላቸው ፡ ዝናምም ፡ እንዲዘንም ፡ ጸለየላቸው ።

፲፩ ፤ የወዳጆቹን ፡ ልመና ፡ እንደ ፡ መልካም ፡ መዐዛ፡ ወዶ፡ የሚቀበል ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በኤልያስ ፡ ጸሎት ፡ ሰማይ ፡ ዝናሙን ፡ እንዲሰጥ ፡ ስለ ፡ አዘዘ ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ ዝናም ፤ ሙሉ ፡ ሰብል ፡ አግኝተው ፡ ደስ ፡ ብሏቸዋል ፡ የተራቡት ፡ ጠግበዋል ። ፩ ፡ ነገ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ቍ ፡ ፩—፲ ። ፲፰ ፡ ፵፪ ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፳፭ ። ያዕ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፲፯—፲፰ ።

፲፪ ፤ አናንያ ፡ አዛርያ ፡ ሚሳኤል ፡ የተባሉት ፡ ሦስቱ ፡ ሰዎችም ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የነበረው ፡ ናቡከደነፆር ፡ በቁመት ፡ ስድሳ ፡ ክንድ ፡ በወርድ ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ጣዖት ፡ አቁሞ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ እንዲሰግድለት ፡ ባዘዘ ፡ ጊዜ ፤ ካንተ ፡ እጅና ፡ ሥልጣን ፡ ከቅጣትህም ፡ ኹሉ ፡ ሊያድነን ፡ የሚቻለው ፡ አምላካችን ፡ በሰማይ ፡ አለ ፤ ስለዚህ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ላቆምከው ፡ ለወርቅ ፡ ምስል ፡ አንሰግድም ፡ ቢሉት ፤ ከነልብሳቸው ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ጣላቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ የታመኑበት ፡ አምላካቸው ፡ ከእሳት ፡ ነበልባል ፡ አዳናቸው ። በዚህም፡ ኀይሉን ፡ ጌትነቱን፡ገለጠ ። ይህንንም ፡ የመሰለ ፡ በመጽሐፍ፡ ቅዱስ ፡ በየገጹ ፡ በያንቀጹ ፡ ይገኛል ። ዳን ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፩—፴ ። እንግዲህ ፡ የትውክልት ፡ ፍጻሜው ፤ የሃይማኖት ፡ ምስክር ፡ የሃይማኖት ፡ መግለጫ ፡ መኾኑ ፡ ነው ። በኀጢአት ፡ ላይ ፡ ክሕደት ፡ ሲጨመር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ እንዲያመጣ ፤ ሃይማኖትም ፡ በትውክልት ፡ ካልተፈጸመ ፤ ማንኛውም ፡ ክርስቲያን ፡ በሃይማኖቱ ፡ ልበ ፡ ሙሉ ፡ መኾኑን ፡ ትቶ ፡ ጥርጣሬ ፡ ከጨመረበት ፤ በሃይማኖቱ ፡ ሊጠቀም ፡ ወይም ፡ ሊረዳ ፡ አይችልም ። ምክንያቱም ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ የጅብድ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ልበ ፡ ሙሉነት፡ከሌለ ፤ የመሣሪያው ፡ ጥሩነት ፡ ብቻ ፡ ወታደርን ፡ ሊያግዘው ፡ ስለማይችል ፡ ነው ።

፲፫ ፤ በዚህ ፡ መሠረት ፡ ትውክልት ፡ ልበ ፡ ሙሉነት ፡ በሥጋዊም ፡ በመንፈሳዊም ፡ ረገድ ፡ ግዳጅ ፡ ፈጻሚ ፡ ናትና ፡ አስቀድሞ ፡ በልበ ፡ ሙሉነት ፡ የታማኝነቱን ፡ ተግባር ፡ ለፈጸመ ፡ አገልጋይ ፡ ዕጽፍ ፡ ድርብ ፡ ዋጋ ፡ አለው ።

፲፬ ፤ እኛ ፡ ኹላችን ፡ ሳንጠራጠር ፡ የምንሻውን ፡ በልበ ፡ ሙሉነት ፡ በሰማይ ፡ ካለው ፡ አባታችን ፡ እንለምን ። ልጁ ፡ ዳቦ ፡ ቢለምነው ፡ ድንጊያ ፤ ዕንቍላል፡ቢለምነው፡ እንቧይ ፤ ዓሣ ፡ ቢለምነው ፡ እባብ ፡ የሚሰጥ ፡ አባት ፡ የለም ። ለባሕርዩ ፡ ጥመት ፡ ክፋት፡



የሚስማማው ፡ ሰው ፡ ለልጁ ፡ መልካም ፡ ማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ ከኾነ ፤ ቸርነት ፡ የባሕርዩ ፡ የኾነው ፡ አምላካችን ፡ አባታችን ፡ የለመንነውን ፡ የፈለግነውን፡አይከለክለንምና ሳንጠራጠር ፡ በሃይማኖት ፡ የምንፈልገውን ፡ ከሱ ፡ እንለምን ። ማቴ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፯—፲፩ ። አባታችን ፡ ሆይ ፡ ፍጹም ፡ ሃይማኖትን ፡ ትሰጠን ፡ ዘንድ ፡ ፈቃድህ ፡ ይሁን አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚሻው ፡ ምንድነው ?
፪ ፤ ሃይማኖትንና ፡ ምግባርን ፡ የሚያዋሕዳቸው ፡ ምንድነው ?
፫ ፤ የትውክልት ፡ ትርጓሜው ፡ ምንድነው ?
፬ ፤ ትውክልት ፡ የሚሰጥ ፡ ለማነው ?
፭ ፤ ስለ ፡ ትውክልት ፡ ማስረጃ ፡ ምን ፡ ታገኛለህ ?
፮ ፤ ገበሬ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ?
፯ ፤ የትውክልት ፡ ተቃዋሚ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፰ ፤ ኤልያስ ፡ ምንድነው ?
፱ ፤ ኤልያስ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፲ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለኤልያስ ፡ ምን ፡ አደረገለት ?
፲፩ ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ የጣላቸው ፡ እነማናቸው ?
፲፪ ፤ ተጠራጣሪ ፡ በሃይማኖቱ ፡ ይጠቀማልን ?
፲፫ ፤ የመሣሪያ ፡ ጥሩነት ፡ ለፈሪ ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ?
፲፬ ፤ ታማኝ ፡ አገልጋይ ፡ ምን ፡ ያገኛል ?
፲፭ ፤ ልጅ ፡ ከአባቱ ፡ የለመነውን ፡ ያጣልን ?
፲፮ ፤ እግዚአብሔርሳ ፡ ለሚለምኑት ፡ የሚሹትን ፡ አይሰጥምን ?

ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

## ፍ ቅ ር ።

፩ ፤ ፍቅር ፡ ኹለት ፡ ወገን ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍቅረ ቢጽ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መውደድ ፡ ወንድምን ፡ መውደድ ፡ ተብሎ ፡ ይለያል ።

፪ ፤ ሰው ፤ አንደኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩን ፤ ኹለተኛ ፡ ባልንጀራውን ፡ ወድሙን ፡ ሊወድ ፡ ይገባል ። ስለ ፡ ፍቅር ፡ ከፈጣሪያችን ፡ የተቀበልነው ፡ ትእዛዝ ፡ ይ ነው ።

፫ ፤ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ቀዳሚት ፡ እምኵሉ ፡ ትእዛዝ ። ስማዕ ፡ እስራኤል ፡ እግዚአ ሔር ፡ አምላክከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ። ወአፍቅሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አ ላክከ ፡ በኵሉ ፡ ልብከ ፤ ወበኵሉ ፡ ነፍስከ ፤ ወበኵሉ ፡ ሕሊናከ ፤ ወበኵሉ ፡ ኀይልከ

www.ethiopianorthodox.org

ዛቲ ፡ ይእቲ፡ ቀዳሚት ፡ ትእዛዝ ። ወካልዕታሂ ፡ እንተ ፡ ትመስላ ፡ አፍቅር፡ ቢጸከ፡ከመ፡ ነፍስከ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ቍ ፡ ፴፬—፵ ።

፬ ፤ የመጀመሪያይቱ ፡ ትእዛዝ ፡ እስራኤል ፡ ስማዕ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ አንድ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ አምላክኽንም ፡ በሙሉ ፡ ልብኽ ፡ በፍጹም ፡ ሰውነትህ ፡ በፍጹም ፡ ዐሳብኽ ፡ በሚቻልህም ፡ ኹሉ ፡ ውደድ ፡ የምትለው ፡ ናት ። ኹለተኛይቱም ፡ ትእዛዝ ፤ የመጀመሪያይቱን ፡ ትእዛዝ ፡ የምትመስላት ፡ የምትተካከላት ፤ ባልንጀራኽን ፡ እንደራስኽ ፡ አድርገኽ ፡ ውደድ ፡ የምትለው ፡ ናት ።

፭ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንዳስረዳነው ፡ መጀመሪያይቱ ፡ ለሃይማኖት ፤ ኹለተኛይቱ ፡ ለምግባር ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ አሳይተናል ። ከዚህም ፡ የመጀመሪያይቱ ፡ ትእዛዝ ፡ የምትጸናበትንና ፡ የምትፈጸምበትን ፤ ኹለተኛይቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ከመጀመሪያይቱ ፡ ጋራ ፡ የምትመሳሰልበትንና ፡ የምትተካከልበትን ፡ እናሳያለን ። ስለዚህ ፡ አንባቢው ፡ ተመልካቹ ፡ አስተውል ።

፮ ፤ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሲወድ ፤ አምልኮቱን ፡ ለሌላ ፡ እንዳይሰጥ ፤ ትእዛዙን ፡ ሕጉን ፡ በሙሉ ፡ ሊጠብቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ እግዚአብሔር ፡ ተርቦ ፡ ሰው፡ሊያበላው ፡ ተጠምቶ ፡ ሊያጠጣው ፡ ተራቁቶ ፡ ሊያለብሰው ፡ እንግድነት ፡ ሊቀበለው ፡ ታስሮ ፡ ሊያስፈታው ፡ ታሞ ፡ ሊጠይቀው ፡ በማንኛውም ፡ ሥራ ፡ ችግር ፡ ኑሮበት ፡ ሊረዳው ፡ አይደለም ። ይህንን ፡ ስል ፡ በማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕራፍ ፡ ፳፭ ፡ ከቍጥር ፡ ፴፮ ፡ እስከ ፡ ፵ ፡ ያለውን ፡ ለጊዜው ፡ አቈይቼ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በሚከተለው ፡ መሥመር ፡ ምስጢሩ ፡ ተጽፎልሃል ።

፯ ፤ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ መውደዱ ፡ ትእዛዙን ፡ መጠበቁ ፡ ነው ። መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብትወዱኝስ ፡ ትእዛዜን ፡ ጠብቁ ፡ ሲለን ፡ እግዚአብሔርን፡ መውደድ ፤ ትእዛዙን ፡ መጠበቅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስረድቶናል ። ስለዚህ ፡ ማንኛውም ፡ ክርስቲያን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሊወድ ፡ ትእዛዙን ፡ ሊጠብቅ ፡ ይገባዋል ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፴፬ና ፡ ፴፭ ። ፲፭ ፡ ፲—፲፫ ።

፰ ፤ እንዲህ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ይባላል ። የእግዚአብሔርንም ፡ ፈቃድ ፡ በመፈጸም ፤ ትእዛዙንም ፡ በመጠበቅ ፡ ዘለዓለማዊውን ፡ ብፅዓን ፡ ሊወርስ ፡ ይችላል ።

፱ ፤ እግዚአብሔር፡ሰውን፡ይወዳል ፡ እንጂ ፤ ከቶ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይወደዋል ፡ ማለት ፡ ውሸት ፡ ነገር ፡ ነው ። ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚወድ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ በአርአያው ፡ በምሳሌው ፡ ፈጥሮ ፡ ከፍጥረት ፡ አክብሮ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሾሞ ፡ በተድላ ፡ ገነት ፡ ቢያኖረው ፤ ፍቅሩን ፡ ባንዲት ፡ ቅጠል ፡ ባለወጠ ፡ ነበር ፤ አምላክነቱንም፡ ሲፈላለግ ፡ ባልተገኘም ፡ ነበር ።

፲ ፤ ሰው ፡ በተሟላለት ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ ለዐይኑና ፡ ለሕሊናው ፡ የራቀውን ፡ ሊወድ ፤ ለራሱም ፡ ወዳጅነት ፡ የለውም ። ለዚህም ፡ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ መልካምና ፡ ክፉ፡ ከምታስታውቀው ፡ ዕንጨት ፡ በበላችሁ ፡ ቀን ፡ ትሞታላችሁና ፡ ከእሱዋ ፡ አትብሉ ፡



ቢላቸው ፤ በፈቃዳቸው ፡ ሞትን ፡ ስበው ፡ ጐትተው ፡ ወዳጅ ፡ ከማድረጋቸውና ፡ ቅጠል፡ በመስረቅ ፡ ሞትን ፡ መቃብርን ፡ በራሳቸው ፡ ከማስፈረዳቸው ፡ ይልቅ ፤ ልጆቻቸው ፡ በስርቆት ፡ በምንዝር ፡ በልዩ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ ሕይወታቸውን ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ ሊያሳልፉ ፡ ሲጣጣሩ ፡ መታየታቸው ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፩—፲፱ ። ጥበበ ፡ ስሎ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፲፫—፲፮ ።

፲፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ እኛን ፡ እንደ ፡ ወደደን ፡ ሳንለምነው፡የሚያሻንን ፡ ዐውቆ ፡ ወዶ ፡ ከመስጠቱም ፡ ሌላ ፤ ስለ ፡ እኛ ፡ ሕይወት ፡ ልጁን ፡ አሳልፎ ፡ ለሕማም ፡ ለሞት ፡ በሰጠው ፡ ጊዜ ፤ እውነትና ፡ ቸርነት ፡ ምስክር ፡ ኾነዋል ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፲፭ - ፲፰ ።

፲፪ ፤ እግዚአብሔር፡ መጀመሪያ ፡ ባደረገልን ፡ ስጦታ ፡ ሳይጠጠት ፤ በበደልነውም፡ በደል ፡ ቅርታ ፡ ሳይገባው ፡ ልጁን ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ለመስቀል ፡ ሞት ፡ አሳልፎ ፡ እስከ ፡ መስጠት ፡ ደርሶ ፡ ፍቅሩን ፡ ከገለጠው ፤ እኛም ፡ ደግሞ ፡ በሙሉ ፡ ልባችን ፡ በፍጹም ፡ ሰውነታችን ፡ በሚቻለን ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንውደደው ፤ የምንወደውም ፡ ከኾነ ፡ ትእዛዙን ፡ እንጠብቅ ፡ ፊልጵ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፰ና ፡ ፱ ።

፲፫ ፤ በሃይማኖት ፡ ክሕደትን ፤ በትውክልት ፡ ኑፋቄን ፡ ሳንቀላቅል ፡ እሱን ፡ ብቻ፡ በማምለክ ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ በመታመን ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ በመውደድ ፡ የመጀመሪያይቱን ፡ ትእዛዝ ፡ ስንፈጽም ፡ በመጀመሪያይቱ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረትነት ፤ እሱዋን ፡ የምትመስ
ላትን ፡ የምትተካከላትን፡ ኹለተኛይቱን፡ ትእዛዝ ፡ እንሥራ ፤ ባልንጀራችንን ፡ እንደራ
ሳችን ፡ አድርገን ፡ እንውደድ ።

፲፬ ፤ ባልንጀራ ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ነው ። ከብዙውም ፡ በቅርቡ ፡ ልናስታውሳቸው
የሚገባ፡ ኹለቱ ፡ በኑሮ ፡ የምትመስል ፡ ሚስትና ፡ የልብ ፡ ባልንጀራ ፤ ሦስተኛውም ፡ በተ
ፈጥሮ ፡ የሚመስል ፡ ድኻ ፡ ናቸው ።

፲፭ ፤ ለወንድ ፡ ባልንጀራው ፡ ሚስቱ ፡ ናት ። ለሴትም፡ባልንጀራዋ፡ባሏ፡ነው ፤ እ
ዚህ ፡ ኹለቱ ፡ ልዩነት ፡ የሌለባቸው ፡ አንድ፡ አካል ፡ ናቸው ። እንዲህ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ኹለ
ቱም ፡ ከወላጆቻቸው ፡ ተለይተው ፡ ተዛምደው ፡ ይኖራሉ ። እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ያደ
ረገውንም ፡ ሰው ፡ ሊለየው ፡ ስለማይችል ፤ ከቶ ፡ ሊለያቸው ፡ የሚችል ፡ የለም ። ማቴ
ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፫ - ፮ ።

፲፮ ፤ ክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንደ ፡ ወደዳት ፡ ሰውም ፡ ሚስቱን ፡ በፍ
ቅር ፡ ያገለግላል ፤ እንደ ፡ ዐይኑ ፡ ብሌኑም ፡ አድርጎ ፡ ይጠብቃታል ፤ ይህን ፡ በቦታው
እናመጣዋለን ። ኤፌ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፳፪ - ፴፫ ።

፲፯ ፤ ሰው ፡ የሰማይ ፡ አባቱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መምሰልና፡በፍቅሩም ፡ አድልዎ
የሌለበት ፡ ፍጹም ፡ መኾን ፡ ስለሚገባው ፡ እግዚአብሔር ፡ አማኒ ፡ መናፍቅ ፡ ኃጥእ
ጻድቅ ፡ ሳይል ፡ ለኹሉ ፡ ዝናምን ፡ እንዲያዘንም ፤ ፀሓይንም ፡ እንዲያወጣ ፤ ሰውም
ኹሉን ፡ መውደድ ፡ ኹሉን ፡ ማክበር ፡ ይገባዋል ። ማቴ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፵፭ - ፵፰ ።

፲፰ ፤ ለክርስቶስ ፡ አካል ፡ ብልት ፡ መኾን ፡ ግን ፤ በደሙ ፡ ለከበሩ ፡ በጸጋው
ለተቀደሱ ፡ ልጅነትን ፡ ለወረሱ ፡ ለክርስቲያን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከጀርባ ፡ ኾድ ፡ ይቀርባል

www.ethiopianorthodox.org

እንደ ፡ ተባለ ፤ ይልቁንም ፡ በሃይማኖት ፡ የሚመስል ፡ ወንድምን ፡ በጣም ፡ መውደድ ፡ በችግሩም ፡ ኹሉ ፡ በጥበቅ ፡ መርዳት ፡ ይገባል ።

፲፱ ፤ ፍቅር ፡ ገንዘብን ፡ በመስጠት ፡ ብቻ ፡ አይፈጸምም ። ሰውነትን ፡ ለወገን ፡ ለውጥ ፡ አድርጎ ፡ በመስጠትም ፡ ነው ፡ እንጂ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ።

፳ ፤ ሰው ፡ የሰውን ፡ የመላእክትንም ፡ ቋንቋ ፡ ቢያውቅ ፡ ተራራ ፡ እስከ ፡ ማፍለስ ፡ የሚያስችል ፡ ሃይማኖት ፡ ቢኖረውም ፤ ገንዘቡን ፡ ለምጽዋት ፡ ሰውነቱን ፡ ለእሳት ፡ ለስለት ፡ ቢሰጥም ፤ ፍቅር ፡ ከሌለበት ፡ ዕውቀቱ ፡ ሃይማኖቱና ፡ ቸርነቱ ፡ ኹሉም ፡ ከንቱ ፡ ናቸው ።

፳፩ ፤ ያለፈውን ፡ የሚመጣውን ፡ የተሰወረውን ፡ የተገለጸውን ፡ ሩቁን ፡ ቅርቡን ፡ ለማወቅ ፡ የሚቻልበት ፡ ፍልስፍና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ቢኖርም ፤ ፍቅር ፡ ከሌለው ፤ እንደ ፡ ከበሮ ፡ እንደ ፡ ነጋሪት ፡ እንደ ፡ ጥሩንባ ፡ እንደ ፡ መለከት ፡ ወይም ፡ እንደሚጮህ ፡ ደወል ፡ ቃጭል ፡ መኾን ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የሚረባው ፡ የሚጠቅመው ፡ ነገር ፡ የለውም ።

፳፪ ፤ ፍቅር ፡ ያስታግሣል ፤ በፍቅር ፡ መቀናናት ፡ የለም ፤ ፍቅር ፡ አያጨካክንም ፤ ፍቅር ፡ አያስቈጣም ፤ ፍቅር ፡ አያስተፋፍርም ፤ ፍቅር ፡ አያስታብይም ፤ ፍቅር ፡ ክፉ ፡ አያሳስብም ፤ ፍቅር ፡ የግል ፡ ጥቅምን ፡ አያሻም ፤ ፍቅር ፡ በእውነትነት ፡ እንጂ ፤ በሐሰት ፡ በግፍም ፡ ደስ ፡ አያሰኝም ።

፳፫ ፤ መጻእያትን ፡ የሚናገር ፡ ብዙ ፡ ቋንቋ ፡ የሚያውቅ ፡ ብዙ ፡ ፍልስፍና ፡ ያለው ፡ ብልኀ ፡ መካሪ ፡ አራቆ ፡ ተናጋሪ ፡ ኹሉም ፡ ያልፋሉ ። ሃይማኖት ፡ ትውክልት ፡ ተፋቅሮ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራሉ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፩ - ፲፫ ።

፳፬ ፤ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ መውደዱ ፡ የሚታወቅ ፤ ወንድሙን ፡ ወዳጅ ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነው ። የሚያየውን ፡ ወንድሙን ፡ የማይወድ ፡ ከኾነ ፡ ግን ፤ የማያየውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እወደዋለሁ ፡ ቢል ፡ እውነተኛ ፡ አያሰኘውም ፡ ፩ ፡ ዮሐ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ።

፳፭ ፤ ስለዚህ ፡ ፍቅር ፡ ከኹሉ ፡ የበለጠ ፡ የበረታና ፡ የጠበቀ ፡ ማሰሪያ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ሰው ፡ ባልንጀራውን ፡ ከወደደው ፤ ሚስቱን ፡ ከብቱን ፡ የሱ ፡ የኹነውን ፡ ኹሉ ፡ አይፈልግበትም ፤ በፍቅር ፡ የሰውና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ተዋሕዶ ፡ ይጸናልና ፡ ሕግን ፡ ኹሉ ፡ በፍቅር ፡ ለመፈጸም ፡ እንዘጋጅ ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፰ - ፲ ።

ፈጣሪያችን ፡ ትእዛዙን ፡ ለመፈጸም ፡ ይርዳን ። አሜን ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ ፍቅር ፡ በስንት ፡ ወገን ፡ ይከፈላል ?
፪ ፤ ስለ ፡ ፍቅር ፡ የመጀመሪያይቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ማነኛይቱ ፡ ናት ?
፫ ፤ ኹለተኛይቱስ ?
፬ ፤ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሲወድ ፤ ሊያበላው ፡ ሊያጠጣው ፡ ነውን ?



፭ ፤ መድኀኒታችን ፡ ስለ ፡ ፍቅር ፡ ምን ፡ አዝዞናል ?
፮ ፤ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሲወድ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፯ ፤ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይወዳል ፡ ሊባል ፡ ይቻላልን ?
፰ ፤ ሰው ፡ ሌላውን ፡ ይወዳልን ? ራሱንስ ?
፱ ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ወደደን ፡ በምን ፡ ይታወቃል ?
፲ ፤ ባልንጀራ ፡ ስንት ፡ ዐይነት ፡ ነው ?
፲፩ ፤ ክርስቶስ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምን ፡ አድርጓል ?
፲፪ ፤ ሰው ፡ ለሚስቱ ፡ ምን ፡ ሊያደርግ ፡ ይገባዋል ?
፲፫ ፤ ፍቅር ፡ በገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ይፈጸማልን ?
፲፬ ፤ ሰው ፡ ፍቅር ፡ ከሌለው ፡ በሥራ ፡ ይጠቀማልን ?
፲፭ ፤ ፍቅር ፡ ክፉዎች ፡ ነገሮችን ፡ ያሳስባልን ?
፲፮ ፤ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ መውደዱ ፡ በምን ፡ ይታወቃል ?

ምዕራፍ ፡ ፶፭ ።

ጸ ሎ ት ።

፩ ፤ ጸሎት ፡ ሰው ፡ ዐሳቡን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚገልጥበት ፤ እግዚአብሔር
የሰውን ፡ ልመና ፡ ተቀብሎ ፡ ፈቃዱን ፡ የሚፈጽምበት ፡ ረቂቅ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከ
ዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ መነጋገር ፡ ይባላል ።

፪ ፤ የጸሎት ፡ መሠረቱ ፡ ሹ ፡ ታገኛላችሁ ፤ ለምኑ ፡ ይሰጣችኋል ፤ ደጅ ፡ ምቱ ፡
ፈትላችኋል ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

፫ ፤ ጸሎት ። ጸሎትና ፡ ምህላ ፡ ተብሎ ፡ በኹለት ፡ ይከፈላል ፤ ጸሎት ፡ ማን፡
ሰው ፡ በቤቱም ፡ ኾነ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ብቻውን ፡ ኾ
ዐሳቡን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚነግርበት ፡ ነው ። ምህላ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ፈውሰ ፡ ሕሙ
ስለ ፡ ሀገርና ፡ ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ሕይወት ፡ ቸነፈር ፡ ወይም ፡ ጦር ፡ ረኃብ ፡ ወይም ፡ ሌ
ብርቱ ፡ አሥጊ ፡ ነገር ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፤ በብዛት ፡ በማኅበር ፡ የሚጸለይ ፡ ጸሎት ፡ ነው ።
ህላ ፡ ጸሎት ፡ ሲጸለይ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ቸነፈር ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፤ አሮን ፡ በሽተኞች
ባንድ ፡ ወገን ፡ ጤነኞችን ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ አድርጎ ፡ የክህነት ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ ማዕጠን
ወርቁን ፡ ይዞ ፡ በራስኽ ፡ የማልክላቸውን ፡ አብርሃምን ፡ ይስሐቅን ፡ ያዕቆብን ፡ ዐስበ
የወገኖችህን ፡ ኀጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ጸለየላቸው ፡ ነው ።

፬ ፤ ዛሬም ፡ ካህናት ፡ ከጠቀስናቸው ፡ አሥጊ ፡ ነገሮች ፡ ማነኛውም ፡ በሀገ
ላይ ፡ ቢመጣ ፤ ወደ ፡ ሀገር ፡ እንዳይገባ ፤ ገብቶ ፡ ቢኾን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ እንዳያመ
የክህነት ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፤ ማዕጠንት ፡ ይዘው ፤ ሥዕለ ፡ ማርያም ፡ መስቀል ፡ አ
በው ፤ ማኅበረ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሰብስበው ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ከድንግ

www.ethiopianorthodox.org

መወለድኽን ፤ በእኛ ፡ ሥጋ ፡ መሰቀል ፡ መሞትኽን ፡ ዐስበኽ ፡ የሕዝብኽን ፡ ኀጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ። እግዚአብሔር ፡ አብን ፤ በተሰቀለ ፡ ልጅኽ ፡ በተቸነከረው ፡ ልጅኽ ፡ ብለኽ ፡ መሰቀሉን ፡ መሞቱን ፡ ዐስበኽ ፡ የሕዝብኽን ፡ ኀጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ፤ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ተመለስልን ፡ እያሉ ፡ በምህላ ፡ ይጸልያሉ ።

፭ ፡ የምህላ ፡ ጸሎት ፡ መዓትን ፡ መቅሠፍትን ፡ ይመልሳል ፤ ጦርን ፡ ቸነፈርን ፡ ያስታግሳል ። መሠረቱም ፡ ጾም ፡ ለዩ ፡ ምህላ ፡ ስበኩ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ነው ። ይህ ፡ ጸሎት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተለመደ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ለጸጥታ ፡ አጠባበቅ ፤ በጦር ፡ ጊዜ ፡ ለመከላከያ ፡ ከምታዘጋጃቸው ፡ መሣሪያዎች ፡ ዋናው ፡ ነው ፤ ስለ ፡ ዚህ ፡ አጥብቀን ፡ ልንከተለው ፡ ይገባናል ።

፮ ፤ የምህላ ፡ ጸሎት ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ከዙፋናቸው ፡ ወርደው ፤ ወንድ ፡ ሙሽራ ፡ ሴት ፡ ሙሽራ ፡ ከጫጉላቸው ፡ ከመጋረጃቸው ፡ ወጥተው ፤ ለምግብ ፡ የደረሱ ፡ ልጆችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከምግብ ፡ ለምግብ ፡ ያልደረሱ ፡ ሕፃናት ፡ ከጡት ፡ ተከልክለው ፤ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ምንጣፍ ፡ ለብሰው ፤ ዐመድ ፡ ነስንሰው ፡ የሚጸልዩት ፡ ከፍተኛ ፡ ጸሎት ፡ ነው ። ኢዩ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፪ - ፲፫ ።

፯ ፡ ጸሎት ፤ ሰው ፡ ብቻውን ፡ ኾኖ ፡ ዐሳቡን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚገልጥበት ፡ መኾኑን ፡ ከላይ ፡ እንዳስረዳነው ፤ በቤት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ይጸለያል ። ለዚህም ፡ ጧት ፡ ፫ ፡ ሰዓት ፡ ፮ ፡ ሰዓት ፡ ፱ ፡ ሰዓት ፡ ሠርክ ፡ (፲፩) ፡ ሰዓት ፡ ንዋም ፡ (መኝታ) ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ የሚባሉ ፡ ሰባት ፡ ጊዜዎች ፡ አሉት ። መዝ ፡ ፻፲፱ ፡ ቍ ፡ ፷፬ ።

፰ ፡ ጸሎት ፡ በሰባቱ ፡ ጊዜያትና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በግልጥ ፡ ይጸለያል ። በቤትና ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ በስውር ፡ ይጸለያል ።

፱ ፤ ከጸሎትም ፤ መዝሙረ ፡ ዳዊትና ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፤ ጸሎትና ፡ ምስጋና ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፤ ክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ ሊጸልያቸው ፡ ይገባል ። የቀረው ፡ ጸሎት ፡ ግን ፤ ሰው ፡ በፈቃዱ ፡ የሚወስነው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ቢጨምር ፡ ቢቀንስ ፡ አይከለከልም ። ማቴ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፭ - ፲፭ ።

፲ ፤ ጸሎት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ መነጋገር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ በስውርም ፡ በግልጥም ፡ የነገሩትን ፡ ተቀብሎ ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ ለሚቻለው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ይቀርባል ። ስለዚህ ፡ ክርስቲያን ፡ ኹሉ ፤ አስፈላጊውን ፡ ኹሉን ፡ ከሚችል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሳይጠራጠር ፡ ቢለምን ፡ ያገኛል ።

፲፩ ፤ ጸሎት ፡ የጊዜ ፡ የቦታ ፡ ልዩነት ፡ እንዳለው ፤ የሥርዐትም ፡ ልዩነት ፡ አለው ። የቦታ ፡ ልዩነት ፡ ምድር ፡ በመላዋ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኾነችና ፡ እግዚአብሔር ፡ የሌለበት ፡ ቦታ ፡ ስለሌለ ፤ ሰው ፡ በሽተኛ ፡ ቢኾን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቢርቀው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መግባት ፡ የሚከለክል ፡ ነገር ፡ ቢያገኘው ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ ኾኖ ፡ ጸሎቱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀርባል ። ጤነኛ ፡ ቢኾንና ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መግባት ፡ የሚከለክል ፡ ነገር ፡ ባይኖርበት ፡ ግን ፤ የፈጣሪው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ በሚ



ጠራባት ፡ ለፈጣሪው ፡ ማደሪያ ፡ ልትኾን ፡ በተለየችውና ፡ በታወቀችው ፡ በቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጸሎቱን ፡ ይፈጽማል ። መዝ ፡ ፷፬ ፡ ቍ ፡ ፩ ። ፻፴፪ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

፲፪ ፤ የጊዜ ፡ ልዩነት ፡ አይሁድ ፡ መድኀኒታችንን ፡ ማታ ፡ በጌቴሴማን ፡ ይዘ
ታል ፤ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ አስረው ፡ ወደ ፡ ቀያፋ ፡ ቤት ፡ ወስደውታል ፤ ጧት ፡ በጲ
ጦስ ፡ ፊት ፡ ለፍርድ ፡ አቁመውታል ፤ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ ልብሱን ፡ ገፈው ፡ ገርፈውታል
በ፮ ፡ ሰዓት ፡ ሰቅለውታል ፤ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ ስለኛ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ሞቷል ፤ ባ፲፩ ፡ ሰዓ
ዮሴፍ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ አውርደውታል ። ስለዚህ ፡ ክርስቲያን ፡ ኹሉ
ስለሱ ፡ የሞተለትን ፡ ክርስቶስን ፡ እያሰበ ፡ በቀን ፡ ፯ ፡ ጊዜ ፡ ሊጸልይ ፤ በቀን ፡ ፯ ፡ ጊ
ሊያመሰግን ፡ ተጽፏል ። ይህ ፡ ጸሎት ፡ ቦታ ፡ አይወሰንበትም ።

፲፫ ፤ የሥርዐት ፡ ልዩነት ፤ የታመመ ፡ ሰው ፡ በዐልጋው ፡ ላይ ፡ ከዐልጋውም ፡ ወርዶ
ተቀምጦ ፡ ይጸልያል ። ጤነኛ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ቆሞ ፡ አንገቱን ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ አዘንብሎ
ዐይኑን ፡ ሸፍኖ ፡ ደረቱን ፡ እየመታ ፤ ዕንባውን ፡ እያፈሰሰ ፤ አቤቱ ፡ ዙፋንህ ፡ ሰማይን
አቅንቶ ፡ ማየት ፡ የማይቻለኝ ፡ ኀጢአተኛ ፡ ነኝ ፡ እያለ ፤ ወይም ፡ መድኀኒታችን ፡ በ
ስቀል ፡ ላይ ፡ ስለኛ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ እንደ ፡ ተሰቀለ ፤ ሰውም ፡ ኹለት ፡ እግሩን ፡ ገጥ
ቆሞ ፡ እጆቹን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ዘርግቶ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አቅንቶ ፡ ሰውነቱን ፡ ከ
ደል ፡ ልቡናውን ፡ ከቂም ፡ ከበቀል ፡ ለይቶ ፤ በሰማይ ፡ የምትኖር ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ ል
ናችንን ፡ ትቀበል ፡ ዘንድ ፡ ፈቃድኽ ፡ ይኹን ፤ እኛም ፡ የበደሉንን ፡ ይቅር ፡ እንድንል
በደላችንን ፡ ይቅር ፡ በለን ፤ የዕለት ፡ የዕለት ፡ ምግባችንን ፡ ስጠን ፤ ከክፉ ፡ ኹሉ ፡ አ
ነን ፡ እንጂ ፤ ወደ ፡ ፈተና ፡ አታግባን ። መንግሥት ፡ ኀይል ፡ ምስጋና ፡ ለዘለዓለም
ያንተ ፡ ናትና ፡ እያለ ፡ ሊጸልይ ፡ ይገባዋል ። ማቴ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፲—፲፫ ። መገ
፻፫ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

፲፬ ፤ ጸሎት ፤ ሥጋዊንና ፡ መንፈሳዊ ፡ ጠላትን ፡ ለማሸነፍ ፡ የምትረዳ ፡ የመ
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰይፍ ፡ ስለ ፡ ኾነች ፤ ጠላታችን ፡ ጋኔን ፡ የሚውጠውን ፡ ሲፈልግ ፡ እንደ
ተራበ ፡ አንበሳ ፡ ይጮሀልና ፡ ፍርሃት ፡ ሽብር ፡ ጥርጥር ፡ በሌለበት ፡ ሃይማኖት ፡ የ
ተን ፤ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰይፍ ፡ ጸሎትን ፡ ይዘን ፡ እንከላከለው ። የሰላም ፡ አምላ
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰይጣንን ፡ ከእግራችን ፡ በታች ፡ ይጣልልን ። አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ጸሎት ፡ ምን ፡ ይባላል ?
፪ ፤ የጸሎት ፡ መሠረቱ ፡ ምንድነው ?
፫ ፤ ጸሎት ፡ በስንት ፡ ዐይነት ፡ ይከፈላል ?
፬ ፤ ጸሎት ፡ ምንድነው ፡ ምህላስ ፡ ምንድነው ?
፭ ፤ አሮን ፡ ምን ፡ አድርጓል ? ካህናት ፡ ምን ፡ ያደርጋሉ ?
፮ ፤ የምህላ ፡ መሠረቱ ፡ ምንድነው ?
፯ ፤ የምህላ ፡ ጸሎት ፡ ጥቅሙ ፡ ምንድነው ?

www.ethiopianorthodox.org

፰ ፤ ምህላ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተመለደ ፡ ነወይ ?
፱ ፤ የምህላ ፡ ጸሎት ፡ ሥርዐቱ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፲ ፤ በጸሎት ፡ የቦታ ፡ ውሳኔ ፡ አለ ፡ ወይ ?
፲፩ ፤ የጸሎት ፡ ጊዜያት ፡ ስንት ፡ ናቸው ?
፲፪ ፤ ጸሎት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፲፫ ፤ በሌላስ ፡ ቦታ ? ጸሎት ፡ በስውር ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ በግልጥ ?
፲፬ ፤ ጸሎት ፡ ለማን ፡ ይቀርባል ?
፲፭ ፤ የጸሎት ፡ የቦታ ፡ ልዩነት ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፲፮ ፤ የጸሎት ፡ የጊዜ ፡ ልዩነት ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፲፯ ፤ ምክንያቱስ ?
፲፰ ፤ የጸሎት ፡ የሥርዐት ፡ ልዩነት ፡ እንዴት ፡ ነው ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፯ ።

## ጾ ም ።

፩ ፤ ጾም ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ በተወሰነ ፡ ባልተወሰነም ፡ ጊዜ ፤ ይፈጸም ፡ ነበር ። በሐዲስ ፡ ኪዳንም ፡ የዘወትርና ፡ የተወሰነ ፡ ጾም ፡ አለ ።

የጾም ፡ መሠረቱ ፤ ቀድሱ ፡ ጾመ ፡ ወሰብኩ ፡ ምህላ ። ኢዮ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፯—፲፰ ። ጾም ፡ ለዩ ፡ ምህላ ፡ ያዙ ፡ የሚለው ፡ ነው ። ጾም ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ክፉ ፡ ከማየት ፡ ዐይንን ፡ ክፉ ፡ ከመስማት ፡ ጆሮን ፡ ክፉ ፡ ከመሥራት ፡ እጅን ፡ ወደ ፡ ኀጢአት ፡ ከመሄድ ፡ እግርን ፡ ክፉ ፡ ከመናገር ፡ መላስን ፡ ክፉ ፡ ከማሰብ ፡ ልብን ፡ መከልከል ፡ ታላቅ ፡ ጾም ፡ ነው ፤ ሥራውም ፡ ከፍጹምነት ፡ በላይ ፡ ነው ።

፪ ፤ ስለዚህ ፡ ቅዱስ ፡ ጾም ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሲያስተምር ፡ ልቡናቸውን ፡ ከክፉ ፡ ዐሳብ ፡ ንጹሕ ፡ ያደረጉ ፡ ሰዎች ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ እነሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያዩታል ፡ ብሎዋል ። ማቴ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፰ ።

፫ ፤ አንደበትን ፡ ክፉ ፡ ከመናገር ፡ መከልከል ፡ ስለሚገባ ፤ ከትእዛዛት ፡ አንዲቱ ፡ ታንሳለች ፤ አንዲቱ ፡ ትበልጣለች ፡ ብሎ ፡ ለሌላው ፡ የሚያስተምር ፡ ራሱም ፡ የሚሠራ ፤ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ታናሽ ፡ ይኾናል ፤ ከትእዛዛት ፡ አንዲቱ ፡ ካንዲቱ ፡ አታንስም ፡ ብሎ ፡ ራሱ ፡ የሚሠራ ፤ ለሌላው ፡ የሚያስተምር ፤ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ታላቅ ፡ ይኾናል ። ማቴ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፲፱ ።

፬ ፤ ከእናንተ ፡ አስቀድሞ ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ በሐሰት ፡ አትማል ፡ ተብሎ ፡ ነበር ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በሰማይ ፡ በምድር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ (ቤተ፡ክርስቲያን) ፡ በራሳችሁም ፡ አትማሉ ፡ ብያችኋለሁ ። ሰማይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዙፋን ፡ ምድርም ፡ መመላለሻው ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ አገሩ ፡ ናትና ፡ ከራስ ፤ ጠጕራችሁም ፡ አንዱን ፡ ነጭ ፡ አንዱን ፡ ጥቍር ፡ ማድረግ ፡ አትችሉምና ። ማቴ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፴፬—፴፯ ።



፭ ፤ እጅን ፡ ክፉ ፡ ከመሥራት ፡ ስለ ፡ መከልከል ፡ ከእናንተ ፡ አስቀድሞ ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ነፍስ ፡ አትግደል ፡ የገደለ ፡ ይፈረድበታል ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ ሰምታችኋል ። እኔ ፡ ግን ፡ ወንድሙን ፡ በከንቱ ፡ የሚያሳዝን ፡ ኃጥእ ፡ ነው ፤ ይፈረድበታል ፡ ብያችኋለሁ ። ቀኝ ፡ እጅኽ ፡ ምክንያተ ፡ ስሕተት ፡ ኾና ፡ ብታስትኽ ፡ ቈርጠኽ ፡ ጣላት ። ዐይንን ፡ ክፉ ፡ ከማየት ፡ ስለ ፡ መከልከል ፡ ቀኝ ፡ ዐይንህ ፡ ምክንያተ ፡ ስሕተት ፡ ኾና ፡ ብታስትኽ ፡ አውጥተኽ ፡ ጣላት ።

፮ ፤ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምናችሁ ፡ ጸንታችሁ ፡ የምትኖሩ ፡ ምእመናን ፡ ራሳችኹን ፡ መርምሩ ፤ ክፉ ፡ ከመስማት ፡ ጆሮዋችሁን ፡ ክፉ ፡ ከማየት ፡ ዐይናችሁን ፡ ከልክሉ ።

፯ ፤ እግርን ፡ ከክፉ ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፤ ቀኝ ፡ እግርኽ ፡ ምክንያተ ፡ ስሕተት ፡ ኾና ፡ የማይገባ ፡ ሥራ ፡ ብታሠራህ ፡ ቈርጠኽ ፡ ጣላት ፤ ሙሉ ፡ ሰውነት ፡ ኖሮህ ፡ በኋላ ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ከምትገባ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አንድ ፡ ዐይን ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ አንድ ፡ እግር ፡ ኾነኽ ፡ ኖረኽ ፡ ኋላ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ብትገባ ፡ ይሻልሀል ፡ ብሎ ፡ አስተምሮናል ። ማቴ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፳፱—፴ ።

፰ ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዐይንኽን ፡ አውጣ ፡ እጅኽን ፡ እግርኽን ፡ ቈርጠኽ ፡ ጣል ፡ ብሎ ፡ ሲያስተምረን ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ዕውር ፡ አንካሳ ፡ ቈራጣ ፡ ኾኖ ፡ በችግር ፡ እንዲኖርና ፡ ሌላውንም ፡ በልመና ፡ እንዲያስቸግር ፡ አይደለምና ፡ የሚመስለው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይህ ፡ የመድኀኒታችን ፡ ትእዛዝ ፡ ሰውነታችንን ፡ በሕግ ፡ በሥርዐት ፡ ሠርተን ፡ ቀጥተን ፡ ወስነን ፡ እንድንኖር ፡ የሚያመለክት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ይህንኑ ፡ ዐውቆ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ ምክንያት ፡ ከመፍጠር ፡ ይጠበቅ ።

፱ ፤ በእውነተኛ ፡ ሕግ፡ጸንቶ፡የሚኖር፤እውነት ፡ ነገርን፡የሚናገር፡ የኀጢአትን፡መንገድ ፡ የሚጠላ ፡ ጉቦ ፡ ከመቀበል ፡ እጁን ፡ ክፉ፡ ከመስማት፡ ጆሮውን ፡ ግፍ ፡ ከማየት ፡ ዐይኑን ፡ የሚከለክል ፤ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚደረግለት ፡ ጽኑእ ፡ ረድኤት ፡ ከመከራው ፡ ኹሉ ፡ ተጠብቆ ፡ ይኖራል ፤ አንደኛው ፡ ጾም ፡ ይህ ፡ ነው ።

፲ ፤ ኹለተኛው፡ ጾም፡ ግን፡ ከምግብ፡ መከልከል፡ ነው፤ ስለዚህ፡ ማንኛውም፡ ጾዋሚ፡ ሰው ፡ እንዳገኘ ፡ ከበላ ፤ እንዳገኘ ፡ ከጠጣ፡ ሰውነቱን፡ ወስኖ ፡ ገቶ፡ መኖር ፡ አይቻለውምና ፡ ለሰውነት ፤ ኀይል ፡ ጽንእ ፡ ልምላሜ ፡ ከሚኾኑት ፡ የምግብ ፡ ዐይነቶች ፡ ተከልክሎ ፡ ሕገ ፡ ጾምን ፡ ይፈጽማል ።

፲፩ ፤ ጾም ፡ ሰው ፡ ከእንስሳት ፡ የሚለይባት ፤ ከመላእክት ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰልባት ፡ ታላቅ ፡ ሚስጢር ፡ ስለ ፡ ኾነች ፤ እንደ፡እንስሳት፡ሰዓት ፡ ጊዜ፡ሳይወስኑ ፡ ከጧት፡እስከ፡ማታ፡ ከመብላትና ፡ ሥጋንም ፡ ለአፈር ፡ ከማስባት ፡ ተከልክሎ ፤ በጸሎት ፡ በትዕግሥት ፡ በኀዘን ፡ በልቅሶ ፡ የሚፈጽማት ፡ ሕግ ፡ ናት ።

፲፪ ፤ ሕግነቷም ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ጾም ፡ ለዩ ፡ ብሎ ፡ ያዘዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ጽድቅ ፡ የሚራቡና ፡ የሚጸሙ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ ሲል ፡ በመጀ

www.ethiopianorthodox.org

መሪያ ፡ ትምህርቱ ፡ በዐዋጅ ፡ ያዘዛት ፡ ያጸናት ፡ የማትለወጥ ፡ የማትናወጽ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ናት ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ድንገተኛ ፡ ደራሽ ፤ እንደ ፡ ጎርፍ ፡ ድንገተኛ ፡ ፈሳሽ ፡ ወይም ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ሕግና ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ተረት ፡ አይደለችም ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

፲፫ ፤ በጾም ፡ ሕግ ፡ የተወሰነና ፡ ያልተወሰነ ፡ የሚል ፡ አከፋፈል ፡ አለበት ። የተወሰነ ፡ ጾም ፡ በክርስቶስ ፡ አምኜ ፡ ጸንቼ ፡ እኖራለሁ ፡ የሚል ፡ ሰው ፤ እሱ ፡ እንደ ፡ ሄደ ፡ ሊሄድ ፡ እሱ ፡ እንደ ፡ ኖረ ፡ ሊኖር ፡ ስለሚገባው ፤ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ እንደ ፡ ጾመ ፡ እኛም ፡ እሱን ፡ መሪ ፡ አብነት ፡ አድርገን ፡ የምንጾመው ፡ ጾም ፡ ነው ። ፩ ፡ የዮሐ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

፲፬ ፡ በሥርዐተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተወሰነ ፡ ጾም ፡ በ፯ ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ። አንደኛው ፡ ዐቢይ ፡ ጾም ፡ ነው ። ይኸውም ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የጾመው ፡ ነው ። ይህ ፡ ጾም ፡ ዐቢይ ፡ ጾም ፡ ጾመ ፡ ኢየሱስ ፡ ሑዳዴ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ማቴ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፩—፲፫ ።

፲፭ ፡ ዐቢይ ፡ ጾም ፡ መባሉ ፡ አንደኛ ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተቀበልንው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ኹለተኛ ፡ የሰው ፡ ድኅነቱ ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ለመፈጸሙ ፡ መታሰቢያ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከሌሎቹ ፡ በበለጠ ፡ ዐምሳ ፡ ዐምስት ፡ ቀን ፡ ስለሚጾምና ፡ በመጨረሻውም ፡ በአክፍሎት ፡ መሠረትነት ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ ስለሚጾም ፡ ነው ።

፲፮ ፤ ከዐሙስ ፡ ማታ ፡ እስከ ፡ እሑድ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ የሚፈጸመው ፡ የአክፍሎት ፡ ጾም ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዐሙስ ፡ ማታ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ በማዕድ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ በአባቱ ፡ መንግሥት ፡ አዲሱን ፡ እስክጠጣው ፡ ድረስ ፡ እንግዲህ ፡ ከዚህ ፡ የወይን ፡ ጭማቂ ፡ አልጠጣም ፡ ሲል ፡ በንግግር ፡ የመሠረተው ፤ በኋላም ፡ እሱ ፡ በመቃብር ፡ እነሱ ፡ በሐዘን ፡ ሦስቱን ፡ ቀን ፡ አሳልፈው ፡ በገሊላ ፡ በትንሣኤው ፡ በተገናኙ ፡ ጊዜ ፤ ልጆቼ ፡ አንዳች ፡ የሚበላ ፡ ነገር ፡ አላችሁን ፡ ብሎ ፡ ጠይቆ ፡ የማር ፡ ወለላ ፡ የተጠበሰ ፡ ዓሣ ፡ አቅርበውለት ፡ በመብላት ፡ የፈጸመው ፡ ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳፮ ፡ ቍ ፡ ፳፱ ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፳፬ ፡ ቍ ፡ ፴—፵፫ ።

፲፯ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ ለለ ፡ ዓመት ፡ ወለለ ፡ መዋዕል ፡ ደንግፃ ፤ ወተከዛ ፤ ዕለተ ፡ ሕማም ፡ እንዘ ፡ ትትሔዘባ ፡ በየዓመቱ ፡ በየዘመኑ ፡ የሞቱን ፡ የሕማሙን ፡ ቀን ፡ እያሰባችሁ ፡ እዘኑ ፡ አልቅሱ ፡ ብሎ ፡ በቃል ፡ ያስተማራትን ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ በቃል ፡ በሥራም ፡ ያስጠናትን ፡ ይህንን ፡ ጾም ፡ አክብራ ፡ ጠብቃ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አለች ፡ ትኖራለች ። ኢሳ ፡ ፴፪ ፡ ቍ ፡ ፱ ።

፲፰ ፤ ኹለተኛ ፤ ጾመ ፡ ድኅነት ፤ ይህ ፡ ጾም ፡ በሳምንት ፡ በሳምንት ፡ የጌታችን ፡ የአምላካችን ፡ የመድኀኒታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሕማሙ ፡ የሞቱ ፡ መታሰቢያ ፡ አድርገን ፡ ረቡዕና ፡ ዐርብ ፡ በተባሉት ፡ ቀኖች ፡ የምንጾመው ፡ ጾም ፡ ነው ።



፲፱ ፤ ይህ ፡ ጾም ፡ ከረቡና ፡ ካርብ ፡ ወጥቶ ፡ ሊሎችን ፡ ዕለታት ፡ አይነካም ፤ ምክ
ያቱም ፡ ረቡዕን ፡ የምንጾምበት ፤ አይሁድ ፡ በሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ በቀያፋ ፡ ቤት ፡ ተሰብ
በው ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ተኣምራት ፡ ያደርጋል ፤ ብንተወው ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ያምን
ታል ፤ ሮማውያን ፡ ደግሞ ፡ መጥተው ፡ አገራችንን ፡ ይወርሱናል ፡ ምን ፡ እናድር
አሉ ።

፳ ፤ ከመካከላቸውም ፡ የካህናቱ ፡ አለቃ ፡ ቀያፋ ፡ የካህናት ፡ አለቃ ፡ ኾኖ ፡ በ
ቀባቱ ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ሕዝብና ፡ ስለ ፡ አሕዛብ ፡ ቤዛ ፡ (ለውጥ) ፡ ኾኖ ፡
ዲሞት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ገልጦለት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ከሚጠፉ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቢሞ
ይሻላል ፡ ብሎ ፡ ቍርጥ ፡ ቃል ፡ በመስጠቱ ፤ በዚሁ ፡ ተስማምተው ፡ ምክረ ፡ ሞቱ
ስለ ፡ ፈጸሙበት ፡ ነው ። የዮሐ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፵፮—፶፫ ።

፳፩ ፤ ዐርብን ፡ የምንጾምበት ፤ ረቡዕ ፡ በአይሁድ ፡ ጉባኤ ፡ ቍርጥ ፡ የሞት ፡ ምክ
የተፈጸመበት ፡ ክርስቶስ ፡ አምላካችን ፡ ዐርብ ፡ ቀን ፡ በካህናት ፡ አለቃ ፡ ሸንጎና ፡ በ
ላጦስ ፡ ዐደባባይ ፡ ይሙት ፡ በቃ ፡ ተፈርዶበት ፡ ለእኛ ፡ ለኀጢአተኞች ፡ ለውጥ ፡ ኾ
ስለ ፡ ሞተልንና ፡ በልደቱ ፡ የጀመረውን ፡ ቸርነት ፡ በሞቱ ፡ ስለ ፡ ፈጸመልን ፡ ነው ። በዚ
ምክንያት ፡ የረቡዕና ፡ ያርብ ፡ ጾም ፡ የድኅነት ፡ ጾም ፡ ይባላል ። ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፶፬ ።

፳፪ ፤ ጻፎችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የኛና ፡
ሐንስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ይጾማሉ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርትህ ፡ ለምን ፡ አይጾሙም ፡ ብለ
ቢጠይቁት ፤ ሙሽራ ፡ ከእነሱ ፡ ጋራ ፡ ሳለ ፡ የሙሽራ ፡ ሚዜዎች ፡ ሊጾሙ ፡ አይችሉ
ነገር ፡ ግን ፡ ሙሽራው ፡ ከእነሱ ፡ የሚለይበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣልና ፡ ማለት ፡ አይሁ
እኔን ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቴ ፡ ለይተው ፡ የሚሰቅሉበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣልና ፡ ያን ፡ ጊ
ይጾማሉ ፡ ብሏቸዋል ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፴፫—፴፭ ።

፳፫ ፤ ስለዚህ ፡ ክርስቲያን ፡ ክርስቶስ ፡ ከሞተበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ራሱ ፡ ሊ
ካህናት ፡ ክርስቶስ ፤ አገልጋዮቹ ፡ ነቢያትና ፡ ሐዋርያት ፡ የፈጸሙትን ፡ የጾም ፡ ሕ
በትሕትና ፡ በመታዘዝ ፡ ያለ ፡ ማንጐራጐር ፡ ይፈጽማሉ ።

፳፬ ፤ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ጾም ፡ ነበር ፤ ጸዋሚዎችም ፡ ፍ
እያደሉ ፡ መማለጃ ፡ እየበሉ ፡ ወንድማቸውን ፡ እየበደሉ ፡ ብድራታቸውን ፡ እየተከ
ያለሚገባ ፡ ይጾሙት ፡ ነበር ፤ ስለዚህም ፡ ጾሙ ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጣቸው ፡ አልቻለም ። አ
ም ፡ ፶፰ ፡ ቍ ፡ ፫—፬ ።

፳፭ ፤ አዲስ ፡ ጨርቅ ፡ ከአሮጌ ፡ ጨርቅ ፡ እንዳይጣፍ ፡ ቢጣፍም ፡ አዲሱ ፡ 
ውን ፡ እንዲጐትተው ፤ መቀደዱም ፡ እየባሰው ፡ እንዲሄድ ፤ የብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ጾም ፡
ርስቲያን ፡ እንዳይገባቸው ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አስረድቷል ። 
ሁም ፡ አዲስ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ በአሮጌ ፡ ዕቃ ፡ እንዳይቀመጥ ፤ ቢቀመጥ ፡ ግን ፡ አ
የወይን ፡ ጠጅ ፡ አሮጌውን ፡ ጋን ፡ ይሰብራዋል ፤ ጠጁም ፡ ይፈሳል ፤ ዕቃውም ፡ ይበላ
እንዲሁ ፤ የሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ጾም ፡ የሙሴ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ነን ፡ ለሚሉ ፡ ለጻፎ
ለፈሪሳውያን ፡ እንደማይስማማ ፡ በግልጥ ፡ ተናግሯል ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፴፮—

www.ethiopianorthodox.org

፹፮ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አዲሱ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ባዲስ ፡ ዕቃ ፡ ይደረጋል ፡ ኹለቱም፡ ይጠባበቃሉ ፡ ብሎ ፤ ያዲሲቱ ፡ ሕግ ፡ የወንጌል ፡ ጾም ፡ ለአዲሶቹ ፡ ምእመናን ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተማረ ። ስለዚህ ፡ ክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ በነበረው፡ ጾም ፡ ፈንታ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሰጠቻቸውን ፡ ሰባቱን ፡ አጽዋም ፡ በሕግ፡ ይጾማሉ። እነዚህም ፡ አንደኛ ፡ ጾመ ፡ ኢየሱስ ፤ ኹለተኛ ፡ ጾመ ፡ ድኅነት ፤ ሦስተኛ፡ ጾመ ፡ ነነዌ ፤ አራተኛ ፡ ጾመ ፡ ሐዋርያት ፡ (ሰኔ) ፤ ዐምስተኛ ፡ ጾመ ፡ ፍልሰታ ፡ (ነሐሴ) ፤ ስድስተኛ ፡ ጾመ ፡ ነቢያት ፡ ገና) ፤ ሰባተኛ ፡ ገሃድ ፡ (ጋድ) ፡ ናቸው ። እነዚህ፡ አጽዋም ፡ በሕግ ፡ የታወቁ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተጠኑ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በግልጥ ፡ ይጾማሉ ።

፹፯ ፤ ከእነዚህ ፡ ሌላ ፡ መብል ፡ ለኾድ ፡ ነው ፡ ያጸናዋል ፤ ኾድም ፡ ለመብል ፡ ነው ፡ ይሸከመዋል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ኹለቱንም ፡ ያሳልፋቸዋል ። መብል ፤ አይረባንም ፡ አይጠቅመንም ፡ ያለውን ፡ ቃል ፤ ያወቁ ፡ የጠበቁ ፡ ፍጹማን ፡ ምእመናን ፤ እንብላ ፡ እንጠጣ ፡ ነገ ፡ እንሞታለን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፤ ነገ ፡ እንሞታለንና ፡ እንጹም ፡ እንጸልይ ፡ በማለት ፡ የሚጾሙት ፡ ጾመ ፡ ፈቃድ ፡ አለ ፤ ይህ ፡ ጾም ፡ በስውር፡ ይጾማል ። ስለዚህም ፡ ጾመ ፡ ፈቃድ ፡ ይባላል ። ጾምን ፡ የሚፈጽሙ ፡ ስለ ፡ ጽድቅ ፡ የሚራቡና ፡ የሚጠሙ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርርቶስ ፡ እንደ ፡ መሰከረላቸው፡ብፁዓን ፡ ናቸው ። ይህ ፡ ብፅዓን ፡ እንዳይቀርብን ፡ እንጹም ፡ እንጸልይ ።

፹፰ ፤ የጾም ፡ ተቃዋሚው ፡ ምክንያት ፡ መፍጠር ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ መድኅኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በምትጾሙበት ፡ ጊዜ ፡ ፊታችሁን ፡ ታጠቡ ፤ ራሳችሁን ፡ ተቀቡ ፡ ብሏል ። ክፉ ፡ ካልሠራን ፡ ሥጋ ፡ ቅቤ ፡ ብንበላ ፡ ወተት ፡ ብንጠጣ ፡ ምን ፡ አለበት ፡ ይላሉ ። ይህ ፡ ምክንያት ፡ ለመፍጠር፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በእውነቱ፡ በልቶ፡ ጠጥቶ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ወስኖ ፡ ገቶ ፡ መኖር ፡ የሚቻል ፡ ኾኖ ፡ አይደለም ። ማቴ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፲፯—፲፰ ።

፹፱ ፡ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የመድኅኒታችን ፡ ንግግር ፡ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፡ መኾኑን ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ። ሰዎች ፡ ሥጋዊ ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ሳይተዉ ፡ በኀጢአት ፡ ላይ ፡ ኀጢአት፡እየሠሩ ፤ በክፋት ፡ ላይ ፡ ክፋትን ፡ እየጨመሩ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ከበደል ፡ ልቡናቸውን ፡ ከቂም ፡ ከበቀል ፡ ሳይከለክሉ ፤ በቁጣና ፡ በማጣት ፡ ምክንያት ፡ የሚፈጽሙትን ፡ ጾም ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አድርገው ፡ እንጾማለን ፡ እንጸልያለን ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ አይሰማንም ፡ ይላሉ ።

፺ ፤ ክርስቶስ ፡ በጾማችሁ ፡ ጊዜ ፡ ፊታችሁን ፡ ታጠቡ ፤ ራሳችሁን ፡ ተቀቡ ፡ ብሏል ፡ ብንበላ ፡ ብንጠጣ ፡ ምን ፡ አለበት ፡ የሚሉትና ፤ ብንጾም ፡ ብንጸልይ ፡ እግዚአብሔር ፡ አይሰማንም ፡ የሚሉት ፡ ኹለቱ ፡ ምክንያቶች ፡ ከእውነት ፡ ውጭ ፡ ናቸው ። እውነትስ ፡ ክርስቶስ ፡ በጾማችሁ ፡ ጊዜ ፡ ፊታችሁን ፡ ታጠቡ ፡ ሲል ፤ እያለቀሳችሁ ፤ ራሳችሁን ፡ ተቀቡ ፡ ሲል ፡ ፍቅርን ፡ ይዛችሁ ፡ ጹሙ ፡ ማለቱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማወቅ ፡ ነው ። አይሰማንም ፡ ለሚሉትም ፡ እግዚአብሔር ፡ በጾማችሁ ፡ ጊዜ ፡ ፈቃዳችሁን ፡ እየፈጸማችሁ ፡



ምኑ ፡ አልሰማኽንም ፡ ትሉኛላችሁ ፤ ሰው ፡ በኀጢአት ፡ ጾም ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ ድር ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ቀለበት ፡ አንገቱን ፡ ቢያቀጥን ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ጾም ፡ አልፈቅደውም ፤ ይስማን ፡ ካላችሁ ፤ ሰውነታችሁን ፡ ከበደል ፡ ልቡናችሁን ፡ ከቂም ፡ ከበቀል ፡ ለይታችሁ፡ ጹሙ ፡ ብሎ ፡ እንዳዘዘ ፡ ማስተዋል ፡ ነው ።

፺፩ ፤ ጾም ፡ እንደ ፡ ምክንያት ፡ ፈጣሪዎች ፡ ወይም ፡ በማጣትና ፡ በቁጣባ ፡ ምክንያት ፡ እንደሚጾሙት ፡ ሰዎች ፡ ዐሳብ ፡ አይደለችምና ፡ ሥርዐቷ ፡ ሰዓቷ ፡ ጥቅሟ ፡ በእውነት ፡ የታወቀላት ፡ በቃልም ፡ ኾነ ፡ በሥራ ፡ አምላካችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሠራት ፡ የፈጸማት ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ያዘዛት ፡ እውነተኛ ፡ ሕግ ፡ መኾኗን ፡ ዐውቀን ፡ ሥጋ ፡ ከቅቤ ፡ ከሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ ከክፉ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ተከልክለን ፡ እንፈጽማት ።

፺፪ ፤ አባታችን ፡ ሆይ ፡ እውነተኛውን ፡ ጾም ፡ እንድትገልጽልን ፤ ለመፈጸም ፡ እንድታበቃን ፤ እንዲሁም ፡ ክፉ ፡ ዐሳብን ፡ የሚፈጥረው ፡ ይህ ፡ የሥጋ ፡ ዘመድ ፡ ያለ ፡ ጾምና ፡ ያለ ፡ ጸሎት ፡ አይወጣምና ፡ በጾምና ፡ በጸሎት ፡ ድል ፡ እንድንነሣው ፡ ታደርገን ፡ ዘንድ ፡ ፈቃድኽ ፡ ይኹን ። አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ጾም ፡ በብሉይና ፡ በሐዲስ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፪ ፤ የጾም ፡ መሠረቱ ፡ ምንድነው ?
፫ ፤ ጾም ፡ ስንት ፡ ዐይነት ፡ ነው ?
፬ ፤ አንደኛው ፡ ጾም ፡ የትኛው ፡ ነው ?
፭ ፤ ክፉ ፡ ሥራን ፡ ስለ ፡ መጾም ፡ ( መከልከል ) ፡ ክርስቶስ ፡ ምን ፡ ብሏል ?
፮ ፤ ስለ ፡ ዐይንና ፡ ስለ ፡ ጆሮ ፡ ስለ ፡ እጅና ፡ ስለ ፡ እግር ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ምንን ፡ ያመለክታል ?
፯ ፤ ኹለተኛው ፡ ጾም ፡ የትኛው ፡ ነው ?
፰ ፤ የጾም ፡ ትርጓሜ ፡ ምንድነው ?
፱ ፤ የኹለተኛው ፡ ጾም ፡ መሠረት ፡ የትኛው ፡ ቃል ፡ ነው ?
፲ ፤ ሰው ፡ በጾም ፡ ማንን ፡ ይመስላል ?
፲፩ ፤ በሕግ ፡ የታወቁ ፡ አጽዋም ፡ ስንት ፡ ናቸው ?
፲፪ ፤ ዐቢይ ፡ ጾምን ፡ ከማን ፡ ተቀበልን ?
፲፫ ፤ ጾመ ፡ ድኅነት ፡ ማለት ፡ ምንድነው ?
፲፬ ፤ ጾመ ፡ ድኅነት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ተጀመረ ?
፲፭ ፤ ፈሪሳውያን ፡ ምን ፡ ጠየቁ ?
፲፮ ፤ ክርስቶስ ፡ ምን ፡ መለሰ ?
፲፯ ፤ ሙሽራውና ፡ ሚዜዎቹ ፡ እነማን ፡ ናቸው ?
፲፰ ፤ አዲሱ ፡ ለአሮጌው ፡ ይስማማዋል ፡ ወይ ?
፲፱ ፤ ሰባቱ ፡ አጽዋም ፡ ማን ፡ ማን ፡ ናቸው ?

www.ethiopianorthodox.org

፳ ፤ ምክንያተኞች ፡ ምን ፡ ይላሉ ?
፳፩ ፤ ኹለቱ ፡ ምክንያተኞች ፡ ማን ፡ ማን ፡ ናቸው ?
፳፪ ፤ የክርስቶስ ፡ ንግግር ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ?
፳፫ ፤ ምክንያተኞች ፡ የሚሉት ፡ እውነት ፡ ነውን ?
፳፬ ፤ ጾም ፡ እንደ ፡ ምክንያተኞች ፡ ዐሳብ ፡ ናትን ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፯ ።

## ም ጽ ዋ ት ።

፩ ፤ ምጽዋት ፡ ሰው ፡ ያለውን ፡ ለሌለው ፡ ድኻ ፡ ወንድሙ ፡ በመትረፍ፡እግዚአብሔርን ፡ የሚመስልባት ፡ ታላቅ ፡ ጸጋ ፡ ናት ። የምጽዋት ፡ መሠረት ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ዕንጀራኽን ፡ ለተራብ ፡ ስጥ ፤ ድኾችን ፡ በቤትኽ ፡ አሳድር ፤ የተራቆተ ፡ ብታይ ፡ አልብሰው ፤ የቤትኽን ፡ ርኁብ ፡ ቸል ፡ አትበል ፡ ሲል ፡ ያዘዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብፁዓን ፡ መሃርያን ፡ እስመ ፡ ሎሙ ፡ ይምህርዎሙ ። ለነሱም ፡ ፍትሑ ፡ ርቱዕ ፡ ( ቅን ፡ ፈራጅ ) ፡ ሥላሴ ፡ ይራሩላቸዋልና ፡ ለሰው ፡ የሚያዝኑ ፡ የሚራሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ በመጀመሪያ ፡ ትምህርቱ ፡ የሰጠው ፡ ዐዋጅ ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፶፰ ፡ ቍ ፡ ፯—፰ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

፪ ፤ ምጽዋት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ምሕረት ፡ (ችሮታ) ፡ ወይም ፡ ርዳታ ፡ ትባላለች ። ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳንለምነው ፡ ከሰጠን ፡ ስጦታና ፡ ዘወትርም ፡ ከሚያደርግልን ፡ አድራጎት ፡ ሌላ ፡ ሰውን ፡ ሊያስበውና ፡ ሊጐበኘው ፡ የማይገባ ፡ ሲኾን ፤ ልጁን ፡ ለውጥ ፡ አድርጎ ፡ እስከ ፡ መስጠት ፡ ደርሶ ፡ ቸርነቱን ፡ ምጽዋት ፡ እንዳደረገልን ፡ ዐስቦ ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ያቅሙን ፡ ያኽል ፡ ለወንድሙ ፡ ምጽዋት ፡ ምሕረት ፡ ሊያደርግ ፡ ይገባዋል ።

፫ ፤ ምጽዋት ፤ የጕልበት ፡ የገንዘብ ፡ የምክር ፡ ተብሎ ፡ በሦስት ፡ ይከፈላል ። የጕልበት ፡ ምጽዋት ፡ ገንዘብ ፡ የሌለው ፡ ድኻ ፡ ከሱ ፡ በታች ፡ የአካል ፡ ድኻዎች፡የኾኑትን ፡ አይቶ ፡ በሚቻለው ፡ ለዕውሩ ፡ መንገድ ፡ በማሳየት ፤ እጅ ፡ እግር ፡ ለሌላቸው ፡ የራቀውን ፡ በማቅረብ ፤ የቀረበውን ፡ በማራቅ ፤ በጠቅላላው ፡ የጕልበት ፡ ርዳታ ፡ በማድረግ ፡ ለዕውሮች ፡ ዐይን ፡ ለአንካሳዎች ፡ እግር ፡ ቢኾናቸው ፤ ሳይለምነው ፡ ሙሉ ፡ አካልን፡ ለሰጠው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በመታዘዝ ፡ የሚያሳየው ፡ ፍጹም ፡ ፍቅር ፡ ነው ፤ በዚህም ፡ የማያልፍ ፡ ዋጋውን ፡ ያገኛል ።

፬ ፤ የገንዘብ ፡ ምጽዋት ፡ ሰው ፡ የሚቻለውን ፡ ያኽል ፡ ከወርቅ ፡ ወይም ፡ ከታላላቅ ፡ ሀብታት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ውሃ ፡ ድረስ ፡ የሚያደርገው ፡ ስጦታ ፡ ነው ። ይህም ፡ ራስ ፡ ዐስቦ ፤ ነዳያን ፡ አሉበት ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ የሚቸግራቸውን ፡ በመስጠት ፡ የጐደለባቸውን ፡ በመሙላት ፤ ወይም ፡ ነዳያን ፡ ከቤት ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በሌላም ፡ ቦታ ፡ ማንኛውንም ፡ ሰው ፡ አግኝተው ፡ የሚቸግራቸውን ፡ ነገር ፡ ቢለምኑ ፡ ይከፍሉኛል ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ባለማድረግ ፡ ባለመበሳጨትና ፡ ባለማንጐራጐር ፡ የሚፈጸም ፡ ነው ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፴ ።



፭ ፤ ለተራብ ፡ ማብላት ፡ ለተጠማ ፡ ማጠጣት ፡ እንግዳ ፡ መቀበል ፡ የተራቈተ ማልበስ ፡ የታሰረ ፡ ማስፈታት ፡ የታመመ ፡ መጐብኘት ፡ ምጽዋትን ፡ ፍጹም ፡ ያደር ታል ። እነዚህ ፡ ሰባቱ ፡ ነገሮች ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ የፍርድ ፡ መቀበያ ኾነው ፡ ይጠበቃሉ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳፭ ፡ ቍ ፡ ፴፩—፵፮ ።

፮ ፤ ምጽዋት ፤ መጀመሪያዋም ፡ መጨረሻዋም ፡ ርኅራኄ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ለሚ ራት ፡ ኹሉ ፡ በአርኣያውና ፡ በምሳሌው ፡ የፈጠረው ፡ እግዚአብሔርን ፡ መምሰልን ፡ ት ጠዋለች ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፤ ዋጋ ፡ አገኝበታለሁ ፡ እጠቀምበታለሁ ፡ ብድሬን እቀበልበታለሁ ፡ ሳይል ፤ ታናሽና ፡ ታላቅ ፡ ሳይመርጥ ፤ ሃይማኖትን ፡ ልጅነትን ፡ ሥ ውን ፡ ደሙን ፡ ተስፋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በጠቅላላው ፡ መልካሙን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ለፍጥረቱ ፡ እንዲሰጥ ፡ አማኒ ፡ መናፍቅ ፡ ኃጥእ ፡ ጻድቅ ፡ ሳይለይ ፡ ለኹሉ ፡ ዝናምን ፡ እ ዲያዘንም ፤ ክፉና ፡ መልካም ፡ ሳይለይ ፡ ለኹሉ ፡ ፀሓይን ፡ እንዲያወጣ ፤ እንዲሁ ፡ ሰው በምጽዋት ፤ ባዕድ ፡ ዘመድ ፡ ጠላት ፡ ወዳጅ ፡ አማኒ ፡ መናፍቅ ፡ ኃጥእ ፡ ጻድቅ ፡ ሳይለይ ሥራውን ፡ ቢፈጽም ፤ ኹሉን ፡ በመውደድ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይመስለዋል ማቴ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፵፭—፵፰ ።

፯ ፤ የተራብ ፡ ማብላት ፤ የተጠማ ፡ ማጠጣት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ከደሙ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ አብሮ ፡ የተፈጠረ ፡ እንጂ ፤ በእውነቱ ፡ በትምህርት ፡ ጥናት የተገኘ ፡ አይመስልም ። ይኸውም ፡ ከነገሥታት ፡ ከመኳንንት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሙ ተኛ ፡ ( የቀን ፡ ሠራተኛ ) ፡ ድረስ ፡ ከዕለት ፡ ራቱ ፡ ቈርሶ ፡ እንዳቅሙ ፡ ለድኾች ከሚሰጠው ፡ የዕለት ፡ ስጦታ ፡ ሌላ ፤ በሳምንት ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ የጌታችን ፡ የኢ ሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የትንሣኤውን ፡ መታሰቢያ ፡ በማድረግ ፤ በሰንበቴ ፡ ቤት ፡ በወር በዓመት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የእመቤታችንን ፡ የድንግል ፡ ማርያምን ፡ የነቢያት ፡ የሐ ርያትን ፡ የጻድቃን ፡ የሰማዕታትን ፡ መታሰቢያ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ በዝክር ፡ በማ ኅበር ፡ የሚፈጽመው ፡ የምጽዋት ፡ ሥራ ፡ ለተመልካቹ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ አስደናቂ ነው ።

፰ ፤ በጐጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የሚኖር ፡ ሕዝብ ፡ የምጽዋትን ፡ ነገር ፡ መም ራንን ፡ ሳያደክም ፡ በእናት ፡ በአባቱ ፡ መምህርነት ፡ ብቻ ፡ ስለሚያጠናው ፤ ልማዳቸ ንም ፡ ከርስታቸው ፡ ጋራ ፡ ስለሚወርሰው ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እንዳቅሙ ፡ በሳምንት ፡ በሳ ንት ፡ ዐርብ ፡ ዐርብ ፡ ቅዳሜና ፡ እሑድ ፤ በወር ፡ በወርም ፡ የጌታችንን ፡ የእመቤታችንን የቅዱሳንንም ፡ መታሰቢያ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነት ፡ የቅ ሳንን ፡ አማላጅነት ፡ በመታመን ፤ ላንዳንድ ፡ ድኻ ፡ የሚሰጥ ፡ ድርጎ ፡ አለ ። ስጦታውም ቢጨምር ፡ እንጂ ፤ ከአንድ ፡ ዕንጀራ ፡ ያነሰ ፡ አይኾንም ። የእግዚአብሔርም ፡ ገንዘብ ስለ ፡ ኾነ ፤ ስሙ ፡ የመድኀኔ ፡ ዓለም ፡ ዕንጀራ ፡ የሰንበት ፡ ዕንጀራ ፡ የማርያም ፡ ዕንጀራ በጠቅላላውም ፡ የበዓላት ፡ ዕንጀራ ፡ ይባላል ።

፱ ፤ በምጽዋቱም ፡ ጊዜ ፡ ዝክርም ፡ ኾነ ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰዓት ፡ መ ሰቢያው ፡ የሚደረገው ፡ በጌታ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ሰጪዎቹ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር

www.ethiopianorthodox.org

ስለ ፡ ሥላሴ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ መድኀኔ ፡ ዓለም ፡ ወይም ፡ በእንተ ፡ ተዝ
ካረ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ በእንተ ፡ ተዝካረ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክር
ስቶስ ፤ በእንተ ፡ ተዝካረ ፡ መስቀሉ ፡ ለመድኀኔ ፡ ዓለም ፡ እያሉ ፡ ያላቸውን ፡ ሲሰጡ ፤
ድኾቹም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልን ፤ መድኀኔ ፡ ዓለም ፡ ይስጥልን ፡ ብለው ፡ ይቀበሏ
ቸዋል ። መታሰቢያው ፡ በእመቤታችን ፡ ወይም ፡ በቅዱሳን ፡ ስም ፡ ቢኾን ፡ ምስጉን ፡
እግዚአብሔር ፡ በእመቤታችንና ፡ በቅዱሳኑ ፡ ላይ ፡ የገለጠውን ፡ ጥልቅ ፡ ምስጢር ፡ እያ
ሰቡ ፤ መንክር ፡ እግዚአብሔር ፡ በላዕለ ፡ ቅዱሳኒሁ ። በቅዱሳን ፡ ላይ ፡ ቸርነቱን ፡ የገለጠ፡
እግዚአብሔር ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ እያሉ ፤ ሥራውን ፡ እያደነቁ ፤ ስሙን ፡ እያመሰገኑ ፤ ስለ ፡
ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ስለ ፡ አምላከ ፡ ሙሴ ፡ ስለ ፡ አምላከ ፡ ኤልያስ ፡ ስለ ፡ አምላከ ፡ ጴጥ
ሮስ ፡ ስለ ፡ አምላከ ፡ ጳውሎስ ፡ ስለ ፡ አምላከ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ስለ ፡ አምላከ ፡ ጊዮ
ርጊስ ፡ ስለ ፡ አምላከ ፡ ሚካኤል ፡ ስለ ፡ አምላከ ፡ ገብርኤል ፡ እያሉ ፡ ሰጪዎቹ ፡ ያቅማ
ቸውን ፡ ይሰጣሉ ። ተቀባዮቹም ፡ ከእመቤታችን ፡ የተወለደው ፡ አምላክ ፡ የሙሴ ፡ አም
ላክ ፡ ይስጥልን ፡ እያሉ ፡ ይቀበላሉ ። መዝ ፡ ፷፰ ፡ ቍ ፡ ፴፭ ።

፲ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሰጪዎቹም ፡ ኾነ ፡ ተቀባዮች ፡ የቅዱሳንን ፡ ስም ፡ ለፈጣሪያቸው፡
ስም ፡ ዘርፍ ፡ የፈጣሪያቸውን ፡ ስም ፡ ባለቤት ፡ አድርገው ፡ ሲናገሩ ፤ ሰጪዎቹ፡ከድኾቹ ፡
ብድር ፡ እንደማይፈልጉ ፡ በመግለጥ ፤ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እያሉ ፡ ሲሰጡ ፤ ድኾችም፡
ባለጸጎች ፡ ከእነሱ ፡ ብድር ፡ የማይፈልጉ ፡ ምስጋናም ፡ የማይሹ ፡ መኾናቸውን ፡ ተገንዝ
በው ፡ ዋጋ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እንጂ ፤ ከእነሱ ፡ የማይገኝ ፡ መኾኑን ፡ በመግለጥ ፤ እግዚ
አብሔር ፡ ይስጥልን ፡ ብለው ፡ ሲቀበሉ ፤ ሰጪ ፡ ባለጸጋና ፡ ተቀባይ ፡ ድኻ ፡ በአንድ ፡
ልብ ፡ በአንድ ፡ አፍ ፡ ከታናናሾች ፡ ወንድሞቼ ፡ ለአንዱ ፡ ያደረጋችሁትን ፡ ለኔ ፡ አደ
ረጋችሁት ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አከበሩት ፡ አገለገሉት ። ይህንንም ፡ እኔ ፡ እንደማው
ቀው ፡ ለማስረጃ ፡ ያኽል ፡ በአጭሩ ፡ ተናገርኩ ፡ እንጂ ፤ የምጽዋት ፡ ነገር ፡ በመላ ፡ ኢት
ዮጵያ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘንድ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ በስውር ፡ በግልጥ ፡ ከፍ ፡
ብሎ ፡ ይሠራል ።

፲፩ ፤ እንግዳ ፡ መቀበል ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተለመደ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ እንደ ፡ ዛሬ ፡ ብዙ ፡ መን
ገዶች ፡ በሥልጣኔ ፡ ሳይከፈቱና ፡ የብዙ ፡ ቀን ፡ ጉዞ ፡ በአጭር ፡ ቀን ፡ የሚቈረጥ ፡ ሳይ
ኾን ፤ በየቦታውም ፡ የንግድ ፡ ቤቶች ፡ በገዛተው ፡ ሳይከፈቱ ፤ ባለፈው ፡ ዘመን ፡ ማንም፡
መንገደኛ ፡ ላንድ ፡ ቀን ፡ ለኹለት ፡ ቀን ፡ ራት ፡ የሚኾነውን ፡ ለሸክም ፡ ዐቅሙ ፡ የሚ
ፈቅድለትን ፡ ያኽል ፡ ሥንቅ ፡ ይዞ ፡ ከቤቱ ፡ ይወጣል ። ዐቅሙ ፡ እንደ ፡ ፈቀደለትም ፡
ሲሄድ ፡ ውሎ ፡ ማታ ፡ በደረሰበት ፡ ቦታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንግዳ ፡ ብሎ ፡ ከሰዎች ፡
ደጅ ፡ ይቀመጣል ። ባለቤቶቹም ፡ ሰውዬውን ፡ ባያውቁት ፡ የመጣ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ስም ፡ መኾኑን ፡ ተመልክተው ፤ ቤት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ግባ ፡ ብለው ፡ በሰላም ፡
ተቀብለው ፡ እግሩን ፡ አጥበው ፡ እሳት ፡ አሙቀው ፡ ራቱን ፡ አብልተው ፡ ምንጣፉን ፡
አዘጋጅተው ፡ በሚገባ ፡ ያሳድሩታል ። ትርፍ ፡ ምንጣፍ ፡ ትርፍ ፡ ዐልጋ ፡ ወይም፡መደብ ፡
ባይኖራቸው ፡ እንኳን ፡ መልካሙን ፡ ቦታ ፡ ማለት ፡ ዐልጋውን ፡ ወይም ፡ መደቡን ፡ ምን



ጣፉን ፡ ለእንግዳው ፡ ሰጥተው ፡ በመሬት ፡ ይተኛሉ ፡ እንጂ ፤ ከቶ ፡ እንግዳውን
ንም ፡ ነገር ፡ አያሳዝኑትም ፤ ከእንግዳውም ፡ በበለጠ ፡ ለራሳቸው ፡ አያደሉም ።

፲፪ ፤ የተራቆተ ፡ ማልበስ ፡ ኹለት ፡ ልብስ ፡ ያለው ፡ አንዱን ፡ ለሌለው ፡
ባለው ፡ መሠረት ፤ ኹለት ፡ ልብስ ፡ በቤት ፡ ቢኖር ፡ አንዱን ፡ ለሌለው ፡ መስጠት
ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፲ና ፡ ፲፩ ።

የታሰረ ፡ ማስፈታት ፡ ቢቻል ፡ ዕዳውን ፡ ከፍሎ ፡ ወይም ፡ ከንጉሥ ፡ አ
የታሰረውን ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ ማውጣት ፤ ባይቻል ፡ ግን ፡ በጸሎት ፡ መርዳት ፡ ነው
ቆተ ፡ ማልበስ ፡ የታሰረ ፡ ማስፈታት ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በከሃሊነቱ ፡ እን
ለአዕዋፍ ፡ ለአንስርት ፡ ማረፊያ ፡ መሳፈሪያ ፤ ላላፊ ፡ ላግዳሚው ፡ መጠጊያ ፡
በታላቅነት ፡ በልምላሜ ፡ ለፈጠራቸው ፡ ለባለጸጎች ፡ ነው ። ከመምህራንም ፡
ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ላሉት ፡ ዕድላቸው ፡ ነው ።

፲፫ ፤ የታመመ ፡ መጠየቅ ፡ ብቻ ፡ ዐይንን ፡ ላክ ፡ አድርጎ ፡ የተኛበትን ፡
አይቶ ፡ ማለፍ ፡ አይደለም ። ቢቻል ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ በጕልበት ፡ የራቀውን
ረብ ፡ መርዳት ፡ ነው ። ያም ፡ ባይቻል ፤ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንደነ ፡ ኢዮብ ፡
ሰዎች ፡ እየጠቀሱ ፡ ማጽናናት ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያደረገላቸውን ፡ የፈውስ ፡
እየነገሩ ፡ በሃይማኖቱ ፡ ጕድለት ፡ በትዕግሥቱ ፡ ብስጭት ፡ እንዳይኖርበት ፡ ማ
ነው ። ኢዮ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፩ - ፲ ። ፵፪ ፡ ፩ - ፲፯ ።

፲፬ ፤ ምጽዋት ፡ የምትባለው ፡ ርኅራኄ ፡ መኾኗን ፡ ማወቅ ፡ አለብን ። በ
በጌታ ፡ ስም ፡ ነዳያንን ፡ የሚረዱ ፤ ዕንጀራቸውን ፡ ለተራበ ፡ የሚቈርሱ ፤ ነዳያ
ስቶስ ፡ ወንድሞች ፡ መኾናቸውን ፡ ዐውቀው ፡ በፈጸሙት ፡ ቅዱስ ፡ ተግባር ፡
ንና ፡ የላከውን ፡ አባቱን ፡ ይቀበላሉ ። ስለዚህ ፡ ፈቃዱን ፡ በሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡
ስቶስና ፡ አባቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ አድረውባቸው ፡ ይኖራሉ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ

፲፭ ፤ በነቢያት ፡ በጻድቃን ፡ ስም ፡ ድኾችን ፡ የሚቀበሉ ፤ ሀብታቸው
ኾች ፡ የሚያካፍሉ ፤ በደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ በሐዋርያት ፡ ስም ፡ ቀዝቃዛ ፡ ውሃ
ኹሉ ፤ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ የክርስቶስ ፡ መኾናቸውን ፡ አምነው ፡ ተቀብ
ክርስቶስን ፡ ይቀበላሉ ። በዚህም ፡ የወይኑ ፡ ባለቤት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቀኑ ፡
ለሠራተኞች ፡ ዋጋ ፡ ለመክፈል ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤ የተከለም ፡ ያጠጣም ፡ ያረመም
ኰትም ፡ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ ዋጋቸውን ፡ ያገኛሉ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፴፭ -

፲፮ ፤ የዕውቀት ፡ ምጽዋት ፡ ምክር ፡ ነው ። ሰው ፡ ባለማወቅ ፡ ክፉው ፡ ሃ
በጎ ፡ ሃይማኖት ፡ መስሎት ፤ መጥፎው ፡ ምግባር ፤ መልካም ፡ ምግባር ፡ መስሎ
ሲኖር ፤ መክሮ ፡ አስተምሮ ፡ ከክፋት ፡ ወደ ፡ በጎነት ፤ ከኀጢአት ፡ ወደ ፡ ስርየ
ለስ ፡ ነው ። የዕውቀት ፡ ምጽዋት ፡ በማስተማር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ በቦታው ፡ እናመ

፲፯ ፤ የምጽዋትን ፡ ነገር ፡ ጌታ ፡ በቃል ፡ ጠላትኽ ፡ ቢራብ ፡ አብላው ፤ በደ
ኖር ፡ ድኻ ፡ መጻተኛ ፡ ቢኖር ፡ ቸል ፡ አትበለው ፡ ለለመነኽ ፡ ስጠው ። ካንተ ፡

www.ethiopianorthodox.org

የሚወደውን ፡ አትከልክለው ፤ ወለድም ፡ አትጠይቀው ፡ ብሎ ፡ ፊት ፡ ለእስራኤል ፡ ፵ ፡ ዘመን ፡ መና ፡ ከደመና ፡ አውርዶ ፡ ውሃ ፡ ከደንጊያ ፡ አፍልቆ ፡ በመመገብ ፤ ኋላም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ዐምስት ፡ ዕንጀራ ፡ አበርክቶ ፡ ላ፭ሺ ፡ ሰዎች ፤ ፯ ፡ ዕንጀራ ፡ አበርክቶ ፡ ላ፬ሺ ፡ ሰዎች ፡ በማብላቱ ፤ በቃል ፡ በሥራም ፡ ያስተማረን ፡ ነው ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፫ ። ዘፀ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፡ ፲፫—፳፩ ። ፲፫ ፡ ፴፪—፴፱ ።

፸፰ ፤ የምጽዋት ፡ ተቃዋሚዎቿ ፡ ንፍገትና ፡ ጭካኔ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ይትሌቃህ ፡ ኃጥእ ፡ ወኢይፈዲ ። ኃጥእ ፡ ሰው ፡ ሀብትን ፡ ጕልበትን ፡ ዕውቀትን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይቀበላል ፤ በምጽዋት ፡ በርዳታ ፡ በማስተማር ፡ አይከፍልም።መዝ ፡ ፴፮፡ቍ፡፳፩።

፸፱ ፤ ንፉጎች ፡ ገንዘብን ፡ ይሰበስባሉ ፤ ጕልበታቸውን ፡ ይቆጥባሉ ፤ ዕውቀታቸውን ፡ ይደብቃሉ ፤ የሰበሰቡትም ፡ ለማን ፡ እንዲኾን ፡ አያውቁም ። አለን ፡ አለን ፡ ሲሉ ፡ ባላሰቡት ፡ ሰዓት ፡ ባልጠረጠሩት ፡ ዕለት ፡ ድንገተኛ ፡ ጠሪ ፡ ( ሞት ) ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤ ሀብታቸው ፡ ለወራሽ ፤ ሰውነታቸው ፡ ለዐፈር ፡ ይኾናል ። ወርቃችን ፡ ለዝና ፡ እኽላችን ፡ ለቀጠና ፡ ይሆናል ፡ እያሉ ፡ ይመኩበት ፡ የነበረ ፡ ሀብታቸው ፤ ብናስር ፡ እናጠብቃለን ፤ ብንመታ ፡ እናደቃለን ፡ እያሉ ፡ የተወራረዱበት ፡ ጕልበታቸው ፤ አእምሮዋችን ፡ ረቂቅ ፡ መዓርጋችን ፡ ምጡቅ ፡ እያሉ ፡ የታጀሩበት ፡ ዕውቀታቸው፡ያልፋል ፤ ይጠፋል ፤ እንደ ፡ ኢምንት ፡ ይሆናል ። መዝ ፡ ፴፱ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

፹ ፤ እንዲህ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ብራብ ፡ አላበላችሁኝም ፤ ብጠማ ፡ አላጠጣችሁኝም ፤ እንግዳ ፡ ብኾን ፡ አልተቀበላችሁኝም ፤ ብራቆት ፡ አላለበሳችሁኝም ፤ ብታመም ፡ አልጠየቃችሁኝም ፤ ብታሰር ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስፈታህ ፡ እንኳ ፡ አላላችሁኝም ፤ ይህንንም ፡ ከታናናሹ ፡ ወንድሞቼ ፡ ከድኾች ፡ ላንዱ ፡ አለማድረጋችሁ ፤ ለኔ ፡ አለማድረጋችሁ ፡ ነውና ፤ ለሰይጣንና ፡ ለመልክተኞቹ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀው ፡ ወደ ፡ ዘለዓለም ፡ እሳት ፡ ሂዱ ፡ የሚል ፡ ታላቅ ፡ የወቀሳ ፡ ቃልና ፡ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ ይጠብቃቸዋል ።

፹፩ ፤ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ሀብትን ፡ ጕልበትን ፡ ዕውቀትን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይቀበላል ። በተቀበለውም ፡ ድኾችን ፡ ይረዳበታል ፤ ገንዘቡን ፡ ለድኻ ፡ ይበትናል ፤ ስም ፡ አጠራሩም ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ። መዝ ፡ ፴፯ ፡ ቍ ፡ ፳፩—፳፯ ። ፻፲፪ ፡ ፱ ።

፹፪ ፤ ጻድቃን ፤ የሚለወጠው ፡ አልሮ ፤ የማይለወጠው ፡ እንዲተካ ፡ ዐውቀው ፡ ሰው ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ይመስላል ፤ ዘመኑም ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ያልፋል ፤ ሀብቱም ፡ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አበባ ፡ ይረግፋል ፤ ዕውቀቱም ፡ ይጠፋል ። እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ ሀብት ፡ ጕልበት ፡ ዕውቀት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የኛ ፡ ምናችን ፡ ነው ። ሀብታችንን ፡ በምጽዋት ፡ ጕልበታችንን ፡ በመርዳት ፡ ዕውቀታችንን ፡ በመምከር ፡ በማስተማር ፡ ላይ ፡ እናውለው ፡ ብለው ፡ ይመክራሉ ። ምክራቸውም ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ፤ ይፈጽሚታል ፤ ይሠሩባታል ፤ ይጠቀሙባታል ።

፹፫ ፤ ጻድቃን ፡ ፍጹማን ፡ ታዛገሮች ፡ በመኾናቸው ፤ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የእነሱ ፡ ናትና ፡ ብራብ ፡ አብልታችሁኛል ፤ ብጠማ ፡ አጠጥታችሁኛል ፤ እንግዳ ፡ ብኾን ፡ ተቀብላችሁኛል ፤ ብራቆት ፡ አልብሳችሁኛል ፤ ብታመም ፡ ጠይቃችሁኛል ፤ ብታሰር ፡



ወዳለሁበት ፡ መጥታችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስፈታህ ፡ ብላችሁኛል ። ይህንንም ፡ ከ፡ ናናሾች ፡ ወንድሞቼ ፡ ከድኾች ፡ ለአንዱ ፡ ማድረጋችሁ ፡ ለእኔ ፡ ማድረጋችሁ ፡ ነውና አባቴ ፡ የመረጣችሁ ፡ የባረካችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የተዘጋጀላችሁን መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ትወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወደኔ ፡ ኑ ፡ የሚል ፡ የብፅዓን ፡ ቃልና ፡ የዘ ዓለም ፡ ሕይወት ፡ ይጠብቃቸዋል ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳፭ ፡ ቍ ፡ ፴፩—፵፯ ።

፹፬ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ለምጽዋት ፡ መታዘዝ ፡ ከመሥዋዕት ፡ እንዲበልጥ ፡ ዐውቃ ክርስቶስ ፡ በቃልም ፡ በሥራም ፡ ያስተማራትን ፡ በመፈጸም ፤ እሳትን ፡ ውሃ ፡ እንዲያ ፋው ፡ ኀጢአትን ፡ መፋቅ ፡ ዲያብሎስን ፡ ማራቅ ፡ ሥጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጠላትን ፡ ማ ቃት ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ መስጠት ፡ በሚቻላት ፡ በምጽዋት ፡ ኀይል ፡ ከእግዚአ ሔር ፡ ጋራ ፡ ታርቃ ፡ ኀጢአትን ፡ መቀሠፍትን ፡ መዓትን ፡ አርቃ ፡ ነጻነቷን ፡ ጠብቃ ሥጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጠላትን ፡ ድል ፡ ነሥታ ፡ ታሪኳን ፡ አስፋፍታ ፡ በሰላም ፡ ትኖ ለች ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

፹፭ ፤ ወንድሞቼ ፤ ምጽዋት ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ሲኾን ፡ በስውር ፤ በዓል ፡ በማ ረግ ፡ ጊዜ ፡ በግልጥ ፡ ትሠራለች ። ምጽዋትን ፡ የሚቃወማት ፡ ሰጪው ፡ ከሰው ፡ ከንተ ውዳሴን ፡ በመሻት ፡ ይዩልኝ ፡ ይስሙልኝ ፡ ብሎ ፡ የሚፈጽመው ፡ ዐሳብና ፡ ሥራ ፡ ነወ እንጂ ፤ የተመልካቹ ፡ ዐይን ፡ የጻድቁን ፡ ዋጋ ፡ ሊያስቀርበት ፡ አይችልም ። ይልቁንም የበጎ ፡ አብነት ፡ ሊኾን ፡ ይችላል ።

፹፮ ፤ ምጽዋት ፡ በበዓል ፤ በጥቂት ፡ እንጂ ፡ በብዙ ፤ በገንዘብ ፡ እንጂ ፡ በድግስ ሊኾን ፡ አይገባም ፤ በበዓል ፡ በብዙ ፡ ድግስ ፡ ይሁን ፡ የሚሉ ፡ ጥቅማቸውን፡የሚፈልገ ቀላዋጮች ፡ ናቸው ፡ የሚል ፡ ስብከት ፤ ለሕዝብ ፡ የሥራ ፡ መሰናክል ፡ ከሚኾኑት ፡ ካ ዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ይዘራል ። ማስረጃም ፡ የሚያደርጉት ፡ ምሳ ወይም ፡ ራት ፡ ባደረግኽ ፡ ጊዜ ፤ ባለጠጎችን ፡ ወዳጆችኽን ፡ ጎረቤቶችኽን ፡ ትተኽ፡ የ ከፍሉህ ፡ የሌላቸውን ፡ ድኾችን ፡ ዕውሮችን ፡ አንካሶችን ፡ ጥራ ፡ ያለውን ፡ ወደ ፡ ጕ ራቅ ፡ ፈቀቅ ፡ አድርገው ፤ ቀዝቃዛ ፡ ውሃ ፡ የሰጠ ፡ ዋጋውን ፡ አያጣምና ፡ ዐሥር ፡ ሳ ቲም ፡ ዐምስት ፡ ሳንቲም ፡ ይበቃል ፤ በስውር ፡ የሚያይኽ ፡ አባትኽ ፡ ዋጋኽን ፡ ይሰ ሀል ፡ ብሏልና ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሰብስቦ ፡ ብዙ ፡ ደግሦ ፡ ማብላት ፡ አያስፈልግም ፡ የሚሉ ትች ፡ ነው ።

፹፯ ፤ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ ምጽዋታችሁ ፡ ለሰው ፡ ዐይ አይኹን፡ማለቱ ፤ ሰው ፡ ይይልኝ ፡ ብለን ፡ እንዳንሠራው ፤ በስውር ፡ የሚያይኽ ፡ አባት ገልጦ ፡ ዋጋኽን ፡ ይከፍልሃል ፡ ማለቱም ፤ ሰው ፡ ተሰውሮ ፡ የሚያየው ፡ እግዚአብሔ ብቻ ፡ ዋጋውን ፡ እንዲከፍለው ፡ በማመን ፡ እንዲሠራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ብዙ ፡ ደግ በብዙ ፡ ማብላትን ፡ ማጠጣትን ፡ አንተስ ፡ ምሳ ፡ ወይም ፡ ራት ፡ ባደረግኽ ፡ ጊዜ ፡ ድ ችን ፡ ጠም ፡ አዳሪዎችን ፡ ጥራ ፡ እንዲህም ፡ ያደረግኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ የሚከፍሉ የላቸውምና ፡ አንተ ፡ ምስጉን ፡ ነህ ፡ ብሎ ፡ አጽንቷታል ፡ ቀድሷታል ። ማቴ ፡ ም ፡ ቍ ፡ ፩—፬ ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፡ ፲፪—፲፬ ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፰ ፤ ስለዚህ ፡ እኛ ፡ መምህራችን ፡ ክርስቶስን ፡ ተከትለን ፡ ምጽዋትን ፡ ቁም፡
ነገር ፡ እናድርጋት ። የተራብ ፡ በማብላት፡ የተጠማ ፡ በማጠጣት ፡ እንግዳ ፡ በመቀበል፡
ሥላሴን ፡ መላእክትን ፡ ለመቀበል ፡ የታደሉ ፡ አብርሃምን ፡ ሎጥን ፡ የተራቆተ ፡ በማል
በስ ፡ የታመመ ፡ በመጠየቅ ፡ የታሰረ ፡ በማስፈታት ፡ (አይሁድ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ሲያናፉ
እንደ ፡ ግስላ ፡ ሲደነፉ ፡ በነበሩበት ፡ በዚያ ፡ በመከራ ፡ ቀን ፡ ችንካሩን ፡ ነቅለው ፤ ከመ
ስቀል ፡ አውርደው ፡ ራቁቱን ፡ የተሰቀለውን ፡ የዓለም ፡ እንግዳ ፡ ክርስቶስን ፡ በነጭ፡
ሐር ፡ በድርብ ፡ በፍታ ፡ ለመገነዝና ፡ ቅዱስ ፡ ሥጋውን ፡ በንጹሕ ፡ መቃብር ፡ ለማኖር፡
የታደሉ ፡ ዮሴፍን ፡ ኒቆዲሞስን ፡ ለመምሰል ፡ እንድንችል ፤ በሰማይ ፡ ቤቶቻቸው ፡ ይቀ
በሉን ፡ ዘንድ ፡ በዐመፃው ፡ ገንዘብ ፡ ከድኾች ፡ ጋራ ፡ እንወዳጅበት ።

፳፱ ፤ የዓለም ፡ ልጆች ፡ ስንኾን ፡ ከብርሃን ፡ ልጆች ፡ ይልቅ ፡ ብልጫ ፡ የሚሰ
ጠንን ፡ ይህንን ፡ የጥበብ ፡ ፋና ፡ ይዘን ፡ ለሰይጣንና ፡ ለመልእክተኞቹ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀው፡
ቦታ ፡ የሚወስደውን ፡ መንገድ ፡ ትተን ፡ ወደ ፡ ዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ለመድረስ ፡ ስለ፡
እኛ ፡ ሕይወት ፡ ኹሉን ፡ አቃሎ ፡ ኀፍረተ ፡ መስቀልን ፡ የታገሠውን ፡ ፍጹም ፡ አለቃ
ችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እንከተለው ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ቍ ፡ ፩—፲ ። ፲፱ ፡ ፩—፫ ።
ሉቃ ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ቍ ፡ ፩ - ፲፫ ።

የእውነትና ፡ የሕይወት ፡ መንገድ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ባንተ ፡ ወደ ፡ አብ
ለመቅረብ ፡ የበቃን ፡ አድርገን ። አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ምጽዋት ፡ ምንድናት ?
፪ ፤ የምጽዋት ፡ መሠረት ፡ ምንድነው ?
፫ ፤ ሰው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነት ፡ ዐስቦ ፡ ምን ፡ ሊያደርግ ፡ ይገባዋል ?
፬ ፤ ምጽዋት ፡ በስንት ፡ ይከፈላል ?
፭ ፤ የገንዘብ ፡ ምጽዋት ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፮ ፤ የጕልበትና ፡ የምክርሳ ?
፯ ፤ ስለ ፡ ምጽዋት ፡ የተነገሩ ፡ ቃላት ፡ ማን ፡ ማን ፡ ናቸው ?
፰ ፤ የምጽዋት ፡ መጀመሪያና ፡ መጨረሻ ፡ ምንድነው ?
፱ ፤ ምጽዋት ፡ ማንን ፡ ታስመስላለች ?
፲ ፤ እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ ያደርጋል ?
፲፩ ፤ ሰውስ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ?
፲፪ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምጽዋትን ፡ የሚያደርግባቸው ፡ መታሰቢያዎች ፡ ምን
ምን ፡ ናቸው ?
፲፫ ፤ በጐጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ስለ ፡ ምጽዋት ፡ ምን ፡ ልማድ ፡ አለ ?
፲፬ ፤ ሰጪዎቹ ፡ የማንን ፡ ስም ፡ ይጠራሉ ?
፲፭ ፤ ተቀባዮቹስ ፡ ምን ፡ ይመልሳሉ ?
፲፮ ፤ እንግዳ ፡ መቀበል ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንዴት ፡ ነው ?



፲፯ ፤ እንግዳው ፡ ሲሄድ ፡ ውሎ ፡ ማታ ፡ በደረሰበት ፡ ምን ፡ ያደርጋል ?
፲፰ ፤ ባለቤቶች ፡ ምን ፡ ይሉታል ?
፲፱ ፤ ደግሞስ ፡ ምን ፡ ያደርጉለታል ?
፳ ፤ የተራቆተ ፡ ማልበስ ፡ የታሰረ ፡ ማስፈታት ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፳፩ ፤ የታመመ ፡ መጠየቅ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፳፪ ፤ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ ለድኾች ፡ የሚራሩ ፡ ማነን ፡ ይቀበላሉ ?
፳፫ ፤ በቅዱሳን ፡ ስም ፡ ለድኾች ፡ የሚራሩ ፡ ማነን ፡ ይቀበላሉ ?
፳፬ ፤ የዕውቀት ፡ ምጽዋት ፡ ምንድነው ?
፳፭ ፤ ምጽዋትን ፡ ያስተማረን ፡ ማነው ?
፳፮ ፤ የምጽዋት ፡ ተቃዋሚዎች ፡ ማን ፡ ማን ፡ ናቸው ?
፳፯ ፤ ንፉጎች ፡ ምን ፡ ያደርጋሉ ?
፳፰ ፤ ንፉጎችን ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ይጠብቃቸዋል ?
፳፱ ፤ ጻድቃን ፡ ምን ፡ ያደርጋሉ ?
፴ ፤ ጻድቃንን ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ይጠብቃቸዋል ?
፴፩ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በምጽዋት ፡ ምን ፡ ጥቅም ፡ አግኝታለች ?
፴፪ ፤ ምጽዋት ፡ በስውር ፡ በግልጥስ ፡ እንዴት ፡ ትሠራለች ?
፴፫ ፤ የተመልካች ፡ ዐይን ፡ የጻድቁን ፡ ዋጋ ፡ ያስቀራልን ?
፴፬ ፤ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ምጽዋት ፡ ምን ፡ ያመካኛሉ ?
፴፭ ፤ ክርስቶስ ፡ ምን ፡ ብሏል ?
፴፮ ፤ እንግዳ ፡ በመቀበል ፡ ዋጋ ፡ ያገኙ ፡ እነማን ፡ ናቸው ?
፴፯ ፤ የተራቆተ ፡ በማልበስ ፡ የታሰረ ፡ በማስፈታት ፡ ዕድል ፡ ያገኙ ፡ እነ
ናቸው ?
፴፰ ፤ በዐመፃው ፡ ገንዘብ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይገባናል ?

ምዕራፍ ፡ ፳፰ ።

## ስ ግ ደ ት ።

፩ ፤ ስግደት ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚያቀርበው ፡ በኋ
ዚአብሔር ፡ ላከበራቸው ፡ ቅዱሳን ፡ እንደ ፡ ደረጃቸው ፡ የሚፈጽመው ፡ ነገር ፡
ግደት ፡ መሠረቱ ፡ በመቅደሱ ፡ ዙሪያ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስገዱ ፡ የጌታችን ፡
መበት ፡ ቦታ ፡ እንሰግዳለን ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ። መዝ ፡ ፳፱ ፡ ቍ ፡ ፪ ። ፻፴

፪ ፤ ስግደት ፤ የአምልኮ ፡ ስግደት ፡ የጸጋ ፡ ስግደት ፡ ተብሎ ፡ በኹለ
ላል ። የአምልኮ ፡ ስግደት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ከቶ ፡ ለሌላ ፡ አይሰጥ
ርብም ። ምክንያቱም ፤ ራሱ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አ
ማይ ፡ ካሉ ፡ ከፀሐይ ፡ ከጨረቃ ፡ ከከዋክብት ፡ ወይም ፡ በምድር ፡ በባሕር ፡ ካ

www.ethiopianorthodox.org

ታት ፡ ማንንም ፡ አታምልክ ፤ በሰው ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሥዕልና ፡ ምሳሌ ፡ አታድርግ ፤ አታምልካቸው ፤ አትስገድላቸው ፡ ስለ ፡ አለ ፡ ነው ። ዘፀ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ ፡ ፩—፫ ። መዝ ፡ ፺፩ ፡ ፱ ።

፫ ፤ እውነት ፡ ነው ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ ከወርቅና ፡ ከብር ፡ ከዕንጨትና ፡ ከደንጊያ ፡ የተሠሩ ፡ የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ወዳጆቻቸውን ፡ የማይጠቅሙ ፡ ጠላታቸውን ፡ የማይጎዱ፡ ራሳቸውን ፡ ወይም ፡ ዜጋቸውን ፡ ከጥፋት ፡ የማያድኑ ፡ ከንቱዎች ፡ ናቸው ። አፍ ፡ አላቸው ፡ አይናገሩም ፤ ዐይን ፡ አላቸው ፡ አያዩም ፤ ገሮ ፡ አላቸው ፡ አይሰሙም ፤ አፍንጫ ፡ አላቸው ፡ አያሸቱም ።

፬ ፤ እጅ ፡ አላቸው ፡ አይዳስሱም ፡ እግር ፡ አላቸው ፡ አይሄዱም፡ አይንቀሳቀሱም፤ በጕሮሮዋቸው ፡ ድምፅ ፡ በአንደበታቸው ፡ ትንፋሽ ፡ የለባቸውም ። እነሱና ፡ የሚፈጥሯቸው ፡ ማለት ፡ ዕንጨቱን ፡ ጠርበው ፡ ደንጊያውን ፡ አለዝበው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክና ፡ ምሳሌ ፡ የሚሠሯቸው ፡ ከንቱዎች ፡ ናቸው ። ለእነዚህ ፡ የአምልኮት ፡ ወይም ፡ የጸጋ ፡ ስግደት ፡ ሊቀርብላቸው ፡ አይገባም ። መዝ ፡ ፻፲፭ ፡ ቍ ፡ ፲፭—፲፰ ።

፭ ፤ ሰው ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ማዕድና ፡ የአጋንንትን ፡ ማዕድ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ መብላት ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ጽዋና ፡ የአጋንንትን ፡ ጽዋ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ መጠጣት ፡ የማይቻል ፡ ሲኾን ፤ እግዚአብሔርን ፡ ትቶ ፡ ጣዖትን ፡ ቢያመልክ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የሚገባውን ፡ አምልኮ ፡ መሥዋዕት ፡ ስግደት ፡ ለጣዖት ፡ ቢያደርግና ፤ የዛር ፡ የጋኔን ፡ ውሽማ፡ይዞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቢያስቀናው ፤ ያባቶችን ፡ ኀጢአት ፡ በልጆች ፡ የሚመራመር ፡ እውነት ፡ ፈራጅ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ ቅጣቱን ፡ ይቀበላል ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፲፱—፳፪ ።

፮ ፤ ስለዚህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቅድስና ፡ ቅዱሳን ፡ የኾኑ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ አምልኮትን ፡ መሥዋትን ፡ ስግደትን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀርባሉ ። የወዳጆቹን ፡ ዋጋ ፡ የማያስቀር ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርም ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ ምሕረቱን ፡ ያደርግላቸዋል ።

፯ ፤ ዓለም ፡ ኹሉ ፤ ግርማውን ፡ ያየችው ፡ ድምፁን ፡ የሰማችው ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሳትቀር ፡ በሰማይ ፡ ሰራዊት ፡ በምድርና ፡ በባሕር ፡ ባሉት ፡ ፍጥረታት ፡ አምሳል ፡ የተሠሩ ፡ ጣዖታትን ፡ በማምለክ ፡ ሲታለሉና ፡ ሲሰናከሉ ፤ ኢትዮጵያ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ብቻ ፡ ስታመልክ ፤ ክብሯን ፡ ጠብቃ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አለች ፤ ወደ ፡ ፊትም ፡ ትኖራለች ።

፰ ፤ አፍ ፡ ሥራ ፡ ሲያጣ ፡ ወዳጁን ፡ ያማል ፡ እንደሚባለው ፡ ያኽል ፤ ኢትዮጵያ፡ በድሮ ፡ ዘመን ፡ ጣዖታትን ፡ ታመልክ ፡ ነበር ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ከሐሚተኞች ፡ ድምፅ ፡ ይሰማል ፤ እውነተኛ ፡ ማስረጃ ፡ ግን ፡ የለውም ። ዛሬም ፡ የሀብታት ፡ የምስጢራት ፡ መገኛ ፡ የኾነ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስና ፡ የሥራው ፡ መታሰቢያዎች ፡ የኾኑ ፡ ሥዕሎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለሚገኙ፤ከእውነት፡ ለመራቅ፡የፈለገው፡ ጊዜያዊ ፡ መላስ ፡ እንደ ፡ ጣዖት ፡ አምልኮት ፡ አድርጎ ፡ ሲቈጥርባት ፡ እንሰማለን ።



፱ ፤ የሀብታት ፡ የምስጢራት ፡ መታሰቢያ ፡ የኾኑትን ፡ ጽላትንና ፡ ሥዕል
እግዚአብሔር ፡— በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ የመሠረታቸው ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከሕ
ናዋ ፡ ያነቃቻቸው ፡ ወይም ፡ በቅልውጥ ፡ ያመጣቻቸው ፡ አይደለም ። መታሰቢያነታ
ውና ፡ መጽሐፍነታቸውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ነው ። ዘፀ ፡ ም ፡ ፴ ፡ ቀ
፴፬—፴፯ ።ዕብ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፫—፭ ።

፲ ፤ ስለዚህ ፡ ሙሴ ፡ ሥዕለ ፡ ኪሩብ ፡ በተሳለበት ፡ ጽላተ ፡ ኪዳን ፡ ባሉበ
በታቦት ፡ ፊት ፡ ሲሰግድ ፡ ሲጸልይ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ ለክርስቶስ ፡ ስም ፡ በሰማይ ፡
ድር ፡ ከምድርም ፡ በታች ፡ ያለ ፡ ጕልበት ፡ ኹሉ ፡ ይሰግዳል ፡ ይንበረከካል ። አን
ትም ፡ ኹሉ ፡ ይገዛለታል ፡ ብሎ ፡ የተናገረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ መሪ ፡ አድርጋ ፡ ኢ
ጵያ ፡ በጽላትና ፡ በሥዕል ፡ ላይ ፡ ለተገለጠው ፡ ለክርስቶስ ፡ ስም ፡ ለክርስቶስ ፡ አርአ
ትሰግዳለች ፤ ትንበረከካለች ፤ አንደበቷንም ፡ ለምስጋናው ፡ ታስገዛለች ። ፊል ፡ ም ፡
ቍ ፡ ፱ና ፡ ፲ ።

፲፩ ፤ ጽላተ ፡ ኪዳን ፡ ባሉበት ፡ ታቦት ፡ በነበረው ፡ በኪሩብ ፡ ሥዕል ፡ ላይ ፡
ልጦ ፡ በማነጋገር ፡ ለሙሴና ፡ ለአሮን ፡ ዐስበ ፡ ጸሎታቸውን ፡ ሲከፍል ፡ የኖረ ፡ እግ
ብሔርም ፤ ኢትዮጵያ ፤ በጽላት ፡ በሥዕል ፡ አማካይነት ፡ የምታቀርብለትን ፡ ጸሎ
ዘወትር ፡ ይቀበላል ፤ ዋጋዋንም ፡ ይከፍላል ።

፲፪ ፤ ወንድሞቻችን ፡ ብርሃንን ፡ ከጨለማ ፡ ኀጢአትን ፡ ከጽድቅ ፡ ክርስቶስ
ከሰይጣን ፡ ማቀላቀል ፡ የማይገባ ፡ ሲኾን ፤ የጣዖትንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አምልኮ
የቤተ ፡ ጣዖትንና ፡ የቤተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሥርዐት ፡ ለይቶ ፡ ባለማወቅ ፤ ታቦተ ፡
ዚአብሔርን ፡ ከቤተ ፡ ጣዖት ፡ እያገቡ ፡ ጽላት ፡ ሥዕል ፡ መስቀል ፡ ከጣዖታት ፡ ይ
ራሉ ፡ የሚሏችሁን ፡ አትስሟቸው ።

፲፫ ፤ የቄሳርን ፡ ለቄሳር ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስጡ ፡ እንዳለ
ኹሉ ፤ ጽሕፈቱን ፡ መልኩን ፡ ማኅተሙን ፡ አይቶ ፡ ለይቶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ለእ
አብሔር ፤ የጣዖትን ፡ ለጣዖት ፡ በመስጠት ፡ ፈንታ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መታሰቢ
ለጣዖት ፤ የጣዖትን ፡ መታሰቢያ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እየሰጡ ፡ የሚያስተምሩት ፡ ት
ርት ፤ ልዩ ፡ የተንኰል ፡ ሥራ ፡ ነውና ፡ በፍሬ ፡ ትምህርታቸው ፡ ዕወቋቸው ፤ ተጠ
ቁባቸው ።

፲፬ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ በራስኽ ፡ የማልክላቸው ፡ አብርሃምን ፡ ይስሐቅን ፡ ያ
ብን ፡ ዐስብ ፡ እያለች ፤ ለአብርሃም ፡ ለይስሐቅ ፡ ለያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ ጸሎቷን ፡ ታቀ
ለች ፤ እሱን ፡ ብቻ ፡ ታመልካለች ፡ እንጂ ፤ በአምልኮቷ ፡ እንቅፋት ፡ የለባትም ።
ረዱ ፡ ብትወዱም ፤ ኢትዮጵያ ፡ እጆቿን ፡ በማስተካከል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ት
ጋለች ፡ ያለውን ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ቃል ፡ ተማሩ ። መዝ ፡ ፷፰ ፡ ቍ ፡ ፴፩ ።

፲፭ ፤ ስግደት ፡ ቢቻል ፡ ከቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባይቻል ፡ ግን ፡ በቤትም ፡ ኘ
በሌላ ፡ ቦታ ፡ ምድር ፡ በመላዋ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ናትና ፡ ክርስቶስን ፡ እያሰቡ ፡ ት

www.ethiopianorthodox.org

ርቱ ፡ መስቀሉን ፡ በፊት ፡ አድርጎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መስገድ ፡ ይገባል ። ለዚህም ፡ መሠ
ረቱ ፡ ጌታችን ፡ አምላካችን ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በጌቴሴማን ፡ የፈጸ
መው ፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ፡ ሥራ ፡ ነው ።

፲፮ ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ ሥጋ ፡ ላሉት ፡ ወይም ፡ ለሞቱት ፡ ዘመዶቹ ፡
መታሰቢያ ፡ የኾነውን ፡ ሥዕል ፡ ይዞ ፡ ቢገኝ ፤ በሥዕሉም ፡ የዘመዶቹን ፡ ሥራ ፡ እያስታ
ወሰ ፡ የናፍቆት ፡ ምልክቱን ፡ ቢገልጥ ፤ ያንን ፡ ሰው ፡ ወረቀቱ ፡ ወይም ፡ ቀለሙ ፡ ዘመ
ድኽ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ የለም ። እሱም ፡ ይህ ፡ የመዘመዴ ፡ ወይም ፡ የወዳጄ ፡ ሥዕል ፡
ነው ፡ ለመታሰቢያ ፡ ከኔ ፡ ዘንድ ፡ ይኖራል ፡ ይላል ፡ እንጂ ፤ ይህ ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡
ይህ ፡ ቀለም ፡ ዘመዴ ፡ ነው ፡ አይልም ። ሰውዬው ፡ የተናፋቂ ፡ ዘመዱን ፡ ፍቅር ፡ ለመግ
ለጥ ፡ ሥዕሉን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ጌጣጌጥ ፡ አዘጋጅቶ ፡ አክብሮ ፡ ያስቀምጠዋል ።
ይህም ፡ ለተመልካቹ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ዘመዱ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ወዳጁ ፡ ያለውን ፡
የጋለ ፡ ፍቅር ፡ ያስረዳል ፡ እንጂ ፤ ከወረቀቱ ፡ ጋራ ፡ ያለውን ፡ ዝምድና ፡ ከቶ ፡ ምን ፡
ጊዜም ፡ አይሰብክም ።

፲፯ ፤ እንዲሁ ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ
ሥላሴ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጊዜ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ድርጅት ፡ የፈጸሙትን ፡ ሥራ ፡ ለማስታዋስ ፡
ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አርአያ ፡ ጋራ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መታሰቢያዎችን ፡ የያዙ ፡
ሥዕሎችን ፡ ከቤቱ ፡ አስቀምጦ ፡ ቢገኝ ፤ ከኢትዮጵያዊው ፡ ቤት ፡ የጃንሆይ ፡ ሥዕል ፡
እንዳለ ፡ ይነገራል ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ ሥዕሉ ፡ ኹኔታ ፡ ተመልካቹ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያዊው ፡
ቤት ፡ በገባበት ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አሁን ፡ ጃንሆይ ፡ በእገሌ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የትምህርት ፡
ሚኒስቴርን ፡ ወይም ፡ የእርሻ ፡ ሚኒስቴርን ፡ ይጐበኛሉ ፡ ተብሎ ፡ አይነገርም ። ወይም ፡
ኢትዮጵያዊውን ፡ ይህ ፡ የገኘኽ ፡ ሥዕል ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ገኘኽ ፡ ወረቀቱ ፡
ነው ፡ አይለውም ። የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይሳሳታል ። ምክንያቱም ፡ የሕያው ፡ ሥራ ፡
ባለቤት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በዙፋናቸው ፡ ላይ ፡ እያሉ ፡ ገኘኽ ፡ ወረቀቱ ፡ ነው ፡ ማለት ፡
ባለቤቱን ፡ ከመካድ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ።

፲፰ ፤ በዚሁ ፡ አንጻር ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ከመኾኑ ፡ በፊት ፤ ሰው ፡ ከመኾኑም ፡
በኋላ ፡ የፈጸመውን ፡ ሥራ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ሥዕል ፡ አዘጋጅቶ ፤ በሥዕሉ ፡
ላይም ፡ መግለጫ ፡ የሚኾነውን ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ሥዕል ፡ እግዚአብሔር ፡ አዳምን ፡ እንደ
ፈጠረ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፡ እንደ ፡ ተጠመቀ ፡ እንደ ፡ ተሰቀለ ፡ ያሳያል ፡ እያለ
የመሰለውንም ፡ ኹሉ ፡ ጽፎ ፡ ከፊቱ ፡ አድርጎ ፡ በሥዕሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያስታወሰ
ዐሳቡን ፡ ቢገልጥ ፤ በዚህ ፡ አርአያ ፡ ተወልደኽ ፡ በዚህ ፡ አርአያ ፡ ተሰቅለኽ ፡ ያዳንከኝ
አምላክ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ስግደትም ፡ ይገባሀል ፡ እያለ ፡ ለፈጣሪው ፡ ምስጋና ፡ ስግደት
ቢያቀርብ ፤ ወረቀቱ ፡ ሰውዬውን ፡ ፈጥሮታል ፡ ወይም ፡ ሰውዬው ፡ ጣዖት ፡ ያመልካል
አይባልም ፤ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ግን ፤ አንደኛ ፡ ወንድሙን ፡ በከንቱ ፡ በማሳዘኑ ፤ ኹለ
ተኛ ፡ በወንድሙ ፡ ላይ ፡ የሐሰት ፡ ምስክር ፡ በመኾኑ ፤ ሦስተኛ ፡ የሥዕሉን ፡ ማስረጃ
የመስቀሉን ፡ ምልክት ፡ እያየ ፤ ሰውንም ፡ በደሙ ፡ የተበጀው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ



መኾኑን ፡ እያወቀ ፤ በዐይኑ ፡ ሥጋ ፡ ሥዕሉን ፡ በዐይነ ፡ ሕሊናው ፡ የፈጣሪውን ፡ መልክ
እያየ ፡ የሚሰግደውን ፡ ሰው ፡ ጣዖት ፡ ታመልካለኽ ፡ ሲለው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጣዖት
ማለቱ ፡ ነውና ፡ ኀጢአቱ ፡ አይሰረይለትም ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ፴፩ ። መዝ ፡ ፳፩
ቍ ፡ ፲፩ ።

፲፱ ፤ ፍጡር ፡ ኹሉ ፡ ለአእምሮው ፡ አጋዥ ፡ ይሻል ። ስለዚህም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከ
ግዚአብሔር ፡ የተፈጸሙትን ፡ የሀብታት ፡ የምስጢራት ፡ መታሰቢያዎችን ፡ ሥዕልን
መስቀልን ፡ ጽላትን ፡ አክብራ ፡ ትቀበላለች ። በላያቸው ፡ ለተገለጸው ፡ ለእግዚአብሔር
አርአያና ፡ ለተጻፈው ፡ ስሙም ፡ ትሰግዳለች ፤ በዚህ ፡ ሥራዋም ፡ የመልካም ፡ ሥራ
ዋጋው ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከዓለማውያን ፡ ጓደኞቿ
በተለይ ፡ ረኀቦም ፡ ዘመን ፡ በሰፊ ፡ ታሪክ ፡ ክብሯን ፡ ነጻነቷን ፡ ጠብቃ ፤ ሥጋዊና ፡ መ
ፈሳዊ ፡ ጠላትን ፡ አጥቅታ ፤ ሰላምንና ፡ ድል ፡ አድራጊነትን ፡ ተጐናጽፋ ፡ ትኖራለች
በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ትወርሳለች ።

## የ ጸ ጋ ፡ ሰ ጊ ድ ።

፳ ፤ የጸጋ ፡ ሰጊድ ፡ አንደኛ ፤ ለእናትና ፡ ለአባት ፤ ኹለተኛ ፤ በዕድሜና
በመዓርግ ፡ ለከበረ ፡ ሰው ፤ ሦስተኛ ፤ ለመምህራን ፤ አራተኛ ፡ ለነገሥታት ፤ ዐ
ስተኛ ፡ ለጳጳሳት ፡ ለሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፤ ስድስተኛ ፤ ለመንፈሳውያን ፡ መላእክትና ፡ ለ
ቃን ፡ ለሰማዕታት ፡ ለነቢያት ፡ ለሐዋርያት ፡ ሰባተኛ ፤ ከዚህ ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፡ ከእግዚ
ብሔር ፡ በታች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዙፋን ፡ ለኾነችው ፡ ለእመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ድ
ግል ፡ ማርያምና ፡ ክቡር ፡ ደሙ ፡ ለፈሰሰበት ፡ መስቀል ፡ የሚቀርበው ፡ ስግደት ፡ ነው

፳፩ ፤ የጸጋ ፡ ስግደት ፡ መባሉም ፡ እግዚአብሔር ፡ በጸጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ ስለሚገ
ጽባቸውና ፡ ምስጢራዊ ፡ ሥራውን ፡ ስለሚገልጽባቸው ፡ ነው ። ለእመቤታችን ፡ ድ
ግል ፡ ማርያምና ፡ ለክቡር ፡ መስቀሉ ፡ የሚቀርበው ፡ ስግደትም ፤ የልዑል ፡ እግዚአ
ሔር ፡ ዙፋን ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ነው ። የጌታችን ፡ እግር ፡ ከቆመበት ፡ እንሰግዳለን ፡ የሚለ
ቅዱስ ፡ ቃልም ፡ የሚያስተምረን ፤ እግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ላደረጋቸው ፡ ለቅዱሳን
ይልቁንም ፡ መርጦ ፡ ከኀጢአት ፡ አንጽቶ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቀድሶ ፡ ሥጋዋን ፡ ነ
ስዋን ፡ ለተዋሐዳት ፡ ለእመቤታችን ፡ ድንግል ፡ ማርያምና ፡ ለተሰቀለበት ፡ መስቀሉ
እንድንሰግድ ፡ ነው ።

፳፪ ፤ ለእናት ፡ ለአባት ፡ በዕድሜና ፡ በመዓርግ ፡ ለከበሩ ፡ ሰዎች ፡ በጠቅላላው
ለቅዱሳን ፡ ጻድቃን ፡ ለመላእክትም ፡ የተፈጸመው ፡ ስግደት ፤ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እን
ሚያስተምረን ፤ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ይገኛል ። ያዕቆብ ፡ ለወንድሙ ፡ ለዔሳው ፡ ለአባትና ፡
ናቱ ፤ ኢያሱ ፡ በኢያሪኮ ፡ ለተገለጸለት ፡ መልአክ ፡ ናታን ፡ ለዳዊት ፡ የኢያሪኮ ፡ ሰዎች
ለነቢይ ፡ ኤልሳዕ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ለዳንኤል ፡ ሰግደዋል ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፴፫ ፡ ቍ ፡ ፯ ። ኢያ
ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፲፬ና ፡ ፲፭ ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፫ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ቅዱሳን ፡ ለቅዱሳን ፡ ሲሰግዱ ፤ ቅዱሳን ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማደሪያ ፡ በመኾናቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ለአምላክኽ ፡ ልትሰግድ ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ ልታመልክ ፡ ይገባሀል ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ትተው ፡ ረስተው ፡ ለቅዱሳን ፡ የአምልኮ ፡ ስግደት ፡ ያቀረቡ ፡ አይደለም ። ይኸውም ፡ ዕዳ ፡ በደል ፡ ኾኖ ፡ አልተቈጠረባቸውም ። ምክንያቱም ፤ ቅዱሳን ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማደሪያ ፡ መኾናቸውን ፡ በማመን ፡ ለቅዱሳን ፡ የሚቀርበው ፡ ስግደት ፡ ያደረባቸውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመሻትና ፡ በመውደድ ፡ ስለሚደረግ ፡ የስግደት ፡ ፍጻሜው ፡ ያው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቀርብ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ። ዘዳ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፲ ።

፳፬ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ኢያሱ ፡ በሰገደለት ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ የቆምክባት ፡ ምድር ፡ የተቀደሰች ፡ ናትና ፡ ጫማኽን ፡ አውልቅ ፡ ብሎ ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፤ ባንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሐዋርያው ፡ ዮሐንስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መልእክተኛ ፡ ቢሰግድ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልእክተኛ ፡ እኔ ፡ እንዳተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ነኝና ፡ ልትሰግድልኝ ፡ አይገባህም ፡ ዕወቅ ፡ እንዳለው ፡ ተጽፎ ፡ እናነባለን ። ከእነዚህ ፡ ቃላት ፡ መካከል ፡ የቦታና ፡ የዘመን ፡ ርቀት ፡ እንዳለ ፡ እንዲሁ ፡ የምስጢር ፡ ርቀት ፡ አላቸው ። ስለዚህ ፡ ለቅዱሳን ፡ ስግደት ፡ አይገባም ፡ የሚል ፡ አንዳንድ ፡ ሰው ፡ አይታጣም ።

፳፭ ፤ የቦታና ፡ የዘመን ፡ ርቀት ፡ አላቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ። የምስጢር ፡ ርቀት ፡ ግን ፡ ያላቸው ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ የላቸውም ። ምክንያቱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያው ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅዱሳኑ ፡ እንዲገለጥ ፡ አምነው ፡ ኢያሱና ፡ ዮሐንስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መልእክተኞች ፡ ቢሰግዱ ፤ ከመልእክተኞችም ፡ ወደ ፡ ኢያሱ ፡ የተላከው ፡ የቆምክባት ፡ ምድር ፡ የተቀደሰች ፡ ናትና ፡ ጫማኽን ፡ አውልቅ ፡ ብሎ ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ቢሰጥ ፤ ወደ ፡ ዮሐንስ ፡ የተላከውም ፡ እኔ ፡ እንዳንተ ፡ ነኝና ፡ አትስገድልኝ ፡ ቢል ፤ ኹሉም ፡ ከቅድስናቸው ፡ በላይ ፡ የኾነው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቅድስና ፡ በማስረዳታቸው ፤ ሰው ፡ በቅዱሳን ፡ ለቅዱሰ ፡ ቅዱሳን ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢሰግድ ፡ ዕዳ ፡ የማይኾንበት ፡ መኾኑን ፡ ስለ ፡ ገለጹልን ፡ ነው ።

፳፮ ፤ እነዚህ ፡ ቃላት ፡ ከቶ ፡ ለቅዱሳን ፡ መስገድን ፡ አይቃወሙም ። ስለዚህም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ መላእክት ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ለመውረስ ፡ የታደሉትን ፡ ሰዎች ፡ ለማገልገል ፡ የሚላኩ ፡ ቢኾኑም ፤ ሰው ፤ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከመላእክት ፡ ደረጃ ፡ በታች ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ወደ ፡ ኢያሱ ፡ የተላከው ፡ መልአክ ፡ ስግደቱን ፡ ተቀብሎ ፡ ጫማህን ፡ አውልቅ ፡ ብሎ ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠው ። ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ግን ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ሰው ፡ በመኾኑ ፤ ሰው ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ክብሩ ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ መዓርጉ ፡ ስለ ፡ ተመለሰ ፤ ወደ ፡ ዮሐንስ ፡ የተላከው ፡ መልአክ ፤ እኔ ፡ እንዳንተ ፡ ነኝና ፡ አትስገድልኝ ፡ በማለቱ ፤ ቅዱሳን ፡ ሰዎችና ፡ ቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ ባንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋዮች ፡ መኾናቸውን ፡ አስረድቷል ። እንግዲህ ፡ በኢያሱና ፡ ወደርሱ ፡ ተልኮ ፡ በነበረበው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ መካከል ፡ የታየው ፡



ልዩነት ፡ ቀርቶ ፤ በዮሐንስና ፡ ወደርሱ ፡ በተላከው ፡ መልአክ ፡ እግዚአብሔር ፡ መካ
እንዳየነው ፤ እኩልነት ፡ ቅዱሳን ፡ ሰዎች ፡ ከመላእክት ፡ ደረጃ ፡ ከደረሱ ፤ ለመላእ
የሚቀርበው ፡ የጸጋ ፡ ስግደት ፡ ለቅዱሳን ፡ ሰዎችም ፡ ሊቀርብላቸው ፡ ይገባል ፡ በማ
ፈንታ ፤ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ለቅዱሳን ፡ የሚቀርበውን ፡ የጸጋ ፡ ስግደት ፡ ይቃወ
ማለት ፡ ውሸት ፡ ነገር ፡ ነው ።

፳፯ ፤ ይልቁንም ፡ በኤልሳቤጥ ፡ ማሕፀን ፡ ያለው ፡ ሕፃን ፡ የአምላክ ፡ እ
የድንግል ፡ ማርያምን ፡ ድምፅ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፤ በደስታ ፡ እንደ ፡ ዘለለ ፡ እንደ ፡ ሰ
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ካስረዳ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ማሳበል ፡ አይቻልምና ፡ ለእ
ብሔር ፡ ዙፋን ፡ ለእመቤታችን ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ያለ ፡ ማንጐራጐር ፡ በጕል
ችን ፡ ተንበርክከን ፡ ግንባራችንን ፡ መሬት ፡ አስነክተን ፡ መስገድ ፡ ይገባናል ። ለ
ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፵ - ፵፬ ።

፳፰ ፤ እንግዲህ ፡ በዚያም ፡ ኾነ ፡ በዚህ ፡ የስግደት ፡ ፍጻሜ ፡ መድረሻው ፡ ዐ
እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ ስግደትን ፡ በክርስትና ፡ ተግባራችን ፡ ውስጥ ፡ አድርገን ፡
ጠቀምበት ፡ እንድንችል ፡ እግዚአብሔር ፡ በቸርነቱ ፡ ይርዳን ። አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ስግደት ፡ ምንድነው ? የስግደት ፡ መሠረቱ ፡ ምንድነው ?
፪ ፤ ስግደት ፡ ምንና ፡ ምን ፡ ተብሎ ፡ በስንት ፡ ይከፈላል ?
፫ ፤ የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ እንዴት ፡ ናቸው ?
፬ ፤ ለአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ስግደት ፡ ይገባልን ?
፭ ፤ የእግዚአብሔርንና ፡ የአጋንንትን ፡ ማዕድ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ መብላት ፡ ይቻላ
፮ ፤ የዛር ፡ ውሽማ ፡ ይዞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማስቀናት ፡ ይገባልን ?
፯ ፤ አምልኮቱን ፡ የለወጡትን ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ ያደርጋቸዋል ?
፰ ፤ በአምልኮቱ ፡ ለጸኑትስ ፡ ምን ፡ ያደርግላቸዋል ?
፱ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ መታሰቢያዎች ፡ ይገኛ
፲ ፤ የሀብታት ፡ የምስጢራት ፡ መታሰቢያዎችን ፡ የሰጠ ፡ ማነው ?
፲፩ ፤ መታሰቢያነታቸውና ፡ መጽሐፍነታቸው ፡ ለምንድነው ?
፲፪ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በሥዕል ፡ አማካይነት ፡ ባቀረበችው ፡ ጸሎት ፡ ምን ፡ ታገኛ
፲፫ ፤ ብርሃንን ፡ ከጨለማ ፡ ኀጢአትን ፡ ከጽድቅ ፡ ክርስቶስን ፡ ከሰይጣን ፡ ለ
ቀል ፡ ማስተካከል ፡ ይገባልን ?
፲፬ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ጸሎት ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፲፭ ፤ በኢትዮጵያ ፡ አምልኮት ፡ ጕድለት ፡ አለን ?
፲፮ ፤ ምስክሩስ ፡ ምንድነው ? ለስግደት ፡ ቦታ ፡ ይወሰናልን ? መሠረቱስ ፡ ምንድነ
፲፯ ፤ ሰው ፡ የወዳጁን ፡ ሥዕል ፡ ስለ ፡ ያዘ ፡ የወረቀት ፡ ዝምድና ፡ አለው ፡ ይባላ
፲፰ ፤ በሥዕል ፡ አማካይነት ፡ ጸሎቱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚያቀርብ ፡ ሰው ፡ ጣ
ያመልካል ፡ ይባላልን ?

www.ethiopianorthodox.org

፲፱ ፤ የጸጋ ፡ ሰጊድ ፡ ምንድነው ? የሚቀርበውስ ፡ ለማነው ? የጸጋ ፡ ስግደት ፡ መባሉ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ?

፳ ፤ የጌታችን ፡ እግር ፡ ከቆመበት ፡ እንሰግዳለን ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ምን ፡ ያስተምረናል?

፳፩ ፡ ቅዱሳን ፡ ለቅዱሳን ፡ ቢሰግዱ ፡ ዕዳ ፡ ኾነባቸውን ?

፳፪ ፡ ቅዱሳን ፡ ለቅዱሳን ፡ ሲሰግዱ ፡ ስተው ፡ ረስተው ፡ ነውን ?

፳፫ ፤ የስግደት ፡ ፍጻሜው ፡ ምንድነው ?

፳፬ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ኢያሱን ፡ ምን ፡ አለው ?

፳፭ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ዮሐንስን ፡ ምን ፡ አለው ?

፳፮ ፤ ለኢያሱና ፡ ለዮሐንስ ፡ በተነገሩት ፡ ቃላት ፡ መካከል ፡ ርቀት ፡ አለን ?

፳፯ ፤ ለኢያሱ ፡ የተነገረው ፡ ቃል ፡ ምን ፡ ያስረዳል ?

፳፰ ፤ ለዮሐንስ ፡ የተነገረው ፡ ቃል ፡ ምን ፡ ይገልጣል ?

፳፱ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለኤልሳቤጥ ፡ ምን ፡ ተናገረ ?

፴ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ማሳበል ፡ ይቻላልን ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፱ ።

## ት ሕ ት ና ።

፩ ፤ ትሕትና ፡ አንደኛ ፡ ለእግዚአብሔር ፤ ኹለተኛ ፡ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ ራስን ፡ ዝቅ ፡ ማድረግ ፡ ነው። የትሕትና ፡ ጠቅላላ ፡ ፍጻሜውና ፡ መጨረሻው ፡ መታዘዝ ፡ ነው ። ያለ ፡ ማንጐራጐር ፡ ያለ ፡ መበሳጨት ፡ ለሚፈጽመው ፡ ሰው ፡ ፍሬው ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ነው ።

፪ ፤ የትሕትና ፡ መሠረቱ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሊያገለግል ፡ እንጂ ፤ ሊያገለግሉት ፡ እንዳልመጣ ፡ ከእናንተ ፡ የበላይ ፡ አለቃ ፡ ሊኾን ፡ የሚወድ ፡ አገልጋይ ፡ ይሁናችሁ ። እናንተ ፤ ጌታችን ፡ መምህራችን ፡ ትሉኛላችሁ ፤ ነገሩም ፡ እውነት ፡ ነው ፤ እኔ ፡ በእርግጥ ፡ ጌታችሁ ፡ መምህራችሁ ፡ ነኝና ፡ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ጌታችሁ ፡ መምህራችሁ ፡ ስኾን ፡ እግራችሁን ፡ ካጠብኳችሁ ፤ እናንተም ፡ ለወንድሞቻችሁ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጉ ፡ የሚለው ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ። ማር ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፵፫—፵፭ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፲፪—፲፬ ።

፫ ፤ ጌታችን ፡ አምላካችን ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እሱ ፡ ሳይሠራው ፡ ልንሠራው ፡ ያዘዘን ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ የለም። ሰው ፡ ራሱ ፡ የማይሠራውን ፡ ለሌላው ፡ እንደሚያዝዝና ፡ ባልዋጀበት ፡ ጣት ፡ የዘንዶ ፡ ጉድጓድ ፡ ይለኩበት ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ሳይኾን ፤ ቸር ፡ መምህር ፡ እውነተኛ ፡ መሪ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፤ እሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ሠርቶ ፡ ጋሻውን ፡ ተቀብለን ፡ እንድንሠራ፡አስተምሮናል ፡ አዝዞናል ።

፬ ፤ የትሕትና ፡ ትርጓሜው ፡ ራስን ፡ ዝቅ ፡ ማድረግ ፡ ሲኾን ፤ መጨረሻው ፡ መታዘዝ ፡ ነው ፡ ብለናል ። ስለዚህም ፡ መታዘዝ ፡ በጠቅላላው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡ ኾኖ ፡ ሰው ፡ በሙሉ ፡ ልቡናው ፡ ያለ ፡ ማንጐራጐር ፡ የሚፈጽመው ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።



ሐዋርያት ፡ ከመካከላቸው ፡ እኔ ፡ ልሾም ፡ እኔ ፡ ላዝዝ ፡ በማለት ፡ ሲከራከ መምህራቸው ፡ ጌታቸው ፡ ከመካከላቸው ፡ ተነሥቶ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሊያገለግል ፡ እ ሊያገለግሉት ፡ እንዳልመጣ ፡ ከእናንተ ፡ የበላይ ፡ አለቃ ፡ ሊኾን ፡ የሚወድ ፡ አገልጋ ይሁናችሁ ፡ አላቸው ። በቃል ፡ የተናገረውንም ፡ በሥራ ፡ ሲፈጽም ፤ ልብሱን ፡ አው ሸርጥ ፡ ታጥቆ ፡ እግራቸውን ፡ አጠባቸውና ፡ ሊያገለግላቸው ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ አስ ቸው ። በቃል ፡ በሥራ ፡ ያስተማራቸውንም ፡ እንዲፈጽሙ ፡ እናንተም ፡ ለባልንጀ ችሁ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጉ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

፭ ፤ በዚህ ፡ መሠረት ፡ ሰው ፡ በመንፈስና ፡ በሥራ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይታዘዛ የትእዛዙ ፡ አፈጻጸም ፡ ዐይነትም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

አንደኛ ፡ ሰው ፡ ፍጹም ፡ ትሕትናውን ፡ ሲያሳይ ፡ ዐዋቂ ፡ ቢኾን ፡ ዕውቀት ፡ ምኔ ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ባለጠጋ ፡ ቢኾን ፡ ብልጥግና ፡ ለኔ ፡ ም ነው ፤ ቢሰጥ ፡ የማያልቅበት ፡ ባለጠጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ መትቶ ፡ ያደቅ ፡ አስሮ ፡ የሚያጠብቅ ፡ ጉልበተኛ ፡ ጀግና ፡ ቢኾን ፡ ጉልበት ፡ ለኔ ፡ ምኔ ፡ ነ ብርቱውን ፡ ማድከም ፡ ደካማውን ፡ ማበርታት ፡ የሚቻለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነ እንጂ ፤ ለኔስ ፡ የሚስማማኝ ፡ ድንቍርና ፡ ድኽነትና ፡ ድካም ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በመምከ በማስተማር ፡ በመስጠት ፡ በመልእክት ፡ ድኾች ፡ ወንድሞቹን ፡ ቢረዳ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ግዚአብሔር ፡ የታመነ ፡ አገልጋይ ፡ ይኾናል ።

፮ ፤ የትሕትና ፡ ፍጻሜ ፡ ራስን ፡ መናቅ ፤ የዕውቀት ፡ ራስ ፡ ታላቅ ፡ ባለጠ ኀያል ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማወቅ ፤ ክብሩንና ፡ ትእዛዙንም ፡ በእውነ መጠበቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ እንደዚህ ፡ ዕውቀት ፡ ሀብት ፡ ጉልበት ፡ ለእኛ ፡ ምናችን ፡ አ ለም ፡ ብለው ፡ የሰው ፡ ሕይወት ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ የሚያልፍ ፤ ዕውቀቱ ፡ ሀብቱና ፡ ጕ ቱም ፡ እንደ ፡ አበባ ፡ የሚረግፍ ፡ መኾኑን ፡ ዐውቀው ፡ እኛ ፡ የሚገባንን ፡ እንጂ ፤ ከ ገባን ፡ በላይ ፡ የሠራን ፡ አገልጋዮች ፡ አይደለንም ፤ ከዕውቀትም ፡ ነዳያን ፡ ነ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የእነሱ ፡ ናትና ፡ ለሰ የሚያዝኑ ፡ የሚራሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። ለነሱም ፡ ፍትሐ ፡ ርቱዕ ፡ ሥላሴ ፡ ይራሩ ዋልና ፡ በተባለው ፡ መሠረት ፡ የማያልፈውን ፡ የዘለዓለም ፡ ብፅዓን ፡ ከጌታቸው ፡ በላሉ ፡ ማቴ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፫ና ፡ ፮ ።

፯ ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ እግር ፡ እንዳጠበ ፤ ለጓደኞ ንና ፡ ከበታቻችን ፡ ላሉት ፡ ኹሉ ፡ በትሕትና ፡ ማገልገል ፡ ይገባናል ፤ የበታቻችን ስንል ፡ ግን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ አእምሮው ፡ ስፋት ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ጽናት ፡ የዕድ መበላለጥ ፡ ያለው ፡ መኾኑን ፡ ማስረዳት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በተፈጥሮ ፡ ታናሽ ፡ ታላቅ፡አ ማለት ፡ አይደለም ።

በዚህ ፡ መሠረት ፡ እኛን ፡ ሊያገለግል ፡ የመጣውን ፡ ፈጣሪያችንን ፡ እያሰብ የበላይ ፡ ልንኾን ፡ ብንወድ ፤ በትምህርት ፡ በምጽዋት ፡ በመርዳት ፡ ለወንድሞቻች አገልጋዮች ፡ መኾን ፡ ይገባናል ።

www.ethiopianorthodox.org

፰ ፡ መምህራን ፡ ለተማሪዎቻቸው ፡ ባለጠጎች ፡ ለድኾች ፡ ብርቱዎች ፡ ለደካሞች ፡ በማገልገል ፡ ትሕትናን ፡ ሲያከናውኑ ፡ ከጻናችው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ራሳ ችሁን ፡ ዝቅ ፡ አድርጉ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ይፈጽማሉ ። በማስተማር ፡ በምጽዋት ፡ በርዳታ ፡ የሚፈጸመው ፡ ትሕትና ፡ ውሳኔ ፡ የለውም ።

፱ ፡ ኹለተኛው ፡ መታዘዝ ፤ ለእናትና ፡ ለአባት ፡ ለሽማግሌ ፡ ለመምህራን ፡ ለመ ኳንንት ፡ ለነገሥታት ፡ ነው ። ለእናት ፡ ለአባት ፡ በፍጹም ፡ ልቡና ፡ ራስን ፡ ማዋረድና ፡ መታዘዝ ፡ እንዲገባ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ አባትኽንና ፡ እናትኽን ፡ አክብር ፡ ብሎ ፡ አዝዟል ። በሰሎሞንም ፡ አድሮ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ያባትኽን ፡ ትእዛዝ ፡ ስማ ፤ የእናትኽንም ፡ ትእዛዝ ፡ ቸል ፡ አትበል ፡ ብሎ ፡ መክሮናል ። ዘፀ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ ፡ ፲፪ ።

፲ ፤ አባትንና ፡ እናትን ፡ ማክበር ፤ ራስንም ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ለወላጅነታቸው ፡ መታዘዝ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጸጋ ፡ ነው ፤ ረዥም ፡ ዕድሜን ፡ ሀብትንና ፡ በረከትን ፡ ይሰጣል ። ለዚህ ፡ ትምህርት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ለመረዳት ፡ የምንመለከታቸው ፡ መጽሐፎቻ ችን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንጂ ፤ በከሰል ፡ ውሃ ፡ ያልተጻፉ ፡ ሴት ፡ ኖኅ ፡ አብርሃም ፡ ይስ ሐቅ ፡ ያዕቆብ ፡ እነሱንም ፡ የመሰሉ ፡ አባቶቻችን ፡ ናቸው ። ዕብ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፩—፳፩ ።

፲፩ ፤ አባትንና ፡ እናትን ፡ ማክበር ፤ ለቃላቸውም ፡ መታዘዝ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተ ለመደ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ማንም ፡ ልጅ ፡ አባቱ ፡ በሞት ፡ ወምይ ፡ በሀገር ፡ ርቀት ፡ ካል ተለየው ፡ በቀር ፤ አባቱና ፡ እናቱ ፡ ያዙበታል ፡ እንጂ ፤ በራሱ ፡ ለማዘዝ ፡ መብት ፡ የለ ውም ። ጠቅላላ ፡ ዐሳብም ፡ በወላጆች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ አባትና ፡ እናት ፡ ልጃ ቸው ፡ አንደኛ ፡ እነሱን ፡ ኹለተኛ ፡ ራሱን ፡ ሦስተኛ ፡ አገሩንና ፡ ንጉሡን ፡ አራተኛ ፡ ፈጣሪውን ፡ የሚያከብርበትንና ፡ የሚፈራበትን ፡ የሚያገለግልበትን ፡ መሥመር ፡ ለማ ስያዝ ፡ መጀመሪያ ፡ ትምህርትን ፡ ቀጥሎ ፡ ጽሕፈት ፡ ድጉስትን ፡ እርሻ ፡ ቁፋሮን ፡ በጠቅላላ ፡ የእጅ ፡ ሥራን ፡ ያስተምሩታል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የንግድን ፡ መንገድና ፡ የወታ ደርነትን ፡ ሥራ ፡ ያለማምዱታል ።

፲፪ ፤ እንዲሁም ፡ በመንፈሳዊው ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መገሥ ገሥን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መታጠቅን ፡ መስገድን ፡ ጾምን ፡ ጸሎትን ፡ በሙሉ ፡ መንፈሳዊ፡ ሥራን ፤ በሥጋዊም ፡ ረገድ ፡ ለንጉሥና ፡ ንጉሥ ፡ ለሾመው ፡ መታዘዝን ፡ በጠቅላላው ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ንጉሥ ፡ ማክበርን ፡ ያስጠኑታል ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፫—፲፯ ።

፲፫ ፤ በሥጋዊና ፡ በመንፈሳዊው ፡ ዓላማ ፡ የሥራን ፡ መሥመር ፡ ካሳዩትና ፡ ካለ ማመዱት ፡ በኋላ ፤ በዘር ፡ በሃይማኖት ፡ የምትመስለውን ፡ ሴት ፡ አጭተው ፡ ያጋቡታል ። አስፈላጊውንም ፡ ሰጥተው ፡ ንብረት ፡ ያሲዙታል ። ልጃቸውም ፡ ያዘዙትን ፡ ኹሉ ፡ ይፈ ጽማል ፡ እንጂ ፤ በእድገቱም ፡ ጊዜ ፡ ኾነ ፡ በጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ ቃላቸውን ፡ አይቃወምም ። ከትእዛዛቸውም ፡ አንድ ፡ ነጥብ ፡ አይሰርዝም ። የጋብቻን ፡ ነገር ፡ ወደፊት ፡ እናመጣዋለን ።

፲፬ ፤ ልጅ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ እስኪሸኝ ፡ ድረስ ፡ በተቻ ለው ፡ መጠን ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ሲያገለግል ፡ ይኖራል ። ሽማግሌ ፡ አባቱን ፡ ባልቴት ፡



እናቱን ፡ በሚገባ ፡ ጦሮ ፡ ቀብሮ ፡ በረከታቸውን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ በዘመኑ ፡ አበወ እንደ ፡ ነበረው ፡ ልማድ ፤ እሱ ፡ ደግሞ ፡ ለቤቱ ፡ ሰቦቹና ፡ ለልጆቹ ፡ የበላይ ፡ አለ፡ አዛዥ ፡ ገዥ ፡ ይኾናል ።

፲፭ ፤ የሽማግሌን ፡ ፊት ፡ ማክበር ፡ እንዲገባ ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር፡ሽማግሌ አክብር ፡ ሲል ፡ አዝዞናል ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ እናትንና ፡ አባትን ፡ እንደምንፈራ እንደምናከብር ፡ ያኽል ፡ ሽማግሌዎቻችንን ፡ ማክበር ፡ ይገባናል ። ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ( ትዮጵያ ፡ ታላቅ ፡ ሥራት ፡ ኾኖ ፡ ከዛሬ ፡ በፊት ፡ ይሠራበት ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ አን ሰው ፡ በመንገድ ፡ ሲተላለፍ ፡ በዕድሜ ፡ ወይም ፡ በመዓርግ ፡ የሚበልጠውን ፡ ሰ ከማቋረጫ ፡ መንገድ ፡ አቅራቢያ ፡ ቢያይ ፤ እስኪያልፍ ፡ ቆሞ ፡ ይጠብቃል ፡ እን አቋርጦት ፡ አይሄድም ። ይህም ፡ አክብሮ ፡ ተቀብሎ ፡ የመሸኘት ፡ ያኽል ፡ የሚቈጠ ነው ።

፲፮ ፤ እንዲሁም ፡ ሕፃናት ፡ በመልእክትና ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በመሄ አመካኝተው ፤ ከመንገድ ፡ ላይ ፤ ሥራ ፡ ፈተው ፡ ቦዝነው ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ቢያ ቸው ፡ የዝምድናን ፡ ርቀትና ፡ ቅርበት ፡ ሳይመረምር ፤ ባዕድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሳያር ዘመድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሳያቀርብ ፡ በትክክለኛ ፡ ፍርድ ፤ እሺ ፡ ያለውን ፡ በግንባር ፡ እን ያለውን ፡ በጨንገር ፡ ቀጥቶ ፡ በሚገባቸው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያውላቸዋል ። ስለዚህም ፡ ገር ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ መልካም ፡ ሽማግሌ ፡ ቢኖር ፤ ልጆቹ ፡ ኹሉ ፡ አባባ ፡ እገሌ ፡ ያየ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይቈጡናል ፡ ይገርፉናል ፡ እያሉ ፡ መጥፎ ፡ ልማድን ፡ ትተው ፡ በቁም ፡ ነ ላይ ፡ ይገኛሉ ። ይህም ፡ ልማድ ፡ ከመምህርነት ፡ ደረጃ ፡ የመጀመሪያውን ፡ የያዘው ፡ ነ

፲፯ ፤ ለመምህራን ፡ መታዘዝ ፡ እንዲገባን ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ የነገ ሁን ፡ መምህሮቻችሁን ፡ ዐስቡ ፤ መምህሮቻችሁን ፡ አክብሩ ፡ ሲል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱ አዝዞናል ። ይህም ፡ ሳሙኤል ፡ ለዔሊ ፡ ይፈጽመው ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ያለ ፡ ነው ። ችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ እናንተን ፡ የተቀበለ ፡ እኔን ፡ ተቀበለ ፡ በማለቱ ፤ ለ ህር ፡ መታዘዝ ፡ ለክርስቶስ ፡ መታዘዝ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስረድቷል ። ዕብ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡

፲፰ ፤ ተማሪዎች ፡ ለመምህራን ፡ ሲታዘዙ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ ቢኾን ፡ ንያት ፡ አይሰጥበትም ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደቀ ፡ መ ርቱን ፡ እንደ ፡ በግ ፡ በተኵላ ፡ መሐከል ፡ ላካቸው ፤ ለመንገድም ፡ በከረጢታቸው ፡ ጥሪ ሥንቅ ፡ ወይም ፡ መሐለቅ ፡ መለዋወጫ ፡ ጨርቅ ፤ ለእጃቸው ፡ በትር ፡ እንዳይዙ ፤ ረሱበት ፡ ቦታ ፡ የዕለት ፡ ምግባቸውን ፡ እንዲበሉ ፤ ከዕለት ፡ ምግብ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ዘብ ፡ እንዳይቀበሉ ፤ ሞትን ፡ እንዳይፈሩ ፤ በስሙ ፡ ማስተማርን ፡ እንዳያፍሩ ፡ አዘዛቸ

፲፱ ፤ እነሱም ፡ ቅርታ ፡ ሳይገባቸው ፡ ትእዛዙን ፡ ተቀብለው ፡ በነገሥታት ፡ ፊ ላንተ ፡ ስመሰክር ፡ አላፍርም ፡ በሞት ፡ ጥላ ፡ ውስጥ ፡ እንኳን ፡ ብሄድ ፡ አንተ ፡ ከኔ ፡ ጋ ነህና ፡ ክፉውን ፡ አልፈራም ፡ እያሉ ፡ እንደ ፡ በጎች ፡ በተኵላ ፡ መኻከል ፡ ተሰማሩ ። ረ ነውን ? መከራ ፡ ነውን ? መሰደድ ፡ ነውን ? መራቈት ፡ ነውን ? እሳት ፡ ነውን ? ስለት ፡ ነው መሰቀል ፡ ነውን ? የክርስቶስን ፡ ፍቅር ፡ የሚያስተወን ፡ ማነው ፡ እያሉ ፡ ዓለምን ፡ ዞረ

www.ethiopianorthodox.org

አስተማሩ ፤ እነሱም ፡ ደግሞ ፡ ከክርስቶስ ፡ የሰሙትን ፡ ትእዛዝ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቶቻቸው ፡ አስተማሩ ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፲፬-፲፯ ። መዝ ፡ ፸፫ ፡ ቍ ፡ ፩ ። ፻፲፱ ፡ ቍ ፡ ፺፯ ።

፳ ፤ ይህ ፡ ልማድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተለመደ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ተማሪዎች ፡ የመምህሮቻቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ከአባትና ፡ ከእናት ፡ ትእዛዝ ፡ በበለጠ ፡ እንደ ፡ ፈጣሪያቸው ፡ ትእዛዝ ፡ ያኽል ፡ አድርገው ፡ ይቀበሉታል ። ምክንያቱም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እናንተን ፡ የተቀበለ ፡ እኔን ፡ የተቀበለ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፵ ።

፳፩ ፤ የኢትዮጵያ ፡ መምህራን ፡ መንፈሳዊና ፡ ሥጋዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትን ፡ ጨምረው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ጽሕፈትንና ፡ ቃል ፡ ማንበብን ፡ ብቻ ፡ አያስተምሩም ። አጥፊ ፡ ተማሪም ፡ ቢገኝ ፡ እንደ ፡ ጥፋቱ ፡ መጠን ፡ መምህሩ ፡ በግንባር ፡ በጨንገር፡ይቀጣዋል ፡ እንጂ ፤ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አይቀርብም ። ለዚህም ፡ መሠረቱ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ በበትር ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ በፍቅር ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ ዝግጅት ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ልመጣ ፡ ትወዳላችሁ ፡ ሲል ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ነው ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፳፩ ።

፳፪ ፤ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መምህራን ፡ ሥራን ፡ ጠባይን ፡ ሃይማኖትን፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ ሲያስተምሩ ፤ ተማሪዎቻቸውም ፡ እግራቸውን ፡ ተከትለው ፡ ትእዛዛቸውን ፡ ተቀብለው ፡ በሥርዐት ፡ ስለሚያድጉ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ለንጉሥ ፡ ለሀገር ፡ በታማኝነት ፡ በሚያቀርቡት ፡ አገልግሎት ፡ ጕድለት ፡ የለበትም ።

፳፫ ፤ ለንጉሥ ፡ መታዘዝ ፡ እንዲገባ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ፍሩ ፡ ንጉሥን ፡ አክብሩ ፡ ሲል ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አዝዞናል ። በአቀማመጥ ፡ በቅርጥ ፡ በሥራ ፡ ልዩነት፡ ያላቸው ፡ ሕዋሳት ፡ በራስ ፡ ተሰብስበው ፡ ከራስ ፡ በተገኘው ፡ አእምሮ ፡ እየተመሩ ፤ ሥራቸውን ፡ እንዲያከናውኑ ፤ በአቀማመጥ ፡ በሥራ ፡ በኑሮ ፡ ተለያይተው ፡ የሚኖሩ ፡ የአንድ ፡ አገር ፡ ሕዝብም ፡ ባንድ ፡ ንጉሥ ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ተሰብስበው ፡ ከራስነቱ፡በተገኘው ፡ ዕውቀት ፡ እየተመሩ ፡ ኑሮዋቸውን ፡ እንዲያደረጁ ፡ በዕውቀት ፡ እንዲገለምሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሥን ፡ ለሕዝብ ፡ መሪ ፡ አድርጎ ፡ ሰጥቷል ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ።

፳፬ ፤ ራስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ያገኘውን ፡ ዕውቀት ፡ በልብ ፡ ለሕዋሳት ፡ ኹሉ ፡ እያዛመተ ፡ ዐይንን ፡ ለማየት ፡ ገሮን ፡ ለመስማት ፡ በጠቅላላው ፡ ሕዋሳትን ፡ ኹሉ ፡ ሥራቸውን ፡ እንዲያከናውኑ ፡ ቢያዝዝ ፤ ሕዋሳት ፡ በዋናው ፡ ሞት ፡ ወይም ፡ በግለኛው ፡ ሞት ፡ ማለት ፡ በዕውርነት ፡ በአንካሳነት ፡ እነዚህን ፡ በመሰለው ፡ ኹኔታ ፡ ካልታሰሩ ፡ ትእዛዙን ፡ ከመፈጸም ፡ አይታገዱም ።

፳፭ ፤ እንዲሁም ፡ ንጉሥ ፡ በማስተካከል ፡ ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ እድገት ፡ በሚመራበት ፡ ዘመን ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ራሴ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፤ ቢሾም ፡ ቢሽር ፡ ቢገድል ፡ ቢምር ፡ ቢያርቅ ፡ ቢያቀርብ ፡ ና ፡ ወይም፡ሂድ ፡ የቆመውን ፡ ቍረጥ ፤ የወደቀውን ፡ ፍለጥ ፡ ብሎ ፡ ቢያዝዝ ፡ ትእዛዙን ፡ የሚቃወም ፡ የለም ።

፳፮ ፤ የንጉሥ ፡ ልብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ የተያዘች ፡ ስለ ፡ ኾነች ፤ መዓቱን፡ ወይም ፡ ምሕረቱን ፡ ሊፈጽም ፡ ወደ ፡ ወደደበት፡ቦታ፡እንደ፡መስኖ፡ውሃ፡ይመልሳታል ።



በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ሕዋሳት ፡ እንደ ፡ ታዘዙ ፡ ከመፈጸም ፡ በቀር ፡ ዐይ
ገሮ ፡ ገሮ ፡ ዐይን ፡ እጅ ፡ እግር ፡ እግር ፡ እጅ ፡ አፍ ፡ አፍንጫ ፡ አፍንጫ ፡
ልሁን ፡ ብትል ፡ እንዳይቻላት ፤ እንዲሁም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ በየታዘዙበት ፡ ይኖሪ
እንጂ ፤ ንጉሥን ፡ ቀብቶ ፡ ያነገሠ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመቃወም ፡ አይቻ
ውም ።

፳፯ ፤ ትሕትና ፡ ራስን ፡ ዝቅ ፡ በማድረግ ፤ በሙሉ ፡ ልቡናም ፡ ለእግዚአብሔ
ለንጉሥ ፡ ለአባት ፡ ለእናት ፡ ለወንድም ፡ በመታዘዝ ፡ ይፈጸማል ።

እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በምሕረቱ ፡ ባሰበን ፡ በቸርነቱ ፡ በጐበኘን ፡ ጊ
ከወደቅንበት ፡ የመከራ ፡ ቦታ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርገን ፡ ዘንድ ፡ ከጸናቺው ፡ ከእግዚ
ሔር ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ራሳችንን ፡ ዝቅ ፡ እናድርግ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ም ።

፳፰ ፤ የትሕትና ፡ ተቀዋሚው ፡ ትዕቢት ፡ ነው ። ትዕቢቱ ፡ ኹለት ፡ ዐይ
ስለ ፡ ኾነ ፤ አንደኛው ፡ ትዕቢት ፡ ኹለተኛው ፡ ትዝኅርት ፡ (ኵራት) ፡ ይባላል ።

ትዝኅርት ፤ ያለባበስ ፡ ያቈራረስ ፡ ያጐራረስ ፡ ያስተያየት ፡ ያካሄድ ፡ ያረማመ
በጠቅላላው ፡ የሥጋዊ ፡ ኹኔታ ፡ ነው ። ትዕቢት ፡ ግን ፡ የልቡና ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ የነ
ጭምር ፡ ነው ።

፳፱ ፤ የትዕቢት ፡ መጀመሪያው ፡ ምንጩ ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ። ኋላ ፡ ግን ፡
ቺን ፡ ዕፀ ፡ በለስ ፡ ብትበሉ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትኾናላችሁ ፤ ክፉና ፡ መልካ
ታውቃላችሁ ፡ ሲል ፡ በዘራው ፡ ሐሰተኛ ፡ ስብከት ፤ አዳምና ፡ ሔዋንም ፡ ከወጥመ
ገቡ ። ከዚያ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ የትዕቢት ፡ መንፈስ ፡ ስላደረበት
ግዚአብሔር ፡ የታዛዥነትን ፡ መልክ ፡ ሊያሳይ ፡ አልቻለም ።

፴ ፤ አዳም ፡ ከዲያብሎስ ፡ የወረሳት ፡ የመጀመሪያ ፡ ኀጢአቱ ፡ ይህቺ ፡ ትዕ
ናት ። በዚች ፡ ኀጢአት ፡ ምክንያት ፤ የዓለም ፡ ጕዳና ፡ ኹሉ ፡ የተባላሸ ፡ ወጣ ፡
ኾነ ። በዚህች ፡ ኀጢአት ፡ ምክንያት ፡ በሰው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሞት ፡ ስለ ፡ ተፈረደ
ዳም ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ የበደሉትንም ፡ ያልበደሉትንም ፡ ሞት ፡ አንድ ፡ አድርጎ
ቸው ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ።

፴፩ ፤ በዚያ ፡ በመከራ ፡ ዘመንም ፡ የሚያድን ፡ የሚረዳ ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ ባየ ፡
ክብር ፡ ጽድቅ ፡ ጥቅም ፡ የማይሻው ፡ አምላክ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ የባሪያውን ፡ ሥጋ ፡ ነሥ
ሰው ፡ ኾነ ፤ በመስቀል ፡ እስከ ፡ መሞትም ፡ ድረስ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ተዋረደ ። ፊ
ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፯-፱ ።

በጲላጦስ ፡ በሄሮድስ ፡ አደባባይ ፡ በሕዝብና ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ራቁ
በመቆሙ ፤ ራቁቱን ፡ በመሰቀሉ ፤ ሞትን ፡ ኀጢአትን ፡ ቀጣቸው ። በመስቀሉ ፡ ኀ
ትዕቢት ፡ ተሻረች። ትሕትና ፡ ሰፋች ። በደሙም ፡ ምንጭነት ፡ በቅላ ፡ ለምልማ ፡ አ
ፍሬዋን ፡ ለምእመናን ፡ ሰጠች ።

፴፪ ፤ ወንድሞቻችን ፡ ራሱን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደረገ ፡ ይዋረዳልና ፡ ራሱንም
ረደ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላልና ፡ ከሰይጣን ፡ የተገኙትን ፡ ትዕቢትን ፡ ትዝኅርትን ፡ ት

www.ethiopianorthodox.org

ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥራና ፡ በቃል ፡ ያስተማረንን ፡ ትሕትናን ፡ ገንዘብ ፡ እናድርግ ። ትሕትናን ፡ በሙሉ ፡ ልቡ ፡ የሚፈጽም፡ሰው፡ ኹሉ ፤ በፍቅሩ፡ ተስቦ ፤ ከዙፋኑ ፡ ወርዶ ፤ ለሞት ፡ ተዋርዶ ፡ የተበጀውን ፡ አምላክ ፡ በመታመን ፡ እንዳገለገለ ፡ ምስክሩ ፡ ሥራው ፡ ነው ። መጽ ፡ ኪዳን ፡

፴፫ ፤ ስለዚህም ፡ ትሑት ፡ ሰው ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ሳያፍር ፡ ሳይፈራ ፡ የፈጣሪውን ፡ ቸርነት ፡ በሥራና ፡ በቃል ፡ ከመሰከረ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ በሰማያዊ ፡ አባቱና ፡ በቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ ፊት ፡ ገልጦ ፡ ዋጋውን ፡ እንደሚሰጠው ፡ የታመነ ፡ ነውና ፤ ኹላችን ፡ ለትሕትና ፡ እንሽቀዳደም ፤ ለፍጻሜውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳን ። አሜን ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ የትሕትና ፡ መሠረት ፡ ማነው ?

፪ ፤ ስለ ፡ ትሕትና ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ፡የምናገኘው ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ የትኛው፡ ነው ?

፫ ፤ ክርስቶስ ፡ ለሐዋርያት ፡ ትሕትናን ፡ ሲያስተምር ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ ነውን ?

፬ ፤ ለአባት ፡ መታዘዝ ፡ እንዴት ፡ ነው ?

፭ ፤ የሀገር ፡ ሽማግሌ ፡ አከባበር ፡ እንዴት ፡ ነው ?

፮ ፤ በኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ ምንገደኛ ፡ በዕድሜና ፡ በመዓርግ ፡ የሚበልጠውን ፡ ሲያይ ፡ ምን ፡ ያደርግ ፡ ነበር ?

፯ ፤ የኢትዮጵያ ፡ መምህራን ፡ ምን ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ?

፰ ፤ አንድ ፡ አጥፊ ፡ ተማሪ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርብና ፡ በገንዘብ ፡ ይቀጣ ፡ ነበርን ?

፲ ፤ ንጉሥን ፡ ማክበር ፡ እንዴት ፡ ነው ?

፲፩ ፤ ንጉሥን ፡ ስለ ፡ ማክበር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ በመጽሐፍ፡ ቅዱስ ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ ይገኛል ?

ምዕራፍ ፡ ፴ ።

ን ጽ ሕ ና ።

፩ ፤ ኩኑ ። ቅዱሳነ ። እስመ ፡ አነሂ ፡ ቅዱስ ፡ አነ ። እኔም ፡ ቅዱስ ፡ ነኝ ፡ እናንተም ፡ ቅዱሳን ፡ ኹኑ ። ዘሌ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፪ ።

ይህ ፡ ቃል ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኬ ፡ ነው ፡ የሚልና ፡ ሰውነቱን ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የሚታመን ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከሚጠላው ፡ ከማንኛውም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ርቆ ፤ ከርኩስም ፡ ንጹሕ፡ኾኖ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩን፡ እንዲያገለግልና ፡ ሕጉን ፡ እንዲከተል ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ።

፪ ፤ ንጽሕና ፡ ፫፡ ዐይነት ፡ ነው ። ፩ኛ፡ በሥራቸው፡ ንጹሓን ፡ የኾኑ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው፡ ባለው፡ መሠረት ፤ ሰውነታቸውን፡



ከበደል ፡ ልቡናቸውን ፡ ከቂም ፡ ከበቀል ፡ ንጹሕ ፡ አድርገው ፡ በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር፡ ላይ፡ አምልኮተ፡ ጣዖትን ፡ ሳይቀላቅሉ ፤ በተበደለ ፡ ፍርድ ፡ ሳያደሉ ፡ መማለጃ ፡ ሳይበሉ፡ ኹሉን ፡ በመውደድ ፡ እግዚአብሔርን፡ መስሎ ፡ መኖር ፡ ነው።መዝ ፡ ፪፲፱ ፡ ቍ፡ ፩። እንዲህስ ፡ ያለ ፡ ፍጹምና ፡ ንጹሕ ፡ ልብ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያዩታልና ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፰ ።

፫ ፤ ፪ኛውም ፡ አንደኛው ፡ ከማክበር ፡ ጋራ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ሊፈጽሙት ፡ የታዘዘው፡ ባልና፡ ሚስት፡ አንድ፡ አካል ፡ ናቸው።እግዚአብሔር ፡ አንድ፡ ያደረገውን፡ ሰው፡ ሊለየው ፡ አይችልም፡ ባለው ፡ መሠረት ፤ አንድ ፡ ወንድ ፡ ባንድ ፡ ሴት ፤ አንድ ፡ ሴት ፡ ባንድ ፡ ወንድ ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩበት ፤ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ተመሥርቶ ፡ በሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ የጸና፡ የተቀደሰ፡ ጋብቻ ፡ ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ፮ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፱ ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ፡ ፳፯።

፬ ፤ ጋብቻ ፡ በመጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ታዘዘው ፡ ሲፈጸም፡ የከበረ ፡ ነው ፤ እንኳን ፡ ለሰውነታቸው ፡ ለምንጣፋቸው ፡ ርኵሰት ፡ የለውም ፤ ምስጢሩም፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ፡ ተዋሕዶውም ፡ መለያየት ፡ የለሌበት ፡ ጥብቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ነቢይ ፡ ሰሎሞን ፡ በክርስቶስና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መስለውታል ። ይህ ፡ ሕግ ፡ ክርስቶስ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራስ ፡ ገዥ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ወንድ ፡ ለሴት ፡ የበላይ ፡ አሳዳሪ ፡ አዛዥ ፡ መኾን ፡ እንዲገባው ፤ ክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንደ ፡ ወደዳትና ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ ለወጠላት ፤ እንዲሁም ፡ ወንድ ፡ ሚስቱን ፡ ሕይወቱን ፡ እስኪለውጥላት ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡ ሊወዳትና ፡ ሊረዳት ፤ እንደ ፡ ዐይኑም ፡ አርጎ ፡ ሊጠብቃት ፡ እንዲገባው ፤ ክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ተዋሕዶ ፡ እንዲኖር ፡ ወንድም ፡ በሚስቱ ፡ ብቻ ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፤ እንዲሁም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለክርስቶስ ፡ እንደምትታዘዝ ፡ እሱንም ፡ ብቻ ፡ በማምለክ፡ ጸንታ ፡ እንድትኖር ፤ ሴት ፡ ለባሏ ፡ መታዘዝ ፡ በሱ ፡ ጸንታ ፡ መኖር ፡ ጌታዬ፡ልትለውና ፡ በፍጹም ፡ ልታከብረው ፡ እንደሚገባት ፡ ያዝዛል ። ኤፌ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፳፪ - ፴፪ ።

፭ ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ ወንድ ፡ ለሚስቱ ፡ የሚገባትን ፡ ለእስዋ ፡ እንጂ ፡ ለሌላ ፡ እን‹…› ያደርግ ፤ ሴትም ፡ ለባሏ ፡ የሚገባውን ፡ ለርሱ ፡ እንጂ ፡ ለሌላ ፡ እንዳታደርግ ፡ ይከለክላል፡ ወንድ ፡ ራሱ ፡ ሀብቱም ፡ ቢኾን ፡ ለሚስቱ ፡ እንጂ ፡ ለርሱ ፡ እንዳይደለ ፤ እንዲሁ‹…› ሴት ፡ ራሱዋ ፡ ያላትም ፡ ኹሉ ፡ ቢኾን ፡ ለባሏ ፡ እንጂ ፡ ለእርሱዋ ፡ እንዳይደለች ፡ በ‹…› ብቻ ፡ አንድ ፡ ከኾኑ ፡ በኋላ ፡ በየበኩላቸው ፡ ለራስ ፡ ማድላትን ፡ የተደገፈ ፡ ግለኛ ፡ ሥ‹…› ጣን ፡ እንደ ፡ ሌላቸው ፡ ያስተምራል ።

፮ ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ በባሕርዩ ፡ የምትንቀሳቀሰውን ፡ እንስሳዊት ፡ ጠ‹…› ይን ፡ እንዲያሸንፍ ፤ በጠቅላላው ፡ መሻት ፡ መግዛትን ፡ እንዲችል ፡ የሚያደርገውና ፡ ኖኅን ፡ ሄኖክን ፡ የሚያስመስለው ፡ ታላቅ ፡ ንጽሕና ፡ ነው ።

፯ ፤ ፫ኛ ፡ ድንግልና ። ድንግልና ፡ አንደኛውን ፡ የሚፈጸም ፤ ኹለተኛውን ፡ የ‹…› ይከተል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከማሕፀን ፡ ጀምሮ ፡ ለመረጣቸውና ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ ለ‹…› ደላቸው ፡ ጃንደረቦች ፤ ወይም ፡ ራሳቸውን ፡ ስለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ጃንደረባ ፡ ላ‹…› ረጉ ፡ ሰዎች ፡ በሕግ ፡ የታወቀና ፡ የተፈቀደ ፡ ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፲—፲፱ ።

www.ethiopianorthodox.org

፰ ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከናቱ ፡ ማሕፀን ፡ ጀንደረባ ፡ ኾኖ ፡ ከተወለደና ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ ከሰለበው ፡ በቀር ፤ ከእንስሳት ፡ የሰው ፡ ከሰው ፡ የመላእክት ፡ ሕግ ፡ እንዲበልጥ፡ ዐውቆ ፡ ሥጋ ፡ ደካማ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ መንፈስ ፡ ግን ፡ ብርቱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተረድቶ ፤ ሚስትን ፡ ልጅን ፡ ቤትን ፡ ንብረትን ፡ ትቶ ፡ ለዓለሙ ፡ ከማሰብ ፤ ለኑሮም ፡ ከመጨነቅ ፡ ወጥቶ ፤ መስቀሉን ፡ ተሸክሞ ፤ በሕይወቱ፡ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ክርስቶስን ፡ ለመከተል ፡ የሚፈልግ ፤ ድንግልናውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብፅዓት ፡ አድርጎ ፡ ቢሰጥ ፤ በብሉይ፡ኪዳን ፡ በሐዲስ ፡ ኪዳንም ፡ ያማረና ፡ የተወደደ ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፳፯-፳፱ ።

፱ ፤ ይህን ፡ ሕግ ፡ የሚፈጽም ፡ መልከጼዴቅን ፡ ኤልያስን ፡ ይመስላል ። ፈጣሪውን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ይከተላል ። ንጹሕ ፡ መባል ፡ ንጽሕና ፡ የባሕርዩ ፡ ከኾነው ፡ ከልዑል ፡ አምላክ ፡ ጀምሮ ፡ በአምላክ ፡ ቸርነት ፤ በሰውም ፡ በመላእክትም ፡ ወገን ፡ ንጽሕና ፡ ዕድል ፡ ኾኖ ፡ ለተሰጣቸው ፡ ኹሉ ፡ ይሰጣል ። ነገር ፡ ግን ፡ ለእሳት ፡ ሙቀት ፡ እንጂ ፡ ቅዝቃዜ ፤ ለውሃ ፡ ቅዝቃዜ ፡ እንጂ ፡ ሙቀት ፡ እንደሌለ ፤ በእግዚአብሔር ፡ አምላካችን ፡ ጽድቅ ፡ እንጂ ፡ ኀጢአት ፤ እውነት ፡ እንጂ ፡ ሐሰት ፡ ስለማይገኝበት ፤ ንጹሐ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ። ፍጡራን ፡ ግን ፡ ማንኛውንም ፡ ቀለም ፡ እንደሚቀበል ፡ አዲስ ፡ ጨርቅ፤ ጽድቅም ፡ ኀጢአትም ፡ ስለሚስማማቸው ፤ በንጽሕናቸው ፡ ጕድለት ፡ አለበት ።

፲ ፤ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ተብሎ ፡ ቅዱሳን ፤ ንጹሕ ፡ ተብሎ ፡ ንጹሓን ፡ ቢያሰኘም ፤ በቅድስናውና ፡ በቅድስናችን ፤ በንጽሕናውና ፡ በንጽሕናችን ፡ መኻከል ፡ ያለው ፡ ርቀት ፤ ሕሊና ፡ መርምሮ ፡ የማይደርሰው ፡ ነው ።

፲፩ ፤ ድንግል፡መባል፡ግን፡ በባሕርዩ ፡ ፍትወት ፡ እንስሳዊት ፡ ለምትንቀሳቀስበት ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ለፈጣሪ ፡ ከፍጡራንም ፡ ለመላእክት ፡ አይሰጥም ። ስለዚህ ፡ ፍትወትን ፡ ታግለው ፡ ድል ፡ ነሥተው ፤ ያለፉ ፡ ቅዱሳን ፡ አበው ፡ መላእክትን ፡ የመምሰልና ፡ ውሳጤ ፡ መንጠላእት ፡ ገብቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማገልገል ፡ ዕድል ፡ አላቸው ።

፲፪ ፤ ወደ ፡ ደስታ ፡ ቦታ ፡ ለመድረስ ፡ ጠባቡን ፡ በር ፡ ያለፉ ፡ አባቶቻችን ፡ ብጹዓን ፡ ናቸው ። ድንግልና ፡ ከዓለሙ ፡ መለየት ፤ ቦታ ፡ ወስኖ ፡ ከዲያብሎስና ፡ ከሰራዊቱ ፡ ጋራ ፡ መዋጋት ፤ በጠቅላላውም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በገዳመ ፡ ቆሮንቶስ ፡ የፈጸመውን ፡ ቅዱስ ፡ ተግባር ፡ መፈጸም ፡ ስለሚያስፈልገው ፤ በየጫካው ፡ በየበረሃው ፡ በየተራራውና ፡ በየኮረፍታው ፡ ጤዛ ፡ ልሰው ፡ ድንጋይ ፡ ተንተርሰው ፤ ግርማ ፡ ሌሊትን ፡ ድምፀ ፡ አራዊትን ፡ ጻብአ ፡ አጋንትን ፡ ረኀቡን ፡ ጽሙን ፡ ቍረ ፡ ክረምትን ፡ ዋዕየ ፡ ሐጋይን ፡ ችለው ፡ ታግሠው ፤ የፍየል ፡ ሌጦ ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ለብሰው ፡ ለዓለሙ ፡ ፍቅር ፡ ሳይጨነቁ ፤ የምትመጣውን ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ሲናፍቁ ፡ በቦታና ፡ በግብር ፡ ተባሕትዎ ፡ ሕይወታቸውን ፡ ያሳለፉ ፡ አባቶቻችን ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።

፲፫ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር፡የድል፡አክሊል፡ለሚገባቸው ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ቀን፡ ስላዘጋጀ ፤ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ባንደኛውና ፡ በኹለተኛው፡በሦስተኛውም፡ክፍል ፡የተገለጠውን ፡ የፈጸሙ ፡ ኹሉ ፤ ደስታቸውን ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ይወስዳሉ ። ዕብ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፴፯-፴ ።



፲፬ ፤ የንጽሕና ፡ ተቃዋሚው ፡ ዝሙት ፡ ነው ፤ ንጽሕና ፤ በሕግ ፡ የተከለከለ
ኹሉ ፡ ከመሥራት ፡ መጠበቅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ከሕግ ፡ ተላልፎ ፡ የተከለከውን ፡ መ
ትና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ሰውነትን ፡ ማርከስ ፡ ዝሙት ፡ ነው ። ንጹሕና ፤ (
ባር ፡ ኹሉ ፡ ፍጻሜ ፡ እንደ፡ ኾነ ፤ ዝሙትም ፡ የኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ናት ፤ ስለ
ከዝሙት ፡ ርቀን ፡ ንጽሕናን ፡ ለመፈጸም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳን ። አሜን ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ንጽሕና ፡ ማለት ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፪ ፤ ከንጽሕና ፡ ክፍሎች ፡ አንደኛው ፡ ኹለተኛውና ፡ ሦስተኛው ፡ ምን ፡ ፃ
ናቸው ?
፫ ፤ ጋብቻ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፬ ፤ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ትምህርት ፤ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ ይገኛ
፭ ፤ ድንግልና ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፮ ፤ ከጋብቻ ፡ ልዩነቱ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፯ ፤ ስለ ፡ ድንግልና ፡ ትምህርት ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ ይገኛ

ምዕራፍ ፡ ፴፩ ።

ት ዕ ግ ሥ ት ።

፩ ፤ ትዕግሥት ፡ ለሰው ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ መከራ፡ቢያገኘው፡በሕሊናው፡መማ
በሃይማኖቱ ፡ መጠራጠር ፡ ሳይኖርበት ፤ የደረሰበትን ፡ መከራ ፡ አልፎ ፡ ከፈጣሪ ፡ የ
ገኘውን ፡ ዋጋ ፡ በማያወላውል ፡ ተስፋ ፡ የሚፈጽመው ፡ ታላቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ።
ትዕግሥት ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የተሰጠን ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ በእግዚአብሔር ፡ የ
ታመኑ ፡ ኹሉ ፡ ታገሡ ፤ ልባችሁን ፡ አጽኑ ፤ እኔ ፡ ዓለምን፡ድል፡ነስቸዋለሁና፡እናንተ
ጽኑ ፤ ወደ ፡ ጠባቡ ፡ በር ፡ ለመግባት ፡ በርቱ ፤ ጨክኑ ፡ የሚለው፡ነው ። መዝ ፡ ፴፩ቍ፡
፪ ፤ ይህ ፡ ቃል ፡ በመሪነቱ ፡ ከየአንዳንዳችን ፤ መታዘዝን ፤ ይጠይቃል ።
ግሥት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሲኾን ፡ ዋጋ ፡ ለማሰጠት ፡ የሚችለው ፡ በፈተናው ፡ ጊዜ ፡
ብሮ ፡ ለሚፈጽመው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በመልካም ፡ ጊዜስ ፡ ኹሉም ፡ ጻድቅ ፡ ነው ። ጠ
፴፪ ፡ ቍ ፡ ፭ ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ የጦር ፡ ሜዳነት ፡ እንደ ፡ ተራበ ፡ አንበሳ ፡ አፉን ፡ ሰ
ቅቅ ፡ ሊውጣቸው ፡ ከሚፈልግ ፡ ከሰይጣንና ፡ ባሪያ ፡ ልታደርጋቸው ፡ ከምትፈ
ቸው ፡ ከኀጢአት ፡ ጋራ ፡ ሊዋጉ ፡ የተሰለፉት ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ብዙዎች ፡ ነበሩ ፤
ግን ፡ አሸናፊዎች ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፰ ።
፫ ፤ የትዕግሥት ፡ ተቃዋሚው ፡ ፈተና ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ፈተና ፡ ሲመጣ ፤ (
ሚስት ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ወንድም ፡ አያት ፡ ባዕድ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ ጠላት፡በ
ንብረት ፡ ማንኛውንም ፡ ሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ ኹኔታ ፡ ሳይለይ ፤ በኹሉም ፡ ዐይነ
ይመጣልና ፤ ትዕግሥትን ፡ የዘወትር ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገ ፡ ከጥፋት ፡ ይድናል ፤ ከ

www.ethiopianorthodox.org

መዱ ፡ ያመልጣል ፡ እንጂ ፤ ቍጡ ፡ ብስጩ ፡ ሰው ፤ ሊያልፈው ፡ አይችልም ። ፈተና ፤ ራስን ፡ ወገንን ፡ ወይም ፡ ገንዘብን ፡ በመውደድ ፡ ይመጣል ።

፬ ፤ ምንጮቹ ፡ ግን ፡ የተወሰኑ ፡ አይደሉም ፤ ኾኖም ፡ ትዕግሥትን ፡ ጋሻ ፡ አድርጎ ፡ የሚከራከር ፡ ያሸንፈዋል ። ከተከራካሪዎች ፡ ውስጥ ፡ ጥቂቶቹ ፡ ከነሱም፡በላይ፡ በስውርና ፡ በግልጥ ፡ መሪያቸውን ፡ ተከትለው ፡ የፈጸሙት ፡ ቅዱስ ፡ ተግባር ፡ ባጭሩ ፡ ከዚህ ፡ ተጠቅሶዋል ።

፭ ፤ ሀ) ከአዳም ፡ ሰባተኛው ፡ ትውልድ ፡ ሄኖክ ፡ በዘመኑ ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎች ፡ መሐከል ፡ በጊዜው ፡ የገጠመውን ፡ ኹሉ ፡ ታግሦ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመልካም ፡ ስለ፡ አገለገለው ፤ እግዚአብሔር ፡ ሞትን ፡ ወደማያይበት ፡ ቦታ ፡ አወጣው ።

ለ) ኖኅ ፡ በሰባ ፡ ትካት ፡ መሐከል ፡ ይሠራ ፡ ከነበረው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኀጢአት፡ ተጠብቆ ፡ ተግዳሮታቸውንም ፡ ታግሦ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ አዳነው ፤ ለዓለምም ፡ አባት ፡ አደረገው ።

፮ ፤ ሐ) አብርሃም ፡ በሀገር ፡ ባባት ፡ በሚስት ፡ በልጅ ፡ ፍቅር ፡ ተፈተነ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሃይማኖት ፡ በትዕግሥት ፡ ለሥራ ፡ ስለ ፡ ረዳችውና፡በኹሉም ፡ ታማኝ ፡ ኾኖ፡ስለ፡ ተገኘ ፤ እምነቱ ፡ ጽድቅ ፡ ኾኖ ፡ ተቈጠረለት ። ያዕ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፳፩—፳፬ ። ዕብ ፡ ም፡ ፲፩ ፡ ፩—፲፭ ። የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ የሕዝብና ፡ የአሕዛብ ፡ አባት ፡ ተባለ ።

መ) ኢዮብ ፡ በራሱ ፡ በልጆቹ ፡ በከብቱና ፡ በሚስቱ ፡ ተፈተነ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በኹሉም ፡ በደል ፡ አልተገኘበትም ። ስለዚህ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በመላእክት ፡ ዘንድ፡ ተመሰገነ ። ሐዋርያትም ፡ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ያለ ፡ ትዕግሥት፡የሚታገሡትን ፡ ሰዎች ፡ እና መሰግናቸዋለን ፡ ብለው ፤ የትዕግሥት ፡ መሪነቱን፡ገልጠው ፡ ክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ እሱን፡ እንዲከተሉ ፡ አስተማሩ ። ኢዮብ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፩—፲ ።

፯ ፤ ሠ) ዳዊት ፤ በሳኦል ፡ በልጆቹ ፡ በራሱም ፡ ዐሳብ፡ተፈተነ ፤ በራሱ ፡ ኀጢአት፡ የመጣበትን ፡ በንስሐ ፤ በሳኦልና ፡ በልጆቹ ፡ የመጣበትን፡በትዕግሥት፡ አርቆ ፤ የእግዚአብሔር፡ታማኝ፡ ኾነ ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ፩-፳ ። ራሱ፡ዳዊት፡ከኀጢአቴ ፡ ኹሉ ፡ አዳንከኝ፤ ለሰነፎች ፡ መዘባበቻ ፡ አደረግኸኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንተ ፡ ፈጥረኸኛልና ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ አፌን ፡ አልከፈትኩም ፤ ትዕግሥቴም ፡ ታንተ ፡ ያገኘሁት ፡ ነው ፡ ብሎዋል ። እግዚአብሔርም ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ልቤ ፡ የታመነ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ሲል ፡ መስክሮለታል ። መዝ ፡ ፴፱ ፡ ቍ ፡ ፰ ፡ ፱ ። የሐ ፡ ሥ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፳፪ ።

፰ ፤ ረ) ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ በትዕግሥት ፡ ሰውነታችንን ፡ ገንዘብ ፡ ማድረግ ፡ እንድንችል ፤ ሸክም ፡ የከበዳችሁ ፡ ኹሉ ፡ ወደኔ ፡ ኑ ፡ እኔ ፡ አሳርፋችኋለሁ ፡ ሲል ፡ የጠራን ፡ አምላካችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አይሁድ ፡ መከራ ፡ ሲያጸኑበት ፡ አልተቀየመም ፤ ሲሰድቡትም ፡ አልተሳደበም ። በግ ፡ ጠጕሩን ፡ ሲሸልቱት ፤ ከሌሊት ፡ ቍር ፡ ከመዓልት ፡ ሐሩር ፡ የምድንበትን ፡ ጠጕሬን ፡ ለምን ፡ ትሸልቱኛኛላችሁ ፡ ብሎ ፡ እንደ ማይናገር ፡ ሲወጉት ፡ ሲቸነክሩት ፡ ሲገፉት ፡ ሲገርፉት ፡ ሲተፉበት ፡ በምን ፡ ዕዳዬ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አልተናገረም ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፳፫ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፳፰ ።



፱ ፤ ሲቻለውም ፡ አባት ፡ ሆይ ፤ የሚሠሩትን ፡ አያውቁምና ፡ ይቅር ፡ በላቸው ፡ ብሎ ፡ ጸለየላቸው ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ቍ ፡ ፴፬ ፤ እንጂ ፤ በቃል ፡ አልዘለፋቸውም ። በመቅሠፍትም ፡ አልገረፋቸውም ። ስለዚህም ፡ ኑ ፡ ተከተሉኝ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ጠራን ፡ ልንከተለው ፡ በፈለግን ፡ ጊዜ ፡ ሰይጣን ፡ ድል ፡ እንዳይነሣን ፤ ሥጋ ፡ ደካማ ፡ ነው ፡ መንፈስ ፡ ብርቱ ፡ ነውና ፡ ወደ ፡ ፈተና ፡ እንዳትገቡ ፡ ትጉ ፡ ጸልዩ ፡ ብሎ ፤ ከፈተና ፡ ለማምለጥ ፡ ብንፈልግ ፡ አስቀድሞ ፡ በጸሎት ፡ መከላከል ፡ እንዲገባን ። ማቴ ፡ ም ፡ ፳፮ ፡ ቍ ፡ ፵፩ ። ፈተናው ፡ እንደ ፡ ወጥመድ ፡ ድንገት ፡ ቢደርስብን ፡ ግን ፡ በትዕግሥት ፡ መታገልና ፡ ማሸነፍ ፡ እንዲገባን ፡ ሰፊ ፡ መንገድ ፡ አለ ፤ ፍጻሜውም ፡ ጥፋት ፡ ነው ። ወደሱ ፡ የሚገቡ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ወደ ፡ ሕይወት ፡ የምትወስድ ፡ ጠባብ ፡ በር ፡ ጭንቅ ፡ መንገድ ፡ አለች ፤ ወደሷ ፡ የሚገቡ ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ።

፲ ፤ ስለዚህ ፡ ወደ ፡ ጠባቡ ፡ በር ፡ ለመግባት ፡ በርቱ ፤ ክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ መከራ ፡ ቢያመጡባችሁ ፡ ከሀገር ፡ አስወጥተው ፡ ቢሰዱዋችሁ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ። ከእናተ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበሩት ፡ ነቢያትንም ፡ እንዲሁ ፡ አድርገዋቸዋልና ፡ ቢሰድቧችሁ ፤ በስሜ ፡ ስለ ፡ አመናችሁ ፡ ቢጠሉዋችሁ ፤ እንደ ፡ ክፉ ፡ አድራጊ ፡ ክፉ ፡ ስም ፡ ቢያወጣላችሁ ፡ ዋጋችሁ ፡ በሰማይ ፡ ነውና ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ። ፯ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

፲፩ ፤ ዓለም ፡ ወገኖቹን ፡ ይወዳል ። እናንተ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ከዓለም ፡ መረጥኋችሁ፡ እንጂ ፤ ከዓለም ፡ አይደላችሁም ፤ ስለዚህ ፡ ዓለም ፡ አይወዳችሁም ። ዓለም ፡ እኔንም ፡ ወዶ ፡ ቃሌንም ፡ ጠብቆ ፡ ቢኾን ፡ እናንተንም ፡ በወደደ ፡ ቃላችሁንም ፡ በጠበቀ ፡ ነበር ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፭ ፡ ቍ ፡ ፲፯—፳፩ ።

፲፪ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ዓለሙን ፡ ድል ፡ ነስቼዋለሁና ፡ እናንተም ፡ ጽኑ ፡ በትዕግሥታችሁ ፡ ነፍሳችሁን ፡ ታገኛላችሁ ፡ ብሎ ፡ አስተምሮናል ። ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ ፴፪ ። መከራን ፡ የሚታገሡ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይወርሳሉ ። ስለዚህ ፡ እኛ ፡ ኹላችን ፡ ትዕግሥትን ፡ ማጥናት ፡ አለብን ። ነገር ፡ ግን ፡ በቀናችው ፡ ሃይማኖት ፡ በበጎ ፡ ምግባር ፡ ጸንተን ፡ መከራን ፡ ብንታገሥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ኀጢአት ፡ ሠርተን ፡ በፍርድ ፡ የመጣብንን፡ መከራ ፡ ብንታገሥ ፡ ዋጋ ፡ የለንም ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፳ ።

፲፫ ፤ በመልካም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የመጣባቸውን ፡ መከራ ፡ የሚታገሡ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኀይሉ ፡ ጌትነቱ ፡ ቸርነቱ ፡ ይገለጽባቸዋልና ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። ኹላችንም በትዕግሥት ፡ የሚገኘውን ፡ ብፅዓን ፡ ለማግኘት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳን ። አሜን ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ትዕግሥት ፡ ማለት ፡ ምንድነው ?
፪ ፤ ስለ ፡ ትዕግሥት ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ማነኛው ፡ ነው ?
፫ ፤ የትዕግሥት ፡ አብነቶች ፡ እነማን ፡ ናቸው ?
፬ ፤ ሄኖክ ፡ ለአዳም ፡ ስንተኛው ፡ ትውልድ ፡ ነው ?
፭ ፤ የሄኖክ ፡ ሥራው ፡ ምንድነው ?

www.ethiopianorthodox.org

፯ ፤ ሄኖክ ፡ ሞትን ፡ አይቶአል ፡ ወይ ?
፯ ፤ ኖኅ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፰ ፡ የአብርሃም ፡ ታሪክ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፱ ፤ ዳዊት ፡ ምን ፡ አድርጓል ?
፲ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ምን ፡ አለ ?
፲፩ ፤ ኢዮብ ፡ በድሎዋል ፡ ወይ ?
፲፪ ፤ ስለ ፡ ኢዮብ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ምን ፡ ተነግሮዋል ?
፲፫ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
፲፬ ፤ ስለ ፡ ትዕግሥት ፡ የሰጠው ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ የትኛው ፡ ነው ?
፲፭ ፤ ኀጢአት ፡ እየሠሩ ፡ መከራን ፡ ቢታገሡ ፡ ያጸድቃል ፡ ወይ ።

ምዕራፍ ፡ ፴፪ ።

## ን ስ ሐ ።

፩ ፤ ንስሐ ፡ የግእዝ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ትርጓሜውም ፡ ጸጸት ፡ ማለት ፡ ነው ። ጸጸት
ነቱ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ በሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ተጸጽቶ ፡ ኀጢአቱ ፡ ይሰረይለት ፡ ዘንድ ፡ እግዚ
አብሔርን ፡ በኀዘን ፡ በልቅሶ ፡ ሲለምን ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የጕልማሳ ፡ ሚስት ፡ ሳልቀማ ፡
የሰው ፡ ገንዘብ ፡ ሳልሰርቅ ፡ ቀረሁ ፡ ልሰርቅም ፡ ብሄድ ፡ ውሻ ፡ ጮኾብኝ ፡ ባለቤት ፡
ነቅቶብኝ ፡ ባዶ ፡ እጄን ፡ መጣሁኝ ፡ ብሎ ፡ የሚያደርገው ፡ ጸጸት ፡ አይደለም ።

፪ ፤ ስለ ፡ ንስሐ ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የተሰጠን ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ነስሑ ፤
እስመ ፡ ቀርበት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ። መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ቀርባለችና ፡ ንስሐ ፡
ግቡ ፡ የሚለው ፡ ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ። በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማ
ያት ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ባገኘን ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፡ ነገሮችን ፡ እንመለከትበታለን ።

፫ ፤ አንደኛ ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጥር ፡ እግዚአብሔር ፡ ለወዳጆቹ ፡ ያዘጋጀውን ፡
ዐይን ፡ ያላየውን ፡ ጆሮ ፡ ያልሰማውን ፡ የሰው ፡ ልቡና ፡ ያላሰበውን ፡ ዘለዓለማዊውን ፡
ሕይወት ፡ ያመለክታል ። ኹለተኛ ፡ ለዘለዓለማዊው ፡ ሕይወት ፡ መገኛ ፡ የኾነውን ፡
አምላካችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ያመለክታል ። ስለዚህ ፡ ዘለዓለማዊውን ፡ ሕይ
ወት ፡ ለመውረስና ፡ የሕይወት ፡ ራስ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መቅደስ ፡ ለመኾን ፡ በን
ስሐ ፡ ከኀጢአት ፡ መንጻት ፡ ያስፈልጋል ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፲፩—፵፬ ። ፳፭ ፡ ፴፬ ፡
ሉቃ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ቍ ፡ ፳፩ ።

፬ ፤ ንስሐ ፡ ያደፈ ፡ ልብስን ፡ እንደ ፡ ማጠብ ፡ ከኀጢአት ፡ በኋላ ፡ የምትገኝ ፡
ናት ፡ እንጂ ፤ አስቀድሞ ፡ ድርን ፡ ጉርዶ ፡ እንደ ፡ ማግባት ፡ ከኀጢአት ፡ በፊት ፡ የምት
ገኝ ፡ አይደለችም ።

፭ ፤ ንስሐ ፡ አንደኛው ፡ በራስ ፡ ሕሊና ፡ ራስን ፡ ወቅሶ ፤ ፪ኛ ፡ በመምህራን ፡ ትምህ
ርት ፡ ደንግጦ ፡ ይፈጸማል ። በመምህራን ፡ ትምህርት ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ አክአብ ፡
በራስ ፡ ሕሊና ፡ ራስን ፡ መውቀስ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ነው ። ዳዊት ፡ የኦርዮንን ፡
ሚስት ፡ ቀምቶ ፤ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ኦርዮንን ፡ በግፍ ፡ በማስገደሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነ



ቢዩ ፡ በናታን ፡ ቃል ፡ ገሠጸው ፤ ኋላም ፡ እስራኤልን ፡ በማስቈጠሩ ፡ በመልእክተኛው
በጋድ ፡ ቃል ፡ ወቀሰው ። ዳዊትም ፡ በፊትም ፡ ኾነ ፡ በኋላ ፤ ከነቢያት ፡ በደረሰው ፡ ተ
ግጽና ፡ ምክር ፡ ደንግጦ ፡ በሠራው ፡ ኀጢአት ፤ ተጸጽቶ ፡ ንስሐ ፡ ገባ ። እግዚአብሔርም
ንስሐውን ፡ አይቶ ፡ ይቅር ፡ አለው ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፩—፲፫ ። ፳፬ ፡ ፩—፲፰

፮ ፡ እንዲሁም ፡ አክአብ ፡ በናቡቴ ፡ ላይ ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፤ በነቢዩ
በኤልያስ ፡ ቃል ፡ ገሠጸው ። አክአብም ፡ በሠራው ፡ ስለ ፡ ደነገጠበት ፡ እግዚአብሔር
ድንጋጤውን ፡ አይቶ ፡ በዘመኑ ፡ መከራ ፡ አላመጣበትም ፡ አለ ። ፩ ፡ ነገ ፡ ም ፡ ፳፩
ቍ ፡ ፲፯—፳፱ ።
ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተያዘባት ፡ ሌሊት ፡ ፈጣሪውን
አላውቅም ፡ ብሎ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ከካደ ፡ በኋላ ፤ ዶሮ ፡ ሲጮህ ፡ ዶሮ ፡ ሳይጮህ ፡ ፫ ፡ ጊዜ
ትክዳኛለህ ፡ ያለውን ፡ የአምላኩን ፡ ቃል ፡ ዐስቦ ፤ በሕሊናው ፡ ተወቅሶ ፡ መራራ
ልቅሶ ፡ አለቀሰ ። እግዚአብሔር፡ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ንስሐውን፡ አይቶ ፡ ኀጢአቱን
ይቅር ፡ ብሎ ፡ በጎቼን ፡ ጠብቅ ፡ ሲል ፡ የሐዋርያነትን ፡ ሹመት ፡ ሰጠው ፤ የመንግሥተ
ሰማያትን ፡ መክፈቻ ፡ እሰጥሀለው ፡ ሲል ፤ በቂሳርያ ፡ የሰጠውን ፡ ተስፋም፡ ፈጸመለት
ማቴ ፡ ም ፡ ፳፯ ፡ ቍ ፡ ፰፱—፸፭ ። ፲፯ ፡ ፲፱ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፲፭—፲፯ ።

፯ ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ በመምህራን ፡ ምክር ፡ ቢኾን ፡ ከራስ ፡ ሕሊና ፡ ለመወ
ስም ፡ ቢኾን ፡ በሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ተጸጽቶ ፡ ንስሐ ፡ ከገባ ፤ የእግዚአብሔር፡ይቅርታ
ፈጥኖ ፡ ይደረግለታል ። ንስሐ ፡ ፍጹም ፡ ትሕትናን፡ማሳየት ፡ ያስፈልጋታል ። ስለዚ
ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሾመለት ፡ ለካህኑ ፡ ኀጢአቱን ፡ ነግሮ ፡ ስርየት ፡ መቀበል
ይገባዋል ።

፰ ፤ ይህም ፡ በብሉይና ፡ በሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ የጸና፡ሕግ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ የበደለ ፡ ኹ
በካህን ፡ ቃል ፡ የኀጢአቱን ፡ ስርየት ፡ ያገኛል ። ኀጢአትን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንጂ
ለቄስ ፡ መንገር ፡ አይገባም ፡ ብለው ፡ የሚያስተምሩ፡አንድ ፡ አንድ፡ አይታጡም ። ነገ
ግን ፡ ይህ ፡ ትምህርት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ማነኛዩቱም ፡ ወገን ፡ ብ
ድል ፡ ካህን ፡ ኀጢአቷን ፡ ያስተሰርይላት ፤ ኀጢአቱን ፡ የተዋችሁለት ፡ ይሰረ
ታል ፤ ኀጢአቱን ፡ ባትተውለት ፡ ግን ፡ አይሰረይለትም ፡ ሲል ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡
ቢያት ፤ በሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ለሐዋርያት ፡ የሰጠውን ፡ አምላካዊ ፡ ትእዛዝ ፡ የሚቃወ
ስለ ፡ ኾነ ፤ ትምህርቱ ፡ ከክርስትና ፡ ምንጭ ፡ የተገኘ ፡ አይደለም ። ዘሌዋ ፡ ም ፡
ቍ ፡ ፰ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳፪—፳፫ ።

፱ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ኹል ፡ ጊዜም ፡ በብሉይ ፡ ኪዳንና ፡ በሐዲስ ፡ ኪዳ
ትምህርት ፡ የጐለመሰች ፡ እንደ፡መኾኗ ፡ መጠን ፤ ንስሐን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ዛዝ ፡ ትፈጽማለች ። የንስሐ ፡ ጥምቀት ፡ በዕንባ ፡ መታጠብ ፡ ነው ።

፲ ፤ ስለ ፡ ዚህ ፡ ስለ ፡ ፈውሰ ፡ ሕሙማን ፡ ከሚደረገው ፡ ማየ ፡ ምንዛኅ፡በቀ
ኹለተኛ ፡ ጥምቀት ፡ የለም ። የክርስቶስ ፡ መስቀሉ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤
ርስቲያንም ፡ ጥምቀት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ናት ። ኹለተኛ ፡ ጥምቀት ፡ የሚያደር

www.ethiopianorthodox.org

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በቅዱስ ፡ ጳውሎስ፡ አድሮ ፡ ምእመናን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተጠመቁና፡ መንፈስ፡ቅዱስን፡ከተቀበሉ፡በኋላ፡ ኹለተኛ ፡ ሊጠመቁ ፡ አይገባም ፡ ሲል ፡ ያዘዘውን፡ ኹለተኛ፡ጥምቀትን፡ማሰብ፤ ወልደ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመስቀል ፡ እንደ ፡ ማሰብ ፡ መኾኑን ፡ ያስተማረውን ፡ መተላለፍ፡ ነው ። ዕብ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፩—፯ ።

፲፩ ፤ የንስሓ ፡ ጥምቀት ፡ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ ዐልጋዬን ፡ በዕንባዬ፡ አጥባለሁ ። ምንጻፌንም ፡ በዕንባዬ ፡ አርሳለሁ ፡ እንዳለው ፡ በአንብዐ ፡ ንስሓ ፡ መታ ጠብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሌላ ፡ ጥምቀት ፡ የለም ፡ መዝ ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፮ ። በንስሓ ፡ ጊዜ ፡ ሰው፡ ኹሉ ፡ የማይገባ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መለየቱን ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማያት፡ መውጣቱን ፡ ኢያሰበ ፡ ማዘን ፡ ማልቀስ ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ፤ አግኝቼ ፡ ነበር ፡ አጣሁ ፤ ጠምጄ ፡ ነበር ፡ ፈታሁ ፡ ብሎ ፡ ማዘን ፡ ማልቀስ ፡ አይገባም ።

፲፪ ፤ ወደ ፡ እውነተኛው ፡ ንስሓ ፡ ለመመለስ ፡ እንድንችል ፡ ደንጋዩን ፡ ልብ ፡ ከኛ ፡ አውጥቶ ፤ መንፈሳዊውን ፡ ልብ ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንለምነው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ንስሓ ፡ ማለት ፡ ምንድነው ?

፪ ፤ ለንስሓ ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ ይገኛል ?

፫ ፤ ንስሓ ፡ በምን ፡ በምን ፡ ይፈጸማል ?

፬ ፤ የዳዊትና ፡ የአክአብ ፡ የጴጥሮስ ፡ ንስሓ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ነወይ ?

፭ ፤ ኀጢአትን ፡ ለቄስ ፡ መንገር ፡ ይገባል ፡ ወይ ?

፮ ፤ ስለዚህ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተሰጠ ፡ ትእዛዝ ፡ አለን ?

፯ ፤ የንስሓ ፡ ጥምቀት ፡ ምንድን ፡ ነው ?

፰ ፤ ፪ኛ ፡ ጥምቀት ፡ ይገባልን ?

## ምዕራፍ ፡ ፴፫ ።

## ተዘክሮተ ፡ እግዚአብሔር ።

፩ ፤ ተዘክሮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማሰብ ፡ ማለት ፡ ነው ። እግዚአብሔርም ፡ ማለት ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋችን ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ባሕርንና ፡ የብስን ፡ የሚታየውንና ፡ የማይታየውን ፡ ኹሉን ፡ የፈጠረ ፡ ኹሉን ፡ ቻይ ፡ አምላክ ፡ ማለት ፡ ነው ። በዕብራይስጢ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ የሆዋ ፡ ሻዳይ፡ ይባላል ፤ አምላክን፡ማሰብ፡ ለአምላኪዎች ፡ የበለጠውን ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ ሲኾን ፤ ለተመላኪው ፡ ከምስጋና ፡ በስተቀር ፡ የሚያተርፍለት ፡ ነገር ፡ የለም ።

፪ ፤ ማነኛውም ፡ ፍጡር ፡ በተለይም ፡ ሰው ፡ አምላኩን ፡ ፈጣሪውን ፡ በማነኛ ውም ፡ ጊዜ ፡ ማሰብ ፡ እንዲገባው ፤ ስትቆምም ፡ ስትቀመጥም ፡ ስትነሣም ፡ ስትተኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽን ፡ ማሰብን ፡ አትዘንጋ ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ በሕግ ፡ ተጽፏል ።



በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ፍጡር ፡ ኹሉ ፡ ማነኛውንም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ለማራ
ወይም ፡ እንዳይደርስበት ፡ ለማድረግ ፤ እንዲሁም ፡ በተደረገለት ፡ ለማመስገን ፡ ለጸ
ትም ፡ ኾነ ፡ ለምስጋናም ፡ አምላኩን ፡ ያስባል ። ዘዳ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፯ ፡ ፯ ።

፫ ፤ አምላክ ፡ ሲባል ፤ አረማውያን ፡ ትምህርት ፡ በሌለው ፡ የአምላክን፡ናፍቆ
ብቻ ፡ በያዘ ፡ ልቡና ፡ የሚያመልኩት ፤ የሚጠሩት ፡ ሳይገባው ፡ ጸሎትንና ፡ ምስጋና
የሚያቀርቡለት ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ምሳሌ ፡ እየተመሰለ ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነ
መልክ ፡ ከንጨት ፡ ከድንጋይ ፡ የተፈለፈለ ፡ ጣዖት ፡ አይደለም ።

፬ ፤ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ የተከናወነ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ዐይን ፡ ሳለው ፡
ያይ ፤ ጆሮ ፡ ሳለው ፡ የማይሰማ ፤ አፍንጫ ፡ ሳለው ፡ የማያሸት ፤ እጅ ፡ ሳለው ፡ የማ
ስስ ፡ እግር ፡ ሳለው ፡ የማይሄድ ፤ መላወስ ፡ መንቀሳቀስ ፡ የማይቻለው ፡ ወዳጁን ፡
ይጠቅም ፡ ጠላቱን ፡ የማይጐዳ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ነው ። እሱ ፡ አምላክ ፡ አይደለም ።
ውና ፡ ሥራውም ፡ ከንቱዎች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ አብረው ፡ ያልፋሉ ፡ ይጠፋሉ ። መዝ ፡ ፻፲
ቍ ፡ ፬—፰ ።

፭ ፤ ሕያው ፡ ባሕርይ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ፡ ግን ፡ ያልነበረውን ፡ ያልኖረወ
ማንኛውንም ፡ ፍጥረት ፡ ካለመኖር ፡ ወደ፡ መኖር ፡ አምጥቶ ፡ መፍጠርና ፡ ማሳለፍ ፡ የሚ
ለው፡ስለ ፡ ኾነ፤ኹሉን ፡ አሳልፎ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ። ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ እንደ፡ጥላ፡
ፋል ፤ እንደ፡ሣር ፡ አበባ ፡ ይረግፋል ። ሰማይና ፡ ምድር፡ እንደ ፡ መጋረጃ፡ ይለወጠ
እንደ ፡ ወረቀት ፡ ይጠቀለላሉ ። እሱ ፡ ግን፡ መቼም ፡ መች ፡ አያልፍም ፤ አይለወጥ
ትናትና ፡ ዛሬ ፡ ነገም ፡ እሱ ፡ ነው ። ይህን፡ ጊዜ ፡ ነበረ ፤ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ተገኘ ፤ እስ
ህን ፡ ጊዜ ፡ ይኖራል ፤ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ያልፋል ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ።

፮ ፤ ክርስቲያናዊ ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ ኀያልና ፡ ገናና ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ ያመልካ
ለሱ ፡ ብቻ ፡ ይሰግዳል ፤ በአምልኮ ፡ ጸሎትም ፡ የሱን ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ይጠራል ። መ
፻፪ ፡ ቍ ፡ ፳፭—፳፯ ።

፯ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከውነተኞች፡ ክርስቲያኖች ፡ አንዷት ፡ ናትና ፡ በሃይማኖት
ተቀዳሚነት ፡ ያላት ፡ ናት ። ስለዚህም ፡ ከቅዱሳን ፡ አበው ፡ በተቀበለችው፡ እምነ
መሠረት ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኳን ፡ በጊዜው ፡ ኹሉ ፡ ታስባለች ፤ ቅዱስ ፡ ስሙን
በጸሎት ፡ በአምልኮት ፡ ትጠራለች ፤ አመሰግንሀለሁ ፡ አመሰግንሻለሁ ፡ ማለትን ፡
ደገፈው ፡ የምስጋና፡ ብድር፡ መከፋፈል፡ ከራስ ፡ እስኪወለድና፡ ደኅና፡ ዋልክ ፤ ደ
ዋልክ ፡ ደኅና ፡ ዋል ፤ ደኅና ፡ ዋል ፤ ደኅና ፡ እደር ፡ ደኅና ፡ እደር ፡ የሚለው ፡ ግዕ
ትርጓሜና ፡ ስሜት ፡ የሌለው ፡ እንግዳ ፡ ባህል ፡ እስኪፈጠር ፡ ድረስ ፡ ኢትዮ
ሥራዋን ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ስትሠራ ፡ ኖራለች ። በአገር ፡ በ
ዛሬም ፡ አልተለወጠም ፤ አጠራሩም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

፰ ፤ ሀ) ይማኖትና ፡ ተስፋ ፡ ደም ፡ አርግቶ ፡ የሚፈጥረው ፡ አምላክ ፡ የሚሳ
ነገር ፡ የለምና ፡ ለኔ ፤ የፈጠረኝ ፡ አምላክ ፡ እሱ ፡ ያውቅልኛል ።

www.ethiopianorthodox.org

ለ) ምስጋና ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አደርክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደኅና ፡ ነኝ ። የሕይወት ፡ ኑሮ ፡ አለኽን ፡ ለፈጣሪዬ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይድረሰው ፡ አዎን ።

ሐ) ጸሎት ። ደኅና ፡ ያዋልክ ፡ አምላክ ፡ ደኅና ፡ አሳድረኝ ፤ ደኅና ፡ ያሳደርክ ፡ አምላክ ፡ ደኅና ፡ አውለኝ ፤ አንተ ፡ የቸርነትኽን ፡ ሥራ ፡ ሥራልኝ ።

መ) በረከት ። በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፤

፱ ፡ ሥላሴ ፡ ባርኩት ። እግዚአብሔር ፡ ይባርክልን ።

ሠ) ሐውጾ ፡ ድውይ ። ድውይን ፡ መጐብኘት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይማርኽ ፤ እንኳን ፡ እግዚአብሔር ፡ ማረኽ ፤ እንኳን ፡ ለፀሓዩ ፡ አበቃኽ ።

ረ) እስረኛ ፡ መጠየቅ ። እግዚአብሔር ፡ ያስፈታኽ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይርዳኽ ፤ እንኳን ፡ እግዚአብሔር ፡ አስፈታኽ ።

ሰ) አዘንተኛን ፡ ማጽናናት ። እግዚአብሔር ፡ ያጥናኽ ፤ እግዚአብሔር ፡ ያስ ችልኽ ።

፲ ፤ ቀ) የተጐዳን ፡ መጠየቅ ። እግዚአብሔር ፡ ርጥባን ፡ ያውርድልኽ ፤ የጠፋ ውን ፡ ይተካልኽ ። ይህ ፡ የገንዘብ ፡ ጥፋት ፡ ሲኾን ፡ ነው ።

በ) ፍርድን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መስጠት ። እግዚአብሔር ፡ ይይልኽ ፤ እግዚ አብሔር ፡ ይፍረድ ፡ ወይም ፡ ያፈራርደን ።

ተ) ምስክር ። አንድም ፡ ጥፋት ፡ እንደሌለብኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስክር ፡ ነው ። ዘወትር ፡ እንደ ፡ ማሰብኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስክር ፡ ነው ።

ኀ) መጨ ፡ ተስፋ ። የምድሩን ፡ እንጂ ፡ የሰማዩን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ። የዛሬውን ፡ እንጂ ፡ የሚመጣውንስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቅልኛል ።

፲፩ ፤ ነ) ምኞት ። ይማርኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያኑርኽ ። . . . ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ነው ።

አ) የታወቀን ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለመደበቅ ፡ ሲሞክር ፤ ሌላው ፡ ያወቀ በት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ማወቁን ፡ ለመግለጥ ፡ የሚነገር ፡ ቃል ። . . . . በእግዜር ፡ አገ ውኛ ፡ ይባላል ።

ከ) የደብዳቤ ፡ አጻጻፍ ። . . ለክቡር ፡ አቶ ፡ እገሌ ፡ መድኀኔ ፡ ዓለም ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሰንብተሀል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደኅና ፡ ነኝ ።

፲፪ ፤ ወ) የፍርድ ፡ አቤቱታ ። እግዚአብሔር ፡ ያሳይዎ ፤ ክርስቶስ ፡ ያመልክ ትዎ ። . . . መላኩ ፡ ይንገርዎ ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ ፤ በደሌን ፡ አይተው ፡ እውነተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ይስጡኝ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ እውነተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ይስጡኝ ።

ዐ) ፍርድ ። . . . ፍትሕ ፡ ይጠብቅ ፤ ወንጀለኛን ፡ ያውድቅ ፤ ባደላ ፡ ያድላ በት ፤ በአመጠኛ ፡ ሰይፍ ፡ ሞት ፡ ይዘዝበት ። . . . ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ነው ።



ዘ) ምስክርነት ። ስማ ፡ ምስክር ፡ ነው ። ነፍሴን ፡ በውነት ፡ መስክሬ ፡ እንዳወ ጣት ፡ ያድርገኝ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ነው ።

፲፫ ፤ (የ) ማኅበራዊ ፡ የሙግት ፡ ሥራት ። ዳኛ ፡ እግዜር ፡ አቶ ፡ እገሌ ፡ ስለ ፡ በደ ለኝ ፡ በኋት ፡ ደንብ ፡ ዳኝኝ ። . . . . አቶ ፡ እገሌ ፡ በኋት ፡ አምላክ ፡ ተዳኝ ። አስተ ውል ፡ ዳኛ ፡ እግዜር ፡ ማለት ፡ ዳኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ።

፲፬ ፤ ኋት ፡ ማለትም ፡ አኀው ፡ አኀት ፡ የሚሉትን ፡ የግእዝ ፡ ቃላት ፡ በውስጡ ፡ ጠቅሎ ፡ ወንድማማቾች ፡ እትማማቾች ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ በኋት ፡ ደንብ ፡ በኋት ፡ አምላክ ፡ ማለት ፡ በወንድማማቾች ፡ በእትማማቾች ፡ ደንብ ፤ በወንድማማቾች ፡ በእትማ ማቾች ፡ አምላክ ፡ ተዳኝ ፡ ብሎ ፡ ዳኛ ፡ እግዜር ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ሲተረጕም ፤ ማኅበረ ፡ ሐዋ ርያትን ፡ የሚያስታውስ ፤ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገኘ ፡ ክርስቶስን ፡ የሚያስተምር ፡ ነው ፡

፲፭ ፤ (ደ) መማፀን ። ወንድም ፡ ከወንድሙ ፡ ቢጣላ ፡ ዳኛ ፡ ወዳለበት ፡ እስኪያ ርስ ፤ ተበዳዩ ፡ በዳዩን ፡ የመሪውንና ፡ የፈጣሪውን ፡ ስም ፡ እየጠራ ፡ ያማፅነዋል ፡ ማለት ፤ በንጉሥ ፡ አምላክ ፡ በኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አምላክ ፤ አቶ ፡ እገሌ ፡ ከስሼሀለሁ ፡ አት ሂድ ፡ ይለዋል ። . . . አስተውል ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ መሪው ፡ ከፍጡራን ፡ መካከል የተመረጠ ፡ ቢኾንም ፤ መርጦ ፡ ባነገሠው ፡ መሪ ፡ አድሮ ፡ ሕዝቡን ፡ የሚያስተዳድር እግዚአብሔር ፡ መኾኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነው ።

፲፮ ፤ (ገ) መሐላ ። ሰው ፡ ኹሉ ፡ ማነኛውንም ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ መኾኑን ፡ ሌላው እንዲረዳለት ፤ ወይም ፡ ሰው ፡ ማነኛውንም ፡ ዐሳብ ፡ ለመፈጸም ፡ ከልቡ ፡ ቈርጦ ፡ መ ጣቱን ፡ ለመግለጥ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ጠርቶ ፡ ቃሉን ፡ በመሐላ ፡ ሲሰጥ ሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ዘወትር ፡ በጸሎቴ ፡ እንደማስባችሁ ፡ ልጁ ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ባስተማረኝ ፡ ትምህርት ፡ መሠረት ፡ የማመልከው ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስክሬ ነው ፡ ይላል ።

፲፯ ፤ (ጠ) ይቅርታ ። ወንድሙ ፡ ከወንድሙ ፡ ተጣልቶ ፡ አንደኛው ፡ በደሉን ዐውቆ ፡ ይቅርታ ፡ ሲጠይቅ ፤ ወንድሜ ፡ ማረኝ ፡ ቢለው ፡ ተጠያቂው ፡ ይቅር ፡ ስለ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ በማለት ፡ ዕርቁን ፡ ይፈጽማል ። ይህም ፡ የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶ ስን ፡ ትምህርት ፡ የሚያሳስበን ፡ ነው ። ማቴ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ፲፬ ።

(ጸ) ትምክሕት ። . . . ማንም ፡ ሰው ፡ ሙሉ ፡ ሕሊናውን ፡ በፈጣሪው ፡ ላይ አድርጎ ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ልበ ፡ ሙሉነቱን ፡ ሲገልጥ ፡ እኔ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ምንም ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ አልፈራም ፡ ይላል ። ዳዊትም ፡ በሞት ፡ ጥላ ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ብሄድ ፡ አንተ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ነህና ፡ ክፉውን ፡ አልፈራም ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ይህንኑ ፡ የ መረከዘ ፡ ነው ። መዝ ፡ ፳፫ ፡ ቍ ፡ ፬ ።

፲፰ ፤ (ጰ) ምክር ። አባት ፡ ልጁን ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ሲመራ ፡ ልጄ ሆይ ፡ ሰው ፡ ጠላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠላ ፡ ሰው ፡ ወደደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደደ ፡ ነውና እግዚአብሔር ፡ እንዲወድህ ፡ ለወንድምኽ ፡ መልካም ፡ አድርግ ፡ ይለዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

አስተውል ፤ ጠላ ፡ ወደደ ፡ በሚሉት ፡ አንቀጾች ፡ ውስጥ ፡ ማለት ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ውስጠ ፡ ታዋቂ ፡ ኾኗል ።

፲፱ ፤ (ፀ) መራገምና ፡ በደልን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መስጠት ። ማንም ፡ ሰው ፡ ሲገፉና ፡ ሲበደል ፡ በራሱ ፡ የመጣውን ፡ በደል ፡ ፍርዱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰጥቶ ፤ ለብዙ ፡ የሚተርፍ ፡ ሲኾን ፡ በመርገም ፡ ይወስነዋል ። ይህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይይልህ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይፍረድብህ ፤ እግዚአብሔር ፡ ያጥፋህ ፡ እንደማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ አደራረግ ፡ አንጥረኛው ፡ እለ ፡ እስክንድሮስ ፡ ብዙ ፡ ግቀየኝ ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ብድሩን ፡ ይስጠው ፤ የሰላም ፡ አምላክ ፤ ሰይጣንን ፡ ከእግራችሁ ፡ በታች ፡ ይጣለው ፡ ይቀጥቅጠው ። እግዚአብሔር ፡ ይይልህ ፡ ካለው ፡ ከሐዋርያው ፡ ጳውሎስና ፡ ከሊቀ ፡ መላእክት ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ አነጋገር ፡ ጋራ ፡ ይተባበራል ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ቍ ፡ ፲፱ ። ፪ ፡ ጢሞ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ። ይሁዳ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፱ ።

፳ ፤ (ፈ) በረከት ። ሰው ፡ ኹሉ ፡ ያባትነትን ፡ ደረጃ ፡ ሲያገኝ ፡ ልጆቹን ፡ ይባርካል ። የሚባርካቸውም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ነው ። አባቶች ፡ በመንፈሳዊም ፡ ኾነ ፡ በሥጋዊ ፡ ዓላማ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ለልጆቻቸው ፡ የሚሰጡት ፡ በረከት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነው ። ይህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥኽ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይባርክኽ ።

፳፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ያክብርኽ ፡ በመሰለውም ፡ ኹኔታ ፡ ይፈጸማል ። አፈጻጸሙም ፤ ይህችን ፡ አገር ፡ ላንተ ፡ ካንተም ፡ በኋላ ፡ ለዘርኽ ፡ እሰጣታለሁ ፡ ያለኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ይባርክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ዘርኽን ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ኮከብ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ ያብዛው ። በረከትኽ ፡ ከሰማይ ፡ ጠል ፡ ከምድር ፡ ስፋት ፡ የበዛ ፡ ይሁን ። በሎዛ ፡ የታየኝ ፡ አምላኬ ፡ እነዚህን ፡ ልጆች ፡ ይባርካቸው ። እግዚአብሔር ፡ ለሄኔሴፎሩ ፡ ወገን ፡ ቤት ። . . . . ይቅርታን ፡ ይስጥ ። ኹሉ ፡ የሚገኝባት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰላም ፡ ከሁላችሁ ፡ ጋራ ፡ ትኹን ፡ ባለው ፤ በአብርሃም ፡ በይስሐቅ ፡ በያዕቆብ ፡ በጳውሎስ ፡ ንግግር ፡ አንጻር ፡ ይፈጸማል ። ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፤ ሕዝቡን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ባርኳቸው ፡ ብሎ ፡ ስላዘዛቸው ፡ አባቶቻችን ፡ ልጆቻቸውን ፡ ሲባርኩ ፡ ኖረዋል ፡ ሲባርኩም ፡ ይኖራሉ ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፳፯ ፡ ቍ ፡ ፳፯—፴ ። ፵፰ ፡ ፲፭—፲፯ ።

፳፪ ፤ (ፐ) ጸሎትና ፡ ፍትሐት ። ጸሎትና ፡ ፍትሐት ፡ አበው ፡ ለውሉድ ፡ መምህራን ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቶቻቸው ፡ ወንድም ፡ ለወንድሙ ፡ በጠቅላላውም ፡ ካህናት ፡ ለሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚያደርጉት ፡ ነው ። ይህም ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡ ሕዝብኽን ፡ አድን ፤ ርስትኽንም ፡ አክብር ፡ ጠብቃቸው ፤ እስከ ፡ ዘለዓለሙም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጋቸው ፤ እግዚአብሔር ፡ ይፍታ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። መዝ ፡ ፳፰ ፡ ቍ ፡ ፱ ።

፳፫ ፤ መሠረቱም ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ በስምኽ ፡ ጠብቃቸው ፤ በውነትህም ፡ ቀድሳቸው ፤ ኀጢአቱን ፡ ይቅር ፡ ያላችሁት ፡ ይሰረይለታል ፤ በምድር ፡ የፈታችሁት ፡ በሰማይ ፡



የተፈታ ፡ ይሆናል ፡ ያለው ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቃል ፡ ነው ። ማቴ ፡
፲፰ ፡ ቍ ፡ ፲፰ ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ቍ ፡ ፲፩ ። ፳ ፡ ፳፫ ።

፳፬ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከሀ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ በተሰጠው ፡ አስተያየት ፡ መሠረት ፡ ኢ
ዮጵያ ፡ ተዘክሮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስትፈጽም ፡ ኖራለች ። ይሄውም ፡ ሕዝቡ ፡ ከ
ቶቹ ፡ ወርሶ ፡ በሙሉ ፡ ልማድ ፡ አድርጎ ፡ የሚፈጽመውን ፡ ባጭሩ ፡ አሳየሁ ፡ እን
በመምህራኑ ፡ አማካይነት ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የሚፈጽመው ፡ የቁም ፡ ነገር ፡ ሥ
ብዙ ፡ ነው ። ለተዘክሮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሠረቱ ፤ ዘዳግም ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፯ ፤ የ
ፈው ፡ ይህንንም ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ የማዝዝህን ፡ ነገር ፡ በልብኽ ፡ ያዝ ፤ ለልጆችኽም ፡ አ
ውታቸው ፤ በቤትኽም ፡ በተቀመጥክ ፡ ጊዜ ፡ በመንገድም ፡ በሄድክ ፡ ጊዜ ፡ በተኛኽ
ጊዜ ፡ በተነሣኽም ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽን ፡ ማሰብን ፡ አትዘንጋ ፡ ያለ
የሕግ ፡ ቃል ፡ ነው ።

፳፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ በዚሁ ፡ ቃል ፡ ለመጠቀም፡ ይርዳን ። አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ተዘክሮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ምንድነው ?
፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ምንድነው ?
፫ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ለማሰብ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ አለን ?
፬ ፤ ትእዛዙስ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፭ ፤ አረማውያን ፤ ከንጨትና ፡ ከድንጋይ ፡ የሚያዘጋጁት ፡ እውነተኛ ፡ አምላ
ይባላልን ?
፮ ፤ እውነተኛው ፡ አምላክ ፡ የትኛው ፡ ነው ?
፯ ፤ የሚታወቀውስ ፡ በምንድነው ?
፰ ፤ ፍጥረት ፡ ያልፋል ፡ አምላክ ፡ እሳ ?
፱ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ተዘክሮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዴት ፡ ትፈጽማለች ?
፲ ፤ ከሀ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ የተዘረዘረውን ፡ አጥንተሀልን ?
፲፩ ፤ አስተማሪው ፡ በሐሳቡ ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮችን ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፬ ።

፩ ፤ ምስጋና ፤ ፍጡር ፡ ኹሉ ፡ ለፈጣሪው ፡ ተገቢ ፡ የኾነ ፡ ምስጋናን ፡
ዜው፡ያቀርባል ። ልዑል ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከፍጡራኑ ፡ የሚሻ ፡ ምስጋና ፡ ብቻ ፡ ነ
ስለዚህም ፡ በተደረገላቸው ፡ ኹሉ ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ በውነት ፡ አመስጋኞች ፡ ኾነ
የተገኙ ፡ ኹሉ ፡ ብፁዓን ፡ ይባላሉ ። መዝ ፡ ፪፻፱ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ ፡ ከነዚህም ፡ ብፁዓን ፡ መካከል ፡ አንዲቱ ፡ እናት ፡ አገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ናት ። ኢትዮጵያ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ የፍጡራን ፡ ክብር ፡ በማይቀላቀልበት ፡ ልዩ ፡ አምልኮት ፡ ታመልከዋለች ፤ ቅዱስ ፡ ስሙንም ፡ ታመሰግነዋለች ። በኢትዮጵያ ፡ የምስጋና ፡ ፍጻሜውና ፡ መድረሻው ፡ ወዳንድ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ኾኖ ፤ የጊዜ ፡ የዘመን ፡ ደንብ ፡ ያለው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የምስጋና ፡ ስልት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አለ ። ይህም ፡ ቀጥሎ ፡ የተገለጠው ፤ ነው ።

፫ ፤ (ሀ) የጊዜ ፡ ደንብ ፤ የሌሊት ፡ ምስጋና ።

የሌሊት ፡ ምስጋና ፡ ሌሊት ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ እጃችሁን ፡ አንሥታችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ፡ ተብሏልና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ የሚወድ ፡ በቀንም ፡ ኾነ ፡ በሌሊት ፡ ሕጉን ፡ የሚፈጽም ፤ ከውሃ ፡ ዳር ፡ በቅላ ፡ ቅጠሏ ፡ እንደማይጠወልግ ፤ በየጊዜውም ፡ ፍሬዋን ፡ እንደምትሰጥ ፡ ዛፍ ፡ በመኾኑ ፤ ስለ ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድኽ ፡ አንተን ፡ አመሰግን ፡ ዘንድ ፡ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ እነሣለሁ ፡ እያለ ፡ ማንኛውም ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ሰው ፡ ሌሊት ፡ ሰውነቱን ፡ አንቅቼ ፡ ከልቤ ፡ ጋራ ፡ ተጫዋውቼ ፡ ሌሊት ፡ ያንተ ፡ ናት ። ቀኑም ፡ ያንተ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሌሊትና ፡ መዓልት ፡ ያመሰግኑሀል ፡ ብዬ ፤ አቤቱ ፡ በሌሊት ፡ ስምኽን ፡ ዐሰብኩ ፤ ሕግኽንም ፡ ጠበቅሁ ፡ በማለት ፡ የሚፈጽመው ፡ ከእንስሳት ፡ የሚለይበት ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ብሎ ፡ በማመስገን ፡ እንቅልፍ ፡ የሌላቸው ፡ ትጉሃን ፡ መላእክትን ፡ የሚወዳደርበት ፡ ነው ። መዝ ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፪ — ፬ ። ፻፶፯ ፡ ቍ ፡ ፯ ። ፻፲፱ ፡ ቍ ፡ ፶፭ና ፡ ፳፪ ። ፻፴፬ ፡ ቍ ፡ ፪ ።

፬ ፤ ስሙም ፡ መዝሙር ፡ ዘሌሊት ፡ ሰዓታት ፡ ዘሌሊት ፡ ትጋሀ ፡ ሌሊት ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። አፈጻጸሙም ፡ ሰዓታት ፡ ዘሌሊት ፤ እግርን ፡ አስተካክሎ ፡ ወገብን ፡ አቅንቶ ፡ ቆሞ ፡ በዜማ ፡ ይዘመራል ።

፭ ፤ መዝሙር ፡ ዘሌሊት ፡ እንደ ፡ መጀመሪያው ፡ ሥርዐት ፡ ኾኖ ፡ ጾም ፡ ቢኾን ፡ በመቋሚያ ፡ ዝማሜ ፡ ብቻ ፤ በሌላው ፡ ጊዜ ፡ ጽናጽልና ፡ ከበሮ ፡ ተጨምሮበት ፤ ንኡስና ፡ ዐቢይ ፡ መረግድ ፤ ንኡስና ፡ ዐቢይ ፡ ጽፍዓት ፡ በሚባለው ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ እየተጨመረበት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የዜማ ፡ ስልት ፡ ጣዕም ፡ እየተለዋወጠለት ፡ ይዘመራል ። መዝ ፡ ፻፵፱ ፡ ቍ ፡ ፩ — ፱ ። ፻፶ ፡ ቍ ፡ ፬ና ፡ ፭ ።

፮ ፤ ትጋሀ ፡ ሌሊት ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሰውዬው ፡ ችሎታ ፡ ከቁመትና ፡ ከስግደት ፡ ጋራ ፡ በሉኖሳስ ፡ ይፈጸማል ። ሉኖሳስ ፡ ማለት ፡ የጩኸት ፡ ዜማ ፡ ድምፅ ፡ የሌለበት ፡ በልብና ፡ በከንፈር ፡ ኅብረት ፡ የሚፈጸም ፡ እንቅስቃሴ ፡ ነው ። ይህም ፡ ኹኔታ ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በከንፈራቸው ፡ ያቀርቡኛል ፡ በልባቸው ፡ ግን ፡ ከኔ ፡ በጣም ፡ የራቁ ፡ ናቸው ፡ ካለው ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ ኹኖ ፤ አንተን ፡ ሳመሰግን ፡ ከንፈሮቼን ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ ከንፈሮቼ ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ስምኽን ፡ ያመሰግናሉ ፡ ያለውን ፡ የሚከተል ፡ መኾን ፡ አለበት ። መዝ ፡ ፳፫ ፡ ቍ ፡ ፭ ። ፷፩ ፡ ቍ ፡ ፳፫ ። ኢሳ ፡ ም ፡ ፳፱ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ።

፯ ፤ (ለ) ስብሐተ ፡ ነግሕ ፡ የጧት ፡ ምስጋና ፤ ውሎ ፡ ማኅሌት ፡ የቀን ፡ ሙሉ ፡ ምስጋና ፡ ነው ። ይህ ፡ ምስጋና ፡ እላይ ፡ ስለ ፡ መዝሙር ፡ ዘሌሊት ፡ በተናገርነው ፡ አኳኋን ፡ ይፈጸማል ። ኹለተኛም ፡ ሰዓታት ፡ ዘመዓልት ፡ የሚባል ፡ አለ ፤ ይህም ፡ በሰዓታት ፡



ዘሌሊት ፡ ዐይነት ፡ ይፈጸማል ። ለነዚህ ፡ ምስጋናዎች ፡ መሠረታቸው ፡ ጧት ፡ ለም
ጋና ፡ ባንተ ፡ ፊት ፡ ቆሜ ፡ ስዘምር ፡ እታያለሁ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፡ ሰውነቴ ፡ አንተን ፡
ምታለችና ፡ ማለት ፡ አንተን ፡ ናፍቃለችና ፡ ማልጄ ፡ ወዳንተ ፡ እገሠግሣለሁ ፡ ያለው
ቅዱስ ፡ ቃል ፡ ነው ። መዝ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፪ና ፡ ፫ ። ፳፫ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፰ ፤ (ሐ) ቅዳሴ ። ይህ ፡ ምስጋና ፡ ቄሱ ፡ ኅብስቱን ፡ በጻሕል ፡ ወይኑን ፡ በጽዋ
አድርጎ ፡ ፩ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ ወልድ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ ውእቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብሎ
በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ኅብስቱ ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ ወይኑ ፡
ርስቶስ ፡ ደም ፡ እንዲኾን ፡ ኅብስቱን ፡ ወይኑን ፡ የሚባርክበት ፡ የሚያከብርበት ፡
ዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፤ ይህ ፡ ኅብስት ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፡ እንኩ ፡ ብሉ ፤ ይ
ጽዋዕ ፡ ደሜ ፡ ነው ፡ እንኩ ፡ ጠጡ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፤ ኅብስቱን ፡ ወይኑን ፡ ሥጋው
ደሙን ፡ የሚያደርግበት ፤ ሥጋዬን ፡ የበላ ፡ ደሜን ፡ የጠጣ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ይኖራል ፡ እኔ
ከሱ ፡ ጋራ ፡ እኖራለሁ ፡ ስላለ ፤ ምእመናን ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ በመቀበላቸው ፡
መናንን ፡ የሚዋሐድበት ፡ ነው ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፶፬—፶፯ ። ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፳፮—

፱ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቀሳውስት ፡ ዲያቆናት ፡ ከብሉያት ፡ ከሐዲሳት ፡ እንደ ፡ ጊዜ
ኹኔታ ፡ አስፈላጊውን ፡ ጥቅስ ፡ እየመረጡ ፡ ኅብስቱ ፡ ወይኑ ፡ በጥንት ፡ መልኩ ፡
ደምናየው ፡ ኅብስት ፡ ወይን ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፤ በርግጥ ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ የክርስቶ
ደም ፡ መኾኑን ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ፡ ለምእመናን ፡ ያስተምሩበታል ።

፲ ፤ (መ) ዝማሬና ፡ ዕጣን ፡ ሞገር ። ይህ ፡ ምስጋና ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክ
ቶስ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ በሰጣቸው ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ በምታደ
በት ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ ማለት ፡ ሥጋዬን ፡ በምትበሉበት ፤ ደሜን ፡ በምትጠጡበት ፡ ጊ
ኹሉ ፡ ሞቴን ፡ ትንሣኤዬን ፡ ዐስቡ ፡ ብሎ ፡ እንዳዘዛቸው ፤ ቀሳውስት ፡ በቤተ ፡
ደስ ፡ መዘምራን ፡ በቅኔ ፡ ማኅሌት ፡ ነገረ ፡ መስቀሉን ፡ እየገለጡ ፡ የሚያቀርቡት ፡
ጋና ፡ ነው ። በሐ ፡ በመ ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ለተገለጠው ፡ ምስጋና ፡ ሥርዐት ፡ መሠረ
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዐሙስ ፡ ማታ ፡ በደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ መሓከል ፡ የ
መው ፡ ጥልቅ ፡ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፡ ነው ። በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚፈጸሙ ፡ የምስጋ
ስልቶች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለመረጃ ፡ ያኽል ፡ የሰጠነው ፡ ይበቃል ።

፲፩ ፤ እንዲሁም ፡ ከሕዝቡ ፡ አፍ ፡ በየወራቱ ፡ በየዓመቱ ፡ በየጊዜው ፡ በየሰዓ
ለጊዜው ፡ ተመሳሳይ ፡ የኾነ ፡ ምስጋና ፡ ለልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቀርባል ። ይኸው
ባጭሩ ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ወፌ ፡ በሶራው ፡ ላይ ፡ ወፌ ፡ በግምጃው ፡ ላይ ፤ ሻሽ ፡ አ
ረፈ ፤ የማይ ፡ ውሃ ፡ ነሺ ፡ የበረሓ ፡ እያሉ ፡ የሚዘፍኑትንና ፡ እሱንም ፡ የመሰለ
ኹሉ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ዘፈን ፡ የሰማኹት ፡ በጐጃም ፡ ነው ። በሌላውም ፡ አገር ፡
ዳለ ፡ እንጃ ። ምስጢሩም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ። ወፌ ፡ በሶራው ፡ ላይ ፡ ወፌ ፡ በግምጃ
ላይ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፤ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ መካሕ ፡ ዘይወጽእ ፡ እምኤዶም ፡ ቀይ
አልባሰ ፡ እምባሶር ፡ ኀያል ፡ ወግሩም ፡ በልብሰቱ ። ቀይ ፡ ግምጃ ፡ ለብሶ ፡ ከኤዶም
የወጣ ፤ በአለባበሱም ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡ ያ ፡ ጀግና ፡ ማነው ? ሲል ፤ ኢሳያይስ ፡ በ

www.ethiopianorthodox.org

ቢት፡ ባመለከተው፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ ወርዶ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ ያመለክታል ። ኢሳ ፡ ፷፫ ፡ ፩ ። ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ።

፲፪ ፤ ወፌ ፡ ማለት ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ የወረደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሲያሳይ ፡ በሶራው ፡ ላይ ፡ በግምጃው ፡ ላይ ፡ ማለት ፡ ደግሞ ፡ ቀይሐ ፡ አልባስ ፡ እምባሶር ፡ ብሎ ፡ ነቢዩ ፡ እንዳመለከተው ፤ ባሶር ፡ ማለት ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ሥጋ ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ምንም ፡ በዐማርኛ ፡ ባሶር ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ሶራ፡ ወደ፡ማለት ፡ ቢለወጥ ፤ ሶራ ፡ ማለት ፡ ቅላትን ፡ ከዚያውም ፡ ሥጋን ፡ ደምን ፡ የሚያመለክት ፡ ነውና ፡ ሰው ፡ ኾኖ፡በሥጋ፡ተገልጦ፡ የታየ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠቅሶ ፡ እንደ፡ማሳየት ፡ ያኽል ፡ የሚያመለክት ፡ ነው ።

፲፫ ፤ ሻሽ ፡ አረፈረፈ ፡ የሚለው ፡ ቃልም ፤ ከመ ፡ ዕፍረት ፡ ዘይውኅዝ ፡ እምርእሱ ፡ እስከ ፡ ጽሕሙ ፡ እንዲል ፤ ከቀርነ ፡ ቅብዑ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የሚደፋው ፡ የክህነት ፡ ቅብዐት ፡ ከራሱ፡ እስከ፡ ጽሕሙ ፡ ደርሶ ፤ ከሻሹና፡ ከኀባኔ ፡ መልበሱ ፡ ተርፎ ፡ ይታይ፡ ከነበረው ፡ ከአሮን ፡ ክህነት ፡ ይልቅ ፡ የፍጡራንን ፡ ቅብዐት ፡ የማይሻው ፡ የወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክህነት ፡ ብልጫ፡ ያለው፡ መኾኑን፡ ያሳያል ። መዝ፡ ፻፴፫ ፡ ቍ. ፪—፬።

፲፬ ፡ የማይ ፡ ውሃ ፡ ነሺ ፡ የበረሓ ፡ የተባለው ፡ ቃልም ፡ ማይ ፡ ማለት ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ በጠቅላላው ፡ ውሃ ፡ ማለት ፡ ሲኾን ፤ በጐጃም ፡ ልማድ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ( ማይ) ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመሥዋዕት ፡ የተቀደሰውንና ፡ የተቀዳውን ፡ ማይ ፡ ውሃ ፡ ስለ ሚያመለክት ፡ ጥምቀት ፡ በዮርዳኖስ ፡ ውሃ ፡ በተፈጸመው ፡ በወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥምቀት ፡ መቀደሷን ፡ የሚያመለክት ፡ ነው ። ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፫—፲፯ ።

፲፭ ፡ ባጭር ፡ ለማስረጃ ፡ ያኽል ፡ ጥቂቱን ፡ ጠቀስን ፡ እንጂ ፤ በኢትዮጵያ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ድምጥ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስልት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ የሚነገርበት ፤ ረቂቅ ፡ ምስጢር ፡ የሚገለጥበት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስጋናው ፡ ብዙ ፡ ነው ።

ስሙን ፡ አመስግነን ፡ ለቅዱሳኑ ፡ የሚሰጠውን ፡ ብዕዓን ፡ እንድናገኝ ፡ የአምላካችን ፡ ፈቃዱ ፡ ይሁንልን ። አሜን ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ኢትዮጵያ፡ በእግዚአብሔር፡ ምስጋና፡ የፍጡራንን፡ ክብር ፡ ትቀላቅላለችን ?

፪ ፡ የሌሊት ፡ ምስጋና ፡ ምን ፡ ምን ፡ ተብሎ ፡ ይከፈላል ? አፈጻጸሙስ ፡ እንዴት ፡ ነው ?

፫ ፤ የጧት ፡ ምስጋና ፡ ምን ፡ ይባላል ?
የቀን ፡ ምስጋናስ ?

፬ ፤ ቅዳሴና ፡ ዝማሬ ፡ የሚባለውስ ፡ እንዴት ፡ ነው ?

፭ ፤ ከሕዝቡ ፡ የሚሰማው ፡ ምስጋና ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ?

፮ ፡ ወፌ ፡ በሶራው ፡ ላይ ፡ የሚለው ፡ ምን ፡ ያመለክታል ?

፯ ፤ ሻሽ ፡ አረፈረፈ ፡ የሚለውስ ፡ ምን ፡ ያሳያል ?

፰ ፤ የማይ ፡ ውሃ ፡ ነሺ ፡ የሚለውሳ ፡ ምን ፡ ያስረዳል ?

፱ ፡ ስለ፡ ማይ ፡ ውሃ ፡ በጐጃም ፡ ምን ፡ ልማድ ፡ አለ ?



## ምዕራፍ ፡ ፴፭ ።

## በ ዓ ላ ት ።

፩ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ተገቢ ፡ በዓል ፡ ታከብራለች ። የበዓል ትርጓሜው ፤ ዕረፍት ፡ ክብር ፡ ደስታ ፡ ማለት ፡ ነው። ዕረፍት ፡ መባሉ ፡ ሰው ፡ ከሥጋዊ ድካም ፡ ስለሚያርፍበት ፡ ነው ። ክብር፡ መባሉ፡ ለሰው፡ ከሥጋዊ ፡ ሥራ ፡ በዓሉን ፡ ምክ ንያት ፡ አድርጎ ፡ ዐርፎ ፡ ከመዋሉ ፡ ይልቅ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ በበዓሉ ቀን፡ ዐርፎ፡ በመዋሉ፡ ክብር ፡ የሚያገኝበት፡ ስለ ፡ ኾነ፡ ነው ። ደስታ ፡ መባሉም ፡ በ ሉን ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ ዐርፎ ፡ ለጊዜው ፡ ሥጋዊ ፡ ተድላ ፡ ደስታን ፡ የሚፈጽ በት ፡ በኋላም ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ የሚወርስበት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ። ይኸውም በሳምንት ፡ በወር ፡ በዓመት ፡ የሚገኝ ፡ ቀን ፡ ነው ።

፪ ፤ ለበዓል ፡ አከባበር ፡ ሥሩ ፡ መሠረቱ ፡ በደስታ ፡ በዓል ፡ አድርጉ ፡ የሚለው የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ነው ። መዝ፡ ፻፲፰፡ ቍ. ፳፬ ። በዓለም፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ ከ ንጨት ፡ ተፈልፍለው ፡ ከደንጊያ ፡ ተቀርጸው ፡ የተሰናዱ ፡ የማይጠቅሙ ፡ የማይጎዱ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጣዖታት ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፤ ብዙ ፡ ደካሞች ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ እንጂ ፤ አምላኮች አለመኾናቸውን ፡ ቢያውቁም ፤ አምላክን ፡ በመናፈቅ ፡ ብቻ ፡ በዓል ፡ ያደርጉላቸው ነበር ። በኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ምንጊዜም ፡ ቢኾን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ እንጂ ፤ በጣዖት ስም ፡ በዓል ፡ ማድረግ ፡ አልተጀመረም ፤ አልተሞከረም ፡ የለም ።

፫ ፤ በዓላቱም፡ የሚከተሉት፡ ናቸው። በሳምንት፡ ውስጥ፡ የሰንበትን ፡ ቀን ፡ ታ ብራለች። ሰንበት፡ ስድስት፡ ቀን፡ ሥራኸን፡ ሥራ፤ ሰባተኛው፡ ቀን፡ግን፡ የእግዚአብሔር ሰንበት ፡ ነውና ፡ ዕረፍበት ፡ እንጂ ፤ አትሥራበት ፡ በሚለው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት በሕገ ፡ ልቡና፡ በሕገ፡ ኦሪት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ቅዳሜ ፡ ብቻ ፡ ሲከበር ኖራል ። በሕገ ፡ ወንጌል ፡ ግን ፤ ሰንበተ ፡ ክርስቲያን ፡ እሑድ ፡ ስለ ፡ ተጨመረችበት ሰንበታት ፡ ኹለት ፡ ኾነዋል ። አከባበሩም፡ ከቅዳሜ፡ የእሑድ፡ ከፍ ፡ ብሏል ። ምክን ቱም ፡ ቅዳሜ ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ያስገኘችው ፡ ዕረፍት ፡ እንስሳት ፡ የማይለዩበት ፡ ሰው ከበሬና ፡ ከአህያ ፡ የማይሻልበት ፤ የነፍስ፡ ነጻነት፡ የማይገኝበት ፡ ሲኾን ፤ እሑድ ፡ ያ ኘችው፡ ዕረፍት ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ሞቶ ፡ በተነሣባት ፡ ጊዜ ፤ የሰውን፡ልጆ ከወደቁበት ፡ በእግረ፡ አጋንንት፡ ሲጠቀጠቁ ፡ ከኖሩበት ፡ ከእቶነ ፡ ገሃነም፡ስለ ፡ አስነ ውና ፡ ወደ፡ አባቱ ፡ ስለ፡ አቀረባቸው ፤ ከሰይጣን፡ ቁራኝነት ፡ ከኀጢአት ፡ ባርነት ፡ ነ አውጥቶ ፡ የመንግሥቱ፡ ወራሾች ፡ ስለ፡አደረጋቸውና ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ከፍጡራን ፡ ለየ ፡ የሥጋና ፡ የነፍስ ፡ ዕረፍትን ፡ ስለ ፡ አገኙባት ፡ ነው ። ዘፀ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፰—፲፪ ።

፬ ፡ ስለዚህም ፡ የቅዳሜ ፡ ዕረፍት ፡ ምድራዊ ፡ ሥጋዊ ፡ ሲኾን ፤ እሑድ ፡ የ ኘው ፡ ዕረፍት ፡ ምድራዊና ፡ ሰማያዊ ፤ ሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ያው እንደ ፡ ጥላ፡ የማያልፍ ፤ እንደ፡አበባ ፡ የማይረግፍ ፡ የማይሻር ፡ የማይለወጥ ፡ የማይፈር የማይናወጽ ፡ በመኾኑ ፡ ከቅዳሜ፡የእሑድ ፡ ሰንበትነት፡ ዕጽፍ ፡ ድርብ ፡ ብልጫ፡ አለ

www.ethiopianorthodox.org

፭ ፤ የእሑድን ፡ ሰንበትነት ፡ የሚሽሩ ፡ ቅዳሜን ፡ የሚያከብሩ ፡ ወገኖች ፡ ይገኛሉ ፤ ለጥያቄም፡ መልስ፡ የሚያደርጉት ፡ እሑድን ፡ እግዚአብሔር ፡ በጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ የሥራ ፡ መጀመሪያ ፡ ኋላም ፡ በትንሣኤው፡ የሥራው፡ መጨረሻ ፡ ሲያደርጋት ፡ ቅዳሜን፡ ፊትም ፡ ፍጥረትን ፡ ፈጽሞ ፡ ኋላም ፡ በመቃብር ፡ ዐርፎባታልና ፡ ስለዚህ ፡ እሑድን ፡ መሻር ፡ ቅዳሜን ፡ ማክበር ፡ ይገባል ፡ የሚለው ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ. ፩—፪ ።

፮ ፤ በዚህም ፡ ጊዜ፡ ፊትም፡ ዕረፍት ፡ መቼ ፡ ተፈጠረች ፤ ኋላም ፡ ሙስና ፡ መቃብር ፡ መቼ ፡ ጠፋ ፤ የሞት ፡ ጥላና ፡ ጨለማ ፡ በአለበት ፡ በጥልቁ ፡ ጕድጓድ ፡ አኖሩኝ ፤ ሞተው ፡ በመቃብር ፡ ከተጣሉ ፡ ከሙታን ፡ ጋራ ፡ ተቈጠርሁ ፡ ያለው ፡ ትንቢት ፡ መቼ ፡ ተፈጸመ፡ ቢሏቸው፤ በቂ፡ መልስ ፡ አይሰጡም ። የሚያስደንቀውም፡ ተቀበረ ፤ ፫ ፡ ቀንም፡ በመቃብር ፡ አደረ ፤ ያለው ፡ ቃል ፡ ርቋቸው ፤ በመቃብር ፡ ውስጥ ፡ መተኛትን ፤ ከሙታን ፡ ውስጥ ፡ መቈጠርን ፤ ለክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ዕረፍት ፡ አድርገው ፡ መቍጠራቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ እግዚአብሔር ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ከሥራው ፡ ዐረፈ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የሚያመለክተው ፤ እግዚአብሔር ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ዕረፍትን ፡ መፍጠሩን ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ሠራና ፡ ዐረፈ ፡ በማለት ፡ መሓከል ፡ ልዩነት፡አለመኖሩን ፡ ለመግለጥ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ አለማመናቸው ፡ አያስደንቅም ፡ ነበር ። መዝ ፡ ፹፰ ፡ ቍ ፡ ፫—፯ ። ማር ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፳፯ ።

፯ ፤ ነገር፡ ግን ፡ ይህ፡ዐፈጻጸም ፡ ማለት ፡ እሑድን ፡ መሻር ፡ ቅዳሜን ፡ ማክበር ፡ ክርስቶስንና ፡ ክብሩን ፡ የዘለዓለም ፡ ዕረፍቱንና ፡ መንግሥቱን ፡ ጠልቶ ፤ ከክርስትና ፡ ወጥቶ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ነኝ ፡ ማለትን ፡ ትቶ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ መንገድ ፡ አይገኝለትም ።

፰ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ወበእሑድ ፡ ሰንበት ፡ ጌሠት ፡ ማርያም ፡ መግደላዊት ። በእሑድ ፡ ሰንበት ፡ ማርያም ፡ መግደላዊት ፡ ገሥግሣ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ሄደች ፤ ድንጊያው ፡ ተነሥቶ ፡ መቃብሩ ፡ ተከፍቶ ፡ በመቃብሩም ፡ ውስጥ ፡ ኹለት ፡ መላእክት ፡ አግኝታ ፡ ከአፋቸውም፡ የትንሣኤውን ፡ የምስራች ፡ ሰምታ ፡ ለሐዋርያት ፡ ነገረቻቸው ። በዚሁ ፡ ቀን፡ ማታ፡ ክርስቶስ ፡ ለሐዋርያት ፡ ተገለጠላቸው ፡ የሚለውን ፡ የወንጌል ፡ ቃል ፡ ተከትላ ፡ ሞቱን፡ ትንሣኤዩን፡ ዐስቦ፡ ያለውን፡ ቃል፡ ተቀብላ፡ በየሳምንቱ ፡ ዐርብ፡ ዐርብ ፡ ተዝካረ ፡ ሞቱን ፤ በየሳምንቱ ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ ተዝካረ ፡ ትንሣኤውን ፡ ታደርጋለች። ሥጋዊ ፡ ዕረፍት ፡ ከተገኘባት ፡ ከቀዳሚት ፡ ሰንበት ፡ በበለጠ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ዕረፍት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የተገኘባትን ፡ እሑድ ፡ ሰንበትን ፡ ታከብራለች ። ዐማርኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ወበእሑድ ፡ ሰንበት ፡ ያለውን ፡ በቀጥታው ፡ እሑድ ፡ ሰንበት ፡ ብሎ ፡ በመተርጐም ፡ ፈንታ ፡ ከሰንበትም ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ማልዳ ፡ ማርያም ፡ መግደላዊት ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ሄደች ፡ ስለሚል ፤ እላይ ፡ የጠቀስናቸው ፡ ወገኖች ፡ የሳምንት ፡ መጀመሪያ ፡ ወደ ፡ ማለት ፡ ይለውጡታል ። የዐማርኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጸሓፊ ፡ ከሰንበት፡ በመጀመሪያው፡ ቀን፡ ሲል፤ በክርስቶስ፡ ትንሣኤ፡ መሠረትነት፡ ክርስቲያን ፡ በየሳምንቱ፡ እሑድ፡ እሑድ፡ ያርፉበት፡ ዘንድ፡ ለተከፈተው፡ ሰንበተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያች ፡ ቀን ፡



መጀመሪያ ፡ መኾኗን ፡ ሲያሳይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ እሑድን ፡ ለመንቀፍ ፡ ቅዳሜን ፡ ለ
ገፍ ፡ አይደለም። ስለዚህ፡ ይህን ፡ በዓል፡ ልንጠቀምበት፡ ያስፈልጋል ። ዮሐ ፡ ም፡ ፳፡ ፩—

## ኹለተኛ ፡ የዘመን ፡ መለወጫ ፡ በዓል ።

፱ ፤ የዘመን ፡ መለወጫ ፡ በዓል ፡ የታወቀው ፡ ፫ ፡ ዐይነት ፡ ነው ። አንደኛ ፡
ራኤል ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ያከብሩት ፡ የነበረው ፡ ሚያዝያ ፡ ፩ ፡ ቀን ፤ ኹለተኛ ፡
ለም ፡ ክርስቲያን ፡ የክርስቶስን ፡ ልደት ፡ ተቀዳሚ ፡ በማድረግ ፡ የሚያከብሩት ፡ ጎ
፩ ፡ ቀን ፤ ሦስተኛ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጥንት ፡ መሠረትነቱን ፡ ዐውቃ ፡ የምታከብረው ፡ መ
ረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ነው ። እስራኤል ፡ የዘመን ፡ መለወጫ ፡ በዓልን ፡ በሚያዝያ ፡ ማደ
ቸው ፤ በዚሁ ፡ ወር ፡ ከግብጽ ፡ ባርነት ፡ ነጻ ፡ ስለ ፡ ወጡና ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህነን ፡
ነት ፡ በዓል ፡ በየዓመቱ ፡ እንዲያከብሩት ፡ ስለ ፡ አዘዛቸው ፡ መኾኑና ፡ የዓለም ፡ ክር
ያን ፡ ጥር ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ማክበራቸው ፡ የክርስቶስን ፡ ልደት ፡ ምክንያት ፡ በማድ
መኾኑ ፡ የታወቀና ፡ ብዙ ፡ ማተት ፡ የማያሻው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ለወጣቶች ፡ አስቸጋሪ ፡ መ
ስለሚታያቸው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዐውደ ፡ ዓመት ፡ መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡
ችንን ፡ እንሰጣለን ። ዘፀ ፡ ፲፫ ፡ ፬ ።

፲ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ይህንን ፡ በዓል ፡ የተቀበለችው ፡ ከካም ፡ ነው ፡ የተጀመ
ትም ፡ ካምና ፡ ኩሳ ፡ ልጁ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡበት ፤ አኵስም ፡ በኩሳ ፡ ስም ፡
መሠረተችበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ዘመኑም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ካራት ፡ ሺሕ ፡ ዘጠኝ ፡ መ
በላይ ፡ ሲኾን ፤ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በኋላ ፡ በኖኅ ፡ ዕድሜ ፡ በስድስት ፡ መቶ ፡ አንድ ፡ ዓመ
ጀምሮ ፡ ሲከበር ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡
ልፎ ፡ እነሆ ፡ ደርሰንበታል ። ኖኅም ፡ ሲያከብረው ፡ ጥንቱን ፡ ዓለም ፡ የተፈጠረ
ወር ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፤ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ የወረደ ፤ በአበው ፤ እየተላለፈ ፡
ከሱ ፡ የደረሰ ፡ እንደ ፡ መኾኑና ፡ ኋላም ፡ የቀላይ ፡ አፎች ፡ የተከፈቱበት ፤ የጥፋት ፡
መጕደል ፡ የተጀመረበት ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ ወዲህ ፡ ክረም
በጋ ፡ መፈራረቅ ፡ የጀመሩበት ፡ ምድር ፡ የፍሬ ፡ ዕንስ ፡ የአበባ ፡ መልክ ፡ ያሳየች
ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ።

፲፩ ፤ የፊተኛው ፡ ሲጨመር ፡ ሰባት ፡ ሺ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ኹለት ፡
ኖች ፡ ማሳለፉ ፡ ነው ። ስሙም ፡ በግእዝ ፡ ርእሰ ፡ ዐውደ ፡ ዓመት ፤ በዐማርኛ ፡ የዘ
መለወጫ ፡ ዕንቍጣጣሽ ፤ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ እየተባለ ፡ ይጠራል። ርእሰ ፡ ዐውደ ፡ ዓ
ማለት ፡ የዘመን ፡ መለወጫ ፡ መጀመሪያ ፤ ዕንቍጣጣሽ ፡ ማለት ፤ ዕንቍ ፡ ዕፅ ፡ አወ
ብሎ ፡ የአበባውን ፡ መፈንዳት ፡ ወይም ፡ ዕንቍ ፡ ዕጣ ፡ ወጣሽ ፡ ብሎ ፡ መልካሚቱ ፡ ም
ኢትዮጵያ ፡ በዕጣ ፡ ለካም ፡ መድረሷን ፡ የሚያመለክት ፤ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ማ
በዓሉ ፡ ከመጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ዕረፍት ፡ ጋራ ፡ የተደጋገፈ ፡ መኾኑን ፡ የሚገልጥ ፡
ኾነ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪ ፤ በዕብራውያን ፡ ቊጥር ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ አቈጣጠር ፡ መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ የነበረው ፡ ጥቅምትን ፡ ይነካል ። እግዚአብሔርም ፡ በ፯ኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በመጀመሪያ ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰች ፡ በዓል ፡ አድርጉ ፤ በዓሉም ፡ ተዝካረ ፡ (በዓል) ፡ መጥቅዕ ፡ ይባላል ፡ ሲል ፡ ሙሴን ፡ ያዘዘው ፡ ስለዚሁ ፡ ነው ። ይህም ፡ በዓል ፡ ለዓመት ፡ ጥንት ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፤ የአውራኅም ፡ ጥንታቸው ፡ ነውና ፡ በዓመት ፡ ወሮች ፡ በመጀመሪያ ፤ በመጀመሪያ ፡ ቀን ፡ ይከበራል ። ምክንያቱም ፤ ለወር ፡ ለዓመት ፡ ጥንት ፡ መጀመሪያ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ። በዓለ ፡ መጥቅዕ ፡ ተዝካረ ፡ መጥቅዕ ፡ መባሉም ፤ መጥቅዕ ፡ ደወል ፡ በተደወለ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉን ፡ እንዲሰበስብ ፤ ይህም ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የሐልዮ ፡ የነቢብ ፡ ቃሉን ፡ ከሰጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ዕለትን ፡ ሰዓትን ፡ ወርን ፡ ዓመትን ፡ ሰብስቦ ፡ የሚያስገኝ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ። ስለ ፡ አቈጣጠሩ ፡ ፊትና ፡ ኋላ ፡ መኾን ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተሰቀለበት ፤ አይሁድ ፡ ሚያዝያ ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ያከበሩት ፡ የፋሲካ ፡ በዓል ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ አቈጣጠር ፡ መጋቢት ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ መመልከት ፡ ብቻ ፡ ሊያስረዳን ፡ ይችላል ። ዘሌ ፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ቍ ፡ ፳፫ና ፡ ፳፬ ።

፲፫ ፤ አባቶቻችን ፡ ጥንተ ፡ ፍጥረትን ፡ መጋቢት ፤ ጥንተ ፡ ቀመርን ፡ ሚያዝያ ፡ ሲያደርጉ ፡ ሰምተናል ፤ ማስረጃም ፡ ያደረጉት ፡ ቃል ፤ ይህ ፡ ወር ፡ የወሮች ፡ መጀመሪያ ፡ ይሁናችሁ ፡ ያለውን ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ሚያዝያ ፡ የወሮች ፡ መጀመሪያ ፡ ይሁናችሁ ፡ ብሎ ፡ ሲያዝዝ ፤ ምክንያቱ ፡ ለጊዜው ፡ እስራኤል ፡ ከግብጽ ፡ ስለ ፡ ወጡበት ፤ ኋላም ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ከሲኦል ፡ ስለ ፡ ወጡበት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግልጥ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ የሚያዝያ ፡ ወር ፡ ለእስራኤል ፡ የወሮች ፡ መጀመሪያ ፡ እንዲኾን ፡ ሲያዝዝ ፤ ለእስራኤል ፡ የነጻነት ፡ መጀመሪያቸው ፡ በመኾኑ ፡ እንጂ ፤ ጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ በመኾኑ ፡ አይደለም ። ይህስ ፡ ባይኾን ፡ ቀዳማዊውን ፡ ቀዳማዊ ፡ ባላለው ፡ ነበር ፤ ስለ ፡ በዓልም ፡ ሚያዝያ ፡ በገባ ፡ በ፲፬ ፡ ቀን ፡ በዓለ ፡ ፋሲካን ፡ አክብሩ ፡ ብሎ ፡ በዓለ ፡ መጥቅዕን ፡ ሰርቀ ፡ ወርኀ ፡ (መባቻ) ፡ በጥቅምት ፡ እንዲያከብሩ ፡ ባላዘዛቸውም ፡ ነበር ። ዘፀ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፡ ፪ ።

፲፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ የፋሲካን ፡ በዓል ፡ እስራኤል ፡ በሚያዝያ ፡ እንዲያከብሩ ፡ ሲያዝዛቸው ፡ የመባቻን ፡ በዓል ፡ ደግሞ ፡ በ፯ኛው ፡ ወር ፡ መጀመሪያ ፡ እንዲያከብሩ ፡ ይኸውም ፡ በዓለ ፡ መጥቅዕ ፡ ለፍጡራን ፡ ያይደለ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ በዓል ፡ መኾኑን ፡ ዐውቀው ፡ እንዲጠብቁት ፡ በማዘዙ ፤ ጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ ጥንተ ፡ ወር ፡ ጥንተ ፡ ዓመት ፡ ያው ፡ በዕብራውያን ፡ አቈጣጠር ፡ ጥቅምት ፤ በኢትዮጵያውያን ፡ አቈጣጠር ፡ ግን ፡ መስከረም ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ መኾኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ። ሚያዝያ ፡ ቀዳማዊ ፡ በኾነስ ፡ ኖሮ ፡ የመባቻን ፡ በዓል ፡ ሚያዝያ ፡ ፩ ፡ ቀን ፤ ፋሲካንም ፡ በ፲፬ኛው ፡ ቀን ፡ አክብሩ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ከሚያዝያ ፡ አውጥቶ ፡ ለሌላ ፡ ወር ፡ ባልሰጠውም ፡ ነበር ።

፲፭ ፡ መስከረም ፡ ማለትም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዚህ ፡ እስከ ፡ ብሩህ ፡ ሰማይ ፡ ድረስ ፡ መልቶ ፡ የነበረውን ፡ ውሃ ፡ ከ፫ ፡ ከፍሎ ፤ በጠፈር ፡ በሐኖስ ፡ በውቅያኖስ ፡ ከወሰነ ፡ በኋላ ፤ ደረቁ ፡ ይገለጥ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፤ ምድር ፡ ገበሬ ፡ አርሶ ፡ አለስልሶ ፡ እንዳከረ



ማት ፡ ኹሉ ፡ ለዘር ፡ የተመቸች ፡ ኾና ፡ ተገኝታ ፡ ነበርና ፡ መሐሰ ፡ ቈፈረ ፤ ከረመ ፡ ከረ
የሚሉትን ፡ ኹለቱን ፡ ግሶች ፡ በማቀነባበርና ፡ በማስተባበር ፡ መስከረም ፡ አጥብቆ ፡ ታ
ከረመ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ስሙን ፡ ከግብሩ ፡ ነሥቶ ፡ የሚጠራበት ፡ ነው ። ክቡር ፡ አለ
ኪዳን ፡ ወልድ ፡ ክፍሌም ፡ አታሚን ፡ አታኒም ፡ የተባለውን ፡ ቃል ፡ ሲተረጕሙ ፡ አ
ወይም ፡ ኤታን ፡ ማለት ፡ ጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዕብራይስጢውን ፡ በማዋ
ገልጠው ፡ ይኸውም ፡ በዕብራውያን ፡ ፯ኛ ፡ ወር ፡ ጥቅምት ፡ በኢትዮጵያውያን ፡
ሓይ ፡ አቈጣጠርና ፡ በአቡሻክር ፡ ጠንቃቃ ፡ ቊጥር ፡ ግን ፡ መስከረም ፡ መኾኑን ፡
ረድተዋል ። የግእዝ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ፪፻፵፱ ፡ ገጽ ፡ ተመልከት ።

፲፮ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በአኵስም ፡ መዲናነት ፡ የተቀበለችውና ፡ ስታከብረው ፡
ትኖረው ፡ መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ የሚውለው ፡ ርእሰ ፡ ዐውደ ፡ ዓመቷ ፡ የኩሽ ፡ ኩሳ ፡
ናና ፡ መቃብር ፡ በመኾኗ ፤ አኵስም ፡ ርእሰ ፡ አህጉረ ፡ ኩሺ ፡ (ኩሳ) ፡ እሞን ፡ ለአህ
ኩሺ ፡ (ኩሳ) ፡ ተብላ ፡ የምትጠራውን ፡ አኵስምን ፡ (አኩሺም) ፡ ያኽል ፡ ጥንታዊትነ
ሲመሰክር ፡ የሚኖር ፡ ነው ።

፲፯ ፡ ፸ወ፩፪ ፡ ፵ወ፫ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ በዘመነ ፡ ማቴዎስ ፡ ወእምኔሁ ፡
ወ፳፪ ፡ ዓመተ ፡ ኵነኔ ፡ ፲ወ፱፪ ፡ ፵ወ፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ እያለች ፡ ደምራ ፡
ዝራ ፡ ዐጥፋ ፡ ነጥላ ፡ ጠቅልላ ፡ ከፍላ ፡ የምትሰጠው ፡ የዘመን ፡ ቊጥርም ፡ የጥንት
ፍሬ ፡ ነው ። መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ ለእኛ ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ለክብራችን ፡
ረካችን ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ ነውና ፡ ዐውቀን ፡ እንጠቀምበት ። ኩፋ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፲፱—

፲፰ ፤ ፫ኛ ፤ ልደቱ ፡ ለእግዚእነ ። ይህ ፡ በዓል ፡ ሰውን ፡ በመልካችን ፡ በ
ያችን ፡ እንፍጠር ፡ ብሎ ፡ በጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ የተናገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የሰ
ልጆች ፡ ለማዳን ፡ አመ ፡ ከመ ፡ ዮም ፡ እገብእ ፡ ኀቤከ ። የዛሬ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ዛሬ
ወደ ፡ አንተ ፡ እመጣለሁ ፡ ሲል ፡ በሰጠው ፡ ተስፋ ፤ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡
ስት ፡ ድንግል ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ያለ ፡ አባት ፡ የተወለደበት ፡ ነው ። ቅደ
ዓለም ፡ ከአብ ፡ ያለ ፡ እናት ፡ የተወለደው ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ድ
ዓለም ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ መወለዱና ፡ ወልደ ፡ ማር
መባሉ ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ክብርና ፡ ሕይወት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ሥጋ ፡ ቃልን ፡ ተዋ
ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ ከሰማያውያን ፡ መላእክት ፡ ከምድራውያን ፡ ኖ
ምስጋናን ፡ በግልጥ ፡ የተቀበለበትን ፤ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ዕርቅ ፡ የተመሠረተበትን
ንን ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከዓለም ፡ ክርስቲያኖች ፡ ጋራ ፡ በመተባበር ፡ ታ
ዋለች ። ዘፍ ፡ ፲፰ ፡ ፲ ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፫—፲፱ ።

፲፱ ፤ መሠረቱም ፡ እነሆ ፡ በኤፍራታ ፡ በጐል ፡ ተጥሎ ፡ በጨርቅ ፡ ተጠቅ
አገኘነው ፤ በግዕዘ ፡ ሕፃናት ፡ ሲያለቅስ ፡ ሰማነው ፤ እንግዲህስ ፡ ወደ ፡ እግዚአብ
ቤት ፡ ገብተን ፡ የጌታችን ፡ እግር ፡ ከቆመበት ፡ እንሰግዳለን ፡ የሚለው ፡ ትንቢ
ቃል ፡ ነው ። መዝ ፡ ፻፴፪ ፡ ቍ ፡ ፯ና ፡ ፰ ።

www.ethiopianorthodox.org

፳ ፤ ፬ኛ ፤ ጥምቀቱ ፡ ለእግዚእን ። ይህ ፡ በዓል ፡ በፊት ፡ የጥፋት፡ ውሃ ፡ ከምድር፡ ላይ ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ጨርሶ ፡ ስለ ፡ ጐደለ ፡ ኖኅ ፡ በዓል ፡ አድርጎበታል ። ኋላም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ሲጠመቅ ፡ በጥምቀቱ ፡ ጥምቀታችንን ፡ ቀድሶበታል ። የባሕርይ ፡ አምላክነቱን ፡ የባሕርይ ፡ ልጅነቱን ፤ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አስመስክሮበታል ። ስለዚህም ፡ ስሙ ፡ ኤጲፋንያ ፡ ( አስተርእዮ ፡ ) መገለጥ ፡ ይባላል ። ኢትዮጵያ ፡ ይህንን ፡ በዓል ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ከአበው ፤ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ ከነቢያት ፤ በሕገ ፡ ወንጌል ፡ ከሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ በመተባበር ፡ ታከብረዋለች ፤ በየዓመቱም ፡ ጥር ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ እየወረደች ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በውሆች ፡ ላይ ፡ ተገለጠ ፤ የምስጋና ፡ አምላክ ፡ ድምጡን ፡ ሰጠ ፤ እግዚአብሔር ፡ በውሆች ፡ ላይ ፡ ታየ ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ መታሰቢያውን ፡ ታከብራለች ። መሠረቱም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተገልጦልናልና ፡ በደስታ ፡ በዓል ፡ አድርጉ ፡ የሚለው ፡ ቃለ ፡ ትንቢት ፡ ነው ። መዝ ፡ ፳፱ ፡ ቊ ፡ ፫ ። ፻፲፰ ፡ ቊ ፡ ፳፯ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቊ ፡ ፲፫—፲፯ ።

## ፭ኛ ፡ ፋሲካ ፤ ትንሣኤሁ ፡ ለእግዚእን ።

፳፩ ፤ ይህ ፡ በዓል ፡ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ የጥፋት ፡ ውሃ ፡ ከምድር ፡ ላይ፡ ጨርሶ፡ስላለቀና ፡ ስለ ፡ ደረቀ ፤ ኋላም ፡ እስራኤል ፡ ከግብጽ ፡ ስለ ፡ ወጡበት ፡ ፊት ፡ በዘመነ ፡ ኖኅ ፡ ኋላም ፡ በዘመነ ፡ ሙሴ ፡ ከብሯል ። እስከ ፡ ክርስቶስም ፡ የማይለወጥ ፡ የዓመት ፡ በዓል ፡ ኾኖ ፡ ኖሯል ። በመጨረሻውም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ስለ ፡ ተነሣበትና ፡ የሰውን ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ከወደቁበት ፡ ከሲኦል ፡ ጕድጓድ፡አንሥቶ ፤ ለሰይጣን ፡ ለኀጢአት ፡ ከመገዛት ፡ ነጻ ፡ አውጥቶ ፤ ከሞት ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ ስላሸጋገረበት ፤ ዘለዓለማዊ ፡ መንግሥቱን ፡ ስለ ፡ አወረሰበት ፤ ዘለዓለማዊ ፡ የክርስትና ፡ በዓል ፡ ሆኗል ።

፳፪ ፤ ኢትዮጵያም ፤ ከአበው ፡ ከነቢያት ፡ ከሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ በመተባበር ፡ ስታከብረው ፡ ትኖራለች ። መሠረቱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፋሲካ ፡ አድርጉ ፤ ሞቴን ፡ ትንሣኤን ፡ ዐስቡ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ነው ። ስሙም ፡ ፋሲካ ፡ ይባላል ። ትርጓሜውም ፡ ነጻነት፡ ነው ። በብሉይ ፡ ፋሲካ ፡ በሐዲስ ፡ ትንሣኤ ፡ ይባላል ። ነጻነትን ፡ አጽንቶ ፡ ከሞት ፡ ወደ፡ ሕይወት ፡ ከኀሳር ፡ ወደ ፡ ክብር ፡ የተሸጋገርንበት ፡ መኾኑን ፡ ያመለክታል ።

## ፮ኛ ፡ ዕርገቱ ፡ ለእግዚእን ።

፳፫ ፤ ይህ ፡ በዓል ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ አዳም ፡ ከኛ ፡ እንዳንዱ ፡ ኾነ ፡ ሲል ፡ ተናግሮት ፡ የነበረውን ፡ ተስፋ ፡ ስለ ፡ ፈጸመው ፤ ሥጋ ፡ በተዋሕዶተ ፡ ቃል ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ኾኖ ፡ በየማን ፡ አብ ፡ በዘባነ ፡ ኪሩብ ፡ ስለ ፡ ተቀመጠ ፤ ጌታ ፡ ጌታዬን ፡ በቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ። የያዕቆብን ፡ ሥጋ ፡ ለተዋሕዶ ፡ የመረጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልልታ ፡ በመለከት ፡ ድምጥ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ፡ የሚለው ፡ ትንቢት ፡ የተፈጸመበት ፡ ነው ። መሠረቱም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ለወጣ ፡ ለዐረገ ፡ ዘምሩ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ። መዝ ፡ ፵፯ ፡ ቊ ፡ ፭ ። ፳፰ ፡ ቊ ፡ ፴፫ ። ፻፲ ፡ ቊ ፡ ፩ ።



ኢትዮጵያ ፡ ይህን ፡ በዓል ፡ ለክርስትና ፡ አክሊል ፡ አድርጋ ፡ ታከብረዋለች ፤ በተለ[...]
በጐጃም ፡ ርእሰ ፡ ማኅበር ፡ ኾኖ ፡ ይከበራል ።

## ፯ኛ ፡ በዓለ ፡ ጰራቅሊጦስ ።

፳፬ ፤ ይህ ፡ በዓል ፡ አንደኛ ፡ ኖኅ ፡ ከመርከብ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ መሥዋ[...]
ሠውቶ ፡ ሰውን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ስላስታረቀበትና ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከኖኅ ፡ [...]
ኪዳኑን ፡ ስለ ፡ አጸናበት ፡ የዕርቅ ፡ ምልክት ፡ የኾነ ፡ ቀስቱንም ፡ ለኪዳኑ ፡ መታሰቢያ[...]
መና ፡ ላይ ፡ ስላሳየበት ፤ በዘመነ ፡ ኖኅ ፡ ኋላም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ከፋሲካ ፡ [...]
ዐምሳ ፡ ቀን ፡ ቈጥራችሁ ፡ የምድራችሁን ፡ እኽል ፡ ማጨድ ፡ በምትጀምሩበት ፡ [...]
፶ኛውን ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ አድርጉት ፡ ብሎ ፡ ስላዘዘው ፤ ከዘመነ ፡ [...]
እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ሲከበር ፡ ኖሮዋል ። ዘፍ ፡ ም፡፰፡፳—፳፪ ። ፱፡፩—፲፯ ። ዘሌ ፡ ፳፫[...]

፳፭ ፤ ኋላም፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በዕለተ ፡ ዕርገቱ ፡ ከኢየሩሳሌ[...]
ወጡ፡የአብን ፡ ተስፋ ፡ ጠብቁ፡ዮሐንስ ፡ በውሃ ፡ አጥምቆ ፡ ነበር ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ [...]
ጥቂት፡ቀን፡ድረስ፡ ማለት ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ትጠመቃላችሁ ፤ [...]
ቃላችሁ፡ባለው ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ ከትንሣኤው፡በ፶ኛው ፤ ከዕርገቱ ፡ ባ፲ኛው ፡ ቀን
ዋርያት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ስለ ፡ ላከላቸውና ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ የሰው ፡ ልጆች፡መን
ቅዱስን ፡ መጀመሪያ ፡ በመቀበላቸው ፤ በአዳም ፡ ኀጢአት ፡ ምክንያት ፡ ያጡትን ፡
ነት ፡ ( በጸጋ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በመወለድ ) ፡ ስለ ፡ ተመለሰላቸው ፡ ዘለዓለማዊ ፡
ስትና ፡ በዓል ፡ ኾኖዋል ። ስሙም ፡ በዘመነ፡ኖኅ ፤ በዓለ ፡ ሠዊዕ ፡ በዘመነ ፡ ሙሴ ፡ [...]
ሰዊት ፤ በዘመነ ፡ ክርስቶስ ፡ በዓለ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ተብሏል ። የሐዋ ፡ ሥራ ፡ ም[...]
ቊ ፡ ፭ ። ኢትዮጵያ ፡ ይህንን ፡ በዓል ፡ ከኖኅና ፡ ከሙሴ ፡ ከሐዋርያትም ፡ ጋራ ፡ በ[...]
በር ፡ ታከብረዋለች ፤ መሠረቱም ፡ በሥጋዊ ፡ በደማዊ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ መንፈሴን ፡
ለሁ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ነው ። ኢዩኤ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቊ ፡ ፳፰ ።

፳፮ ፤ ለማስረጃ ፡ ያኽል ፡ እነዚህን ፡ ሰባቱን ፡ ጠቀስን ፡ እንጂ ፤ የመሳሰሉዋ[...]
በዓላት ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ቢኾንም ፡ ኢትዮጵያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ እ[...]
በጣዖት ፡ ስም ፡ የምታከብረው ፡ በዓል ፡ የላትም ። ኹል ፡ ጊዜም ፡ የአገራችንን ፡ ዓ[...]
ለመከተል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳን ። አሜን ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ በዓል ፡ ማለት ፡ ምንድነው ?
፪ ፤ መሠረቱስ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ ይገኛል ?
፫ ፤ የሳምንት ፡ በዓል ፡ ማነው ?
፬ ፤ ከቀዳሚት ፡ ሰንበትና ፡ ከእሑድ ፡ ሰንበት ፡ ማን ፡ ይበልጣል ?
፭ ፤ ልዩነቱስ ፡ እንዴት ፡ ነው ?

www.ethiopianorthodox.org

፮ ፡ ዕረፍት ፡ የተፈጠረች ፡ መቼ ፡ ነው ?
፯ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐረፈ ፡ ሲባል ፡ ምስጢሩ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፰ ፡ በመቃብር ፡ ማደር ፡ ለክርስቶስ ፡ ዕረፍት ፡ ኾኖ ፡ ይቈጠርለታልን ?
፱ ፡ የዘመን ፡ መለወጫ ፡ በዓል ፡ መቼ ፡ ተጀመረ ?
፲ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዐውደ ፡ ዓመት ፡ ከእስራኤልና ፡ ከዓለም ፡ ክርስቲያኖች ፡ ይገጥማልን ?
፲፩ ፡ ዕንቍጣጣሽ ፡ ማለት ፡ ምንድን ፡ ነው ?
፲፪ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ተብሎ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተጠራ ?
፲፫ ፡ መስከረም ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ?
፲፬ ፡ የዕብራውያንና ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ የወር ፡ አቈጣጠር ፡ ይገጥማልን ?
፲፭ ፡ የልደት ፡ በዓል ፡ መቼ ፤ በምን ፡ ምክንያት ፡ ተጀመረ ?
፲፮ ፡ የጥምቀትስ ፡ በዓል ፡ ስሙ ፡ ማን ፡ ይባላል ?
፲፯ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የጥምቀትን ፡ በዓል ፡ እንዴት ፡ አድርጋ ፡ ታከብራለች ?
፲፰ ፡ የፋሲካ ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ በብሉይና ፡ በሐዲስ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ነውን ?
፲፱ ፡ የዕርገት ፡ በዓል ፡ መቼ ፡ ተጀምሯል ?
፳ ፡ በዓለ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ በዘመነ ፡ ኖኅ፡በዘመነ ፡ ሙሴ ፡ እንዴት ፡ ይከበር ፡ ነበር ?
፳፩ ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስሳ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
፳፪ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ በሕገ ፡ ኦሪትና ፡ በሕገ ፡ ወንጌል ፡ ማን ፡ ማን ፡ ተብሎ ፡ ተጠርቷል ?
፳፫ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከነዚህ ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ በዓላት ፡ አሏትን ?
፳፬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የበዓልን ፡ አከባበር ፡ ከማን ፡ ተቀበለች ?

አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፡ ይህንን ፡ አምኃ ፡ በቸርነትህ ፡ ተቀበል ፡ በኀ ፡ ፍሬም ፡ እንዲያፈራ ፡ ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ በቅዱስ ፡ ስምኽ ፡ ተማፅኜ ፡ እለ ምንሀለሁ ።

ማ ው ጫ ።


| ምዕራፍ ። | አርእስት ። | ከገጽ ፡ እስከ ፡ ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | ጸሎት ፡ | ፲፫ ፡ |
| | መቅድም ፡ | ፲፭—፳፯ |
| | መግቢያ ፡ | ፳፱ ፡ |
| ፩ | የኢትዮጵያ ፡ እምነት ፡ በሦስቱ ፡ ሕግጋት ፡ | ፴፩—፴፫ |
| ፪ | ኢትዮጵያ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ | ፴፫—፴፭ |
| ፫ | ኢትዮጵያና ፡ ዜናዋ ፡ | ፴፭—፵፫ |
| ፬ | ኢትዮጵያና ፡ ማስረጃዎቿ ፡ | ፵፫—፶ |
| ፭ | ፍቅር ፡ የጋራ ፡ ነው ፡ | ፶ —፶፬ |
| ፮ | ታላቅ ፡ ስም ፡ | ፶፬—፶፱ |
| ፯ | ገናና ፡ መንግሥት ፡ | ፶፱—፷፬ |
| ፰ | ክህነት ፡ | ፷፬—፷፱ |
| ፱ | ቋንቋ ፡ | ፷፱—፸፯ |
| ፲ | ልምላሜ ፡ | ፸፯—፹ |
| ፲፩ | ኢትዮጵያ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ | ፹ — ፹፫ |
| ፲፪ | ኢትዮጵያ ፡ በኦሪት ፡ ያገኘችው ፡ ሀብት ፡ | ፹፫—፻፯ |
| ፲፫ | ኢትዮጵያ ፡ በሕገ ፡ ወንጌል ፡ | ፻፯—፻፲፱ |
| ፲፬ | አንዲት ፡ ሃይማኖት ፡ | ፻፲፱—፻፳፪ |
| ፲፭ | አንደኛ ፡ ዐምደ ፡ ሃይማኖት ፡ | ፻፳፪—፻፴፫ |
| ፲፮ | ኹለተኛ ፡ ዐምድ ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ | ፻፴፫—፻፴፰ |
| ፲፯ | ሦስተኛ ፡ ዐምድ ፡ ድኅረ ፡ ዓለም ፡ | ፻፴፰—፻፵፪ |
| ፲፰ | አራተኛ ፡ ዐምድ ፡ ምስጢረ ፡ ሥጋዌ ፡ | ፻፵፪—፻፶፪ |
| ፲፱ | ዐምስተኛ ፡ ዐምድ ፡ ምስጢረ ፡ ጥምቀት ፡ | ፻፶፪ —፻፶፯ |
| ፳ | ስድስተኛ ፡ ዐምድ ፡ ምስጢረ ፡ ቍርባን ፡ | ፻፶፯—፻፷፭ |
| ፳፩ | ሰባተኛ ፡ ዐምድ ፡ ምስጢረ ፡ ትንሣኤ ፡ | ፻፷፭—፻፸፬ |
| ፳፪ | ኹለቱ ፡ ትእዛዛት ፡ | ፻፸፬—፻፸፰ |
| ፳፫ | ትውክልት ፡ | ፻፸፰—፻፹፩ |
| ፳፬ | ፍቅር ፡ | ፻፹፩—፻፹፭ |
| ፳፭ | ጸሎት ፡ | ፻፹፭—፻፹፰ |
| ፳፮ | ጾም ፡ | ፻፹፰—፻፺፬ |


www.ethiopianorthodox.org

## ማውጫ ።

| ምዕራፍ ። | አርእስት ። | ከገጽ ፡ እስከ ፡ ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፳፯ | ምጽዋት ፡ | ፻፺፬—፪፻፩ |
| ፳፰ | ስግደት ፡ | ፪፻፩—፪፻፰ |
| ፳፱ | ትሕትና ፡ | ፪፻፰—፪፻፲፬ |
| ፴ | ንጽሕና ፡ | ፪፻፲፬—፪፻፲፯ |
| ፴፩ | ትዕግሥት ፡ | ፪፻፲፯—፪፻፳ |
| ፴፪ | ንስሓ ፡ | ፪፻፳—፪፻፳፪ |
| ፴፫ | ተዘክሮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ | ፪፻፳፪—፪፻፳፯ |
| ፴፬ | ምስጋና ፡ | ፪፻፳፯—፪፻፴ |
| ፴፭ | በዓላት ፡ | ፪፻፴፩—፪፻፴፰ |

## የግድፈት ፡ ማረሚያ ።

| ገጽ | መስመር | ግድፈት ፡ | እርም ፡ |
|---|---|---|---|
| ፪ | ፪ | አናደኛው ፡ | አንደኛው ፡ |
| ፲፫ | ፳፯ | አቡነ ፡ ማርቆስ ፡ | አቡነ ፡ ማርቆስ ፡ ጳጳስ ፡ |
| — | — | ዘጐጃም ፡ | ዘጐጃም ፡ |
| ፳፬ | ፩ | መሢሐዊን ፡ | መሲሐዊውን ፡ |
| ፺፩ | ፴፫ | መውዳድ ? | መውደድ ፡ |
| ፺፯ | ፫ | ፈጠረ ፡ አለ ፡ | ፈጠረ ። አለ ። |
| — | ፴፬ | ለምን ፡ | ለምን ፡ ተውኸኝ ። |
| — | — | ተውኸኝ ። | |
| ፻፫ | ፰ | ያሜጋ ፡ | ያሜጋ ። |
| ፻፲፫ | ፲፫ | ሲተረጎምላት ፡ | ሲተረጐምለት ፡ |
| ፻፲፰ | ፲፰ | ምን ፡ አደረጉ ፡ | ምን ፡ አደረጉ ? |
| ፻፳፫ | ፰ | ዛሬም ፡ ባሉ ፡ | ዛሬም ፡ ያሉ ፡ |
| — | ፳፯ | የምች ፡ ታምር ፡ | የዎች ፡ ታዎር ፡ |
| ፻፴፱ | ፬ | ሮሜ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ | ሮሜ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳ ፡ |
| ፻፵ | ፳፩ | ወእ ፡ | ወያ ፡ |
| ፻፵፬ | ፳፱ | በድንግልና ፡ ትወልዳለች ፡ | በድንግልና ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ልዳለች ፡ |
| ፻፶ | ፫ | ቀረበለት ፡ | ቀረበት ፡ |
| ፻፶፫ | ፴ | በክስርቶስ ፡ | በክርስቶስ ፡ |
| ፻፶፬ | ፴፫ | እግዚአብብሔር ፡ | እግዚአብሔር ፡ |
| ፻፷ | ፲፰ | አለዋቂዎች ፡ | አላዋቂዎች ፡ |
| ፪፻ | ፲፯ | ወምይ ፡ | ወይም ፡ |
| ፪፻፲፫ | ፲፩ | ትዕቢቱ ፡ | ትዕቢት ፡ |
| » | ፲፯ | ይህ ፡ ቹን ፡ | ይህችን ፡ |
| » | ፳፪ | የተባላሽ ፡ | የተበላሸ ፡ |
| ፪፻፲፭ | ፯ | አደኛው ፡ | አንደኛውን ፡ |
| » | ፲፫ | የለሌበት ፡ | የሌለበት ፡ |
| ፪፻፲፯ | ፪ | የተከለከውን ፡ | የተከለከለውን ፡ |
| » | ፫ | ንጹሕና ፡ | ንጽሕና ፡ |
| ፪፻፲፰ | ፲ | ሰባ ፡ ትካት ፡ | ሰብዐ ፡ ትካት ፡ |
| ፪፻፲፱ | ፲፪ | ኮናተ ፡ | ከናንተ ፡ |
| ፪፻፳፩ | ፲፬ | እስጥሀለው ፡ | እሰጥሀለሁ ፡ |
| ፪፻፳፪ | ፱ | ኢያስበ ፡ | እያሰበ ፡ |

www.ethiopianorthodox.org

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ተፈጸመ ።

ያለደራሲው ፡ ፈቃድ ፡ ማሳተም ፡ ክልክል ፡ ነው ።

አ. ታ. (ሀ—ዳ)

www.ethiopianorthodox.org